# እግረ መንገድ



## ስብሀት ገብረእግዚአብሔር

ስብሀት ገብረ እግዚአብሄር

# እግረ መንገድ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

All Rights Reserved

የመጀመሪያ ሕትመት - የካቲት 2011 ዓ.ም

# ማውጫ

የአርታኢው ማስታወሻ ........ 7

## እግረ መንገድ ፩

ስንዴው ሸሀዬ ........ 11
ውርድወት ........ 15
ንግስተ ሳባ ........ 20
ዮዲት ........ 37
ይኩኖ አምላክ ........ 49
አቦዬ ጣዲቁና ክርስቶስ ሳምራ ........ 58
ሬሙስና ሮሙለስ ........ 63
ወይዘሪትና ወይዘሮ ሮማ ........ 73
ጁሊየስ ቄሳር ........ 78
ሀረር ........ 91

ስአሊው ጥበበ ተርፋ ..... 122
ጀርመን ..... 135
የሰው የለው ሞኝ ..... 140
ሰይጣን ..... 144
አለቃ! ..... 149
ታሪክ ..... 154
ተረት ..... 158
ማሙሽና ሚሚ ..... 165
የእማ ስርአት ማህበር ..... 170
የንዴት ወሬ ..... 174
ሰላማዊ ሰልፍ ..... 178
ፍልስፍና ..... 184
ምኞት ..... 189
የሆድ ነገር ..... 193
አርተር ኬስለር ..... 197
ሱፊ ..... 201
እኔ! ..... 204
እኔን ፍለጋ ..... 209
ትዝታ ..... 213
ትእዛዝ ..... 218
ያእቆብና ኤሳው ..... 222

# እግረ መንገድ ፪


ውምብድና ........................................ 229

ታክሲና ወያላ ........................................ 243

ሞትና ህይወት ........................................ 252

ሆዱ ........................................ 269

የአበላል ስርአት ........................................ 274

ውርስ ........................................ 279

የአዜ ባካፋ ብልሀት ........................................ 283

ተረትና ታሪክ ........................................ 287

ጋዜጠኝነት ........................................ 296

ድሮ ቀረ? ........................................ 301

የፀሀይ ህዝብ ........................................ 306

ሰውና ውሻ ........................................ 311

እንግሊዝና ጋንዲሂ ........................................ 315

ባለስልጣን ........................................ 320

ጥንታውያን የጥበብ ሰዎችና ስራዎቻቸው ........................................ 324

ቻይና ........................................ 335

አዳኝና ታዳኝ ........................................ 341

ቢሮክራሲ! ........................................ 346

# የአርታኢው ማስታወሻ

‹‹እግረ መንገድ›› ውስጥ ስብሀት ያልዳሰሰው ምን ነገር አለ? ታሪኩ፣ ተረቱ፣ ፍልስፍናው፣ ስነልቦናው፣ ኪነጥበቡ ወዘተ ሁሉም ተጎብኝተዋል። ይሄ ሀቅ እለተሰንበት አዲስ ዘመንን ያነበቡ ሁሉ የሚያውቁት ነው።

በዚህ አምድ ላይ ሳይቋረጡ በተከታታይ ለአምስት አመታት የወጡት መጣጥፎች ደራሲው ስብሀት ገ/እግዚአብሄር በንባብ፣ በልምድና በማያሰልስ ጥረት ያካበታቸው የእውቀት ዘርፎች ምን ያህል ስፋት እና ጥልቀት እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው።

በዚህ ቅፅ የቀረቡላችሁ መጣጥፎች ከትምህርትና ከንባብ የተቀሰሙ እውቀቶች ብቻ አይደሉም። ስብሀት በህይወቱ ያጋጠሙትን ነገሮች በራሱ አይን እያየ እናንተም እንድታዩዋቸው ማድረጉ መጣጥፎቹ አብነት ሊሆኑ ይችላሉ።

ስብሀት በእግረ መንገድ የአምስት አመት ጉዞው እያየ፣ እያነበበ፣ እያወቀና እየተገነዘበ ወደኛ ሊያስተላልፍልን ‹‹እነሆ ገበረከት›› ያለን ቁም ነገሮች በርካታ በጣም በርካታ ናቸው። በዚህ ቅፅ [የሁለት] አመት እግረ መንገድ ፍሬዎቹን ነው የሰጠናችሁ።

ባንድ ወቅት ‹‹ሌቱም አይነጋልኝ›› ታትሞ ለአንባቢያን ሲቀርብ ለማስተዋወቅ በሀገር ፍቅር ትያትር ትንሽዋ አዳራሽ ውስጥ በተዘጋጀው ውይይት ላይ እኔና ዘነበ ወላ ‹‹እግረ መንገድ››ን የመፅሀፍ ቅርፅ አስይዘን እንደምናቀርብላችሁ ቃል እንደገባነው ሁሉ ቅፅ ሁለትና ሦስትን በተከታታይ እንደምናደርስላችሁ ቃል ብንገባስ ምን ይመስላችኋል? ‹‹ቃል የእምነት እዳ እንጂ...›› እንዳለው ባለቅኔው ፀጋዬ ገብረመድህን፡፡

ቅፅ አንድ እግረ-መንገድ በዚህ ቅርፅ እንድትወጣ በርካታ የስብሀት ወዳጆች ባቅማቸው ተባብረውናል፡፡ ጋዜጦችን በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቤተ መፃህፍት ጥራዝ ውስጥ እንድናገኛቸው በማስቻል አቶ ሰብስቤ ከበደ ላደረጉት ትብብር በደራሲውና በአንባቢያን ስም ሊመሰገኑ ይገባቸዋል፡፡

እኔና ዘነበ ወላን ደግሞ ቃላችንን ውጥን ባለመቅረታችን የቃል አምላክ ታመስግነን ይሆን? ለማንኛውም ከሁላችንም በላይ እድለኛ የሆናችሁት አንባቢያን ከስብሀት ገ/እግዚአብሄር ጋር እግረ መንገዳችሁን ተያያዙት....

ደምሴ ፅጌ

1996 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# እግረ መንገድ ፩

# ስንዴው ሸህዬ

እግረ መንገዴን ወሎዬዎች ወደሚያዘወትሩት ግሮሰሪ ጎራ አልኩ።

እግረ መንገዱን ስንዴው ሸህዬ ወደጨዋታችን ጎራ አለ። ‹‹ጂግና! ደርጉን አምስት አመት ሙሉ ገትሮ የያዘ ወንድ!››

‹‹ለምን ኖሯል የሸፈተው?››

‹‹ግልገል አይገዛኝም አለ። በምን ይያዙት? ‹አቀስታ ነው› ሲሉት ኢላዳ ይገኛል። ‹ኢላዳ ነው› ሲሉት ወለቃ በረሀ ይገባል። ወታደር ሲልኩበት ሲፈጃቸው።››

‹‹ሰራዊት ነበረው ማለት ነው?››

‹‹ምን መሰሉዎት፣ የቦረና ሽፍቶችና የጎጃም ሽፍቶች እርስ፣ በርስ ይተዋወቃሉ። እንደ ማህበር አይነት ነገር አላቸው። ስንዴው ሸህዬ እንግዲህ የሚያውቃቸውን ሽፍቶች ሁሉ ይልክባቸዋል። ‹የደርጉን ጠበል ጠዲቅ ኑ ቅመሱልኝ።›

‹‹እና ይመጣሉ?››

‹‹መምጣት ነው?! ፈጁት'ንጂ የደርጉን ወታደር።››

‹‹ተራዎቹ ሽፍቶች ያስዘፍኑለታል። እንዲህ በይ አንቺ!››

ያ ስንዴው ሽሀዬ የመጣ'ንደሀ አውቆ
አወይ መገላገል ዘጠኝ ወር ተጨንቆ!››

‹‹ሲፎክር ‹ስንዴ ሽሀየ የሼሆቹ ልጅ!› ነው የሚለው፡፡ ቀላል ሰው አልነበረም፡፡ ሽፍታ ብቻ ሳይሆን አገር ጠባቂ ጭምር ነበር››

‹‹ታድያስ! ስንዴው ክንዱን ሳይንተራስ ማናባቱ ቀን የደረሰ ሽፍታ ነው ገነቱ ድርሽ የሚለው? - እስክንትር - ኢላዳ - እስከ አቀታ ድረስ ኧረ! ማናባቱ ነው የስንዴው ሽሀዩን አገር የሚዘርፍ? ደፍሮ ጠቦት የሚያነሳ የለም፡፡ እውነት እናቱ ወልዳዋለቻ! ስንዴው ለራሱ ወለቃ በረሀ ግዛቱ ነው! ጌታዬ››

‹‹እሱ አይዘርፍም ከብት አይነዳም ማለት ነው?››

‹‹ይነዳዋል እንጂ! ምነው አይነዳው? ግን ሩቅ በጣም ሩቅ አገር ሄዶ ነው የሚዘርፈው፡፡ የገዛ አገሩን የሚዘርፍ'ኮ ሽፍታ አይደለም - ተራ ሌባ ነው፡፡ ሽፍታ አገሬውን ይጠብቀዋል'ንጂ አይዘርፈውም፡፡››

‹‹ጃንሆይ ይህን ስለሚያውቁ - እና ጦርነት ቢመጣ ከሽፍታ እኩል እንደሌለ ስለሚያውቁ - ሽፍታን እጅግም አይከታተሉም ነበር፡፡ ደርጉ ነው ለቅጦ የጨረሳቸው፡፡››

‹‹'ቦረናን ቀሚስ ነው ማለብሳት' ብሎ ፎክሮ ነበር››

‹‹ይህ ሰላቢ! አላህ ይፍጀው አቦ!››

‹‹ስንዴውን አንድ ቀን አይቼው አውቃለሁ፡፡ ጠይም ነው፤ መካከለኛ ቁመት፡፡ ፈረሱ - አይ ፈረሱ! ትልቅ ነው - ከሌላ ፈረስ ይበልጣል፡፡ ነጭ - ነጭ ነው በጣም ነጭ፡፡ ጭራው ረዥም ሆኖ ተጎንጉኖ ጫፉ ላይ እንደሪባን አይነት ቋጠሮ ተቋጥሯል፡፡ አይ ማማሩ! እርካቡን ረግጦ ገና ቁጭ እንዳለበት ሁለት የፊት እግሩን አንዴ ወደ ሰማይ አነሳና ጋለበ - አይ ሲያምርባቸው ስንዴውና ፈረሱ! ከአይን እስኪሰወሩ ተከተልናቸው፡፡ ያን ፈረስ ማን ይቀመጠው ይሆን?››

‹‹ለመሆኑ ስንዴው ሽህዬ አገሩ ማን ይባላል?››

‹‹ክፍክፍ ወይራ - አራጣ - ቦረና - ወሎ - ኢትዮጵያ፡፡››

ያ በህይወቱ ሳለ ነበር፡፡ ዛሬ ስንዴው ሽህዬ የሚገኘው እንደዚህ አይነቱ ወግ፣ ጨዋታ ውስጥና ዘፈኖች ውስጥ ነው፡፡

‹‹ስንዴው ሽህዬ ፈረሱ ነጭ ልብሱ ነጫጭ
ይወረወራል እንደ ልምጭ!››

ይቺ ድንቅ ግጥም ታላቅ እህቷን አስታወሰችኝ - ቀደም ሲል ስለዚያው አገር ጀግና የተዘፈነች፡፡ ተደጋግማ በሬዲዮ ሰምቻት በቃሌ የያዝኳት፡፡

‹‹ቦረና ቦረና ቦረና ገነቴ
አብረከረከችኝ ገባች በጉልበቴ››

መክፈቻዋም አዝማቿም ናት፡፡ ስትቀጥል - አገርህን ካሞጋገስክ በኋላ አገርህ ያበቀለቻትን ውቢት ወይም ያፈራችውን ጀግና ማሞገስ፣ ማመስገን፣ ማስዋብ ነውና የዘፈን ቁምነገሩ

‹‹አሊ በለው መጣ - ቦረና ደረሰ
የፈረሱን ጭራ እየነሰነሰ
ሰው እንደገለባ እያግበሰበሰ!››

አንዳንዱ አዝማሪ ደግሞ የምትቀጥለውን ነው አዝማች የሚያደርጋት፡፡ አዝማች ማለት እየተደጋገመ የሚመጣና - የሚከተሉትን ግጥሞች የሚጠራ የሚያመጣ የሚያዝምት ግጥም ነው፡፡ ከለላ የአሊ በለው መንደር ናት!

‹‹ከለላ ነው ቤቱ - ከለላ ነው ቤቱ
ከለላ ነው ቤቱ - ያበራል ጥይቱ!››

‹‹አሊ በለው ግን ለምን ነበር የሸፈተው?›› ብዬ ጠየኩ

‹‹መች ሽፍታ ነው?››

‹‹እንግዲያስ?››

‹‹ሌባን፣ ቀጣፊን፣ ዘራፊን፣ ሽፍታን ከቦረና ያጠፋ አገረ ገዥ!›› እነሆ በረከት! ብዬ አበቃለሁ አባ ኪዳነማርያም እንደሚሉት፡፡

ሀምሌ 18 ቀን 1985

# ውርድወት

ከሶስት የጉራጌ ተወላጅ ጓደኞቼ ጋር አንድ ቀን እንዳጋጣሚ በመዝናናት በመጫወት ሰአት ውርድወትን በትረካ መነፅር አየኋት፡፡ ጆሮ ነው መነፅራችን፡፡ እነሆ በረከት!

ምድረ ጉራጌ ውርድወትን በዘፈን ሲያወድሳት እነሆ አምስት ትውልድ አልፎ ስድስተኛው እየቀጠለ ነው በግምት፡፡

ውርድወት በሺ አመት አንዴ ብቅ ከሚሉት የውበት ተአምራት አንዷ ናት፡፡ ከውበቷ የማያንስ ወኔም ነበራት፡፡ እና ጭንቅላት! አሟልቶ የሰጣት፡፡

እንግዲህ በሷ ዘመን ወንዶች እንደሀብታቸው አቅም ሁለትም ሶስትም ሚስት ማሳደር ይችላሉ፡፡ ያገኟትን ሌላ ሴትም ቢወሽሙ ባህል ይፈቅዳል፡፡ ሴቷ ግን ከህጋዊ ባሏ ሌላ ወንድ አይፈቀድላትም፡፡ ውርድወት ይህ ልክ አልመሰላትም፡፡ ሀሳቡን ከየት አመጣችው ግን?

አንድ ቀን ሴቶቹን ሰበሰበችና “ወይ ወንዶቹም እንደ'ኛ ይከልከሉ ወይ እኛም እንደነሱ ይፈቀድልን” አለቻቸው፡፡

“አብደሻል? እንኳን ሲደረግ ታስቦም አያውቅ”

“ለምን?”

"ባህል ነዋ!"

"እና ባህል የሆነ'ንደሆን ምንድነው? እኛም እንደነሱ ስጋ ለብሰናል፣ ደማችንም ሞቃት ነው፤ ይነዝራል እንደነሱ። ታድያ ለምን እኛ ታስረን እነሱ ይቦርቃሉ? ወይ እነሱም ይታሰሩ ወይ እኛም እንቦርቅ። እኩል!"

አሳመነቻቸው።

እንዴት እናድርግ? ተባለ። ውርድወትና ሁለት ሌሎች ሴቶች ተመረጡ፣ ሴቶቹን ወክለው ጉዳዩን ላገር ሽማግሌዎች እንዲያቀርቡ።

አንድ ቀን ያገር ሽማግሌዎች አገር ጤና ብለው ያገር ጉዳይ ሊመክሩ እትልቁ ዛፍ ስር እንደተቀመጡ ውርድወትና ሁለቱ መጡና የሴቶቹን መልእክት ለሽማግሌዎቹ አደረሱ በአክብሮት።

"እሺ ወደዚያ ገለል ብላችሁ ቆዩንና በጉዳዩ መክረንበት ስናበቃ እንጠራችኂለን" ተባሉ።

ብዙ የሚያከራክር አልነበረም። 'ይቺ ባቂላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም' ሆነ።

"ጎበዝ" ተባባሉ እነሽሜ "ዛሬ ማታ ሴትዋ ሁሉ እራትዋ ዱላ ነው"

"እናሽንፋለን!"

"አንጠራጠርም!"

እነ ውርድወትን እንዲህ አሉዋቸው "ሁላችሁም ነገ በዚህ ሰአት ወደዚህ ኑ። መልሳችንን እንነግራችኂለን።"

እነ ውርድወት መልእክታቸውን ለሴቶቹ ሲያደርሱ፣ በተባለው ጊዜ አንድ ላይ እጅብ ብለው እንዲሄዱ መክረው የት እንደሚገናኙ ተስማሙ።

አቤት ያን'ለት ማታ የወረደ ዱላ! አቤት ያስተጋባው የእንስት ኡኡታ! ስንቷ ትሆን በሆዷ ውርድወትን የረገመች!

በነጋታው ሽማግሌዎቹ ትልቁ ዛፍ ስር ተቀምጠው ሲጠብቁ ውርድወት ብቻዋን መጣች። (የትላንት ማታው ልምጭ፣ አለንጋ፣ ጥፊ፣ እርግጫ ስራውን ሰርቷል!)

ውርድወትን እንዲህ አሏት "እኛ የአባቶች ባህል ይፍረስ ብለን መወሰን አንችልም። አንቺ ግን እንደፈቀደሽ መሆን ትችያለሽ ነፃ ነሽ።"

እሷም በነፃነት የምድረ ጉራጌን ጆግና (መልኩና ቁመናው ደስ ያላትን) እያቀያየረች ብዙ አመት ኖረች። አበጋዝ አልቀራት፣ አዝማች አልቀራት፣ ሶሬሳ አልቀራት፣ ዳመስ፣ ዳሞ፣ ይማም አልቀራት። በውርድወት የመጣ ጆግኖቹ አይጣሉም። ካንዱ ጋር ሰንብታ ስታበቃ አይኗን ወደሳበው ወደ ሌላው መሄድ ነው። ያ ትታው የምትሄደው ሰው "ለምን ተወችኝ?" ብሎ መቆጨት የለም "ኧረ እንኳን አቀፈችኝ! ለምን ላንድ ሌሊት ብቻ አይሆንም!" ('ካንቺ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት' የሚሉላት ነበረች።)

ውርድወት ፈረሰኛ ጆግና እንደምትወድ የታወቀ ነው። ስለዚህ የተመሰከረለት አዳኝ ወይም ጦረኛ "እስቲ እድሌን ልሞክር በለስ ቢቀናኝ!" ብሎ ጭኖ ተነስቶ እሷ ልታየው ወደምትችልበት ቦታ ሽምጥ ይጋልብና፣ ድንገት ልጓም ቀጥ አድርጎ ይይዝና፣ የፈረሱ ሆድ ሽቅብ እስኪታየው ያህል ወደ ጎን ዘንበል ብሎ ያዞርና ወደመጣበት ተመልሶ ይሸመጥጣል።

በለስ ቀንቶት ከሆነ ውርድወት ወዲያውኑ ትከተለዋለች፣ ወይ ጥቂት ቀናት ቆይታ ወደሱ ትመጣለች። አለዚያ ሌላ ቀን እድሉን ይሞክር ይሆናል።

አንዳንድ ሴቶች በወንዶች ላይ ሙሉ ስልጣን አላቸው፣ የማያልቅ የመፈቀር ተአምራቱን ያወርዱታል። ሄለን የተባለችው የትሮይ ጦርነትን በውበቷና በፍቅሯ መዘዝ የቀሰቀሰችው። አስር አመት ፈጀ ያ ጦርነት። ክሊዮፓትራ የተባለችው የመጨረሻዋ የግብፅ ንግስት ውበቷ ፍፁም ከመሆኑ የተነሳ "የክሊዮፓትራ አፍንጫ ትንሽ አጠር ወይም ረዘም ቢል ኖሮ የአለም ታሪክ ሌላ ይሆን ነበር" ተባለላት። ጁሊየስ ቄሳር ሊያስገብራት መጣ። አስገበረችው። ለጥቂት አመት የእቅፏ ተገዥ አደረገችው፣ ወንድ ልጅ እስኪያስወልዳት በፍቅሯ አስራ አቆየችው። እኩያ የማይገኝለቱ ጁሊየስ ተገድሎ፣ የእሱ ቀኝ እጅ የነበረው ማርክ አንቶኒ ግብፅን ሊያስገብር መጣ። ክሊዮፓትራ እሱንም አስገበረችው።

በፍቅር አሳበደችው፣ እሷም አበደችለት። ፍቅረኛሞችነታቸው በለጠባቸ ውና ንጉስና ንግስት መሆናቸውን ሲበዛ ችላ አሉት። እዚህ ላይ ነው ጁሊየስ ቄሳርና ማርክ አንቶኒ ልዩነታቸው። ጁሊየስ አበደ አበደና ድንገት ከእብደቱ ነቃ። ንጉስ መሆኑን አስታወሰ። እና ውቢት ክሊዮፓትራን ስሞ ተሰናብቶ ሄደ ቄሳር ወደ ዙፋኑ። ለመሆኑ እንደሱ ንጉስ ነግሶ ያውቃል? ወይ ክሊዮፓትራ!

አንቶኒዮ ግን ዘውዷን ከራሱ አውርዶ አሽቀንጥሮ ወደ ሮማ ወረወራትና "እሺ የኔ ክሊዮ፣ እንዋደድ" አላት።

"እሺ የኔ ጌታ" አለችው።

ሌሎች ዙፋኑ ላይ መቀመጥ የሚፈልጉት ግን ይህ የፍቅር ጉዳይ ስላልገባቸው (ደደቦች) ግብፅን ወረሯት። ለክሊዮፓትራ ፍቅር ሲል አንቶኒዮ ራሱን ገደለ።

ለአንቶኒዮ ፍቅር ስትል ክሊዮፓትራ ራሷን ገደለች።

አንዳንድ ሴቶች በወንዶች ላይ ሙሉ ስልጣን አላቸው። ውርድወት የተባለችው ውብ በህይወቷ ምድረ ጉራጌን በፍቅር ንዳድ ያቃጠለችውና ካለፈች በኋላ ደግሞ ተከታታይ ትውልዶች በሚዘፍኑላት ዘፈኖችና በሚነገሩላት ታሪኮች ፍቅርን የምትለኩሰው፣

ማን ናት እሷ?

በጥንት ዘመን ኖራ ቢሆን ኖሮ እንደ አፍሮዳይት (የግሪኳ የፍቅር መላኪት - እንደ ቬኑስ የሮማዋ - ወይም እንደ አንዷት ሌላ) ውርድወትን ትውልዶች ቀስ በቀስ እየተቀባበሉና የባሰውን እየኳኳሉ ከሰውነት አውጥተው ከአማልክት መሀል የምትቀመጥ ፀሎትና መስዋእት የሚደረግላት፣ ፍቅር ያደናገራቸው በስሟ ስለት የሚሳሉላት ተመላኪት ያደርጓት ነበር።

እርጅና እንደልማዱ እጁን ሲዘራጋባት

"ተው ዘወር በል ወደዛ!" አሉት የላይ ቤተ አማልክቱ። እና ውርድወትን እንዲህ አሏት

"እነሆ ውርድወት ሆይ፣ በየሺ አመት በሰዎች መሀል ተመላኪት ተወልዳለች፡፡ አንቺ እኩያችን ነሽ፡፡ ሰዎችን ተያቸውና ወደኛ ነይ፡፡ ትፈቅጂያለሽ?"

"እፈቅዳለሁ"

"አትፈሪም የአማልክትን መንገድ መሄድ?"

"አልፈራም" አለች በፈገግታ፡፡ አማልክቱም ፈገግታዋን አይተው እኩል ፈገግ አሉ፡፡ ከፈገግታቸው መሀል መብረቅ መጣና ውርድወትን ወሰዳት፡፡

ይህ አስደንጋጭ ተአምር አትልቁ ዛፍ ስር ተቀምጠው እያወጉና እየተጫወቱ ምድረ ጉራጌን ከዝጌር ጋር ሲጠብቁ የነበሩትን ሽማግሌዎች አሳሰባቸው፡፡

እቺ ልዩ ፍጡር መልካም እድላችን ሆና እኛ መሀል የበቀለች የልጅ ልጆቻችን እንዳይረሷት ምን ዘዴ ይበጃል?

እንደሷ ውብ ወራት ፈለጉና የጉራጌ ልጅ ሁሉ የሚያከብረው - ምስጢሯን አውቆ ይሁን ሳያውቅ - በአል አወጁላት፡፡

መስቀል!

ሳምንት ሙሉ ይከበራል መስቀል፡፡

(እቺ ለወጣቶች አንባቢያን! በዚያን ዘመን ውርድወት በትግራይ ወይ በአማራ አገር ተወልዳ ቢሆን ኖሮ በድንጋይ ይወግሯታል? ወይስ ውሀም እንጀራም የሰጣት እርጉም እንደ አርዮስ ብለው ካገር ያባርሩዋታል? ወይስ ጀግኖቹ ይጋደሉባታል? ጉራጌ ግን ጠቢብ ነው ውርድወትን አስተናገደ፡፡)

ልጆቹ የልጅ ልጆቹ ደሞ እሱቅ ወይ ሌላ ቦታ እያስተናገዱት ነው ያዲሳባን ኗሪ፡፡

የውርድወት ዘሮች መሆናቸውን አንርሳ፡፡ ትንሽ ከበሬታ!

ሀምሌ 25 ቀን 1985

# ንግስተ ሳባ

ውርድወት ውቢቱ እና ንግስት ሳባ ሌላ ሰው አርጎት የማያውቀውን በማድረጋቸው እንዲሁም ውብና ብልህ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ። እና በቆራጥነታቸው።

በመሰረቱ ማንንም ባልከተል እመርጣለሁ። ውርድወት ወይም ሳባ ግን አንድ ቀን መጥተው "ና ተከተለኝ" ቢሉኝ ሰዎቼን ተሰናብቼ እንደምከተላቸው ነው። "ኢድ ባክህ! ማነው ሊመጡ አይችሉም ያለህ? ማን እንደሆኑ አልገባህም ለካ። ዳሩ ላንተ እነሱ ሊገለፁልህ አይሆንላቸውም። ከእኛ እኩል በሴት አታምንማ! ፈጣሪያችን፣ ሞትን ድል ማድረጊያችን መሆናቸው ገና አልገባህም። እንዲገባህ ፀሎት አርግ፣ ወዳጄ!" ካሉት በኋላ ሰባኪ እንደበታቸውን ዘጉና ያዝማሪ ነብሳቸውን ጠሯት፣ 'ንግስተ ሳባን በስድ ንባብ እያንሳፈፍሽ አምጭልን' አሉዋት።

ብሩክታይት የተባለች ውቢት በግብር መልክ ለደራጎን ተዳርጋ ባሰኘው ሰአት መጥቶ ይበላት ዘንድ ከዛፍ ግንድ ጋር ታስራ ግና ቀኑ ልዩ ስለነበረ ፍጡነ ረድኤት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማእታት ፈረሱን ጋልቦ ከተፍ ብሎ ደራጎንን በጦር ልቡን ወግቶ ሲገድለው ይህን ስእል ያላዩ ጥቂቶች ቢኖሩ ነው።

ጥንት ከሰማእቱ ዘመን አስቀድሞ ምናልባት አንድ ሺ አመት ከክርስቶስ ልደት በፊት፣ አክሱምን አንድ ዘንዶ ይገዛት ነበር (ምናልባት የደራጐኑ ዘር ወይም ያገር ልጅ ሊሆን ይችላል) ምግቡም በቀን በቀን አንድ ወጣት ነበር (ስአሊለነ ቅድስት)

ዘንዶው በዚህ አኳኋን አርባ ይሁን ሰባ አመት ገዛ። ወይም መቶ ሃያ እንደተራኪው ይለያያል። ደሞ ቁጥሩ ለታሪኩ እምብዛም ልዩነት አያመጣም።

ከእለታት አንድ ቀን፤ እነሆ አንጋቦስ የተባለ ብልህ ጀግና የአክሱምን ታላላቅ ሰዎች ለብርቱ ጉዳይ ሰበሰባቸው። እንዲህም አላቸው 'እኔ ዘንዶውን ብገድልላችሁ እናንተ ታነግሱኛላችሁን?'

ከዘንዶው ገላግለን እንጂ ከዚያ በኋላ እንኳን አንተ ውሻ ይግዛን አሉት በአጥንት ሊገላገሉ! "ዙፋኑን ላንተና ለልጅ ልጆችህ እንሰጣለን እስከወዲያኛው!" ሲሉም በዘመኑ አማልእክት ማሉለት።

"እስታይል!" አለና አንጋቦስ ሆዬ በጉበዛዝት ባልንጀሮቹ ታጅቦ፣ የመስዋእት ፍየል በግርማዊ ትከሻው ተሸክሞ ዘንዶው ወደሚኖርበት ዋሻ አመራ። ከዋሻው ፊት ለፊት መሬቱ ላይ ብዙ ሹል እንጨቶች ተከሉ፤ ወደ ዋሻው በኩል ያጋደሉ (ያዘነበሉ) በዚያ ፍየሉን ከእንጨቶች በወዲያ በኩል አሰሩት፤ ከዚያ ዘንዶውን ጠሩት።

"ማናባቱ ነው ከእንቅልፌ የሚቀሰቅሰኝ!?" ብሎ ተናዶ ዘንዶ ብቅ ብሎ ያያል። እዚያ ፊት ለፊት ምን የመሰለ ፍይል ታስሮለታል። ሲስገበገብ በኃይለኛ ፍጥነት ሲሮጥ (እግርም አለው እንዴ?) ሹሎቹ እንጨቶች ላይ በሆዱ ስከት። "እኛ ነን ቁርስህ" አሉት ይህ በጦረኞች ቋንቋ የአንጋቦስ ስትራቴጂ ይባላል።

እነ አንጋቦስ ዙሪያውን ካደፈጡበት እየዘለሉ ወጡና በሰይፍና በጦር "ይህ ነው ምስህ!" (የአንጋቦስ ታክቲክ)

ዘንዶ እዚያው ሲጥ!

አንጋቦስ አክሱም ዙፋን ላይ መውጣት! በሆታና በእልልታ ነዋ ያውም! እንኳን ዙፋኑ ሌላውም በተገባው! (አሉ አክሱማውያን ለጊዜው)

ሆነም ንጉስ አንጋቦስም ስልጣንና እድሜን ጠግቦ (የሚጠገቡ ከሆነ?) ለነዛዜ ሞት በመብቃቱ የዚያን ዘመን አማልክትን እያመሰገነ የአክሱምን ታላላቅ ሰዎች ለመጨረሻ ጊዜ አስጠራቸውና ቃል ኪዳናቸውን አስታወሳቸው።

"አማልክቱ ለገዛ ምክንያታቸው ወንድ ልጅ ነፍገውኛል። ይሁን እንጂ ልጄ ሳባ ከወንድ ልጅ ብትበልጥ እንጂ ስለማታንስ በቃላችን መሰረት እሷ ናት የኔን አልጋ የምትወርስ"

"ይሁን ንጉሥ ሆይ" አሉት። ሞተ ቀበሩት፡

ባህል በሚያዘው መሰረት የሀዘን ቀናት ካለፉ በኋላ (አርባ?ሰባ?መቶሃያ?) ጠርተው ያነግሱኛል ብላ ብትጠብቅ ምንም። አፍ አውጥታ ከአባቷ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ብታስታውሳቸው፣

"እኛ ለአባትሽ የማልንለት ወንድ ይወልዳል ብለን እንጂ፣ እንዴት እኛ ቁጭ ብለን ሳንሸና ሴት ትነግስብናለች ባክሽ?" አሉዋት።

ሄዳ አባቷ መቃብር ጋ ተንበርክካ (?) አለቀሰች።

ሆነም፤ ልእልት ሳባ ካፈሰሰቻቸው የእንባ ጠብታዎቿ አንዷ (ሰባተኛዋ አስረኛዋ አስራሁለተኛዋ አርባኛዋ) በመሀላና በክህደት ምክንያት ቀስ እያለች ተለወጠች። ያንን አንጋቦስ በስትራቴጂና በታክቲክ የገደለውን ዘንዶ ሆነች። ወይ የሳባ እንባ! እንዲያው ቁርጥ እኮ!

ሳባ ሆዬ እንባዋን ጠራረገችና ዘንዶውን አስከትላ ስተት ብላ ወደ ከሀዲዎቹ ታላላቅ ሰዎች "ወፈርሁ ወደንገፁ ፈድፋዶ መኳንንት!" እንዲል መፅሀፉ።

መኳንንት ሆዬ እየተርበተበቱ እና ሌላም ነገር እየሆኑ (ያኔ ነው ይባላል ሽንታም ቅዘናም የሚሉት ዘፈኖች የተፈጠሩት)

"ዘንዶሽን ውሰጅልን እንጂ ከንግዲህ ከነዘር ማንዘሮችሽ ንገሺ" አሉዋት። ልእልት ሳባም ስንደዶ አፍንጫዋን ባለንጋ ጣቶቿ ይዛ በልቧ "ሽንታም፣ ቅዘናም!" የሚባለውን ዘፈን (በኋላ አገርና አህጉር ያጥለቀለቀውን) እየዘፈነች ወዳባቷ መቃብር ተመለሰች።

ዘንዶዋም ጉንጯን ሳማት "በዚህ አይደል የወረድነው? አይንና አፍንጫችንን ግን ደፍረን አንስምም። በሩቅ እጅ እንነሳለን እንጂ" አለ (እጅ ነበረው'ንዴ ግን?)

እና ተመልሶ እያነሰ ሄደ። የእንባ ጠብታም ሆነ። ወዲያው ወደ ሰማይ ተነነ።

በዚህም ላባቷ የመኳንንቱን ቅሌት እንደሚነግረው አወቀች። ወደ ላይ ቀና ብላ ፈገግ አለችና

"ቻው አባዬ! መጥቼ እስክንገናኝ ድረስ!" አለችው

"ኦኬ ቤቢ! ወደ ፊት!" አላት ነገሰች።

**ነሀሴ 2 ቀን 1985**

## ፪

እግረ መንገድዋን ውርድወት ውቢቱ ያገሯን ልጆች ልታስታውሳቸው በምናብ አይን ውል ልትልባቸው ወደ አዲስ አበባ መጣች። ውርድወትን ለአለም ዘውድ ጎንጤ አጫወትኳት። በዚህ አምድ እንድጥፈው አዘዘችኝ። ፈገግታ የለበሰ ትእዛዝ እና የታመኑ የወሬ ምንጮችን ጠቅሶ ሮይተር እንደዘገበው ከሆነ ውዳሴ ውርድወትን ለፍቅር አምላክ አማትበን ብእራችንን ተሳልመን ስለዓፍነው የሻሩም አሉ፣ ያረሩም አሉ። የሻሩትም ይበልጥ ይሽሩ ዘንድ፣ ያረሩትም የባሰ ያሩ ዘንድ የሚከተለውን እንጨምርላቸዋለን።

ሀረግ መዛኙ ሲቃውንት ውርድወት የሳባ ቀጥተኛ ተወላጅ መሆኗን በእርግጠኝነት መስክረዋል (ቀጥተኛ ተወላጅነት ከናት ወደሴት ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ እየመጣ ሳባ እገሊትን ወለደች እገሊት እገሊትን ወለደች እያለ መጥቶ ቀጥታ ውርድወት ላይ ከተፍ፡፡) በአባት መቁጠርማ አያስተማምንም፡፡ (አክሱም የሳባ አገርና ጉራእ የውርድወት አገር ቅርብ ለቅርብ ናቸው፡፡) (ለወጣት አንባቢያን - ጉራጌዎች ጉራእ ከሚባል ትግራይ ወይ ኤርትራ ውስጥ ከሚገኝ አገር ፈልሰው በአበጋዝ ስብሀት መሪነት አሁን ወዳሉበት ወደ ሰባት ቤት የመጡ ናቸው፡፡ ሰባት ቤት ጉራጌ፣ አስራ ሁለት ቤት እስራኤል፡፡ አንድ፣ ሶስት፣ ሰባት፣ አስር፣ አስራ ሁለት፣ አርባ - እነዚህን ቁጥሮች አስቡባቸው እስቲ)

ሳባን ወደ እስራኤልም ጉዞዋ ሸኝተናት በቸር ተመለሺ፣ አማልክቱ ይከተሉሽ ብለናት ከተሰናበትናት በኋላ ምን ምን አጋጠማት፡፡

ንግስት ሳባን አጅበው ከሄዱት እልፍ እምአእላፍ ሰዎችና እንስሳት አንዱ ግእዝ አረብኛ እና እብራይስጥ የሚባሉ እህትማማች ተመሳሳይ ቋንቋዎች የሚያውቅ የሮይተር ዜና ሰብሳቢ ነበር፡፡ እሱ ያስተላለፈውን ዘገባ ከዚህ በታች እናሰፍራለን፡፡ በነገራችን ላይ እኔም ተከትያት ልሄድ ፈልጌና ሞክሬም ጥሬም ነበር፡፡ *አዲስ ዘመን* ቢባል፣ *እለተ ሰንበት* ቢባል "ባጀት የለንም" አሉኝ፡፡ ይኸው እስክሪብቶዬን ለግራ እጄ ላቀብልና እጃችሁን ልምታ "ማር-ያ-ም-ን!" ወደ ሮይተር ዘገባ፡፡

ንግስት ላገራቸው መኳንንት እንደ ደራጉን የሚያስፈሩ ናቸው፡፡ ለተቀረው ዜጋቸውና ለውጭው አለም ግን እንደቢራቢሮ ወይም እንዳበባ ውብና ብርሀናማ ናቸው መሬት የሚያስሰውን የሀር ቀሚሳቸውን ለብሰው ሲራመዱ ማየት የውበትና የግርማ ተአምር ማየት ነው፡፡

ለዚህም ነው ንጉስ ሰለሞንን ያህል ጠቢብ ውበታቸው (ለዚያውም'ኮ ይህን ስሜት የሚያሳድሩብን በግራ እግራቸው እያነከሱ ነው) አሸንፎት ዋና የመስተንግዶ ህጉን ያስጣሰው፡፡ ለአመል ነው የሚያነክሱት፣ ግን አብዛኛው ሰው ማንከሳቸው አይታየውም፡፡

እንግዳ ክቡር ነው፤ የእጊዚሀር ወኪል ነው፡፡ አክብረው ይቀበሉታል፤ አክብረው ያስተናግዱታል፤ አክብረው ይሸኙታል፡፡ ባህርና ምድረበዳ አቋርጣ እሱን ብላ የመጣች የተከበረች እንግዳ፡፡

ሰለሞን ግን እንግዳይቱን ሸፍጧት አታሏት ድንግሏን ወሰደባት፡፡ (ይህ ሰላቢ ይሁዲ) ምን ይሄ ብቻ! አስረገዛትም እንጂ፡፡ እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገን መኳንንቱ በመጨረሻ የግዳቸውን ሳባን ሲያነግሷት "ድንግል እስከሆንሽ ድረስ ብቻ ነው ግን የኛ ንግስት የምትሆኚው፡፡ ለማንም ይሁን ለማን መቼም ይሁን የትም ድንግልናሽን ያስረከብሽ እለት ግን 'ቫይ ቪያ ዲስክሪሲያቶ!' ብለን ነው በካልቾ የምናባርርሽ ብለዋት ተስማምታለች፡፡

"ጣልያንኛም አያስፈልግም ካልቾም አያስፈልግም!" አለቻቸው እየገላ መጠቻቸው "ምርጫዬ ወይ ዘውድ፤ ወይ ወንድ መሆኑን አውቃለሁ" (የዳግማዊ ዘንዶው ፍርሀት ሲለቃቸው ጊዜ እንደገና ሙግት ክርክር አመጡ) እስቲ እግዚሄር ያሳያችሁ እንዲህ'ኮ ጉድ የሰራት ያ ሰላቢ ሰለሞን፣ ያውም'ኮ ሰባት መቶ ሚስቶች ሶስት መቶ እቁባት (ቅምጦች) እያሉት ነው፡፡ ባይገርማችሁ ወደዚያ ጉድ እንዴት ተደረሰ ግን?

ንጉስ ሰለሞንን ካገር ድምበር የመጣ መልእክተኛ ነግሮታል፡፡ "ጥበበኛ ነህ ሲሉ ስለሰማሁ ጥበብህን ለማየት ከሩቅ አገር መጥቻለሁ፡፡ ፍቀድልኝ"

"በልዩ ጥንቃቄና ከበሬታ እንድታጅቧቸው ንግስቲቱን፡፡ የኔን እህት እንደምታመጡልኝ ያህል" ብሎ ተቀባዮች ላከላት፡፡ "ዙፋንን ያህል አንገብጋቢ ነገር ለአደጋ ትታ ጥበብ ለማየት 'ምትመጣ-ሚመጡ ልበል እንጂ፡፡ ዙፋንስ? አለምስ? ምኔ ነው? አይቼው በቅቶኛል ያሉ አሮጊት ንግስት ሳይሆኑ አይቀሩም" ብሎ ገመተ

ሰለሞን እንደልማዱ ተዝናንቶ ስለጥበብና ስለሴት ልጅ እያሰበና ንብ ቢራቢሮውን እያስተዋለ አትክልት ውስጥ ሲዘዋወር ያ ክልፍልፍ አጋፋሪ (የኘሮቶኮል ወይም የስነ ስርአት ሹም) እየሮጠ መጣና ልናገር

ይፈቀድልኝ እንኳን ሳይል ቁና ቁና እየተነፈሰ "መጣች ደረሰች የሩቅ አገር ንግስቲቱ እህትህ" አለ፡፡

"እንቺ ነው 'ምትላቸው!?" ትንሽዬ ቁጣ፡፡

"ይቅርታ ይደረግልኝ ንጉስ ሆይ! ከወጣትነታቸውና ከውበታቸው የተነሳ ልቤ ውስጥ አንተን አንተ እንደምልህ ሆነብኝ፡፡"

"አትዘባረቅ እንግዲህ፡፡ ንግስቲቱ ወጣት ናቸው ነው የምትለኝ?"

"ካንተ ይወጥታሉ" አለ እየተቻኮለ

"ደግሞ በግራ በኩል ትንሽ ታነክስ ነበር ወደዚህ ሳጅባት፡፡ ወዳንተ ግቢ በአንበሳ በር በኩል ተከትያት ልክ በሩን ስትሻገር መሬቱን ከሚያስሰው ብርቅርቅ ቀሚሷ ስር የሆነ ነገር ተፈናጥሮ እፊታችን ወደቀ ምንድነው ብዬ ባየው - ያህያ ሸሆና! ቀጥሎ ገርሞኝ ሳያት ሁለት እግሯ እኩል ይረግጣል አታነክስም፡፡"

"ምን እያልክ ነው ግን?"

"ግራ እግሯ ሸኮና የነበረው አንተ ቅፅር ግቢ ስትገባ ተፈናጥሮ ወደቀላት ወይ አንተ ወይ ቤትህ አዳናችኋት፡፡"

"አትዘባርቅ አልተባልክም? ቤሸቲያ! ህጠራው!" ብሎ አካለበው በጠራ እብራይስጥኛ የፖለቲካ ጥበብ አስገድዶት ባይሆን ኖሮ ገና ድሮ "ሻይ ቢያ ዲስክሪሲያቶ!" አንድ ካልቾ መርቆለት አሰናብቶት ነበር፡፡ እስቲ እዝጌር ያሳያችሁ!

"ግድ የለም ቀኑን ይጠብቅ!" አለ ሰለሞን ለራሱ፡፡ በዚያች ደቂቃና ሰከንድ ነው ይላሉ ሰለሞን የማይረሳ ዝነኛ ጥበቡን የተናገረው.... ዙሪያውን የቆሙት ይሰሙት ዘንድ ዝግ ጆሮዋቸውን አንኳኳ እህህ! ብሎ ጉሮሮውን በመጥረግ፡፡

"ለሁሉ ጊዜ አለው!" አለ ሰለሞን የሰሙት አደነቁ፡፡ ሊፃፍ ይገባዋል ተባለ ተፃፈ ከጭማሪ ጋር፡፡ "ለአህዛብም ለክርስቲያንም ልመርቅላቸው" አለ ጠቢብ ንጉስ፡፡

ሆነም፤ ጊዜው በደረሰ ጊዜ ንግስተ ሳባን ወደ ንጉስ ሰለሞን አመጡዋት። ባያትም ጊዜ ልቡ ትርክክ አለ - ቅፅበታዊ ፍቅርም እልቡ ውስጥ ገብቶ አቃጠለው። ነደደ።

ሰለሞን ከጥበቡ ብዛት የተነሳ ሳባን ከቁርስ በኋላ አትክልት ውስጥ እንንሸራሸር ብሎ ወሰዳትና የረጋ ውሀ ተሻገሩ። ሰለሞን ጊዜውን አነጣጥሮ አይኑን ወደ ውሀው ቢወረውር - ለቅፅበት ወለል ብላ ታየችው በውሀው መስታወት። አቤት የእግሮቿ ውበት! እስከሚገናኙ ድረስ አያቸው ጭኖቿን። ሰአሊለነ ቅድስት የሴት ልጅ ውበት ተአምር!

"ካንቺ ጋር አድሬ ሲነጋ ልሙት

ላፈር አይደለም ወይ የተፈጠርኩት" ሲል ሰለሞን ሌላ ጥበብ በልቡ የተናገረው ያን ጊዜ ነበር።

ቀናትም ሳምንታትም አለፉ። ሰለሞንና ሳባ ሲበዛ ተግባቡ ተዋደዱ በጣም አርቦሽ ሆኑ። የሰራውን ቤተመቅደስና ከእንደበቱ የሚወጣውን ጥበብ አደነቀች። እንኳንም መጣሁ አለች። አንድ እንቆቅልሽ አቀረበችለት - ጥበበኛነቱን ለመጨረሻ ለመፈተን። ልክ የዝጌር አበባ የሚመስሉ የክር አበባዎች ሰፍታ እውነተኞቹ አበባዎች መሀል ተከለቻቸውና ሰለሞንን ጠርታ "የትኞቹ ናቸው የኔ ስፌት አበባዎች? በእጅሀ ሳትነካ ባፍንጫህ ሳታሸት በአይንህ ብቻ ለይተህ ንገረኝ" አለችው።

እና ለይቶ ነገራት። ይሄ ቡዳ!

"ብራቮ ልጅ!" አለችው ጀርባውን መታ እያደረገች "እንዴት አወክ ለመሆኑ?"

"ንቦቹና በራሪ ነፍሳቱ እንዲሁም ሌሎች ጥቃቅን ፍጡራን ያንቺን አበቦች አይጎበኙዋቸውም" አላት

"እንዲያው ምን ላርግህ? የኔ ባትሆን እንዴት ይቆጨኝ ነበር!"

"ያንቺ ነኝ እንዴ?"

"ነሀና!"

"ታድያ ምነው እንደ አዳምና ሄዋን እንተቃቀፍ ስልሽ እምቢ ትያለሽ?"

"እየነገርኩህ! ድንግል ሆኜ እንድኖር መሀላ አለብኝ እያልኩህ!"

"ታድያ አንቺ የማልሽ እንደሆነ እኔ በፍቅር መሞት አለብኝ!"

"ተው'ንጂ እንደሱ አትበል የኔ ቆንጆ"

ጊዜው ደረሰና ሰለሞን በሳባ ላይ ቆራጥ ርምጃ ሊወስድባት ተነሳ።

ነሀሴ 9 ቀን 1985

## ፫

ሆነም፣ ንግስት ሳባ ለጠቢቡ ንጉስ ወርቅ፣ ሀር፣ ከርቤ፣ እና ከዚያም ሁሉ በላይ ያን ማራኪ ውበቷን - ገፀ በረከት ይዛለት ጥበብን ትማር ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም መጣች። እሹ ታገኛላችሁ ነውና እሱም ጥበብን አስተማራት። የሁለት መቶ ሃያ አምስት ተከታታይ ትውልድ ንጉሶች ምንጭ እናት የመሆንን ጥበብ አስተማራት። አለም የሚያውቀው ነው ሁለት መቶ ሃያ አምስተኛውና መጨረሻው እኚህ የኛ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ነበሩ። እኛ ምን ቸገረን ይሁን አፈ-ታሪካችንን እንቀጥላለን።

ጨረቃይቱ ንግስታችን የዳዊትን ከተማ ዘለአለማይቱን ኢየሩሳሌም በአህያ ሽኮናዋ ረግጣ ድና ተመስገን ባለች በሰባተኛው ወር፣ ከወሩም በሰባተኛው ሳምንት፣ ከሳምንቱም በሰባተኛው ሰአት፣

ጠቢቡ ንጉስ ሰለሞን ድንግሊቱን ንግስት ሳባን እነሆ በረከት ሊላት ትላንትን ብቻ ሳይሆን ዛሬንም ነገንም አጣርታ በምታየው ጥበቡ ወሰነ፡፡

ወዲያው ጠቢቡ ንጉስ ወጥ ቤቱን አስጠራ፡፡ "ሞክሼ" አለው - በዚያው ዘመን ንጉስ የወጥ ቤት ሞክሼ መሆን መብቱ ነበር፡፡ "ለዛሬ እራት ብዙና በርከት ያለ ጨው የተለወሰ አሳ ነው የንግስቲቱ፤ የኔ ግን የጨው ብዛት እንዳይታወቀን ሌሎች ቅጠላት ወቅመማት! ሌላው ሰው ግን እንደመሰለህ ያቀረብከውን እራት ይብላ፡፡"

"ትእዛዝህ ደስታዬ ነው ንጉስ ሆይ" አለና ሰግዶ ወደ ትእዛዝና ደስታው ሄደ እየተጣደፈና "አውቀዋለሁ ይህን ወንበዴ፡፡ ዛሬ ማታ ይቺ ልጅ አታመልጠውም" ብሎ እያሰበ፡፡

አሳውን እንደታዘዘው ሲያዘጋጅ እቺ ሀሳብ ታጫውተው ነበር፡- "እሺ እንደፈቃድህ ይሁን" እንደምትለው ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ጥያቄው የግዷን ነው ወይስ የውዷን ነው እሺ'ምትለው? እያወቀች ነው ወይስ እየተታለለች ነው?

ወይስ እሷ ራሷስ በውል ታውቅ ይሆን የት ድረስ ወዳ እንደምትሄድና የት ድረስ እንደሚያታልላት? (እዚች ላይ አንዲት የፈረንሳዮች አባባል) "በጦርነትና በፍቅር የመጣ ማናቸውም ነገር ይፈቀዳል"

የሚጠበሰው አሳ ልዩ አይነቱ የጠባሹን ሀሳቦች እንደሚሰማ ጥንት በባቢሎን ዘመን ጀምሮ ለአዋቂዎች የታወቀ ነው፡፡ እና ንጉስ ሰለሞን ጠባሹ ምን ያስብ እንደነበረ ከተጠበሰው አሳ በሰማ ጊዜ ሳያስበው ሳቁ አመለጠው

"ሳቅ መጋራት ይፈቀዳል አንቱዬ!" አለችው በለስላሳው እያየችው

"ይፈቀዳል፡፡ ግን ለዛሬ ቢተላለፍ መልካም ፈቃድሽ ይሁንልኝ ሳብዬ የልቤ ንግስት፡፡ ለኔ ከሳቅ የሚብስብኝ ነገር ስላለ እሱን ብናነሳ ይቀድምብኛል፡፡ በነገራችን ላይ አሳ ጥብሱ እንዴት ነው?"

"ለሞክሼህ ነገርልኝ። እስከዛሬ እንዲህ የሚጥም ጣት የሚያስቆረጥም አሳ ጥብስ ቀምሼ አላውቅም።"

እሷ ጣት ስትል እሱ ለስንተ መቶ ሺኛ ጊዜ አይኖቹን ወደ ጣቶቿ ወረወረ። ሆኖም ግን ምንም ጠቢብ ቢሆን አለንጋ ጣቶቿን ደጋግሞ ባያቸው ቁጥር ለምን የበለጠ እያማሩ እንደሚቆዩት ሊያውቅ አልቻለም (ጥበብ ሌላ፤ ፍቅር ሌላ)

ሳናውቅ ወደፊት! አለ ሰለሞን አንዲት ጣቱን በመፈክርኛ ጨብጦ እያነሳ።

"እኔ'ምልሽ ሳብዬ፤ ያንቺ መሀላ እኔን ሊያስረኝ ይገባል?"

"አልማልኩም'ኮ" ካለችው በኋላ፤ እሱ በሷ ቦታ ሆኖ ለአክሱም መኳንንት "ምርጫዬ ወይ ወንድ ወይ ዘውድ መሆኑን አውቃለሁ" ሲልላት ታያትና ድንገት ከት ብላ ሳቀች።

ሳቋ በአይኑም በጆሮውም ገብቶ ወረረውና አብሯት እየሳቀ "ሳቅ መጋራት ይፈቀዳል እቴዋ?" አላት ሴት ወዶ እንደማያውቅ ያህል በአዲስ ልብ እየወደዳት። ያሳቃትን ሀሳብ ነገረችው። ቷ! ብሎ ፈንድቆ ሳቀ። እራት ተበልቶ ማእድ እስኪነሳ ድረስ ሳቁ አስራሁለት ጊዜ አገረሸበት። በነጋታው ኢየሩሳሌም ስለንጉሱ ሳቅ ስትደነቅና የሳቀባቸውን አርባ ምክንያቶች ከመሬት ተነስታ ማለቴ ከሰለሞን ሳቅ ተነስታ ስትፈጥር ዋለች።

በሳቆቹ መሀል የምሩን እንዲህ አላት

"እቴዋ፣ ያንቺ መሀላ የሰው ነው። ሁለታችንም ከባድ ሸክም የሆነውን ነግሶ አገር መምራት እናውቃለን። ሰው ሰራሽ ነው። የኔና ያንቺ መዋደድ ግን ገና ከመጀመሪያው ፈጣሪ ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥረን 'ይሁን!' የተባለ ነው። አንቺ መሀላሽን ጠብቂ። ከእንግዲህ ግን ላስጠንቅቅሽ፤ ካሁን አንስቶ እንግዳዬ አይደለሽም። ፈጣሪ የላከልኝ ፍቅረኛዬ ነሽ ካንቺ በፊት ስንት ሴት እንደማውቅ ልነግርሽ

አያስፈልግም፡፡ ብዙ ናቸው ብለን እንለፈው፡፡ ጣቶችሽን እያቸውማ፡፡ ላንቺ ዝም ብሎ ጣቶች ሳይሆኑ አይቀሩም ለኔ ግን እነዚህ ጣቶች ውስጥ ከዚህ በፊት ካወኩዋቸው ብዙ ሴቶች ብዙ ውበት የበለጠ ብዙ ውበት አላቸው፡፡

"ያለ ምክንያት የሚሆን ምንም ነገር የለም፡፡ እንዲህ የወደድኩሽ እኔ በማላውቀው ምክንያት ነው፡፡ ግን ከዚች ሰአት ወዲያ እንድታውቂው የምፈልገው የመስተንግዶን ባህል ባንቺ የመጣ ልጥሰው ወስኛለሁ፡፡ ድንግልናሽ ብርቅ ሀብት ከመሰለሽ የኔን ብርቅ ሀብት አትንኪብኝ፤ ያንቺን አልነካብሽም፡፡ ከነካሽብኝ ግን መንካት ብቻ አይደለም አስወልድሻለሁ"

"አትለኝም!" አለችው

"እልሽ እንጂ! ያውም ቢያንስ ሁለት መቶ ሃያ አምስት ነገስታት እስክትወልጂ ድረስ"

"አንድ ማህፀን አይጠባቸውም? አይጨናነቁም?"

እንደገና የንጉሱ ሳቅ በመላው የግብር አዳራሽ አስተጋባ

"እንዴት አርጎ ነው የፈጠረሽ ግን?" አላት አይኖቹ ውስጥ የአድናቆት ከዋክብት እያበሩ፡፡

"ልንገርህ ታምነኛለህ? ፈጣሪ አዳምንም ይሁን ሄዋንን ሲፈጥር ፈጠራቸው እንደተነገረን፡፡ ሲያይ ጊዜ ሲፈጥራቸው እጁን አልታጠበም ነበር፡፡ እኔን ሊፈጥረኝ ሲነሳ ለራሱ እንዲህ አለ፡፡ ‹እኔው ነኝና ፈጣሪ ሆዬ! ያሁኗንስ ሄዋን እጄን ታጥቤ ነው የምፈጥራት› አለና እጁን ታጥቦ ፈጠረኝ፡፡"

"አትይኝም!"

"እልህ እንጂ!" አለችው ሁለመናዋ ሳቅ እስኪመስለው ጉራማይሌ ጥርሶችዋ እያብለጨለጩበት፡፡ (በዚያች ቅፅበት ነበር ንጉስ ሰለሞን

መሀልየ መሀልይ በተባለው ያ ለሳባ የተፃፈ የፍቅር ግጥሙ በምእራፍ አርባ ቁጥር ሰባት እንዲህ ያለው፡-

"ልሳምሽ አልኩ እንጂ መች አልኩኝ እንተኛ
እንዴት ነው ከንፈርሽ የጥርስሽ ዘበኛ
እንደ ኢየሩሳሌም እንደ አክሱም ዕዮን
ተሳልሜው መጣሁ አይንና ጥርሷን")

እንዲህም ማለቱ የሁለቱን ፍቅረኛሞች አገሮች ማገናኘት ማቀራኘት ደስ ስላሰኘው ነው፡፡

ከዚያም አልባሹን አስጠራውና በሹክሹክታ "ንግስት መኝታ ውስጥ ውሀ እንዳይኖር፤ የኔ አልጋ አጠገብ ያቺ የምወዳትን ጠርሙስ ውሀ ሞልተህ አኑር"

"ትእዛዝህ ደስታዬ ነው ንጉስ ሆይ" አለና ሄዶ የታዘዘውን ፈፀመ፡፡

ከግብር በኋላ አልባሽና ወጥቤት ከሌሎች አገልጋዮች ጋር እራታቸውን እየበሉ ተነጋገሩበት የሰለሞንን የአሳ-ጨውና የውሀ ትእዛዝ፡፡

"ይኸ አራዳ ዱርዬ" አለ ወጥ ቤትየው ሰለሞንን እያደነቀ፡፡ መኝታ ክፍሎቻቸው ጎን ለጎን ሆነው በቀይ የሀር መጋረጃ ብቻ የተዘጋ በር እንደሚያገናኛቸው ያውቃል፡፡ በአሳ ጥብሱ ብዙ ጨው በልታለች፡፡ ለሊት ውሀ ይጠማታል፡፡ እመኝታዋ ውሀ የለም፡፡ አልባሹን እየተራገመች ቀስ ብላ መጋረጃውን ከፍታ ውሀ ለመጠጣት ወደሱ መኝታ ትገባለች፡፡ ልክ እየተንገበገበች ውሀውን ጠጥታ እንዳበቃች አድፍጦ ቆይቶ አፈፍ ያረጋትና "መጣሽብኝ እንጂ አልመጣሁብሽም" ይልና-ይሄ ሌባ!

ነሀሴ 16 ቀን 1985

# ፬

አበው በጥበባቸው ሳባ ወደ እየሩሳሌም ስትዘምት ደንገጡሯን ታስከትል ዘንድ መከሩ፡፡ እሷም የተዋበች የሳባ አብሮ አደግ ነበረች፡፡ ጓደኛዋም ናት፣ ለሳባ ለሴቲቱ ታማኝ አገልጋይዋም ናት ለንግስቲቱ፡፡

እንግዲህ ይታያችሁ በአንድ ክፍል ንግስቲቱና ደንገጡርዋ ለእራት በጨውና ቅመማቅመም ያበደች የአሳ ጥብስ በልተው አልጋቸው ላይ ተጋድመዋል፡፡ ሻማይቱ ልታልቅ ትንሽ ስለቀራት በሽታ ትንቀለቀላለች፡፡

"ውሀ ጥም ሲገለኝ ነው አንቺዬ"

"እኔስ!" በሹክሹክታ ነው፤ እወዲያኛው ክፍል ንጉስ ተኝተዋል፡፡ ሁለቱን መኝታ ክፍሎች የሚያገናኛቸው በር መዝጊያው ቀይ የሀር መጋረጃ ነው፡፡ ቀይ በዚህ ታሪክ ውስጥ አደገኛ ትርጉም እንዳለው ከወዲሁ እየተስተዋለ፡፡ ሹክሹክ፡፡

"ያ ነጃሳ አልባሽ ደግሞ እርማችንን ዛሬ ውሀ ቢጠማን እርሙን ዛሬ ውሀ ሳያኖርልን መቅረቱ"

"አይገርምሽም!" ዛሬ ለሊት ተገርመው ላያባሩ ነው እነዚህ ልጆች፡፡

"ሂጂና ቀስ ብለሽ ከወዲያኛው ክፍል ውሀ አምጪ"

መጋረጃውን ከፍታ ወደዚያኛው ክፍል ዘለቀች፡፡ ንጉሱ በጀርባቸው ተኝተው-አልተኙም ኧረ! ወደ ጣራው አፍጥጠዋል፡፡ ደንገጡሪት ፈርታ ቦዶ እጅዋን ወደ ንግስቲቱ ተመለሰች፡፡

ሆኖም ሰለሞን በጥበቡ ሲያስፈልግ ድብን ያለ እንቅልፍ ተኝቶ አይኑ ወደ ሰማየ ሰማያት ያፈጣል ሲነቃ ደግሞ አይኑን ይከድናል፡፡ ጥበብ ነዋ! ቆይቶ ቆይቶ ሰለሞን ነቅቶ አይኑን ከድኖ ጥበበ ጥበባትን ሲያሰላስላት ሳለ እመት ደንገጡሪት ሆዬ በውሀ ጥም እየተቃጠለች ተኝቷል ብላ ቀስ ብላ የውሀ ጠርሙሱን አነሳች፡፡

አፈፍ አደረጋት እጅዋን፤ ድንግጥ! ክው! ብላ ቀረች። ጠርሙሱን ተቀበላት ከፈተው ሰጣት። ዥው አርጋ ጠጣች። ስትጨርስ እጅዋን ይዞ ወደ አልጋው ወሰዳት። እነሆ በረከት አላት። ይኸ ሁሉ የሚሆነው በዝምታ ነው። ያን ጊዜ ነው ንጉስ ሰለሞን "ቅኔ ብር ናት - ዝምታ ግን ወርቅ ናት" ሲል የተፈላሰፈው።

ደንገጡሪትን ባዶ እጅዋን ወደ ንግስቲቱ ላካት። (የመስተንግዶ ስም ሲያወጣላት ማቆያ አላት እንዲል መፅሀፉ።)

"ይህን ሁሉ ጊዜ ቆይተሽ ባዶ እጅሽን መጣሽ?" በሹክሹክታ።

"ፈራሁ እናቴ! ወደ ሰማይ አፍጧል አሁንም። ሞቷል መሰለኝ ፈራሁ።"

ሶስተኛዋ ሻማ ስትጋመስ ሳባ የመጣው ይምጣ እንጂ በውሀ ጥም አልሞትም ብላ በቀስታ ተነስታ መጋረጃውን (ቀዩን) ከፍታ ወደዚያኛው ክፍል ዘለቀች። አሰይ ተኝቷል። ቀስ ብላ በሹክሹክታ ደርሳ ጠርሙሱን አንስታ ከፍታ ዥው አድርጋ ጠጣች። ወይ አንቺ እምዬ! ውሀ እንዲህ አርጎ ይጣፍጣል!? ልክ ጠጥታ ስትጨርስ አፈፍ! ክው! ድንግጥ!

"ውል አፍርሰሻል" አላት በፈገግታና በሹክሹክታ

"የምን ውል?"

"እኔም ያንቺን ብርቅ ድንግልሽን አልነካብሽም፤ አንቺም የኔን ብርቅ ንብረቴን አትነኪም"

"ታዲያ ምን ንብረት ነካሁ?"

"ከውሀ የበለጠ ብርቅ ንብረት ይኖራል ብለሽ ንግስት ሆይ?" አላት አልጋ ላይ እያጋደማት።

"እውነትም!" አለች በጥበቡ እየተገረመች።

በዚህ አኳኋን ነበር ይባላል ሰለሞናዊ ስርወ መንግስታችንና ዛጉዬ ስርወ-መንግስታችን ባንዲት ለሊት የተፀነሱት በጨውና በውሀ ጥበብ።

ሆነም፣ ንጉስ ሰለሞንም ከብዙ አጀብ ጋር ወጥቶ ንግስተ ሳባን በክብር ወደ አገሯ ሸኛት። እመንገድ ላይም ወንድ ልጅ ተገላገለች። ደንገጡርዋም እንደዚሁ። ሁለቱም ብላቴናዎች አብረው አደጉ።

ሆኖም አንድ እለት ልኡል ምኒልክ ከሌሎች ጎረምሶች ጋር ገና ሲጫወት አንዱ ምላሰኛ "የታባክ" ብሎ ሰደበው፣ ከዚያ በፊት የታባክ የሚሉት ስድብ አይታወቅም።

ምኒልክ ይህ ስድብ ሲከነክነው ዋለ። እራት ላይ እናቱን ጠየቃት "አባቴ ማነው?"

ስለኢየሩሳሌም ጉዞዋ በዝርዝር አጫወተችው።

"ሰለሞን ሲሸኘኝ ይቺን ቀለበት ሰጠኝና እንዲህ አለኝ። ወንድ የወለድሽ እንደሆነ አድጎ አባቱን ማወቅ ሲፈልግ ይቺን ቀለበት ምልክት አስይዘሽ ላኪልኝ። እንግዲህ ስንቅና ጓዝ ይዘጋጅልህና ተራህን ወደ ኢየሩሳሌም ሂድ ታድለህ! በነገራችን ላይ መልኩ ቁርጥ አንተን ነው" አለችና በናፍቆት ፀጉሩን ዳበሰችው።

ምኒልክና ወንድሙ ወደ ንጉስ ሰለሞን ዙፋን ሲገቡ ወንድምየው ሄዶ እዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን አባቱን ሳመው። ምኒልክ ግን አልሳመውም፣ መልኩ እሱን አይመስልማ። ዙሪያውን የቆሙትን መኳንንት ተመለከተና ሄዶ አንዱን ሳመው መልኩ እሱን ይመስላል ሰለሞንም በልጁ ብልህነት ተደሰተ "እውነትም የሳባ ልጅ" አለው በናፍቆት ራሱን እየደባበሰ። ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የነበረው መኳንንት ተነሳና ሰለሞን ዙፋን ላይ ተቀመጠ።

ምኒልክና ወንድሙ ባባታቸው ቤተመንግስት ብዙ ወራት ኖሩ። ኦሪትም ተማሩ። ወደ አገራቸው ሊመለሱ ሲሆን ሰለሞን መኳንንቱን ጠርቶ እንዲህ አላቸው

"በኩር ልጄ ወደ ሀገሩ ሊሄድ ነው የናንተም በኩር ልጆች አብረውት ይሂዱና ባለሟሎች ይሁኑት"

ምኒልክም የፅላተ ሙሴን ዋጋ አውቋልና ልክ ቁርጥ እሱን የሚመስል ፅላት አስቀረፀ፡፡ በውድቅት ቤተመቅደስ ገብቶ እውነተኛውን ፅላት ወስዶ በቦታው ያንን ያስቀረፀውን ፅላት አኖረ፡፡

ምኒልክ፣ ወንድሙ እና ያ ሁሉ የሰለሞን የመኳንንት ልጅ በብዙ አጀብ ወደ አክሱም ተጓዙ፡፡ ከዚያም ሲደርሱ ቤተመቅደስ አሰርተው ፅላቱን እዚያው አኖሩ፡፡ ዛሬ ፅላተ ሙሴ ፅዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛል፡፡

በዚህ አኳኋን ነበር እኛ ሀበሾች ኦሪትን ከእስራኤላውያን የተቀበልነ፡፡ እውነተኛውንም ፅላት የወረስነ፡፡ ያእቆብ በረከቱንና ብኩርናውን ከኤሳው እንደወሰደው (ሰረቀ አይደለም መቼም) በብልሀት ወሰደበት፡፡ ምኒልክም ፅላቱን ከሰለሞን በብልሀት ወሰደው፡፡ ይህም ማለት የእስራኤልን በረከት እኛ ወረስነ፡፡ ከዚህም የተነሳ እነሱ ኢየሱስን እምቢ ሲሉት እኛ ወንጌሉን ተቀበልነ፡፡ "አይሁድ ክህዱ፤ ንህነስ አመነ" እንዲል፡፡

ምኒልክ የሰለሞናዊ ስርወ መንግስታችን አባት ሲሆን ወንድሙ ደግሞ የዛጉዬ ስርወ መንግስታችን አባት ነው፡፡ (ስም የለውም'ንዴ ግን?)

ነሀሴ 23 ቀን 1985

# ዮዲት

ሲያቀብጠን እግረ መንገዳችንን ወደ ውድ አገራችን አፈ-ታሪክ ጎራ አልን፤ እነሆም ሳናውቀው የማያልቅ የነገስታት ሀረግ መምዘዝ ጀመርን፡፡ እንዳመጣብን እንቀጥላለን እንጂ ምን እናደርጋለን - - -

"ዮዲት ጉዲት!" ብለህ ድንገት ብትጮህበት ማንም አክሱማዊ ላይ ወይ ይፈረጥጣል፣ ወይ ይጮሀል፣ ወይ ይንበረከካል በፍርሀት፡፡ የዮዲት ጉዲትን ፍርሀት በደሙ ወርሶታል፡፡ "ዮዲት ጉዲት ታደንግፅ ወታፈርህ ፈድፋደ ወታርበድብድ" እንዲል፡፡

አንባቢ ዮዲት ጉዲት ማናት ወይም ማን ነበረች? ሳይል አይቀርም፡፡ አክሱማውያን ግን ያውቋታል፡፡ ገና በህፃንነታቸው ነው ስለጆሮ ቆራጭ፣ ስለጭራቅና ስለዮዲት ጉዲት የሚያውቁት፡፡ ባጭሩ ስለሞናዊውን ስርወ-መንግስት አጥፍታ ዛጉዌውን ስርወ-መንግስት የተከለች ናት፡፡

አሁን መንፈሳዊ ሀረጓን እንመዛለን እንዳመጣብን፡፡ የዮዲት አባት ደብተራ ግራመስቀል ልጁ ስትወለድ አርብ እኩለ ለሊት ስለነበረ ተስፋና ፍርሀት እየተፈራረቁበት ኮከብ አስቆጥሮ፣ ጠጠር አስጥሎና መጣፍ አስገልጦ ሲያበቃ ስምዋን ዮዲት አላት፡፡ ይህም ስምዋ እንደ ዮዲት አይነት ጠንካራና ቆራጥ እንድትሆን አደረጋት፡፡ ማለት እኛ የክርስትና ልጅ እንደምንሰጥ ሁሉ ደብተራ ግራመስቀልም የመንፈስ ልጅ ሰጣት ልጁን ለዮዲት ይሁዲት፡፡ በመንፈስ፡፡

የውቢቱንና የጥበበኛይቱን የንግስተ ሳባን የስጋ አባት ታሪክ ነግረናችኋል። አሁን ደሞ የሳባ ስርወ-መንግስት ሲያበቃ የዛጉዌውን ስርወ መንግስት ለባልዋ ያስጨበጠችውን የዮዲትን የመንፈስ ወይም የስም እናቷን ታሪክ እንናገራለን።

ያው ሁሉም ከእስራኤል ነው እንግዲህ። ሆነም፤ ናቡከደነፆር በነገሰ በአስራ ሁለተኛው አመት የጦር አበጋዙን ሆሎፈርኔስን ከብዙ ሺ ሰራዊት ጋር ልኮ በእስራኤል የምትገኘውን የቤቱሊያን ከተማ አስከበበ። ከተማይቱም በሬን አልከፍትም አላስገባም ብላ ተጋተረች። ግና ምን ይሆናል ሁሉን እምቢ ማለት ሲቻል ሆድን ግን እምቢ ማለት አይቻልምና ከአርባ ቀን ከበባ በኋላ የከተማዋ ኗሪዎች በጉባኤ ከንቲባ አዝያስን እንዲህ አሉት "በረሀብ ልናልቅ ነውና እጃችንን እንስጥ" እርሱም "እሺ እንዳላችሁ" አላቸው።

በዚህ ጊዜ ዮዲት የተባለች ከስምኦን ነገድ የምትወለድና እጅግ የተዋበች ሴት ተነስታ "እኔ ወደ አበጋዝ ሆሎፈርኔስ እንድሄድና እጅ የምንሰጥባቸውን ሁኔታዎች እንድደራደር ይፈቀድልኝ" አለች። ተፈቀደላት ገረድዋን አስከትላ ወደ አበጋዝ ድንኳን ሄደች ተኳኩላ አጊጣ። ሰውዬው ሲያያት ልቡ ደነገጠባት። የጨዋታዋ ለዛም ማረከው። ጋበዛት ቢያንስ አርባ ቀኑ ነው ሴት ካገኘ (እንበል ምናለበት ታሪካችን እንዲያምርልን)

ዋናው ቁምነገር በጦር ሊማርክ የመጣውን የጦር አዛዥ በውበትዋ ማረከችው። በመጀመሪያው ቀን እድንኳኑ ውስጥ ብቻቸውን ሲደራደሩ ሲሳሳቁ ሶስት ሰአት ሙሉ አሳለፉ። ከካምፑ ወደ ከተማው ዮዲትንና ደንገጡርዋን የክብር ዘብ ሸኛቸው።

በነጋታው ዮዲትና ሆሎፈርኔስ አራት ሰአት ሙሉ ሲያወሩ እያያት እየሰማት እየተመኛት ያውም ካርባ ቀን ፆም በኋላ።

እንደገና በነጋታው። በአራተኛው ቀን አላስቻለውም ወንድየው። ሴቲቱ አቸነፈች። በሰራዊት ጦር ያልቻለችውን ውጊያ የቤቱሊያ ከተማ

በዮዲት ውበትና አንደበት እንዲሁም ጭንቅላት አንጎል ብሬይን እና ወኔ ቻለችው።

"ካልከስ እኔም አልቻልኩም" አለችው በፍቅር እያየችው። ላገሯና እሱን ሳታየው በፊት ለወሰነችው ታማኝ ሆና እንጂ ዮዲትና ሆሎፈርኔስ ሁለቱም ሀይለኛ ከባድ አደገኛ ባለክንፍ ባለሰማይ ሰረገላ ፍቅር ይዟቸዋል።

በኋለኛው ዘመን ለሮሚዮና ለጁሊየት ያልተፈቀደላቸውን የስጋዊ ፍቅርና ስንብት ተፈቀደላቸው። ሺ አመት ለምታክል አንዲት ሰአት ራቁት ለራቁት ተቃቀፉ።

ሆሎፈርኔስ ገነት ገብቶ የዮዲትን ክንድ ተንተርሶ ወደ እንቅልፉ አለም ጭልጥ! ዮዲት ትንፋሹ የእንቅልፍ መሆኑን አረጋገጠች። እየዳሰሰችው እየሳመችው ቀስ ብላ ተነሳች። ለባበሰች። አየችው እንደገናም ወደደችው። እሷን ሊያቅፍ የፈታውን ትጥቅ አየች አደነቀች። ሰይፉን አነሳች። ከአፎቱ መዘዘችው።

ሆሎፈርኔስን በአይኗ ሁለመናውን ስማ ተሰናበተችው። አንገቱን ቀረጠችው። ጭንቅላቱን በጨርቅ ጠቅልላ ለደንገጡርዋ አሸክማ ባለፉት ሶስት ቀናት እንደሆነው ሁሉ በክብር ታጅበው ከካምፑ ወጥተው ወደ ተከበበችው ከተማ ገቡ። አቤት ስንቱ ያርባ ቀን ያመኛ ወታደር ነው ዮዲት እንደጨረቃ ስታልፍ እየታየችው ተመስገን፤ ለካ ደምና ቁስል ሞት ብቻ አይደለም እዚህ አለም ላይ። ለካ ፀሀይ ጨረቃ ኮከብ ጤዛ አበባ የምትመስል ሴት አለችበት። ተመስገን! ምነው ሞቴን እቅፏ ውስጥ ባደረክልኝ! "እዝጌሩ ደሞ ክፋቱ ጠሎትህ ይሰማል" አለ አበጋዝ ሆሎፈርኔስ

ዮዲት በጉባኤ የሆሎፈርኔስን ጭንቅላት በፀጉሩ ይዛ ለከንቲባ አዝያስ አበረከተች። እነሆ በረከት! ብላ ነዋ ያውም!

"እንደተደናገጡ እንውጣና እንምታቸው" አለች ዮዲት። ወጡና መቱዋቸው። ድል አደረጉዋቸው። ዮዲትም ለእስራኤል አምላክ የምስጋና

መዝሙር ዘመረች። ከዚያ ምስጋናም መስዋእትም ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ ይባላል።

የኛይቱ ዮዲት ሰባት አመት ሲሆናት አባቷ እንዲህ አላት "ምንም የኔ ልጅ ብትሆኚም ከእንግዲህ መፆም ይኖርብሻል። አንቺ ግን ወደፊት መሬት የምትደባልቂ ነሽ ብሎኛል ሀንዱ መዳፍ አንባቢ። የእኔን መዳፍ አንብቦ ከልጅነቴ ጀምሮ የደረሰብኝን ሁሉ ነገረኝ። እና ሁሉንም በትክክል አነበበው። ለካ የምንኖራቸውና የሚደርሱብን ነገሮች ተፅፈዋል። የሚመጡት ግራ መዳፋችን ላይ። ያለፉት ቀኝ መዳፋችን ላይ። 'ስለዚህ.......አንቺ ልዩ ነሽና እንደፈለግሽ፣ መፆም ትፈልጊያለሽ ወይስ አትፈልጊም?"

"አልፈልግም አባዬ" አለች ዮዲት ሳታመነታ።

"ለሰው ግን አንነግርም"

"እረ እኔ መፆሙም በጣም ደስ እያለኝ ነው አባዬ" አለች በዚያ ተንኮለኛና ሳቂታ ፈገግታዋ። ማንም ተራ የሰባት አመት ልጅ ሳትሆን ዮዲት በሰባት አመትዋ እንደሁልጊዜም ከእድሜ ቀደመችበት። ሲያቅፉት ሲስማት ግን ያው የሚፈሩላት የሚሰጉላት ብርቅ ልጅ ናት።

ዮዲት አስራ አራት አመት ሲሆናት አባቷ እንዲህ አላት "እሙዬ በጊዜ ከትላንት ወደ ነገ ጉዞሽ ላይ አሁንም እንደገና መንገዱ ሊገነጠል ነው። ድል አድርጌ ልዳርሽ ወይስ ይቅርብሽ?"

"ይቅርብኝ" አለችው ሳታመነታ።

"ብትፈልጊ ከናትሽ አገር ከላስታ፣ ብትፈልጊ ከአባትሽ አገር ከአክሱም መምረጥ ትችያለሽ። ዘረን ካየናቸው በኋላ የመረጥሽውን ለብቻችን ትነግሪኝና፣ በይፋ ለይሉኝታው ደሞ እኔ መርጬው ልጅህ ለልጄ እና የመሳሰለውን ሌላው ወግ እኔ እቀጥላለሁ።"

"ከፈቀድክልኝስ ባትድረኝ እመርጣለሁ። ካንተ ጋር መኖር ይሻለኛል። አባቴስ፣ እናቴስ አንተ አይደለህ?"

ድንገት እንጀቱ ተላወሰ አባትዬው፡፡ እቅፍ አደረጋት፡፡ ገና ጡት እንደጣለች ነበር እናቷ የሞተችባት፡፡ እና ደብተራ ግራመስቀልም እናቲቱን ሲበዛ ይወዳት ስለነበርና መሞቷን አስቀድማ አውቃ ኖሮ "አደራ ልጄን ለ'ንጀራ እናት እንዳትዳርጋት፡፡ ልታገባ ተፈለግክ ወስደህ ሮሀ ለናቴ ስጥልኝ" ብላው ነበር፡፡

ሮሀ ማለት በኋለኛው ዘመናት ላሊበላ የተባለው የኦሪታውያን ዋና ከተማ ነው፤ የታሪክ ማስታወሻ ለወጣቶች፡፡ እኛ ሀበሾች አስቀድሞ አህዛብ ነበርን፤ ማለት አማልክትና ጣኦታት በብዛት ነበሩን የዛሬን አያድርገውና፡፡ ከዚያ በአንድ ሺ አመተ አለም (ከክርስቶስ በፊት) የሳባ ልጅ ከኢየሩሳሌም ኦሪትን አመጣልን፡፡ ያን ሁሉ አማልክት ከዳነውና ወደ አንዱ አምላክ ተሰባሰብን፡፡ ከዚያ በአራተኛው ክፍለ ዘመን ፍሬምናጦስ ከእስክንድርያ ክርስትናን አመጣለን፤ አክሱማውያን አንዱን አምላክ ካዱትና አንድም ሶስትም የሚሉትን አምላክ ተቀበሉ፡፡ ላስቴዎቹ ግን በኦሪታቸው ፀኑ፡፡ እንግዲህ ዮዲት በአባቷ ክርስቲያን በእናቷ ኦሪታዊት ናት እንበል፡፡

አንዱ የታደለ የማርያም ፅዮን ዲያቆን ከዮዲት ጋር ፍቅር ያዘው፡፡ ከወርቅና ከሌላ ክቡር ድንጋይ የተሰሩ የቤተክርስቲያኑ ንብረቶች ቀስ በቀስ ሲጠፉ ድንገት ተስተዋለ፡፡ ጎበዝ አይንህን ክፈት ተባለ፡፡ ዲያቆን ሲሰርቅ እጅ ከፍንጅ ተያዘ፡፡ ምራ አሉት፡፡ ቶርች ማድረግ ወሬ መገልበጥ የዛን ጊዜ የለም፡፡ ቄሱ "ገዝቼሀለሁ! ከእንግዲህ ከነብስህ ከስጋህ ምረጥ" አሉት፡፡

ዲያቆኑ ወደ ዮዲት መራቸው ያ ሁሉ ከፅዮን የጠፋው ጌጣጌጥ ወርቃ ወርቅ እሷ ዘንድ ተገኘ፡፡

ቀሳውስት ወዲያቆናት ዮዲትን ያዟት፡፡ አንድ ጡትዋን ቆረጧትና ትተዋት ሄዱ፣ ቢገድሏት በተሻላቸው ነበረ፡፡ አባቷ ሲመለስ በደም ተበክላለች፡፡ ደግነቱ ደብተራው የእፅዋትን ምስጢር ያውቃል፡፡ ልጁን ከሞት አዳናት፡፡

ከዛ ወደ እናቷ አገር ወሰዷትና ለብዙ አመታት በቀልን አዘጋጁላቸው ለፅዮን ቀሳውስት። አቤት በቀል! የዮዲት ሰራዊት አክሱምን ወረረ። ህዝቡን ፈጁት። የአክሱምን የውሀ ጉድጓዶች አርባውንም ባፈር በድንጋይ ደፈኑዋቸው። አበቃላት አክሱም ሞተች። ታሪክና ሀይማኖት ሆና ቀረች። የንጉሱ ዘሮች ሁሉ ሲያልቁ አንድ ህፃን ልኡል ብቻ አመለጠ። ጥቂት ታማኝ መኳንንትና ወታደሮቻቸው ይህን ልኡል ይዘው ወደ ደቡብ አመለጡ። ዝዋይ ደሴት ለሰባት አመታት ከኖሩ በኋላ ወደ መንዝ ዘለቁ። ተመልሰው በምድረ ሀበሻ ለመንገስ ገና ሁለት መቶ አመት ይወስድባቸዋል። እንናገርላቸዋለን እግረ መንገዳችንን። አንባቢም እግረመንገዱን ይሰማ ይሆናል።

አስተዋይ አንባቢያን "ደብተራ ግራመስቀል ምን አይነት ሰው ነው?" ሳይሉ አልቀረም። ቅፅል ስሙ ነው፤ ቅኔ ነው። አንድም መላውን የአክሱም ደብተራ ወቀሲስ በጉባኤ ስላፋጠጣቸውና ግራ ስላጋባቸው። አንድም መስቀሉን በግራ እጁ ስለሚያሳልም። አንድም ሲፅፍ ይሁን ሌላ ስራ ሲሰራ በግራ እጁ በመሆኑ።

የመንበረ ሲኖዶስ ተሰበሰበና ግራኙን ደብተራ "ውግዘ ከመአርዮስ" ብለው ኮንነው ሲያበቁ ያው እንደተለመደው አንጀቱ በቂጡ ይጎለጎልና ይሞታል ነብሱም ቀጥታ ገሀነም ነው 'ምትገባው። እንደሌሎቹ ነብሳት ኢየሱስ ተመልሶ በህያዋንና በሙታን እስኪፈርድ አትቆይም የግራመስቀል ነብስ። እንዲያውም ገና እንደተፈጠረች ነበር ቀጥታ ገሀነብ ገብታ መቃጠል ይገባት የነበረው። ግራመስቀል ሆዬ ገና ሲኖዶሱ (ያ ሁሉ ደብተራና ቀሲስ ኤጲስ ቆጶስ ቆመስና ኧረ ስንቱ) ሊኮንኑት እንደጠሩት እሱ ተሽቀዳድሞ የማሰብ ካራቴ መታቸው ጠየቃቸውም እንዲህ ሲል

"ፈጣሪ በገዛ እጁ ጠፍጥፎ የገዛ እስትንፋሱን የገዛ ነብሱን ውስጡ የተነፈሰበት፥ ፍጡር አንድ አካሉ ወይ መላ አካሉ እርኩስ ሊሆን ይችላልን?"

"አይችልም" ተባለ

"ቀኝ እጀን የፈጠረው እሱ፣ ግራ እጀንም የፈጠረው እሱ፤ በግራ እጀ ጨብጬ ይኸው የምባርካችሁም እሱ ራሱ በተሰቀለበት መስቀል። በሉ ምን ትሆኑ" አለ ግራመስቀል በልቡ። ምን ይሁኑ! አብዛኛዎቹ እንዳፈጠጡ ጥቂቶቹም አፋቸውን እንደከፈቱ ቀሩ። እንደዚያቸው ደርቀው እንዲቀሩ እዚያው ትቷቸው ወጣ ደብተራ ግራመስቀል

እንዲህ አይነቱ ነበር የዮዲት አባት።

ለወጣት ደራሲያን! የዮዲትን አባት ያገራችን አፈ-ታሪክ አያውቀውም። እኔ ፈጥሬው ነው። አልፎ አልፎ ከራስህ(ሽ) ፈጥረህ(ሽ) ልጨምርበት ካልሆነማ ምኑን ቅርስህ(ሽ) ሆነው?

ነሀሴ 30 ቀን 1985

## ፪

ዮዲት ከአክሱም ጠፋች። አመታት አለፉ። የውቢቱን ጡት የቀረጡት ካህናትም በየተራ አልፈው ዲያቆናቱ ካህናት ሆኑ።

ዮዲት ወደ አገሯ ተመልሳ ይህን ሁሉ አመታት ያሳለፈችው የተቀረጠ ጡት ከመበቀል የላቀ፣ አገር አቀፍ የሆነ ወታደራዊ ጀብዱ ስታውጠነጥን፣ ስታቅድና ስታዘጋጅ ነበር ...

... ጊዜው ሲደርስ፣ ዮዲት ንግስት ከላስታ ተራራዎች ተነስታ አክሱም ላይ እንደ ምፅአት ወረደችባት! የሰራዊቷ ጠቅላይ አዛዥ ፍቅረኛዋና ባሏ መራ ተክለ ሀይማኖት ነበር (ሁለቱ የንጉስ ላሊበላ ቅድመ አያቶች ሆኑ ማለት ነው)

የአፄ ሰራዊት "ድባቅ ተመታ" አፄም እንደ አባቶቹ አገር ሰላም መስሎት "ተኝቶ ነበር" አምባ ወህኒ ላይ ይኖሩ የነበሩት ልኡካንም

ለዮዲት ተመቻችተውላት ቆዩ። ዘመዶቹ አቤዎች በየተራ ሲገዙ የራሱን እድል እየታዘበ የሸመገለው አንስቶ፣ ገና ወሀኒ ከገባ ሰባት አመት ከጥቂት ወራት የራሱን እድል እስከ ሆነው ድረስ አንድ ሳይቀር ተሰየፉ!

Shakespeare መድረክ ላይ አንዱ የእንግሊዝ ንጉስ ጨፈቃ ውጊያ ላይ በጠላቶቹ ተከቦ መድረሻ ሲያጣ፣ እንደሚገድሉት እያወቀም ቢሆን፣ የሰው ምኞት እስከ መጨረሻው ትንፋሽ ስለማይሞት፣ "A horse! A horse! My kingdom for a horse!" ይላል። ሌላው ምስኪን ንጉስ በንዲህ አይነት ቀውጢ ሰአት "Uneasy lies the head that wears a crown" ይላል።

የኛ አገር ከዚህ የተለየ ነው። አንዱ ንጉስ ሞቶ ሌላው ሲነግስ፣ በነጋሪት አዋጅ ያስነግራል፡-

"ስማ፣ ስማ፣ ላልሰማም አሰማ
የሞትነውም እኛ፣ ያለነውም እኛ
ገበሬም እረስ፣ ነጋዴም ነግድ..."

አርቆ አስተዋይ የዛጉዌ መንግስት፣ አክሱም ከጊዜ በኋላ እንደ ዋና ከተማ ምናልባት ለማንሰራራት እድል እንዳታገኝ ለመጠንቀቅ ያህል፣ አርባውን የውሀ ጉድጓዶችዋን ደፈነቻቸው - ሀያልዋ አክሱም ታፍና ሞተች...

ዮዲት የአክሱምን ሀውልቶች ልትሰባብራቸው ትችል ነበር። ሀውልቶቹን ለመቅረፅና ለማቆም ያስቻለ፣ በኋላም የላሊበላን አብያተ - ክርስትያን ተራራውን እየፈለፈሉ ለመቅረፅ ያበቃ ጥበብ (technology) በምድረ ሀበሻ ነበረላት። እሷ ግን አላማዋ የቀዳሚ ነገስታትን ታሪክ ለማጉደፍ ወይም ለማፍረስ ሳይሆን፣ የታሪክን አቅጣጫ ለመለወጥ ነበር።

አክሱም ፅዮንንም አክብራ "ጧፏን ሳትነካ" ሰራዊቷን ይዛ፣ ምድረ ሀበሻን ለማስተዳደር ወደ ሮሀዋ ተመለሰች። ያ የምታምንበት ታቦት

"በመናፍቅ እጅ" መሆኑ ቢከፋትም፣ ወረራዋ ፖለቲካዊ እንጂ ሀይማኖታዊ አልነበረም...

## ታሪካዊ መረጃ

ሰ) ... ያ ሁሉ ሲሆን፣ ከተሰየሩት ንጉሳውያን የአንዱ ህፃን ልጅ አለ፣ ለታሪክ ትረፍ ያለው። ይህን መአት ያየች የሰማች ልእልት እናቱ፣ ገና በአራት እግሩ "እየጋለበ" አዳራሹን አልፎ የሚወጣ እየመሰለው ሲስቅ፣ የእናት አንጀቷ በፍርሀት ይንዘፈዘፋል።

ይህን ጊዜ ታማኝ አገልጋዮቿ (ጎበዛዝት ናቸው) ይደርሱና "ልእልት ሆይ፣ ሰላም ወደሚገኝበት አገር አጅበንዎ እናመልጥ ዘንድ መልካም ፈቃድዎ ይሁን" አሉዋት።

ልእልት እናት ነብሷ ወደ መሀሪው አምላክ እልልል! እያለች ወደ ደቡብ ሽሽቱ ተጀመረ። ከአክሱም መአት ለማምለጥ አጋጣሚ ያገኙ ሁሉ እየተከተሉዋቸው፣ አውሬም ሽፍታም የማይደፍረው "ኢምንት ህዝብ" ሆነው ነበር ለጉዞው የተነሱት

ርቀቱም መድረሻውም አደጋውም በማይታወቀው መንገድ በተስፋ ሲራመዱ፣ የፅዮንዋ ማርያም እንደምትጠብቃቸው በመተማመን ነበር (ቀሳውስትም ዲያቆናትም አብረው መሄዳቸው አይቀርም ብለን እናምናለን)

በየመሸበት ከብርድም ከአደጋም የሚጠለሉበት ስፍራ መርጠው እያደሩ ጧት ጉዞው ሲቀጥል፣ ወንዶቹ አውሬ ለማደንም፣ ፍራፍሬ ለመሰብሰብም ግራና ቀኙን አካባቢ ያስሳሉ።

እንዲህ እየተጓዙም ቢሆን፣ እቱ አስገዳጅ - ጣፋጭ አስገዳጅ - ኑሮ መቀጠልዋ ስለማይቀር፣ ሴቶቹ የስራ ድርሻቸውን ለመወጣት ወይ ህፃናቱ ሲጫወቱ እየጠበቁ፣ ወይ ጨቅላቸውን እያጠቡ፣ ወይ ለመጀመሪያ ያረገዙችውን አይዞሽ እያሉ፣ ወይ ምግብ እያዘጋጁ፣ ወይ

እየፈተሉ፣ ወይ ሰፌድ ወንፊት አገልግል እየሰፉ ይውላሉ - ማገፍ ሲኖርባቸውም እያረፉ...

... ከሰባት አመት ጉዞ በኋላ ዝዋይ ሀይቅ ደረሱ። ዮዲት ጉዲት ባትመጣ ኖሮ፣ ያ የዚህ ረዥም ጉዞ ምክንያት የሆነው ልኡል ይህን ጊዜ ወደ አምባ ወህኒ ተወስዶ ከቤተ ዘመዶቹ ጋር ይተዋወቅ ነበር። ተጓዦቻችን በዝዋይ ዙርያ ሰባት አመት አረፉ (እየኖሩ! እየተባዙ!)

ከዚያ ለሁለት ተከፈሉ። አንዶቹ "ከዮዲት አደጋ በቂ ርቀናል፣ ዝዋይም ለሰባት አመት ምቹ አገር ሆኖልናል። እዚህ ነው የምንኖረው" አሉ፤ ለየምክንያታቸው - እድሜ እየገፉ በመሄዱ፣ ወይም ሁልጊዜ መንገዝ አገር መለወጥ ስለበዛባቸው፣ ወይም ከሚወዱት ታቦት መራቅ ስለሚሆንባቸው፣ ወይም ሌላ ሌላ። ሌሎቹ (ጉዞውን ለመቀጠል የተወሰኑቱ) እንዲህ አሉ "እኛ ከአክሱም የሸሸነው ለማንም የማይቀረውን ሞት ፈርተን አይደለም። የዚህ ልኡል የዘር ዘር ማረፍያ ብቻ ሳይሆን፣ ሀይል መገምቢያ ማንሰራርያ፣ ሰርተን እየኖርን አቅም ማጠንከሪያ የሚሆነን አገር ፍለጋ ነው የምንጓዘው። ማለት የአብዛኞዎቻችን ቀልብ (አቃቤ መልአክ) "አገሩ ይህ ነው" ሲለን፣ ደረስን ማለት ይሆናል።

በዝዋይ ቀሪዎቹ፣ የሰባት አመት ጉዞና የሰባት አመት ኑሮ የተጋሩዋቸው ወገኖችን ሸኙዋቸው። እነዚያ ለሚቀጥለው ጉዞ ነቀሉ...

... የት የት አገር፣ ለስንትና ስንት ወራት ወይ አመታት በመንገድ እያረፉ (እየተባዙ) እዚያ ሳያውቁት ሲጠራቸው የነበረ አገር ሲደርሱ፣

"ምን እዝ?" ተባባሉ፣ ይባላል በዘመኑ ግእዝ (ማን የሚሉት አገር ነው ይሄ? መባባላቸው ነበር)

ከዚያ ወዲህ አገረ መንዝ ተባለ ዛሬም ይባላል፣ ፀሀፊያችሁ ካልተሳሳተ በስተቀር።

በዚያ በለም ብርዳማ ደጋ መንዝ፣ አርቀ ዘመናት ዘልቆ አላሚዎቹ የአፄና የዘጋዎቹ ዝርያዎች ሲኖሩ ሲባዙ፣ ትውልድ ትውልድን ሲተካ፣

ከእለታት አንድ ቀን፣ ታዝሎ የሸሸው ልኡል ቀጥተኛ የልጅ ልጅ ልጅ... ተወለደ። ይኩኖ አምላክ (አምላክ ይሁነው!) ተባለ

ዮዲት ንግስት የአገረ ሀበሻን ዙፋን ከሰሎሞናዊው ስርወ መንግስት ነጥቃ የዛጉዌን ስርወ መንግስት በሮሀ ላሊበላ እንደተከለች አይነት፣ ይኩኖ አምላክም ዙፋኑን ዛጉዌዎች ሶስት መቶ(?) አመት ከተቀመጡበት በኋላ፣ በጦርነት ደም ተፋስሶ ነጥቆዋቸው ሳይሆን፣ በሰላማዊ ድርድር ማለት በዲፕሎማሲ ተረከባቸው (በቅርቡ በነአጤ ምኒልክ፣ በነአፄ ኃይለ ሥላሴ ያስደነቀን ያኮራን የአቢሲንያ ነገስት የዲፕሎማሲ ጥበብ በአፄ ይኩኖ አምላክ ተጀመረ - የአቡነ ተክለሀይማኖት ቡራኬ ታክሎበት!)

አፄ ይኩኖ አምላክ ለቀጣይ ምእራፍ ይቆይልንና አንባብያን ሆይ፣ የእስካሁኑ የዮዲት ንግስት ገድል የዛጉዌ ነገስት ታሪክ አንዱ ግማሽ ብቻ መሆኑን እያጤናችሁ፣ ቀሪው ግማሽ፣ የንጉስ ላሊበላ ተአምራት እነሆ - ስአሊለነ ቅድስት!

## ፫

ገና በአንድ አመቱ ከንግስት እናቱ ጋር ፀሀይ እየሞቀ ሲጫወቱ ቆይተው፣ እሱ ተዝናንቶ ጋደም ሲል፣ ለሆነ ጉዳይ ተነስታ ሄደች...

... ስትመለስ ልጇ እንደተጋደመ የንብ መንጋ "ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ" አልብሶታል፣ እና ልጁ በተጋደመበት እንቅልፉን ይለጥጣል!

"ላሊበላ!" አለች እናት (በዘመኑ የአገው ልሳን "ይነግሳል!" ማለት ነው) ትንቢት ሆነላትና ከዚያ በኋላ ስሙ ላሊበላ ተባለ።

ልጇ'ኮ በአስር አመት የሚቀድመው፣ ህጋዊ አልጋ ወራሽ የሆነ ወንድም አለው። ሰው ሲባል፣ እንኳን ዙፋንን ለሚያክል ስልጣንና ግርማ

ሞገስ ቀርቶ፣ ከዚያም በተጨማሪ ግርማ ሞገስ "ስሙ ከመቃብር በላይ" ውሎ፣ በተከታዮች ዘመናት ለመወሳቱ ቀርቶ፣ ለኩርማን ርስት እንኳ የናቱን ልጅ ይገድላል (አይታወቅብኝም እስከመሰለው ድረስ!)

አልጋ ወራሹ ሰዎችን እያረሳሳ ጊዜውን ጠብቆ፣ ላሊበላ ሶስት አመት (ሰባት አመት?) ሲሆነው መርዝ አጠጣው (አበላው?)

ላሊበላ ለሶስት ቀንና ሌት (አስራ አምስት ቀንና ሌት?) የሞተ ያህል ራሱን ስቶ ቆየ...

... ወደ ሰማይ ቤት ተወስዶ፣ መንግስተ ሰማያትን ጎብኝቶ፣ በመጨረሻም የላስታን ተራራዎች አስፈልፍሎ የሚያስራቸው አብያተ ክርስትያን እቅድና የግንባታቸው አቀማመጥ፣ እንዲሁም የተቀረው አስፈላጊ የድንጋይ ቀረፃ ጥበብ ዝርዝር እውቀት ተገለፀለት (በዚያ ጮርቃ እድሜ መሆኑን እንገነዘባለን)

"ከዛሬ ጀምሮ ምን መቼ የት ማድረግ እንዳለብህ ጊዜው ሲደርስ ሳታስበው ይታወቅሀል" ተባለ።

አስራ አራት አመት ሲሆነው (ወይስ ሰባት አመት?) ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ትረካችን መቼቱ በደምብ እንዲታየን፣ ስለመስቀል ጦርነቶች እንነግራችኋለን።

ይሄ ግን ረዘም ያለ ታሪካዊ መረጃ ስለሚያስፈልገው፣ የሚቀጥለው እትማችን ላይ "ታሪካዊ መረጃ (ረ)" በሚል ርእስ ይቀርብላችኋል።

ቸር ይግጠመን!

# ይኩኖ አምላክ

ዮዲት ጉዲት፣ አህመድ ግራኝ፣ ደርጉ - - - እነዚህ ለማጥፋት የተላኩ ናቸው ተብሎ ይታመናል ከኛ አገር። ዮዲት በሮሀ የተከለችው አገዋዊና ኦሪታዊ ስርወ መንግስት ወደ ኋላ ዘመን ክርስቲያን ሆኖ አሁን ዓለም የሚደነቅባቸውን የላሊበላን የአለት ፍልፍል ቤተክርስቲያኖች አሰራ።

ዳሩ ምን ይሆናል፣ የዛጉዌ ነገስታት ገና ሁለት መቶ አመታት እንደገዙ ሰለሞናዊያን ዙፋኑን መልሰው ነጠቁዋቸው። አነጣጠቁስ እንጣጠቅ መሰላችሁ? ፈጣሪ ራሱ የፃፉት አሪፍ ተውኔት ናት።

ቀዳማዊ ምኒልክ "አይጠፋም ምንጊዜም ይዳፈናል እንጂ" ሲል በገና የደረደረው ስለ ሰለሞናዊው ስርወ መንግስት ትንቢት ሲተነብይ ነው ልንል እንችላለን ከፈለግን። የዘመኑ እረኞችም እንደልማዳቸው ይህንኑ ትንቢት ሲዘፍኑት "ዳቦዬን መልስልኝ ቂጣህን ውሰድልኝ" ብለዋል ልንልም እንችላለን ካሰኘን።

--ከአክሱም ተነቅሎ እመንዝ ቀስ በቀስ ስር ሲሰድ ቆይቶ የነበረው ሰለሞናዊው ስርወ መንግስት ይኩኖ አምላክ የተባለ አንድ እድለኛ ልጅ ወለደ። ስሙ "አምላክ ይሁነው፣ ይቅናው" ማለት ነው። ቀዳማዊ ምኒልክ እንደልማዱ በገና ሲደረድር "ስምን መልአክ ያወጣዋል" ብሎ የተቀኘውም ስለይኩኖ አምላክ ትንቢት ሲናገር ነው ልንልም እንችላለን መልካም ፈቃዳችሁ ከሆነ-------

ይኩኖ አምላክ ጎረምሳ ሆኖ በላሊበላ ከተማ ቤተመንግስት ውስጥ የፈረሶች ጠባቂ ሆኖ (ወረገኑ ነው እንዴ የሚባለው?) ያገለግል ነበር። ንጉሱ ይኩኖ አምላክን ይጠላው ነበር። ውቃቢው ነግሮታል። እንዳው እንደ ወገቡ ቅማል ጥምድ አድርጎ ያዘው። (እና ንጉሱ ቅማል የሌለው እንደሆነ ምን ይጠበስ? ደሞስ ያ ንጉስ ቅማል እንደሌለው ማን ፈትሾ አረጋገጠ?) ያስርበዋል። ይኩኖ ራቡ እየሞረሞረው ፈረሶቹ የሚበሉትን የእህል ብጣሪ ሳይቀር ይጋራቸው ነበር። "ሆድ ይፍጀው እንጂ" አለ ይኩኖ አምላክ አውቆ ይሁን ሳያውቅ ቅኔ እየተናገረ። የቅኔው ፍቺ ለመሆኑ ግን ለኛ ግልፅ አይደለም።

አንድ ለሊት ንጉሱ ከበድ ያሉ የአገር ጉዳዮችን ሲያወጣ ሲያወርድ እንቅልፍ እምቢ ብሎት ነበር (ንጉስ እንቅልፍን አያዝምና እንቅልፍ ንጉስን ያዛል እንጂ። ዝኒ ከማሁ ለሞት እንዲል መፅሀፉ ካሰኘውና ከፈለገ። እና የሚያነበው ካገኘ። ሼክስፒርም "ዘውድ የደፋ ራስ መኝታው አይመቸውም" ብሏል የማይለው የለውምና።)

ንጉስ እንደዚህ በንጉሳዊ ስነ ስርአት እንቅልፍ እያጣ እያለ ዶሮ ጮኸ ሙሹ ተራ ኩኩሉ?! "የኔን ራስ የበላ ይነግሳል!?" አለና ሸለለ 'ንጂ። ይኸው! ከንግዲህማ ንጉሱና እንቅልፍ ተፋቱ። እስቲ ይህ ጉደኛ ዶሮ ይደግማት እንደሁ አያለሁ አለ፤ እሰማለሁ ማለቱ ነበር። ንጉስ መግዛት እንጂ ሰዋስው ማወቅ አይኖርበትም ካልፈለገ። ለማንኛውም ዶሮው ያንኑ መልእክት ሲደጋግም አደረ። "የኔን ራስ የበላ ይነግሳል!"

ሲነጋ ንጉስ ሆዬ ወጥ ቤቱን ያስጠራና "ለምሳ አውራ ዶሮውን አረጂልን" ይላታል ታርዳለች። እና ጭንቅላቱን ቆርጣ ወደ ውጭ ትጥለዋለች።

(ምናልባት ከዚያ በፊት የዶሮ ጭንቅላት አይበላም ነበር ይሆን?) እና ንጉሱ በመገረሙም እንቅልፍ በማጣቱም ራሱ ደንዞ፣ እንጎሉ ፈዞ የዶሮ ራስ እንደማይበላና ራሱንም አብስይልኝ ለማለት ትዝ አላለውም።

ለማንኛውም ምስኪን እድለኛ ይኩኖ አምላክ ረሀቡን እያስታመመ በዚያ ሲያልፍ የተጣለውን የዶሮ ራስ ከመሬት ያገኛል። "እቺን ይወዳል

ይኩኖ!" ይልና ወስዶ ጠብሶ ቁርጥምጥም አርጎ ዋጥ፣ ስልቅጥ እነሆ በረከት!

በንጉስ ማእድ ለምሳ የዶሮ መረቅ ሻሽ በመሰለ ስስ የጤፍ እንጀራ ተበልቶ አብቅቶ የምድረ ሀበሻ ጥርስ ስጋ ለመብላት ስትሾል ብልቶቹ ከድስት አንድ በአንድ ወጡ። ንጉሱ ቢያዩ ቢያዩ ጭንቅላት የለም።

"ራሱንስ አንቺ?" ተባለች ወጥ ቤት

"እሱንማ ጣልኩት። አይበላም ብዬ ነው። እኛ አገር አንበላውም።"

"በይ ቶሎ ሂጂና ከጣልሽበት ፈልገሽ አምጪ ስጋሽን ለጅብ ሳልጥለው!"

ሄደች ፈለገች አጣች ተመለሰች እያለቀሰች።

ንጉስ አገልጋዮቹንና ባሮቹን ሰበሰበና "ከእናንተ መሀል እዚህ ቦታ የዶሮ ጭንቅላት ያገኘ አለ?" አላቸው።

ይኩኖ ሆዬ ጉዷን አላወቀች እጅ ነሳችና ራሷን አጋለጠች ያኔ ማጋለጥ የሚሉት ነገር ባይኖርም።

"ንጉስ ሆይ መልካም ፈቃድዎ ይሁንና እኔ ሎሌዎ አግኝቼው ክፉኛ ርቦኝ ስለነበር ጠብሼ በልቼዋለሁ። (ሆድ ክብርን ያስረሳልና ነው'ንጂ ባገሬ እንኳን ጭንቅላቷን ዶሮዋን ራስዋን አንበላትም - ስጋዋን ማለቱ። ኧረ እንዲያውም እኛ ዶሮ አናውቅም። ትል ምናምን የማይቀራት ቀፋፊ ፍጡር ብሎ እያሰበ ሊሆን ይችላል ከፈለገ)

"እርግጠኛ ነህ?" አሉ ንጉሱ

-- "ሆድ ለባሰው ጭንቅላት አታውሰው ነው ጃንሆይ" አለ ይኩኖ አምላክ አሁንም ሳያውቅ፣ ወይም አውቆ ጥልቀት ያለው ቅኔ እየተናገረ።

"ያዙት!" አሉ ንጉሱ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው። (በንዲህ አይነት ሁኔታ እንኳን ንጉስ ደሀ እሳት መልበስና እሳት መጉረስ ይኖርበታል ባህል ነዋ! ወግ ሊሆንም ይችላል ከፈለገ)

ወታደሮቹ ይዘው ምስኪን ይኩኖን እያዳፉ ወስደው ከገደል አፋፍ ወረወሩትና መዳፎቻቸውን ሶስት ሶስቴ አራግፈው ተመለሱ።

"አንድ ሀሳብ ረገፈ." አሉ ንጉሱ በጠሊቅ እየተንገፈገፉ። እፎይ! ግና ምን ይሆናል አንዳንድ አታክልት እፅዋትና ዛፎች አሉ፤ ሊበቅሉበት በማይችል የሚመስል ስፍራ የሚበቅሉ። መብቀሉንስ ይብቀሉ፣ ማን ዘራቸው ወይ ተከላቸው? የሚያስብሉ።

ይኩኖ የተወረወረበት ገደል ልሙጥነቱ ከደብረዳሞ ገደል አይለይም። እንዲያም ሆኖ ግን ምስኪኑ ይኩኖ ሰባት ሰኮንዶች ከነሰባት ለሊቶቻቸው ሲወድቅ ውሎ ሰንብቶ ከርሞ አይ መርዘሙ ሰባት ሰኮንድ ወደ መቀመቅ እየወረደ ከሆነ በተለይ ለሊቶቹ መርዘማቸው። "እንዳ'ዳል መጫኛ ለሊቱ መርዘሙ" ተብሎ የተዘፈነውም ለዚህ ነው። ሰኮንድ ለሊት አለው ወይ? ቀኑ ለሊት ካለው የቀኑ ቁራጭ የሆነው ሰኮንድ እንዴት የራሱ ለሊት አይኖረውም? የሰኮንድን ለሊት የሚያውቋት ግን፣ ወይ ብፁአን ናቸው፣ ወይ ከገደል አፋፍ የተወረወሩ ህቡአን ልኡላን ናቸው።

ህቡእ (ማለትም ድብቅ) ልኡል ይኩኖ አምላክ ከገደሉ አፋፍ እንደወረወሩት በልቡ "መንገዱ ረዘመ ረዘመ ረዘመ፣ ወደ አንቺ ስመጣ ልቤ እየደከመ" የሚለውን ዘፈን እየዘፈነ ሲወድቅ፣ ሰኮንዷ ነግታ ስትመሽ፣ ሲወድቅ ሰኮንዷ መሽታ ስትነጋ ሲወድቅ።

እገደሉ አንድ ስንጥቅ ውስጥ ይሁን አግድም ጉድጓድ ውስጥ የበቀለች የተባረከች የወይራ ዛፍ እቅፍ አታረገውም!?

"ሰኣሊለነ ቅድስት! ተመስገን ፈጣሪዬ ጠባቂዬ" ብሎ ጥቂት እንደተነፈሰ ማን ይመጣል? የገደል ዝንጀሮዎች፣ ወይ አስራ ሁለት፣ ወይ አርባ ሊሆኑ ይችላሉ። ወይ ሰባ። በየተራ እየተጠጉት ፀጉራቸውን እየነጨ፣ እየነጨ ረዥም ገመድ ገመደ። ዘጠና ዘጠኝ ክንድ ሊሆን ይችላል። ሁን አለው።

ይኩኖ አምላክም ዝንጀሮዎቹን አመስግኖ አሰናብቶ ሲያበቃ ገመዲቱን ከወይራው ግንድ ቅርንጫፍ ጋር አስሮ ወረደ ቀስ እያለ

እግሮቹ በገደሉ ደረት ላይ እጆቹ በገመዱ ላይ እኩል እየተራመዱ ወርዶ መሬት ሊደርስ ሰባት ክንድ ያህል ሲቀረው ገመዲቱ አለቀችበት።

እና? እናማ ዛፊቱ ከገደሉ ላይ ሆና ጎምበስ አለች። ይኩኖ እግሩ መሬት ነካ (ዛሬም ቢሆን ዛፊቱ እንዳጎነበሰች ትታያለች የሚያያት ካገኘች)

ይኩኖ ሆዬ ከዚህ የሮጠ "ያዘው! ያዘው!" እያሉ ክትክታ ዱላ የያዙ ጎበዛዝት አንድ ወንዝ አቋረጡና እየሮጡ እየጮኹ እፊታቸው ካለው ጫካ ሊደርሱ ጥቂት እንደቀራቸው ከጫካው ውስጥ አራት አንበሳዎች ከነጎፈራቸው ከነመደነግፅ ግርማ ሞገሳቸው ከነጩኸታቸው ብቅ አሉ። ጎበዛዝት ቀኝ ኋላ ዞረው ሩጫቸውን ቀጠሉ "እግሬ አውጪኝ" የሚባለውም ከዚያ ወዲህ ነው ልንል እንችላለን የሚሰማን ካገኘን።

አንበሳዎቹ ይኩኖ አምላክን ከላስታ ያጀቡት ትግራይ ድምበር አድርሰውት ተመለሱ "ወርእዩ አርባዕቱ አናብስት ወፈረሁ ፈድፋድ" እንዲል መፅሀፉ። "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለውንም የሰለሞናዊያኑን ነገስታት መፈክር ያስታውሷል።

መስከረም 9 ቀን 1986

## ፬

በላሊበላ ቤተ መንግስት ጭንቀት ነገሰበት። ንጉሱ አዋቂዎችን አስጠርቶ የሆነውን ነገራቸውና ምክር አምጡ አላቸው። ምንም ሊመክሩት ወይም ሊያስረዱት አልቻሉም። ብቻ አንድ የበቁ መነኩሴ በቅርቡ ወደ ላሊበላ መጥተዋል እሳቸውን ቢያማክሩ ይሻላል ንጉስ ሆይ፣ አቡነ ተክለሀይማኖት ይባላሉ አሉት። አስጠርቶ ነገራቸው ችግሩን። ምናልባት ትርጉሙ ቢገለፅልኝ ብለው ሱባኤ ገቡ ማለትም ሰባት ቀን

ለብቻ ተገልለው እፍኝ ቆሎ ብቻ ለራት እየበሉና ውሀ እየጠጡ ፀለዩ ሰገዱ፡፡ ያን ጊዜ አቡነ ተክልዬ ገና ወደ ደብረ ሊባኖስ አልሄዱም እግራቸውም ሁለቱም ደህና ነው፡፡ ክንፍም ገና አላቆጠቆጡም፡፡ ከሱባኤ ሲወጡ ለንጉሱ ነገሩት "አይዞህ እጣህን ተቀበል፡፡ ይኩኖ አምላክ ይነግ ሳል፡፡ ስለዚህ ያንተ ዘር አይነግስም፡፡ አንተ ግን ከዙፋንህ አትወርድም፡፡"

"አይ! እድሌ" አሉ ንጉሱ፡፡

"አይ! እድሌ" አለ ይኩኖ አምላክ በሌላ ዜማ ሰራዊቱን እየሰበሰበ፡፡

የሰለሞናዊው ስርወ መንግስታችን ሰራዊትና የዛጉዌ ስርወ መንግስታችን ሰራዊት ተፋጠጡ፡፡ ምድረ ሀበሻ በኋላ ልማድ እንዳደረገችው በጎበዝ ደም ልትጥለቀለቅ ሆነ፡፡ ምናልባት ይሄ ጊዜ ታይቶ ይሆናል የንጉስ ሰለሞን አባት "ኢትዮጵያ ታበፅህ እደዊሀ ሀበ እግዚአብሄር" ብሎ ትንቢት የተናገረው፡፡

መፍሰስ ሳይኖርበት የንፁሀን ደም ለምን ይፍሰስ? አሉና ሱባኤ ገቡ፡፡ ከሱባኤው ሲወጡ ቀጥታ ወደ ይኩኖ አምላክ ሄዱ፡፡ በእግር ነዋ ያውም! የበቃ መነኩሴ በካዲላክም አይሄድ፤ ካዲላክ አለማዊ ምቾት በመሆኑ፡፡ በፈረስም አይሄድ የእግዚአብሄር ፍጡር ነፃ መሆን አለበት፣ እኔ ነፃ ላወጣው አልቻል እንጂ ቢያንስ በባርነቱ ላይ እኔ አልጨምርበት የቅዱስ እግዚአብሄር ፍጡራን ነን እኔም በቅሎውም፡፡ እሱም በተፈጠረለት አራት እግር ይሂድ፤ እኔም በተሰጠኝ ሁለት እግር እሄዳለሁ፡፡ ለምን እወጣበታለሁ? እሱ ልውጣብህ ቢለኝ እሽ እለዋለሁ እንዴ? እንግዲያስ?

ይኸን ጊዜ "እንዴ አባ" ብሎ ጠይቋቸው ሊሆን ይችላል አንዱ የኛ ቢጤ "ፈረስ ግመል በቅሎ መቀመጥ አህያ መጫን ሀጢአት ነው የሚሉ?"

"በአለማውያን ይፈቀድ ይሆናል ምናልባት፡፡ አለም በቃኝ ስጋዬን ጎድቼ ነብሴን እጠቅማለሁ ብሎ ለመነነ መነኩሴ ግን እንዴት ሊፈቀድ ይችላል?"

አቡነ ተክልዩ ሰተት ብለው ወደ ይኩኖ አምላክ ሄዱ። በእግር።

"ልኡል ሆይ" አሉ ለጥ ብለው እጅ ከነሱት በኋላ "ይደለዋ ክብር ለወለደ ንጉስ" አላለምን መፅሀፉ? "አንተ የማታውቀው እኔና ንጉሱ 'ምናውቀው ምስጢር አለ። መልካም ፈቃድህ ይሁንና አድምጠኝ" ብለው አስፈቅደው ቀጠሉ። "ያ ጭንቅላቱን ጠብሰህ የበላኸው ዶሮ ለሲቱን የኔን ራስ የበላ ይነግሳል የሚል ትንቢት ሲናገር አድሮ ነበር የታረደው፤ ነቢያት ይታረዳሉ የታወቀ ነው። አንተ እንደምትነግስ እኔም ንጉሱም እናውቃለን። አሁን አንተም አወቅክ። ስለዚህ ጦርነት ተዋግታችሁ ድል አድርገኸው ብትነግስ የሚፈሰው ደም ባንተ ላይ ነው። በክርስቲያን ንፁህ ደም ዋኝተህ የምትደርስበት ዙፋን የፀና አይሆንም ልክ ነኝ?"

"ልክ ነዎት አባ ምን ይመክሩኛል?"

"እሱ ሲሞት አንተ አልጋውን ትወርሳለህ ደሞ እድሜውን እንዲያሳጥርልህ አትመኝ። ጊዜህን ጠብቀህ እግዚአብሄር ባለልህ ቀን ስትነግስ መንግስትህ ንፁህ በመሆኑ እግዚአብሄር ደስ ይለዋል። የልጅ ልጆችህም ለብዙ ትውልድ በዚች በቅድስት አገር ይነግሳሉ።"

"መልካም መክረውኛል አባ ሆይ! ለወደፊቱም ምክርዎ አይለየኝ። ንጉሱንስ ምን ይመክሯቸዋል?"

"አነጋግሬው ስመለስ ልንገርህ መልካም ፈቃድህ ቢሆን ልኡል ሆይ!"

"እርስዎ እንዳሉ"

አቡነ ተክልዩ ከይኩኖ ድንኳን ወጥተው (ድንኳን ጥሎ ነበር?) ሰተት ብለው ወደ ንጉሱ ቤተመንግስት ሄዱ። በእግር። "ንጉስ ሆይ" አሉት "መልካም ፈቃድህ ይሁንና የምናገረው ቁምነገር አለኝ።"

"ይቀመጡ ይንገሩን"

"የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ ይኩኖ አምላክ ነው ካንተ ቀጥሎ የሚነግሰው፤ መንገሱን ታውቃለህ። ስለዚህ በናንተ ምክንያት ንፁህ ደም ከሚፈስ የእግዚአብሄርን ነገር ስሙና ላስታርቃችሁ።"

"እንዴት አርገው?"

"አንተ እንደነገስክ ቆይ እስከ እለተ ቀንህ። አምላክ ወደ አባቶችህ ሲጠራህ አልጋህን ይኩኖ አምላክ ይወርሳል።"

"የኔስ ልጅ?"

"ያባቱን አገር ዋግን ይወርሳል። ዋግ ስዩም የሚባል ልዩ ቀሚስ ይለብሳል። በንጉስ ቀኝ እጅ ይቀመጣል። በክብርና በማእረግ ከአፄ ቀጥሎ ዋግ ስዩም ይሆናል። ለመጪዎቹ ትውልዶች - ደሞ እግዚአብሄር በጥበቡ ሌላ ታሪክ እስኪሰራ ድረስ።"

ንጉሱ አሰበበትና የአቡነ ተክልዬን ምክር ተቀበለ። ንጉሱንና ይኩኖን አቡነ ተክልዬ ታቦት ፊት አማማሏቸው በመሀላቸው ፀኑ። እንዲህ አድርገው አቡነ ተክልዬ የክርስቲያን ደም ሳይፈስ ስርወ መንግስት በሰላም እንዲወራረስ አስቻሉ። ይህ የሆነው በሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ሶስት አመተ ምህረት ነበረ። ቀዳማዊ ሀይለስላሴ አፄ በነበሩበት በኛ ዘመን ወደኋላ ጊዜ እስከ መስከረም ሁለት አስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት አመተምህረት ድረስ ዋግ ስዩም የነበሩት የዛጉዌ ዘር ዋግሹም ወሰነ ሀይሉ ይባሉ ነበር።

በነገራችን ላይ አፄ ይኩኖ አምላክ የምድረ ሀበሻን ሲሶ ለቤተክርስቲያን ሰጡ ተከታዮችም አፄዎች የይኩኖ አምላክን ስጦታ እንዳፀደቁት ኖሩ።

(ለወጣት ደራስያን - ተስተውሎ ይሆን ወይ እንዴ ምናልባት? ንጉሱ ስሙ አልተጠራም። ይኩኖ ነው ስም ያለው። ያኛውም ነበረው መቸስ። እንዲያውም ታሪክ ውስጥ ተፍፃሜተ መንግስት ይትባረክ ሊሆን ይችላል። እፊ ታሪክ ውስጥ ግን ንጉስ ካልክ ያው አንድ ንጉስ ብቻ ስለሆነ ያለው እንደተፀውኦ ስም ያገለግላል። ከዚህም ጋር ድራማው ውስጥ ንጉሱ ተሸናፊ ስለሆነ ስም የለውም። ይኩኖ ግን)…..

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ይመጣል፤ ስለሞናዊው ስርወ-መንግስታችን ከዚህ በፊት ጠፋ ተብሎ ከታመነ በኋላ ሁለት መቶ አመታት ሲያርፍና

ሲጎለብት ቆይቶ በይኩኖ አምላክ መልክ ብቅ አለ ለሰባት መቶ ሶስት አመት እቺን ቅድስት አገር ከገዛ በኂላ አሁን በዘመናችን ከአልጋው ወርዷል። በሚመጡት አመታትና ዘመናት ተመልሶ እንደገና ዘውድ. ይደፋ ይሆን? ማን ያውቃል አዋቂዎች የተባሉት እንኳ ምናልባት ትላንትን ያውቁት ይሆናል እንጂ ነገን አውቃታለሁ የሚል ግን አዋቂ አይባልም ድንቄም አዋቂ! ነው የሚባለው

መስከረም 16 ቀን 1986

# አቡዬ ጣዲቁ እና ክርስቶስ ሰምራ

እኛ የተባረክን የምድረ ሀበሻ ሰዎች መንፈሳዊ ብልፅግናችን የሚመነጨው የሚመጣውም ከኢየሩሳሌም ብቻ አይደለም። ከግብፅም ነው። ከእስክንድርያ መንበረ ማርቆስ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጳጳሶቻችን ሁሉ ግብፃውያን ነበሩ። በዚህ በኩል ደግሞ በምፅዋና በሀረር አድርጎ የመጣልን ከመካ የመነጨው መንፈሳዊ ሀብታችን አለ።

በአምስት አቦ ናቸው ያን እለት ‹‹ስለ አቡዬ ጣዲቁ!›› ተብሎ ይለመናል። ‹‹አቡዬ ጣዲቁ ገደል እንደ አከርማ የሚሰነጥቁ›› ተብሎም ይገጠማል። ግጥሙን ከሰማ በምናብ የሚታየኝ እኝህ የዝቋላው አቦ ገደሉን በክርን ሲሰነጥቁት ነበር። እሳቸው ግን ይህን መከረኛ ገደል የሚሰነጥቁት በመብረቅ ሳይሆን አይቀርም። በክርንም ይበሉት በመብረቅ ይህ የፈረደበት ገደል በቀን አስር ጊዜ ሲሰነጠቅ ይኖራታል እድሜ ልኩን።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን በስእል ስናያቸው ፀጉር ለብሰው እጃቸውን ዘርግተው ቆመው አንድ አይናቸውን ወፍ ስትጠጣ በቀኛቸው አራት አንበሶች በግራቸው አራት ነብሮች አጅበዋቸው ነው። ምናልባት ስናያቸው እንዳንሳሳት ብሎ ሳይሆን አይቀርም ሰአሊው የዱር እንስሳቱ አጠገብ ‹‹አናብስት›› እና ‹‹አናብርት›› ብሎ ፅፎባቸዋል። አቡዩ ጢማቸው መሬት ደርሷል።

አቦ የተወለዱት ግብፅ ነው። አርብ እለት ሳይሆን አይቀርም፤ የተወለደውን ህፃን አጣጥበው - ልዩ ህፃን ነው ፀጉር የለበሰ - ለናቱ ሰጧት። እናት ጡት አውጥታ ስትሰጠው ህፃኑ ‹‹በስመ-አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ! በፆሙ?›› ብሎ ተናገረና አልጠባም አለ በነጋታውም አልጠባ፤ እንዲያውም ጡት የሚሉት ነገር አልጠባም። እህልም በልተው አያውቁ አቡዬ ጣዲቁ።

አቡዬ ጣዲቁ ሲያድጉ አባይን ወንዝ ተከትለው ሳይሆን አይቀርም ወደ ጎጃም መጡ። እዚያ ቢያዩ አገሩን አጋንንትና ርኩሳን መናፍስት ይፈነጩበታል። በጣም አዘኑ ሱባኤ ገቡ። ተራ ሱባኤ አልነበረም። ከትልቅ ዛፍ ላይ እግራቸውን በሀረግ ታስረው ቁልቁል ተንጠለጠሉ። ሀምሳ አመት ሙሉ ተንጠልጥለው ፀሎት ሲያደርሱ ኖሩ። በመጨረሻም ኢየሱስ በራእይ ታያቸውና ‹‹ምን ላድርግልህ?›› አላቸው። ‹‹ይህን ሁሉ አጋንንትና ርኩሳን መናፍስት ከጎጃም ጠራርገህ አስወጣልኝ›› አሉት። ‹‹በል በቃህ ውረድ›› አላቸውና ጎጃምን አፀዳት ክበር ተመስገን! ብለው አመስግነውት ሲያበቁ አባይን ተሻግረው ወደ ዝቋላ መጡ። ቢያዩ ጊዜ ጎጃም ፀዳች እንጂ የተቀረው ምድረ ሀበሻ የአጋንንትና የርኩሳን መናፍስት መፈንጫ ነው። በጣሙን አዘኑ ሱባኤ ገቡ። ደግሞ ከትልቅ ዛፍ ላይ እግራቸውን በሀረግ ታስረው ቁልቁል ተንጠለጠሉ። ሌላ ሀምሳ አመት ሙሉ ቁልቁል ተንጠልጥለው ፀሎት አደረሱ። በመጨረሻም ኢየሱስ በራእይ ታያቸውና ‹‹ምን ልፈፅምልህ?›› አላቸው ‹‹ይህንን አጋንንትና ርኩሳን መናፍስት ከምድረ ኢትዮጵያ ጠራርገህ አስወጣልኝ›› አሉት።

"አንተ ራስህ አታስወጣቸውም?" አላቸው "በምን አቅሜ?" ሲሉት "በዚህ" አለና መብረቁን ሰጣቸው። እነሆ በረከት! አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በተሰጣቸው መብረቅ አጋንንቱንና ርኩስ መናፍስቱን እያንጋጉ ከአገር አስወጧቸው።

አንደኛውን ጋኔን ግን እዚህ ቢሾፍቱ አይተውት መብረቃቸውን ቢወረውሩበት አንድ እግሩን ቆረጡት።

አቡዬ ጣዲቁ አዘነለትና "በል እሱ ሀይቅ ውስጥ ኑር" አሉት። ቆሪጥ ዘለለና ሆራ ሀይቅ ውስጥ ጥልቅ! ቋሚ አድራሻው መሆኑን የሚያውቁና ቅንድቡ የሚገጥም ቀይ ብላቴና አርደው የሚገብሩለት የተለያዩ ሰዎች ነበሩ እየተባለ ይወራል። አሁንስ ሊኖሩ አይችሉምን?

አቡዬ እጅግ ርህሩህ ነበሩ። አራዊት እንኳን አይሸሿቸውም ነበር። አናብስትና አናብርት ያጅቡዋቸው ነበር። አንድ ቀን አቡዬ ጣዲቁ አንዲት ወፍ አገኙ በውሀ ጥም ልትሞት የደረሰች። ውሀ ሊያጠጧት ዙሪያውን ቢመለከቱ ምንም ውሀ የለም ታዲያ ውሀ የጠፋ እንደሆን የእግዜር ፍጡር ይሞታል እንዴ? አይሞትም። አቡዬ ጣዲቁ ለወፊቱ አንድ አይናቸውን አጠጧትና ከሞት ተረፈች።

ከእለታት አንድ ቀን - ያ መምጣቱ የማይቀር ቀን - መልአከ ሞት መጣና አቡዬ ጣዲቁን እንሂድ አላቸው

"ሂድ ከዚህ ጥፋ እኔ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የምሞት አይደለሁም።"

"እምጣው ተብዬ ታዝገርለሁ"

"የራስህ ጉዳይ!"

ኦኦ! ሰውየው ዋዛ 'ማይደሉ። መልአከ ሞት ፈርቶ ትቷቸው ወደ ሰማይ ተመለሰና እምቢ አልመጣም አሉኝ ብሎ አመለከተ።

ኢየሱስ ራሱ ወረደና "ይበቃሀል እንሂድ!" አላቸው።

"አልሄድም"

"አዳም በለሲቱን በልቷልና ሞትም ተፈርዶበታልና መሞት አለብህ"

"እኔ በለስ አልበላሁም"

"እኔ እንኳ የሞት ፅዋ አልቀረልኝም"

"የማሪያም ልጅ አንተ ለምክንያት ሞተሀል። እኔ ግን የምሞትበት ምንም ምክንያት የለም። አልገደልኩ። እህል 'ንኳ በልቼ አላውቅም። ኸረ

የእናቴንም ጡት አልጠባሁም፡፡ ታዲያ ለምን እሞታለሁ? ሞት አይገባኝም"

አቡዬ ጣዲቁ በዚህ ሙግት ሲረቱ ለትንሽ!! ዳሩ ምን ይሆናል ያ ከይሲ መጣ ከሲኦል አንዲት ዝምብ አስከትሎ፡፡ የምን ዝምብ? አንድ ቀን አቡዬ ጣዲቁ ሳያውቁ ልብ ሳይሉ በጭራቸው እሽ! ሲሉ የገደሏት ዝምብ፡፡

"እንግዲህማ ምን አረጋለሁ? ልሙተው'ንጂ" አሉ አቡዬ ጣዲቁ በዝምቢቱ ተረቱ፡፡

አይ ዝምብ! ድሮውንስ የሰይጣን ፍጡር አይደለች? እግዚአብሄር የፈጠረውን ንብ ሲያይ ጊዜ እኔም ንብ ልፍጠር እስቲ ብሎ ፈጠራት ይላሉ፡፡ እንግዲህ ማንም ይፍጠራት ማንም ባይፈጥራት ይሻል ነበር፡፡ ብዙ ነገሮች አሉ ባይፈጠሩ ይሻል የነበረ፡፡

መንፈሳዊ ብልፅግናችንን ካሳደጉት መሀል ከአቡዬ ጣዲቁ ቀጥላ ክርስቶስ ሰምራ ደስ ትለኛለች፡፡ አለማዊውን ጎዳናም ተጉዛዋለች፡፡ ቀጭንዋንም መንፈሳዊ መንገድ ሄዳለች፡፡ ክርስቶስ ሰምራ አለሟን ያየች ባለፀጋ ሴት ነበረች አስራ ሁለት ልጆች ወልዳ የዳረች፡፡ ብታየው ብትመረምረው ጊዜ ታዲያ ይህ አለም ባዶ ነው፡፡ እድሜያችን ደሞ የአንድ ሻማ እድሜ ናት፡፡ አንዴ በርተን የምንጠፋ ነን በስጋነታችን፡፡ ነብሳችን ግን ዘላለማዊት ናት፡፡

ክርስቶስ ሰምራ ቤተዘመዷን ተሰናብታ መነነች፡፡ ለነብስዋ አደረች፡፡ ጊዜው ሲደርስ አንድ ቀን ኢየሱስ በራእይ መጣና "ክርስቶስ ሰምራ ሆይ! መንገድሽ እጅግ አስደስቶኛልና ምን ላድርግልሽ?" አላት

"ለዲያብሎስ ወንጌልህን እንድሰብክለት ፍቀድልኝ" አለችው፡፡

"ይሰማኛል ብለሽ?"

"ልሞክር"

"በይ እሺ ሞክሪ"

ክርስቶስ ሰምራ ወደ ሲኦል አፋፍ ሄደችና ቁልቁል ተጣራች "ዲያብሎስዬ የእኔ ሳጥናኤል! ስማኝ እስቲ!"

ሰይጣንም እንዴ ግራ ሆኗልና በንዴት እያጓራ ሽቅብ በረረ፡፡ ክርስቶስ ሰምራን አፈፍ አደረገና ቁልቁል ወረወራት፡፡ ከዚያ ተመልሳ ስትወጣ በልብሷ እጥፋቶች ተቆናጠው እልፍ እመአእላፍ ነብሳት ከሲኦል ወጡ፡፡ ወስዳ ወደገነት አደረሰቻቸው፡፡

ኢየሱስም "ክርስቶስ ሰምራ ሆይ!" አላት "ስለ መልካም ሙከራሽ ዛሬ ከሲኦል ያመጣሻቸውን ነብሳት ቁጥር በቀን በቀን አንድ ጊዜ ከሲኦል እያወጣሽ ወደ ገነት እንድትወስጂ ስልጣን ሰጥቼሻለሁ፡፡ እስከወዲያኛው፡፡ እናቴም በመንግስተ ሰማያት በቀኝዋ እንድትቀመጪ ጋብዛሻለች፡፡"

መስከረም 23 ቀን 1986

# ሬሙስና ሮሙለስ

እንደ እኔ አገር ቤት ለተወለደ ሰው እንደ ከተማ አስገራሚ ነገር የለም ቢኖርም፡፡ እና አንዳንድ የታደለ ባላገር ሲደናበር ወይም እግረ መንገዱን አንዳንድ ከተማዎችን ይጎበኛል፡፡ እኛ ግን እንደዚያ ብዙ ድንበሮችን እንደ ዘለቀውና ምእራብንና ምስራቅን እንዳስተዋወቃቸው አልተጓዝንም፡፡ እንደ ዝነኛው ማርኮፖሎ በእግር፣ በፈረስ፣ በሰረገላና በመርከብ አልተጓዝንም፡፡ በቆላ ሀሩር፣ በደጋ ቁር፣ በራብ በጥም መከራችንን አይተን አይደለም ከተማዎቹን 'ምንሄድባቸው እነሱ ናቸው የሚመጡልን፡፡ እድሜ ለማርኮ ፖሎ እና ለደፋርና አስተዋይ መሰሎቹ ተጓዦች፡፡ በየፊናቸውና እንደየተሰጣቸው እስከመጨረሻው ሄደው የምድሪቱንም የሰማይቱንም አይተው ተመልሰው ነግረውናል፡፡ እዚች አዲስ አበባችን ቁጭ ብለን እነሱ ያዩትና የሰሙትን ሲነግሩን መኮምኮም፡፡

ባልደረቦቻችን ሀረር ደርሰው ተመልሰው ስለአባድር ከተማ እስኪነግሩን ድረስ ወደ ሮማ ወደ ዘላለማዊቱ ከተማ...ባህር ተሻግረን በዘመናት ወደኋላ የትየለሌ!!...

ጥንት፣ ጥንት፣ ጥንት፤ አሁን ኢጣሊያ እየተባለች በምትጠራው አገር ታይበር ወንዝ አጠገብ በምትገኝ አንዲት ከተማ ንጉሱ ታናሽ እህቱ ተቀናቃኝ ልጅ እንዳትወልድበት ለመጠንቀቅ ያህል የአማልክቱ የቬስታ ድንግል አገልጋይ እንድትሆን አስገደዳት (ኧረ! እንኳን አልገደላት) አይ ደጉ ዘመን!

እዚያው በድንግልናዋ ፀንታ ቤተመቅደሱን ስታገለግል ሳለች አረገዘችና መንታ ወንዶች ወለደች፡፡ ከሰው ወልዳ ቢሆን ኖሮ የቬስታን ድንግል አርክሳለችና በሞት በተቀጣች፡፡ እሷ ግን የወለደችው ማርስ ከተባለው የጦር አምላክ ሆነ፡፡ ነው አለች እንግዲህ ድርቅ ብላ፡፡ ይህ እንግዲህ አስታውሱ በደጉ ዘመን ነው፡፡ ያኔ አማልክቱ ወንዶቹም ሴቶቹም ወደ ምድር ወርደው ዞር ዞር ሲሉ ቁመናው ደስ የሚላቸውን የተቃራኒ ፆታ የሆነ ስጋ የለበሰ ሰው ያጋጠማቸው እንደሆነ እና ያሰኛቸው እንደሆነ አልጋም ላይ ይሁን ሳር ላይ ተጋድመው፣ አጋድመው እነሆ በረከት! ብለው መንገዳቸውን ይቀጥሉ ነበር፡፡

ነጣቂው ንጉስ መንትያዎቹን ህፃናት በአንዲት ሳጥን ጀልባ አካል ተጨምረው ታይበር ወንዝ ውስጥ እንዲጣሉ አደረገ፡፡

ወንዙ ሳጥን ጀልባይቱን እያላተመ ሲወስድ ካሁን አሁን ሰጠሙ እያለ እየጓጓ ከአይኑ እስኪጠፉ ከሸኛቸው በኋላ መዳፎቹን እያራገፈ "አንድ ሀሳብ ረገፈ" አለና ወደ ጉዳዩ ሄደ፡፡

ታይበር ሆዬ በዚያን ዘመን ምኑ ሞኝ ነው "ሆ! እኔ እብድ ነኝ የማርስን ልጅ እምበላ? ይሄ ነጃሳ ንጉስ ግን ባልጠነቀቅ ኖሮ ከማርስ ከወዳጁ ጋር ሊያጣላኝ ነበር" ያኔ ዘላለማዊ በመሆኑ ራሱም እንደ አምላክ ይቆጠር የነበረው ታይበር ወንዝ እነዚያኑ ህፃናት ለዚያ ለነጃሳ መጥፊያ ይሆኑ ዘንድ እና እግረ መንገዳቸውን ታሪካዊቱን ዘላለማዊቱን ከተማ ይቆረቁሩ ዘንድ በኋላ ሮማ ልትበቀልባቸው የተመረጡት ሰባት ኮረብታዎች አገር ሲደርሱ በለስ ግንድ ስር ትቷቸው ጉዞውን ቀጠለ፡፡

ማንም ጠያቂ በሌለበት ጊዜና ቦታ "እነዚህ ህፃናት እንግዲህ የምታጠባቸው ሴት ታጋጥማቸዋለች? ወይስ የራበው አውሬ ይጎርሳቸዋል?" የሚል ጥያቄ ሾከክ እያለ ያልፋል፡፡

ተኩላይቱ ደሞ መጣች፤ ቆም ብላ ዙሪያውን እየተገላመጠች እያነፈነፈች መሬት መሬቱን በማይሳሳተው አፍንጫዋ እያሰሰች፡፡

"እናስ ጎረሰቻቸው?" እያለ አንዱ ጅል ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል

ብትጎርሳቸውማ ኖሮ መች ታሪክ ይሰሩ ነበር? ለመሆኑ አስበህ ታውቃለህ? ስንትና ስንት አራዊት ስንትና ስንት ህፃናትን ጎርሷል'ኮ እግዜር ይቅር ይበለንና፡፡ ስለነሱ ሰምተህስ አውርተህስ ታውቃለህ?

"ለምን አልጎረሰቻቸውም ግን?"

አንዳንድ ፋራ ጥያቄ በካራቴ ካገላበጡት አራዳ ጥያቄ ይወጣዋል እንዳሁኑ፡፡

መልስ - አንድም ቀደም ሲል በለስ ቀንቷት ግዳይ ጥላ በልታ ጠግባ ተርፏት ትታው እየመጣች ነበር ያየናት፡፡ ለራሷ ጉዳይ እያነፈነፈች ለአደን ሳይሆን፡፡ አንድም ሰው ሳይርበው ቢሆን የሚገል አረመኔ ነውና ቡችላዎቿን ገድለውባት ሁለት ተርታ ጡቶቿ አግተው ለማጥባት ተዘጋጅተው ግን ለማን ወይ ለምን እንደሚያጠቡት እየጨነቃቸው እና እየወጠራቸው ሊፈነዱ የደረሱ እየመሰላቸው፡፡ አንድም ተኩላይቱ በቀጥታ ከአማልክቱ በተለይ ከአባታቸው ከማርስ የተላከች ተአምራዊ ጡጦ ነበረች፡፡

ለማንኛውም ተኩላይቱ ተንበረከከችና መንትያዎቹን አጠባቻቸው፡፡ አያችሁልኝ አማልክቱ ሲፈጥሩን ወይም ጡጦ ሲልኩልን? ምን መንታ በመሆናቸው ወተት ያንሳቸዋል? ሁለት ብቻ በመሆናቸው ያንን ሁለት ተርታ ቁጥር የለሽ ጡት ጠብተውስ ሊያጋምሱት ነው እንኳን ሊጨርሱት? ለአሁነኛዋ ግትር ጥያቄ ደሞ መልስ ስላልቆጠርኳቸው ነው'ንጂ እነሱ ቁጥር አላቸው፡፡

እንግዲህ ይኸውላችሁ የድሮዎቹ አማልክትም ስንትና ስንት ተአምር ይሰሩ ነበር፡፡ ምን ያረጋል? ድሮ ቀረ፡፡ በኋላኛው ዘመናት ሮማ አለምን ረግጣ በምትገዛበት ጊዜ እስራኤልን ሳይቀር (ጲላጦስ ጴንጤናዊን ያስታውሷል) "መንገዶች ሁሉ ሮማ ያደርሳሉ" በሚባልበት ወቅት በአደባባይና በቤተ መቅደስ ትላልቅ የእብነ በረድ ሀውልቶች ይታዩ ነበር፤ ተኩላይቱ ቆማ ህፃናቱም ከጎንና ከጎኗ ቆመው ራሳቸውን ወደኋላ ዘምበል አድርገው ሲጠቧት፡፡

ለማንኛውም ተኩላይቱ ህፃኖቹን ወሰደችና ልክ እንደልጆችዋ እያጠባችና በኋላም ያደነችውን ስጋ እያበላች አሳደገቻቸው፡፡ ጥቂት ወራት ወይም ጥቂት አመታት ያልፋሉ፡፡ የደጉ ዘመን ሰዎችና አራዊትም ያሁኑን ያህል ተጠማምደው አንዱ የሌላው ባርያ ሆኖ ሳይሆን በጫካ ውስጥ ይሁን በወንዝ ዳር እግረ መንገድ ወይም ባጋጣሚ ሲገናኙ በቃልም ባይሆን በስሜት ደህና ናችሁ ወይ ይባባሉ ነበር፣ አማልክቱ ምስጋና ይድረሳቸውና፡፡

አሁንም የገዛ ራሱን በጎች እያረባና እያገደ የሚኖር ጎልማሳ እረኛ ደጦ አማልክቱ እይ ሲሉት ተኩላይቱ መንትያዎቹን ጡት ካስጣለች በኋላ ሳይሆን አይቀርም ከግዳዩ አብረዋት ሲቋደሱ አየ፡፡

"እረግ" አላት "እመቤት ተኩሊት እነኚህን ልጆች ከየት አመጣሻቸው? ደሞስ ምነው አልበላሻቸው?"

"የታይበር ወንዝ ልጆች ቢሆኑብኛ" አለችው፡፡ "ያ የሚያጠጣኝ የጥሜ ጌታ፡፡"

እረኛውም "ለአማልክት ውለታ መዋል ሳይበጅ አይቀርም" እያለ በልቡ "ተኩሊት ሆይ!" አላት "ምናልባት የአንቺ ባላደራነት ሳያበቃ ይቀራል? የኔ ሳይጀመር ይቀራል?"

"እውነትክን ነው" አለችው "ጡት መጥባት ይችሉበት ነበረ'ንጂ አጥንት መቆረጣጠሙን አይችሉትም፡፡"

ተቀበላት፡፡ ተሰናበታት፡፡ ወሰዳቸው፡፡ ልጆች ስላልነበሩት ልክ እንደ ልጆቹ ተንከባክቦ አሳደጋቸው፡፡ ስም አወጣላቸው፡፡ ሬሙስ እና ሮሙለስ አድገው ሲጎረምሱ የሽፍታ አለቆች ሆኑ፡፡ አበው እንደሚሉት ከፀሀይ በታች ተደብቆ የሚቀር ነገር የለምና ውሎ አድሮ ሬሙስና ሮሙለስ ማንነታቸው ታወቀ "እኛው ነንና ሬሙስና ሮሙለስ" አሉና ከሽፍቶቻቸው ሌሎች ጎበዞችም ጨምረው እዚያ አጎታቸው ነጣቂው ንጉስ ላይ ዘመቱ፡፡ መቱት፡፡ አሰናበቱት፡፡ ወደ ላይ ቤት ሳይሆን ወደ ታች ቤት ጥንታዊያን ግሪካዊያንና ሮማዊያን ሲሞቱ ሀዲስ ወይም ሄዲዝ

ወደሚባለው ከምድር በታች ወደሚገኝ ስፍራ ይወርዱና ኑሮ አይሉት ሲኦል አይሉት እንደጥላ መሳይ ነገር ሆነው መኖር እየናፈቃቸው ይኖራሉ፡፡

ሬሙስና ሮሙለስ ከዙፋን ተባሮ የነበረው አያታቸውን መልሰው አነገሱት፡፡ ከዚያ ለቀው ታይበርን ወርደው ያደገበት የሰባት ኮረብታ አገር ሲደርሱ ከተማ መሰረቱ፡፡ የሚኮሩባት ከተማ ሆነች፡፡

ሮሙለስ ከተማይቱን በካብ ከበባት፡፡ ሬሙስ ግን በወንድሙ ካብ ላይ ሳቀበት ምን መሳቅ ብቻ ካቡን ዘለለው እንጂ፤ ሮሙለስ ቁጣው ገነፈለ፡፡ ወንድሙን ገደለው አንዳንድ ጊዜ የቀበጡ እለት ሞት ይገኛል፡፡ ይኸው፡፡

"ማንም ሌላ ሰው በካቤ ላይ ቢዘል እንደዚሁ ይጠፋታል" አለ ሮሙለስ፣ መጥፎ ምልኪ ነጻሳ ቀን እቺ በሮሙለስ ስም የተሰየመችው ዘላለማዊት ሮማ ስንትና ስንት ምእተ አመታት ስትኖር በጦርነት ነው የኖረችው፡፡

እንግዲህ ጦርነት ሲኖር የጠባቂ አምላኳ የጃኑስ ቤተመቅደስ በሮች ይዘጋሉ ሰላም ሲሆን ይከፈታሉ እና በስንትና ስንት ዘመናት ታሪኳ ውስጥ የጃኑስ ቤተመቅደስ በሮች ተከፍተው የዋሉበት ቀን በጣት ይቆጠራል፡፡ ይኸው ጃኑስ ይመስክር! እስቲ ያ ለካፊ ሬሙስ አርፎ ቢቀመጥ ኖሮ እኮ ማን ዝለል አለው? እዚያ እንደሆነ ሰይጣን የለም ገና ክርስትና አልመጣማ፡፡

የሮማ ጠባቂ አምላክ ጃኑስ ከፊት ሲያዩትም ያው ፊቱ ይታያል፡፡ ማለት የጃኑስ ራስ ሲታይ ሁለት ራሶች ኋላ ለኋላ ተጣብቀው ይመስላል፡፡ ለዚህ አይደል ጠባቂ የሆነው፡፡ በየት በኩል ትመጣበታለህ? ጃኑስ እየጠበቃት ሮማ ስንትና ስንት ታሪክ ሰራች፡፡ ጥቂቱን በሚቀጥለው እንቀጥልላችኋለን፡፡

መስከረም 30 ቀን 1986

# ፪

በመጀመሪያ ሮማ አጥቂም ተዋጊም አልነበረችም ተከላካይ እንጂ። በስድስተኛው ምእት (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ሮማውያን ንጉስ ታርኩዊንዮስ ሱፐርቡስን "ውረድ ከንግዲህ እኛ ንጉስ አንፈልግም፤ ደሞ ሮማን ለቀህ ውጣ። እዚህ አትፈለግም አውት! ጥፋ" አሉት።

ታርኩዊንዮስ ሆዬ ሹክክ እያለ ይሄድና ለንጉስ ላርስ ፓርሴን አቤት ይላል። ላርስ ፓርሴናም በሮማ ላይ ትልቅ የኤትሩርያ ጦር ያዘምታል። ሰራዊቶቹ ከሮማ ውጪ ገጠሙ የሮማ ጦር ሲያፈገፍግ ሲያፈገፍግ ወደ ሮማ ገባ። የታይበርን ወንዝ በሱብሊስያ ድልድይ ተሻገረ ሮማውያኑ እሱን ድልድይ ማፍረስ ግድ ሆነባቸው። እስኪያፈርሱት ድረስ ሶስት ጀግኖች ሮማውያን ድልድዩ ጋ ሆነው የላርስ ፓርሴናን መላ ሰራዊት ገትረው ያዙት። አጥር ሆኑ።

ከዚያም ሁለቱ ጀግኖች ወደቁና ሁንይትዩስ አንድ አይና ብቻ ድልድዩ ላይ ብቻውን ቀርቶ አንድ ሙሉ ሰራዊት በሰይፍና በጋሻው ስልጣን ገትሮ ያዘ። ከኋላው ሮማውያኑ ድልድዩን አፍርሰው ሲጨርሱ ሁንይትዩስ አንድ አይና ወደ ታይበር ወንዝ ቁልቁል ተወረወረ። ወንዙን ዋኝቶ ተሻግሮ ካገሩ ሰዎች ጋር ተቀላቀለ። ጀብዱ ከሰሩ አይቀር እንዲህ ነው።

ሆኖም ግን ዝንተ አለሙን ለሮማውያን ወጣቶች እንደአርአያ ሲተረክ የዘለቀው የሁንይትዩስ አንድ አይና ጀግንነት ለሮማውያኑ ፋታ ሰጣቸው እንጂ ዞሮ ዞሮ መሸነፍ አልቀረላቸውም። ለላርስ ፓርሴና ከተማይቱን ከበባት። ሮማውያን እጃቸውን ሰጡ። ከተማቸውን አስረከቡ። የፓርሴናንም የበላይነት ተቀበሉ። ከታይበር ወንዝ በስተሰሜን ያለውን ግዛታቸውን ለቀቁ። የጦር መሳሪያቸውንም አስረከቡ። ወደፊትም ብረትን ለእርሻ መሳሪያነት ብቻ እንዲሰሩበት ቃል ገቡ።

ለመሆኑ ለዚህ ጦርነት መነሻ ምክንያት የነበረውን ታርኩዊንዮስ ሴፐርቡስን መልሶ አነገሰው ወይ? ያ ሀይሉ ላርስ ፓርሴና? አይመስል፡፡ እእ (ላርስ ፓርሴናን ምን ታደርገዋለህ? ምንም አታደርገውም ቀኑ የሱ ነዋ) ባለጊዜ ይባላል በአበው አባባል፡፡ አንድ በልልኝ ሮማ እያረስኩና በትንሹም እየነገድኩ ልኑር ብትል አላስኖር አሏት፡፡

ላርስ ፓርሴና ከዚች ህይወት ከተሰናበተና እታችኛው አለም ወርዶ ጥላ ሆኖ መኖር ከጀመረ በኋላ ሮማ ‹‹እርም ነው ንጉስ፣ ባፍንጫዬ ይውጣ›› ብላ ሴነት በሚባለው ያገሩ ታላላቅ ቤተሰቦች ሽማግሌዎች አባላት በሆኑበት ምክር ቤት ትተዳደር ቀጠለች፡፡

አራት መቶ ሀምሳ ስምንት ከክርስቶስ ልደት በፊት (እ.ኤ.አ) ሮማ ላርስ ፓርሴናን ረስታ አገር ጤና ብላ ኑሮዋን ስትቀጥል በየት በኩል? ኤኩዌ ይሁን እንዲህ የመሰለ አስጠሊታ ስም ያለው ህዝበ ሰራዊት ሮማን ለመውረር እየፎከረ መጣ፡፡

ሰላማዊ የሀገር ጉዳይ ባገር ሽማግሌዎች እየተመከረ ቢሆን ይመረጣል እንጂ ወራሪ ጠላት ታጥቆ ሲመጣ ግን አንድ ባለሙሉ ስልጣን አዛዥ ያስፈልጋል፡፡ ዲክቴተር ይሉታል ያን ጊዜ፡፡ እንግዲህ ከሮማ ወጣ ብሎ ጀግናው ሲንስናቱስ መለስተኛ እርሻው ላይ እየሰራ ይኖራል፡፡ ሴኔት ሴናትናቱስ ዘንድ ባስቸኳይ ላኩበት፡፡ ‹‹ሮማ ተወረረች፤ና ድረስላት››

ሲናትናቱስ በሬዎቹን ፈታ፣ የጦር ልብሱን ለበሰና ወደ ሴኔት ምክር ቤት ገሰገሰ፡፡ ባለሙሉ ስልጣን አዛዥ አድርገው ሾሙት፡፡ በሮማ ላይ ሰለጠነባት አዘዛት አዋጋት፡፡ በሁለት ሳምንት ውስጥ የጠላትን ወራሪ አባረረ፡፡ ቫይቪያ! ዲስክራሲያቶ ብሎ! አንድ ካልቾ ሰጣቸው ማለትም ቂጥን በእግር መሸኘት፡፡

ሮማ ፈነጠዘች ለልጅዋ ለሲናትናቱስ ውለታውን ልትመልስ ፈለገች፡፡ ሴነት ጠሩትና ‹‹አንተ ባትኖራት ኖሮ እናትህ ሮማ ጠፋች ማለት አልነበረም? አሁንም እነሆ ሴነት ምክር ቤት ስልጣኑን ይልቀቅና እንደ የእድሜ ልክ ባለሙሉ ስልጣን አዛዥ ሁን›› አሉት፡፡

ሲናትናቱስም ተናገራቸው እንዲህ አላቸው ‹‹አባቶቼ ስለስልጣናችሁ በጣም አመሰግናለሁ ልቤ ግን ከስልጣን ይልቅ እርሻ ይወዳል፡፡›› ተሰናበታቸውም፡፡ ወደ እርሻውም ተመለሰ፡፡ ስልጣን መንፈሳዊ መርዝ ነው፡፡ ያሰክራል ወይም ሱስ ያሲዛል ቢባልም አንዳንድ ሰዎች ግን ስካሩም ሱሱም አያድርባቸውም ማን ያውቃል? ይኸኔ ጨቅጫቃው የሲናትናቱስ አባት ቁርጥማቱም ምናምኑም እያንጫንጫቸው ይቆዩና አንበሳው ሲናትናቱስ ሮማን ከጠላት አስጥሎ ሲመለስ አባቱ የተቀበሉት ‹‹እንዲህ ነው እንጂ ጀግና አገሩን የሚያስጠራ!" ብለው በመሳም ሳይሆን "መች ይሆን አማልክቱ ይቅር የሚሉኝና ከሞኝነትህ የሚያስጥሉኝ? እድሜ ልክ ሙሉ ስልጣን ሰጥተውህ እምቢ አልክ አሉ እውነት ነው?"

"እውነት ነው አባዬ"

"ኧረ አባዬህ ይጥፋ ይሄ የሴት ልጅ!"

"አባዬ በሙሉ ሮማ ምድር አንተ ብቻ ነህ የወለድከኝ አንተ ብቻ ነህ የማታውቀኝ፡፡ አንተ ብቻ ነህ የምትንቀኝ፡፡ እኔ ግን ቂም አልይዝብህም፡፡ እኔ ባልኖር ኖሮ ዞረህ ራስህን እንደምትንቅና እንደምትጨቀጭቅ ይሰማኛል፡፡ ደሞ ልንገርህ ምድሪቱና አማልክቱ ሰሩኝ እንጂ አንተ አልሰራህኝም ስለዚህ አባዬ፣ እኔን ለቀቅ እርጅናህን ጠበቅ!"

አቤት እንዲህ ቢለው እንጼት በተገባ ሲናትናቱስ ግን ያለው ‹‹እሺ አባዬ፣ እንዳልክ አባዬ›› ነው፡፡ ጀግና ላባቱ መልስ አይሰጥም፡፡ እንበል እንግዲህ አፈ ታሪካችን እንዲያምርልን፡፡

ወይዘሪት ሮማ ታይበር ወንዝ ዳር ቁጭ አለችና ያለፉትን ተከላካይ ሆና የተዋጋቻቸውን ጦርነት ብታስብ ብታሰላስል ጊዜ ለካ ተከላካይም ሆነች አጥቂ ጦርነት ግን አልቀረላትም፡፡ ታዲያ ለዚህ ለዚህ በገዛ ምድሯ ሆና አገሯንም እየጎዳች ተከላካይ ጦርነት ከመዋጋት ሌላ አገር ዘምታ አጥቂ ጦርነት መዋጋት አይመረጥም?

"እኔው ነኝና ሮማ!" አለች ሮማ በቁራጥ ድምፅ "ወደፊት!"

ሴነት ምክር ቤት ግብር ይሰበስብና ወታደር ይመለምልና አንዱን ጀኔራል "ይህን ሰራዊት እንትና የተባለች አገር ላይ አዝምት" ብለው ስልጣን ይሰጡታል። ያቺን አገር የሮማ ሰራዊት ይወራታል። ያስገብራታል። ከሮማ ክፍለ ሀገሮች አንዷ ትሆናለች። ህዝቧም ሮማዊ ዜጋ ይሆናል።

ቀጥሎ ሮማ ዙሪያውን ታስተውልና "አሁን ደግሞ ማንን ልውረር? አዎን እንቶኔን አገር ልውረር።" ያ አገር ይወረራል፣ ይሸነፋል፣ ይገብራል የሮማ ክፍለ ሀገር ይሆናል። ሰዎቹም የሮማ ዜጎች ይሆናሉ።

እንዲህ ስትል፣ ስትል ሮማ ዛሬ ኢጣልያ የሚባለውን አገር አብዛኛውን ጠቅልላ በስተምስራቅ ዳርቻው ብቻ ግሪካውያን ከተማዎችና መንግስታት ቀሩዋት። እነዚህ ግሪኮች የሚያስተባብራቸውና የጦር አዛዣቸው ንጉስ ፒሩስ ነበር። የሮማው ሰራዊት የፒሩስን ሰራዊት ገጠመው። ፒሩስ አሸነፈ። ግን በጣም ብዙ ወታደር አለቀበት። እንደገና ፒሩስና ሮማ ይጋጠማሉ። እንደገና ፒሩስ ድል ያደርጋል። ግን ብዙ ብዙ ሰው ያልቅበታል። እንዲህ እያለ ሲቀጥል ሲቀጥል አንድ ቀን ከረዥም አስከፊ ውጊያ በኋላ አንዱ አዋጊ መኮንን መጣ ሰላምታ ሰጠውና።

"የምስራች ንጉስ ፒሩስ! ድሉ ያንተ ነው።"

"ከኛ ወገን ስንት ወደቀ?"

ይነገረዋል በጣም ብዙ ሰው ነው ያለቀበት።

"እሄሄ!" አለ ፒሩስ እራሱን እየነቀነቀ "ከእንግዲህ አንድ ድል ከጨመርኩ አለቀልኝ አለቅሁ።"

በዚህ ሁሉ መሀል አንድ የፒሩስ የቅርብ ተባባሪ በምስጢር ወደ ሮማ ሴነት (ምክር ቤት) መጣና እንዲህ አላቸው ‹‹ሮማውያን አበው! እኔ ከንጉስ ፒሩስ ጋር ባንድ ገበታ የምበላ ሰው ነኝ የሚጠቅማችሁን ሀሳብ ይዤ መጥቻለሁ።››

‹‹ተናገር››

‹‹ፒሩስ ወይን ጠጅ ውስጥ መርዝ ጨምሬ ብገድልላችሁ ስንት ትከፍሉኛላችሁ?››

‹‹እኛ ከሀዲ አንወድም። በፍጥነት ፈረስህ ላይ ወጥተህ በፍጥነት የሮማን ግዛት እንድትለቅ- ቫይቪያ (ትራዳቶሪ ፊሊዬዲካኔ!) ማለትም ‹‹ከዚህ ጥፋ ከሀዲ የውሻ ልጅ!››

ከሀዲው ጭራውን ሸጉጦ ወደመጣበት ተመለሰ።

ሴነትም ደብዳቤ ፅፈው ላኩ እንዲህ ሲሉ *"ይድረስ ለንጉስ ፒሩስ ከቅርብ ሰዎችህ አንዱ መድሀኒት ሊያቀምስህ ያስባልና ተጠንቀቅ።"*

ከርሞ ባጅቶ እነ ፒሩስም ድል ሆኑ። ሮማ ዛሬ የኢጣሊያ ምድር የሚባለውን በሙሉ ጠቀለለች። ከዚያም ባህር እየተሻገረች ወረራዋን አስፋፋች በሜዲትራኒያን ባህር ዙሪያ ያለውን አለም በሙሉ ተቆጣጠረች። በሰሜንም ስፓኝን ያዘች ጀርመንን ፈረንሳይን - ያን ጊዜ ስማቸው ሌላ ነው - ምእራብ አውሮፓ'ን በሙሉ ተቆጣጠረች። ፓክስ ሮማዊ ማለትም የሮማ ሰላም ተዘረጋ።

ጥቅምት 7 ቀን 1986

# ወይዘሪትና ወይዘሮ ሮማ

ባለፈው ፅሁፍ ስለ ወይዘሪት ሮማ አጫወትናችሁ። አሁን ስለ ወይዘሮ ሮማ እንቀጥላለን።

ወይዘሪትና ወይዘሮ ሮማ አንድም ሁለትም ናቸው በስማቸው በታሪካቸው አንድ። በወይዘሪት ሮማ ዘመን ታሪኩን የሰሩት አንድ አንዶች በወይዘሮ ሮማ ዘመን ታሪኩን የሰሩት ሌሎች ሌሎች። ስማቸውም ዘመናቸውም ለየቅል።

ታሪኳ ግን አንድ ታሪክ ናት። የዘላለማዊቱ ከተማ ታሪክ። (ለወጣት ደራስያን! እኛ እዚህ ሮማ ዘላለማዊቱ ከተማ፤ ኢየሩሳሌም ሰማያዊቱ ከተማ። ሁለቱም በየበኩላቸው የኛ ድንቅ ናቸው። አሁን ወይዘሮ ሮማን እናድንቅ። በሚቀጥለው እማማ ሮማን እናዝንላቸዋለን። እርጅና ሲያበሰብሳቸው ምነው አያሳዝኑም ‹‹እድሜ አተላ›› የሚለውን የአበው ዘፈን እንዝፈንላቸው እንዲሁም ‹‹ሰው እንዳስቀመጡት አይገኝም›› የሚለውን ዘለሰኛ እናዝምርላቸው።)

ታዳጊዋ ወይዘሪት ሮማ አሪፍ የነበረችበት ሰአት የጭንቅ ጭንቅ እያስጨነቃት የነበረውን የግሪኩን ንጉስ ፔሩስን በመርዝ ማስገደል ስትችል ከፔሩስ ጋር አብሬ ስለምበላ በመርዝ ብገድልላችሁ ስንት ትከፍሉኛላችሁ ያላትን ከሀዲ በካልቾ አባረረችና ለፔሩስ ተጠንቀቅ

አብሮህ የሚበላ ሰው በመርዝ ሊገልህ ያስባል ስትል ላከችበት። ማለፍ አይቀርላቸውም መቸስ ዘመናት አለፉ። ወይዘሮ ሮማ በሰሉ። በሀብትና ምቾት ብዛት በሞራል የመጣ እየለሰለሱ መጡ። ምን አይነት ዘመን ሴነት (የታላላቅ ቤተሰቦች ሽማግሌዎች ምክር ቤት) አንዱ ቄሳር ሲሞት የሚቀጥለውን ቄሳርነት በገንዘብ መሸጥ ጀመረ። አንድ ጊዜማ ግልፅ ጨረታ ሆነ። የእስፓኝ አገረ ገዥ የነበረው የጦር አዛዥ በመልእክተኛ ‹‹ቄሳር ብታረጉኝ ይህንን ያህል እከፍላለሁ›› አለና ሌሎች እንከፍላለን ካሉት የበለጠ በመሆኑ ቄሳር ሆነ ላጭር ጊዜ።

በዚያን ዘመን ቄሳሮቹ ዘመነ መንግስታቸው አጫጭር ነበር። ለምን ቢሉ ጠባቂያቸው የሆነው የክብር ዘብ ክፍለ ጦር ስለሚገድላቸው። የሁኔታው አመጣጥ እንዲህ ነው። የቄሳር የክብር ዘብ ያገሩ ሰዎች ላቲኖች ከሆኑ አዛዦቸው ቄሳርን ገድሎ ሴነትን አስገድዶ ወይም አግባብቶ ቄሳር ሊሆን ይችላል የሚል ፍርሀት አየለ። (ጊዜው እያስተማምንማ ድሮ ቀረ ሮማዊ ለሮማዊ የወንድማማች ያህል መተማመን) ስለዚህ ቄሳር የክብር ዘቡን ከግዙፎቹና ከፀጉረ ነጫጮቹ ጀርመኖች ብቻ ይመለምል ጀመር። አዛዦቸውም ጀርመን ነበር። ይነግሳል ተብሎ አይታለምም አይንገስ እንጂ ያነግሳል ግና። አሁን ከሚገዛው ቄሳር በዘር (ሀረግ ቢመዘገዘ) የማያንስ ብዙ ሀብትና የስልጣን ጥማት ያለበት ይህ ሰው የክብር ዘቡን አዛዥ በምስጢር እንዲህ ይለዋል። ‹‹ብታነግሱኝ ለያንዳንዱ ተራ የክብር ዘብ አባል ይህን ያህል ገንዘብ ለመቶ አለቃዎች ይህን ያህል ለሻለቃዎች ይህን ያህል ላንተ ለወዳጄ ደሞ ይህን ያህል፣ በጥሬ ወርቅ ገንዘብ እከፍላለሁ።››

ቄሳር በነገሰ በጥቂት አመቱ ይገደላል። ይሄኛውቄሳር ይሆናል። ከጥቂት አመታት በኋላ እሱ የተጫወታት የጉቦ ጨዋታ ሌላ የእሱ ቢጤ ከክብር ዘብ አዛዥ ጋር ይጫወታል። ቄሳር በነገሰ በጥቂት አመቱ ይገደላል። ወዘተ።

ይህ የሮማ መበላሸት አንድ ገፅታ ነበር። ሌላ ገፅታ ሮማ ትንሽ በትንሽ እየቆረሰች ኢጣሊያ ምድርን ከጠቀለለች በኋላ ባህር ማዶ

ተሻገረች። እንደልማድዋ ሌሎችን አገሮች አንድ ባንድ ጠቀለለቻቸው ግብፅን ጭምር። አስተማማኝ አመታዊ የስንዴ ሲሳይ። አብዛኛው ተራ የሮማ ከተማ ተወላጅ ስራ ፈት ሆነ። ስንዴ በነፃ ይታደላል። እድሜ ለግብፅ።

ከዚህም ጋር ኮልዚየም የተባለ ሃምሳ ሺህ ተመልካች የሚይዘው እንደ ስታዲየም የሚያገለግለው ባለአራት ፎቅ ህንፃ በነፃ ገብቶ ስንትና ስንት የደም መፋሰስ ትርዒት እያዩ መዋል አለ።

አዲሱ ቄሳር ለንጉሱ የደስ ደስ የሮማ ከተማን ህዝብ ትርኢት ይጋብዛል። ምናልባት ዘጠኝ ቀን አከታትሎ። ልዩ ልዩ ሹማምንት በልዩ ልዩ ምክንያት እንደዚሁ ይጋብዛል። ከማያልቁት ጦርነቶች ከአንዱ በድል አድራጊነት የተመለሰን የጦር አበጋዝ የደስ ደስ ይጋብዛል።

ከማያልቁት ጦርነቶች የሚመጡ ምርኮኞች ገበያ ተወስደው በባርነት ይሸጣሉ። የሮማ ከተማ ስራ አብዛኛው በባሪያ ጉልበት ይሰራል፤ የኗሪው ሁለት ሶስተኛ ባሮች ናቸው። ሲሶው ብቻ ናቸው ነፃ ዜጎች። እነዚህ ነፃ ሲሶ ዜጎች ናቸው ያንን የተለያየ የደም ማፋሰስ ስፖርቱንና የሰረገላ እሽቅድድሙን በነፃ ሲመለከቱ የሚውሉት።

ከጦር ምርኮኞች መሀል መልካም ቁመና ያላቸው ወንዶች የግላዲያተር ስልጠና ይሰጣቸውና ከቢዚሮም እየገቡ እርስ በርስ ይጋደላሉ። ግላዲያተር ማለት ሌላውን ግላዲያተር የሞት ግጥሚያ የሚገጥም ጎበዝ ነው። አንድ ላንድ ሊጋጠሙ ይችላሉ። ሰራዊት ለሰራዊት ሆነውም ሊዋጉ ይችላሉ። ወይም አንድ ግላዲያተር ሶስት ቀን ፆሙን ካደረ አንበሳ ነብር ተኩላ ድብ ወይም ሌላ አውሬ ጋር ይጋጠማል እስከሞት። የሮማ ህዝብ ይሄ ደም ሲፈስ እያየ መዋል ሱስ ሆነበት።

ሮማ ባህር ማዶ ስትሻገር ከካርታጅ ጋር ተጋጨች። ካርታጅ ከጢሮስ የሄዱ የፊንቂ ሰዎች በሰሜን አፍሪካ የቆረቆሯት በጣም ምቹ ወደብ ያላት ከተማ ናት ‹‹ቃርት ሀዳሽት›› አኗት ‹‹አዲስ ከተማ››። እሷም የራሷ ሰፊ ግዛት አላት። ካርታጅ አንድ ለየት ያለ ባህል ነበራት።

የበኸር ልጅን ለአማልክት መስዋእት ያቀርባሉ ትልቅ እቶን ውስጥ ይጨምሩታል። የሚቃጠል መስዋእት ይሉሀል ይሄ ነው፤ ወይም ራሳቸው ዘለው ገብተው ይቃጠላሉ። መስዋእት ለአምላክ። ወደኋላ ጊዜ በበኸር ልጆቻቸው ፈንታ የባርያ ልጆችን ይሰዉ ነበር። ካርታጅ በጦርነቶች እየተሸነፈች ስትሄድ አማልክቱ ተቀይመው ነው ተባለ። የበኸር ልጅ ለምደን እንዴት በባርያ ልጅ ትሸነግሉናላችሁ? ብለው ተቀየሙ።

ካርታጅ እና ሮማ ሶስት ጊዜ ተዋጉ። ሶስቱንም ጊዜ ሮማ ድል አደረገች። በመጀመሪያው ጦርነት የካርታጅ የጦር አዛዥ ሀሚልካር ባርካ የተባለው አደገኛ ተዋጊ ነበር። ከዚያ ጦርነት በኋላ ጄኔራል ሀሚልካር ልጁ ሀኒባልን ባስር አመቱ ቤተመቅደስ አስገብቶ አስማለው ‹‹እድሜ ልኬን ሮማውያንን እጠላለሁ፤ ባለኝ አቅም አጠፋቸዋለሁ››

ሁለተኛው የካርታጅ እና የሮማ ጦርነት በ218 ከክርስቶስ ልደት በፊት ተጀምሮ ለአስራ ሰባት አመት ተካሄደ። የካርታጅ አዝማች ጄኔራል ሀኒባል ባርካ ነበር። ሀኒባል ዝሆኖቹንና ሰራዊቱን አልፐስ በሚባሉት ዘላለም በበረዶ በተሸፈኑት ተራሮች አሻግሮ ሰሜን ኢጣልያ ገባ። ከዚያ ለአስራሰባት አመት ሮማን ፍዳዋን አሳያት ሀኒባል ጀግናው። በጦር ስልት አልተቻለም። የረዥም ጊዜ ስትራቴጂ ቢባል ወይም ያጭር ጊዜ ታክቲክ ሀኒባል ሆነ ጌታዋ።

ሴነት በጄኔራል እገሌ የሚመራ ሰራዊት ይልካል። ሀኒባል ድባቅ ይመታዋል። አብዛኛው የሮማ ሰው ያልቃል። ሌላ ጄኔራልና ሌላ ሰራዊት ይልካል፤ ሀኒባል አፈር ያበላዋል። በመጨረሻ ግን ሴነት ጄኔራል ኩዊንቱስ ፋቢዩ ላክሲሙስን ሾመ። ኩዊንቱስ ሞኝ አይደለም አቅሙን ያውቃል ሀኒባልን በቀጥታ ውጊያ አልገጠመውም። ብቻ ከሩቅ ይከታተለዋል። እንደበፊቱ አገሩን እንደልብ እየወረረ እንዳይመገብ ይከለክለዋል። ከዚህም ጋር ካርታጅ ውስጥ በሀኒባል ላይ ምቀኞች ተነሱበትና ተጨማሪ ወታደርም ገንዘብም እንዳይላኩለት አደረጉ። ቀስ በቀስ የሀኒባል ጦር እየመነመነ መጣ። ኢጣልያን ለቆ ወደ ካርታጅ መመለስ ግድ ሆነበት።

ሀኒባል ሮማን ከማንቀጥቀጡ የተነሳ ለሚቀጥሉት ትውልዶች የሮማ እናቶች ልጆቻቸው አልታዘዝ ሲሉዋቸው ‹‹ሀኒባልን ነው የምጠራልህ ዋ!›› ብለው ያስፈራሩዋቸው ነበር።

ሀኒባልን ያህል ልዩ ፍጡር የሚያደናቅፉትና የሚሸጡት እንዴት ያጣል? ከካርታጅ ወጥቶ እዚህም እዚያም ተንከራተተ ሀኒባል አንድ አይናው። በመጨረሻም በ183 ከክርስቶስ ልደት በፊት ሮማውያን ከሚማርኩኝ ሞት ይሻለኛል ብሎ ራሱን ገደለ።

ከሁለተኛው የካርታጅ እና የሮማ ጦርነት በኋላ ጥቂት አመት ቆይቶ ሺፒዮ የተባለ የሴነት አባል ካርታጅን ጎበኘ። እቺ ካርታጅ በጣም እያንሰራራች አገኛት። ፈራት። ጠመዳት። ሴነት ተሰብስቦ የአገር ጉዳይ ሲመክር የውይይቱ ርእስ ምንም ይሁን ምን ሺፒዮ ስለጉዳዩ ሀሳቡን ይሰጥና ‹‹ከዚህ በተረፈ ካርታጅን ማውደም አለብን›› ብሎ ይደመድማል ሁልጊዜ።

ሶስተኛው የካርታጅ እና የሮማ ጦርነት በ149 ከክርስቶስ ልደት በፊት ተከፈተ። የሮማው የጦር መሪ ያ ሺፒዮ ራሱ ሆነ። በሶስት አመት ውስጥ ካርታጅን ድል አደረጋት። የካርታጅን ከተማ ከበባት። የካርታጅ ኗሪዎች ሮማውያኑ ራሳቸው እስኪደንቃቸው በጀግንነት ተዋጉ። አብዛኞዎቹ አለቁ የቀሩት ለባርነት ተዳረጉ።

ሺፒዮ ካርታጅን አፈረሳት። በድንጋይ ላይ ድንጋይ አልቀረም ከዚያ ቦታው ታረሰ ጨው ተዘራበት። ካርታጅ አለቀላት። ለሺፒዮም ሴኔት የከበረ ስም ሰጡት። ሺፒዮ አፍሪካትስ ተባለ። ካርታጅ አፍሪካ ነቻ።

ጥቅምት 14 ቀን 1986

# ጁሊየስ ቄሳር

ከእግዜር በታች ገኘርያችን ገዳይ አኗሪያችን ንጉስ፣ ፕሬዝዳንት ወዘተ ነው መልኩንና ስሙን እየቀያየረ፡፡ ከነዚህ ስጋ ለበስ የጥቂት አመት እድሜ አማልክት ለኔ ከሁሉቹም ልቆ የሚታየኝ ጋዬስ ጁሊየስ ቄሳር እንዳጋጣሚ ደሞ (ወይም እንደ አማልክቱ እቅድ) የጁሊየስ ቄሳር የትውልድ ሀረግ ሲመዘዝ የፍቅር ሴት አምላክ ከሆነችው ከቬኑስ ይወለዳል፡፡ በነቬነስ ዘመን ሰዎችና አማልክት አልፎ አልፎ ይዋለዱ ነበር፡፡ እኛ በዚህ ጉዳይ አንጠየቅበትም፡፡

የጁሊየስ ቄሳር ተአምራዊ ታሪክ ከመርዘሙ የተነሳ እንደፌንጣ ወይም እንደቁንጫ ወይም እንደካንጋሮ እየነጠርን ብዙውን እያለፍነው ጥቂት ቁንጮ ድርጊቶቹን ብቻ እነሆ፡፡

<u>አንድ</u> - ጎረምሳው ጁሊየስ ቄሳር ኮርኔልያን አግብቶ ነበር። ላሁኑ ጨዋታችን ማወቅ ለማያስፈልገን ምክንያት ሱላ የተባለው ቆራጥ የሮማ ፈላጭ ቄሳርን አዘዘው - ኮርኔልያን ፍታት አለው፡፡ ማንም ሮማዊ ቢሆን እሺ ጌታዬ (ሺ አመት ንገስ ጌታዬ) ነበር የሚለው፡፡ ግና ጁሊየስ ቄሳር በመሆኑ እምቢኝ አሻፈረኝ አንተ አልዳርክልኝ አለው፡፡ ከየት መጣሁና ታፋታኛለህ? ሸሸ ጁሊየስ ቄሳር አመለጠ፡፡

በነገራችን ላይ ይሄ ሱላ ቀላል ሰው አልነበረም፡፡ አምስት አመት ሮማዊውን አለም ከገዛ በኋላ ለመቀጠል ማንም ሳይከለክለው በገዛ ፈቃዱ

ስልጣኑን ለቀቀና ወደ እርሻው ሄደ። ቀደም ሲል ሲናትናቱስ ከሁለት ሳምንት ሙሉ ስልጣኑ በኋላ እድሜ ልክ ሙሉ ስልጣን እንመርቅልህ ቢሉት እምቢ ብሎ ወደ እርሻው ተመልሶ ነበር። ሱላ ደግሞ ከአምስት አመት በኋላ።

<u>ሁለት</u> - ሱላ ከስልጣን ሲወርድለት ጁሊየስ ቄሳር ከሸሸበት ተመለሰ። በዚች ሰአት ሮማ በባህር ላይ ለማጅ ተዋጊ ነች።

ሴነት ጁሊየስ ቄሳርን የጎለበተ የባህር ሀይል ወዳለውና በባህር ማዶ ወደሚኖረው የቢቲንያ ንጉስ ኒኮሜዲስ ላከው - የጦር መርከቦችን ያመጣ ዘንድ። ሄደና አመጣ። በዚያ ወጣት እድሜው እጅግ አስደናቂ የዲፕሎማሲ ችሎታ (ማለትም ባገር ደረጃ ንጉስ ኒኮሜዲስን አግባባው እሺ አሰኘው) ማለትም ከሱላ ሀያሉ ጋር ተጋተረ ሰአቱ የመጋተር ሲሆን። ከንጉስ ኒኮሜዲስ ጋር ሲሆን ደሞ ተለሳለሰ ሰአቱ የመለሳለስ ስለሆነ።

<u>ሶስት</u> - ጁሊየስ ቄሳር ከፍተኛ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ሮድስ ደሴት በመርከብ ይጓዛል። ባህር ዘራፊ መርከብ ታገኛቸውና ይማረካሉ መርከቡ በሙሉ። እነዚህ ወንበዴዎች ሲማርኩህ ወይ ይገድሉሀል ወይ ወደ ወገኖችህ ልከህ ይህንን ያህል ገንዘብ ላኩና አስፈቱኝ ትላቸዋለህ። ሲልኩልህ ወንበዴዎቹ ገንዘቡን ተቀብለው ነፃ ይለቁሀል።

ጁሊየስ ቄሳር - "የኔ ዋጋ ስንት ነው?"

ወንበዴዎቹ - "አንድ ሺህ ሴስተርር ሲዝ" በወርቅ። (እንበል)

ጁሊየስ ቄሳር - "እናንት ወራዳ ውርጋጦች! እኔ ጋዩስ ጁሊየስ ቄሳር ነኝ በአንድ ሺ ብቻ የምገመት? አምስት ሺ ሲያንሰኝ ነው ልንገራችሁ በትንሽ ስለገመታችሁኝ በትልቅ እቀጣችኋለሁ። እያንዳንድሽን በስቅላት!!"

ገንዘባቸውን ተቀብለው በጉራው ስቀውበት አሰናበቱት።

<u>አራት</u> - የሮማ ጄኔራሎችና የአለም ጄኔራሎች ጥምር ቁንጮ ጉልላታቸው ማነው? ጁሊየስ ቄሳር። ለምን ቢሉ ሙሉ ጄኔራል ብቻ

ሳይሆን ሙሉ ወታደርም ጭምር በመሆኑ። ወታደሮቹ እንደማንም ጄኔራል መፍራትና መታዘዝ ሳይሆን በችሎታው ያደንቁትና በማንነቱ ሲበዛ ይወዱት ነበር 'የፉገራ' ሳይሆን የእውነት ይሞቱለት ነበረ።

ተራ ጄኔራል ቢሆን ኖሮ ለእሱ ክብር ማእረግና ፕሮቶኮል ምን ይገባው ነበር? አገሩ ሜዳ ሲሆን በሰረገላ መሄድ፤ አገሩ ውጣ ውረድ ሲሆን መኘታም መቀመጫም እውስጡ ያለው አራት ወይም ስምንት ጉልበታሞች ወታደሮች ተሸክመውት የሚሄዱ፤ ሰው በሸክም ሰረገላ ውስጥ እየተንፈላሰሰ መንዝ ይገባው ነበር።

ጁሊየስ ቄሳር ግን ሜዳም አገር ይሁን ኮረብታማ በበረዶም ይሁን በሀሩር እንደማንኛውም ተራ ወታደር በእግሩ ነው የሚሄደው። መቼም ቢሆን የትም ቢሆን።

ተራ ጄኔራል (ተራ እንበለው እንጂ) የመንንኘርያ ብቻ ሳይሆን የመመገቢያ ልዩ መብቶች አሉት። ዝመት ተብሎ ከሮማ ሲነሳ ከሚስቱ በስተቀር አብዛኛዎቹን የወጥ ቤቱን ባሮችና አሽከር ገረዶች ጠቅልሎ ይዟቸው ይዘምታል። በልዩ ወጥ ቤት ድንኳኑ ውስጥ የተለየ ምግቡን ይሰሩለታል ያቀማጥሉታል።

ጁሊየስ ቄሳር ግን ልዩ ወጥ ቤት የለውም ከተራው ወታደር ጋር ነው የሚበላው የሚጠጣው - ያውም ልክ እንደተራ ወታደር እየተራገመ፤ እየተሳደበና እየተቃለደ።

ስለዚህ ወታደሮቹ በሙሉ ልብ፤ በሙሉ ወኔ ስለሚዋጉለት የጠላት ጦር ብዛት ከእነሱ ከእጥፍ በላይ ቢሆንም እንኳን ድል የነሱ ነው።

የምር የመዋጋት የመጋደል ሰአት ስትደርስ ተራው አዋጊ ጄኔራል ወታደሮቹን ወደ ደራው የሞት ገበያ ሊልካቸው ሲል ጋሻ ጦር ሰይፍና ጎራዴ፤ ገምባሌ የራስ ቁር የደረት ጡሩር ይዘውና ለብሰው እየተቁነጠነጡ ሳለ ንግግር ያደርግላቸዋል

"ወታደሮች! ዛሬ ለሮማ ለመዋደቅ እድል የሰጣችሁን አማልክት ልታመሰግኑ ይገባል። ለውድ እናታችሁ ወልዳ ላሳደገቻችሁ ከመሞትና ከመገደል የበለጠ ምን ፅድቅ ምን ብፅአት ሊኖር ይችላል?" ወዘተ . . .

ጁሊየስ ቄሳር ግን በዚያች ሰአት ወታደሮችን እንዲህ ይላቸዋል ምናልባትም ጥሬ ካሮት እየገመጠ ሊሆን ይችላል፡፡

"ወቱ! እንግዲህ በርትተህ ተዋጋ፡፡ ብርቱ ጠላት ነው እፊትህ ያለው በብዛት ሁለት ሶስቴ ሊበልጠን ይችላል፡፡ ግና እነሱና መሪያቸው ማ'ናቸው? እኔና እናንተስ ማ'ነን? (ከካሮቱ ገመጥ) እንግዲህ ምን ትጠብቃለህ? አትነፋውም? ወደታችኛው አለም አናሰናብታቸውም?"

ይሄኔ አንዱ ወታደር ወይም ሹም ይነሽጠውና "ከጁሊየስ ቄሳር ጋር ወደፊት!" ይላል፡፡

እንዲህ ብለው ተነስተው እነጁሊየስ ቄሳር ተሸንፈው አያውቁም ምናልባት ከአንድ ሁለቴ በስተቀር፡፡

ከ58 እስከ 51 ከክርስቶስ ልደት በፊት ባለው ሰባት አመት ውስጥ ጁሊየስ ቄሳርና ውድ ሰራዊቱ አሁን ፈረንሳይና ጀርመን የሚባሉትን ያን ጊዜ (?) የሚባለውን ሰፊ የጀርመኖች አገር አቀኑ፡፡

49 ከክርስቶስ ልደት በፊት፡፡ ታሪካዊ አመት፡፡ ጁሊየስ ቄሳር ድል በድል ሲቀዳጅ እዚያ ሮማ ውስጥ ባለ ሰራዊቱና ተደናቂው "ታላቁ ፓምፔይ" እና የሀብታሞች ሀብታም የሆነው ክራሱስ የሮማን ግዛት ለሁለት ሊከፍሉት ፈልገው ጁሊየስ ቄሳርንም ሊያዳክሙት አቅደው ላለፉት ሁለት አመታት ገንዘብም ስንቅም ምንም እንዳይላክለት አድርገው ቆይተዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጁሊየስ ቄሳርና ሰራዊቱ ወደ ኢጣሊያ ተመለሱ፡፡

ኢጣሊያ ምድር ገብተው ምንም ያህል ሳይጓዙ ሩቢኮን ወንዝ ዳር ደረሱ፡፡ በህጉ መሰረት ማንም ጄኔራል ሰራዊቱን ከሩቢኮን ወዲያ ትቷቸው ከጥቂት የክብር ዘብ ጋር ብቻ ነው ወደ ሮም መዝለቅ የሚችለው፡፡

ስለዚህ ጁሊየስ ቄሳር ሊሰናበታቸው ወታደሮቹ ተሰብስበዋል "እምቢ እዚህ አንቀርም አብረንህ ወደ ሮማ እንገባለን" ይሉታል፡፡ "ከእናንተ ጋር

ያቺን ወንዝ ከተሻገርኩ ሴኑት እና ሮማ ላይ ጦርነት አወጅኩ ማለት'ኮ ነው" ይላቸዋል፡፡ "ይሁና! እንዋጋለን" ይሉታል፡፡ ይሄኔ ትልቁን የገንዘብ ሳጥን ከድንኳኑ ያስመጣና ከፍቶ ያሳያቸዋል "ባዶ ነው እንደምታዩት፡፡ ምን እከፍላችኋለሁ?" ይላቸዋል፡፡

አንድ አዛውንት ወታደር "ይኸውና ያለኝን ሁሉ" ይልና ከከረጢቱ ገንዘቡን አውጥቶ እሳጥኑ ውስጥ ይጨምረዋል፡፡ እኔም እኔም እያሉ ወታደሮቹ ሁሉም እንደዚሁ ገንዘባቸውን ሳጥን ውስጥ ይጨምራሉ፡፡

"ሳጥኑ አሁን ሙሉ ነው" ይሉታል፡፡

"እንዲህ ካላችሁማ መቸስ ምን አደርጋለሁ?" ይልና ጁሊየስ ቄሳር ከነሰራዊቱ ወደ ሮማ መረሸ፡፡ እስካሁን ድረስ ፈረንጆች መመለሻ የሌለው ቆራጥ ውሳኔ መውሰድ ለማለት ‹‹ሩቢኮንን መሻገር›› ይሉታል፡፡

**ጥቅምት 21 ቀን 1986**

# ፱

## የቄሳር ተቃዋሚዎች

ባለፈው ፅሁፍ የጄኔራሎች ቁንጮ ጉልላት የሆነው ጋዩስ ጁሊየስ ቄሳርን በጨረፍታ አይተነዋል፡፡ የሚቃወሙትን የሚፋለሙትን በሚጢጢ ጨረፍታ እንያቸው፡፡

ፓምፔይ በትውልዱ ከማንም የላቀ በግሪክና በምስራቅ በኩል ብዙ ተዋግቶ አያሌ ድሎችን የተቀዳጀ "ታላቁ ፓምፔይ" ሊባል የበቃ፣ ህዝብ በጣም የሚወደውና የሚያደንቀው፡፡ እሱ የሮማን ግዛት ምእራባዊውን ግማሽ ይዟል ሮማን ራሷን ጭምር፡፡

ክራሱስ ምስራቃዊውን ግማሽ ይዟል፡፡ አስቀድመው ግን ከጁሊየስ ቄሳር ጋር ለሶስት ሊጋሩት ነበር ውላቸው፡፡ ሁለቱ ጁሊየስ ቄሳርን አገለሉት፡፡ ከሲሶ ግማሽ ይመረጣል፡፡

ክራሱስ የሀብታሞች ሀብታምና የቀንቋኖች ቀንቋና ነበር። አብሮ አደጉና የልብ ጓደኛ የሆነው አንድ ደሀ ፈላስፋ ክራሱስ ቤት በጥገኝነት ይኖራል። ከዜሮ ዲግሪ በታች የሚደርስ በብርድ የሚያንቀጠቅጥ ክረምታቸው መጣ። ያ ደሀ ጥገኛ ጓደኛው ይህን ብርድ ሊከላከል የሚችል ልብስ የለውም። ክራሱስ በጣም አዘነለትና ወፍራም ካፖርት አዋሰው። ክረምቱ ሲያልፍ ክራሱስ ካፖርቱን መልሶ ተቀበለው። ጓደኝየው ክራሱስን አልታዘበውም። ይልቅስ ቀንቋናነቱን አሸንፎ ሊያውሰው በመቻሉ ምን ያህል እንደሚወደው ተገነዘበ። በደግነቱንም አደነቀው። በሽታውን ያውቅለታል ጓደኛው አይደለ----

ለመሆኑ ክራሱስ ይህን ብዛቱን ማመን የሚያስቸግረውን ሀብት ለማካበት መነሻ ካፒታል ከየት አገኘ? ደስ የምትል ታሪክ ናት።

የክራሱስ አባት የዚያ አምስት አመት ሮማን በፈላጭ ቆራጭነት የገዛት የሱላ የቅርብ ረዳቱ ነበር። ሲዋጋለትም ነበር የሞተው። ስለዚህ ሱላ ስልጣን እንደያዘ ወጣቱን ክራሱስ አስጠራው "ስለ አባትህ ውለታ ምን ላድርግልህ?" አለው።

"በሮማ ከተማ የእሳት አደጋ መከላከያ አገልግሎት በሞኖፖሊ ስጠኝ"

ሰጠው። በሮማ እሳት ሲነሳ ክራሱስን በሩጫ ይጠሩትና እሳት አጥፊ ቡድኑንና መሳሪያዎቻቸውን አስከትሎ ከተፍ ይላል። እሳቱን ለማጥፋት ይዘጋጃሉ። አያጠፉትም ከዚያ ይልቅ "ሸጠው" ይለዋል

"አልሸጠውም"

"እሳቱ በልቶ ከሚጨርሰው ይልቅ በመቶ ሺህ አትሸጥልኝም?"

"አራት መቶ ሺህ ከፍሎ ነው አባቴ ያሰራው"

"እሳቱ ግን እንደምታየው ነው"

"እሺ ባይሆን ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ ክፈለኝ"

"መቶ ሺህ። እየቆየን ስንሄድ ደሞ መቶዋ ሺ እየቀነሰች ትሄዳለች እሳት ነዋ"

ማርከስ እየተራገመ "እሺ መቶ ሺህ" ይላል። የክራሱስ አገልግሎት እሳቱን ያጠፋዋል ክራሱስ ቪላውን ለማሳደስ ሀምሳ ሺህ ያወጣና በአራት መቶ ሺህ ይሸጠዋል። ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ አተረፈ. እድሜ ለእሳት!

በዚህ አሸፋፈጥ ያተረፈውን ገንዘብ ንግድ ላይ ያውላል። ጁሊየስ ቄሳር ጄኔራልየው እና ክራሱስ የገንዘብ ተአምረኛው ቢመዛዘኑ ማን ይመዝን ይሆን? እስከዛሬ ድረስ ስለ በጣም ሀብታም ሰው ሲነገር "እሱ ክራሱስ ነው ከይሲ" ይባልለታል። ንፉግነቱ እምብዛም አይተወውም። ስንትና ስንት ቆንቋናና ንፉግ ሞልቶ የለም'ዴ እያንዳንዳችን የምናውቀው። ክራሱስ ገንዘቡን አመለከ፣ ለገንዘብ ሲል ኖረ፣ የገንዘብ ዛር ደግሞ የወደዳትን ያህል መልሳ ወደደችው። በቁጥር የለሽ ሴስተርሲዝ አሻረችው።

አሁን የክራሱስን ሙሾ እናወርዳለን በስድ ንባብ።

የገንዘብ ጥበብ ከአማልክቱ እኩል የተካንከው ክራሱስ ሆይ! ምነው የገንዘብ ዛርህ እያሻረችህ እያለ ባልከዳሀት ኖሮ!? አንተ ግን ሰው ነህና ለመሳሳት የተፈጠርክ ነህና ተሳሳትክ፤ ከዳሀትና ሄደህ ለማርስ ለጦርነት አምላክ አደርክላት። የጁሊየስ ቄሳርና የፓምፔይን የጦር ሜዳ ሞገስ ትለብሰው ዘንድ ተመኘህ። እና በገንዘብህ መአት ሰራዊት ቀጠርክና ወዴት ዘመትክ? ወደ ፓርትያ?

ያማልክት አባት ጁፒተር ያሳያችሁ አማልክቱ ያመልክቷችሁ ሮማ ታዳጊ ከተማ ከነበረችበት ዘመናት አንስቶ አሁን በጨዋታችን እስከያዝነው አመት ድረስ ሮማ የተዋጋችውን ሁሉ ስታሸንፍ ካርታጅ እና ሀኒባል ሳይቀሩ ሁሉንም ስታንበረክክ (ግብፅን፣ እስራኤልን፣ ግሪክን ጨምሮ) ፓርቲያ ግን አልተቻለችም። ሮም አለምን ሁሉ ክተት ብላ መዝመት እየቻለችም ፓርትያን ትንሿን አገር ግን ማስገበር አልቻለችም

ሮማና ፓርትያ ኅልያድና ዳዊት ያህል ናቸው፡፡ ይችኛዋ ኅልያድ አልሞተችም እንጂ፡፡

አሁን ክራሱስ በፓርትያ ላይ ዘመተ "ያው የተለመደው ነው" ሞት ብዙ፣ ብዙ ምርት አመረተ ታዲያ ለካ ማሸነፍ ተራው የፓርትያ ኖሮ ክራሱስ ድል ሆነና ተማረከ፡፡

"ዝነኛው ክራሱስ ሆይ!" አለው የፓርትያ ንጉስ እንበል "እኛ የፓርትያ ሰዎች እንግዳ ተቀባይ ነን እንግዳ የአማልክቱ ነዋ፡፡ እንዲያውም አማልክቱ ለገዛ ምክንያታቸው እንግዳ ሆነው በምሽት ላይ ይመጡብን የለም? ስለዚህ ተዝናና እንግዳችን ነህ፡፡"

ዘና አለ ክራሱስ፡፡ "በጦርነት ተሸንፌህ አለቀ፡፡ በኛ ባህል ደሞ ለእንግዳችን የምናቀርብለት እሱ በጣም የሚወደውን እራት ነው፡፡ አንተ ደሞ ከሁሉም የምትወደው ወርቅን ነው፡፡ ስለዚህ..." አለና በግድ አፉን አስከፍቶ የቀለጠ ወርቅ አጠጣው ይባላል፡፡ (የክራሱስን ጉሮሮ አያድርገን)

ሌላም ይባላል፡፡ እንበል የፓርትያ ንጉስ ክራሱስን ሲያየው አሳዘነው፡፡ "በጎደሎ ቀን ከንግድ አለም ወደ ጦር አለም ጥልቅ አለና ምንም ያህል ሳንዋጋ ማረክነው፡፡ ለሮማዊ ምህረት ማድረግ ቢፈቀድ ኖሮ ይህን በማርነው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ደግ ሞት እንስጠው፡፡"

ክራሱስና ጭንቅላቱ ተለያዩ፤ አሁን ንጉስየው ሰራዊቱን ለማስደሰት የክራሱስን ጭንቅላት የሮም ወኪል አደረገው፡፡

"ወርቅ ስለምትወድ ወርቅ ጠጣ" ብሎ አጠጣው ይባላል፡፡ እንበል ሁለቱም ሆኖ ቢሆን የሚቻል ነው፡፡ ግን የቱ? ለማንኛውም ከፓርትያ ስንመለስ የሮማን አለም ለመጠቅለል የሚፋለሙ ፓምፔይና ቄሳር ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ጁሊየስ ቄሳር ሩቢኮን ወንዝ እንደተሻገረ ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ ፍጥነት ሮም ከተማን ለመያዝ እየመረሸም በሌላ በኩል ደግሞ በየቀኑ ለሴኔት እና ለፓምፔይ እውነተኛ የእርቅ የሰላም

መልእክቶችን እየላከ ነው። በበኩሉ ለሁሉቱም ዝግጁ ነው። እነሱ ይምረጡ። ውጊያ መረጡ። ጁሊየስ ቄሳርና ሰራዊቱ ወደ ሮማ ሲፈጥኑ በሚያልፉበት ሁሉ አገሬው ያቅፉቸዋል ስንቅ ያቀብላቸዋል መሳሪያና ወኔ ያለው ይቀላቀላቸዋል። እየበዙ እየጠነከሩ ይጓዛሉ።

ጁሊየስ ቄሳር ሰተት ብሎ ሮማ ይገባል። ፓምፔይ ራሱ ግሪክ አገር ነው ያለው። ጠላቶቹ ጁሊየስ ቄሳር ሮማ ይገባል ብለው ሲጠነቀቁ ቀርቶ ሰባት አመት አገረ ገዥ ሆኖ ከቆየበት ከሩቅ ጀርመን አገርንኳ ይንቀሳቀሳል አላሉም።

ሮማንና መላ የኢጣሊያ ምድርን ከያዘ በኋላ አሁንም የያዘው ይበቃዋል ሲባል ቢዘምትም ወደ ግሪክ ወደ ፓምፔይ ነው ሲባል -

በዚያ አስደንጋጭ ፍጥነቱ ወደ እስፓኝ መረሸ። የፓምፔይ ልጆች ናቸው ገዥዎችዋ የእስፓኝ። ተጋጠሙ። በዚህ በኩል ወንገዘ በዚህ በኩል እነሱ መሸገው የቆዩበት እሱ ግን የማያውቀው አገር። ቁጥራቸው ደሞ የትና የት! ከበቡት ያዙት አለቀለት ሲባል -

ጁሊየስ ቄሳርና የሰባት አመት ብስል ሰራዊቱ እነዚያ እንጨርሳቸዋለን ኮርተን ተንቀባረን ሲሉ የመሬትና የወንዝን አቀማመጥ አየና ጁሊየስ ቄሳር ቦታውን ወደ ጦር መሳሪያነት ለወጠ። ወንዙን እዚህ ገደቡት። ወደዚያ ፈሰሰ። የጦርነቱ ሁኔታ የተገላቢጦሽ ሆነ - የጁሊስ ቄሳር ሰራዊት ያኛውን ሰራዊት በወንዝና በእኔ ምን አውቃለሁ ከበቡት። መውጫ አልነበረውም ተማረከ። ጁሊየስ ቄሳር የፓምፔይ ልጆች እንደተሸነፉ ጠላት ሳይሆን እንዳገር ልጅ ተጣልቶ እንደታረቀ አስተናግዶ አሰናበታቸውና (እስፓኝ ግን በቁጥጥሩ ስር ናት) ሁልጊዜም በማይታመነው ፍጥነቱ ወደ ግሪክ አመራ ፓምፔይን ሊገጥመው።

ጥቅምት 28 ቀን 1986

## ፫

## የጁሊየስ ቄሳር ፍፃሜ

ጁሊየስ ቄሳር እስፓኝን ከፓምፔይ ልጆች ማርኮ ሲያበቃ በዚያው ፍጥነቱ ወደ ግሪክ መረሸ፣ ፓምፔይን ራሱን ሊገጥመው። ዘግይቶ የደረሰን ዜና። ጁሊየስ ቄሳር ከሰሜን አፍሪካ መልእክት ደረሰው። እንግዲህ ጁሊየስ ቄሳር ሩቢኮን ወንዝ ሊሻገር ሲዘጋጅ የቅርብ ታማኝ ረዳቱን እንዲህ ብሎ ልኮት ነበር። «እኔ ኢጣሊያን ቀጥሎም እስፓኝን ከያዝኩ ወደ ግሪክ እቀጥላለሁ። አንተ ከፊሉን ሰራዊት ይዘህ ወደ ሰሜን አፍሪካ ዝመት» መልእክቱ «እንዳዘዝከኝ ዘመትኩ። ሰሜን አፍሪካን ሳላስጨብጥህ በመሞቴ ከልብ ይቅርታ እለምንሀለሁ።» ምን አይነት መልእክት! ለጁሊየስ ቄሳር እየተዋጋህ ህይወትህን መሰዋት አይበቃም። ሰሜን አፍሪካንም ይዘህ ማስረከብ አለብህ። አለዚያ ነብስህ በሰላም አትወጣም የጁሊየስ ቄሳር ዘማች ስትሆን ያን ያህል ታመልከዋለህ። ምንስ ቢሆን የፍቅር ሴት አምላክ የሆነችው የውቢት ቬኑስ የልጅ ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አይደለም? ይላሉ የዘመኑ ሀረግ መዛዥ ሊቃውንት። በኛ አገር ረዥም ታሪክ ደሞ ዙፋኑን ይዘህ ግዛትህ ከፀና ሀረግ መዛዥ ሊቃውንት ከተፍ ይሉና በቀጥታ ከቀዳማዊ ምኒልክ መወለድክን ይመሰክሩልህና «አዬ» ሆነህ በታሪክ ማህደር ከሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ረድፍ ተራ ቁጥርህን ትይዛለህ» ይላሉ አንዳንድ ታሪክ አዋቂዎች።

በመጨረሻም ፓምፔይና ጁሊየስ ቄሳር ተጋጠሙ «የፋረሳላ ጦርነት»። የፓምፔይ ሰራዊት በብዛት እጅግ ቢበልጥም የቄሳር ሰራዊት በጀርመን አገር የሰባት አመት የውጊያ ልምድ አለው።

ፓምፔይ ድል ሆነና ወደ ግብፅ ሸሸ። ለፓምፔይ የደረሱት የጥቅል ብራና መልእክቶች በሁለት ትልልቅ የተቆለፉ ሳጥኖች ቀረቡለት ለጁሊየስ ቄሳር። የስንቱ ጉድ ሊወጣ ሆነ። ማነው የጁሊየስ ቄሳርን ምስጢሮች በስውር ለፓምፔይ የላከለት? እነማን ይሆኑ? ወዘተ...

እዚህ ላይ የጁሊየስ ቄሳር ሌላ ባህርይ ይወጣል፡፡ ሳጥኖቹን ያስከፍታል፡፡ እሳት አቀጣጥሉ ይላል፡፡ ያን ሁሉ የምስጢር ደብዳቤ ያቃጥለዋል አንድዋንም እንኳን ሳይከፍት፡፡

ጁሊየስ ቄሳር ሊጠረጠሩ በሚችሉ ቃላት ሳይሆን በማያወላውል በድርጊት እንዲህ አለ ‹‹ያለፈው አለፈ እስከ አሁን የርስ በርስ ውጊያ ላይ ነበርን፡፡ ከንግዲህ ግን አብረን የምንሰራው ብዙ ስራ ወደፊት ይጠብቀናል፡፡›› በኋላ ሲታይ እውነትም እንደዛ ሆነ፡፡

ለጊዜው ግን ጁሊየስ ቄሳር ፓምፔይን ወደ ግብፅ ተከተለው፡፡ ሌላ ሰራዊት ሰብስቦ ሌላ የርስ በርስ ጦርነት እንዳይቀጥል፡፡ ጁሊየስ ቄሳር የግብፅ ዋና ወደብ አሌክሳንደርያ ገና ከመድረሱ እወደድ እሾም እሸለም ባዮች በጌጣጌጥ ጨርቅ የተሸፈነ ሰፊ ሰሀን አቀረቡለት፡፡ ጨርቁን ገለጡት፡፡ የፓምፔይ ጭንቅላት እዚያ አይኑን አፍጥጧል፡፡ ጀግናው ጁሊየስ ቄሳር ገና ዛሬ ሞትን በማየት ደንግጦ ሽምቅቅ አለ፡፡ ወደዚያ በኩል እየዞረ አይኑን በካባው ሸፈነ፡፡ በሌላ እጁ ወደዚያ ውሰዱልኝ! አለ፡፡

በኋላ አመታት አልፈው ጁሊየስ ቄሳር የሮማዊው አለም ብቸኛ ፈላጭ ቆራጭ ገዥ በነሱ ቃልም ዲክቴተር ሆኖ በሴኔት (መማክርት) ከተሾመ በኋላ ከምክር ቤቱ አዳራሽ ሊገቡ ሲሉ ባለው በተንጣለለው የመማክርቱ መግቢያ መነጋገርያ መቆያ ክፍል የአማልክቱን የሚያክል የፓምፔይን ሀውልት አስቀረፀ፡፡ እና መላው ሮማዊው አለም የሚሰግድለት ሰውዩ ወደ መማክርቱ አዳራሽ ሊገባ ሲመጣም ሊሄድ ሲወጣም ለፓምፔይ ሀውልት ይሰግዳል፡፡ በኋላም የገደሉት እዛው ሀውልት ስር ነው፡፡

ከዚያ በፊት ግን አሁን ወደ ግብፅ እንመለሳለን፡፡ ግብፅ የስልጣኔ ምንጭ መሆኗ አልፎ አሁን የሮማ ስንዴ አቅራቢ እርሻ ከሆነች ብዙ አመታት አልፈዋል፡፡ ግብፅ የራሷ ንጉስ አላት ግን የሚነግሰው በሮማ መልካም ፈቃድ ነው፡፡ ጁሊየስ ቄሳር የስንዴ እርሻውን በሚታመን እጅ ለመተውና ፈጥኖ ወደ ሮማ ለመመለስ ነው ሀሳቡ፡፡

እና ምን ያጋጥመዋል? ወጣት የሆኑ ወንድምና እህት ለግብፅ ዙፋን እየተፋለሙ ነው። ጁሊየስ ቄሳር ለሴቲቱ አግዞ አነገሳት። ለጥቂት አመትም በእቅፏ ሮማን አስረሳችው። ስሟ ክሊዮፓትራ ይባል ነበር። እሷን ተሰናብቶ እግረ መንገዱን አንድ ሁለት ጦርነት ተዋግቶ ድል አድርጐ ወደ ሮማ ተመለሰና በአጭር ጊዜ ውስጥ እድሜ ልክ ባለሙሉ ስልጣን ፈላጭ ቆራጭ ወይም ዲክቴተር ሆኖ ከተሾመ በኋላ በሮማ ግዛቶች ብዙ መሻሻልን አስገኝቷል። ሰባት አመት የገዛቸው ጀርመኖች ከንግዲህ ቅኝ ግዛት መሆናቸው ቀርቶ ባለሙሉ መብት ሮማውያን ዜጐች ሆኑ። ለሌሎቹም ከምድረ ኢጣሊያ ውጪ ለነበሩ ታማኝ ቅኝ ግዛቶች ሮማዊ ዜግነት ተሰጣቸው። የግብርን ሁኔታ በጣም አሻሻለው። ቀን መቁጠሪያውን (ካላንደር) እንዲሻሻል አደረገ። አሁን ኢትዮጵያ የምትከተለው የዘመን አቆጣጠር ‹‹ጁሊየን›› ይባላል። ጁሊየስ ቄሳር ካላንደር ማለት ነው።

ተቀናቃኞቹ እንዳይነግስ ፈራን በሚል ሰበብ ሴራ ጠንስሰው ወደ ምክር ቤት ሊገባ ሲል ከበው በጩቤ ወግተው ገደሉት።

ጁሊየስ ቄሳር ወደር የለሽ ሮማዊ ነበር፤ ስለክብሩ ልዩ አስተያየት ነበረው። ሚስቱ ፓምፔያ ፑብሊዩስ ክሎድዮስ ከተባለ ሰው ጋር ስለተጠ ረጠረች ፈታት። እሱ'ኮ በበኩሉ አልጠረጠራትም። እንግዲያማ! ‹‹የቄሳር ሚስት ከጥርጣሬ በላይ መሆን አለባት›› አለ። እንግዲህ ሮማ በዙሪያዋ የሚገኙትን አገሮች አንድ በአንድ እየጠቀለለች ነው እንደዚያ የሰፋችው። አንድ ጄኔራል መናኛ ድል ሊያገኝ ይችላል። ከተወሰነ የጠላት ቁጥር በላይ በጦር ሜዳ ከገደለ ከተወሰነ ስፋት በላይ ግዛት ለሮማ ከጨመረላት እና ከተወሰነ የንብረት ዋጋ በላይ ከማረከ - እነዚህን ሶስት ነገሮች ካሟላ ሴኔት የድል ሰልፍ ያውጅለታል። ሮማ ውስጥ ዋናው ጎዳናው ላይ የእብነበረድ ቀስት ይገነባለትና በአልና ፌስታም ይደረግለታል።

ከሙሉ ሰራዊቱ ጋር በደማቅ ሰልፍ ወደ ከተማይቱ ይገባል ምርኮውን ሁሉ አስከትሎ። የሮማ ህዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ እያየ

እያደነቀው ሰልፉ በድል ቀስት ስር ያልፋል፡፡ እየዘመረ ጄኔራልየውን እያሞገሰ፡፡

የጄኔራልየው ድል ከዚህም በላይ ይገባዋል ከተባለ ድርብ ድል ይታወጅለታል፡፡ ለጁሊየስ ቄሳር ተደርጐ የማያውቅ አራት እጥፍ ድል ታወጀለት፡፡ ሰልፉ ሰልፍ አይምሰላችሁ፡፡ ጁሊየስ ቄሳርን ወታደሮቹ ከመጠን በላይ ይወዱት እንደነበረ እናስታውሳለንና መዝሙሩ እንዲህ ይል ነበር - ወታደሮቹ በጩኸትና በአስቂኝ ዜማ የሚዘምሩት (ጄኔራልየው አብሯቸው እየሳቀ)

‹‹መላጣው ሴተ ፊጅ አሳዳጅ መጣላችሁ -
ሮማውያን ሚስቶቻችሁን ደብቁ!››

ጁሊየስ ቄሳር ከተገደለ በኋላ ስሙ እጅግ ገነነ፤ እንዲሁም እጅግ ክቡር ሆነ፡፡ ከሱ በኋላ የመጡት የሮማዎች ነገስታት ማእረጋቸው ‹‹ቄሳር›› ሆነ ዘመናዊው የጀርመን ንጉስ ነገስት ‹‹ካይዘር›› ይባል ነበር - ቄሳር፡፡ እንዲሁም የሩስያ ነገስታት ‹‹ዛሩ›› ይባሉ ነበር - ቄሳር፡፡

ባይገርማችሁ ጁሊየስ ቄሳር እውነትና ተነባቢ ከሆኑት የላቲን ደራሲ አንዱ ነው ኧረ ስንቱ! ስንቱ! ስንቱ!

ዳሩ ምን ዋጋ አለው ጁሊየስ ቄሳርን ያህል ሰው እንኳን ሲሞት!?

**ህዳር 5 ቀን 1986**

# ሀረር

## ሀረር አንድ

ባቢሎን - ኢያሪኮ - ባግዳድ - ሀረር። የኛ ምድራዊ ክፍለ አለም ታላላቅ ከተሞች የስልጣኔ መዲናዎች። ኢየሩሳሌም - መካ መዲና - ሀረር። የኛ መንፈሳዊ አለም ታላላቅ ከተሞች። ሁለቱም ሰልፍ ውስጥ ሀረር አለችበት። ታላቅ እስላማዊም ከተማ ናት። እንዴት ቢሉ?...

እንደ ታላቅ ከተማ ሁሉ ሀረርም እንዴት እንደተመሰረተች የሚነገር አያሌ መቶ አመታት ወደኋላ የሚሄድ አስገራሚ ታሪክ አላት። ልዩ ከተማ ልዩ አመሰራረት። ጥንት ጥንት በትግራይ ውስጥ በደጉ ንጉስ በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት አንድ ብርቱ ትልቅ ሰው ጠላቶች በዙበት። ለጊዜው ቅናትና ምቀኝነት አስተባብሯቸው ሊያጠፉት ሆነ።

ሚስቱም ይህን በሚገባ ተገንዝባ በድብቅ አዋቂ ቤት ሄደች።

‹‹ቶሎ ከዚህ ካልጠፋችሁ ያጠፏችኋል። ወደዚህ ጉዞ ስትነሱ ለባልሽ ቅቤ አጠጪው። መንገድ ላይ አንበሳ ይበላዋል። ግን በልቶ አይጨርሰውም። አንበሳውን ፈርታችሁ ከየሸሻችሁበት ስትመለሱ ታያላችሁ። ባልሽ ሆድ ውስጥ የምታገኚውን ቅቤ ለልጆችሽ አጠጪያቸው።››

አጠጣቻቸው። አደጉ። ጀግና ሆኑ። አባታቸው ቅቤ ጠጥቶ የጀመረውን ጉዞ ያንኑ ቅቤ ከሱ ተቀብለው ጠጥተው ያንኑ ጉዞ

ወርሰውት ቀጠሉት። ተራው ሰው እርሻ ወይ ቤት ወይ ሌላ ነገር ይወርሳል። እነዚህ ግን ጉዞውን ወረሱ። ወደ ደቡባዊ ምስራቅ ሳይሆን አይቀርም የተጓዙት። ሄዱ ሄዱና አንድ አገር ደረሱ። ልክ እነሱን ሊቀበል የቆየ አገር መሰላቸው።

እመሀል ላይ የስድስት ሺህ ጫማ ከፍታ ያለው አገር ሰፊ ጋራ ይመስላል። ከስሩ ዙሪያ ዙሪያውን ቢመለከቱ ለጊዜው ለአደንም ቢሆን በኋላ ለእርሻም ቢሆን የሰጠ ነው። አነስተኛ ወንዞች እንደልብ ሜዳ በሜዳ። መልክአ ምድሩ ከዚያ ዝቅ ይላል። ቆላማ በረሀማ እየሆነ ይሄዳል።

እዚህ ያልኖርን የት ልንኖር ነው? ተባባሉ። ብቻ እኛ ትንሽ ማረስ ትንሽ መገንባት ቢኖርብን እንጂ እቴ ስፍራ ገነት አይደለችም'ንዴ። ባንድ ልብ ተስማሙ።

የጉዞአቸው መነሻ ሰበቡ የሰዎች ቅናትና ምቀኝነት ከፋት ይሁን'ንጂ መድረሻው አላማው ግን ያ ላይኛው ኃይል አዘጋጅቶላቸው ወደቆየው ስፍራ ይመጡ ዘንድ ነበር። ሀረርን ይቆረቁሩ ዘንድ ነበር። ፈጣሪ መምጫው አይታወቅም። በምድራዊት ገነት ይኖሩ ዘንድ በገዛ አገራቸው ምቀኛ አበዛባቸው የታሪኩን መጀመሪያ ምእራፍ ሲኖሩት መአት ላከባቸው ያሰኛል። የሚቀጥሉትን ምእራፎች ሲኖሯቸው ሲታይ ጊዜ ግን ለካ ያ መአት እውስጡ በረካ ተጠቅልሎበታል።

እነዚያ ካገር ያባረሩዋቸው ምቀኞች ዘወር ብለው ቢያዩ ጊዜ በጋራ ግንባር ፈጥረው ሊመቀኙት የሚችሉት ትልቅና ብርቱ ሰው የለም። "ኤጭ! ም'ናባቱንስ!" አሉና ዞረው እርስ በርስ መቀናናትና መመቀኛኘት እንደእባብ ውስጥ ውስጡን መነዳደፍ ቀጠሉ። እንተዋቸው። በኋላ ግራኝ አህመድ ከሀረር መጥቶ የእጃቸውን ይሰጣቸዋል።

"አፈጣጠኔ እንደ ጅብ

አመካከቴ እንደ አንበሳ

አጨካከኔ እንደ እናቱ መጣሁልህ በል ጠብቀኝ" ይላቸዋል ፍዳቸውን ሊያሳያቸው።

ለማንኛውም አንዳንዶቹ አደሬዎች በዚህ አኳኋን ከትግራይ መጡ ሲሉ ሌሎቹ እንዲህ ይላሉ፡፡ አደሬዎቹ የመጡት ቀይ ባህርን ተሻግሮ ከሚገኘው ሀድራማውት ከሚባለው አገር ሲሆን ሀረርንም የመሰረቷት በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነው፡፡ በዚህ ከሄድን ሀረርና እስልምና እኩያዎች ናቸው፡፡

ከመካ መዲና ቀጥሎ ሶስተኛዋ የእስልምና ቅድስት ከተማ ሀረር ትባላለች፡፡ ጀጎል ውስጥ ማለትም ጥንታዊቷ በካብ የተከበበችው ከተማ ውስጥ ዘጠና ዘጠኝ መስጊዶች አሉ፡፡ እነዚህም ሶስቱ የቅዱሳት ሴቶች መታሰቢያ መስጊዶች ናቸው፡፡ ጀጎልን አርባ አራት አውልያዎች ይጠብቋታል፡፡ እንዲሁም ሶስት መቶ ሰባ ሶስት አድባራት አሏት፡፡

"ሀረር የእስልምና ምንጭ መዲና ናት" ይላል አንድ የሀረር ሊቅ፡፡ "'አደሬ' ደሞ እንጋፋ ሴማዊ ነው ሀረር የአለም እምብርት ናት እንደዚሁም አምስቱ የሀረር በሮች አንዱ በር ከአንዱ አህጉር ያገናኟታል፡፡ መንፈሳዊ ግንኙነት፡፡" የምሩን ይሁን የቀልዱን አያስታውቅም፡፡

የጀጎል ገዥ አሚር ይባል ነበር፡፡ ደጋግ አሚሮችም ነበሩ፡፡ ነጁስ እርጉም አሚሮችም ነበሩ መሆን ያለበት ነው፡፡

አንዱ ደግና ብልህ አሚር አዋቂዎችን ያከብር ነበር ይባላል፡፡ ነፋስንም ድርቅ ሊመጣ ከሆነ አገር ጥሎ 'ሚጠፋ የወፍ ዘርንም እና ሌሎች ምልክቶችንም ማንበብ የሚችሉ አዋቂዎች መጡና የሚቀጥለው አመት ድርቅ ይሆናል አሉት፡፡ እንኳን ነገራችሁኝ አለ፡፡ በጥጋቡ አመት የ'ህል ግብርን እጥፍ አድርጎ አወጀና ሰበሰበ፡፡ ያ የድርቁ አመት እንደተፈራው ሲከተል ጊዜ ያ እጥፍ የነበረውን መልሶ ለህዝቡ አደለ የሚችሉትን እያስከፈለ ለማይችሉት በነፃ እየሰጠ ለሀረር ክፉውን ቀን አሳለፈላት፡፡

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ በሌላ ጊዜ ደሞ ጀጎል ውስጥ ሌላ አሚር ተወለደ፡፡ ይሄ እንግዲህ መች ነበር ብንል ከ1895 ኢ.ም. በፊት

አስር አመት ይሁን መቶ ወይም አምስት መቶ አመት ይሁን አልደረሰንበትም። በ1895 ጂቡቲንና አዲስ አበባን የሚያገናኘው ባቡር ድሬዳዋ መንደር ሲደርስ ጊዜ ድሬዳዋ መንደር መሆኑን ድንገት እርግፍ አድርጋ ተወችና ነጋዴ ከተማ ሆነች። ንግዱን ከሀረር ነጠቀቻት።

አሁን ሀረር ቅድስት መዲና እና ጀጎልን ዙሪያ አገር ታች ታቹን በመስኖ እያረሰች ወይም እያሳረሰች የምትኖር የቤት እመቤት ሆነች። ካመት አመት የሚያደርስ ማሽላ፣ ቡና፣ ጫት፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ ይመረታል። እዚያ ታች አገር። እዚያ ስናርስ ወይንም ስናሳርስ እንውልና አመሻሽ ላይ ወደ ጀጎል ሽቅብ እንወጣለን ዳገቱን። ከአምስቱ በር በአንዱ እንገባለን። ፀሀይ ጠልቃ ሲጨልም አምስቱም በር ይዘጋል። በአምስቱም በር ሌሊቱን ሙሉ ዘብ ጠባቂዎች ተመድበዋል።

ራስ መኮንን ከመጡ በኋላ በሳቸው ዘመን በራስ ተፈሪ ዘመን እና በልጃቸው በልኡል መኮንን መስፍን ሀረር ዘመን ጀጎል ዙሪያ ሀረር ተለጣፊ ከተማ ሆና አደገች።

ሀረር የጦፈች የንግድ መናኸሪያ በነበረችበት ዘመን ክፉ አሚር ነገሰባት። ስግብግብ አባሰብስብ በመሆኑ ህዝቡን በግብር አማቀቀው። ህዝቡን ስንል አንድ አርባ ሀምሳ ሺህ የሚሆን አደሬን ማለታችን ነው። ከዚህም በላይ ሀረርን የባርያ ንግድ ከተማ አደረጋት። ሱማሌውንስ፣ ኢሳውንስ፣ አፋሩንስ እየፈነገሉ ሲያመጡለት እሱ በብዙ ትርፍ ለአረቦች ይሸጥላቸዋል። እንዲህ አርጎ ቅድስቲቱን ሀረር የከይሲ ስራ ቦታ አደረጋት።

ወደኋላ ጊዜ የሀረር አሚሮች ልዩ አይነት ገዥ ሆኑ። ሰራዊት የሌለው ንጉስ ከውጭ ሀይሎች ጋር በስምምነት እንጂ በጦርነት መገናኘት ቀረ። የጀጎል ቀጥቃጮች አካፋ ማጭድ ማረሻ ይሰራሉ እንጂ ጦር ጎራዴ ሰይፍ አይሰሩም።

በ1880 ኢ.ም ያጤ ምኒልክ ጦር መጣ። ከጀጎል ወጣ ብሎ ሰፈረ። አሚር ብር አገባለሁ አለ ስምምነቱ ፀደቀ። ወታደሩ ጀጎል አልገባም።

በኋላ ራስ መኮንን መጡ። ይህ ሁሉ ሲሆን አደሬ ጆጎል ውስጥ ስራውንና ኑሮውን ልክ እንደ ድሮው ካደረገ በኋላ ግን እንጃ።

ኧረ'ንጃ!

የሀረር ልጆች የሪሀን ሽታ ይናፍቃቸዋል። ሀረር ሪሀን ሪሀን ትሸታለች። ሪሀን ሪሀን የሀረር ቅጠል ናት። አቤት ሽታዋ ደስ ማለቱ!

ህዳር 12 ቀን 1986

## ፪

## ሀረር ሁለት

እሰይ! ሪሀን ቅጠል ሸተተን። ሀረር ቅድስት መዲና ደረስን ማለት ነው። ‹‹አማን ተኸ! አማን አብሸር›› ጊዜውን መርጠን በሺዋሊድ ነው የመጣነው። የገባነውም በኤረር በር ነው። ከረመዳን ወር በኋላ ሸዋል የሚባለው አስረኛ ወር ከወሩም በስምንተኛው ቀን ሸዋሊድ ስነ ስርአት ይከበራል - በሀረር ብቻ።

በረመዳን ወር ውስጥ አማኝ በልዩ ልዩ ምክንያት ጥቂት ቀናትን ከፆሙ ሊያጎድል ይችላል። ወይ ጉዞ ላይ በመሆኑ፣ ወይ የወር አበባ ላይ በመሆኑዋ፣ ወይ በሆነ በሽታ ምክንያት መፆም አልተቻለም። እነዚያን ቀኖች የረመዳንን ፆም አሟልተው ለፆሙት ፆሙ ከተፈታ በኋላ ላንደሉት አማኞች የሸዋል ወር የመጀመሪያው ስድስት የፆም ቀናት ሆኖ ይቀጥላል። ማካካሻ ፆማቸውን ይፆሙበታል።

የዚህ የተጨማሪ ፆም ፍፃሜ በስምንተኛው ቀን ይከበራል። በልዩ ድምቀት የሚከበረው ኤረር በር ነው። ድምቀት የሚሰጠው ደግሞ ነቢ ጋር ነው። ነቢ ጋር ቃሉ ‹‹የነቢዩ ቤት›› ማለት ሲሆን በአምስቱ በር አምስት ነቢ ጋር ይገኛል።

ነቢጋር ውስጥ አርብ፣ አርብ ዝክር ይደረጋል ማለትም አማኞች ተሰብስበው ነቢዩን ይዘክሩታል ያስታውሱታል፡፡ ስራውንም፣ ቃሉንም፣ ያስታውሳሉ ነብሳቸውን ለጀነት ያዘጋጁታል፡፡

ኤረር በር ባለው ነቢጋር ስነ ስርአቱ ለሶስት ቀን ይቀጥላል፡፡ በሸዋል (ባስረኛው) ወር በስድስተኛው ቀን የጀመረ በርጫ እየተደረገ አታሞ እየተመታ የነቢዩ መሀመድ (ሰአወ) የህይወት ታሪክ ይነገራል፡፡ በግጥም ሊሆን ይችላል፡፡ እጣኑም ሰንደሉም መንዙማውም፡፡

ስለነቢዩና ስለሌሎች ቅዱሳን የሚዘመር ነው፡፡ ቅኝቱ በአታሞ ምት ነው፡፡

የኤረር በር አድባሩ ‹‹ሸላሚ አህመድ›› ይባላል ሸላሚ አህመድ፡፡ ለምን ይህ ሁሉ ፆም ፀሎት? ‹‹ልመና ፀሎት የሚመጣውን አደጋ ያረግበዋል ለዚህ ነው ሀረር እስከ አሁን የኖረችው›› ይባላል አደሬው ሊቅ ከቢር ይሉታል እነሱ፡፡

ሀረርን ጀጎል አጥርዋን ሪህን ጠረንዋ ካደረጉ -- ከአብዮታዊ ሁሉን አፍራሽ ዘመን በኋላ አላየኋትም እንጂ በጃንሆይ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት አይቻት ነበር፡፡ አስራ አምስት ቀን ሙሉ ኖርኩ ሀረር ውስጥ የሀረር ልጆች በቤታቸው እያስተናገዱኝ፡፡ ማስተናገዱን ያውቁበታል፡፡

እና ምን አየሁ? ሀረር ህያው ስልጣኔ መሆኗን አየሁ፡፡ የሰው ልጅ ስልጣኔ የማሽን ሳይሆን ወይም የቢሮክራሲ፡፡ ከማህፀን እስከ መቃብር ያለችውን አጭር ግን አስጨናቂ ጉዞ ስንሄዳት የፈረንጆቹን ሳስታውስ ለነሱ አቴንስ የኛን የጥንት ስመለከት ሀረር የሰው ልጅ ህያው ስልጣኔ ናቸው፡፡ ምነው ሄራክለስ በነበረባት አቴንስ ተወልጄ በነበር ይላሉ ብዙዎቹ ፈረንጆች፡፡

እኔም እንዲህ እላለሁ - ለሚፈልጉ ሰዎች እንደገና መወለድ የሚቻል ቢሆን እኔ ዘልዬ በዚያች ላስራ አምስት ቀን ባየኋት ሀረር ነበር የምወለደው፡፡ ከተወለድኩባት በኋላ ግን ዘጠና ዘጠኝ አመት ኖሬባት ወደ

አባቶቼ እንቅልፍ እስክሄድ ድረስ ወላ አንድ ደርግ ወላ አንድ አብዮት የለም። አስጠንቅቀናል።

እዚያ ለመኖር ለምን መረጥኩ? ሀረር ልጅዋን ከተወለደ አንስቶ እስኪሞት ድረስ ትኮተኩተዋለች ትንከባከበዋለች።

አደሬ ገና ሲወለድ እናቱን እንኳን በደህና ተገላገልሽ ሊሏት ከሚመጡት ሰዎች አንድ የስጋ ዘመድ ያልሆነ ብዙ ጊዜም ሽማግሌ የሆነ ህፃኑን ያየውና ይወደዋል። ‹‹ይህ ልጅ የኛ ነው እንደኛ ነብር ነው!›› ይላል እንደኛ እርግብ ነው፣ ወይ ሌላ ሊል ይችላል። የሱ ልጅ ያደርገዋል። እንደሁለተኛ አባት ይሆነዋል። እድገቱን ይከታተላል። ቁርአን ትምህርት ቤት ሲገባ አስተማሪውን ይጠይቃል። ‹‹ይህ ልጅ ትምህርቱ እንዴት ነው?››

አደሬ እያደገ ሲሄድ የጀምአ አባል ይሆናል። ጀምአ በግምት ከአምስት እስከ አስር አባላት ይኖሩታል። አብሮ አደግ ጓደኛሞች ናቸው ለበርጫ አብረው ነው፣ ለኑሮም አብረው ነው። እንበል አንዳቸው ንግዱ እምቢ ብሎታል። ሌሎች የጀምአው አባላት በየበኩላቸው እንደየአቅ ማቸው እቃዎች ገዝተው ሱቁን ይሞሉለታል። እቃዎቹን ሸጦ በትርፉ ንግዱን ይጠግናልበተቻለ ፍጥነት ዋናቸውን ለጓደኞቹ ይመልስላቸዋል።

መላቅ የአንድ ቶያ (ሰፈር) ሀላፊ ነው። ቃዲ (ዳኛ) የፈረደውን መላቅ ያስፈፅማል ለፍርድ ያቀርባል። መላቅ ጧት ጧት ከጣራ ላይ ወይም ከሆነ ከፍተኛ ስፍራ ላይ ቆሞ ቶያውን ዙሪያውን ይመለከታል። አንድ ቤት አይጨስም። መላቅ ቀስ ብሎ ያጠያይቃል። ‹‹የእነ እገሌ ቤት አይጨስምሳ! ምን ሆነዋል?›› ‹‹ተቸግረዋል።›› መላቅ ካላቸው ሰዎች መዋጮ ይጠይቅላቸዋል። እስከሚቀጥለው አዝመራ የሚያደርስ ማሽላና ሌላም እህል ለዘር ጭምር ይሰጣቸዋል። ህብረተሰቡን እንዲህ በመላ ይጠብቀዋል።

ከቢር ምሁር ነው። ሰላማዊ ሰው ነው። ተጫዋች፣ ብልህ መላ የሚያመጣ። ወጣት አደሬ በሳምንት የተወሰነ ቀን የሀይማኖት መፅሀፎቹን ይዞ ወደ ከቢር ቤት ይሄዳል። ከቢር ቁርአንንም ሌሎችንም

መፅሀፎች ያስተምረዋል፣ እንደወጣቱ ተሰጥዎ። ስለባህልም ያስተምረዋል በተረት፣ በምሳሌ በጨዋታ ሊሆንም ይችላል።

አንድ ሰው ከቢር የሚሆነው በትምህርት ነው። ሸሪፍ የሚሆነው ግን በዘር ነው። ሸሪፍ ማለት የነቢዩ መሀመድ (ሰአወ) ዘር የሆነ ሰው ነው። ይከበራል።

በሀረር ሽማግሌ በጣም ይከበራል። ሽማግሌ ያገር ጠባቂ ነው። የተጣላ ማስታረቅ ብቻ አይደለም። አዝማሚያውን አይቶ ጠብ ሊመጣ ሲል ሊያስቀረው ይችላል። በመምከር። የሽማግሌን ምክር ይቀበሏል።

ሰው ሲሞት ሀብታም ሳይል ደሀ ሽማግሌዎች ይመጡና ለሶስት ቀን ቁርአን ያነሳሉ። ለሟች ነብስ ፀሎት ያረጋሉ።

ሞት የወንዶች ጉዳይ ነው። ሬሳ ወስደው ፀሎት አድርገው ይቀብሩታል እንጂ ለቅሶ ዋይታ የለም። እናቱ የሞተችበት ስቅስቅ ብሎ ቢያለቅስ በግሉ እንጂ ማህበራዊ ለቅሶ የለም።

ኤጭ! የምን ስለሞት ማውራት ነው? ስለአውዘል ቀርነይኒ አናወራም? ከእለታት አንድ ቀን አሚር አውዘል ቀርነይኒ ቀንድ አበቀለ። በጥምጥሙ ደበቀው። አንድ ቀን ግን ፀጉር ቆራጩ ቀንዱን አየበት።

‹‹ስለዚህ ነገር ከእኔና ከአንተ በቀር የሚያውቅ የለም ትናገርና ወዮልህ!››

‹‹ኧረ እኔ አልናገርም›› ይላል ሰውየው ግን መናገር አስፈለገው። ለሰው እንዳይናገር መጥፊያው ይሆናል፤ ግን ወሬው ሆዱን ነፋው። አልቻለም። በመጨረሻም ከከተማ ወጥቶ ርቆ ሄዶ መሬት ቆፍሮ ለመሬቷ ነገራት ‹‹አውዘል ቀርነይኒ ቀንድ አብቅሏል!›› ይህን ተንፍሶ ወደ ጉዳዩ ሄደ። እዚያች ስፍራ ዋንዛ ዛፍ በቀለ። ጊዜው ሲደርስ ተቆረጠና ከበሮ ሆነ። ሰዎች ከበሮውን ሲመቱት ‹‹አውዘል ቀርነይኒ ቀንድ አብቅሏል!›› ይላል

ወይ አውዘል ቀርነይኒ!

ህዳር 19 ቀን 1986

# ፫

# ሀረር ሶስት

## የግርማ ለማ አሪፍ ማስተካከያ

‹‹አውዘል ቀርነይኒ ቀንድ አበቀለ ያበቀለውን ቀንድ ፀጉር ቆራጩ አየበት ትናገርና ወዮልህ ተባባሉ... ወዘተ›› አለ ጋሽ ስብሀት በእግረ መንገዱ፡፡

እኔ ግን እቃወማለሁ! እንዳውም በጭራሽ ለምን አትሉኝም ጋሽ ስብሀት ሀቋን ቁጭ አላረገማ፡፡ ሀቁ እንዴት ነው? ሀቁማ እንዲህ ነዋ!

አውዘል ቀርነይኒ ስለአላህ መንግስት እየሰበኩ፣ እየሰበኩ ፈጣሪን አገለገሉ፡፡ ኋላ ጊዜ እድሜያቸው እየገፋ ጉልበታቸው እየደከመ ሰውነታቸው እምቢ ቢላቸው ጡረታ ልውጣ ሲሉ አመለከቱ፡፡ ለማን? ለፈጣሪ፡፡ ፈጣሪም የአውዘል ቀርነይኒን ቅን አገልግሎት ተመልክቶ ‹‹የጡረታ አበልህ ምን ይሁንልህ?›› ሲል ጠየቃቸው የሰው ላብ በከንቱ የማያስቀረው ፈጣሪ! አውዘል ቀርነይኒ ደግሞ በሰባቱም ሰማያት ባለውና ቢዛቅ! ቢዛቅ! ከማያልቀው ከዚያ ሁሉ የአላህ ራህመት ስንትና ስንት ነገር ሊጠይቁና ሊያገኙ ሲችሉ

‹‹የደከመ ሰውነቴን አነቃቅቼ ተከታዮቼን አስተምር ዘንድ አላህንም ጠዋት ማታ አመሰግን ዘንድ ባዶ አፌን አይሆንልኝምና ይህቺን ቀምበጥ መርቀህ ስጠኝ›› አሉታ! (እድሜ ለአውዘል ቀርነይኒ) ይሄው ጉዳዩ ለኛም ተረፈ፡፡ ዛሬም ቢሆን የሀረር ሰዎች ጡሀራ አድርገው ተመቻችተውና አጫጭሰው ጫቱን ለመፍታት ሲጀምሩ ከአፋቸው የሚወጣው የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ‹‹አውዘል ቀርነይኒ አላህ የርሀም ነቢይ ከዲር አላይ ሰላም›› የሚል ነው፡፡ ልብ አድርግ! ጫት ይዘህ የአውዘል ቀርነይኒን ስም ስትጠራ በግራ እጅህ በኩል ክንድህን ደገፍ ማለት አለብህ፤ አለዚያ ኩንታል ሙሉ ጫት ስትቅም ብትውል አትመረቅንማ! ደግሞ ጫት ስትተክል ወደ ግራ ጋደል አድርገህ መሆኑን አትርሳ!

ያለዚያ አይበቅልልህም፡፡ ከንቱ እንዳትደክም! ለምን ብትል አውዘል ቀርነይኒ ጫቱን ሲቀበሉ በግራ ክንዳቸው በኩል ጋደል ብለው ተቀምጠው ስለነበር ነው፡፡ ወይ አውዘል ቀርነይኒ!

አውዘል ቀርነይኒ ቀንድ አላበቀሉም እንጂ ብዙ ብዙ አጃኢቦች ሰርተዋል፡፡ አንድ ቀን ምን አደረጉ መሰለህ እሳቸውን ተከትለው በየቦታው እየተዘዋወሩ ትምህርታቸውን ሲቀስሙ የነበሩ ቃልቾች ረጅምና ማለቂያ የሌለው ጉዞ አድርገው ሲደክማቸው ጊዜ ‹ሀኪም ጋራ› እሚባለው ቦታ ላይ ሲደርሱ የሶላት ጊዜ ደረሰባቸው፤ ውሀ የላቸውም ነበርና ጡሀራ ለማድረግ አልተመቸም፡፡ ስለዚህ ያ ሁሉ ተከታይ አውዘል ቀርነይኒ ላይ አፈጠጠባቸው፡፡ ውሀ ደግሞ ያለው እዚያ ታች ነበር ሶፊ! አሁን የሀረር ቢራ ፋብሪካ የተተከለበት ስፍራ ላይ! ታድያ እዚያ ታች ድረስ የማን ጉልበት ይሄድ! በዚህ ጊዜ ሁሉም ሰው የውሀ መያዣ ቅሉን በተርታ እንዲያሰልፍ ተነገረውና እንደተባለው አደረገ፡፡ አውዘል ቀርነይኒ ጫታቸውን ቅመው ቅሎቹ በገዛ ራሳቸው እታች ወርደው ውሀ ተሞልተው እንዲመጡ ወሰኑባቸው! ምስኪኖቹ ቅሎችም ከዚያ ተራራ ላይ ያለማንም ሰው ርዳታ በአውዘል ቀርነይኒ ምርቃትና ትእዛዝ ብቻ እታች ደርሰው ውሀ ተሞልተው መጡ፡፡ ደግሞ ይሄንን ሀሰት ነው ትል ይሆናል! እኔ ምን ቸገረኝ የምትኮነነው ራስህ! ኋላ ነብስህ ከላይና ከታች እንደ ገና ዳቦ እሳት ሲነድባት እዬዬ ብትል የሚደርስልህ የለም፡፡ በዚህ ላይ የአውዘል ቀርነይኒ ከራማ እንዲህ በቀላሉ የሚለቅህ እንዳይመስልህ! በሄድክበት እየተከተለ ነው የሚጫወትብህ፡፡ ቢፈልግ እንደ ኳስ! ቢሻው እንደ ከረምቦላ!... ቢያሻው እንደ ደመና...! ወዮልህ ውርድ ከራሴ፡፡

አንድ ጊዜ ደግሞ አውዘል ቀርነይኒ ምን አደረጉ መሰለህ? መቼም ያው ይባላል ነው! አንዲት አህያ ጭነት በዝቶባት ኑሮዋ ቢመራት ጊዜ ወደሳቸው ሄዳ ብሶቷን አሰማች፡፡ ጌታዋ ጠዋት ማታ እየጫነ ከእንስሳት ሁሉ በታች አድርጐ ረግጦ ጉልበቷን በዘበዛት፡፡ ጫማ አይገዛላት! ወይ አሞሌ አያልሳት፡፡ እንዲያው በጭነት ብቻ ቁም ስቅሏን አሳያት፡፡ አህያይቱ ለእሳቸው አቤት ብላ ብሶቷን በእምባ አጅባ ብትነግራቸው

ጌታዋን በፋክስ ጠየቁት ‹‹ምነው ጃል! ይህን ያህል የምታስመርራት? እዘንላት እንጂ›› ቢሉት ‹‹አህያ ለጭነት መፈጠሩን አያወቁም? እንዴት እዘንላት ይሉኛል? ላም አይደለች አልቤ ወተቷን አልጠጣ እጭናታለሁ ምነው አልጭናት?›› ቢላቸው የአህያዋን በጭነት መጎዳት የጌታዋንም የወተት ችግር ተረድተው አህያዋን ላም አደረጓት ይባላል። መቸም የማይባልና ያልተባለ ነገር የለም። አውዘል ቀርነይኒ ይህንን አላደረጉም በማለት ገሚሱ ሼህ ግምባሩ ናቸው ሲል ከፊሉም የለም•ይህን ተአምር የሰሩ ሼህ ጨሌ ናቸው ይላል። ሼህ አሚድ ናቸው የሚሉም አሉ። ጃኖ ደሞ በመንዙማዋ ይህንኑ ታሪክ (ቂሳ) ሳትጠቅሰው አልቀረችም።

አውዘል ቀርነይኒ ቀንድ የላቸውም። ከፀሀይ መውጫ እስከ ፀሀይ መግቢያ ባለው አለም ሁሉ ያለውን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩበት አንቴና ነገር ነበራቸው ይባላል። ‹ቀርን› ማለት አንድ መቶ አመት (ምእተ አመት) ማለት ነው'ንጂ ቀንድ አይደለም። አሉ! እሳቸው በምድር የነበሩትን ሰይጣናትንና ጉግማንጉግ ሁሉ ሰብስበው ከመሬት በታች ቀብረዋቸዋል። ሰይጣናቱም መሬቱን ቆፍረው እንዳይወጡና ሰውን እንዳያሳስቱ ፈጣሪ በሰጣቸው ጥበብ ብረት አቅልጠው ምድሪቱን ደፈኑባቸው። እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ መሬት ውስጥ እንዲኖሩ የፈረዱት እሳቸው ናቸው። ከፍተኛ ታሪክ ያላቸው ታላቅ ወሊይ ናቸው። ዋዛ ሰው እንዳይመስሉህ። መቼም ያው ይባላል አይደል? ይባላል።

•

ህዳር 26 ቀን 1986

# ፬

# ሀረር አራት

ስለ ሀረር የምንጥፍላችሁን አብዛኛውን የሚነግረን የጀጎልን ህይወት በስእል ለአለም በማሳወቅ ላይ የሚገኘው ጥበበ ተርፋ ነው። ጥበበ ንፁህ የጀጎል ልጅ ነው። አደሬ ግን አይደለም። ግማሽ ቆቱ፣ ግማሽ አማራ

ነው፡፡ ንፁህ የሀረር ልጅ ለመሆን ግን አደሬ መሆን አያሻም፡፡ ጥበበ'ንኳ ጀጎል ተወልዶ ነው ያደገው ሼክ አባድር አሉላችሁ አይደለም፡፡ ይልቅ! አንደኛ ንፁህ የሀረር ልጅ የሚባል ቢኖር ሼህ አባድር ናቸው ግን እዚያ እንኳን አልተወለዱም፡፡ እንዲያውም ወደ ሀረር የመጡት ካደጉ አዋቂ ከሆኑ በኂላ ነው፡፡ መጡ፡፡ ሀረርን ከጥፋት አዳኗት፡፡ እና የአባድር ከተማ ተባለች፡፡ እንደምን ቢሉ --

አረብ አገር ውስጥ አብረው የሚኖሩ አርባ የአላህ አገልጋዮች ነበሩ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ተነሱና ቀይ ባህርን ተሻግረው ወደ ሀረር መጡ፡፡ እና ምን አጋጠማቸው? በሀረርና ዙሪያዋ ኢብሊስ (ሸይጣን) ነግሷል፣ እንደልቡ ይንጎራደዳል፣ ይንጎማለላል ይንፈላሰሳል፣ ይንቀባረራል፡፡ ኧረ በዚያ አካባቢ እንደዚያን ወቅት ቀንቶት አያውቅም ዘመነ ቀይ ሽብር መጥታ እንደገና እስክታሸረው ድረስ፡፡ አርባው እዚያ ሲደርሱ ሞት ረክሶ ጥንቡን ጥሏል! አለች ቅኔ!

ሀረርና ዙርያዋ አደሬዎች ቆቱዎችና ሱማሌዎች ይኖራሉ፤ መኖሩ መኖር ከተባለ፡፡ እንዴት መኖር አይባልም? ምን ልበላችሁ? አደሬው ዋና ስራውና ደስታው ቆቱና ሱማሌ መግደል ሆነ፡፡ ቆቱው በበኩሉ አደሬንና ሱማሌን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ተነስቷል፡፡ አሁንም ቅኔ!? እንደዚሁም ሱማሌው ቆቱና አደሬን ካላጠፋ መኖር የሚቻለው አልመሰለውም፡፡ እና ለሶስት ተፋጁላችኂ! መቸስ ኢብሊስ ከደስታው ብዛት እየተቁነጠነጠ ‹ፍጅታቸውን በዚህ ሂደት ከቀጠሉ ለመጨራረስ ስንት አመት ይቀራቸ ዋል?› የሚል ጥያቄ ኮምፒውተር ውስጥ ጨመረ፡፡ ነበረው'ንጂ! እንኳን ሸይጣንና ሰው እንኳን ኮምፒውተር ፈጥሮ እየሰራበት ይገኛል አይደለም እንዴ? ሰላሳ አመት ቀራቸው አለ ኮምፒውተር፡፡ እሱስ እውነቱን ነበር፡፡ ዳሩ ምን ይሆናል? እነ ሼህ አባድር ደረሱ ገና ሲያያቸው ኢብሊስ ራስ ምታቱ ተነሳበታ፡፡ ቀጥሎ ጨጓራው ተቀሰቀሰበት፡፡ ደም አስቀመጠው፡፡ ከዚህ ሲኦል የሚደርሱ ህመሞች ውስጡ ፈሉበት፡፡

ወይ እነ ሼህ አባድር! ኢብሊስ ገና ሲያያቸው አላህ ሊደቁሰው አርባ ክንዱን እንደላከበት አወቀ፡፡

አርባ ቅዱሳን ብቅ እንዳሉ ምድረ አደሬ በደስታና በተስፋ ተሞላ፡፡ ሙሉ መስተንግዶ አስተናገዳቸው፡፡ ‹‹እናንተ አስተምሩንና አላህ የላካችሁን ስሩ እህል ውሀውንና መጠለያውን እኛ እናቀርብላችኋለን›› አሉዋቸው ጀጎሎች፡፡

እነ ሼህ አባድር ግን ባህል ያቆየውን የሶስት ቀን መስተንግዶ ከተስተናገዱ በኋላ እንዲህ አሉ ‹‹ልናስተምራችሁ ተልከናል፡፡ ግን አባት እናታችን አደምና ሀዋ (አዳምና ሄዋን) ያወረሱን አንዱ ትእዛዝ ‹እንጀራህን በፊትህ ወዝ ትበላለህ› ነው፡፡ ከንግዲህ እንደማንም ሰው ሰርተን የምንበላ ነን››

እንዳሉትም ሆነ፡፡ አንዳቸው አናጢ ነው፣ አንዳቸው ጫማ ሰፊ፣ አንዳቸው አንጥረኛ ወዘተ እና ዛድያላችሁ... ‹‹ወዲህ ለመምጣት ከምድረ አረብ በሚነቀሉበት ጊዜ አርባውም እኩል ነበሩ፡፡ ማለት አለቃ አልነበራቸውም፡፡ አሁን ግን ኢብሊስን ድባቅ ለመምታት ከፈለጉ ከመሀላቸው አንዳቸውን አበጋዝ አዛዥ ጄኔራል መሾም ይኖርባቸዋል፡፡

ማንን? ብቁ የሆነውን ነዋ! ብቁ የሆነው እንዴት ይታወቅ? በሙከራ ወይ በፈተና ወይ በውድድር አያሌ ፈተናዎች ነበሩ ይባላል፡፡ በሁሉም አባድር አንደኛ ወጣ፡፡ ከፈተናዎቹ አንዷ ብቻ ናት ለጊዜው የደረሰችን፡፡ እነሆ!

እነ አባድር አርባ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው በሄዱበት ሁለት የውሀ ቅል አይለያቸውም - አንዱ ለሚጠጣ ውሀ አንዱ በቀን አምስት ጊዜ ለሚደረገው ሶላት (ስግደትና ፀሎት) መታጠቢያ፡፡ ጣሂር (ንፁህ) ካልሆንክ ሶላትህ ከንቱ ልፋት ይሆናል፡፡

እንግዲህ አርባው እቤት ውስጥ ተሰብስበዋል፡፡ አንዳቸው የራሱን ሁለት ቅል ወለሉ ላይ ትቶ ይወጣል፤ የተቀሩት ሰላሳ ዘጠኝ ሁለት፣ ሁለት ቅላቸውን ወለሉ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ ሰማንያ በሉኝ፡፡ ውጭ ያለውን ግባ ይሉታል፡፡ ሰማንያውን ቅል እያነሳህ ለየባለቤቱ ስጥ ይሉታል፡፡ ሰማንያውም ቅል ይመሳሰላል፡፡ እንኳን የሌሎቹን ልታውቅ የራስህንም ከሰማንያው ለይተህ ማወቅ ያስቸግራል፡፡

አባድር ተራውን ውጭ ቆይቶ ሲገባ ያለአንዳች ማመንታት ስማንያውንም ቅል ለየባለቤቱ ሰጠ፡፡ ሼህ አባድር ልዩ ሰው መሆናቸው ተገለጠ፡፡

ሼህ አባድር የአደሬን የቆቱንና የሱማሌን ሽማግሌዎችና ትላልቅ ሰዎች እንዲህ አሉዋቸው ‹‹አሁን እናንተን የሚያፋቅር እንጂ የሚያጣላ ምን ምክንያት ይገኛል? አደሬ ከተሜ ነው፣ ቆቱ ገበሬ ነው፣ ሱማሌ አርብቶ አደር ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ለመገበያየት ለመጠቃቀም ያመቻል፡፡ አደሬው ሸማውን ማረሻውን እና ሌላ ምርቱን ለገበያ ያመጣል፡፡ ገበሬው ቆቱም ማሽላውንና ሌላ የእርሻ ምርቱን ለገበያ ያቀርባል፡፡ ከተሜው አደሬም አርብቶ አደሩ ሱማሌም ይገዙታል፡፡ አርብቶ አደሩ በበኩሉ እጣኑን፣ ስሌኑንና ከብቱን የመሳሰለ ምርቱን ለገበያ ያቀርባል፡፡ ከተሜውም ገበሬውም ይገዙታል፡፡ ይህ የተለያየ አይነት ኑሮ እንዴት ብሎ ይጋጫል?››

‹‹ሱማሌም ብትሆን ከሌላ አርብቶ አደር ጋር በውሀ ጉድጓድ ወይ በግጦሽ የተነሳ ልትጋጭ ትችላለህ 'ንጂ ገበሬውስ ምን ሲፈልግብህ? አንተስ ምን ስትፈልግበት? ከተሜውስ ምን ሲሻማህ? አንተስ ምን ስትሻማው? ምንም፡፡ ቆቱም ብትሆን ከሌላ አራሽ ህዝብ ጋር በመሬት የተነሳ ልትጋጭ ትችል እንደሆነ ነው'ንጂ ዘላኑስ ሆነ ከተሜው የትኛውን ጥቅምህን ተሻምተውህ ነው የምትጠላቸው? አደሬው እንደዚሁ ከሌላ ከተማ ህዝብ ጋር በገበያ ሽሚያ የመጣ ትጣላ እንደሆነ ነው'ንጂ ገበሬውና ዘላኑ በምን ደርሰውብህ? አንተስ በምን ደርሰህባቸው?››

ሼህ አባድር አንድ እውነት በተናገሩ ቁጥር አድማጮቻቸው እያመኑና እየተገረሙ ‹አዎን! እውነት'ንጂ› በሚል አይነት ራሳቸውን ይነቀንቃሉ፡፡ ሼህ አባድር ቀጠሉ፡፡ ‹‹እናንተ'ኮ ሽማግሌዎችና አዋቂዎች ናችሁ፡፡ የህዝቡ መሪዎች ናችሁ፡፡ አላህ የሾማችሁ ህዝባችሁን ትጠብቁ ዘንድ 'ንጂ ለማያስፈልግ እልህ ታፋጁት ዘንድ አይደለም፡፡›› መሪዎች ልባቸው በእፍረት እንደተሸማቀቀች ለመገመት እንችላለን፡፡

‹‹በሉ አሁን በአላህ ስም ታረቁ፡፡››

በዚህ አካኋን ሼህ አባድር በሀረርና ዙሪያዋ ሰላም አወረዱ፡፡ ሀረር ገበያ መጋላ ደራች፡፡ ኢብሊስ ከዚያ አካባቢ ድራሹ ጠፋ፣ እሱ ግን አድራሻ ለውጬ ነው'ንጂ አልጠፋሁም ባይ ነው፡፡

ግና አንዳንድ ለኢብሊስ ያደሩ ሰዎች አሉ፡፡ ህዝብ ደም ሲፋሰስ የሚበለፅጉና የሚረኩ፡፡ እነዚህን ወገኖች ሼህ አባድር አልወደዱላቸውም፣ ሊያጠፏቸው ተነሱ፡፡ አንድ ቀን ሼህ አባድር ከድሬዳዋ በኩል ወደ ሀረር ለመሄድ የደንገጎን ጋራ ሲወጡ ሳለ ጠላቶቻቸው እላይ አድፍጠው ቆይተው ናዳ ለቀቁባቸው፡፡ ሼህ አባድር ድምፁን ሰምተው ቀና ብለው ቢያዩ አንድ ትልቅ አለት ሊጨፈልቃቸው እየወረደ ነው፡፡ እጃቸውን አነሱና አለቱን ቁም አሉት፡፡ በዚያች ቅፅበት በደረሰበት ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ አሁንም ደነገጎን ስንወጣ ይታያል እየወደቀ ነው ግን ቆሟል፡፡ ሲያዩት ካሁን አሁን የሚወድቅ ይመስላል፡፡ በመውደቅ ላይ እንደተንጠለጠለ ይኸው አያሌ ምእተ አመታት አሳልፏል፡፡ የሼህ አባድር ተአምር መሆኑ ያስታውቃል፡፡

**ታህሳስ 3 ቀን1986**

# ፭

# ሀረር አምስት

እንግዳ ሆናችሁ ጀጎል ስትገቡ ድንጋይ ውስጥ እንደገባችሁ ያህል ነው፡፡ ቤቱ ሁሉ የድንጋይ ነው፡፡ መንገዶቹ አቤት መጥበባቸው፣ መጠማዘዛቸው! የድንጋይ ንጣፍ ለብሰዋል፡፡ ይህ ሁሉ ድንጋይ ደሞ በጀጎል ካብ ተከቧል፡፡ ወደ ውጭ ስትመለከቱ የምታዩት ኣቡንና ኮካቡ በላይ ሰማዩን ነው፡፡ የጀጎል ኗሪዎች እንደ ኤሊ ድንጋይ ለብሰዋል ሊያሰኘን ነበር፡፡ ቀና ስንል ጊዜ ሰማዩ ይታያል፡፡ እንግዲህ ጀጎል ውስጥ ድንጋይ ያልሆነ ምን ይገኛል? በር መስኮት ሰማይ፡፡

በጆጎል መንገዶች ስንጠማዘዝ የምናስተውለው ቀጥ ያለ በማስመርያ የተሰመረ የሚመስል መንገድ የለም፡፡ ካብም የለ መጠምዘዣ ማእዘንም የለ፡፡ ልክ እንደ ሰው ገላ የሰው ከተማ ነቻ ጆጎሊቱ (የማሺን አይደለችም ለማለት ነው)

በድንጋይ ተከበን ድንጋይ እየረገጥን ቀን ለቀን በጆጎል መንገዶች ስንዘዋወር የምናስተውለው ሌላ ነገር አለ፡፡ የተዘጋ በር አያጋጥመንም፡፡ እደግመዋለሁ በሩ ሁሉ ክፍት ነው፡፡ አደሬ ሴት ባዶ ቤቷን ትታ ለሆነ ጉዳይ ስትወጣ በሩን አትዘጋውም፤ ክፍቱን እንዳለ ትታው ጎረቤቷን ‹‹ከዲጃ ሄድኩ መጋላ›› (ወይም የሆነ ቦታ) ብላ መሄድ ነው፡፡

ሀገረ ጆጎል ቤቱም ክፍት ነው፡፡ ማህበረሰቡም ግልፅ ነው፡፡ ግልፅ ነው ስል በሌሎች ማህበረሰቦች በተለይም በታሪክና በባህል በቋንቋ ዘመዶቹ በሆኑት በአማራና በትግራይ - ድብቅ የሆነውና ቢታወቅብን የምናፍርበት - በአደሬ ግልፅ ነው፡፡

እንበል አብዲ ከድጃን ከሩቅ ነው የሚያውቃት፡፡ ዘመዱም አይደለች፣ ሌላም ግንኙነት የላቸውም፡፡ አንድ ቀን በሆነ አጋጣሚ ከጓደኛዋ ጋር ወደ ቤቷ ይመጣና ምሳ ይበላል፡፡ ሳምቡሳይቱ ጣት ታስቆረጥማለች፡፡ ከምሳ በኋላ አብዲ ይሄዳል፡፡

አሁንም እንበል ከአምስት ሳምንት በኋላ አብዲ ለምሳ ወደ ቤቱ ሲገሰግስ በከድጃ ቤት አጠገብ ሲያልፍ ያቺ ሳንቡሳ ውል ትለዋለች፡፡ ለምሳ ወደ ቤቱ መሄዱን ይተውና ከድጃ ቤት ይገባል፤ ባለትዳር ነች ልባርጉ፡፡ እንበል ደሞ ባሏን አብዲ ከሩቅ ነው የሚያውቀው፡፡

‹‹አማን ተሁ. . . አቦ ከድጃ በዚህ ሳልፍ ያቺ በንዲህ አይነት ቀን ያበላሽኝ ሳምቡሳ ታወሰችኝና ሰርተሻል በሚል ተስፋ ዘው አልኩ፡፡››

‹‹አብሽር›› ትለዋለች ከድጃ ‹‹ምሳም ደርሷል ሳምቡሳም አለ፡፡›› ከዚያ አብዲና አባ ወራ ጨዋታ ይጀምራሉ፡፡ እዚህ ውስጥ የይሉኝታ ሽፋን የመጠራጠር ቅኔ የለም፡፡ ፊት ለፊት!

‹‹አይ በሪ ሊጂ ኢንታሽ?›› ይላል አባወራ የየት በር ልጅ ነህ? ማለት ነው፡፡ የጀጎል ልጆች የአምስት ሰፈር ልጆች ናቸው፡፡ የአምስቱ በር ‹‹ፈላና በሪ›› ይላል አብዲ፡፡

ፈላና በር ሀረር የተዋጣላት ነጋዴ ከተማ በነበረችበት ዘመን ያወጡላት ስም፡፡ ሀረር ከባህር ማዶ የምትገናኝው አንዱ መንገድ በጅቡቲ ወደብ በኩል ነው፡፡ በጅቡቲና በሀረር መሀል ፈላና ከተማ ትገኛለች፡፡ ሁለቱንም የምታገናኝ ነች፡፡ ከጅቡቲ መጥቶ በፈላና አርጎ ሀረር የሚገባበት በር ፈላና በር ተባለ፡፡ አዲሳባውያን ከውጪ መገናኛ መንገዳቸውን ጅማ መንገድ አስመራ መንገድ እንደሚሉት ማለት ነው፡፡

ቀጥዬ የማጫውታችሁ በጃንሆይ ዘመንና ከዚያ በፊት የነበረ ነው፡፡ ከዚያ ወዲህ ሄጄ ስለማላውቅ፡፡

. . ያን ጊዜ በወንድ ልጅ ጨዋታ ቀን ከአምስቱ የሁለቱ በር ሰፈር ጎረምሶች በየሰፈራቸው ተሰልፈው ተፋጠዋል፡፡ ሽማግሌዎች ተቀምጠዋል ጨዋታውን ሊከታተሉ ነው፡፡ ወዲያውም የትኛው በር እንዳሸነፈ ዳኝነት ሊሰጡ ነው፡፡ ጨዋታው ‹‹በርቲ፣ በርቲ›› ይባላል፡፡ በር ለበር ማለት ነው፡፡

ያደሬ ጎረምሳ ነጭ በነጭ ለብሷል፡፡ ነጭ ያደሬ ቀብ ደፍቷል፡፡ ሁሉም በትር ጨብጠዋል፡፡ ፈላና በር እና እንትና በር ምክቶሽ ሊዋጣላቸው ነው፡፡ ካ! ካ! ካ!

መከተህ ቃጥተህ በዚህ አስመስለህ በዚያ ኳ! ብታረገው . . . እና ቢደማ. . . እንደ ምንም በምክቶሽ የሱን መከታ ጥሰህ ካደማኸው ደም በጣትህ ጠቅሰህ ልብስህ ላይ ትቀባለህ፡፡ አንተ ስላልተፈነከትክ፡፡

መሸፈጥ ማስመሰል መካድ አይቻልም፡፡ ግልፅ ማህበረሰብ፡፡

አምስቱ በር አቅጣጫቸው የተለያየ እንደመሆኑ ያህል የያንዳንዱ ሰፈር ልጆች ደሞ ጠባያቸው ይለያያል፡፡ ያንዱ በር ሰዎች የሌላውን ያራቱን በር ሰፈር ለይተው ያውቋቸዋል፡፡

ጀምአ ግን በር አይወስነውም። ያአምስቱም በር ሰዎች አባላት የሆኑበት አንድ ጀምአ ሊኖር ይችላል።

የቀድሞ ዘመን በፈላና በር ወጥተን መንገዱን ተከትለን ርቀን ብንሄድ ፈላና ከተማ እንደርሳለን። በእንትና (?) በር ወጥተን የሀያ ደቂቃ ያህል መንገድ ሄደን አይ-ኮካሄ ዋሻ እንገናኛለን። እንደ ጥበበ ተርፋ ዘብሔረ ጀጎል አባባል አለም ስትፈጠር ጀምሮ የነበረ ድምፅ ሁሉ እንደ ቀጠለ ነው። ገብተህ መስማትና መውጣት ያንተ ፋንታ ነው። እንደ ሬዲዮ የድምፅ ሞገዶች አንቴናህን ስትጠቀም ትሰማቸዋለህ። ሬዲዮንህን ስታጠፋ አትሰማቸውም። እነሱ ግን ሁል ጊዜ አሉ። አይ-ኮካሄ ውስጥም የአለም ዘላለም ድምፃትና ድምፆች፣ የድምፅ አይነቶች ሁሉ ሁሌ ተከማችተዋል።

አይ-ኮካሄ ዋሻ የሀረር እብዶች ማደርያ ነው። ያን ሁሉ የአለም ድምፅ በውናቸውም በእንቅልፋቸውም ሲሰሙት ያድሩና ሲነጋ የእለት እንጀራቸውንና ጫታቸውን ወደሚሰጣቸው ወደ ሀረሪ ማህበረሰብ ለመሄድ ለመቀላቀል ከአይ-ኮካሄ ሲወጡ እየጮኹ ነው። እያንዳንዳቸው የየግላቸው የሆነ አጯጯህ ይኖራቸዋል፤ መቸስ። ለማህበረሰቡ ግን ሁሉም ያው የእብድ ጩኸት ነው ብሎ ሳይዘጋው አይቀርም። እብዶቹ ከተማ ይውሉና ሲመሽ ወደ አይ-ኮካሄ ዋሻ ይመለሳሉ። እዚያ የአለምን ሁሉ የሁልጊዜ ድምፅ እየሰሙ ሊያድሩ።

ይህ ዋሻ ለምን አይ-ኮካሄ ተባለ ይሆን? የሚል ሀሳብ ይመጣብኛል። አይ-ኮካሄ የእብዶች ጠባቂ አድባር ትሆን እንዴ? እንደ አይ-አቢዳ? እንደ አይ-ኩለያ። ከሀረር ዘጠና ዘጠኝ መስጊዶች አምስቱ የሴት አድባር ወይም ጠባቂ መስጊድ ናቸው።

የአይ-አቢዳ መስጊድ አሁንም እንክብካቤ ይደረግለታል። ግድግዳው ኖራ ይቀባል። ከላይኛው ጋር ለመገናኘት መንገድ የምታሳየን ናት አይ-አቢዳ። በኛ ባዲስ አበባ አባባል ብነግራችሁ አይ-አቢዳ የዚያ ሰፈር አድባር ናት። ግን ከዚያም ትሰፋለች። ለሀረር ሰዎች እንደ አማላጅ ማርያማችን ትመቻቸዋለች፣ ታፅናናቸዋለች። ቁርአን ምን ይላል? ነቢዩስ ይፈቅዳል

ወይ? ብለው በኪታብ (መፅሀፍ) ላይ ሆነ በስሜት ይሄዳሉ፡፡ በስሜታቸው ያውቃሉ እንደምትጠብቃቸው፡፡ ይህ ስለ አይ-አቢዳ ነው፡፡

አይ-ኮለያም መስጊድ ነበራት እድገት ስልጣኔ ተብሎ መጣና መስጊዱ ፈርሶ መንገድ ተሰራበት አሁንየለም፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን አሁን ይህን ስታነቡ ሀረር ቅድስት መዲና ውስጥመሆናችንን ላስታውሳችሁ፡፡ መስጊድዋ በቅርብ ነው የፈረሰው፡፡ የት እንደነበረ የሚያውቁ ሰዎች በይበልጥም ሴቶች ዛሬም ማታ ማታ ባስራ ሁለትስአት እየሄዱ እጣን ያጨሱላታል፡፡ ልክ የድንጋይ መስጊድ እንደነበራት ዘመን ይለማመኗታል፡፡ መስጊዱ በድንጋይ የተሰራው ለሰዎች ሲባል እንጂ አይ-ኩለያ ለራሷ አድባር ናት፡፡ ከሌሎች ጋር ሆነሽ ሀረርን ጠብቂ ተብላ መጣች'ንጂ፣ ከአይ-ኩለያ ጠባቂ አድባራችን አስፋልት መንገድ ይሻላል ካሉ የራሳቸው ጉዳይ፡፡

ስለእስልምና በጥልቀት ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ስሆን ትዝ የማይለኝ፤ ብቻዬን ስሆን ግን በሀሳብ የሚመላለሱብኝ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ሴቶች መስጊድ ይገባሉ ወይ? በመስጊድ ሳልፍ ወንዶች ናቸው የሚታዩኝ፡፡

ስለ ጀነት ስንሰማ ለወንዶች እጅግ የሚስማማ ስፍራ ነው፡፡ በአታክልት ቦታ ትንፈላሰሳለህ፡፡ ባጠገብህ የምንጭ ውሀ እየፈሰሰ ነው፡፡ የሚያገለግሉህና የሚያስደስቱህ ሁሪ የተባሉ እንደ ጨረቃ የተዋቡ ኮረዳዎች አሉ ማርጀትን የማያውቁ፡፡ ሚስትህ ግን የት እንዳለች አይነገርም፡፡ ለመሆኑ ሴቶች ጀነት ይገባሉ ወይ? ከገቡስ የነሱ ጀነት ምን አይነት ስፍራ ይሆን?

እንግዲህ በሀረር ይመሻል፡፡ እብዶቹ ወደ አይ-ኮካሄ ዋሻ ይሄዳሉ፡፡ የጀጎል አምስቱ በር ይዘጋል፡፡ አደሬ በጀጎል ድንጋይ ተከቦ እንደ ኤሊ ወደ ውስጥ ይገባል፡፡ በምርቃና መንገድ ውስጥ. . .

ታህሳስ 10 ቀን 1986

፮

# ሀረር ስድስት

ሀረርና ፕሮፌሰር አርኖልድጆ ቶይንቢ ያለመተዋወቃቸው በጭራሽ ልክ አይደለም። ለምን ብትሉኝ ስልጣኔዎችን ተንትኖ አጥንቶ ለተራ ሰው በሚገባ ቋንቋ የፃፈ አንድ ሊቅ አዋቂ ሰው ቢኖር ፕሮፌሰር ቶይንቢ ነበሩ።

ስላጋጠማቸው በጥናታቸው ውስጥ ያልጨመሩት አንድ አይነት ስልጣኔ አለ። ይኸውም ‹‹እፉዬ ገላ›› ልንለው የምንችል ስልጣኔ ነው። ከሩቅ ሩቅ፣ ሩቅ አገር ፈልሶ መጥቶ እቺ ናት ያንተ ምድር የሚል ስሜት ያድርበትና ይሰፍራል ፍልሰቱ ጉዞው አበቃ። አሁን እዚህ መብቀልና ስር መስደድ ይቻላል። እንደ አደሬ በጀጎል።

‹‹በወንዞችና በለም መሬት የተከበበች ኮረብታማ አገር እሰጥሃለሁ። እዚያም ቅድስት ከተማዬን ታንፃለህ›› የተባለ አይመስልም? ወይም ህዝበ አደሬ ማለቂያ የለሽ የሚመስል አድካሚ ጉዞውን በዱር በገደል በሜዳ በዳገት ‹‹በለሊት ቁር በቀን ሀሩር›› እየተጠበሰ ሲጓዝ፣ አመታት ሲጓዝ - ህፃናትም ነብሰጡሮችም ሳይኖሩት አይቀሩም መቸስ - ለንዲህ አይነት ታሪክ ደግሞ ሰባት አመት ቢሆን ይመረጣል ሲጓዝ፣ ሲጓዝ ዛሬ ጨርጨር በምንላቸው ተራሮች በስተምስራቅ ጎድናቸው አሁን ሀረር የምንለው ስፍራ ሲደርሱ አንዲት የተባረከች ቀን በፈገግታ እየተቀበለች አደሬዎች ሀረር ገቡ። ገቡ፣ ገቡ ቀሩ። ጀጎልን ገነቡ። በዚህ ግብርናውን በዚህ ንግዱን ተያያዙት። በዚህ የምድረ ኢትዮጵያን እስልምና ዘሩት።

የቶይንቢ የትንተና ዘዴ አሁን ለኛ ይመቸናል። ሀረርን ልዩና ብቸኛ ብርቅዬ ስልጣኔ የሚያደርጋት ምንድን ነው? የሀረር አሚርን አደሬዎች ልክ እንደንጉስ ነው የሚያዩት ፈላጭ ቆራጭ ነው። ከፈለገ ደግ አሚር መሆን ይችላል ከፈለገ እርኩስ አሚር። ጀጎል ሁለቱንም አይታለች። ከዚህም ጋር ግን አሚር ቅድስት ጀጎልን መጠበቅ አለበት እንደማንም ንጉስ።

ታድያ የአሚር ህዝብ ብዛት ከአርባ እስከ ሀምሳ ሺህ የሚደርሱ አደሬ ብቻ ናቸው። ያውም ከዚህ ስንቱ ህፃን፣ ስንቱ ሽማግሌ፣ ስንቱ ሴት። እንግዲህ አሚር ሰራዊት ከየት ያምጣ? ከየትም። ግፋ ቢል ለክብር ዘብ ያህል ቢያገኝ ነው።

ስለዚህ አሚር ቅድስት ከተማን የሚጠብቅ ግን ሰራዊት የሌለው ንጉስ ሆነ። በዙርያው ካለው አለም ጋር የሚገናኘው በሰላም በንግድና በሀይማኖት ብቻ ሆነ።

ዙርያውን ያሉት ህዝቦች እንዳይወሩት ያን ጀጎል ካቡን በደህና ቀን ሰርቷል። አምስት በሩ ፀሀይ ስትጠልቅ የሚዘጋውን። በዚያን ዘመን ፈንጂ ወይም ጠመንጃ ገና የለችም። በጦርና በቀስት በክርንና በጥፊ ጀጎልን እንዴት ትሰጠዋለህ? ኤሊ የሚለው ምስል ይኸውና። ህዝበ አደሬ ‹‹ዘመነ እፉዬ ገላን›› ማለትም የስደት ጉዞው አበቃ እንደ ወጣች ቀረች አይነት ሳይሆን ወጥታ ሄዳ ሄዳ ሰው ሆነች - ሰው ከመሆንም አልፋ የታላላቅ እናት ለመሆን በቃች አይነት። ከነዚህ ታላላቅ ልጆቿ አንዱ እኛ አህመድ ግራኝ የምንለው ሰውዬ ነው።

የሀረር ታሪክ ዋና ዋና ሰአቶች ከአረብ አገር ጋር መያያዛቸው አይቀርም።

አንድ የመካና መዲና ታናሽ እህት በመሆኗ ይህ ንፁህ ሀይማኖት ይባላል።

<u>ሁለት</u> አባድርና ሰላሳ ዘጠኝ ቅዱሳን ከአረብ ስለመጡ።

<u>ሶስት</u> ምድረ ሀበሻን ነፃ የሚያወጣት - ማለትም ከአረመኔ አምልኮ ወይም ከካፊርነት የሚያድናትና የእስልምናን ፅድቅ የሚያጎናፅፋት አህመድ ግራኝ መሆኑ አስቀድሞ በአረብ አገር በመታወቁ።

እኔ ሀረርን የያዝኳት በአፈ-ታሪክ ስለሆነ አፈ-ታሪክ የሳቸውን ስም ከየት ያምጣው? ግን አንድ ስም እንኳ ሲያንሳቸው ነበር። እኚህ ሰው አረብ አገር ሆነው አንድ ለሊት በህልማቸው አራት ሰዎችን አብረው ቆመው ያዩዋቸዋል። ሶስቱ ነብዩ መሀመድና (ሰአወ) ሁለት የቅርብ

ሰዎቻቸው ናቸው። አራተኛው ግን ማን እንደሆነ ባለህልሙ አያውቁም። በህይወት ያለ መሆኑን ከእስልምና ጋር የተያያዘ ትልቅ መልእክት የተቀበለ መሆኑን ግን አውቀውታል። እሳቸውም ህልሙ የተላከላቸው ለምክንያት መሆኑ ገብቷቸዋል። ስለዚህ ተነስተው አራተኛውን ሰው ፍለጋ ወጡ፤ የምድረ አረብን ሼኮችና የጦር አለቆች ሁሉንም ዞረው አዩ አንዳቸውም አራተኛውን የህልማቸውን ሰው አይመስሉም። ቀይ ባህርን ተሻግረው ወደ ሀረር መጡ፤ የሀረርን አሚር አዩት። ወጣት ረኻም መልከ መልካም ነበር። በህልማቸው ያዩት አራተኛው ሰው እሱ ራሱ ነው። አህመድ አልጊራኒ? ረኻም ስም ነው። የጀግናው ሙሉ ስም አሚር አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልቃዚ አልጊራኒ ይባላል።

ሰውየው ስለ ህልማቸው ይነግሩትና ይከተሉት ዘንድ ይፈቅዱታል። ጦሩን ሲሰበስብ፣ ሲዘምት ምድረ ሀበሻን እያከታተለ ድል ሲመታ በመጨረሻ ጎንደር አጠገብ በጦር ሜዳ ሲወድቅ - ይህንን ሁሉ ያዩ ወደ አገራቸው ተመልሰው ‹‹ፍቱህ አልሀበሻ›› የተሰኘ የታሪክ መፅሀፋቸውን ይፅፋሉ። ለእስልምና መስፋፋት ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረገ ታላቅ የጦር ጀግና አድርገው ያቀርቡታል።

የኛ አፈታሪክስ ስለግራኝ ምን ይላል? አፄ ልብነ ድንግል በሰላም መግዛት ቢሰለቻቸው ምድሪቱን ጦር አምጪ ብለው ገረፏት። አህመድ ግራኝን ላከችባቸው።

ግራኝ ሲወለድ ሰላሳ ሁለት ጥርሱን ግድግድ አድርጎ አብቅሎ ነው። በዚያችው እለት ደግሞ ራቅ ባለ ሌላ ስፍራ አንድ ፈረስ ተወለደ - እሱም ከነሙሉ ጥርሱ፤ በኋላ የግራኝ ፈረስ ሆነ።

ግራኝ አፄ ልብነ ድንግልን እንዲህ ሲል ላከባቸው። ‹‹አፈጣጠኔ እንደ ጅብ፤ አመካከቴ እንዳንበሳ፣ አጨካከኔ እንደ እናቴ መጣሁብህ።››

አፄና መኳንንቶቻቸው አጨካከኔ እንደ እናቴ ሲል ናቁት። ደሞ ሴት ብሎ ጨካኝ! ነገር ግን ከመኳንንቱ አንዱ እንዲህ አላቸው አፄን ለብቻቸው።

‹‹እስቲ እንዱን መኳንንት የሚስትህን ራስ ቆርጠህ አምጣልኝና ግማሽ መንግስቴን እሰጥሀለሁ ይበሉት ያያሉ››

ጨካኝ የመሰላቸውን ሰው መርጠው ነገሩት፡፡ ‹እሺ ጃንሆይ› ብሎ ሄደ፡፡ ለሊት በእንቅልፏ ሊገድላት ተነሳ አልቻለም፤ አሳዘነችው፡፡ ባዶ እጁን መጥቶ ለጃንሆይ ተናገረ ‹በል ተወው› አሉት፡፡ ሚስቲቱን በሚስጢር አስጠሩና ‹‹የባልሽን ጭንቅላት ቆርጠሽ ብታመጪልኝ ግማሽ መንግስቴን እሰጥሻለሁ›› አሏት፡፡

‹‹ኧረ እኔ አይሆንልኝም ጃንሆይ፣ ባሌን እወደዋለሁ›› አለቻቸው፡፡ እና በንጋታው የባሏን ጭንቅላት አምጥታ ሰጠቻቸው፡፡

የግራኝ መልእክት አሁን ገና ገባቸው፡፡ እንዳለውም መጣ በምድረ ሀበሻ እንከራተታቸው በሽሽት፡፡ መግቢያ ቢያጡ ሰሜን ተራራን ወጡ፡፡ ጫፍ ላይ ሲደርሱ ተራራውን ስም አወጡለት ጨነቀኝ አሉት ጨነቀኝ ሆኖ ቀረ፡፡ እሳቸውም እንደጨነቃቸው እንደተንከራተቱ ሞቱ፡፡

ልጃቸው ገላውዲዮስ አልጋውንም ጦርነቱንም ወረሰ፡፡ ህዝበ ክርስቲያን አለቀ፡፡ እርዳታ ላኩልን ሊል ያን ጊዜ ሀያል አገር ወደነበረችው ወደ ፖርቹጋል ሄዶ ነበር፡፡ ጎንደር አጠገብ ውጊያ ላይ አህመድ ግራኝ በጥይት ተመቶ ወደቀ፡፡ ጦሩም ወደ ሀረር ተመለሰ፡፡ አፄ ገላውዲዮስም የጎንደርን ከተማ መሰረቱ ይባላል፡፡

በምድረ ሀበሻ በያገሩ ትልልቅ የድንጋይ አምድ መሳይ ይገኛል፡፡ አህመድ ግራኝ ነው ከጋራው አምጥቶ የተከለው ይላሉ፡፡ ለምን? ፈረሱን ሊያስርበት፡፡

**ታህሳስ 17 ቀን 1986**

# ፯

# ሀረር ሰባት

## አንድ

አንዱ የተባረከ የእግረ መንገድ አንባቢ እንዲህ ብሎናል፡፡

ፍቀድልኝና ላሻሽልልህ፣ አፄ ልብነድንግል በሰላም በምቾት መግዛት ቢሰለቻቸው መሬትን ጦር አምጪ ብለው ገረፏት ብለሀል፡፡ እሱም ገረፋት፡፡ ገርፎ ገርፎ ሲደክመው አቤት ብታየው ክንዱ ዝሎ ፊቱ ላብ በላብ ሆኖ እሷው መሬቲቱ ላይ እንዘፍ ብሎ የመሞት ያህል ወደቀ፡፡ በድንጋይ ይሁን በእሾህ አልወጋችውም መሬት፡፡ እንዲያውም ለስላሳው አፈር ላይ ሆኖ ተገኝ የወደቀበት፡፡

‹‹እቺ አሮጊት አልሰማችኝም ማለት ነው›› አለና ወታደሮቹን አዘዘባት፡፡ ገረፏት መሬቲቱን፡፡

ወታደር መቼም መታዘዝ 'ንጂ መጠየቅ አያውቅም፡፡ እናታችን፣ መብቀያችን፣ በኋላ ማረፊያችን እናታችን መሬት እንዴት ትገረፍ? አላሉም፡፡ ገረፏት ወዳ እስክትጠላ፡፡ (እሷ ስሜትም አልሰጣት) ጦር አምጪ፣ ጦር ላኪ እያሉ ገረፉዋት፡፡

ጦር ፈለጋችሁ? እኮ! አለችና የበቀለባት የሚወዳት ሀረር ያለው አካሏ አህመድ ግራኝ ሆና ተነሳችባቸው፡፡ ከውስጧ በቅለው አካሏ ሆነው ስለገረፏት፡፡ ሲሄዱ በእግራቸው፣ ሲቀመጡ በቂጣቸው፣ ሲጋደሙ በጎናቸው፣ ሲቀበሩ ለሁለመናቸው ስለተነጠፈችላቸው እነሱ ገረፉዋት አይደል? ውለታዋ ግርፊያ ሆነ፡፡ ሰላምና ምቾት ከሰለቻችሁ እነሆ ግራኝ ወንድማችሁ አለቻቸው፡፡ ያለቁት አለቁ፣ የተረፉት ተንከራተቱ፡፡ መፈጠራቸውን ጠሉ፡፡ የነሱን እጣ ለጠላቴም አይስጠው፡፡

በዚህ አለም ለመጀመሪያ ጊዜ ‹‹የቀበጡ እለት ሞት አይገኝም›› ያለው አፄ ልብነድንግል ነበር ብንል ከፅድቅ ሊቆጠርልን ይችላል፡፡ ይህንንም የተናገረው ጨነቀኝ ተራራ ጫፍ ላይ ቆሞ ቁልቁል ወደ ጎንደር

እያየ ነበር፡፡ ያን ጊዜ ጎንደር ገና ያልተቆረቆረች ቢሆንም በትንቢት ወደ ጎንደር በኩል ማየት የሚከለክለው የለም፡፡

## ሁለት

ሌላው የሀረር ተከታታይ አንባቢያችን ‹‹ምነው ግራኝን አደከምከው? ክርስቲያኑ አስተዳደግህና የመሳሰሉት ተጫኑህ እንዴ?›› አለኝ፡፡

‹‹እውነትክን ነው›› አልኩት፡፡ ሊመስል ይችላል ግና በአፈ ታሪካችን ስለ ግራኝ የሰማሁት ድሮ ጥንት ስለነበር ይህንኑ ብቻ ነው ላስታውስ የቻልኩት፡፡ ስለዚህ እንዴት ላተልቀው እችላለሁ? ግርማ ለማ ባለፈው ጊዜ ስለ አወዙል ቀርነይኒ እንዳገዘኝ አይነት እናንተም የተሳሳተውን ማረም በጎደለውም መሙላት ትችላላችሁ፡፡

እኔ ለራሴ አንድ ሰው፡፡ ሀረርን ያህል ባህር ጠቅልዬ ላውቅ እችላለሁ 'ንዴ? አንድ ሰው'ኮ ብቻውን ሲዘፍን ይሰለቻል፡፡ በተለይ ለዘፋኙ ለራሱ! ስለዚህ ዘፈኔን ልቀጥል፡፡

ዘፋኝ በነበርኩ ጀጎልን በዘፈንኩላችሁ - ድንጋይ ልብሷ፣ ቢራቢሮ ነብሷ እፉዬ ገላ ምስሏ፡፡ አንዳንድ አደሬዎች ዘመናዊነት ሳባቸውና የመንገዱ ንጣፍ ድንጋይ ላይ ሲሚንቶ ደርበው አነጠፉበት፡፡ አሻሻልን ብለው አበላሹ፡፡ ድንጋዩ አልተስማማውማ፡፡ ታፈነ፡፡ የሀረርን አየር ካልተነፈስኩ አለ፡፡ የቤታቸውንም ግድግዳ ሲሚንቶ ግርፍ ያለበሱትም እንደዚሁ ተበላሸባቸው፡፡

ጀጎል አርጅቷል፡፡ የአደሬ ስልጣኔ ግን እንዳለ ህያው ነው፡፡ ይህንንም ለመገንዘብ በማንኛውም ቀን ወደ አባድር መስጊድ ጎራ ማለት ሊበቃ ይችላል፡፡ ሽኬዎቹን እዚያ ታገኛቸዋለህ፡፡ በእለቱ የተመደበውን የቁርአን ክፍል እያነበቡና ትምህርት እየሰጡበት ነው፡፡ ስለ አደሬ ባህልም በሰፊው እያብራሩ ነው፡፡

ወደ አባድር መስጊድ እየመጡ ለአባድር ተስለው የሚሄዱ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ አዎ ክርስቲያኖች፡፡ እስላምማ የዚህ አይነቱን ስለት አያውቅም፡፡ በቀጥታ አላህን መለመን ነው፡፡

ሀረር ከአምስቱ በር በአንዱ ትገባለህ፡፡ ጠባብና ጠምዛዛ የድንጋይ ንጣፍ መንገዶቹን ሄደህ የምትፈልገው ቤት ትደርሳለህ፡፡ ስትገባ ማን ያጋጥምሀል?

የድንጋይ ግድግዳዎቹ ስር ዙርያውን የተነጠፉት መደቦች ላይ ሰዎች ትራስ (መከዳ) ደገፍ ብለው ግማሽ ጋደም ከወደራስ ቀና ብለው ተዝናንተው፡፡

‹‹አመን ተኽ››. . . እዝህኛው መደብ ላይ ጋደም በል ብለው ካዝናኑህ በኋላ አይንህን ትከፍታለህ፡፡ አጠገብህ ያለውንም መጠየቅ ትጀምራለህ፡፡ ያኔ ያደሬ ቤት አቀማመጥ ይገባሀል፡፡

<u>ነደባ</u> ይባላል መደብ፡፡ መጋደም ያው መዝናኛው፡፡ እንግዳው ሲገባ በስተግራ አልፎ አልፎም በስተቀኝ ሊሆን ይችላል፤ አሚር ነደባ ትገኛለች አነስ ጠበብ ያለች መደብ ናት፡፡ ላንድ ሰው ዙርያውን ሁሉ ካሉት መደቦች የምታንስም ከፍ የምትልም እሷ ናት፡፡ ያባወራው ናት፡፡ እንግዳው ሲገባ ያቺ መደብ ሰው ከሌለባት አባወራ እንደሌለ ያውቃሉ፡፡ ማንም ሌላ ሰው አይወጣባትም፡፡

<u>አሚር ነይባ</u> ዙርያ እንዝቅ ብለው ቢትነይባ አሉ፡፡ የጀምአው አባላት ማለትም አብሮ አደጎቹ እና ከአላህ በታች የሚተማመንባቸው የሚተማመኑበት ጓደኞቹ የሚጋደሙባቸው፡፡

ከጀምአው አባላት ሌላው ጢጥ ነይባ ላይ አይቀመጥም፡፡ ከዚህ ስብስብ ካሉ መደቦች እልፍ ብሎ ከግድግዳው እኩል ረዥምና ሰፋፊ መደቦች አሉ፡፡ ለእንግዶች ናቸው፡፡ እዚያ ይቀበሉሀል ቦታ ይሰጡሀል ይዘኸው የመጣኸውን ጫት ትፈታለህ፡፡ ከመደቦቹ በላይ ዙሪያው ግድግዳ ውስጥ እቃዎችና ቁሳቁስ ተሰቅለዋል፡፡ ግድግዳ ውስጥ ቦታ አለ ክፍት ሳጥን የመሳሰለ፡፡ ገና ገምቢዎቹ ግድግዳውን ሲሰሩ ለነዚህ ሳጥኖች ቦታ እየተዉ ነው፡፡ በቃላት መግለፁ ያስቸግራል፡፡ ብቻ ቤቱ ውስጥ ስትገባ ሁሉ ነገር ቦታ ቦታውን ይዟል፡፡ ቤቱ ሊዝረከረክም አይችልም፡፡

ቤት ስትል ሴት ማሰብ አይቀርም። የሀረር እስልምና እና ባጠቃላይም ያገራችን እስልምና ከአረብ እስልምና ለየት ይላል። የሀረር ሴት ፊቷን አትሸፍንም። የምትሸፈነው ገና ወጣት እያለች ባሏ ከሞተባት ብቻ ነው። ሌላ ባል እስክታገባ ትሸፈናለች። ወይ ጫት ትነግዳለች ወይ እህል ትነግዳለች። ስለዚህ በመጠኑ ነፃነት። ማለትም የባሏ ሚስት ናት እንጂ ተገዢው አይደለችም፤ ጤነኛ ስልጣኔ ነው።

**ታህሳስ 24 ቀን 1986**

## ፳

# ሀረር ሰባት

የአደሬን ስልጣኔ ጤነኛ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ጫት ነው ለማለት ይቻላል። ሀረር ቅድስት ከተማ ውስጥ ትናንት አውዘል ቀርነይኒ ራሳቸው ከጀነት ካስመጧት ጊዜ አንስቶ ጫት የፀሎት የዱአ ማድረጊያ ቅድስት ቅጠል ናት 'ንጂ በድሬዳዋ፣ አዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች እንደሚደረገው የምርቃና የሀራራ የይካ እፅ አይደለችም።

ጀጎል ዙሪያ ከሚፈሱት ወንዞች በመስኖ ተጠልፎ የሚወሰደው ውሀ የሚያበቅላቸው የተለያዩ የጫት አይነቶች በመሬቱ መለያየት የተነሳ እናም የመስኖ ወይስ የዝናብ አካባቢ ይብቀል እናም የገበሬዎቹ ትጋትና እንክብካቤ በመለያየቱ በዚህ ምክንያት የአውዘል ቀርነይኒ ጫት ዘመናትን ቆጥራ ብዙ አይነት ጫቶች ሆነች። ከሀረር አካባቢም ወጥታ በየሄደችበት እንደየመሬቱ አይነትና እንደየጠባዩ አይነት የተለያዩ ጫቶች ሆነች። አገሩን አጥለቀለቀችው።

ጧት የጀጎል ገበሬ ቤት ያደሩ አህዮቹን እየነዳ ሲሄድ ወደ ሰፈሩ መስጊድ ይገባል። እንደሱው መስጊድ ከመጡ የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ይገናኛል። ይወያያሉ እንዴት ነው የእህል ጉዳይ? እገሌ የት ቀረ? ትላንትም አላየሁት። የምታውቁት ነገር አለ?

ታሞ ቀረ ሌሎቹ ይጠይቁታል እናም በየግላቸው እንደየልባቸው ስፋትና እንደየኪሳቸው ሙላት እርዳታ ያደርጉለታል ካስፈለገው።

ከመስጊድ ወጥቶ ወደ እርሻው። ነጋዴው ወደ ሱቁ። ቁርስ በልቶ ነው ከቤት የወጣው፤ ሶላትም አርጓል።

በዚህም አይነት እንግዲህ ሆን ተብሎ የጫት ቃሚዎች ጫት መግባት ይጀምራል። ለኢጀባና (ማለትም ለአይን መክፈቻ) ለኢጀባና የምትቃመው ትንሽ ናት። ሰውነትን ለማናቃት። ከዚያ ወደ እለት ተግባርህ ትሰማራለህ። ሽምግልና ያለበት ወደ ሽምግልናው ይሄዳል። ልብስ ሰፊ ወደ ስፌቱ። ገቢ ወጪህን ታሰላለህ።

የመስኖ ጫት በመስመር ይተከላል በአንድ አንድ ሜትር ርቀት። በጫቱ መሀል ማንጎ፣ አቦካዶ፣ ወሽመላ፣ ዘይቱና፣ ግሽጣ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን እና ቡና ይተከላል።

ገበሬው ከኢጀባና በኋላ ቀኑን ሙሉ ሌላ ጫት አይቅምም። ሆጃ ይጠጣል። -- ወተት በቁጢ (ከደረቅ የቡና ቅጠል) ተፈልቶ። ቲምበ (የተፈጨ ትምባሆና አመድ) በጣትና በጣቱ ቆንጥሮ በጉንጩ ያደርጋል - ከላይኛው ሳይሆን ከስረኛው ድድ ጋር ያለው ጉንጬ ሲሰራ ይውላል። ሲመሽ የወራቱን አታክልት - ቃሪያ፣ ዱባ ወዘተ ይዞ ወደ ቤቱ የዳገቱን መንገድ ይያያዘዋል። ለራሱ የምትሆን ትንሽ ጫትም ይዟል። ከእራት በኋላ የሚያመሽባት። እንግዲህ ገበሬው ጫት ይህን ያህልም አይቅምም። በብዛት ከሆነ ቁም ነገሩ።

ለአቅመ አዳም ሳይደርሱ ጫት መቃም የለም። ዕድሜ የማይፈቅድለት ወጣት ጫት ሊገዛ ቢሄድ ሻጩ ‹‹አላውቅህምና ነው አንተ? የእገሌ ልጅ አይደለህም? በል ሂድ ጥፋ ከዚህ። ቆይ ደሞ ባልናገርልህ!›› ብሎ ያስፈራራዋል። በአደሬ ባህል ልጆችን መጠበቅና መንከባከብ የወላጆችና የዘመዶች ብቻ ፋንታ አይደለም፤ የባዳም ጭምር ነው። አደሬ ከሆንክና ከዚህ በፊት አይተኸው የማታውቅ እንኳን ሲያጠፋ ካየኸው ልክ እንደገዛ ራስህ ልጅ አርገህ ነው ከጥፋቱ የምትመልሰው

(ያዲስ አበባችን ኦ! በሰው ልጅ ምን አገባን?) የሚለው ባህል በአደሬው አይን ሲታይ ትንሽ ወደ አውሬዎቹ መጠጋት ሳይመስል አይቀርም፡፡

ጫት ንቃት ይሰጣል፡፡ ጫት ያመረቅናል፡፡ ጫት ለማህበራዊ ጉዳዮች ባህላዊ ስነ ስርአት ያስችላል! ያሳምራል፡፡

‹‹ኒካህ›› ሲደረግ (ፍጥምጥም ማለት ነው) ወንዱ ሁለት ሶስት ሀቃራ (እስር) ጫት ይዞ ይገባል፡፡ ለዘመድና ለመንደር ሰው በየቤቱ ልጆች እየተላኩ ሁለት ሁለት እንጨት ያህል ጫት ያድላሉ፡፡

‹‹የማን ልጅ ናት?›› ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ከንግዲህ ልጅቱ ተይዛለች፡፡ ማህበረሰቡ አውቆታል፡፡

ሰርግ ከደረሰ በኋላ ጫጉላ ቤት ውስጥ ሙሽሪትን ጓደኞቿ ያለማምዷታል፡፡ የሙሽራው ሚዜዎች ጁምኢዎቹ ናቸው፡፡ (ማለት አብሮ አደግ ጓደኞቹ) በበኩላቸው በርጫ ያደርጋሉ፡፡ ቅዱስ ቁርአን ይቀራል (ይነበባል)

ሀዘን ሲቀመጡ ማስተዛዘኛ አንድ ሁለት ሀቃራ ጫት ይዘህ ትሄዳለህ ይቃማል ይቀራል (ቁርአን)፡፡ ማልቀስ የለም፡፡ ከቀብር በኋላ ምሳ ከዚያ ጫትና ቁርአን፡፡

ጀጎል ውስጥ ጫት ቃሚዎች ጫታቸውን እንደ አይነቱና እንደየ ፍጥርጥራቸው ይመርጡታል፡፡ የየትኛው በር የየትኛው ወንዝ መስኖ ጫት ነው? ይባላሉ፡፡ የአው ሶፊ? የአው ኡመር? የስግቻ ጫት ወይንስ የሚቆራ?

እንግዲህ ሲዘንብ ካደረ ጫት አይቆረጥም! መሬቱ አይረገጥማ፡፡ መሬቱ ከመጠጠ በኋላ ነው ጫቱ የሚቆረጠው፡፡ ለባለ ኢጃበና ሊዘገይበት ይችላል፡፡

የእንትን ጫት ፍዝዝ ያደርገናል! የእንትን ጫት ቀልቤን ይነካኛል፡፡

በችግር ጊዜ ካልሆነ ያወዳይ ጫት ሀረር አይገባም ይገባል ድሬዳዋ ነው የሚሄደው፡፡

ጫት ሲቅሙት ‹‹ረሀ›› ይሰጣል - ማለት ያዝናናል የደስ ደስ ይሰጣል፡፡ ‹‹ረሀ›› ከሰጠህ በኋላ መጨመር አያሻም (ይላሉ ሽማግሌዎቹ) ከዚያ መጠን በላይ ስትቅም ግን መጅሊስ (ጉባኤ) ተቀምጠህ ትፈላሰፋለህ፣ ትመረቅናለህ አንዳንድ ሀላፊነቶች ሊያስረሳህ ይችላል፤ ወይ ችላ ሊያስብልህ ይችላል፡፡ ሽማግሌዎቹ ጫት ለረሀ መልካም ነው ይላሉ፡፡ ጫት ለምርቃና ግን ስታበዛው እገሌ ‹‹ፍቅራ›› ሆነ ይሉሀል፡፡ ፍቅራ ማለት ጫት መቃምና ሀይማኖትን መስበክ ’ንጂ በተግባር ምንም የማይሰራ ማለት ነው፡፡

በርጫ እስካለ ድረስ ጀጎል ውስጥ ራዲዮ ጋዜጣ አያስፈልግም፡፡ ሀረር ውስጥ የተደረገ ሁሉ ይደርስሀል፡፡ ምን እቃ እንደገባ ምን ምን እየሆነ እንደሆነ ማን በፍቅር እያበደ እንደሆነ ----- ይህ ሁሉ ይነገራል፡፡ ግልፅ ማህበረሰብ ነው ብለናል ደሞ፡፡

በርጫ ላይ ቁም ነገር አለ፤ መፈላሰፍም አለ፤ ለምሳሌ የአብዲ በሌ ቀልዶች ከአንዱ በርጫ ወደ ሌላው ሲቀባበሉአቸው ቀልዱን የሚፈጥረው ፊት ለፊቱ ያለውን ሰው መነሻ በማድረግ ነው፡፡

በራሱ በሰውየው ነው የሚቀልድበት፡፡ ሰውየው አይቀየምም አብሮ ይስቃል ’ንጂ እንዲያውም እንዲህ ስለተቀለደበት ይኮራል ያወራል፡፡ የአብዲ በሌ ጓደኛ አንድ አይና ባለ ሱቅ ነው፡፡ በዚህ በጓደኛው ብዙ ብዙ ይቀለዳል፡፡ አብዲ በሌ እንደ አቡ ነዋስ አይነት ሰው ነው፡፡

ጫት ሁለት ሂደት ሄዳለች ከረሀ ከዱአ አልፋ ወደ ምርቃና ሄዳለች፡፡ ቡሀራ ሆነህ ስጋህም ነብስህም ፀድተው አላህን መለማመኛ ከመሆን አልፋ የትም እየፈረሽክ ወይም ሳትፈርሽ ወይ እስከ ጭራሹን ታክሲ እየነዳህ ለምርቃና የምትቅማት ሆነች፡፡ ከዚያም ምርቃና ጨብሲ ተከተላት፡፡ ይህም ምርቃናህን ለመበተን የምትጠጣው አልኮል ያለው መጠጥ ነው ኪታቡ የሚከለክለው፡፡ ወደ አላህ ከመትጊያነት አልፋ የአላህን ህግ መጣሻ እየሆነች ሄደች፡፡

ሁለተኛው የጫት ሂደት ወደ ገበያ መውጣቷና እንደ ቅድስት የጀነት ቅጠል ሳይሆን እንደ ማንም ቅጠል ተገዝታ በትርፍ የምትሸጥ መሆኗ ነው፡፡

ምርቃና ወደ ውስጣችን ጉዞ ነው፡፡ ውስጥ ውስጥህን ስትገዝ ቆይተህ ድንገት ትነቃለህ፡፡ ለካ የኢብሊስ ንፋስ ሽው ሲልህ ነው፡፡ ይህኔ ኢብሊስን ምን ብለህ ታባርረዋለህ?

‹‹ኢስታፍሩላህ! ላ ኢላሀ ኢለላህ መሀመዱ ረሱሉላህ!››

ጥር 1 ቀን 1986

# ሰአሊው ጥበበ ተርፋ

የሀረር ልጅ ስለሆነው ሰአሊ ጥበበ ተርፋ ላጫውታችሁ። እናንተም ስለ ሀረር ሳወራ አንዷት ያደገባት አካባቢ ለሰአሊ ምን እንደሆነች፤ እሱስ ምኗ እንደሆነ ታያላችሁ በጨረፍታ።

በጨረፍታ እንጂ ጥበበን በሙሉ ማቅረብ አይቻለኝም። ሰውዬው ስሙና መልኩ እና ቤቱ ያው ናቸው 'ንጂ እሱ ግን'ኮ ‹‹በርከት ባይሉም አነስ የማይሉ›› ልዩ ልዩ ሰዎች ሆኖ ይገኛል።

ምናልባት ዋነኛው ጥበበ ያው ሰው ሆኖ የተፈጠረው ጥበበ ነው። በዚህኛው ጥበበ ሰው ሁሉ ሰው ነው። ደጃዝማች ሆንክ ኮሎኔል፣ ጋጋሪ ሆነች ሸርሙጣ፣ ለማኝም ሆነ መፅዋች እነ እሱ ጥበበም ሆነ እነ እነሱ-- ያው ሰው ናቸው። ለዚህም ነው ጥበበ ከማንም ጋር በምንም አጋጣሚና ሁኔታ ቢገናኝ ሁሌ ያው ራሱ ጥበበ የሚሆነው፤ ስለዚህ ነው ጥበበ ስለ አይ-በኮካሄ ዋሻ ሲያወራ እውስጡ የገባህ የሚመስልህ። እብዶቹን ያውቃቸዋል፤ ያላበድነውን እንደሚያውቀን ሁሉ። የጥበበንና የሀረርን እብዶች ለናሙና ያህል እነሆ!

ሰረደድ የሚባለው እግለሰብ ቤት ያለው እብድ ነው። የሀረር እብዶች የሚያድሩት ከጀጎል ውጪ አይ-በኮከሄ ዋሻ ውስጥ ነው ቢባልም እኮ እብድ እብደቱን እንደፍጥርጥሩ እንዲያብዳት አደራው ስልጣኔ ያስችለዋል።

በረደድ እንደነ ሌኒን ሀውልቶች እጁን እንዲህ እየቀሰረ ነው ንግግር የሚያደርገው፡፡ ፀሀይ ሞቅ ሲልለት በከተማይቱ መንገዶች እየተዘዋወረ ይለፈልፋል፡፡ በረደድ በአደርኛ ያበደ አማራ ማለት ነው፡፡

እንዳለ ግራኝ በወንጭፍና በወስፈንጥር የማይስት አዳኝ ነበር፡፡ አደን ሲሄድ ወጣቶቹ ያጅቡታል በጣም ስለሚያደንቁት፡፡ ከነዚህም አንዱ አባስ ይባላል፡፡ እንዳለ ግራኝ ሲያብድ ጊዜ በአድናቆትና በማጀብ ብዛት አባስ ለማበድ እያቆበቆበ ነው፡፡

ቦብላ ከሚሊተሪ አካዳሚ በኋላ ዩኒቨርሲቲ ገባ፡፡ ሀረር አሉኝ ከምትላቸው ምሁራን አንዱ ነበር፡፡ ማርክሲዝምን ያውቃል፤ አብዮታዊም ነበር፡፡ እብደቱ ሲጀምረው ጥቃቅን ነገሮችን ይለቅም ጀመር ሂደቱ እድገት እያሳየ ሄደ አሁን ተለቅ ያሉ ነገሮችን ይሰበስባል፡፡ እንደ ሲጃራ ፓኬት ለምሳሌ! ምናልባት ቦብላ ከአብዮቱ ዘመን ያተረፋቸውን ስድቦች ይሳደባል፡፡ እብደቱ የጂኒየስ ወይም የጠቢብ እብደት ነው እንደ ሳይንቲስቶች፡፡

ሲያገኘው ጥበበን እንዲህ ይለዋል ‹‹ይህን አምስት አመት ሀረር አልነበርክም፡፡ ብትኖር ኖሮ ለኔ ይህን ያህል ብር ታወጣ ነበር፡፡ አሁን ስንቱን ትሰጠኛለህ?››

ጥበበን ስናገኘው ቆብ ደፍቶ ነው፡፡ ሰባት ስምንት ዘጠኝ ቆብ ሊኖረው ይችላል፡፡ የቆዳ፣ የጨርቅ፣ የሱፍ ቆብ ሸፍኖታል ከልሎታል፡፡ ከቆቡ ወረድ ስንል አይኖቹ መነፅር ከልሏቸዋል፡፡ ከዚያ ወረድ ስንል ፊቱን ጺም ከልሎታል፡፡

እንዴ? ሰውየው ከጀጎል ፍቅር ናፍቆት የተነሳ አዲስ አበባ ውስጥ እየኖረም ስጋ ለበስ ጀጎል እየሆነ ነው እንዴ? አሁን ጥበብንና ሀረርን እንደ ወደ ልብወለድ መሳይ እያስመሰልኳቸው ነው መሰለኝ፡፡

ምን ላርግ ብላችሁ ነው? ሀረር የመካ መዲና ታናሽ እህት የምትሆነው ባንድ ጎኗ ሲሆን በሌላ ጎኗ ደግሞ የባግዳድ ታናሽ እህት ናት፡፡

ባግዳድን ለማታውቁ ትንሽ ማሳወቂያ፡፡ አሁን የኢራቅ ዋና ከተማ የሆነችው ባግዳድ በሌላ ጎኗ የተረት ዋና ከተማ ነች፡፡ ንግስት ሻህራዛድ አንድ ሺህ በአንድ ለሊት ከተናገረቻቸው አስደናቂ ተረቶች ብዙዎቹ በባግዳድ ከተማ ውስጥ የሚደረጉ ናቸው፡፡ ሱልጣን ሀሩን አል-ራሽድ የንጉስ ልብሱን አውልቆ የተራ ሰው ልብስ ለብሶ ተራ ከተሜ መስሎ ከቤተ-መንግስቱ ይወጣና ባግዳድን ይዞራታል፡፡ እንዴት እንደ ሆነች ለማየት፡፡ ባለሚሎቹ የሚነግሩትን ባያምንስ? ፍትህ አለ ወይ ባግዳድ? ሀሩን አል-ራሽድ ባግዳድን ይሰልላታል፡፡ (የኛ አፄ በካፋም እንደዚህ ያደርግ ነበር ይባላል፡፡) በሀረር መንገዶች ስንዘዋወር አንዳንድ ጊዜ ባግዳድ ውስጥ ያለን ይመስለናል ይላል ጥበበ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ጥበበና ሀረር ይምታቱብኛል ወይም ሀሳቤ ውስጥ ይገማመዱና አንድ ይሆኑብኛል ወይም ቃላት የሉኝም፡፡ ስለ ሀረር የሚያውቀውን አብዛኛውን የነገረኝ እሱ ስለሆነ እና በኔ ቤት እንግዲህ አንድ ስልጣኔ ታላቅ ወይም በህይወት ያለ ለመሆኑ መለኪያው የሀብቱ ወይም የሰራዊቱ ወይም የሁለቱ ብዛት አይደለም፡፡ መለኪያው የሰው ልጅ ነው፡፡ ‹‹ሰው የነገሮች ሁሉ መለኪያ ነው›› ብለዋል ግሪኮቹ፡፡

ማለቴ - አንድ ስልጣኔ በስጋ የማይዛመዱትን ሰዎች ከውል ከሩቅም ይሁን ከቅርብ - ለመሳብ የሚያስችል ውበትና ሀይል ሲኖረው - ተስበው ከመጡ በኋላ ደግሞ ከየት እንደመጡ ተረስቶ ወይም ተትቶ በነብሳቸው (ወይም በእምነትና በአስተሳሰብ በአኗኗራቸው) የዚያ ስልጣኔ ሙሉ አባል ሲሆኑ ያ ስልጣኔ በህይወት አለ ማለት ነው፡፡ ባረጀው ጆጎል ውስጥ የምትኖረው የወጣቷ ሀረሪ ስልጣኔ ከሩቅ ትጣራለች፡፡ አረቦችና ህንዶች ለሰላማዊ ጉብኝትና ንግድ መጡ፡፡ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሰር ሪቻርድ በርተን ዝነኛው እንግሊዛዊ ተጓዥ የህንድን አገር ሼክ ተመስሎ ሀረርን ጎበኘ፡፡ በዚያን ጊዜ ካፊር ፈረንጅ (ማለት እስላም ያልሆነ) ቅድስት ከተማ ሀረርን ይረግጣት ዘንድ አይፈቅድለትም፡፡ ሼህ በርተን አገሩ ሲገባ ስለሀረር መፅሀፍ አሳተመ፤ ከእስልምና ውጪ ያለው አለም ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሀረር ሰማ፡፡ ከዚያ በኋላ አርተር ራምቦ ሀረር መጥቶ ለጥቂት

አመት ተቀመጠ፡፡ የክፍለ-ዘመኑ የፈረንሳይኛ ስነ ግጥም ቁንጮ በመሆኑ (በተለይ ከአስራ ዘጠኝ አመት እድሜ በኋላ አንዲት አጭር ግጥም እንኳን ፅፎ የማያውቅ በመሆኑ) ሀረር ፈረንጅ አፍ ገባች፡፡ ከዚያማ በዘመናችን ሀረር ስንትና ስንት ቱሪስት አስተናገደች፡፡

ከ1675 እስከ 85 በፈረንጅ አቆጣጠር ሀረር በግብፅ ወታደራዊ ግዛት ስር ወደቀች፡፡ ማለት አሚር አገሩን መጠበቅ አቃተው፡፡ ለአሚር ይብላኝለት እንጂ፡፡ አደሬ ግን ራሱን መጠበቅ አላቃተውም፡፡ አልሀምዱሊላሂ! የምትከተለው ትንሽዬ ታሪክ ትመስክር፡፡

መስማት እስኪታክተን ድረስ በየዘመኑ በየአገሩ ሲደረግ እንደቆየው ሁሉ የግብፅ ወታደሮችም ማናለብኝ ብለው የአደሬን ሴቶች መድፈር ጀመሩ፡፡

‹‹ዝም ትላለህ ጎበዝ!›› አደሬ ከእለት ስራው በኋላ በየጀምአው በርጫ ላይ መከረ፡፡ ቀጥሎ በቶያ ደረጃ ተመከረ፡፡ ከዚያም በአምስቱ በር ደረጃ ተመከረ፡፡ ምክሩም በስራ ላይ ዋለ፡፡ ሰው እስኪደርስላት መከራከርያ እንዲሆናት፡፡ ከሱሪው ላይ ከእምብርቷ በታች ቦግ ብሎ በሚታይ ቀለም ክር የተጠለፈ መስቀል!

ጉልበተኛው የግብፅ ወታደር ሴት አገኘሁ ብሎ አስገድዶ ቀሚስ ገልቦ ሱሪ ሊያስወልቅ ሲል ምን ያያል ያንን መስቀል፡፡ ‹‹ላ ኢላህ ኢለላህ (እቺማ ካፊር (እስላም ያልሆነች) ናት እሷን መተኛት ሀራም ነው እርኩስ ናት፡፡) ምን ቢርበው የአሳማ ስጋ አይበላም ይተዋታል፡፡ ሰባት አመት እንኳን ሳያገኝ ቆይቶ ቢሆን ክርስቲያን ሴት አይተኛም፡፡ እንግዲህ ከወታደር ጉልበትና ከአደሬ ጭንቅላት ኧረ የትና የት!?

ያቺ መስቀል ስራዋን ስለሰራች ለማስታወሻ ይሁን ወይስ የአደሬን ብልህነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንድትመሰክር ይሁን ወይስ ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ይኑራት (እኛ ገና ያልደረስንበት ምክንያት) ያቺ መስቀል በአደሬ ሴት ሱሪ ላይ የባህል ልብስ ምልክት ሆነች፡፡ እኔን'ኳን ስለ ሰአሊ ጥበበ ተርፋ ልፅፍላችሁ ነበር የተነሳሁት ሀረሪቱ

አልተቻለችም፡፡ ዘፋኙ ስለቦረና የገጠመው የኔን ስሜት ስለሀረር ቆንጆ አርጎ ይገልጥልኛል፡፡

ቦረና ቦረና ቦረና ገነቴ
አብረከረከችኝ ገባች በጉልበቴ››

ይህቺን ባለ ዘጠና ዘጠኝ መስጊድ ከተማ በስውር መስቀልን እንድታስተናግድ ከማድረጉ በስተቀር ግን የአስር አመቱ የግብፅ ወታደራዊ አገዛዝ በአደሬ እለታዊ ህያው ስልጣኔ ላይ ያመጣው ለውጥ የለም፡፡ (የአምስት አመቱ የጣሊያን ግዛት በአዲስ አበባ ላይ ያስከተለችውን ለውጦች ብናስብ ግን!) እንዲያም ስንል ግን ግብፃዊያን በገቡበት በአንዱ በር ሰፈር ግማሹ ጀጎል ግማሽ ግብጢ የሆኑ ጥቂት መኖርያ ቤቶች ተሰርተዋል፡፡

የጀጎል የድንጋይ ቤት ላይ የግብጢ የእንጨትና የመስታወት ፎቅ ለአይን ደስ የሚል በእንጨትና በመስታወት ይህን የመሰለ ውበት ሰሩ! ሀረርኛው ተጋብቶባቸው! ከነዚህ ፎቆች አንዱ ውስጥ ነበር በኋላ አርተር ራምቦ የኖረው እየተባለ በጃንሆይ ዘመን ብዙ ቱሪስት ጎብኝቶታል፡፡ አብሮትም ፎቶ ተነስቷል - ፈረንጅም ሀበሻም ቱሪስት፡፡

አንድ ቀን የጥበበን ቤት የፊት በሩን ከፍቼ ስገባ ፊት ለፊቴ አትክልት ውስጥ ሳር ያለባት ስፍራ ላይ ጥበበ ቁጭ ብሎ አንድ የቆመ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ስእል ይሰራል፡፡ የሰው ስእል፡፡ ጥበበ ቁጭ ብሎ ቁመቱ ከጠፍጣፋው ድንጋይ እኩል ይሆናል፡፡

‹‹ምን እያረጋችሁ ነው?›› ብየው ሊሆን ይችላል ጥበበን፡፡

‹‹ድንጋይ ላይ ያልነበረ ሰውን በስእል ስናኖረው - ስናነጋለት፡፡ ቆይማ እዚህ ጥርሱ ላይ ደግሞ ፈገግታ እናንጋበት፡፡ የነጋበት ድንጋይ፡፡ አየህ በፊትም ጅቡ'ኮ ዝም ብሎ ጅብ ነበር፡፡ ሲነጋ ጊዜ የነጋበት ድንጋይ ሆነ፡፡››

አትክልቱ ውስጥ ሶስት ይሁን አራት ሌሎች ሀውልቶችም አሉ፡፡ ከጥበበ ጋር ስሆን ቁጥሮችና ምናምኖች ትዝ አይሉኝም፡፡ ሀውልቶቹ ቀለማት አይተዋቸው እስኪነጋባቸው ድረስ ድንጋይ ቆርቆሮ እንጨት

ወዘተ የነበሩ ናቸው። ከቆርቆሮው የተሳለችው አጥር ላይ - እሱም ቀለማት ለብሷል መቸስ - አይኖች ይታያሉ። በሩ ላይ ዝነኛዋን ፈረንሳዊት የሲኒማ ተጫዋች ማሪያን ብሪዢት ቦርዶን ታስታውሰኛለች።

ቤቱ ውስጥ ስንገባ በየግድግዳው ላይ የጥበበ ስእሎች ተሰቅለዋል። አንዱ ስእል ቆመን ረዥም ሰአት ማሳለፍ እንችላለን። ለዚያውም አይተን አንጨርሰውም ሌላ ቀንም ሌላ ቀንም፣ እየደጋገምን ብናየው ሁሌ አዲስ ይሆንብናል። ከውበቱ ባሻገር ጭንቅላታችንን ብዙ፣ ብዙ ያጫውተዋል።

ድሮስ ስለ ስእል ምን መናገር ይቻላል? አይቶ ተደንቆ ተደስቶ ዝም ይሻላል።

አሁን ስለ ሰውየው ስለ ሰአሊው ጥበበ ተርፋ - ዘብሔረ-ጆጎል ዝንቱ ውእቱ ሰአሊ ዘይነብር ለአዲስ አበባ። መሳል በጣም ይወዳል። ከተነሳበት ሌሊቱን ሲስል አድሮ አነጋግ ላይ ይተኛል። ስቱዲየው (ማለትም የስእል መሳያ ክፍሉ) ውስጥ እሁድ ከወዳጆቹ ጋር በሚዝናናበት ሰአት እንኳ (ጋደም ብሎ በአደርኛ ትራስ መሳይ ነገር ላይ አስደግፎ) በእርሳስ ይሁን በብእር ወረቀት ላይ ስእል መሳይ ነገሮችን እየሰራ ሳይሆን አይቀርም።

እንዲያም ሆኖ ግን ጥበበ ሰአሊ ብቻ ነው ማለት አይደለም። ከዚያ በቅድሚያ ሰው ነው። እንግዲያውስ ሰአሊነት ከቀን በኋላ የመጣ ነገር አይደለ? ሰውየው የአርባ አራት አመት አባወራ ነው። የሁለት ልጆች አባት።

ሰውየው ሙዚቃን እጅግ በጣም ይወዳታል። ቤቱ ሙዚቃ ሲሰማ ውሎ ሲሰማ ይመሻል። የምእራባዊያን ክላሲካል ሙዚቃ፣ የኒግሮዎቹ ጃዝ ይሁን ብሉዝ፣ ስቃይና ሀዘንን የሚዳስስ የህንድ ሙዚቃ፣ ሰላም የሚንሳፈፍበት የዜን ቡዲህስት ሙዚቃ፣ አታሞዎችና ከበሮዎች ምት የሚቀባበሉበት የምእራብ አፍሪካ ሙዚቃ፣ ሚውረገረግ የሚንቀጠቀጥ የአረብ ሙዚቃ፣ ኧረ ስንቱን ዘርዝረን እንዘልቀዋለን!? የሰማነው ይበቃል

ተዉት አቦ ሰውየው ከዚህ አለም ጋር መጨቃጨቅ አይፈልግም። አንዳንድ ሰዎች እንኳን አሉ ስእሉን ወደውለት በዱቤ ወስደውበት

ሳይከፍሉት ብዙ ጊዜ ከመቆየታቸው የተነሳ ሳይከፍሉት የቀሩ ሊመስሉ ትንሽ የሚቀራቸው። "ክፍለኝ'ንጂ አንተ ረሳ'ክው'ንዴ" ሊላቸው አይሆነለትም። እሱ በበኩሉ ቀለማቱን መስመራቱንና ብርሀናቱን ከነጥላዎቻቸውና ከነጨለማዎቻቸው ይጋተራቸዋል። እፊቱ የሚያፈጠው ባዶ ነጭ ሸራ አይነት። ጥበበ ሙዚቃዎቹን በተቀባይ ጆሮዎቹን ሲሰማቸው ሲወዳቸው ያረፍድና ይውልና ስእሎቹን እየሰራም ይሰማቸዋል፣ ቁርሱን እየበላም። ሲተኛ ከቀን ወደ ለሊት የሚያሻግሩትን ነገሮች እያደረገም ሙዚቃዎቹን ይሰማቸዋል። (በመጨረሻ ሙዚቃውን የሚያጠፋው ማን ይሆን? ገና የታወቀ ነገር የለም)

በሌላ ቀን ሀሩን አል-ራሺድ በለሊት ንጉስነቱን አውልቆ የባግዳድን ከተማ ተራ ሰው ሆኖ እንደሚያያት ሁሉ ጥበበ ተርፋም ስአሊነቱን አውልቆ ከቤቱ ይወጣና አታክልተኛ ሆኖ ፍጥረትን ያያታል። ይሰልላታል ይደነቅባታል። አጃኢብ ነው!

የእፅዋትና የአበባዎች ትብብር ከነንብ፣ ከነቢራቢሮ፣ ከነ ሌላም በራሪ ነፍሳት ጋር እነዚህ በራሪ ነፍሳት ምን ያክለውን ማነስ ትንሽዬ መሆን ለአይን የጥርጣሬ ያህል ከመታየታቸው በስተቀር የሌሉ እስኪመስሉ ድረስ ማነሱን ይችላሉ። ወይም ፈጣሪው ችሎበታል። ጥበበን ከሆንክ እንግዲህ ያ ሁሉ ማነስ ከስእል ተአምራት እኩልና እንዲያውም የበለጠ ያስገርምሀል። አጃኢብ ያስብልሀል።

የማነስ ውድድር የታወጀ ይመስል ክንፍ የሌላቸው ደግሞ በበኩላቸው ከጉንዳን ወደታች እያነሱ ሲሄዱ ለአይን ሊጠፉ እስኪቃጣቸው ድረስ በየጎመኑ ቅደም ተከተል ሲሄዱት ወይስ ያውቁታል? እኛ የማናውቀው ድንቅ መግባባት ሳይኖራቸው አልቀረም እነዚህ ቋሚ እፅዋትና ተንቀሳቃሽ ነብሳት። መሬቱ ሳይሆን አይቀርም የመግባቢያ ቋንቋቸው።

ከትንሽ ወደ ባሰ ትንሽ እያነሱ ሄደው ከአይን የሚጠፉት ጥቃቅን ነፍሳት አትክልተኛ ጥበበ (ስአሊ ጥበበ አለመሆኑን ለማስታወስ ያህል) በእጅ የምትያዝ ማጉሊያ መነፅር ይዟል። ከየትና እንዴት እንዳገኘት

የታወቀ ነገር የለም። መጠኗ በሚጢጢ ሽጉጥና በጠብዢራ የሾርባ ማንኪያ መካከል የሚመደብ። እሷን አሳዳጊ መነፅር ያነፃፅርባቸዋል።

አጃኢብ ነው! አይቶ ከመደነቅ አልፎ የሚያደርገው ነገር ቢኖር እንደገና መደነቅ መደመም ይሆናል።

የስቱዲዮውን ውስጥ ቀለማትን፣ ብሩሾችን እርሳሳትን በቢራቢሮ ልስላሴ የሚይዛቸውና የሚያንቀሳቅሳቸው የጥበበ ቀኝ እጁ አሁን ተለውጦ ልክ ባረሰው መሬት የኮራ ገበሬ ይመስል መሬቱን አፈስ ያደርግና ያሳየኛል። እሱም ራሱ እንደ አዲስ ያየዋል እና ብዙ ያወራልኛል። ስለነዚህ አትክልት የህይወት ታሪክ "ከነዚህ እፅዋት ጋር እንተዋወቃለን አብረን ኖረናል" ጥበበ በግብታዊነት ከህረር አብዮታውያን ንዝንዝ ጭቅጭቅና 'ሙሽራ ደረሰ በርበሬ ቀንጥሱ' ትእዛዞች አምልጦ ወደዚህ መጣ። "ስእሊ ነው" ሲሉዋቸው መጡና "ቀይ ኮከብ ሳልልን" አሉት። የደርግን ሩቅ ሩቅ አባሎች ከመራቃቸው ብዛት የጥፍር ያህል መረሳት ሊደርስባቸው የሚችል ባለስልጣኖች ነበሩ። ጥበበ እነዚህንም የመንግስት ባለስልጣናት ሸወዳቸውና ባቡሩን ተሳፍሮ ወደ አዲስ አበባና ምን እንደሚጠብቀው ወደማይታወቅበት ጭለማ ከተፍ! (ተወን አቦ! ያን ጊዜ አመተምህረት የለም)

እነዚያን የሲኦል አመታት እንዝለላቸውና -

አሁንም ቢሆን ጥበበን ሆኖ መኖር ያስፈራል ባንድ መልኩ ስናየው ወላ ቋሚ ገቢ ወላ ደመወዝ የለውም ሰውየው። ኢግዚብሽን ወደሚያሳይበት መጨ ጊዜ እያነጣጠረ ስእሎቹን መስራት ነው።

ስእሎቹስ ተሰሩ? ስእልና ጊዜን ማን ያገናኝ?

...እነዚያን (የተሰሩ?) ስእልና ገዥን የሚያገናኙ ወይም እናገናኛለን የሚሉ ሰዎች እንለፋቸውና እኔ በበኩሌ ሲበዛ ይደብሩኛል። ጥበበ በበኩሉ ያን ያህልም የሚጨነቅ አይደለም ከመሬቱና አትክልት ጋር ሲመሳጠር ነው የምናገኘው። የእንሰት፣ የሙዝ ኮባ እየተጠቀለሉ መብቀል ጥበበን ያስገርመዋል። የተጠቀለለውን እየፈታህ፣ እየፈታህ ብትሄድ ትደርሳለህ?

መጠቅለያ ቅጠልያው በህይወት ያለው ምን እየጠቀለለ እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ባይን አልቦን ለመጠቅለል ነው ያ ሁሉ መብቀል? አሉ ምስጢሮች የማንደርስባቸው፡፡ አንዲቷ ፍሬ ውስጥ አንድ ሙሉ ዘር አለ፡፡ የሙሉ ዛፍ ህይወት አላማ ልፋትና ተስፋም ፍሬ ለማፍራት ነው፡፡ እውስጧ ሙሉ ዛፍ ያላት ፍሬ፣ በኋላ ከውስጥዋ በቅሎ አላማው በሙሉ እሷን ለመተካት፡፡ እኮ ምን እየተደረገ ነው?

ጥበበ "የጓሮ አትክልት" የሚባለው ነገርም አለው፡፡ የጓሮ አትክልት ስንል ሆድን እናስባለን፡፡ ቆስጣ፣ እስፒናች፣ ጥቅል ጎመን፣ ካሮት፣ ዝኩኒ፣ አጦዶ፣ ኮክ፣ ሮማን፣ ሙዝ፣ ሎሚ፣ ፖም፣ ቡና (ሻይ የለም) እንጆሪ፡፡

እንጆሪ ብትል ፍሬውን መብላት ብቻ አይደለም፡፡ የእንጆሪ ማርማላት ሰርቶ በዳቦ ቀብቶ መብላት ይኸ ይኸ ጥበበ ቤት ተደርጎ ያውቃል፡፡

ጥበበ ሰው አክባሪ ነው፡፡ እንግዳውንም ጓደኞቹንም ሰራተኛውንም ያከብራል፡፡ የእውነት፡፡

ከዚህ ጋር ግን እንዲህ ይላል ጥበበ "የሰው ልጅ ክቡር ነው የሰው ልጅ ትልቅ ነው፣ የሚባል ነገር አይገባኝም ባክህ፡፡ የሰው ልጅ ክፉና ጨካኝ አጥፊ ነው፡፡ ሩቅ ሳትሄድ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉትን እንስሳት ኑሮ አስብ፡፡ ደሞስ ሰው አጉል ፍጡር ባይሆን ኖሮ አቶሚክ ቦምብን ያህል ነገር መስራት ያስፈልግ ነበር? ከዚያም ሀይድሮጅን ቦምብ የተከማቸው ቦምብ ይቺን አለም አስር ሃያ ጊዜ ደጋግሞ ሊያጠፋት ይችላል፡፡ ያውም አንዴ መጥፋት አይበቃትም አጃኢብ!"

**ጥር 22/ 29 ቀን 1986**

# ስለሊውን ስንሰናበት

ጥበበ ተርፉ ተወልዶ ካደገባት ከጆጎል በአብዮታውያን አስገዳጅ ሁኔታዎች ግፊት አምልጦ ወጥቶ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ መኖር ጀመረ። ግማሽ በይፋ ግማሽ በድብቅ መኖር።

ያለ አንዳች የገቢ ምንጭ። የዛን ጊዜውን የጥበበን ኑሮ ሳስታውስ ኢየሱስ የተናገረው ትዝ ይለኛል። ‹‹ቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው! ወፎችም ጎጆ አላቸው! የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሳርፍበት የለውም።››

እሱንስ እንደምንም በቻለው። ላያስችል አያሽክምሳ ከዚህም ጋር አዲስ አበባ ውስጥ አደሬዎች አሉ። እልምዲልላሂ!

ዳሩ ምን ይሆናል ባዲስ አበባ መንገዶች ሲሄዱ ቆይተው ቀና ቢሉ ሰማይን ጆጎል አልደገፈውም። ብንን ይላል ጥበበ። ጆጎልን አለማየት ከሀራም ይብሳል። ዱካክንም ያህል ይቀጣዋል። ባንድ በኩል ብናየው ጥበበ ራቁቱን እንደሆነ አይነት የሚመስል ስሜት ሳያድርበት አልቀረም። አለዚያ ለምን ቀብ ያደርጋል? መነፅሩስ ምንድነው? ጢሙስ የምን ተጨማሪ ነው? ለመክበብ። የጆጎልን አካባቢ ለመተካት። ቀጥሎ የእጅ ጓንቲ ለማድረግ ያስብ አያስብ ገና የታወቀ ነገር የለም። ጠላት ይሁኑ ወዳጅ ገና ለይተን ካላወቅናቸው ሰዎች ይህን ጉዳይ በተመለከተ የሰማነውን በአጭሩ እነሆ!

ጥበበ በጆጎል ናፍቆት ተቅበዘበዘ። ይህንን ያስተዋለ አንድ አደሬ (በበርጫ ሰአት) ‹‹አቦ! ጥበበ አይ-ኮከቤ ዋሻ በሌለበት ከምታብድብንና ግራ ከሚገባን ምናለ በምርቃና አውዘል ቀርነይኒን ብትለማመናቸው።››

‹‹ምን ብዬ?››

‹‹አራዲሎ በኔ ልመና አንተ ጆጎልን ልታያት አሰብክ'ንዴ?››

‹‹ለማንም እንዳትታይ እንዳትታወቅ - ግን ላንተ ለብቻህ በሳምንት እንደ ጁምአ ቀን አመሻሽ ላይ - እንደ ወደ አስራ ሁለት ሰአት ላይ እጣንህን አጭሰህ አንዴ ወደ አድማስ በኩል አይንህን ወርወር ስታደርግ ጀጎል ራሿን እንደ ለማያዊ ሳር ክዳን ተሸክማው ስታይ - አስር ደቂቃ ይበቃሀል። ነብስህ ትሽራለች እውነቱን አይደል?››

‹‹እሱስ እውነትክን ነበር›› ይላል ጥበበ ‹‹እኔ ግን ለናፍቆት ወይ ለገንዘብ ብዬ አውዘል ቀርነይኒን አላስቸግራቸውም። ለስእል ብዬ ግን ላስቸግራቸው እችላለሁ።››

‹‹እንዴት ማለት?››

‹‹ይህ ስጋችን አይታመንም መቸስ አንድ ቀን ወይ አይኔ ወይ እጄ ሊከዱኝ ይችላሉ፤ እንዳቸው ሊከዱኝ እንደጀመሩ ሲታወቀኝ፣ ያን ጊዜ ብቻ ነው አውዙል ቀርነይኒን አንዲት ልመና የምልክባቸው።››

‹‹ምን ትላለህ በልመናው!››

‹‹ኑ! ስእሎቼን እዩልኝና የምታረጉትን አርጉልኝ እላቸዋለሁ።››

‹‹ያዩታል። ምንድነው ይህ ደሞ? ኢብሲሳ! የአለምን ቀለማት ሙጥጥ አድርጎ ጠጥቶ ሰክሮ ያስታወከው የሚመስል ይሉሀል››

‹‹እንተን ቢሆኑ እንደሱ ይሉኝ ነበር። እሳቸው ግን ምን እንደሚሉኝ ልንገርህ?››

‹‹ምን ይሉሀል?››

‹‹እህ! አንተ ሰው ቀስተ ደመናይቱን ሰርቀህ ነው? ለምነህ ነው ወይስ እንዴት አግኝተሀት ነው ለነጣጥቀህ እዚህ ሸራ ላይ የበተንካት? ይሉኛል።››

‹‹አይ ጉራ! አይ ቡፋ! አይ ትእቢት?››

‹‹ጉራ ቡፋ ከመንፋት አውዙል ቀርነይኒን ከማስቸገር ግን የቱ ይቀል ይመስልሀል። ለማንኛውም ያንተን ነገር ሰውየው ጨርሶታል።››

‹‹ምን ብሎ ጨረሰው ባክህ?››

‹‹አይን አላቸው አያዩም››

‹‹አትለኝም!››

‹‹ያልኩህ መሰለኝ፡፡ ሰውየው ያለውን ተጨማሪ ልጨምርልህ?››

‹‹ጨምርልኝ››

‹‹ጆሮ አላቸው አይሰሙም››

ግድ የላቸውም ቀደም ሲል እንዳልነው ጠላት ይሁኑ ወዳጅ ገና ለይተን ያላወቅናቸው ናቸው ይህንን ሲያወሩ የሰማናቸው፡፡

እኛ ግን ወዳጅ ነን - እንዲሁም አድናቂ፡፡ ኧረ ቲፎዞም ጭምር ነን፡፡ ማን ይከለክለናል? ደሞስ ከመቼ ወዲህ ነው እንደ ጃንሆይ ‹‹እኛ›› እያልን መናገር የጀመርነው? አይ-ኮካሄ እየጠራችን ይሆን'ንዴ?

አሁን እውነት ጥበበ ተርፋ የደብተራ ያህል በቃላት ከንቱ ካራቱ ይጫወታል፤ ወይስ ሳላውቀው የራሴን የደብተራ ነብስ አዋስኩት ይሆን 'ንዴ? ለማንኛውም እኔ ግን የተነሳሁት የሚከተለውን ልፅፍላችሁ ነበር፡፡ እስካሁን ያነበባችሁትን ማን ወይም ምን እንዳስፃፈን አላውቅም፡፡

ሀረር የመካ መዲና ታናሽ እህት ብቻ የምትመስላቸው እና በሌላ ጎኗ የቅርቡ ምስራቅ አለማችን የተረት ዋና ከተማ የሆነችው የባግዳድ ታናሽ እህት መሆኗን የማያውቁ አሁን የምንጥፌውን ባያነቡ ይሻላቸው ይሆናል፡፡ እነሆ በረከት!

የእብዶች ማደሪያ የሆነችው ተናፋቂቱ ሲመሽ ኑ ግቡ እንቅልፍ አስጣችኋለሁ ጥንት አለም ከተፈጠረ ጀምሮ ተሰምተው የማያውቁ ድምፆችና ድምፃት ሁሉ አይ-ኮካሄ ዋሻ ውስጥ በጨለማ ዋሻ ተጠቅልለው ይገኛሉ፡፡ እድሜ ከሰጠህ አንድ ቀን ጥበበ ስለአላቸው ይሰራልህና ታየዋለህ፡፡ ጥበበ የአይ-ኮካሄን ጨለማ ከነድምፆቹ በስእል ሊያሳይ አይችልም የሚሉ ቢኖሩ ግን ብዙሀን ለመሆን ተስፋ የሌላቸው

ናቸው፡፡ የሰአሊዎች ቁንጮ ከሆነው ከራምብራንት የጨለማ ስእል ላይ ጥቁር ብልጭታ አይናቸውን ያላስከፈታቸው ናቸው፡፡

የጥበበ ስእሎች ጆጎልን እየረሱዋት ይመስላል፡፡ አይ-ኮካሂ መጣንልሽ! እድገት እንበለው ወይስ ለውጥ በጥበበ ስእሎች ላይ እየታየ ነው፡፡

ባይገርማችሁ ከዚህ ጋር ደግሞ ሰማይና ምድር ከተፈጠሩ አንስቶ የታሰቡ ሀሳቦች እና ሊታሰቡ ሲሉ ሰንፈው የተውት ሀሳቦች እነዚህ ሁሉ ጥበበ ጭንቅላት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ከጥበበ ጋር ስትሆን ስላፈቀደህ አርእስት ልታዋራው ትችላለህ፤ አይሰለችህም አይደብርህም እንዲያውም ጭንቅላትህን ፈጠን፣ ፈጠን ሲል ትሰማዋለህ ጥበበ የሚለውን በመከተል፡፡

ብልጥ ነን የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ ክፋት እንደሌለበት ስለሚያዩ ጥበበ የዋህ ገራገር ይመስላቸዋል፡፡ ጥበበ እነዚህ ብልጦች ሲበልጡት እያየ ውስጡ ይስቃል፡፡ በነሱ ቤት ማንም አልነቃባቸውማ፡፡

ጥበበን ቻዎ ስንለው ሲጃራ እያጨሰ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ሲጃራ የሚያስጥል ድግምት አለ ቢሉት ጥበበ ሊሰማው አይፈልግም፡፡ ሲጃራ ማጨስ ይወዳል!

የካቲት 6 ቀን 1986

# ጀርመን

አንድ ቀን ጥበበ ተርፋ ቤት ስሄድ እሱና አንድ ካርል የተባለ ጀርመናዊ በአንድ ሸራ ዳርና ዳር ጀምረው ለሁለት አንድ ስእል እየሰሩ ነው፡፡ ሁለቱም በየበኩላቸው ስእላቸውን እየሰሩ ይሄዱና ወደ ሸራው መሀል ሲደርሱ ስእሎቹ ይገጣጠማሉ፡፡ አንድ ስእል ይሆናሉ፡፡ ከተገጣጠሙ በኋላ ሁለቱ ሰአሊያን ይህን አንድ ስእላቸውን በየበኩላቸው እዚች ጋ ነካ እዚያች ጋ ቀባ እያደረጉ የስእሉን አንድ ስእልነት ያረጋግጣሉ፡፡

ሌላ ቀን ደሞ ጥበበ ገተ ኢንስቲቲዩት ኤግዚብሽን ሲያሳይ ከመግቢያ ኮሪደር ላይ አንድ ባዶ ሸራ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ አጠገቡ ብሩሾችና ቀለሞች አሉ፡፡ የኤግዚብሽኑ ተመልካች ወደ ኤግዚብሽኑ እየገባ ይሁን ወይም አይቶ እየወጣ ሳለ ካሰኘው እዚህ ሸራ ላይ ስእል ይሰራል፡፡ ጥበበም አብሮት ይሰራል፡፡ ያሰኘውን ያህል ከሰራ በኋላ ይተወዋል፡፡ ሌላ በል ያለው ተመልካች እዚሁ ጅምሩ ላይ ይቀጥልበታል፡፡ ጥበበም ይቀጥልበታል፡፡ እንዲሁም ሌላው የነሸጠው ተመልካች ብሩሽ ያነሳል እውስጡ ያለውን የታየውን ለስእሉ ያዋጣል፡፡ እንዲህ እያለ በተለያዩ ተመልካቾች የፈጠራ መዋጮ ስእሉ ነብስ ይዘራል፡፡ በጥበበ ልብ ውስጥ አንድ ምኞት አለ፡፡ እሱም ሌሎች ሰአሊያንና ቀራፂያን ጓደኞቹ እዚህ ከተማ ውስጥ አልፎ አልፎ ባንዳንድ አመቺ አደባባይ ላይ ለአይን ደስ

የሚሉ ነገሮችን ለመስራት፡፡ ሰው በሀሳብና በጣጣ ውስጥ ተውጦ እየሄደ ይቆይና ድንገት ቀና ሲል ወይም አንዱን የመንገድ ማእዘን ሲዞር የአይን ደስታ ቢያጋጥመው ጥሩ አይሆንም? ይህ ምኞቱን ስራ ላይ ለማዋል ጀርመኖቹ በገንዘብ ለመርዳት ፈቃደኛ ናቸው፡፡ . . . . ያስ ይሁን ያዲስ አበባ ቢሮክራሲ ግን ይህን እንዴት ይፈቅዳል? ስንት ኮሚቴ ለስንት ዘመን ይነጋገርበታል? እኔ በበኩሌ ብዙ ተስፋ አይታየኝም፡፡ ቢሮክራሲው እንኳንና ተደርጎ የማያውቅ ነገር ለመፍቀድና የተለመዱትንም ነገሮች በልዩ ልዩ ኮሚቴና ንኡስ ኮሚቴ እያስጠና ማጓተት ነው ስራውና ችሎታው፤ ጥበበ ግን ተስፋ አይቆርጥም፡፡

ጥበበ ተርፋ የጀርመን መንግስት እንግዳ ሆኖ ለሶስት ወር የስራ ጉብኝት በበርሊንና በሌሎች ስፍራዎች ተዘዋውሮ ያጋጠመውን ካጫወተን ብዙ ነገር ጥቂቱን ባጭሩ እናጋራችሁ፡፡

አስደሳቹ ነገር ምንድነው? መልካም አቀባበልና መስተንግዶ ነበር፡፡ የሄደበትን ጉዳይ ፈፅሞ ተመለሰ፡፡ የጀርመኖች አላማ አፍሪካዊውን ስነ-ጥበብ እንዲዳብር እገዛ ለማድረግ ነው፡፡ ከተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ነብስ አላቸው የሚሏቸውን ሰአሊያን ሙዚቀኞች ከያኒያንና ሌሎች የስነ-ጥበብ ሰዎች ለሳምንታት ወይም ለወራት ተገናኝተው የርስ በርስ ስራዎቻቸውን እያስተያዩ አንዱ ከሌላው ልምድና ግኝት እንዲማር ለማስቻል፡፡ ይህ አሰ ራር ለጀርመኖቹ የስነ-ጥበብ ባለሙያዎችና አፍቃሪዎችም ይበጃቸዋል፡፡

እንግዲህ ከጀርመኖቹ በኩል የተዘረጋው በጎ ፈቃድና ተጨባጭ ጥቅም እንደተጠበቀ ይሁን፡፡ ጀርመኖቹ ባያሳስቧቸው ኖሮ አፍሪካውያን ጠቢባን እንኳን ተገናኝተው ጥበባዊ ሀብት ሊለዋወጡ ቀርቶ በፖስታ ሊተዋወቁ'ንኳ ባልተቻላቸው ነበር እድሜ ለጀርመን!

ከዚህ ጋር ግን ጀርመኖቹ (እና ሌሎቹም ፈረንጆች) አፍሪካዊ ስነ-ጥበብ ወይም ‹‹አፍሪካን አርት›› ሲሉ ጥንታዊውን ባህላዊውን ተደጋጋሚውን ማለታቸው ነው፡፡ ይኸው ነው፡፡ ከዚያ ድግግሞሻዊ ስራ ወጣ ብሎ ከሰራ ‹‹ይሄ'ኮ አፍሪካዊ አርት አይደለም›› ይሉታል፡፡ ግን ይሄ አፍሪካዊ የሰራው ስእል እንዴት አፍሪካዊ ስእል አይደለም ይባላል?

ሩቅ ዘመን እንኳን ሳንሄድ ለምእራባዊው ስነ-ስእል ታሪክ በአስራ ዘጠነኛው ምእተ አመት አነጋግ ላይ የተነሳው ኢምፕሬሽኒዝም አዲስ አይነት አሰራር ነበር፤ ግን ምእራባዊ ስእል አይደለም አልተባለም። ኤክስፕሬሽኒዝም መጣ። ከዛ ኪዩቢዝም፣ ሰርሪያሊዝም። እያንዳንዳቸውም ከቀድሞ አሰራር የተለዩ አዲስ ነበሩ። ባዲስነታቸውም «ምእራባዊ ስእል አይደሉም» አልተባሉም።

ምእራባውያን ሰአሊያን በየሁለት በየሶስተኛው ትውልድ አዲስ አይነት ስእል ይስሩ፤ አፍሪካውያን ግን ያንኑ ብቻ ይደጋግሙስ ይባላል? ሆን ተብሎ አይሁን እንጂ ግን እየተባለ ነው። ምእራባዊው ስነ-ጥበብ የየራሱን ዘመን እንዲመስለው ይገልፁታል። በስእል ይሁን በፅሁፍ በሙዚቃ እንደየዘመኑ ይለዋወጣል። አፍሪካዊው ግን የሙዚየም ሰአሊ ይመስል የድሮውን ብቻ ይድገምን? ፈረንጁ የነገ ሰው ነው፤ አፍሪካዊው ግን የትላንት ሰው ነው።

አፍ አውጥተው አላሉንም'ንጂ ያሉን ያህል ነው። የኛ ፋንታ ይህን በጎ ፈቃድ በግልፅ የሚታይበትን ድጋፋቸውን መቀበል። ጥበባችንን ስንሰራ ግን እነሱ በሚነግሩን ወይም በሚመክሩን ሳይሆን ያገራችን የጥበብ አድባር በምታሳየን ነው መስራት። ውለው አድረው እነሱም ይታያቸዋል። ይሄ የኛ ሁኔታ የገባቸው አያሌ ፈረንጅ ግለሰቦች አጋጥመውታል ጥበበን።

ጥበበ ተርፋ በጀርመን አገር ሶስት ወር ሲቀመጥ በርሊን፣ ሙኒክ፣ በይሮይድ፣ ኑረምበርግ፣ ኮንስታነስ የተባሉ ከተማዎችን እየተዘዋወረ ጎብኝቷል። እንዲሁም ዙሪክን (ስዊዘርላንድ) ባጠቃላይ አንድ ነገር አስተውሏል። ሌሎችም የኛ ተጓዦች ሌላ ፈረንጅ አገርን እያዩ ያስተዋሉት ነው።

ሄደው በአይን ካላዩት ማመኑ ያስቸግራል'ንጂ ፈረንጆቹ ለፍተው፣ ለፍተው በዚች ምድር ላይ የገነኑትን ያህል ምቾትና ድሎት አከማችተዋል። እውስጡ ሲኖሩ ግን እንዴት ነው?

ጢት ሰው ሁሉ ወደየስራው ሲጣደፍ ዘና ማለት ፈገግ ማለት የለም። ኮስተር ብሎ ፈጠን፣ ፈጠን ነው በየአቅጣጫው። ምክንያቱም ለዝግታ ለመንገድ ዳር ሰላምታ ጊዜ የላቸውም። እስራ ቦታቸው ለመድረስ የተወሰነች ጊዜ ብቻ ናት ያለቻቸው። በነሱ ቤት ጊዜ ገንዘብ ነው። መኪና የማይረግጠው አደባባይ አለ። ውፍረታቸው ባዲሳባ ቋንቋ ‹‹የሞጆ ሴት ወይዘሮ›› የሚያስብላቸው ርግቦች መአት ናቸው። አልፎ አልፎ አንዲት አሮጊት ከቤቷ ወይም ከሱቅ በወረቀት ከረጢት ያመጣችላቸውን እህል ትበትንላቸዋለች። እየለቀሙ ‹‹ጉጉግ፣ ጉጉግ!›› እያሉ ደስታቸውን እየገለፁ ደስታ ይሰጧታል። ዙርያውን ሰራተኛው ህዝብ ወደ ስራው ቦታ ለመድረስ ወይ ባቡር ወይ ባስ ለመሳፈር ሩጫ ቀረሽ ፍጥነት ባለው ርምጃ ይፈጨዋል። እዚህም እዚያም እርግብ የምትመግበውን አሮጊት ማንም ልብ አይላትም። ለአሮጊት ጊዜ የለንም ለስራ ቸኩለናል። አሮጊቷን ልብ የሚሏት በዚህ በጠዋት ብርድ ከሞቀ አልጋዋ ወጥታ የእለት ቁርሳቸውን የምታመጣላቸው እርግቦች ብቻ ናቸው። እሷም ብትሆን በየአቅጣጫው ውር ውር የሚለውን ሰራተኛ ህዝብ አታስተውለውም። እንዳይገጫት ከመጠንቀቅ በቀር። እሷ እርግቦችዋ ጋር ደስታዋን እየተቋደሰች 'ምትኖርበት ቤቷ ወይም ወደ ሆስቴልዋ ትመለሳለች።

ይኸው ነው። የፈረንጅ አሮጊትና ሽማግሌ ለአይን ከመታየቱ በስተቀር የሌለ ያህል ነው። ማንም ዘወር ብሎ አያየውም። እርስ በርስ ወዳጅነቱን እንዳይመሰርቱ እድሜያቸው አያስችላቸውም። ብቻቸውን ነው የሚኖሩት። አብሯቸው የሚኖር ውሻ ወይ ድመት ወይ ሌላ ፍጡር ብቻ ነው። ይህ ፍጡር ግን ዞሮ ዞሮ የሰው ያህል አይሆንም።

በቅርቡ አንድ አሜሪካዊ መፅሄት ላይ ያነበብኩት። አንዲት ታታሪ ጃፓናዊት አንድ ድርጅት አቋቁማለች። ብቸኝነት ለበዛባቸው አሮጊቶችና ሽማግሌዎች በሰአት ሰው ታከራያለች። ማለት ለምሳሌ አንድ ወጣት የሷ ሰራተኛ እሮብ፣ እሮብ ከአስር እስከ አስራ አንድ ሰአት እየሄደ አንዱን ሽማግሌ ያጫውታል። አብሮት ሻይ ይጠጣል። ያዋራዋል እንደየ

ባህሪያቸው ይግባባሉ፡፡ ሽማግሌው ለዚች ከሰው ጋር ሆኖ ሊኖራት ለቻላት ስእት በውሉ መሰረት ለድርጅቱ ባለቤት ገንዘብ ይከፍላታል፡፡ እሷም ለዚህ ለወጣት ሰራተኛው ደመወዙን ትከፍለዋለች፡፡

**የካቲት 20 ቀን 1986**

# የሰው የለው ሞኝ

‹‹የሰው የለው ሞኝ፣ የሰው የለው ሞኝ
ባገሩ በወንዙ በስፍራው ሲገኝ
የሰው የለው ሞኝ››

እቺ የዘፈን ግጥም እውነት ወይም ሀቅ የታጨቀባት ነገርዬ ናት። ብዙ ብዙ እውነት ትናገራለች። በደዊን የተባሉትን የአረብ ምድረ በዳ ነዋሪዎች እናስብ። እዚያ በረሀ ውስጥ መኖር መቻላቸው በጣም የሚያስገርም ነው። ምስጢሩ ግመልን ማልመዱና አላህን አምኖ የውሀ ጉድጓድ መቆፈር ላይ ሳይሆን አይቀርም። የሺካጎ ከተማ የጌቶ ሰፈር ወንበዴ እዚህ መኖሯን ያውቅባታል። ምስጢሩ ከፖሊስ መራቅና የሚሰርቁትን ሰው መመዘን ላይ ሳይሆን አይዘልም። ‹‹አካሄዱን አይተህ ጭብጦውን ቀማው›› የምትለውን የቀማኞች ጥበብ ተከናታል።

አንዱን የበደዊን ተወላጅ ካደገ በኋላ ከምድረ በዳው አውጥተን ሺካጎ ጌቶ ሰፈር ብንለቀው በጥቂት ቀናት ውስጥ ያብዳል። ያውም ማጅራት መቺ ባይገለው ነው? እንደዚሁም አንዱን የሺካጎ የጌቶ ዱርዬ ወስደን በደዊኖቹ አገር ብንለቀው በጥቂት ቀናት ይሞታል።

ባገሩ በወንዙ በሰፊው መገኘትን የመሰለ ነገር የለም። ጥንታዊያን ግሪኮች ከሞት ቀጥሎ ትልቁ ቅጣት አድርገው የሚቆጥሩት አንድን ሰው

ካገሩ ከወንዙ ማባረርን ነበር። ስደትን የቀመሰ እቺን ግጥማችንን እጅግ በጣም ያጣጥማታል። እውነትም! ይላል ራሱን እየነቀነቀ።

ሸረሪትን እናስብ። ድርዋን ስታደራ እናያታለን። ሰንበት ሲል ያ ድር ትንኝና ብጤዎቹ ነፍሳት በብዛት ተለጣጥፈውበት እናያለን ደርቀው። ሸረሪት በአገሯ በወንዟ ስትገኝ እንዲህ ነው ታውቅበታለች።

ዝምብ አለች እንጂ። ይልቅ የዝምብ የለውም ሞኝ። አለምን በሞላ ከወረረች ዘንዳ መላው አለም አገሯ ነው ወንዟ ነው። ‹‹ሸረሪት ይላክብሽ›› ብለን ብንረግማትም ቅሉ ዝምብ ግን መባዛትዋንና ሲነሳባትም እርጎ ውስጥ ጥልቅ ማለትዋን ትቀጥላለች። ሰይጣን ንብ አፈጥራለሁ ብሎ ዝምብን ፈጠረ እያልን ስምዋን ብናጠፋም ቅሉ። ዝምቢት ግን ስሜት የሚሰጣት አትመስልም።

እኮ ሰውና ዝምብ ምን ያህል ይለያያል? ያው ሁለቱም ይኖራሉ! ያው ሁለቱም ዘር ተክተው ያልፋሉ። ከዚህ አያልፉም። ይኸው ስጽፍ ዝምቢቱን አንድ ሶስት ጊዜ እሸሸሽ እያልኳት ነው ተመላልሳ ግንባሬ ላይ እያረፈችብኝ። አይ ሰይጣን እግዜር ይይልህ! እስቲ ማን ንብ ፍጠር አለህ! አርፈህ ብትቀመጥ ምን ነበረበት! እንዲህም አርጎ የለ ንብ እቴ!

ኧረ ኮሶ ራሱስ ቢሆን ሆድ እቃችን ገብቶ ሲያበቃ እና ሰርተን ለፍተን የበላነውን ምግብ ሆዳችን ውስጥ በብዙ ሚስጢራዊ ኬሚስትሪ የፈጨነውን ያዘጋጀነውን ምግባችንን እሱ ምንም ሳይለፋ ዋጥ ስልቅጥ የኮሶ የለው ሞኝ። አገሩ ወንዙ የገዛ አንጀታችን መሆኑ ግን እጅግ አሳዝኖናል።

ከምታገዝን ቆፍጠን ብለህ ኮሶህን አትጠጣም? ሳያሽረን ማለት'ኮ ያ ግፈኛ ኮሶ እውስጣችን ተጎልቶ ምግባችንን መምጠጡ አነሰውና እንቁላሎቹን እንድንበትንለት ያስገድደናል። እሱ ቢሞት ግን ያው ዘር ተክቶ ነው። እንቁላሎቹን ከብቶች ከሳር ጋር ይበሉዋቸዋል። ከብቱ ሰውነት ውስጥ ከገቡ በኋላ ፈጣሪ የሰራላቸውን መንገድ ተከትለው እከብቱ ስጋ ውስጥ ቁጭ ይላሉ። ጊዜያቸውን ይጠብቃሉ። ከእለታት

አንድ ቀን ከብቱ ሳር በመብላቱ ሞት ተፈርዶበት ሰው አረደውና በላው፡፡ ብርንዶ ነሽ ቁርጥ ነሽ ክትፎ ነሽ አልቀሩም፣ በሬው አልተረፈም፡፡

ግን በሬ ቢታረድም መጠነኛ በቀል ይበቀለዋል፡፡ አራጁን ከሞት ባሻገር አነጣጥሮ ኮሶን ይተክልበታል፡፡ በዚህ መሀል ኮሶ ተጠቀመች፡፡ አይ ኮሶ! የኮሶ የለው ሞኝ፡፡ አገሩ ወንዙ የሰው አንጀት ብቻም አይደለም የበሬ ስጋም ጭምር ነው፡፡ ኮሶ የዋዛ ሰው እንዳይመስላችሁ፡፡

ዛፍስ ብትሆን ባገሯ በወንዟ ከተገኘች ካንዲት ፍሬ ውስጥ ወጥታ ዛፍ ትሆን የለ? አቤት ስታውቅበት ያቺ ፍሬ አበቃቀሉን! ስር ሰዶ ከምድሪቱ ውሀና ንጥረ ነገራትን በመውሰድና በቅጠሎቹ የፀሀይን ብርሀን በመውሰድ እነዚህን በምስጢራዊ ተአምር ወደ ስር ግንድና ቅጠል ለመቀየር ዛፍ ባገሩ በወንዙ ሲገኝ ያውቅበታል፡፡

ሳርስ ራሷ ብትሆን በቁመት ካልሆነ በሌላ ከዛፍ በምን ታንሳለች? የዛፍና የዘር ቅብብሎሹን ጨዋታ እንደሆን እኩል ትጫወተዋለች፡፡

ኸረ ለመሆኑ ይህ ሁሉ እልፍ እም አእላፍ ፍጡር በየፈርጁ በየተገኘበት ባገሩ በወንዙ የብልጦች ብልጥ መሆኑ በምን የተነሳ ነው?

ሌላ የዘፈን ግጥም አለች፤ በሰማሁዋት ጊዜ ሁኔታዎችን ወለል አርጋ ያሳየችኝ፡፡ ለውጥ እንደተጀመረ ሰሞን ነበር፡፡ ያን ጊዜ እንኳን አብዮት ሊሆን ገና አላሰበም ከመቶ ሃያውም የደርጉ አባላት የርእሰ ብሄር ክብር እንዳላቸው ቢታወጅም ቅሉ መቶ አስራ ዘጠኙ ገና ደፍረው መታየት ሳይጀምሩ ነው፡፡ በህቡእ ወይም በስውር ነበር ሊገዙን የጀመሩት፡፡ አንድ ቀን ታድያ አንዱ ብቻ ደፍሮ እኔ ነኝ መንግስቱ ኃይለማርያም ብሎ በቴሌቪዥን መታየት ሲጀምር እቺ ግጥም በእንጉርጉሮ መሳይ ዜማ ትሰማ ነበር

‹‹ሰው ማለት
ሰው የሚሆን ነው
ሰው የጠፋ'ለት››

አቤት ስንትና ስንት ታሪክ ትናገራለች አይ ግጥም! (እንዲያውስ ግጥም ናት'ንጂ ጥበብ ናት እንጂ) ያዘለችውን ሀቅ እንግሊዞች በምሳሌ ያስቀምጡታል። ‹‹በእውሮች አገር አንድ አይና ንጉስ ነው›› ኧረ ካልክስ ግማሽ አይን ብቻ ቢኖረው እንኳን ንጉስ ነው!

‹‹አባት ማለት
አባት የሚሆን ነው
አባት የጠፋ'ለት››

ጎመንስ ምን አለ? ‹‹አትኩራ ገብስ ጎመን ባወጣው ነብስ?›› በሌላ አባባል

‹‹እህል ማለት
እህል የሚሆን ነው
እህል የጠፋ'ለት›› ተብሎ ቢዘፈንለት ሲያንሰው ነው ጎመን። ከላይ የተናገርነውን የዛፉን ከፍሬ መውጣትና ፍሬ አቶ ጎመን ያውቅበታል ብንል አይበቃም? ተክኖታል ማለት አለብን። አይ አቶ ጎመን!

የካቲት 13 ቀን 1986

# ሰይጣን

አንዳንድ ፈረንጆች ሰይጣን የለም እንኳንና ሰይጣን እግዜሩ ራሱ የለም የሚሉ ቢሆንም እኛ ግን ሰይጣን በረቂቅ ጥበብ ፈረንጆችን ጉድ ሲሰራቸው እየተመለከትን ነው። እና በጣም እየገረመን በጣም እያሳዘነን ነው። በእጅ አዙር እኛንም እያከሰረን ነው። አቶ ልጅ ዲያቢሎስ።

ሰይጣን ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለብሶ ፈረንጆቹን በፋብሪካም በትጋት ገነትን እዚችው ምድር ላይ እንትከላት አላቸው።

የፋብሪካ ስራ ሰራተኛ ሁሉ በሰአቱ በስፍራው እንዲገኝ ያስገድዳል። አንዲት ደቂቃ መዘግየት ክልክል ነው። ቤቴ ራቀብኝ አቶቡስ አመለጠኝ አክስቴ ሞቱብኝና የመሳሳሉት ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም። የፈረንጅ ኑሮ በሰአትና በደቂቃ፣ ታጥሮ ተወጥሮ እንደ ሽማኔ መወርወሪያ ውር ውር ማለት ሆነ። (ይህ እንግዲህ ጥቂቶቹን እድለኞች አይመለከትም)

ገነትን ምድር ላይ የዘረጋት ካፒታሊዝም ነው። የካፒታሊዝም ዋነኛና ብቸኛ አላማ ትርፍ ማትረፍ ነው። የካፒታሊስቶቹ መሰረታዊ እምነት ውድድር ነው። ካፒታሊዝም ገነትን ምድር ላይ የዘረጋት በሰራተኛው መደብ ላብና መስዋእት ነው። በቀን አስራ ስምንት ሰአት ሙሉ እየሰሩ ደመወዛቸው ግን ትንሽ ከመሆኗ የተነሳ ልጆቻቸውን ማሳደግ እንኳን እየተሳናቸው ልጆቹም ሙሉ የፋብሪካው ሰራተኛ ሆነው

ተቀጥረው በቀን አስራ ሁለት ሰአት እየሰሩ መናኛ ገንዘብ ይቀበሉ ነበር፡፡ አንድ የስድስት አመት ልጅ በቀን አስራ ሁለት ሰአት ሙሉ ይሰራ እንደነበር ተዘግቦ ይገኛል፡፡

በዚህ ላይ አንዳንዱ አይነት ስራ ለጤና ጠንቅ የሆነ የከሰል ማእድን ነው፡፡ የጥጥ ልብስ ፋብሪካ ሰራተኞች በዛችው በመናኛ ደመወዝ ለጥቂት አመታት ከሰሩ በኂላ ሳምባቸውን ይታመማሉ ከስራ ይባረራሉ ጥቂት ወራት ወይ አመታት ከተሰቃዩ በኂላ ይሞታሉ፡፡ በተጨማሪ የማእድን ሰራተኞች ቀን የጎደለባቸውእለት መሬት ይደረመስና ይጨፈልቃቸዋል፡፡ ልጆቻቸው ሜዳ ፈሰው ይቀራሉ፡፡ ደሀ ደሞ ልጅ አከታትሎ ሲወልድ ለነገሩ አይል፡፡

እንደዚህ እያለ ሰራተኛው በፋብሪካ ምድራዊ ሲኦል ውስጥ እየተሰቃየ ለካፒታሊስቱ ገነትን በምድር ላይ ዘረጋለት፡፡ ግና ካፒታሊስቱ ባለንብረቷ ነው እንጂ ውስጧ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ እሱ የሚኖረው የገዛ ራሱ ሲኦል ውስጥ ነው ገነቲቱ ተዘርግታለች እንጂ የሚኖሩባት የሉም፣ ወይ ጥቂት ናቸው፡፡ ሰይጣን እኮ ገነትን ምድር ላይ እንገንባት አለ'ንጂ እውስጧ ትኖራላችሁ አላለም፡፡

ካፒታሊዝምን የሚያንቀሳቅሰው ሞተር 'ትርፍ' ነው ካልን መሪው ውድድር መሆን አለበት፡፡ ኩባንያ ከኩባንያ ጋር ይወዳደራል፡፡ አገር ከአገር ጋር ይወዳደራል (ወዶ ሳይሆን ተገዶ፡ ሰራተኛውም ከሰራተኛው ጋር ይወዳደራል የስራ ቦታዎች ጥቂት ሰራተኛ ግን ብዙ)

ኩባንያለኩባንያለጥሬ ዕቃ ይሁን ለገበያ ሲሻሙና ሲወዳደሩ አልፎ አልፎ መጋጨታቸው አይቀርም፡፡ ያገሩ ህዝብና መንግስት ጉዳዩን አጥንተው ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ ማምረትና ማትረፍ መወዳደሩ ይቀጥላል የአገሪቱ ሀብት እያደገ ይሄዳል፡፡

አገር ለአገር ደሞ በበኩላቸው ለጥሬ ምርት ይሁን ለገበያ ሲሻሙና ሲወዳደሩ አልፎ አልፎ መጋጨታቸው አይቀርም፡፡ የአለም ህግና መንግስት የሚሉት ውሳኔ ወይ ፍርድ ሰጪ ወይም አስታራቂ ሀይል

የለም። ወሳኙ ጉልበትና ብልጠት ይሆናል። ጦርነትና ዲፕሎማሲ። የካፒታሊስት አገሮች ውድድር ሁለቱንም የአለም ጦርነቶች አስከተለ። እዚህ ሁሉ ውስጥ ተጠቃሚው ሰይጣን ብቻ ሳይሆን አይቀርም። ሰይጣን አለ ብለናል ቢኖርም ባይኖርም።

እንበልና እኔ የአንድ ኩባንያ የቦርድ ሊቀመንበር ነኝ። ኩባንያው አመታዊ ትርፍ ማስገኘት አለበት። በዚህ አመት ግን ትርፍ ለማስገኘት ሶስት ሺህ ሰራተኛ ከስራ ማሰናበት ይኖርብናል። እናባርራቸዋለን። ይህ ማባረራችን ስንትና ስንት ሰው ወደ ጭንቅ ወደ ረሀብ ምናልባት አንዳንዱንም ራሱን ወደ መግደል ሊያደርስ ይችላል። እንዲያም ሆኖ ግን በዚሁ በማባረራችን ኩባንያችን ሶስት በመቶ ትርፍ ያገኛል። እዚህ ላይ ነው ቁምነገሩ። በዚሁ መስመራችን ከአምስት ሌሎች ኩባንያዎች ጋር አፋጣጭ ውድድር አለብን። ካልቀደምናቸው ይቀድሙናል። ለነዚያ ከስራ ላሰናበትናቸው ሶስት ሺህ ሰዎች በደመወዝ መልክ ልንከፍል የነበረውን ገንዘብ በሌላ ጉዳዮች ላይ ይውላል። ተወዳዳሪዎቻችንን ልንቀድማቸው ያስችላል። ምክንያቱም በየአመቱ እድገት ማሳየት አለብን።

የካፒታሊስት አገር ሰራተኛ ትጉህ ታታሪ ቢሆንም ኩባንያው ሰራተኛ መቀነስ ስላለበት ብቻ ከስራ ሊባረር ይችላል።

ኩባንያዎች እየተወዳደሩ አመታዊ እድገት። አገሮች እየተወዳደሩ አመታዊ እድገት።…

…ማን ያድጋል? ማን አያድግም፣ ማን ይከብራል ማን ይከስራል የሚወስነው ገበያው ነው። አቅርቦትና ፍጆታ ሽያጭና ግዥ። ምርት ማደግ አለበት።

አንዳንድ ጊዜ ምርት ከመጠን በላይ ያድግና…

ከአንድ ሰላሳ አመት በፊት ይሆናል እንዲህ የሚል አነበብኩ ‹ዩናይትድስቴት ገበያ እንዳያራክስባት ስትል ሶስት መርከብ ሙሉ ስንዴ ወደባህር ደፋች› ገርሞኝም አላባራ።

ፈረንጅ አስፈላጊውን ምርት አላስፈላጊውንም ምርት ሲያሳድግ … ሲያሳድግ… በዚህ በኩል ሰይጣን ሌላጉድ ሰራው፡፡ የፋብሪካዎቹና የመኪናዎቹ ጭስ አየሩን እየበከለው ሄደ፡፡ ከተማዎቹ እንደ ጭጋግ የመሰለ ጠቆር ያለ ነገር መልበስ አመጡ፡፡ አሁንም ከአንድ ሰላሳ አመት በፊት እንደተገመተው ኒዮርክ ከተማ ውስጥ የሚኖር ሰው አየሩን በመተንፈሱ ብቻ በሳንባው ላይ የሚደርሰው ጉዳት በቀን ሶስት ፓኬት ሲጃራ እንዳጨሰ ያህል ነበር፡፡ ባሁኑ ጊዜ የሜክሲኮ ከተማ ተማሪዎች አንዳንድ ቀን አየሩ መርዛማ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሁለት ሰአት እንኳን ሳይማሩ ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ይለቀቃሉ፡፡ የአየሩን መርዛማነት ለመከላከል አፊታቸው ላይ ጭምብል (ማክስ) ያደርጋሉ፡፡ ቶሎ ቤት ይገባሉ፡፡ የውጪውን አየር ለመሸሽ፡፡

የቶክዮ ከተማ እግረኞች ሄደው ሄደው አየር ሲያጥራቸው መንገድ ዳር እተተከለ ማሽን ውስጥ ሳንቲም ይጨምሩና ኦክሲጂን (ንፁህ አየር) ይተነፍሳሉ፡፡ ከዚያ መንገዳቸውን ይቀጥላሉ፡፡ እንደገና አየር ካጠራቸው እንደገና ሌላ ማሽን ውስጥ ሳንቲም አጉርሰው ኦክስጅን ይተነፍሳሉ፡፡ አንድ ሳይንቲስት እንዳለው ‹አካባቢያችንን ሲበዛ ከመለወጣችን የተነሳ እውስጡ ለመኖር ራሳችንን መለወጥ ሊኖርብን ነው፡፡›

ፋብሪካዎቹ እቃዎችን በሚያመርቱበት ጊዜ አብሮ አላስፈላጊ መርዛማ ነገሮችን ጭምር ‹ስለሚያመርቱ› እነዚህን መርዛማ ነገሮች በቧምቧ ወደ ወንዝ ወይም ወደ ባህር ይጨምሯቸዋል፡፡ ወንዞቹና ባህሮቹ ተመርዘው አሳዎችና ሌሎች የውሀ ውስጥ ኗሪዎች አለቁ፤ አሁን ወንዞቹና ባህሮቹ ቆሽሸው ግማሽ ህይወት አልባ ሆነዋል፡፡ መች ይሄ ብቻ? እንግዲህ ምድሪቱን ከዚህ ከምንተነፍሰው አየር በላይ ዙርያውን ኦዞን የሚባል ነገር ሸፍኖታል፡፡ ይህ ኦዞን ከፀሀይ ከሚመጡብንና ማንንም ፍጡር ከሚጎዱ አልትራቫዮሌት ከተባሉ ጨረሮች ይከላከልልናል፡፡ አሁን ይኸ ጋሻችን የሆነው ኦዞን በሰሜን በኩል እየሳሳና እየተበጠረቀ እየሄደ ነው፡፡ በፋብሪካዎቹ መርዝ የተነሳ፡፡ ምን አይነት ኬሚካሎች ኦዞንን "እየቀደዱት" እንደሆነና እንዴትስ እነዚህን ኬሚካሎች

መቀነስ እንደሚቻል የታወቀ ነው። ነገር ግን ማወቅ ሌላ ማድረግ ሌላ ሆነ። ፋብሪካዎቹ ተስማምተው ተጨማሪ ወጪ ቢያወጡ ይቻል ነበር። ግን ማን ያስማማቸው? እንዴት ያስማማቸው? ፋብሪካዎቹ የማምረትና የማትረፍ ውድድሩን መቀጠል አለባቸው። ኦዞኑም እየሳሳ መሄዱን ይቀጥላል።

.... እንግዲህ እነሆ። መጀመርያ ሰይጣን የሰውን ልጅ ከገነት እንዲባረር አደረገ። ከገነት! ወጥቶ እምድሪቱ ላይ እንጀራውን ይበላ ዘንድ፣ ለበሽታ ለእርጅና ለሞት እንዲዳረግ ዘንድ ሆነ። ቀጥሎ የሰው ልጅ ሰለጠነ። ንግድና ኢንዱስትሪ ተስፋፋ ጦርነቶችም ተፋፋሙ። ሀይድሮጅን ቦምብ የሰውን ልጅ ከምድር ላይ እንዳያጠፋው የሚል ስጋት መጣ። በዚህ በኩል አየሩ ውሀዎቹ በመርዝ ተበከሉ። በዚህ በኩል ለምርት እድገት ለትርፍ ሲባል የፈረንጅ ልጅ ልቡ እስኪጠፋ እየተጣደፈ ቀልቡ ጠፍቶ የአኗኗርን ጣእም ረስቶ ህይወቱ የፋብሪካ ባርያ ሆነች። በሌላ በኩል የኦዞን ቀዳዳው እየሰፋ ሄደ።

ሰይጣን ባለፊው ከገነት እንዳስወጣን ሁሉ አሁን ደግሞ ከምድሪቱ ገጽ ሊያጠፋን ጥቂት የቀረው ይመስላል። ስአሊለነ ቅድስት።

መጋቢት 4 ቀን 1986

# አለቃ!

ትላንትና አንዱን የድሮ አለቃዬን ከሩቅ አየሁት፡፡ እና የድብርት ጭጋግ ነብሴን ለትንሽ ደቂቃ ሸፈናት፡፡ አለቃ በመሆኑ ሳይሆን ቀሽም ደምባራ አለቃ በመሆኑ፡፡ በሱ የተነሳ ያሳለፍኳቸውን ልዩ ልዩ አለቆች አስታወስኩ፡፡ አንዱ አለቃዬ ሀይለ ሚካኤል ምስግና የሚባል የአስፋው ወሰን ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ነበር፡፡ ለሁለት አመት ብቻ አለቃዬ በመሆኑ አዘንኩ፡፡ አለቃ እንዲኖረኝ እስካስፈለገ ድረስ ሁልጊዜ እሱ አለቃዬ እንዲሆን በወደድኩ፡፡ ምን ዋጋ አለው? እኛ የምንፈልገው ሌላ እነሱ የሚሰጡን ሌላ፡፡

ለመሆኑ ውድ አንባቢ ሆይ ምናልባት አለቃ ነዎት? ምን አይነት አለቃ? ወይስ አለቃ ሆነው ያውቃሉ? እና እንዴት ነበር? ወይስ አለቃ አለዎት? አለቃና ምንዝር ከጥንት የነበረና አስፈላጊ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት ነው፡፡

በህብረት ከደን የሚመጡ እንደ ጅብ፣ እንደ ተኩላ ያሉ አራዊትም አለቃና ምንዝር አላቸው፡፡ እነንብና እነጉንዳንማ ከአለቃና ምንዝር አልፈው ንግስትና ጭፍራ ነው ያልዋቸው፡፡

እዚህ ላይ ከአንድ መፅሀፍ ያነበብኩዋትን አስፍራለሁ፡፡ የመፅሀፉ ርዕስ Dominant Man (የበላይ ሰው) ሲሆን የደራሲውን ስም ግን ስለረሳሁ ይቅርታ፡፡ አለቃና ምንዝር በሚል መነፅር ስናያቸው የሰው

ልጆች ፍጥረታቸው በሶስት ይከፈላል፡፡ አንድ አብዛኛው ሰው (እንበል ስምንት ሰው ከአስር) ማዘዝ ወይም መምራት አይችልምም አይወድምም፡፡ አብዛኛው ሰው የሚችለውና የሚፈልገው መሪውን መከተል ወይም አለቃውን መታዘዝን ነው፡፡ በተገቢው ሰአትና ስፍራ፡፡

ሁለት ጥቂቱ ሰው (እንበል አንድ ከአስር) ማዘዝና መምራት ይወዳል ደሞ ይችልበታል፡፡ ጄኔራሎች፣ ሚኒስትሮች፣ ጳጳሶች፣ የኩባንያ መሪዎች፣ የማፍያ አለቆች፡፡

ሶስት ሌላው ጥቂት ሰው (እንበል አንድ ከአስር) መምራትና ማዘዝም አይወድም መከተልና መታዘዝም አይሆንለትም፡፡ ፈላስፋዎች፣ አርቲስቶች፣ ሰአሊዎች፣ ባህታውያን፡፡

አለቃና ምንዝር የምንለው ግንኙነት ከሁሉ ጎልቶ ወለል ብሎ የሚታየው በወታደሩ አለም ነው፡፡ አስር አለቃ፣ ሀምሳ አለቃ፣ መቶ አለቃ፤ እስከ ጄኔራል ማን ማንን እንደሚታዘዝ የታወቀ ነው፡፡ መለዮውም ያስታውቃል፡፡ መታዘዝ እንጂ ማዘዝ ማመንታት መከራከር የለም፡፡ ጥያቄ ለማቅረብ 'ንኳን አስቀድመህ ማስፈቀድ አለብህ "ጥያቄ ይፈቀዳል ሻለቃዬ?" ትላለህ፡፡ አንተ መቶ አለቃ ሆነህ "አይፈቀድም" ከተባልክ "እሺ ሻለቃዬ!" ብለህ ሰላምታ ትሰጣለህ'ንጂ "ታድያ ትእዛዝ ሳይገባኝ እንዴት እፈፅማለሁ?" ብለህ አትጠይቅም፡፡ ሻለቃው ኮሎኔሉን በተራው ያለማመንታት ይታዘዘዋል፡፡ እንዲህ ካልሆነ ጦርነት የምንዋጋ በውይይትና በምክር በኮሚቴ ከሆነ መሸነፋችን ነው፡፡ የምናሸንፈው በቀራጥ ማዘዝና በፈጣን መታዘዝ ነው፡፡ እንዲሁም በመታኮስ ሳይል አይቀርም ወታደራዊ ነብስ ያለው አንባቢ፡፡

በተኳሹ ወታደር አለም ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ቀን "የክርስቶስ ወታደሮች ነን" በሚሉት በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ቄስ ውስጥ መሀልም ከመንደር ዲያቆንና ቄስ አንስቶ እስከ ሮማው ጳጳስ የተዘረጋው ሰንሰለታዊ አለቃና ምንዝር ስርአትም አለቃህን ያለአንዳች ማመንታት እንድትታዘዝ ያስገድድሀል፡፡ መታዘዝን ያጎደለ ቅጣቲቱን ይጠግባታል፡፡ ሁለተኛ አይለመደውም፡፡

በሌላ አባባል ሴሞነሪ በሚባል የቅስና ትምህርት ቤት ገብተህ ተምረህ ስትጨርስ ዲያቆን ትሆናለህ ከዚያ ቄስ ትሆናለህ። እያልክ እያልክ ጳጳስ እስከ መሆን መድረስ ትችላለህ። አንተ ለካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ነው የምትገዛው የምትታዘዘው። ለሷ ነው ያደርከው። ለሷ ነው የምትኖረው።

በነገራችን ላይ ይኸ የካቶሊካዊት ቤተክርስትያን የኢየሱስ ወታደሮች የማዘዝና የመታዘዝ ዕነ· ስርአት በቀጥታ ከጥንታዊት ሮማ ቄሳራዊ አለም አቀፍ አስተዳደር የተወሰደ ነው። አስገራሚ አሰራር ያገኘው ወይም የፈጠረው የጁሊየስ ቄሳር የእህት ልጅና የስልጣን ወራሽ ነበር። አውጉስቶስ ቄሳር።

ምንዝር አለቃ ያልነው ማህበራዊ ግንኙነት በወታደሮቹና በቀሳውስቱ ለተት ብሎ ይሰራል። ሳያመነታ።

ዳሩ ምን ይሆናል? ይህ ግንኙነት ከነዚህ ሁለት ድርጅቶች ሲወጣ አንዳንዴ ግራ ሊገባው ይጀምራል። አንዳንዴም እንደ ወፈፌ ያደርገዋል። እንቀጥላለን። ለምሳሌ ቢሮክራሲ የሚባለው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ስርአትም መሰረታዊ እምነቱንና ምኞቱ እና ብዙ ጊዜ ውሸቱ “አሰራራችን ልክ እንደ ካቶሊክ ቀሳውስትና እንደ ወታደራዊው ስርአት ነው” ይላል። ነበር ልበል እንጂ። ምክንያቱም ቢሮክራሲ እንደ ወፍ በራሪ ነን ብሎ የሚፎክር ኤሊ ነው። ደሞ ልንፈርድበት አይገባንም፣ ልናስታውሰው እንጂ። እስቲ ባጭር ጨረፍታ አየት እናርገው። አብረን ብዙ እንዳንቆይ ድብርታችንን ያቺን ጭጋጉን ሊያለብሰን ሆነ።

ቢሮክራሲ ህልውናው ከሚመለከተው ክፍል ወደሚመለከተው ክፍል በወረቀት መንቀሳቀስ ነው። አንዲት ከውጭ የመጣች ፋይል መዝገብ ቤት በገባች በወርዋ ጉዳይዋ ያልቅላትና “ፋይሉ ተዘጋ” ተብሎ ወደ መዝገብ ቤት ተወስዶ ይቀመጣል። ጉዳዩን ሲያዩት ግን ያቺ ፋይል አራት የተለያዩ ሰዎች ብቻ ናቸው አንብበው ምልክት አድርገው ያስተላለፏት። ፋይሊቱ ከየት ወዴት እንደምትሄድ የታወቀ እስከሆነ ድረስ እና ተላላኪ እስካለ ድረስ ጉዳይዋ በአንድ ቀን ሊፈፀምላት ይችል

ነበር። ግና እንዲያ ስራውን ካጣደፈውማ ምኑን ቢሮክራሲ ሆነው? ደግሞም'ኮ ባለጉዳዩ እዚያ መስሪያ ቤት የሚያውቀው ሰው ካገኘ የፋይሊቱ ጉዳይ በአንድ ቀን ተፈፅሞ "ፋይሉ ተዘግቷል" ተብሎ ቁጥር ተቀብሎ፣ ወደ መዝገብ ቤት ትመለሳለች። እንዲህ ነው የአበሻ ቢሮክራሲ።

እውስጡ ስንገባ ሀበሻዊ ቢሮክራሲ እጅግ የተወሳሰበ ተንኮልና መሰሪነት የተሞላበት ሆኖ እናገኘዋለን። ለምሳሌ በጃንሆይ ሀይለስላሴ ጊዜ ሲነግሩን ምክትል ሚኒስትሩ ሚኒስትርየውን ይዘልና ወደ ጃንሆይ ይሄዳል። ሚኒስትሩ ደሞ በበኩሉ ምክትል ሚኒስትሩን ይዘልና ከምክትሉ ምክትል ጋር ይሰራል።

በዚህ የስልጣን ሽኩቻ መሀል ባለጉዳይ ይጉላላል። ቀና የቢሮክራሲ አሰራር ቢኖር በሶስት ቀን ሊያልቅ ይችል የነበረ ጉዳይ ወር ከሁለት ሳምንት ያመላልሳል። የሀበሻ ቢሮክራሲ ልዩ ጠባይ አለው። ባለጉዳይ እያመላለሰ ግንባር ካላሳሳመ ፋይሉ አንድ ክፍል ተወዝፎ ይቀራል። ጉቦውንማ አናንሳው!

በይሉኝታ ተጠምቀው ያደጉ፣ ለስልጣን የተጠሙ፣ ሴራ መሸረብ የሚወዱ ቢሮክራቶች የፈረንጅን የቢሮክራሲ ቅርፅ ወስደው ሀበሻዊ ይዘት ሰጡት። ጉዳይ ለማስፈፀም ወደ መንግስት መስሪያ ቤት ሄዶ የሚያውቅ ሰው ሀበሻዊቱን ይዘት ሳይቀምሳት አይቀርም። እጅ፣ እጅ ነው 'ምትለው አይደል?

የአለቃ ምንዝርን ግንኙነት በተለያየ መስክ እናገኛለን። መምህርና ደቀመዝሙር። አባትና ቤተሰብ፤ ሁሉም አባትን ነው የሚታዘዘው። አልፎ አልፎ ግን ባንዳንድ ቤተሰብ ሁሉም ሚስቲቱን ሲታዘዝ እናገኘዋለን። ሚስቲቱ ፍጥረትዋ ማዘዝ የሚወድና የሚችል አይነት ይሆናል። ባልየው ደግሞ በተፈጥሮው ማዘዝን አይወድም። በንዲህ አይነት ቤተሰብ አዛዥ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ ሴቶች ግን ባልየውን ባይደበድቡት ምን ነበረበት? ባጠቃላይ ሴት ልጅን እየተበቀለች እንደሆነ

ነው'ንጂ ባኗ ራሱ እንደሆነ ደብድቧት አያውቅም። የሚስታቸው ዱላ የሚጥማቸው ባሎች ቢኖሩስ? አይ! አሁንስ ይብቃን።

**ሚያዝያ 2 ቀን 1986**

# ታሪክ

አንዳንድ የታሪክ ዥዋዥዌዎች ይመስጡኛል፡፡ አጣጥማቸዋለሁ፡፡ ሁለት ናሙናዎች ላጋራችሁ፡፡ የትውስታዬን አልበም፡፡ ጥቂት እናገላብጣት ለመዝናናት ያህል፡፡

በልጅነቴ ዘመን ለጃንሆይ ሀይለስላሴ ህፃናት ተማሪዎች እንዲህ ብለው ይዘምሩ ነበር፡፡

‹‹መንግስትን ለዳዊት ቡራኬ ለሴም
እንዳንተ የታደለ ማንም ሰው የለም
እንደማቱሳላ እንደ አብርሀም
እድሜህን ያርዝመው አምላከ ዘላለም
አንተ ባትወለድ መድሀኒታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን››

በጎረምሳነቴ ዘመን ደሞ ጃንሆይ በበአል ቀን ሀምሌ አስራ ስድስት አገር ሙሉ የሚያከብረው የልደታቸው በአል በሚያዚያ ሀያ ሰባት አርበኞቻችን ዶፋሽስትን ወታደር ከዚህ በካልቾ ብለው እንዳባረሩት ጃንሆይ ደሞ በዲፕሎማሲ ሙሶሎኒን በአለም መድረክ ላይ ድል ካደረጉት በኋላ በጀኔራል ዊንጌት ታጅበው በሱዳን በኩል ወደ አገራቸው ተመልሰው ሲገቡ አምስት አመት ሙሉ ወርዳ የነበረችውን አረንጓዴ ቢጫ ቀይዋን ሰንደቃላማችንን አሜድላ ላይ የተከሉበት ቀን፤ በነዚህና

ሌሎች ብሄራዊ በአል ቀናት ጃንሆይ በግልፅ መኪናቸው በዝግታ ሲያልፉ ቀኝና ግራውን የተሰለፉት እልፍ እም አእላፍ ሴቶች ‹‹እልልል! ፀሀዩ ንጉስ›› እያሉ ሲጮሁና አለም ፈገግታ ስትለብስ አስታውሳለሁ።

በጎልማሳነቴ ዘመን ደርግ ‹‹ከትቢያ ተነስቶ›› የጃንሆይን ስልጣን አብዛኛውን እንደጨበጠ ከአለም ተደብቆ የነበረውን የወሎን ረሀብ በመገናኛ ብዙሀን የእነ ጃንሆይ ሀጥያትና ወንጀል አድርጎ በሚያናፍስበት ወቅት ጃንሆይ በዝግ መኪናቸው ሲያልፉ ሰዎች ጮኸው ሲሰድቧቸው እጢዬ ዱብ ሲል አስታውሳለሁ። አቤት እንዴት ነበር የገረመኝ፤ በአላቸውን ወሰደባቸው። የምን ሚያዚያ ሀያ ሰባት ነው!? አሉ ተባለ። የምን ታሪክ መሻማት ነው!? በፍየል ወጠጤ ዜማው ደርጉ አሁንም አወጀ። ድሉ የአርበኞችና የሰፊው ህዝብ ነው ተባለ። ቀኑም መጋቢት ሀያ ስምንት ነው...

. . . . አለፈ ደርጉ፣ አለፈ እርግማን፣ እየለፈፈ ደም እያርከፈከፈ ሬሳ እየረፈረፈ. . . .

. . . . ኢህአዴግ መጣ። ሌላ ቀን ሆነ። የጃንሆይ ፎቶዎች ከተደበቁበት ወጡ፣ ጃንሆይ በታሪክ ወደ ተገቢው ስፍራቸው መመለስ ጀመሩ፤ እንዲያውም በተገቢው ክብር ሊቀበሩ ነው ሲባል ራስታ ዘብሄረ ጃማይካ ‹‹ወይድ!›› አለ ‹‹ከመቼ ወዲህ ነው አምላክ የሚቀበረው?››

ሌላ የታሪክ ኻዋኻዌ ክዋሜ ንክሩማህ እንግሊዞችን ጎልድ ኮስት ‹‹ወርቃማው ባህር ዳር›› ይሉት ከነበረው የምእራብ አፍሪካ ቅኝ ግዛታቸው በቦክስ አስወጥቶ ጋና የምትባለው ነፃ አገር የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት ሆነ። እሱ፣ የእኛው ጃንሆይ፣ የግብፁ ፕሬዚዳንት ጋማል አብደልናስር እና ሌሎች ሆነው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን መሰረቱ። እኛ የዛን ዘመን ወጣቶች ንክሩማህን ከሩቅ እንኮራበት ነበር።

ምክንያቱም የአፍሪካ ርእሰ ብሄሮች ስብሰባ ወይም የተባበሩት መንግስታት አመታዊ ስብስባ ሲደረግ አብዛኞዎቹ የእስያና የአፍሪካ ርእሳነ ብሄሮች በፈረንጅ ሱፍና ከረባት ሲታዩ ንክሩማህ ግን ያገሩን

የባህል ልብስ ለብሶ ነበር የሚታየው። አቤት ሲያምርበት፤ በኛ አይን የኛ ቆንጆ! ጥቁርነታችንን አሳምሮልን በነጮችና መሰሎቻቸው መሀል ስናየው ወይ በሳር መሀል የሚታይ አበባ፣ ወይም አውራዶሮ ከነውበቱ ከነወንድነቱ ይመስለን ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ፕሬዚዳንት ንክሩማህ ከስልጣን መውረዱን ሰማን። ስልጣኑን የነጠቀው ወታደራዊ መንግስት የራሱን መልክ ለማሳመር የንክሩማህን ስራዎች ያንቋሽሽና ያንኳስስ ገባ። እኛም ያኔ ገና ወጣት በመሆናችን በነሱ ፕሮፓጋንዳ ተታልለን ስናበቃ በንክሩማህ ኮርተን የነበረውን ያህል አፈርንበት። አወይ ወጣት . . . መሆን የጠላት ወሬ ማመን።

. . .ጊዜ አለፈ እየከነፈ፣ ስንትና ስንቱን እየሰየፈ። ንክሩማህን የገለበጡት ባለስልጣናት ተራቸውን ተገለበጡ። ከዚያ ወዲያማ ንክሩማህ ቀስ በቀስ ወደ ትክክለኛ የታሪክ ቦታው ይመለስ ጀመር። ዋና ከተማቸው አክራ ውስጥ ሀውልት ተሰራለት።

አሁንም እንደገና ጥንት ወጣቶች ሳለን በግብፅ አገር ራሱን ‹‹ወጣት መኮንኖች›› ብሎ የሚጠራ ምስጢራዊ ቡድን አባላት ንጉስ ፋሩቅን ከዙፋን አውርደው፤ በመርከብ አሳፍረው ወደ አውሮፓ ሸኙት። ያን ጊዜ በጣም መልካም ስም የነበረው ጄኔራል ናጊብን ርእሰ ብሄር አደረጉት፤ አገር ተረጋጋ። ወጣቶቹ መኮንኖች ስልጣን በሚገባ መጨበጣቸውን ካረጋገጡ በኋላ ጄኔራል ናጊብን ከርእሰ ብሄርነቱ አስናብተው፤ እውነተኛው መሪያቸው ኮሎኔል ናስር በይፋ ርእሰ ብሄር ሆነ።

ወደ አገራችን ስንመጣ በስድሳ ስድስት አመተ ምህረት በተቀሰቀሰው ለውጥ ራሱን ‹‹ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ›› ብሎ የሚጠራው ህቡእ የመኮንኖች ቡድን ቀዳማዊ ሀይለስላሴን ከዙፋናቸው ካወረደ በኋላ እጅግ መልካም ስም የነበራቸውን ጄኔራል አማንን የደርጉ ሊቀመንበር አድርጎ ሾማቸው። ምስጢራዊው የመኮንኖች ቡድን አባላት ስልጣን በሚገባ መጨበጣቸውን ካረጋገጡ በኋላ (ወይም ያረጋገጡ ከመሰላቸው

በኋላ) ጄኔራል አማንን ከሊቀመንበርነታቸው ሽረው እውነተኛ መሪያቸው ሻለቃ መንግስቱ ሀይለማርያም በይፋ የደርጉ ሊቀመንበር ሆኑ፡፡ እና ስራቸውን ቀጠሉ፡፡

እንዲህ ነበር፣ ወይስ እንዲህ አልነበረም? አይ ወይዘሮ ታሪክ በጣም የሚገርሙ ሴትዮ!

ታሪክ የተፃፈ ብቻ ነው እንዴ? አስደናቂ ወይ ግሩም የሚሰኝ በሰው ልጅ ላይ የሚደርስ? ሽረ ያልተፃፈው ይበዛል! አሁን እኚህ ደጃዝማች እንቶኔ የጥንቱ፣ የጧቱ፣ አንድ ቀን በጨዋታ፣ ጨዋታ የተነሳ እንዲህ አሉን፡፡ (ጨዋታው ስለ ሀብትና ስለድህነት ነበርና)

‹‹እኔ ልንገርህ አይደለም፤ ድህነትን አላውቃትም፡፡ ደርሳብኝ አታውቅም፤ እግዜር ይስጣቸው፡፡ ድነት ከነቂምዋ ጫነች መጣችብህ ቢሉኝ በከንቱ ለፋች ነው የምላቸው››

እዚህ ላይ አዲስ አበባ ያሉ ቪላዎቻቸው፣ አድአ ያሉ የማኛ ጤፍ ጋሻ መሬታቸው፣ ሲዳሞና ከፋ ያሉ የቡና ጋሻ መሬቶቻቸው በጅምላ ከጠፉ በኋላ እንዲህ ሲሉ ደመደሙ፡፡

‹‹ድህነት እንኳን እኔን የልጅ ልጆቼን ጫፋቸውን አይነካም››

ይህን ባሉ በአምስት ይሁን በስድስቱ እና ሰውየው በህይወት እያሉ ወይዘሮ ታሪክ ጆሮዎቻቸውን አሾሉ፡፡ እና ምን ሰሙ? ‹‹የፍየል ወጠጤ!›› በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ላይ ይደመጥ ነበር፡፡ እግዜአብሄር ይቅር ይበለኝ፡፡

ሚያዝያ 9 ቀን 1986

# ተረት

አሁን ደግሞ ወደ ተረት አለም ብቅ ብለን እንመለሳለን፡፡ ንግስት ሻህራዛድ ለንጉስ ሻሀርያር አንድ ሺህ ከአንድ ለሊቶች አከታትላ ተረቶቹን ነግራዋለች፡፡ ከተረቶቹ ሰባቱ የሲንድባድ መርከበኛውን አስደናቂ ጉዞዎች ይተርካሉ፡፡ ከሰባቱ አንዷን ልፃፍላችሁ፡፡ አስቀድሞ ግን የት እንደተናገርኳት ባጭሩ፡፡ ከአንድ አስር አመት በፊት ማታ አንዲት ሴትዮ መጠጥ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ሴትዮዋ የልጃቸውን ልደት በሻማ፣ በከረሜላ፣ በለስላሳ፣ ኬክና አንድ ደርዘን የሚሆኑ ጓደኞቿን በመጋበዝ እያከበሩላት ነው፡፡ አንዳንድ ወላጆችም መጥተዋል፡፡

ቴሌቪዥን ስላልነበረ ሳይሆን አይቀርም ልጆቹ ተረት እንድነግራቸው ጠየቁኝ ‹‹ተረት፡፡ እምን ተረት ሊነግሩን ነው!›› ተባባሉና ፀጥታ ሆነ፡፡

‹‹ምን አይነት ተረት?›› አልኳቸው፡፡ ‹‹የሚያስፈራ ወይስ የማያስፈራ?››

‹‹የሚያስፈራ! የሚያስፈራ!›› አሉ ለመፍራት እየተዘጋጁ፡፡

‹‹በጥንት ዘመን ባግዳድ በተባለችው የሱልጣን ሀሩን አል-ራሽድ ድንቅ ከተማ ውስጥ የሚኖር ሲንድባድ የተባለ ነጋዴ ነበር፡፡ ይነግድ ይነግድና ሀብት ሲጠራቀምለት ንግዱ ይሰለቸዋል፡፡ ሁሉቀን ሱቅ መዋል፣ እቃ መሸጥ ገንዘብ መቁጠር ስልችት ይለዋል፡፡ መርከብ ይገዛ፣

ወይ ይከራይና ውዲቱን ባግዳድ ተሰናብቷት የባህር ላይ ጉዞውን ይጀምራል።

አንድ ጉዞው ላይ ባግዳድን በለቀቁ በሁለት ሳምንታቸው ማእበል ተነሳ። ትልቅ ማእበል። ጮኸው ፀሎት ቢያደርጉ፣ መርከቢቱ ቀለል ብሏት እንድትንሳፈፍ ብለው ጓዞቻቸውን በሙሉ ወደሚገላበጠው ባህር ቢጥሉ አልሆነላቸውም። መርከቢቱም ሰዎቹም ሰምጠው ቀሩ። ሲንድባድ ብቻ ትረፍ ሲለው የመርከቢቱ አካል የነበረ አንድ ትልቅ የእንጨት ምሰሶ አጋጠመው። አላህን እያመሰገነ እንጨቱን አቀፈውና እየተንሳፈፈበት ጥቂት ቀናት በረሀብና በውሀ ጥም ከተሰቃየ በኋላ አንዲት ደሴት ጋ ደረሰ። ‹ተመስገን አላህ ምህረት የማያልቅብህ!› እያለ ከልቡ እያመሰገነ ደሴቲቱን ረገጠ።

ሲንድባድ በድካሙና በራቡ ላይ የደሴቲቱን ዳርቻ ብቻ ትንሽ ተዘዋውሮ አይቶ ፍራፍሬ በየአይነቱ የበቀለባት፣ ምንጭ ያላት መሆኑን ተገንዝቦ ፍራፍሬውን በልቶ ውሀውን ጠጥቶ (አይ መጣፈጡ) አላህን አመስግኖ ተኛ። ደሴቲቱ ሰው ያለባት አትመስልም።

ሲንድባድ ተኝቶ አርፎ በቅቶት ተነሳ። የት እንዳለ ወዲያውኑ ታወቀው። ደሴቲቱን ዞሮ አያት ፈተሻት። ከነፍራፍሬዎቿ ከነምንጮቿ ገነት ናት ደሞ ማንም ሰው ወይ የዱር እንሰሳት የለባትም። ወፎች ብቻ እና ባህሩ ውስጥ አሳዎች። ሲንድባድ ምናልባት ከሩቅ መርከብ ሲያልፍ ቢያይ መርከቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች እንዲያዩትና መጥተው እንዲወስዱት በማለት ትንሽ ጉብታ ላይ ትልቅ የደረቀ እንጨት ክምር አዘጋጀ፣ መርከብ ሲያይ እንጨቱን ይለኩሳል። ጢሱ ከሩቅ ይታያል።

ሲንድባድ ምንም መርከብ ሳያይ ሳምንት አለፈ፣ ደግነቱ ሰው ከመናፈቅ በቀር የጎደለው የለም። ገነት ናት ደሴቷ። አንድ ቀን ወደ ደሴቷ መሀል ገብቶ አንድ ምንጭ ሲሻገር ሲል ድምጽ ሰማ።

‹‹ልጄ›› አለ ያረጀ ቀጥቃጣ ድምፅ። ሲንድባድ ቢገላመጥ ማንም የለም

‹‹ልጂ›› ሲል ደገመ ያ የሚንቀጠቀጥ ድምፅ። ዘወር አለ አቶ ሲንድባድ። አንድ ሽማግሌ ምንጩ ዳር ጥላ ስር ቁጭ ብለዋል። ሄደ ወደሳቸው።

‹‹አቤት አባቴ››

‹‹ይኸውልህ እንደምታየው የእድሜ ባለፀጋ ነኝ፣ ልጂ። ጉልበት ግን የለኝም። ከወገቤ በታች ሽባ ነኝ። መንዝ ሲኖርብኝ እንግዲህ በሰው ጉልበት ነው። ላጋጠመኝ ጉልበተኛ እንዲህ እንዳንተ ሁኔታዬን እነግረዋለሁ። ለአንድ ምእራፍ ወይ ለሁለት ምእራፍ መንገድ ተሸክመህ ሲደክምህ ሲጀምር ታወርደኝና መንገድህን ትቀጥላለህ። ደሞ እድሌ የላከልኝ ሌላ ጎረምሳ ሲያልፍ ሳይ አሁን አንተን እንደጠራሁህ እጣራለሁ። አሁን የነገርኩህን እነግረዋለሁ። ወጣት በሽማግሌ አይጨክንም መቸስ አንድ ሁለት ምእራፍ ያሻግረኛል። እንዲህ እያልኩ እርጅና በወጣትነት ላይ ሆኜ እየተራመድኩ ጉዞዬን እገፋዋለሁ እልሀለሁ ልጂ እድሜ ከጤና ጋር ከእንጀራ ይስጥህና።››

ሲንድባድ ለሽማግሌው በጣም አዘነላቸውና ተሸክሞ ሊወስዳቸው ወሰነ። አቅፎ ሊያነሳቸው ሲል ‹‹ስማኝ ልጂ›› አሉት በዚያች በምትንቀ ጠቀጥ በምታሳዝን ድምፃቸው ‹‹ከልምድ እንዳገኘሁት ከምታቅፈኝ ወይ ከምታዝለኝ እሽኮኮ ብትለኝ ለሁለታችንም የበለጠ ይመቻል።››

‹‹እሺ›› አለና ሲንድባድ ሽማግሌውን እሽኮኮ ብሏቸው ምንጩን ተሻገረና ረዥም መንገድ ከሄደ በኋላ ይደከመው ጀመር።

‹‹አባቴ እንግዲህ ደስ የሚልዎትን ቦታ ይምረጡ - ላወርድዎት ነው››

‹‹የምን ማውረድ አልክ ወዳጂ›› አሉና የሲንድባድን አንገት በጭኖቻቸው ድንገት በሀይል ጥብቅ አድርገው በጣም አሳመሙት፤ የምን ሽባ አሳዛኝ ሽማግሌ ነው።

‹‹አዬ!›› ብሎ ጮኸ ሲንድባድ በህመም። እግሮቻቸውን ደረቱ ላይ ቆለፉ

‹‹ስማኝ አንተ!›› ብለው አከሉበት ሽማግሌው፡፡ አሁን ድምፃቸው ውስጥ አንድ መንቀጥቀጥ የለም፡፡ ትእዛዝ ነው ያለው ‹‹ስማኝ ከአሁን ሰአት ጀምሮያንተ ስራ እኔን መሸከምና ወዳልኩህ ቦታ መውሰድ ነው፡፡ ሌላ ጭቅጭቅ የለም ገባህ?›› አሉና አንገቱን በሀይል ጭምቅ በጭኖቻቸው፡፡

‹‹እየ!! ገባኝ? እሺ!!›› አለ ሲንድባድ በህመም እየተሽማቀቀ ውስጡን እድሉን እየረገመ ከሞቀው የባግዳድ ሱቁና ቤቱ ጥፋ-ሂድ-ጥፋ-ሂድ ብሎ እዚህ ያደረሰውን ቀልቃላ ኮከቡን እየረገመ፡፡

ሲንድባድ ሽማግሌውን እሽኮኮ እንዳለ እየሄደ ውሎ ለመኝታ እሳቸው ወደመረጡት ቦታ ሄዶ ተኛ፡፡ ሽማግሌው እንደተጠመጠሙበት ሁለቱም ይተኛሉ፡፡

ሽማግሌው ሲንድባድ ላይ እንደተጠመጠሙ ለቀጭኑም፣ ለወፍራሙም ሽንት እንኳን ሳይወርዱ እዚያው ትከሻው ላይ እየለቀቁት ቀናት አለፉ - ሳምንታት አለፉ - ወራት አለፉ፡፡ ግማቱስ አፍንጫ ቻይ ነው እንደምንም ይለመዳል፡፡ የሲንድባድ ትከሻውና ጀርባው ተመላለጠ፡፡ በሽንቡት ቁጥር ያቃጥለዋል፡፡

እንዲህ ሲል፣ እንዲህ ሲል ከሲንድባድ ስቃይ በስተቀር ደሴቲቱ ገነት ናት መቼስ፡፡ አንድ ቀን ሲንድባድ አንድ ትልቅ ቅል ቆረጠ፣ ግማሽ ገንቦ ያህል የሚይዝ፡፡ በዚህ ቅል ውስጥ የበሰለ የወይን ፍሬ ቀጥፎ ሞላና ጨፈለቀው ውሀ ጨመረበት፡፡ በቅጠል ከደነው፡፡ በልጥ አሸገው፡፡ ፀሀይ እሚመታው ቦታ አኖረው፡፡

ጥቂት ቀናት ካለፉ በኋላ ሽማግሌው በዚያ አካባቢ ሲነዱት፣ ሲንድባድ አስፈቀደ ይችውና ቅሉን ወደ ተዉበት ቦታ መጡ፡፡ አገኙት ማን እንዳይወስደው? ሲንድባድ ቅሉን ከፈተና ቀመሰው፡፡ ‹‹አይ ወይን ጠጅ! ለጥቂት ቀናት ህመሜን መርሻ ትሆኚኛለሽ›› ብሎ እያሰበ ሊጠጣ ሲል. . .

‹‹ምንድነው'ሱ እንተ! አምጣው እስቲ›› አሉ ሸማግሌው ሲንድባድን፤ አፉን ሲያጣጥም ሰምተው ጥሩ ነገር ሳትሆን አትቀርም ብለው እያሰቡ።

‹‹ለርስዎ አይሆንም›› ብሎ ሲጠጣ ሲል

‹‹እኮ አምጣ!›› አሉት አንገቱን አንዴ እያጠበቁበት።

በልቡ እየረገማቸው የግዱን አስረከባቸው ቀመሷት። ወደዷት። ጠጧት ወይን ጠጅ ምን እንደሆነ ሳያውቁ ቶሎ ቶሎ ጨረሷት።

‹‹ሌላ እንድትሰራ›› ሳይሉት ይቀራሉ?

ሞቅ እያላቸው ሄደ ሸማግሌው። ሞቅ፣ ሞቅ። እንዲያው ዘና፣ ዘና። እንዲያው ሽና፣ ሽና። እያለ፣ እያለ ብዙም ጊዜ ሳይቆይ ጨርሰው ተዝናኑ። የእግሮቻቸው ቁልፍ ባንገቱ ዙሪያ ላላ።

ሲንድባድ በልቡ ውስጥ የአላህን ስም እየጠራ በድንገት መንጭቆ ወረወራቸው። ወደቁ ሸማግሌው።

የሲንድባድ እፎይታ ይታያችሁ። ሲንጠራራ ሲዘል - ምንጭ ፊልጎ ሲታጠብ አሁንም ተመስገን!

ከዚያ ውዲቱን ከተማ ባግዳድን አስታወሰ - ከወራት በፊት ለአላፊ አግዳሚ መርከቦች በተስፋ ሲለከስላቸው ወደከመረው እንጨት በኩል አመራ።

እና ድንገት ቆመ። ሽማግሌውን ወዳራገፈበት ቦታ ተመለሰ። በስካር ተኝተው ያንኮራፋሉ። ‹‹ደህና ሁኝ መከራ!›› ብሏቸው ሊሄድ ሲል አንድ ሀሳብ መጣበት። ደሞ የፈረደበት ሌላ ምስኪን ሊያጋጥማቸውና እንደኔ ሊነዱት? ብሎ አሰበ። ትልቅ አለት አነሳ። እጆቹን ወደላይ ከዘረጋ በኋላ አለቱን ሸማግሌው ጭንቅላት ላይ አሳረፈው።

ጭፍልቅ! ሸማግሌው ትንሽ ተንፈራፈሩና ፀጥ! አቤት ያቺን ለሊት ሲንድባድ የተኛው እንቅልፍ! ብዙ ሳምንታትም ሳያልፍ በደሴቲቱ አጠገብ

የምታልፍ መርከብ የሲንድባድን ጭስ አይታ መጥታ ይዛው ቀዘፈች። ዙሮ፣ ዙሮ ሲንድባድ ውድ ከተማው ባግዳድ ደረሰና አላህን አመሰገነ።

ተረቷና ልጆቹ ገና ሳይላቀቁ ከኋላ የነበሩ አንድ ሰውዬ ‹‹አንጀቴን አራስከኝ›› አሉኝ ዝቅ ባለ ድምጽ

‹‹እንዴት!›› አልኳቸው እኔ ተረቱን የነገርኩ ለልጆች የሳቸው አንጀት ደሞ ምን አገባው?

‹‹ሰክሮ አውርዶ መጨፍለቁ›› አሉኝ ሰውየው ‹‹እኛም እንደዚያ አውርደን ባንጨፈልቀው ምን አለ በለኝ!›› በዛች ከንፈራቸውን ነከሱ።

‹‹ምኑን?››

‹‹መቼ አጣኸው? አይ'ናንተ ጋዜጠኞች!›› የተንኮል ፈገግታ አሳዩኝ።

አሁን ገና ገባኝ። ስለደርግ መንግስት ኖሯል የሚያስቡት። ‹‹ጥቅማቸው የተነካባቸው›› ከሚባሉት አንዱ ሳይሆኑ አልቀሩም። ተረቴን አንዱንም አልሰሙኝም።

‹‹ይህ ተረት ከብዙ መቶ አመት በፊት በአረብኛ የተነገረ ነው። እንዴት የዛሬን የኛን አገር ሁኔታ አነፃዕሮ አሽሙር ሊነገር ይችላል?››

‹‹እዚህ ላይ አይደል ማስጢሩ? የተማረ ይግደለን››

‹‹ኧረ ባኮትን ጨርሶ አይገናኝም!››

‹‹የሚያገናኘው ቢኖርስ? አይ'ናንተ ምሁራን!››

‹‹አንድ ሌላ ተረት - ሁለት እንዲሆን›› እያሉ ልጆቹ ከሰውየው ገላገሉኝ። ለጊዜው።

በኋላ ግን ይኸ ሰውዬ ብዙ አሳሰበኝ፤ ሳንሱር ማስፈለጉ ለንዲህ አይነቱ ሰው ይሆን? እያልኩ አስባለሁ።

ወይስ የሻህራዛድ ተረት እንኳን እዚህ አገር ከተነገረ ፖለቲካዊ ይዘት ማዘሉ ላይቀርለት ሆነ?

ሚያዝያ 23 ቀን 1986

# ማሙሽና ሚሚ

"አዲስ አበባ ተወልዶ ማደግ ራሱን የቻለ ሲኦል ነው" ይህን ያሉት ሌላ ስፍራ ተወልደው ያደጉ ሰው ናቸው። እንዲያም ሆኖ ግን ትክክል ብለዋል። ከድብርታም እናት ወይም ከወፈፌ አባት ወይም ከመሳሰሉት የተወለዱትን ምስኪኖች ወደዚያ ትተን፤ ተራውን ያዲሳበባ ልጅ እንውሰድ። ወላጆቹም ይወዱታል፤ ራብም የለበትም እንበል እንዲያም ሆኖ ግን....

.... ጣጣው ከጎረቤት ይጀምራል። እማማ ብርቄ ምን እንደነካቸው አይታወቅም። ሕፃን ልጅ ማስፈራራት ይወዳሉ። ለቡና በመጡ ቁጥር ማሙሽን ስለ አያ ጅቦ ያወሩለታል ድምፃቸው ያስፈራል። አይናቸው ይጉረጠረጣል.... "ሀኝ! ነው የሚያደርግህ ጥሩ ልጅ ካልሆንክ ዋ!" ይሉታል። አቤት ሲፈራቸው ማሙሽ! አቤት ሲጠላቸው! እንዲያውም ጅቡ ምነው እሳቸውን በበላቸው ቁርጥምጥም። አንዳንዴ እማማ ብርቄ በህልሙ ይመጡበታል እኔ ነኝ ጅብ ብለው ሊይዙት ሲሉ ይነቃና ያመልጣቸዋል፤ እንዲያው ለነገሩ ግን እኚህ እማማ ብርቄ ሰይጣን መሆናቸውን ያውቁት ይሆን?

አለቃ ገብሩ ደሞ በመጡ ቁጥር "አንተ አፍንጫህ የት ሄደ?" ይሉታል ጭራቸውን እየነሰነሱበት። (ጭራውም፣ ጥምጥሟም የውሸት

ነች፤ ግን ማሙሽ አያውቅም እንጂ) ማሙሽ አፍንጫውን ሲነካ "ይህን አፍንጫ ትለዋለህ?" ይሉታል።

"እኔ አንተን ብሆን አውልቄ እጥለዋለሁ'ንጂ አፍንጫ አለኝ ብዬ አላወራም" ታድያ'ኮ ማሙሽ አፍንጫ አለኝም፤ የለኝም ብሎ አውርቶ አያውቅም። አለቃ ገብሩ አፍንጫቸውን ጥለው ፊታቸው ባዶ ሆኖ ታየው በሀሳብ፤ ፈገግ ሲል "ምን ያስቅሀል?" አሉት "ይልቅ ገንዘብ ካለህ ምን የመሰለ አፍንጫ ልግዛልህ"

"አልፈልግም"

"ተወዋ! ቀረብህ!"

ወይዘሮ ሰርካለም ደሞ በመጡ ቁጥር "ኖ'ስቲ ሳመኝ አንተ ጎረምሳ" ይሉና ጉንጭና ጉንጬን አገላብጠው ይስሙታል። ከንፈራቸው ሁልጊዜ እንደረጠበ ነው። ማሙሽ ሳያዩት ጉንጮቹን ደጋግሞ ይጠርጋል። ቀስ ብሎ ይወጣና ፊቱን ይታጠባል፤ በሳሙና። እንዲያው ለነገሩ ግን እኒህ ወይዘሮ ሰርካለም መሳምና ምራቅ መቀባት ልዩነት እንዳለው አያውቁም ይሆን? ወይስ አውቀው ሆን ብለው ይሆን'ንዴ ምናልባት? አበስ ገበርኩ እቴ! ማሙሽስ ወንድ ነው፤ ፊቱን ከታጠበ በኂላ የወይዘሮ ሰርካለምን ቀፋፊ እርጥበት እንደሚረሳው ሁሉ የአለቃ ገብሩም ደባሪ የአፍንጫ ጉዳይ ሲያድግ ይረሳዋል። ሚሚ ግን "አፍንጫ ጎራዳ" የሚለው የእፍረት ስሜት ትራፊ ካደገች በኂላም አብሯት ይኗል። ሴት በመሆኗ ስለ ውበቷ ጉድለት ተደጋግሞ፣ ተደጋግሞ የተነገራት ነገር በመጠኑም ቢሆን ይከነክናታል። እንዲያውም ለነገሩ ግን እኒህ አለቃ ገብሩ በሳቸው ቤት እነዚህን ህፃናት ያጫወቱ ይመስላቸው ይሆን'ንዴ ምናልባት? ሁልጊዜ ያው ነው የአለቃ ገብሩና የመሰሎቻቸው ነገር። ያዩትን ልጅ ሁሉ ስለ አፍንጫው ማጠር ሁሌ እንደከሰሱት ነው ረዥም አፍንጫ ቢኖረውም።

ይኸን ጊዜ የስነልቦና ሊቁ ዶክተር ሲግመንድ ፍሮይድ ያስተማሩት ትውስ ይለናል። እንዴ! እኚህ አለቃ ገብሩ ስለ አፍንጫ ይህን ያህል ተጨንቀው ህፃናትን ካስጨነቁ ብልሀታቸው ይሁን ችግራቸው ወይም ምስጢራቸው ወይም ምናምናቸው አፍንጫ ላይ ነው ጉዳያቸው እንዴ?

ቀና ብዬ አየሁት አፍንጫቸውን። ቀጥ ያለ አሪፍ አፍንጫ ነው ያላቸው። እንዲያውም ምነው እንዲህ ስለ አፍንጫ ጉድለት አስወተወታቸው? ምናልባት በህፃንነታቸው ጊዜ አዋቂ ሰውጋ (ድንቄም አዋቂ) እዚያ ውጪ ሆኖ በማያገባው ጉዳይ ገብቶ በመለፍለፍ ብዛት "ይህን አፍንጫ ትለዋለህ?!" እያለ "አስቀያሚ አፍንጫ ነው ያለኝ" የሚል እምነት አሳድሮባቸው ይሆናል። እና የገዛ አፍንጫቸው አስቀያሚነት እንዳይታወቅባቸው ተሽቀዳድመው የሌላ ሰው አፍንጫ ያንቋሽሻሉ። ኤጭ! ወዲያ እንተዋቸው እኝህ አለቃ ገብሩ ‹‹አለቃ ገብሩም ምነው ባልተፈጠሩ›› ሳይሉ አይቀሩም ህፃናቱ በህፃንነት።

ሚሚ ሁለት አመት ሲሆናት አንዷ ጎረቤት ሴትዮ ከጎናቸው ሻጥ አርገው አቅፈዋት ቆመዋል። ኮረዶዋ ዘብይደር እየሮጠች አለፈችና ተመልሳ መጥታ "እስምሻለሁ ደሞ!" ብላ ሚሚን ጭምቅ አድርጋ አቅፋ ምጭምጭ አድርጋ የማያልቅ አስጨናቂ መሳም ሳመቻት። ሚሚ ማልቀስ ጀመረች።

"ስታለቅስም ደስ አትልም?" አለች እየሳቀች ወንዲላዋ ዘብይደር "እደግምሻለሁ ደሞ!" በጉልበተኛዋ በመሳምዋ ሚሚ ጭንቅንቅ አላት።

ሚሚ እሪ ብላ አለቀሰች። እንባዋ ይወርዳል። ዘብይደር ከት ብላ ሳቀች እንባዋ እስከሚመጣ። ሚሚን ያቀፏት ሴትዮ እንኳን ሊያስጥሏት አብረው እየሳቁ ነው። ሳመቻት እንጂ አልመታቻት ሳይሉ አይቀርም ስለጉዳዩ ቢጠየቁ።

ደግነቱ የሚሚ እናት እሪታዋን ሰምተዋል። የያዙትን ጥለው እየሮጡ መጥተዋል። ሚሚን ቶሎ ተቀብለው፤ እቅፋቸው ውስጥ ያስገቧትና "አይዞሽ ሚሚዬ ዘብይደርን ላያ ጅቦ እንሰጣትና ይበላታል" እያሉ ይዘዋት ይገባሉ። ወንዲላዋ ዘብይደር እየሳቀች ሩጫዋን ትቀጥላለች።

ማሙሽ አራት አመት ሲሆነው ጀምሮ ተደጋግሞ የሚያጋጥመው ካባቱ ጋር በውይይት ታክሲ ሲሄዱ አጠገባቸው የተቀመጡት ከዚህ

በፊት አይቷቸው የማያውቅ ባለ መነፅር ሰውዬ "ስምህ ማነው ማሙሽ?" ይሉታል "ማሙሽ" ሲላቸው "እውነትክን ነው?" ይሉታል። ደሞ ስለ ስም መዋሸት አለ'ንዴ እያለ ሲያስብ "ስንተኛ ክፍል ነህ?" ይሉታል አፍንጫቸውንና መነፅራቸውን አልፎ አልፎ ነቅነቅ፣ ነቅነቅ ሲያረጉት አንዳች ጭራቅ ወፍ ነገር ይመስላሉ።

"ተማሪ ቤት አልገባሁም" ሲላቸው

"ለምን?" ይሉትና መልስ ሳይጠብቁ ወደ ተለመደው ፍሬ ቢስ ሀበሻዊ ምክንያት ይገባሉ "ተግተህ ተማርና ጎበዝ ተማሪ ሆነህ ዩኒቨርሲቲ ተመርቀህ አባትህንና እናትህን ትጦራቸዋለህ። አገርህን ትረዳለህ እሺ ማሙሽ? ጎብዘህ ተማር። ልጆቹ ና እንጫወት ሲሉህ እምቢየው ትምህርቱን አጠናለሁ በላቸው እሺማሙሽ"

አባቱ እንደሆነ ገና ነህ ለትምህርት አልደረስክም ብለውታል። ታድያ ምንድን ነው እነዚህ የተለያዩ የማይታወቁ አዋቂዎች እንዲህ ስለ ትምህርት የሚነዘንዙት? ያዋቂዎች ነገር ምኑም አይገባም።

ሚሚ አራት አመት ተመንፈቅ ሲሆናት ቄስ ትምህርት ቤት ትገባለች። በዜማ ሀሁ ሲሉ የራሷንም የሌሎችንም እየሰማች መማር ደስ ይላት ነበር። ታድያ እኚህ የኔታ ይማታሉ በረኛቸው ዘንጋቸው። የሚሚን ጭንቅላት ኳ! አቤት ሲያም ይለበልባል። ለምንና መቼ እንደሚማቱ አይታወቅም፣ የኔታ። ኳ! ነው ብቻ፣ ደሞ አይናቸው ወዴት እንደሚያይ አይታወቅም።

"ለምንድነው የኔታ የት እንደሚያዩ የማይታየው?" ብላ ጠየቀች እማዬን

"ጠንጋራ ናቸው"

"ምን ሆነው ነው ግን?"

"እኔ'ንጃ"

"ያዩናል እንዴ?"

"እምና"

"እንዴት አርገው ያዩናል?"

"በቃሽ እንግዲህ በጥያቄ አታድርቂኝ።"

"ጥያቄ ያደርቃል?"

"ኦፍ! ተይኝ እንግዲህ በቃኝ። ሂጂ ውጪ ተጫወቺ።"

ውጪ በእድሜ የሚበልጧት ሴት ልጆች ገመድ ይዘላሉ። "ነይ አዙሪ ሚሚ" ይሏታል። አዙራ ሲደክማት አሁንም አዙሪ ይሏታል። እጅዋ የሚወልቅ እስኪመስላት ታዞራለች። እነሱ በየተራ ይዘላሉ። ሚሚን ግን አያዘልሏትም።

ማሙሽም ሚሚም በየበኩላቸው ትምህርት ቤት ይገባሉ።

ዲስፕሊንና ፕሮግራም ያለው ሲኦል። አሁንም እነ ቲቸር ለምን እንደሆነ ሳይታወቅ ይማታሉ፤ ወይም ይሳደባሉ። አለቃ የሚባል ነገር ደሞ አለ። ዱላ የያዘ። በሆነ ባልሆነም ምክንያት በዱላ የሚጨረግድ። ሰልፍ ላይ እዚያ ወዲያ ያሉ ልጆች ሲጮሁ አለቅየው የሚማታው ያልጮሁትን እነሚሚን አጠገቡ ስላገኛቸው ነው። አለቃ መታኝ ብሎ መክሰስ አይቻልም። ቲቸር መቱኝ ብሎ የሚነገርበት ቦታ የለም። ባጠፉትም ባላጠፉትም መገረፍ ነው እነ ሚሚ። እንዲያም ሆኖ ማደጋቸው አይቀርም። ኧረ ትምህርት ይገባቸዋል። ምስጋና ይድረሰውና!

**ግንቦት 7 ቀን 1986**

# የእማ ስርአተ ማህበር

‹‹በናቴ ሴት ነኝ›› አለ ሰውየው እየተኩራራ፤ እውነትም ሊኩራራ ይገባዋል። . . . እዚያ ያልነበሩ ሊቃውንት እንደሚነግሩን ጥንት፣ ጥንት ከታሪክ በፊት (ሊቃውንቱ ቅድመ ታሪክ ብለው በሚጠሩት ዘመን) የሰው ዝርያ ያው መቸስ ሰው በማህበረሰብ ይኑር እንጂ ማህበረሰቡ ግን እኛ ከምናውቀው አይነት ለየት ያለ ነበር። ኧረ በጣም የተለየ ነበር!

. . . የእማ ስርአተ ማህበር ነበራ! አንቀሳቃሽዋ ዋነኛዋ መሪ እማ የሆነችበት ዘመን በጣም ሩቅ ነው። ሳይንሳዊ ጥናት ገና መካሄድ አልጀመረም። ስለዚህ ሰው የሚያምነው የሚያየውን የሚጨብጠውን ነበር። ሲያዩ ደሞ ሴት ትወልዳለች፤ ወንዱ አይወልድም። ሴት ዘር ትታ ምድርን ሞልታ ታልፋለች። ወንዱ ግን በልቶ ጠጥቶ ሴትን አጫውቶ ምድርን ባዶዋን እንዳገኛት ባዶዋን ትቷት ማለፍ ነው። ምስኪን! አያሳዝንም? ሴት ልጅ አዛኝ ናትና ለወንዱ ታዝንለታለች፤ ታስጠጋዋለች። የቤተሰቡ ስርና ግንድ እማ ናት። የሚኖሩበት ጎጆው ወይም ዋሻው ወይም ዛፉ የእሷ ነው። ስትወልድ ሴት ልጆችዋ እያደጉ ለአቅመ ሄዋን እየደረሱ ሲሄዱ ዙርያውን እነሱም የራሳቸው ጎጆ ወይ ዋሻ ወይ ዛፍ ይኖራቸዋል።

እንዴ! ወንዶቹስ? ወንዶቹማ ጥገኛ ናቸው። እስኪያድጉ የናታቸው ጥገኛ። አድገው ከደረሱ በኋላ የሌላ ሴት ጥገኛ፣ እሷ እስከፈቀደች

ድረስ። በስንፍናው ወይ በሌላ ምክንያት ካባረረችው ሌላ የምታስጠጋ ሴት ፍለጋ ይሄዳል። አምላኪቱ ደግዬ ናትና ሳያገኝ አይቀርም። ሴት ልጅ መጠጊያችን ናትና።

የእማ ‹‹ባል›› እና ወንዶች ልጆችዋ እና የሴቶች ልጆችዋ ‹‹ባሎች›› --- እነዚህ በአደን ይሰማራሉ። ፈጣኑንም ጉልበታሙንም አራዊት በቡድን አድነው ይመለሳሉ። እማ እና፣ ሴት ልጆችዋ እና የልጅ ልጆችዋ በበኩላቸው ከማደርያው ‹‹መንደር›› ብዙም ሳይርቁ ዙርያውን ሜዳውና ጫካውን ያስሳሉ። የሚበላ ፍራፍሬ ስራስር እና አናሳ እንስሳት ይሰበስባሉ።

በእማ ዙሪያ ዘመናት እያለፉ ትውልዶች እየተተኩ የሰው ዘር ልምድና ማስተዋል እየተከማቹ ሲሄዱ ወንዶቹ ከአራዊቱ መርጠው ይሁን ባጋጣሚ እነውሻን፣ እነ ላምን ሲያለምዱ ሴቶች ደግሞ ከእፅዋት እነ ገብስን፣ እነ ጤፍን ‹አለመዱ።› ሁለቱ ‹‹ልምዶች›› ሲገጣጠሙ ግብርና ይመጣል። ስልጣኔ ይከተላል። (በነገራችን ላይ ‹‹ቅጠል በጥሰው ስር ምሰው›› የሚደረጉ መድሀኒቶች ዘመን ቆጥረው በእውቀት ክምችት ብዛት የህክምና በተለይም የመድሀኒት ቅመማ ጥበብ የሆኑት እውቀቶች ከስር መሰረቱ የሴት ልጅ መዋጮ ናቸው) ‹‹በናቴ ሴት ነኝ›› አለ ሰውየው - እውነት አለው።

እኛ ወንዶች በአስጨናቂው የኑሮ ጎዳና ስንጓዝ በየምእራፉ ሴት ልጅ ልዩ፣ ልዩ ገፅታ ለብሳ ታጋጥመናለች። ተጉዘን ማረፊያ እንደሚሆነን ሾላ ወይ ዋርካ ወይ ግራር ዛፍ ከነሰፊ ጥላው። በመጀመሪያው ምእራፍ ሴት ልጅ እናታችን ነች። ከእግዜሩ በታች የፈጠረችን ከውስጧ ያበቀለችን በማህፀንዋ ከስጋዋና ከደምዋ ስትገነባን ስንብታ ስንወለድ ደግሞ እጆችዋ ሲጠርጉን ሲያቅፉን ሲንከባከቡን ይስተዋላል። ጡቶቹዋ ደግሞ ሊመግቡን ተዘጋጅተው ይጠብቁናል። አይገርምም! ህፃኑና ወተቱ ያልተቃጠሩበትን ቀጠሮ ሲያከብሩ? የፈጣሪዋ ሌላ ተአምር

ወደዚህ አለም እስኪመጣ በማህፀኗ አሰንብታ የገነባችውን ህፃን ቀጥሎ እምባውን እየጠራረገች እሹሩሩ እያለች በእቅፏ ታከርመውና

ከውጪው አለም ጋር አለማምዳ ለመኖር ያስችሉት ዘንድ ቋንቋና ባህልን አስተምራ---ይህን ሁሉ ስንቅ ሰንቃ ትሸኘዋለች። የኑሮ ጉዞውን ይቀጥላል።

በጊዜ ጎዳና ስንጓዘው ባጅተን የሚቀጥለው ምእራፍ ጉርምስናችን ይሆናል። እዚያ ሴት ልጅ የባዳ ኮረዳ ገፅታ ለብሳ ትቆየናለች። ውበቷ ያፈዘናል። ጠቅላላ ሁኔታዋ ትኩሳት ይለቅብናል። እሷ ባለችበት አካባቢ ‹‹ሰው›› መሆናችን ይቀርና ‹‹ወንድ›› እንሆናለን። ሌላውን ወንድ ‹‹የጎሪጥ›› እናየዋለን። ፍቅር ያዘን ይባላል። እናታችን ፈጣሪያችን ያንን ሁሉ ስንቅና ትጥቅ ሰጥታ ሸኝታናለችና እቺ ፍቅረኛችንም ‹‹አፀፋውን ትመልሳለች›› ትዳር እንመሰርትና በጊዜ ጎዳና አስከፊው የኑሮ ጉዞ ይቀጥላል. . . ይቀጥላል። . . .ውጣ፣ ውረድ. . .ማጣት፣ ማግኘት. . .ውጥረት፣ ርግበት. . . ‹‹መንገድ አንተ መንገድ ሰው እንዳይሄድ የለምና! ሰው እንዳይሄድ››

በሚቀጥለው ምእራፍ እኛ እድለኞች ወንዶች ሴት ልጅ በደስታ የሚፈነቅለን ገፅታ ለብሳ እናገኛታለን። ከኛ የተወለደች ሴት ልጃችን ሆና ትመጣለች። እቺ ደግሞ ከየት ተገኘች? አሁን እንደዚች ቆንጆ ነገር ተፈጥሮ ያውቃል? ደሞ ቀና ብላ ሰው ስታይ ልክ እናታችንን አትመስ ልም? ወይ አንቺ እምዬ ማርያም! አሁን እቺ አድጋ ተራዋን ሴት ሆና ልትወልድ ነው? ማመኑ ያስቸግራል። ወለል አድርጎ በሚያሳየው በፍቅር አይናችን እያየናት የማይታመን አስገራሚ ጉዞዋን ተጉዛ ሙሉ ሴት ትሆንና ተራዋን ትወልዳለች። . . . ወይ አንቺ እምዬ ማርያም!

. . . በጊዜ ጎዳና ቁልቁለቱን ስንዋብ ከርመን በሚቀጥለው ምእራፍ ሴት ልጅን በእምዬ ማርያም ገፅታዋ እናገኛታለን። እንግዲህ ጉዞዋችን ወደ ማለቂያው እየተቃረበ ነው። የህይወት ብርሀን ከወላጆቻችን ተቀብለን ለልጆቻችን አቀብለን ምድራዊ ተልእኳችንን ፈፅመናል። በተረፈ እምዬ ማርያም አዛኝቱ አለችልን።

እንድትለመንልን እሷን መለማመን ነው። ሴት ልጅ ወደ ምድራዊ ህይወት አስገባችን፣ ሴት ልጅ ወደ ሰማያዊ ህይወት ታስገባናለች።

በነገራችን ላይ እምዬ ማርያም አዛኝ ናት'ንጂ ከእሷ እኩል የሚያሳዝን አለ? እቻትላችሁ አጭር ጥቅስ ከ‹‹አስርቱ ሰልስቱ ህማማተ መስቀል›› የተወሰደች

‹‹ዮሀንስም እመቤቴ ሆይ ልጅሽ ተሰቀለ›› ቢላት ደንግጣ ስትወጣ ደናግል ተከተሏት። አይሁድም ከኛ ሴራ የተለየ ቤቱ ይተኮስ፤ ከብቱ ይወረስ ብለው አድማ አድርገው ህዝብን ሰብስበው ውለው ነበር። ጌታ የተሰቀለበት ከህዝቡ ብዛት የተነሳ ቢሰወራት ‹‹ልጄ የተሰቀለበት የት ነው?›› ብትለው በምእራብ በኩል ተሰቅሏል። እግዚአትነ ማርያም ጌታችን እራቁቱን አካሉን ደም ለብሶ አክሊለ'ሾክ (የሾህ አክሊል) ተሸክሞ በመስቀል ተሰቅሎ ብታየው ‹‹ምነው ቀድሞ ቅዱስ ገብርኤል አምላክን ትፀንሻለሽ ትወልጃለሽ ብሎ ያበሰረኝ ብስራቱ ሞት ሆኖ በገደለኝ ነበር!›› እያለች አንድ ጊዜ ከሾህ፣ አንድ ጊዜ ከድንጋይ ላይ እየወደቀች እስከ እግረ መስቀል ደረሰች

**ግንቦት 14 ቀን 1986**

# የንዴት ወሬ

ከእለታት አንድ ቀን በውይይት ታክሲ እየሄድኩ ወደፊት ተቀምጬ ከኋላ ሁለት ጎረምሶች የንዴት ወሬ ያወራሉ። ስለ ትራፊክ ፖሊስ ነው። ‹‹አንድ ሁለቱን በየተራ ጨለማ ውስጥ አድፍጠህ መጠበቅ። እዚያ ጭጭ ማድረግ። እና ምክንያቱን የሚያስረዳ ደብዳቤ ደረታቸው ላይ በጩቤ ስክት። መንግስት ትኩረት እንዲሰጥበት።››

‹‹አንድ ሞት ሲያንሳቸው ነው አላኖር አሉ'ኮ!››

‹‹ዛሬ ጠዋት (እንትን) ሰፈር ቀጥ ያለ መንገድ ይገኙ ስነዳ እንኳን አደጋ ምንም የለም ዙርያውን። እኔና መንገዱ ነን ያለነው። መጣ አንዱ ትራፊክ ጭፍርር ጠጉሩን በእጁ ወደኋላ እያስተኛ። የእንቅልፍ አይኑን እየጠረገ። ገና እንዳየኝ ፊሽካውን ነፋ፤ ቁርስ መብያው ነኛ። እልህ ያዘኝ ሙሉውን መቀጮ እከፍላለሁ'ንጅ ላንተ ቁርስ አልሆንም. . . በቃ ትኬት ሰጠኝ - ቁርስ አልሰጥም በማለቴ።››

ለጊዜው ትራፊኩን ጠላሁት ናቅሁት (ሀቀኛ ትራፊክ አለ፤ ጉቦኛም አለ ብዬ እያሰብኩም እንኳን ትራፊክ የተባለ ሰው ከነዘርማንዘሩ አስጠላኝ። ውይይታችንን ይነዳ የነበረው ሹፌርማ ውይይታቸውን እየሰማ ማርሹን በንዴት የለወጠ መሰለኝ። ደሞ ሳይሆን አይቀርም)

ከዚያ ታክሲ ወርጄ ምንም ችኮላ ጥድፊያ በሌለበት ሰአት አጠር ያለች በእግር ሲሄዷት የምትመች ቁልቁለት ወደ ቤቱ እየወሰደችኝ ነው።

የውይይቱ ታክሲ ንዴት በርዶልኛል:: መኪና የለኝማ! መኪናም የለኝ፣ ከትራፊክ አልጣላ::

ቀዝቀዝ ያለው የምሽት ነፋስም መንፈስን ያረጋጋል:: በንዴት አይነት ሰአት ቢሾፕ (ጳጳስ) አሸርን አስታውስና እንደሳቸው ለማሰብ እሞክራለሁ::

ቢሾፕ አሸር በአስራ ስድስተኛውና አስራ ሰባተኛው ምእት የኖሩ የአየርላንድ ሰው ናቸው:: ቢሾፕ አሸር በመንገድ ሲሄዱ ቀን ለቀን እንኳ ቢሆን አንዱ ሰኬ እየተንገዳገደ መንገዱን ስቶ ጭቃ ውስጥ ወድቆ ትንሽ ተንፈራግጦ አብቅቶ እንቅልፉን ሲለጥጥ ቢያዩ (በሚሄዱበት ብዙ ሰው ያጅባቸዋል መቸስ) አጠገባቸው ላሉት ሰዎች እንዲህ ይሏቸዋል፣

‹‹የግዜር ፀጋ ባያድርብኝ ኖሮ ያ የምታዩት ሰካራም እኔው ቢሾፕ አሸር ነበርኩ›› ነብሰ ገዳይም ተሰቅሎ ቢያዩ ያው ነው:: ‹‹የግዜር ፀጋ ቢከልለኝ ነው'ንጂ እኔራሴ ያንን ነፍሰ ገዳይ ልሆን እችል ነበር::››

‹‹ወይም በተገላቢጦሽ›› እላለሁ ቁልቁለቱን መንገድ በተዝናና እግር እየተራመድኩ ‹‹የግዜር ፀጋ ቢያርፍበት ኖሮ ያ ነፍሰ ገዳይ ልክ እንደኔ እንደ ቢሾፕ አሸር ይሆን ነበር››

ትራፊክስ ከባለመኪናዎች የሚበላው ዝነኛው የደርጉ ዘመን ፖሊስ ነበር አይደለም እንዴ! መንገድ ላይ ተቀምጠው ኦቾሎኒ ሲጋራ ከረሜላ የሚሸጡትን ምስኪኖች ‹‹ወይ ሆምሳ ወይ አንሳ›› እያሉ የጉቦውን ልክ አፍ አውጥተው የሚነግሩ!

ቆይማ! እዚህ ላይ ምን እያለን ነው? ከትራፊኩ ፖሊስ ይብሳል እያልን ነው? ነው:: የፖሊስ መባስ ታዲያ ትራፊክን ጥሩ እንዲሆን አላደረገውም 'ኮ:: ያው ጉቦ ጉቦ ነው:: ቢሆንም ጉቦ የሚበሉትን ሚኒስትርስ ምን እንበላቸው? አንቱ ሌባ! እንበላቸው:: ነብሳቸው ራሷ ሌባ ብትሆን ነው'ንጂ ለስጋቸው ምን አጡና ነው ጉቦ የሚበሉት? አሀ! ሳላስበው ነጥቤ ላይ ደረስኩ:: ይኸውም-- አዲስ መስመር::

ፖሊሱንስ ትራፊኩንስ ምን አድርጉ ትሉዋቸዋላችሁ? ባለው የኑሮ ውድነት ደመወዛቸው ይበቃቸዋል ወይ? ከየት መጥቶ? እንግዲያውስ? እንግዲያውማ እቅጩን እወቀው ወዳጄ፡፡ የሀገሪቱ ኋላ ቀርነትና ድህነት እስካለ ድረስ ጉቦ አብሮ ይኖራል፡፡ በኛ ብቻም አይደለም በሶስተኛው አለም በሙሉ ጉቦ አለ፤ ይኖራልም፡፡

አንቱ ሌባ ያልናቸው ሚኒስትርስ በየጊዜው በመገናኛ ብዙሀን የምንሰማው ‹‹የሀብታም አገሮች ሚኒስትሮች በሉ›› ተብለው የሚዋረዱበት ጉቦስ? ቅሌት ይሉታል መገናኛ ብዙሀን፡፡

ቆይማ እዚህ ላይስ ምን እያለን ነው? ሁለት አይነት ጉቦ አለ ብለናል፡፡ እነዚህ ምስኪኖችን ለማሳሳት ሰይጣን ጊዜ አይወስድበትም፡፡ ድህነትን በመፍጠሩ እግዜሩ ራሱ ለሰይጣን ያገዘ ይመስላል፡፡ የዚህ አይነቶቹን ጉበኞች ህግ ሲይዛቸው ይቅጣቸው'ንጂ እኛ ግን እንዴት ብለን እንፈርድባቸዋለን? ‹‹ቢርበን ጉቦ አንበላም›› ለማለት አንደፍርም፡፡ ቢሾፕ አሸር የሚደጋግሟትን እናስታውሳለንና፡፡

እንግዲህ ከስንት ደሞዝ በላይ ለሆኑ ነው ጉቦ እንዲበሉ የሚፈቀድላቸው? እናስ ምን ያህል ይብሉ? ደሞስ ከማን ይብሉ? ይህን ድንጋጌ ከማውጣታችን በፊት የኤክስፐርቶች አጥኚ ኮሚቴ እናቋቁማለን፡፡

ከኑሮ ውድነት ጋር ሲመዘን ደሞዛቸው የማይበቃቸው የስራቸው ጠባይ ግን ጉቦ ለመብላት የሚያስችላቸው እነዚህንስ ምን እናርጋቸው? ለኤክስፐርቶች አጥኚ ኮሚቴ እንተዋቸው፡፡ ስራ አጦችንም እንደዚሁ ወደ ክቡራን ጉበኞች ለመሄድ ስለቸኮልን፡፡

ሞልቷቸው ተርፎአቸው እያለ ጉቦ የሚበሉትን ክቡራንስ ምን እናድርጋቸው? ቢሾፕ አሸርን ብንሆን ‹‹ሊቋቋሙት የማይችሉት ፈተና ቢገጥማቸው ነው›› እንል ነበር፡፡ እኛ ግን ‹‹ምነው ሰው መሆንዎን ረሱ?›› እንላቸዋለን፡፡ ብናዝንላቸውም ከልብ አይደለም - ቢሾፕ አሸርን ለማስደሰት እንጂ፡፡

ጉቦ አብሮን ይኖራል ማለቱ በጣም ያሳዝናል - እውነት በመሆኑ። ከዚህ የባሰ አለ። በሶስተኛው አለም ሰላም ሊኖር አይችልም የሚሉ ሊቃውንት አሉ። *ሶስተኛው አለም ህዝቡ ከመጠን በላይ ብዙ፣ ባገሩ ውስጥ ያለው ሀብት ከመጠን በታች ጥቂት። ስለዚህ ብዙዎቹ ጥቂቱን ቢከፋፍሉት ስለማይበቃ ይሻሙታል። በሌላ ቃላት ከሶስተኛው አለም የእርስ በርስ ጦርነት ሊጠፋ አይችልም። አፍሪካን ይመለከቷል። ደቡብ አፍሪካንም ያስታውሷል።*

ኤድ ባክህ! አገር ሁሉ አይደለም እርስ በርሱ የሚፋጀው። በሰላም የሚኖሩ አገሮችም አሉ። እኛም በሰላም መኖር ጀምረናል። ልንቀጥልም እንችላለን። ቢሾኝ አሸር አላሉት'ንጂ የሰው ልጅ ተስፋ አይቆርጥም።

**ግንቦት 28 ቀን 1986**

# ሰላማዊ ሰልፍ

ሰላማዊ ሰልፍን ማን እና የት ሆነህ ታየዋለህ?

ሀ/

አንድ ለስራ ሩብ ሰአት የረፈደባቸው በውይይት ታክሲ የሚሄዱ ነጭናጫ ሰውዬ ልትሆን ትችላለህ! ታክሲው መሀል መንገድ ከብዙ መኪናዎች ኋላና ጎን ይቆማል ሰላማዊ ሰልፍ ለማሰለፍ ነው።

‹‹ኤዲያ ቅድም ካልሞላሁ አልነሳም ብሎ አስረፈደብኝ። አሁን ደሞ እነዚህ. . . (ሰውየው ለራሳቸው ቁርሳቸውን አልበሉም) ሀበሻ ስራውን እንደ መስራት ሰልፍ ካልወጣሁ እያለ ሰው ያስቸግራል እዚህ። ሰነፍ ህዝብ!››

ከሰልፈኞቹ የመፈክር አጯጯህና ካነገቧቸው መፈክሮች እና ከተሳፋሪዎች መጠያየቅ መረጃ እንደተገኘው ለካ እነዚህ ሰልፈኞች ከስራ የተባረሩ ናቸው።

‹‹ታድያ የተባረሩ እንደሆነ እኔን ማስረፈድ አለባቸው? ደሞስ ቀድሞውኑ ተግተው አይሰሩም ነበር? ተግቶ የሰራ መች ከስራ ይባረራል?›› ‹‹ድርጅቱ በጠቅላላ ነው የተዘጋው።››

፤‹‹ጥርቅም አይልም! ለኔ ብሎ 'ንደሆነ በል ባክህ ንዳ ቼ በለው።››

ለ/

ሰላማዊ ሰልፍን ሁለት ሶስት አራት ወዳጆች የሆኑ ችግር የሌለባቸው አዛውንት ቢያዩትስ እንዴት ነው? አራት ኪሎ አንዱ ቡና ቤት በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው ቡና ሻይ እየጠጡ ሰልፉ ሊያልፍ ይችላል። ኸረ ያልፋል።

‹‹ያን ሚጢጢ ሰውዬ አየኸው መፈክሩን በቡጢ ወደ ላይ ሲሰጋው?››

‹‹በንዴት አየህልኝ? ያውቅበታል። ሌላው ቢቀር'ኮ መንጌ መፈክር አስተምሮን ሄዷል››

‹‹እናሸንፋለን!››

‹‹ሳይንሳዊ ሃቅ ነው! አንጠራጠርም!››

‹‹እነዚህ ግን ማሸነፋቸውን እንጃ። ቁጥራቸው አነስ››

‹‹በቁጥር ነው ማለት ነው?››

‹‹ነውና 'ብዙሀን ይመውኡ' አላሉም አባቶች?›› (ብዙሀን ያሸንፋሉ!)

‹‹በሌላ አባባል በብዙሀን ስም መፈክር የሚያነሱና የሚያደራጁ አስተዋይ ብልጥ ጥቂቶች ያሸንፋሉ››

‹‹ነውና። በስም ማሸነፍ አነሰውና ደሞ ብዙሀኑ በተጨባጭ ሊያሸንፍ?››

‹‹ከየት መጥቶ? እሱ ለራሱ ኑሮውን ለማሸነፍ በየፊናው ሱክ ሱክ እያለ ነው እንጀራ ፍለጋ››

‹‹የማሪያ አንቷኔትን ምክር እንስማና ኬክ ልጋብዝህ ብላ››

‹‹አይ! እሷ ንግስት (አሁን ያን የመሰለ አንገት ስለት ይብላው?) ታዘብኩት የፈረንሳይን ህዝብ››

መ/

ስንገምተው መቸስ ሰላማዊ ሰልፍን ለማዘጋጀት ብዙ ትእግስትና ጥንቃቄ ሳይጠይቅ አይቀርም፡፡ በዕሁፉ የሚሰለፈው መፈክር ለምሳሌ አንዳንዱ'ኮ እንኳን አላፊ አግዳሚ አንብቦት የሰልፉን ምንነትና አላማ ሊረዳ ቀርቶ ሁለት ርምጃ ርቀውም አይነበብም፡፡ እንግዲያው ለምን ዕፈን አንግበነው እንሄዳለን ህዝቡ እንዲያነበው ካልሆነ? (እኔማ በትልቁ ፃፉት ነበር ያልኳቸው የት ይሰማሉ ኋላ ስአት ሲደርስ ዕፎ አለሁ ብሎ ሊሰለፍ ይዞ መጣ፡፡ ምን ታረገዋለህ ይሰለፍ እንጂ!)

በድምፁ የሚሰለፈው መፈክርስ ቢሆን፡፡ በአንዳንድ ሰልፍ ሲደመጥ ድምፁ ደካማ የሆነችና እሷንም በአይናፋርነት ምክንያት ወይም የሰልፉን አዘጋጅ ለማበሳጨት ፈልጎ ይሆናል? እንዲያው በትንሹ የሚጮህት ሰውዬ ነው መፈክሩን የሚያወርደው፡፡ ተሰላፊዎች መፈክሩን ስለሚያውቁት ይቀበሉታል እንጂ ተመልካቹ ህዝብ ግን ሊሰማው አይችልም፡፡ ደሞ ሰውየው ከባድ መኪና ወይም አንበሳ አውቶብስ አጠገቡ እያንራበት እያለም መፈክሪቱን ያወርዳታል'ንጂ አለች ልቢቱ! አብዛኛው ህዝብ'ኮ በየፊናው ለየጉዳዩ ሊሯሯጥ ወጣ'ንጂ ሰላማዊ ሰልፍ አያለሁ መፈክር እሰማለሁ ብሎ አልወጣም፡፡ ስለዚህ አይን በሚማርክ ፅሁፍና ጆሮን በሚሞላ ጩኸት የህዝቡን ትኩረት ለመማረክ የማትችል ከሆነ የሰልፉ ልፋት ቢቀርብህ ይሻላል፡፡ ወይስ ሰው ወጣሁ ለማለት ይሆን'ንዴ የሚሰለፈው? ፋሽን ለመከተል!?

**የቅድሞቹ አዛውንት የሚባባሉት**

‹‹ይኸኔ ፈረንጅ አገር ቢሆን ኖሮ እንዲህ ሰልፍ የመብዛቱን አዝማሚያ ያጠኑ ወጣት የቢዝነስ ሰዎች ‹የሰልፍ አዘገጃጀትና አመራር አማካሪዎች ኩባንያ› ብለው ያቋቁሙ ነበር››

‹‹ልክ የሰልፍህን ምንነት ትገልፅላቸውና ሌላውን ሁሉ ለነሱ ትተውላቸዋለህ፡፡ በየት በየት ጎዳና እንደምትሰለፍ ሁሉ ያውቁልሀል፡፡

‹‹የሰልፉን ፈቃድ ማስወጣቱን ሳይቀር ነው የምትተውላቸው እነሱ ጉዳዩን የሚያፈጥን ሰው አላቸው! የመፊክር ፀሀፊና ቀቢ ኩባንያ ሸርካቸው ሊሆን ይችላል።››

‹‹የመፈክር አጯጯህ ኤክስፐርትም ይኖራቸዋል እንዲሁም የጉሮሮ ስፔሻሊስት ሀኪም››

‹‹ወዘተ፣ ወዘተ አይ ፈረንጅ!››

ለ/

የሰላማዊ ሰልፍ ሁሉ አላማ ጉዳዩን ወይም ብሶቱን ህዝብና መንግስት እንዲያውቅለት ለማድረግ ነው። ከአንድ አቅጣጫ ስናየው የሰልፍ ሁሉ አላማ ከሁለት ሊከፈል ይችላል

<u>አላማ አንድ</u>፡- ውጤቱ ተሰላፊዎቹን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ ነው።

ለምሳሌ ‹‹ወደ ስራችን እንመለስ››፣ ‹‹እንመለስ›› ሰልፉ ውጤት አስገኘም አላስገኘም በነሱ ተወስኖ ይቀራል።

<u>አላማ ሁለት</u>፡- ተሰላፊዎቹን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም አገር አቀፍ ወይ ከተማ አቀፍ ዜጋዎችን የሚመለከት ጉዳይ ይሆናል። ምሳሌ ‹‹መሬት ይሸጥ ይለወጥ›› ወይም ‹‹መሬት አይሸጥም አይለወጥም›› ይሄ አይነቱ ሰልፍ ዛሬ በመቶ ተሰላፊ ተጀምሮ የዛሬ ስድስት ወር ግን በመቶ ሺህ የሚቆጠር ሰልፈኞች ሆኖ ትራፊክን ገትሮ አቁሞ የመገናኛ ብዙሀን እና ሪፖርተሮችን ከነካሜራዎቻቸው የሚያራውጥ ሊሆን ይችላል።

ሐ/

የቅድሞቹ አዛውንት አሁንም ስለ ሰላማዊ ሰልፍ እየተጫወቱ ነው (ለነሱ ጨዋታ ነው። ድሮ አምርረው አብቅተዋል)

‹‹እኔ 'ምላችሁ የሰላማዊ ሰልፎችን አመዛዝነን ለአንዱ የኖቤል ሽልማትን ልንሰጠው ተሰይመናል አሉ። ከምታስታውሷቸው ሁሉ ሰልፎች የቱ ነበር ‹‹ሰልፍ ይሉሀል ይሀ ነው!›› ያስባላችሁን አምጡ።››

‹‹በጃንሆይ ዘመነ-መንግስት ታስታውሱ 'ንደሆነ ስለ መሬት ጉዳይ ሲወያይ የነበረው ምክር ቤት ፓርላማ ነበር የምንለው? ጉዳዩን ችላ እያለ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አናዷቸዋል፡፡ ወጡዋ ተማሪዎች በስንትና ስንት ሺ ቁጥራቸው እየዘመሩ›› ያኔ መፈክር ትኑር አትኑር ትዝ አይለኝም፡፡ ፓርላማ ደርሰው ጉዳያቸውን ለጃንሆይ፣ ለመማክርቱም አሰሙ፡፡››

‹‹እና?››

‹‹እናማ ሰልፉ ሲበተን ፓርላማው ካብ ላይ በሩ አጠገብ ከሩቅ የሚታይ ፅሁፍ ተለጥፎ ተገኘ *‹ይከራያል›* ይላል፡፡››

‹‹ተሜ መማክርቱን ምን ሲላቸው ነው? እናንተ ምክር ቤት ስላልሆናችሁ ቤቱን ልቀቁና ይከራይ አይ ተሜ! ተሜ ከጥንትም ተሜ ነው!››

‹‹በፕሬዝዳንት ጆን ፌትጀራልድ ኬኒዲ ዘመነ-መንግስት ይኖር የነበረ ማርቲን ሉተር ኪንግ የተባለ ለጥቁሮች እኩልነት ተዋጊ ትዝ ይበላችሁ፡፡ የሰላማዊ ሰልፍ ጠቢብ ነበር እሱ ሰውዬ፡፡ አንድ ቀን ግማሽ ሚሊዮን ህዝብ አሰልፎ ዋሽንግተን ገባ፤ ግማሽ ሚሊዮን፡፡ ጉዳዩ የሚያስቆጣ ደም የሚያፋስስ ነበር፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግና አምስት መቶ ሺህ ተሰላፊዎቹ ለመንግስትም፣ ለህዝብም፣ ለአለምም ግን በሰላም አቤቱታቸውን አሳወቁ፡፡

‹‹እና ለፈረንጅ አመተ ምህረቶች እኔጋ መምጣት ትችላላችሁ መቸስ ማርቲን ሉተር ኪንግ በ1964 የኖቤል የሰላም ሽልማት ተቀበለ፣ ይህን ሽልማት ካገኙት ሁሉ በእድሜ ወጣት እሱ ነበር፡፡ በ1968 ሰውየው በነብሰ ገዳይ ጥይት ተሰዋ፤ በ1983 የማርቲን ሉተር ኪንግ የልደት ቀን የመላው ዩናይትድ ስቴትስ ብሄራዊ በአል ተብሎ ታወጀ፡፡››

‹‹አሁን በጊዜ ራቁብንና ነው'ንጂ የማህተመ ጋንዲ ሰልፈኞችም ራሳቸውን የቻሉ ተአምራት ነበሩ፡፡››

‹‹ታላላቅ ሰዎች ለብቻቸው የተሰለፏትም አለች››

‹‹አንቺ ናት'ንዴ ደሞ››

‹‹ኧረ አንቺዬ ናት፡፡ ብቻቸውን ነዋ የተሰለፉት››

‹‹ብቻቸውን? ታድያ ሰልፍ ናት?››

‹‹በርትራንድ ራስል ከተሰለፉት ብቻውንም ቢሆን ሰልፍ ናት››

‹‹እኮ ምን ለማለት ነበር የተሰለፈው?››

‹‹በ1918 ነበር፡፡ አንደኛው የዓለም ጦርነት እየተጧጧፈ ነው፡፡ የበርትራንድ ራስል መፈክር ምን ትላለች? ይህ ጦርነት እኛን እንግሊዞችን አይመለከተንም›› ይመለከትሀል'ንጂ ሲሉ አሰሩት፡፡ አሰሩት እንጂ ግን አላንገላቱትም፡፡ በርትራንድ ራስል ነዋ! እንግሊዞች ናቸዋ!››

‹‹እኮ ምን ማለቱ ነው?››

‹‹ሀቁን ይዘህ ከተነሳህ ተከታይ መቁጠር አያስፈልግህም፡፡››

‹‹ምነው ቅድም ብዙሀኑ ይመወኡ ብለን››

‹‹ሀቁን ሲይዙ ነዋ››

‹‹እስቲ ይሁንልህ››

**ሰኔ 5 ቀን 1986**

# ፍልስፍና

በምርታማነት የለካነው እንደሆነ ፍልስፍና ባዶ ነው። ወይ እህል አይመረትበት፣ ወይ ጨርቅ አይሸመንበት፣ ወይ ምኒት አይፈየድበት። እንዲያው ምንም ትርፍ አያስገኝ፣ ምን ልበላችሁ እንደዘፈን'ኮ፣ እንደ መዝሙር፣ እንደ ቀረርቶ......... ዳሩ ምን ይሆናል የሰው ልጆች ነንና ምርት ባይገኝበትም እንዘፍናለን፣ እንዘምራለን፣ እናቅራራለን፣ እንፈላሰፋለን።

ለመነሻችን ፍልስፍና መሰረታዊ አድርጎ ከሚቆጥራቸው ጥያቄዎች አንዱን ዘርዘር አድርገን እንመልከት። አላማ አለህ እንበል። የላቀ አላማ ይሁን ከፈለክም የተቀደሰ። ያንን አላማ ከግብ ለማድረስ የምትወስዳቸው እርምጃዎች የምትጠቀምባቸው ዘዴዎች ይኖሩሀል። ወደ ግብህ እስከደረስክ ድረስ ማንኛውንም ዘዴ ትጠቀማለህ? ወይም "ግቡ ግድ ደርሶ ይቀራል 'ንጂ ይህንንስ አላደርግም" የምትልባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ?

(ቃላቱ ሀሳቤን እንደፈለኩት አልገለፁልኝም። እንደልማዳቸው እየለገሙ ነው። እስቲ በምሳሌ ልሞክረው። አንዳንዴ'ኮ ምሳሌን የመሰለ ነገር የለም ብለዋል አበው።) ለምሳሌ መፅሀፉም አላህም "በሀሰት አትመስክር" ይሉሀል፤ እና አንዱ ጓደኛህ ተከሶ ለፍርድ ቀርቦ ምስክርነት ተጠርተሀል። ሀቁን ብትናገር ጓደኛህ ላይ አስር አመት ፅኑ እስራት ሊፈረድበት ሆነ። ብትፈልግ ግን በሀሰት መስክረህ ልታድነው ትችላለህ።

እንዴት ትመሰክራለህ? በእውነት ወይስ በሀሰት? አማኝ ነህ እንበል ሀይማኖተ ፅኑ። እንግዲህ አላማህ መንግስተ ሰማይትን መውረስ ነው "እንኳን ጓደኛዬ ቀርቶ እናቴ እራሷ ብትሆን በሀሰት አልመሰክርም ምንስ ብሆን የምድር ጉዳይ ሌላ የሰማይ ጉዳይ ሌላ" ትላለህ ወይስ "በኋላ ንስሀ እገባለሁ" ብለህ በሀሰት መስክረህ ጓደኛህን ታድናለህ? እንዲያውስ ለመሆኑ በንስሀና በስርየት ተማምነው የሚነከሩበት ሀጢአት በንስሀ ሊታጠብ ይችላል እንዴ?

ሌላ ምሳሌ እንዲህ አይነቱ ፍሬ ቢስ ቁም ነገር በሚወራበት ሰአት መቸስ መከረኛው አትረፍ ያለው ሂትለር መነሳቱ አይቀርም። አላማው የሂትለርየው

ሀ/ የሰው ዘር ቁንጮ ለሆነው ለጀርመን ህዝብ ተስፋፍቶ የሚኖርበት በቂ ስፋት ያለው መሬት ማግኘት አለበት፤ ባለው ነባራዊ ሁኔታ በወረራ ደካማ ጎረቤት አገሮችን መያዝ። ጥሩ አርያን የሆነው የጀርመን ህዝብ ከሌሎች ዝቅተኛ ዘሮች ጋር እየተዳቀለ እንዳይበከል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊውን ርምጃ መውሰድ። "በቆራጥነት አስፈላጊውን መስዋእትነት እንከፍላለን!"

ይህን ድርብ አላማ ከግቡ ለማድረስ ሂትለራውያንና ናዚ ፓርቲው ድርብ እርምጃ ወሰዱ።

ሀ/ ሁለተኛውን የአለም ጦርነት ለኮሱትና አጋዩት፤ ማለቴ እነሱ ተዋጉ እየተባለ የሚሞቱት ግን እነ ሂትለርየው አይደሉም። ወይስ ናቸው?

ለ/ አርያን ዘርየውን ለማፅዳት ስድስት ሚሊዮን አይሁድንና ስንት ሚሊዮን ስላቭ ዘሮችን በብዙ ጭካኔ የጥፋት (አይሁድ ያልሆኑትም ልክ እንደ አይሁድ ጠፍተዋል። ቁጥራቸው ግን አይነገርም። ነገሩን ደጋግመን የምንሰማው ከአይሁድና ከወዳጆቻቸው ስለሆነ ምናልባት በጂኦግራፊ ምክንያት) ወደ ፍልስፍናችን ስንመጣ ሂትለር ልክ ነበር ወይ? አያጠያይቅም አሉኝ ውድ አንባቢ? እንዴት አያጠያይቅም? ሂትለር ልክ ነበር ወይ? አያጠያይቅም ማለት ነው? ድል፣ በድል ተቀዳጅቶ የአይሁድንና የስላቭን ዝቅተኛ ዘሮች እዚህ አይፈለጉም ከሚላቸው

ስፍራዎች አጥፍቶ ንፁሁን አርያን ጀርመን በአውሮፓ እንደልቡ እንዲያንሰራራ አስችሎ ቢሆንስ ኖሮ? ምናልባት ያን ጊዜ የሂትለር አላማ የተቀደሰ አላማ ይሆን ነበር ወይ? ኧረ እኔ ቀልዴን አይደለም።

ሂትለርን ሲያጥላሉ እንዲህ ይላሉ "እሱ ሊኮተኩተውና የአለም ጌታ ሊያረገው የሞከረው አርያን ዘር ቁመናው ደልዳላ ረዥም ፀጉሩ ነጭ(ብሎንድ) አይኑ ሰማያዊ። ሂትለር ለራሱ ቁመቱ አጭር፣ ፀጉሩ ጥቁር፣ ቡናማ! (ድንቂም!) አዶልፍ ሂትለር ብሎ አርያን!" ይኸ ስድብ እንጂ ክርክር አይደለም። ጭብጡ ሌላ አሽሙሩ ሌላ።

እንዲህም ይላሉ። "አይሁድ'ኮ እጃቸው አመድ አፋሽ ነው። ዛሬ እንዲህ ዴርፋ የሀረር! ሄይል ሂትለር እየተባለ ስሙ ስለሞተ መለዋወጫ ሲሆን ትላንትና ስራ አጥ ሆኖ ክረምቱን በቪየና ከተማ መንገዶች ሲንከራተት ክረምቱንና ራሱን ያሳለፈለት የአይሁድ በጎ አድራጊዎች የምፅዋት ሾርባና ሌላ ምናምን ነበር።" ይህ እውነት እንደተጠበቀ ሆኖ አይሁድ ለሂትለር በቪየና ደግ ባይውሉለትም ኖሮ በእጁ መጥፋት አይቀርላቸውም ነበር። ይቺ የመጨረሻዋ አረፍተ ነገር የሚታሰብባት ሳትሆን አትቀርም።

ሂትለርን ካነሳነው ዘንድ ስለሱ ሰውዬ የምትገርመኝናየምታስቀኝ አንዲት ነገር አለች። ሂትለር ለናዚ ፓርቲ አባላት መታወቂያ ሲሰጥ የመጀመሪያዋን ካርድ ስንት ቁጥር ብሎ ጻፋት መሰላችሁ? አንድ ብሎማ ቢፅፍ "ፉህሩር" መሪ ለመባልና የአገሩን የተለመደ ሰላምታ አስቀርቶ (ሀይ ሂትለር) ለማስባል ባልበቃ ነበር። አንድ ሺህ አንድ ብሎ ነው የፃፈባት። እንግዲህ የመጀመርያውን ካርድ የተቀበለው የናዚ ፓርቲ አባል ከሱ በፊት መታወቂያ ካርድ የተቀበሉ አንድ ሺህ አባላት ያሉ ይመስለዋል። አስረኛዋን ካርድ የተቀበለ አባልም የሚያምነው አስር አባላት ነን ብሎ ሳይሆን አንድ ሺህ አስር ነን ብሎ ነው። ቆየት ብሎ የሂትለር የፕሮፓጋንዳ ሚኒስትር የሆነው ዶ/ር ጉብለስ እንዲህ ብሏል። "አንድ ውሸት ከደጋገሙት እውነት ይሆናል።" እግዚአብሄር ያሳያችሁ እንግዲህ እነንድ ጆሴፍ ስታሊን ከናዚ ፓርቲ ብዙ ጥበባትን ቀስመዋል እየተባሉ ይታሙ ነበር። ይሄ ወዬት ይወስደናልጢባል ወደ ሚቀጥለው ነጥባችን።

ሌላ ምሳሌ - በፈረንጆች አቆጣጠር ከ1095 እስከ 1450ዎቹ የሮማ ጳጳሶች ጦረኞቹን ባርከው እየላኩ ስምንት የመስቀል ጦርነት ተካሄደዋል፡፡ የመስቀል ጦርነት አላማ ምን ነበር? የኢየሱስን መቃብር (ኢየሩሳሌም የሚገኘውን) ከእስላሞች እጅ ለመውሰድ፡፡ ኢየሱስ ራሱ ግን ምን ብሎ ነበር? አንዴ በጥፊ ቢመቱህ ሌላኛውን ጉንጭህን ለሌላ ጥፊ አዙርላቸው፡፡ ተሰቅሎ እያለ ደሞ ምን ብሏል? አባት ሆይ ይቅር በላቸው የሚያደርጉትን አያውቁምና፡፡ ታድያ የዚህን ሰውዬ መቃብር በእጃችን ለማድረግ ጦርነት መክፈት ትክክል ነው? አቤት ስንቱ ነው ያለቀው! በነዚያ ጦርነቶች! ጦርነቶቹ ትክክልና ተገቢ ነበሩ ወይ?

ሌላም ምሳሌ ተኩል -

ከላይኛው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከአስራ ሶስተኛው ምእተ ክፍለ ዘመን እስከ አስራ ስምንተኛው ምእተ ማለቂያ ድረስ አውሮፓ ውስጥ በተለይም በስፓኝ በኢጣሊያና በፈረንሳይ ኢንኩዊዚሽን የሚባል በጳጳሱ የተሰየመ ባለ ልዩ ስልጣን የሀይማኖት ፍርድ ቤት ነበር፡፡ ተልእኮው መናፍቅን እያደኑ ለፍርድ ማቆም ነው፡፡ መናፍቅ ማለት እምነቱ ክርስቲያን እየሆነም የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከሞታስተምረው ትንሽ ወይም በመጠኑ ወይም በጣም ለየት የሚል እንዲያው ወጣ እንደማለት፡፡

በመናፍቅነት የተከሰሰው ሰው ስህተቱን አምኖ ወደ ትክክለኛ ክርስትና ከተመለሰ ንስሀ ይገባና ቅጣቱን ተቀብሎ ሲያበቃ እናት ቤተክርስቲያን ይቅር ትለዋለች፡፡ አይ እምነቱን አልለቅም ያለ እንደሆነ ሁለት ቅጣት ይቀበላል፡፡ መጀመሪያውና ዋናው ቅጣት ቤተክርስቲያን ትረግመውና መንግስተ ሰማያትን ትዘጋበታለች፤ ነፍሱ ወደ ገሀነም እሳት ትወርዳለች፡፡ ሁለተኛው ቅጣት ህዝበ ክርስቲያን አደባባይ ይሰበሰብና መናፍቁን ሰው በእሳት ያቃጥሉታል፡፡ እንደ ገና ዳቦ፡፡ ኢየሱስ ግን ምን ብሎ ነበር? ዳሩ ምን ያደርጋል? ሰውየው የሚለው ሌላ በሰውየው ስም የሚደረገው ሌላ፡፡

ወይስ ኢንኩዊዜሽኑ ትክክል ነበር ይሆን እንዴ? እንግዲህ ላይ ቤት ስንደርስ እናያለን፡፡ ቀስ ብለን እንደርስበታለን፡፡ አያስቸኩለንም፡፡

<u>አሁንም ሌላ ምሳሌ</u> - ሁለተኛው የአለም ጦርነት በፓስፊክ ውቅያኖስ አካባቢ ጃፓንና አሜሪካ እየተፋጁ ነው፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ የጦር ኃይሎች አዛዥና ፕሬዚዳንቱ ሀሪ ትሩማን ከየግንባሩ በደረሳቸው መረጃ መሰረት ዞሮ፣ ዞሮ አሜሪካ ድል ታደርጋለች፤ ግን ከረዥም ወራት ውጊያና ከብዙ ሺህ ወታደር መስዋእትነት በኋላ ይሆናል፡፡ እንግዲያው ጦርነቱን እናሳጥረው አሉና ሚስተር ትሩማን የመጀመሪያው አቶሚክ ቦንብ ሂሮሺማ ላይ እንዲፈነዳ ትእዛዝ ሰጡ፡፡ ኦገስት 6 ቀን 1945 ከተማይቱ ጋየች፡፡ ሁለት መቶ ሺህ ህዝብ አለቀ፡፡ አብዛኛው ሰላማዊ ሰው አሮጊት ሽማግሌ ነፍሰጡርና ህፃን፡፡

እ.ኤ.አ ኦገስት 9 ቀን 1945 ሁለተኛው አቶሚክ ቦምብ ናጋሳኪ ከተማ ላይ ፈነዳ፡፡ አርባ ሺህ ህዝብ ወዲያው ሲሞት ሀያ ሺህ የሚሆነው በልዩ ልዩ ቁስል ምክንያት ከጥቅም ውጪ ዋለ፡፡ ጃፓን እጇዋን ሰጠች፡፡

የፕሬዚዳንት ትሩማን ውሳኔ ትክክል ነበር ወይ? አላማው ጦርነቱን ቶሎ መጨረስ፡፡ እርምጃው አቶሚክ ቦምብ ሰላማዊ ህዝብ ላይ መጣል፡፡ የአላማው ተፈላጊነት እርምጃውን ልክ ያደርገዋል ወይ?

ኢምንት ምሳሌ -

ፍልስፍና ትልቅ ከትንሽ አይልም፡፡ አንድ ተራ አዲስ አበቤየጌቶ ሰፈር ጎረምሳ ባዶ ኪሱን ነው፡፡ (ኦፍኮርስ) አላማው ከገርል ፍሬንዱ ጋር ሆኖ "ዘ-ኤክስተርሚኔተር" የተባለውን በጣም አስጎምጂ የሆነ የአክሽን ፊልም ማየት፡፡ መውሰድ የሚኖርበት እርምጃ መግቢያውን ገንዘብ ከአባቱ ኪስ ውስጥ መስረቅ፡፡ እሳቸው እንደማይነቁበት ያውቃል፡፡ ገንዘቡን ይወስዳል ወይስ አይወስድም?

የዚህ ፅሁፍ መደምደሚያ ቃል ወዘተ...፡፡ (ለመሆኑ ቃል ነው'ንዴ?)

ሰኔ 19 ቀን 1986

# ምኞት

ምኞትን ያህል ሀያል ሞተር የለም፤ ይነዳናል ይወስደናል፣ ያደርሰናል፡፡ ልጅነት የማደግ ምኞት ነው ያሰኛል፡፡ ልጅ ቁመቱን ይለካል፣ ጡንቻውን ይፈትሻል አደኩ ወይ ለማለት፡፡ ሲያድግና አዋቂ ሲሆን ግን ዋና ምኞቱ ማደግ እንደነበረና አሁን ካደገ ዘንድ ዋነኛ ምኞቱ የተፈፀመለት መሆኑን ልብ አይልም፡፡ ምክንያቱም ልቡን አሁንም ሌላ ምኞት ሞልቶታላ፡፡

ምናልባት አሁን ምኞቱ እገሊትን ማግባት ይሆናል፡፡ ያግባት፡፡ የተመኘሁትን አገኘሁ ተመስገን ብሎ ማረፍ አያውቅ የሰው ልብ ሁል ጊዜ አዲስ ምኞት ይሞላዋል፡፡ ቤት ልስራ'ንጂ ሌላ ምንም አልፈልግም ይል ይሆናል፡፡ በብዙ ውጣ ውረድ ቤቱን ይሰራል፡፡ ገና ሰርቶ ከመግባቱ ልቡን ሌላ ምኞት ይሞላዋል፡፡ ዚታዎ'ኮ ያከብራል (ያከብራል እንዴ ግን?) ዚታዎ ነው ወይስ እድል ነው የሚያከብረው ወይስ ይተጋገዙ ይሆን?)

ልባችን ሁልጊዜ ህፃን፤ ምኞት ሁሌ ቢራቢሮ፡፡ ሮጨ ያዝኳት ስንል ብር ብላ ታመልጠናለች፡፡ እንዳንተዋት እልፍ ብላ ታርፋለች፡፡ ቁልጭ፣ ቁልጭ እያለች ትጠራናለች፡፡ ሮጨ ያዝኳት ስንል አሁንም ትበራለች፡፡

ምኞት ብትሉ ድሀ ልጅ ሀብታም ለመ፤ሆን ሳይመኝ ይቀራል? አንድሩ ካርኔጊ (1835-1919) በልጅነቱ ደሀ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሸሚዝ

ብቻ ነበረው። በጣም የሚወዱት እናቱ ማታ ማታ ያጥቡለታል። ብዙም አልተማረም። እንደዚህ ከዜሮ ተነስቶ ከአሜሪካ ታላላቅ ሚሊየነሮች አንዱ ሆነ። አንድ ትልቅ ዛፍ ነበር እግቢው ውስጥ። በመስኮት ወደ ሩቅ እንዳያይ ይከለክለዋል። እንዳያስቆርጠው እናቱ የተከሉት ዛፍ ነው። ብዙ ብዙ ሺህ ዶላር ከፍሎ ዛፉን አስነቅሎ እልፍ አስደርጎ አስተከለው።

አንድሩ ካርኔጊ ተራ ሚሊየነር አልነበረም። ከሶስት መቶ ሀምሳ ሚሊዮን ዶላር በላይ ለልዩ ልዩ በጎ አድራጎትና ለእውቀት ማስፋፊያ አውጥቷል። ያውም በዚያ ዘመን የዶላር ጉልበት። ከሁለት ሺህ አምስት መቶ በላይ የህዝብ ቤተ መፃህፍት አቋቁሟል። እሱ ራሱ የመረጠው የመፃህፍት የእውቀት አለም ለሌሎች ይደርስ ዘንድ።

አሁንም ምኞት ብትሉ ንጉስ ሚዳስ፣ ዳዮኒስስ የተባለው አምላክ "እንደ ምኞትህ ስጥቼሀለሁ" አለው። እና ምን ተመኘ? "የነካሁት ሁሉ ወርቅ ይሁን" አለ "ይሁን" አለው አምላክየው። ድሀ እንኳን ቢሆን እሺ ንጉስን ያሀል ሰው እኮ ነው ንጉስ ሚዳስ። ታዲያላችሁ ድንጋይ ሲያነሳ ድንጋዩ ወርቅ። የእንጨት ወንበር ላይ ሲቀመጥ ወንበሩ ወርቅ፣ ተገረመ፤ ሚዳስ ሆዬ ተደሰተ። ወርቅ በወርቅ ሆነ። ፈነጠዘ። ሆድ መቼስ ስለ ምግብ እንጂ ስለ ወርቅ ደንታ ስለሌለው ሰአቱ ሲደርስ ተራበ።

"ምሳ አቅርቡ" አለ ንጉስ። አቀረቡለት። ዳሩ ምን ይሆናል? ስጋውን ወርቅ! አዬ ጉድ! ሚዳስ ተራበ፣ ሚዳስ ተጠማ፣ ሚዳስ ተጨነቀ።

መች ይሄ ብቻ አትክልት ውስጥ ጭንቀቱንና ራሱን እያንጎራደደ በማሰላሰል ላይ ሳለ ያቺ እንደነፍሱ የሚወዳት ልጁ "አባዬ!" ብላ እየሮጠች መጣችና ዘልላ እቅፍ፤ ወርቅ! አዬ መአት! ሚዳስ እጅጉን አዘነ። ያ ሁሉ የልጁ ሙቀት ድምፅና ሳቅ ብጫ ብረት ሆኖ ቀረ። ወይ ጎዶሎ ቀን፣ ወደ አምላክየው ሄዶ "መልካም ፈቃድህ ይሁንና ወርቁ ይቅርብኝ" ሲል ፀለየ። ፓክቶሉስ ወንዝ ሂድና ታጠብ ተባለ። ታጠበና ዳነ። ለዚህ ነው እስከ ዛሬ ድረስ ፓክቶሉስ ወንዝ ውስጥ ወርቅ የሚገኘው።

እንደገናም ምኞት ብትሉ ምኞትና እድል፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት አንድ ሰውዬ ሎተሪ ገዛ፡፡ ዚታም ደረሰው፡፡ ከነሪሞርኬው ከነተሳቢው ማለት፡፡ (ለመሆኑ ዚታም ተሳቢ አለው እንዴ?)

አንድ አመት ቆየና ሎተሪ ገዛ፡፡ እንደገና ዚታም ደረሰው ከነተሳቢው፡፡ አሁንም አመት ቆየና ሎተሪ ገዛ፡፡ ዚታም ደረሰው እዚህ ላይ “ብታምኑም ባታምኑም” ማለት ይሻላል ወይስ እንተወው? ሶስት ዚታም አንዱ ለነገር ነው ብሎ ሳያስብ አይቀርም--- አበደ ቀወሰ የሚሉም አሉ፡፡ አከራካሪ ጉዳይ ነው፡፡ አበደ ወይስ ቀወሰ?

መከራከር ብትሉ ከዚህ የባሰ አከራካሪ ነገር ይኸውላችሁ --- ይኸ የእድል ሎተሪና የዚታም ምናልባትም የተሳቢው ነገር የሚታመን ነወይ? ተደናቂው ዶርዜ ሸማኔ ጥጥን የሚሸምናትን ያህል የታዋቂውና ተወዳጁ የአዲስ አበባችን የአዳዲስ ጨዋታዎች ቀልዶች ጆኮችና ወዘተዎች ፈጣሪ ይቺን ሎተሪ ከነዚታም ከነ ወዘተዋ.... በሀሳቡ ፈጥሯት በቃላት ሸምኗት ቢሆንስ?

በበኩሌ ሁለቱም ሊሆን ይችላል ባይ ነኝ፡፡ ለምን? በሉኝ፡፡ ለምን ማለት መልካም፡፡ ምክንያቱም ፈጣሪው እዝጌሩና ሎተሪዎቹ እውነት ይህንን ተአምር ሰርተውት ሊሆን ይችላል፡፡ ምን ያቅታቸዋል? «አይመረመሬ›› ይሏቸዋል አበው የሚባሉት አባቶች ብትመረምረው ብትመረምረው አትደርስበትማ

ያዲስ አበባ ተጫዋች ደሞ በሀሳብና በቃላት አለም ውስጥ አይመረመሬ ችሎታ አለው፡፡ ስለዚህ ምን እንበል? ሎተሪውንም ዚታውንም ምናምኑንም ከኪሱ አውጥቷቸው ሊሆን ይችላል እንበል፡፡

ደሞስ ለኛ ምን ልዩነት እንዳያመጣ? ከእግዜሩ መጣ ከሰውየው ሁለቱም የኛው ናቸው፡፡

እንደምን ሁለቱም የኛው ሆኑ? ቢባል እንደምንም ይኋል እዝጌር ይቅር ይበለን እንጂ፡፡

ምኞትና ተስፋ አንድ ናቸው ወይስ ሁለት ናቸው? ምኞትና ተስፋ የአንድ ሀይል ሁለት ገፅታዎች ሊሆኑም ይችላሉ ኮርተው።

እኮ በምን ስልጣን ነው አንዲት ኢምንት ፍሬ መሬት ገብታ ወደታች ስር ወደ ላይ ግንድ ቅርንጫፍ ቅጠል አውጥታ ሰማይድረስ ዛፍ የምትሆን? በምኞት ተስፋ ስልጣን።

ጫጩቷስ እንዴት አድርጋ ነው ከእንቁላል የምትወጣው? በተስፋ ምኞት ካራቴ ነዋ! ዶሮይቱስ በምን ምትሀት ነው እንቁላሏ ውስጥ ጫጩት ያኖረችው? በምኞት ተስፋ

ሀይወት በባህር ውስጥ ነው የተጀመረችው ይሉናል። ይሁን፤ ለመሆኑ እቺ ሀይወት ካለመኖር ወደ መኖር እንደምን ዘለለች? በተስፋ ምኞት። እቺ ሀይወት ከባህር ወደ ምድር በምን መሰላል ወጣች። በተስፋ ምኞት መሰላል። እቺ ሀይወት እንግዲህ በምድር መሄዷን ትታ በሰማይ መብረር እንደምንቻለች? በተስፋ ምኞት ክንፍ ነዋ!

እናስ ከአለማዊ ኑሮ ወደ ዘላለማዊ ኑሮ በምን እንሻገራለን? በተስፋ ምኞት!

አቦ ይሄ ነገር ሊሰለቸን ሆነ። እዚሁ እናቁም። ያነበብነውን በልቦናቸው ያሳድርልን!

በነገራችን ላይ "ምኞት ፈረስ ቢሆን ኖሮ ለማኞችም በጋለቡት ነበር" ይላል የእንግሊዞች ምሳሌ። ከዚህ ፅሁፍ ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው ግን የታወቀ ነገር የለም።

ሰኔ 26 ቀን 1986

# የሆድ ነገር

"ምነው እንዲህ ጥፍት አልሽ ልጂ እንደተደበቅሽው አልቀላሽ?" ትላለች አንዷ። እሷ ብቻም አይደለች ብዙ ሰው ስለመቅላትና መጥቆር ያወራል እንዲሁም ስለ መክሳትና መወፈር።

"ያን የመሰለ ሰውዬ ሲለምናት እምቢ ብላ እድሏን ረግጣ ሄዳ አሁን የእጇን አገኘቻት። አላየሻትም ከስታ መንምና ሳር አክላ?"

"ታድያስ እባክህ እንዴት ነው እንዲህ የወፈርከው? አገባህ እንዴ?" እንዲህ ስለመሳሰሉት ንግግሮች ስናወራ አንድ እገሌ የተባለ ያልታወቀ ሊቅ አንዳንድ ሀሳቦችን ስነዘረ እንደዚህ ሲል

ሁሉም እንደልቡ በማይበላበት አገር ጦማቸውን ባያድሩ 'ንኳን ጦማቸውን የሚውሉ በሚበዙበት አገር ውፍረት ይፈለጋል። ከወፈረ ቢበላ ነው። ከበላ ቢኖረው ነው! ካለው ደግሞ ይከበራል። ባል ሚስቱ ስትወፍር ደስ ይለዋል። ስትታይ ታኮራዋለች። ሚስትም ባሏ ይወፍርላት ዘንድ እሱ የሚወደውን አይነት ምግብ ለማዘጋጀት ጉድ-ጉድ ትላለች። እድለኛ ወፍራም ከሆነችም ገረድዋን ታዝዛለች።

ውፍረት ተወፍሮ ሲበቃው ቦርጭ ማብቀል ይቀጥላል። ቦርጭ ይበቅላል እንዴ? ለመሆኑ ቦርጭ ቃሏ እንዴት ሆነች እንጂ ቦርጮች ግን ይለያያሉ። ለይስሙላ ያህል ብቅ ያለች ተስፈኛ ቦርጭ ትኖራለች። አይዘን

እናድጋለን እድገት የተፈጥሮ ህግ ነውና "የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ተገኘ" እንደሚሉት። አያርግባት እንጂ እድገቷን ትቀጥል ትቀጥልና አሉ ከሚባሉት ቦርጮች አንዷ ትሆናለች። ለአንቱታ እንኳ ባይሆን ለእሳቸውታ ትበቃለች። እኝህ ቦርጭ ዛሬ ከባለቤታቸው ፊት ለፊት ይሄዳሉ። ሰው መንገድ ይለቃል። የኝህ ቦርጭ ባለቤትና ጫማዎቹ ከተያዩ ረዘም ያለ ጊዜ አልፏል። አንዳንዴ ማታ ጫማዎቹ ወልቀው ሲቀመጡ ባለቤት ያያቸዋል።

"ታድያስ ደህና? ተለያየን አይደል?" ይላቸዋል።

"እኛ ሁሌ እዛው ነን። አንተ ነህ የጠፋኸው" ይሉታል። "ወፈርክ"

ሰይጣን ጆሮው ይደፈንና ኧረ ሁለመናው ይደፈን! ይህ ከይሲ ርኩስ! እንዲያውም መደፈን ሲያንሰው ነው። ብቻ እሱን እንተወው ወደ ቦርጫችን! ሰይጣን ጆሮው ይደፈንና የኝህ ቦርጭ ባለቤት ባልታሰበ ሁኔታ ክፉ ቀን ላይ ይወድቃል! እንበል እንደልብ መብላቱ ይቀራል። እሳቸው ይባሉ የነበሩት ቦርጭ እየሟሸሹ ይሄዳሉ። ምን እናርግ አንቱ መባላቸው ይቀራል። ሰው ለባለቤትየው ያዝንና ከንፈሩን ይመጠል። ምስኪን! እምፅፅ! እኔ እኮ ላጣ ሰው ብዙም አላዝን። እኔን የሚያሳዝነኝ አግኝቶ ያጣ ሰው ነው "አግኝቶ ማጣት! ለጠላቴ አይስጠው"

ይህ በእዚህ እንዳለ ምግብም ሌላውም በተትረፈረፈበት በአሜሪካን አገር ግን ቦርጭ ያሳፍራል እንጂ አያኮራም። እዚህ ቢሆን ባለቤቱ የሚንቀባረርበት ቦርጭ እዚያ ይሸማቀቅበታል። እዚህ ቢሆን "እሳቸው!" የሚያሰኝ የተከበረ ቦርጭ እዚያ "አሳማ" ያሰኛል። ወይም ሆድ አምላኩ ያስብላል። ምክንያቱም እዚያ ቦርጭ ለጤና የሚያሰጋ ትርፍ ሸክፍ እንጂ የሀብት ሀውልት አይደለም። ስለዚህም አብዛኞዎቹ የአሜሪካ ምግብ ቤቶች አይን በሚስቡ ቀለማትና በልዩ ልዩ ቅርፅ ወረቀቶች የማያወፍር ምግብ እናቀርባለን ብለው ይፅፋሉ።

(ሀበሻ ይህን ለመጀመርያ ጊዜ ሲያይ ይደነግጣል ይገረማል። ብዙ! ብዙ ሀበሾች ይመጡበታል።) በአሜሪካን አገር ዋና ስራቸው በልዩ ልዩ

ጅምናስቲክ ሩጫና ፍልውሀ አማካይነት የደንበኞቻቸውን ውፍረት መቀነስ የሆነ የስፖርት ቤቶች በጣም ብዙ ናቸው። ውይ አሜሪካውያን! ምን ፈረደባቸው!?

(ይኼኔ ሳትደርሱበት አልቀራችሁም ውፍረትንና ቦርጭን በንዲህ አይነቱ ረቂቅ ስልት ሊተነትን የሚችል ሰው "ቀጥኜ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ ለማለት እንድ ሀሙስ የቀረው ሳይሆን አይቀርም። ነው ደሞ። ትንተናውን ይቀጥላል።)

ጦማቸውን ባያድሩ 'ንኳን ጦማቸውን የሚውሉ በሚበዙበት አገር የሆድ ነገር ነውና ሀሳብ ብዙ ጊዜ ሄዳ፣ ሄዳ መብላትና መጠጣት ላይ ትንጠለጠላለች። ብሂሎችና ምሳሌዎችም ስለሆድና ስለመብላት ያወሳሉ ጥቂቶቹን እነሆ ለቅምሻ

አንድ ሰው ደግ ነው ለማለት "ብሉልኝ ነው ጠጡልኝ!"

ሰዎች ልዩ ልዩ አይነት አሟሟት ሲሞቱ "ውሀ በላው -እሳት በላው - መኪና በላው (በኋላ መኪና ዳጠው እየተባለ ሄደ) ቀይ ሽብር በላቸው ወዘተ እንዳይበላችሁዋ! አፈር ብላ!"

አርጅተው ሲሞቱ "በልተዋል ይበቃቸዋል" እንደዚሁም ዝነኛይቱ አስተውሉት (ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይርበዋል" (?)

ኖርነው ይኸን ኑሮ - እስኪበቃን ኖርነው! ለማለት በላነው - ጠጣነው ለበስነው አለቀ።

ከዚያም እነሆ ከአበውና ከእመው የመጡልን የምሳሌዎች ሰልፍ በአንባቢ ፊት የሚያልፍ

"የበላችው ያገሳታል፣ ላይ በላዩ ያጎርሳታል"

"በልቶ መጠጥ ያጣ፣ ተበድሎ ፍርድ ያጣ"

"በልቶ የከሳ፣ የነገሩትን የረሳ"

"በልጅ አመካኝቶ፣ ይበሏል አንጉቶ"

"በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ"

"በሬ ካራጁ ይውላል"

"ሆዳም ቢሸከም የበላ ይመስለዋል"

"ሆዳም ቢፈተፍት፤ የጠገበ ይመስለዋል"

"ሆዴ በጀርባዬ ቢሆን፤ ገፍቶ ገደል በጣለኝ"

"ሆዴ አታጣላኝ ከዘመዴ"

"ሆድ ባዶ ይጠላል"

"ሆድ ከሁዳድ ይሰፋል"

"ሆድ ያበላውን ያመሰግናል (ውሻ በበላበት ይጮሀል)

"ሆድህን ጎመን ሙላው፣ ጀርባህን ለጠላት አታሳይ"

"ራብ ይከላከላል ባቄላ፣ ጥቃት ያወጣል ዲቃላ"

"ራብን ባለቤቱ ያውቀዋል"

"ራት የላት ምሳ አማራት"

"ራት የሌለው ቄስ ከልቡ አይቀድስ"

እቺ ግን ለየት ትላለች "ራብን ያማርራል ሰው ቁንጣንን ያልቀመሰው።"

ሐምሌ 3 ቀን 1986

# አርተር ኬስለር

አንዳንድ ሰው ስለ ታሪኩ ሲነገር የሚገባው፡፡ የሀንጋሪ ተወላጅ የሆነው አርተር ኬስለር ለኔ እንዲህ አይነት ሰው ነው፡፡ ሳይንቲስት፣ አርቲስትና ታጋይ፡፡ ከ1905-1983 ኖረ፡፡ በፈረንጅ አቆጣጠር ከ1931-1938 የጀርመን ኮሚኒስት ፓርቲ አባል ሆኖ አገለገለ፡፡ ያን ጊዜ ኮሚኒዝም ብዙ ወጣቶችን የሚስብ ርእዮተ አለም ወይም እምነት ነበር፡፡ ‹‹አለም የሰራተኞች ትሆናለች›› የማይሰራ አይኖርም፡፡ ማንም በማንም ላብ አያተርፍም፡፡ መንግስት ለአንዱ መደብ ጥቅም የቆመ ሌላዎቹን መደቦች መጨቆኛ መሳሪያ ስለሆነ ቀስ በቀስ እየተዳከመ ይሄድና ጥራሹኑ ይጠፋል፡፡ ያን ጊዜ እያንዳንዱ ሰው እንደችሎታው ስራ ይሰራል፤ እንደአስፈላጊው ያሀል ደሞ ይሰጠዋል፡፡ ገነትን ምድር ላይ እንዘረጋታለን፡፡ . . .

. . .ኮሙኒዩዝም ከሩቅ በጣም የተዋበ የወጣቶቹን ልብ የሚስብ ሀይማኖት ነበር፡፡ አርተር ኬስለር ከአማኞቹ ታጋዮች አንዱ ነበር፡፡

ከ1936-1939 አሰቃቂው የእስፓኝ የርስ በርስ ጦርነት ተካሄደ አርተር ኬስለር የጦር ግንባር ጋዜጠኛ ሆኖ ወደ እስፓኝ ተላከ፡፡ ፀረ-ኮሙዩኒስት ሀይሎች አሰሩት፡፡ ከጥቂት ወራት እስራት በኋላ አመለጠ፡፡ አመለጠ ሳይሆን ተለቀቀ፡፡ እንዴት ተለቀቀ ብትሉኝ ሳይንቲስት መሆኑን እናስታውስ፡፡ ሆን ብሎ ራሱን እየጎዳ፣ እየጎዳ አንድ በሽታ ያዘው፡፡ በሽታ

የያዘው ሰው ከእስር እንደሚለቀቅ ያውቃል፡፡ ሀኪሙ በሽታውን አረጋገጠለት፡፡ ከእስር ቤት ወደ ሀኪም ቤት ተዛወረ፡፡ በሽታው ሲድን ወደ አገሩ፡፡

በ1938 አርተር ኬስለርና ሌሎች ከልዩ ልዩ አገሮች የተውጣጡ ታጋይ ደራሲያን በጓድ ስታሊን ጋባዥነት ሶቭየት ህብረትን ለጥቂት ሳምንታት ጎብኝተው ኮሚዩኒዝም በስራ ላይ ሲውል ተመለከቱ፡፡ አርተር ኬስለር ከዚህ ጉብኝት እንደተመለሰ ከኮሚዩኒስት ፓርቲ አባልነት ወጣ፡፡ ኮሚዩኒዝም ይሆናል ያልነው አይደለም አሉ፡፡ በ1940 አርተር ኬስለር ‹‹ቀትር ጨለማ›› (Darkness at noon) የተባለውን ልቦለድ አሳተመና ስሙ በአለም ገነነ ‹‹በቀትር ጨለማ›› ሲያነቡት ያስፈራል፡፡ የኮሚዩኒስት ፓርቲ አሰራር ለሰው ልጅ ነፃነት ጠንቅ ነው ይላል፡፡

ልቦለድ ብቻም አልነበረም የሚፅፈው፡፡ ሳይንስና የፍልስፍና ቅልቅል መፅሀፍትንም ደርሷል፡፡ ለተራ አንባቢ በሚገባ አገላለፅ የጉዞ መፅሀፍት ልክ እሱ ያየውን ወለል አርገው ያሳያሉ፤ የሚፅፈው ሁሉ ይጥማል፡፡

አርተር ኬስለር በቂ ገንዘብ እያገኘ ሲሄድ ጊዜ ፀሀፊ ለመቅጠር ወሰነ፡፡ ማስታወቂያ አወጣ በማስታወቂያው መሰረት ከቀረቡት አንዷ የሱን ስራዎች በጣም የምትወድ ቲፎዞ አንባቢው የሆነች ወጣት ነበረች፡፡ እሷን ቀጠራት፡፡ አብራው መዋል ስትጀምር ጊዜ ከፀሁፎቹ እኩል እየወደደችው ሄደች እሱም እየወደዳት ሄደ ተዋደው ተጋቡ ሚስትም፣ ፀሀፊም . . .

እድሜው እየገፋ ሲሄድ አርተር ኬስለር የካንሰር በሽታ ያዘው፡፡ ለተወሰነ ጊዜ እየታከመ መድሀኒት እየወሰደ ሰነባበተ፡፡ አንድ ቀን ግን ማታ ሊተኛ ሲል ሚስቱን ፀሀፊውን ፃፊልኝ አላት፤ ፃፈችለት፡፡

*‹‹እኔ አርተር ኬስለር ያደረብኝን ካንሰር ሂደቱን የማውቀው ስለሆነ እና ከእንግዲህ የቀረኝ ረዥም ስቃይ ብቻ ስለሆነ ስቃዩን ለማሳጠር ስል ህይወቴን በገዛ ራሴ አጥፍቻለሁ በዚህ ጉዳይ ላይ ከኔ በስተቀር ማንም ተጠያቂ የለም፡፡››*

ዓፈችና ሰጠችው፡፡ ፈረመ፡፡ መድሀኒት ዋጠ፡፡ ሞተ፡፡

ሚስቱ-ፀሀፊውም ትእዛዝን ከፈፀመች በኋላ የራሷን ሌላ ደብዳቤ ዓፈች፡፡

*‹‹አርተር በሌለበት መኖር ስለማልፈልግ ተከትየው ሀይወቴን በገዛ ራሴ አጥፍቻለሁ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠያቂዋ እኔ ራሴ ብቻ ነኝ፡፡››*

ፈረመች፡፡ አጠገቡ ተጋደመች፡፡ ከሱ የተረፈውን መድሀኒት ዋጠች፡፡

ሲነጋ ሁለቱም ሞተው ተገኙ፡፡ እንዲህ አይነት የፍቅር ታሪክም አለ፡፡

. . . አርተር ኬስለር ከሚሰጠን ሀሳቦች አንዱ ‹ሆሉን› ይባላል፡፡

ጃኑስ በሚባለው የጥንታውያን ሮማውያን የቤተ አምላክ ይጀምራል፡፡ ጃኑስ ከሌሎች አማልክት ልዩ ነው፡፡ ሁለት ፊት ነው ያለው አንድ ፊቱ ወደ ፊት፣ ሌላው ፊቱ ወደ ኋላ ያያል፡፡ ሆሉን የተባለውም የዚያው ቢጤ ነው፡፡

አንድ የሰውነታችን ሴል (Cell) ባንድ ፊቱ አንድ ሙሉ ሴል ነው እስኪሞት ኑሮውን የሚኖር፡፡ ላንድ ፊቱ ግን የአንድ የሰውነታችን ሀዋስ አካል ነው፡፡ የሰውነታችን ሀዋስ (ለምሳሌ ጉበታችን) በበኩሉ አንድ ሙሉ ሀዋስ ነው፡፡ እስኪሞት ኑሮውን ይኖራል፡፡ በሌላ ፊቱ ግን ጉበታችን የሰውነታችን አንድ አካል ነው፡፡ ሰውነታችን በበኩሉ አንድ ሙሉ ፍጡር ነው፡፡ እስኪሞት ኑሮውን ይኖራል፡፡ ማለት እኔ አንድ ራሴን የቻልኩ ሙሉ ነኝ፡፡ በአንድ ፊቱ፡፡ በሌላ ፊቱ ግን ሙሉ ፍጡር ሳልሆን የማህበረሰቡ አንድ አካል ነኝ፡፡

ቋንቋውን ስንመረምር የስራ ክፍፍልን ስንመለከት እኔ ራሴን የቻልኩ ሙሉ ፍጡር እንዳልሆንኩ እንገነዘባለን፡፡

ይሄ የሆሉን አጠቃላይ ሀሳብ በብዙ መልኩ የሚታሰብበት ነው፡፡

የሰሞኑ የእግር ኳስ ሻምፒዮና ጨዋታ ማራዶና ዳኛው ከነአራጋቢዎቹ ይሄ ነው ሙሉ አካል። ነው'ንዴ ግን? ስታዲየሙን የሚያጨናንቀው ተመልካችስ የት ሄደ? እንግዲያው ሙሉ አካል ማለት ተጫዋቾቹና ተመልካቹ ባንድነት ሲወሰዱ ነው። ነው ይሆን?

የአርተር ኬስለር አስተሳሰቡ ብቻ ሳይሆን አኗኗሩም አርአያ ሊሆነን ይችላል። እስከ መጨረሻ የኑሮው መመሪያ ምን ነበር? ለምናምንበት መታገል አለብን።

**ሐምሌ 10 ቀን 1986**

# ሱፊ

ሱፊ ይባላሉ በእስልምና ውስጥ እንደ ባህታውያንም እንደ መነኮሳትም ፈላስፋዎችም ናቸው። ከማስተማሪያ ዘዴዎቻቸው አንዱ ትረካ ነው። ትረካዎቻቸው ለተለያየ ሰው የተለያየ ትርጉም ሊሰጡ ይችላሉ። ለኛ ሱፊ ወይም የሱፊ ደቀ መዝሙር ላልሆንን የውጪ ሰዎች ደሞ ትረካዎቹ በተረትነታቸው እጅግ ይጥሙናል። እነሆ በረከት!

በረከት አንድ! ርእስዋ "የገነት ውሀ" ትላለች በአረብ አገር በምድረ በዳው የሚኖሩት ዘላኖች በደዊን ይባላሉ። ሀፊትና ሚስቱ ነፊሳ ከቦታ፣ ቦታ እየተዘዋወሩ ጥቂት ቴምር ያፈራ ዘምባባ ሲያገኙ፣ ወይም ለግመላቸው የሚሆን የደራረቀ ግጦሽ ቢጤ ወይም ያንን የለመዱትን ጨው፣ ጨው የሚል የረጋ ውሀ ሲያገኙ እዚያው አርጌ ድንኳናቸውን ይተክላሉ። ለብዙ አመታት እንዲህ ኖሩ። ሀፊት ግዙፎቹን የበረሀ አይጦች እያጠመደ ቆዳቸውን ይሸጣል። ይኸው ነበር ኑሮው።

አንድ ቀን ታድያ አሸዋው ውስጥ አንድ አዲስ ምንጭ ፈለቀ። ሀፊት አንድ እፍኝ ቀመሰለት። ተአምር! ሀፊት ይሄ የገነት ውሀ እንደሆን ታወቀው ምክንያቱም ከዛ እሱ ከለመደው "አተላ" ጨውማ ውሀ ጋር ሲተያይ መጣፈጡ ሌላ ነበር። ኧረ! ኧረ! የትናየት! እኛ ብንቀምሰው ኖሮ ግን ጨው፣ ጨው ስለሚል በተፋነው ነበር።

"ይህንንስ ውሀ ዋጋውን ሊያውቅ ለሚችል ሰው መውሰድ አለብኝ" አለ ሀፊት። ስለዚህ ወደ ባግዳድ ከተማ ወደ ሀሩን አል-ራሽድ ቤተመንግስት ሊሄድ ተነሳ። አልፎ፣ አልፎ ጥቂት ቴምር ለመብላት ካልሆነ በቀር ምንም ሳያርፍ ተጓዘ። ሀፊት ከዚያ ከገነት ውሀ ሁለት ስልቻ ቀድቶ አምጥቷል። አንድ ለራሱ አንድ ለከሊፍ ሀሩን አል-ረሺድ። ከብዙ ቀናት ጉዞ በኂላ ባግዳድ ደረሰና በቀጥታ ወደ ቤተ-መንግስቱ አመራ። ጉዳዩን ሲነግራቸው ሂድ ከዚህ አትዘባርቅ ሊሉት ፈለጉ፤ ነገር ግን ንጉሱ ማንም ሰው ቢሆን እኔጋ ከመጣ እንድታስገቡ የሚል ቋሚ ትእዛዝ ሰጥቷል። ስለዚህ ሀፊት ገባ።

"የአማኞች አዛዥ ሆይ!" አለ ሀፊት "እኔ አንድ ምስኪን በደዊ ነኝ። ነገር ግን የበረሀውን ውሀዎች በሙሉ አውቃለሁ፣ ሌላ እውቀት ባይኖረኝም። እና ይህን የገነት ውሀ አገኘሁ፤ ለአንተ የሚገባህ ስጦታ በመሆኑም ወዲያውኑ እንደ ገፀ በረከት ልሰጥህ ይገፍልህ ገስግሼ መጥቻለሁ።"

ሀሩን አርቆ አስተዋዩ ውሀውን ቀመሰው። እና የህዝብን የልብ ትርታ የሚያውቅ ንጉስ ስለነበረ ውሳኔውን እስኪያስታውቅ ድረስ ዘበኞቹ ሀፊትን ወስደው አንድ ክፍል ውስጥ እያስተናገዱ እንዲጠብቁት አዘዘ። ከዛ የዘብ አለቃውን እንዲህ አለው

"እኛ ከምንም የማንቆጥረው፤ ነገር ግን ለዚህ ሰውዬ እጅግ በጣም ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ነው። ስለዚህ ለሊት ሲሆን ከዚህ ውሰዱት። ትልቁን ወንዝ ትግሪስን ሊያይ በማይችልበት መንገድ ሂዱ። የኛን አገር ጣፋጭ ውሀ ሳታቀምሱት ወስዳችሁ ከመኖርያ ድንኳኑ አድርሱት። እዚያ ስትደርሱ አንድ ሺህ ወርቅ ዲናር ስጡት። እና ሀሩን እንዲህ ብሎሀል በሉት። 'ለስጦታህ አላህ ይስጥህ! ከንግዲህ የገነት ውሀ ጠባቂ ሆነህ ተሹመሀል፤ ለማንም ተጓዥ በኔ ስም ከውሀው በነፃ እንድትሰጥልኝ ይሁን።'"

በረከት ሁለት ደግሞ ርእስዋ "ቂሉ ሰው በትልቁ ከተማ" ትላለች።

አንድ ቂል አንድ ቀን በጣም ትልቅ ከሆነ ከተማ ደረሰ። በመንገዶቹ ያያቸው ሰዎች ብዛታቸው ናላውን አዞረው። "እዚህ አገር ከተኛሁ በኋላ ስነሳ ራሴን እንዴት ላገኘው እችላለሁ። ሆ! እንዳልጠፋ ልጠንቀቅ እንጂ" አለና ሲነሳ መታወቂያ እንዲሆነው ቁርጭምጭሚቱ ላይ አንድ ቅል አሰረ።

እዚያ እንግዶች ማረፊያ ውስጥ ሲተኛ የነበረ አንድ ተንኮለኛ ቀልደኛ ቂልየው ሰውዬ ምን እንደሚያደርግ አይቶት ነገሩ ገብቶታል። ሞኙ ከተኛ በኋላ ተንኮለኛው ቀስ ብሎ ቅሉን ከእግሩ ፈታውና የገዛ ቁርጭምጭሚቱ ላይ አስሮ ተኛ።

ቂልየው ደግሞ ከእንቅልፉ ነቃ። እና ቅሉን አየው። በመጀመሪያ "ሰውዬው እኔ ነኝ" ብሎ አሰበ ከዚያ ዘሎ ተነስቶ ሰውየውን እንቅ አርጎ ያዘና "አንተ እኔ ከሆንክ እንግዲያው እኔ ማነኝ? የትስ ነው ያለሁት?" አለው።

በረከት ሶስት ርእሷ ጠፋች። እናንተ አውጡላት (ኧረ! እንግዲያውስ ርእስ ያስፈልጋት ይሆን እንዴ?) እንዲህ ትላለች

አንድ ሞኛሞኝ ሰውዬ ከአንድ ሰው ቤት ወይን ጠጅ ያመጣበት ዘንድ አንድ ትንሽ ገምቦ ሰጥተው ላኩት። ገምቦውን በጆሮው ይዞ እጁን እያወዛወዘ ሲራመድ ከአንድ አለት ጋር አጋጨው ገምቦው ፍርክስክሱ ወጣ። ጆሮው ብቻ በሞኝ እጅ ቀረ። ሞኙ ጆሮውን እንደጨበጠ እተላከበት ቦታ ደረሰና መልእክቱን ተናገረ።

"ገምቦውስ የታል ወይኑን የምትቀዳበት?" አለው ባለ ወይን ጠጅ

"ገምቦውንማ አንድ ባለጌ አለት ሰረቀኝ"

"እና ጆሮውን ለምንድነው ያመጣኸው?"

"እሱማ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ሞኝ አልምሰልህ። ጆሮውን ያመጣሁት እውነት ለመናገሬ ማስረጃ እንዲሆን ብዬ ነው።"

ሀምሌ 24 ቀን 1986

# እኔ!

መሄዴ ነው እኔኑ ፍለጋ፡፡ አደን ደፈጣ፡፡ የማይሰለች ጨዋታ አልፎ፣ አልፎ ግን የሚያስደነግጥ ጨዋታ፡፡ አልፎ፣ አልፎ ካላስደነገጠማ ምኑን ጨዋታ ሆነው?

ለአንባቢ ያመች ዘንድ የጆ ሀሪን ክብ መስኮት አስቀድማለሁ፡፡ ጆ እና ሀሪ የተባሉ አሜሪካውያን ጓደኛሞች የቀረፅዋት ናት፡፡ እንዲህ ትላለች፣

ውስጣችንን ማለትም፣ አእምሮአችንን፣ ወይም ማንነታችንን ስንመረምረው አራት ሰዎች መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

1/ <u>እኔ የማውቀው ሌሎችም የሚያውቁት</u>፡- ስሜ፣ እድሜዬ፣ ወፍራም፣ ቀይ መሆኔ፣ በራነቴ፣ ንዴቴ እንደክብሪት በግ ብሎ ትንሽ እንኳን ሳይቆይ መጥፋቱ ወዘተ

2/ <u>ስለ እኔ፣ እኔ የማውቀው ሌሎች ግን የማያውቁት</u>፡- ነጎድጓድ ስሰማ የላይ ቤቶቹ ባዶ በርሜል ሲያንከባልሉ እንደሚታየኝ፣ የአውሮፕላን ድምፅ ስሰማ ደሞ ሰው በጩኸቱና በምናምኑ ካላደናቀፈኝ በቀር ድምፁን እከተል እከተልና የት ጋ እየተሰማኝ ነበር? የቱ ጋስ ጠፋ ያ ድምፅ? እላለሁ ስተኛ ደሞ እንቅልፌቱ እስክትመጣ እጠብቃት፣ እጠብቃትና ካሁን፣ ካሁን ስትመጣ አውቅባታለሁ ስል ወስዳኝ -- ነግቶ እነቃለሁ፡፡ የሎሚ ሽታ ለኔ ምን ምን እንደሚለኝ ከኔ ሌላ ማን ሊያውቅ ይችላል? ደሞ የወጥ ጣእምስ?

ማራዶና ጎል ሲያስገባ ስመለከት ምን እንደሚሰማኝስ? ወይም ምንም እንደማይሰማኝስ? የቻይና ንግግር ወይም የአረብ ዘፈን ስሰማስ? እና ጤዛ ስመለከትስ? ጨረቃዋን ሳያትስ? እና የመሳሰሉት።

3/ <u>እኔ የማላውቀው፣ ሌሎች ግን የሚያውቁት</u>፡- እግዜር ያሳያችሁ እንግዲህ! እዚህ አደገኛ አለም ውስጥ እየኖርኩ - ከአዱጋ ማምለጫዎቹንም አንዱ ክፍል ከሌሎች ሰዎች ጋር እየተሻማሁ እየተወዳደርኩ የመኖር ግዴታዬ መሆኑ እየታወቀ ጉዳዩ ውስጥ ስለእኔ ስለራሴ እኔ የማላውቀው ሌሎች የሚያውቁት የተለያየ ነገር አለ። አያስፈራም? ለምሳሌ ስሄድ ምን እመስላለሁ? በሽራፋዬ ስስቅስ? ከሰው ጋር ስደባለቅስ? እንኳን መጣ ይላሉ በልባቸው? ወይስ ምነው ባላየሁት ይላሉ? ስቆጣስ? እውነት አንድ ሰውዬ እንዳለኝ የዜዩስ መጥረቢያ እመስላለሁ ስቆጣ? (በነገራችን ላይ ዜዩስ መብረቅ እንጂ መጥረቢያ የለውም) ሴቶች ሲያዩኝ ደሞ አዘኔታቸው ይቀሰቀሳል። እነዚህና የመሳሰሉትን እኔን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለኔ ጨለማ የዋጣቸው ለሌሎች ግን ብርሀን ውስጥ ወለል ብለው የሚታዩ ናቸው።




4/ <u>ስለ እኔ የማላውቀው ሌሎቹም የማያውቁት</u>፡- ይኸውላችሁ የባሰ የሚያስፈራ መጣ። ስለ ራሴ እኔ የማላውቀው ሌሎችም የማያውቁት

ሲኖርስ? አንዳንዶቹ ስለሚያስቡልኝ አንዳንዱን ነገር ይነግሩኛል። ወይም እኔ በራሴ ተነሳስቼ ፀባዩን አሳምሬ ብጠይቅ የሚነግረኝ ላገኝ እችላለሁ። ይሄ ግን ለኔም ለሌሎችም ድቅድቅ ጨለማ ነው። ህልሜ ከየት ይመጣል? ትርጉምስ አለው ወይ? እኔ ስቆጣ የዜዩስን መጥረቢያ የምመስል ሰውዬ አቶ እገሌን ሳያቸው ፍርሀት፣ ፍርሀት የሚለኝ ለምንድነው? ሰውየው ጎድተውኝ አያውቁም ደግሞስ ሳያቸው ምናቸውም ሊያስፈራኝ የማይችል ኮሳሳ ምስኪን ቢጤ ናቸው፤ ግን ሳያቸው የልቤ ትርታ ቅኝት ወደ ፍርሀት ይለወጣል። ለምን? ሌላ ደግሞ ረስቼው የከረምኩትን እንቶኔን ያለአንዳች መነሻ ምክንያት አስታወስኩትና ስለ እሱ ትንሽ አሰብኩ። እና መንገድ ላይ አገኘሁት። ይሄ ለኔም ለሌሎችም ምስጢር ነው።

ሼክስፒር ያን ሁሉ ድራማና ቅኔ ከየት አመጣው? ሂትለርስ እንደዛ ሊጨክን እንዴት ቻለ? እነ እማሆይ ትሬሳና መሰሎቻቸውስ ለራሳቸው መኖር ትተው ለደኸዩት ለወደቁት ራሳቸውን ለማይችሉት ሰዎች አገልግሎት እንዲኖሩ ያደረጋቸው ምንድን ነው?

ይሄ ጎደለው፣ ይህን አጣ ልንለው የማንችለው ሰው በገዛ ራሱ ታንቆ ተገኘ ይሉናል። እንዴት? ለምን?

ይሄ አራተኛው እኔ በምን ሊመስል ይችላል? ስፋቱም፣ ጥልቀቱም የማይታወቅ በጨለማ የተዋጠ ውቅያኖስ።

እነዚህ አራት እኔዎች እንግዲህ ጆ እና ሀሪ ለትንተና ሲባል የከፋፈሉዋቸው ናቸው እንጂ ስንኖር ያው እኔ አንድ ሰው ሆኜ ነው። እሺ ለጆ እና ለሀሪ ስል አንድም አራትም ልሁን።

እንግዲህ በጆ ሀሪ መስኮት ገብቼ እኔኑ ፍለጋ ስቀጥል በጊዜው ውስጥ እየተንገዘኩ የምለዋወጥ መያዣ የሌለኝ እንትን ሆኜ እገኛለሁ። እንትን እንደሆንኩ እንጂ ምን እንደሆንኩ በውል ላውቀው አልችልም።

ልጅ ሆኜ ነብሴን እጅግ ደስ የሚላት ጢቢ፣ ጢቢ ስጫወት ነበር። ጎረምሳ ሆኜ ነብሴን እጅግ ደስ የሚላት ሴት ልጅን ሳቅፍ ነበር። ዛሬ

አርጅቼ ነብሴን እጅግ ደስ የሚላት ልጂ ስትስቅ ሳይ ነው፡፡ አሁን እነዚህን ሶስት እኔዎች ሳስተያያቸው አንድ ሰው ናቸው? እርግጠኛ መሆን ያስችላል፡፡ እኔ ሽማግሌውስ አንድም፣ አራትም ብሆን ይ'ኸው እዚህ አለሁ፡፡ ያ እኔ የምለው ልጅና ያ እኔ የምለው ጎረምሳ ግን የት ሄዱ? የኔ ትውስታ ውስጥ ከልጅየውም ከጎረምሳውም ከብዙ በጥቂቱ እንደ ፊልም ተቀርፆ ይገኛል እንጂ እነሱ ግን የሉም፡፡ እኮ እንዴት እኔ ውስጥ ተቀርፀው ሊገኙ ቻሉ? ያን ጊዜ ልጅየው ሆነ ጎረምሳው ሲኖሩ እኔ እዚያ አልነበርኩም'ኮ፡፡ ገና አልመጣሁም ነበራ፡፡ ያን ጊዜ ያልነበርኩ ሰውዬ ትውስታ ውስጥ አሁን የሌሉ ያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች ተቀርፀው ይገኛሉ፡፡ ይሄ እንዴት ሊሆን ቻለ? የጊዜና የትውስታ ምስጢራዊ ምትሀት ነው፡፡ ለመሆኑ ጊዜና ትውስታ ምንና ምን ናቸው?

ማርሴል ፕሩስት የተባለው ታላቁ ፈረንሳዊ የሀያኛው ክፍለ ዘመን ልቦለድ ደራሲ "የጠፋ ጊዜን ፍለጋ" በሚያስቸግር ስነጥበብ ያበጥረዋል፡፡ (ወጣት ደራሲያን ብትፈልጉትና ቢያጋጥማችሁ በእንግሊዝኛ ትርጉም REMEMBRANCE OF THINGS PAST ይላል፡፡

በነገራችን ላይ ለማሳጠር ስል ልጅ፣ ጎረምሳ፣ ሽማግሌ አልኩ እንጂ በልጅየውና በጎረምሳው መሀል ብዙ ተከታታይ እኔዎች አሉ፡፡ በጎረምሳውና በሽማግሌው መሀልም እንደዚሁ፡፡ ጢቢ፣ ጢቢ ከሚጫወተው እኔ በፊትም ብዙ ተከታታይ እኔዎች ነበሩ፡፡ ይህንን የእኔዎች የትውስታ እና የጊዜ ምን ነትና ግንኙነትን የጌታ ቡድሀ ተከታዮች ለምሳሌ ያመለክቱታል፡፡ እኔዎቹ ብዙ፣ ብዙ ደቂቃዎች ቢሆኑ ክሩ ከጊዜና ከትውስታ የተገኘ ሲባጎ ነው፡፡

እኔኑ ፍለጋ እንገዲህ ወደ ውስጤ ለማየት ሞከርኩ፡፡ አየሁ አይባልም፣ አላየሁም አይባልም፡፡ እንደው ያልለየለት በእንጥልጥል የቀረ እንቆቅልሽ እመስላለሁ፡፡ መቸስ እንግዲህ ይሁን! ምን አረገዋለሁ ከመቀ በል በስተቀር? ደሞስ ልቀበለው አልቀበለው ማን አማክሮኝ ያውቃል?

እሱ ይቅርና እኔኑ ፍለጋ ውጭውን ስቃኘው ምንድነኝ? ያልሰራሁትን ምግብ የምበላ፣ ያልሸመንኩትን ልብስ የምለብስ፣ ባልሰራሁት ቤት ውስጥ

የምኖር፣ በማልነዳው ታክሲ የምዘዋወር...... ግለሰብ ሆኜ አገኘዋለሁ። ሰው የሚባል በማህበር የሚኖር ዘር አለ። የዚያ ዘር አባል ነኝ። ሰው ሌላ ራሱን የቻለ ምስጢር።

ቋንቋ የሚባል ምትሀት አለው። ይሄ የሰው ዘር ገንዘቡና የስራ ክፍፍል የሚባል ሌላ ድርብ ምትሀት ወይም ተአምር አለው። እነዚህ ተአምራት ከየትስ እንዴትስ ተገኙ?

ሰው በመሆኔ ይሄ የሰው ዘር ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚኖር ለማወቅ ብሞክር ምናልባት ያንን ልፈልገው የተነሳሁት እኔን ለማግኘት ይሆን? ብዙም ተስፋ ያለው አይመስልም። ግን መሞከሬ ይቀራል? እስቲ እናያለን!

ነሀሴ 1 ቀን 1986

# እኔን ፍለጋ

እኔኑ ፍለጋ ስቀጥል የሰው ዘር ምንድንነው? የሚለው ጥያቄ ጋ ደረስኩ። በሁለት እግር የሚሄድ ወይ ፀጉር ወይ ላባ ሳይለብስ ራቁቱን የተወለደ ደካማ ፍጡር ነው በነጠላው ሲታይ። በህብረት ስለሚኖርና ስለሚሰራ ደሞ የሰው ዘር ሚች ከመሆኑ በስተቀር በእውቀትና በችሎታው እንደ አማልክቱ ተአምራዊ ነው። የሰለጠነው አለም የህክምና፣ የቀዶ ጥገና፣ የመድሀኒት ቅመማ ችሎታውና ምጥቀቱ ይታሰባችሁ፣ ሲኒማን የመሰለ ምትሀት ይታያችሁ። የሰው ዘር ጨረቃ ደርሶ መመለሱ ቀላል ነገር አይምሰላችሁ። እንዲያም ሆኖ ግን---

የሰው ዘር ደካማ ይሁን እንጂ ገዳይ ጭምር ነው። ምናልባት እዚህ አለም ላይ ገዳይ የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን አይቀርም። እግዜርን ሳንቆጥር ማለቴ ነው። (በአደን የሚኖር ሲርበው የዱር እንስሳ አድፍጦ ዘሎ ይዞ የሚበላውን፤ እንደ ገዳይ አንቆጥረውም። ሆድ ነው ገዳዩ እሱ አይደለም። ሰው ግን ሊበላ ሳይሆን ሊገድል ነው የሚገድለው። "ገዳይ ቶሎ ና" አላለችም እንኳ ዘፋኝቱ?) ጥንት ቃዬን በድንጋይ ገደለ ከሚባልበት ዘመን ተነስቶ የሰው ልጅ የገዳይ መሳርያውን ሲያሳድግ ወደ ወንጭፍ ተሸጋገረ። ከዚያ ወደ ቀስትና ፍላፃ፣ ነፍጥ ጠብመንጃ እና ወደ መትረየስ ወደ ቦምብ ወደ አቶሚክ ቦምብ አይ ሄሮሺማ! አይ ማሳዘኗ! (ናጋሳኪ ለምን ተደገመች ግን) የጃፓን ቢሮክራቶች ኮሚቴ ሲንቀራፈፉ መልሱን በጊዜ ሳይልኩ ቀርተው ይሆን? የጃፓን የንጋት ፀሀይ ይቅር ትበላቸው!

ኘሬዚዳንት ትሩማን የፈለጉት መልስ "እሺ በቃኝ ተሸነፍኩ" የሚል ነበር። ያ መልስ ሳይመጣ ጊዜ ናጋሳኪን አስደገሙ። (አስደንጋጭ ጥያቄ - ከናጋሳኪ በኋላም ጃፓን በተባለው የጊዜ ገደብ ትሩማን የፈለጉትን መልስ ባትሰጥ ኖሮስ? ስአሊለነ ቅድስት!))

የሰው ልጅ ገዳይ ብቻ አይደለም፤ አምላኪም ነው። የሰው ልጆች መልካቸው እንደሚለያይ - በምድሪቱ ገፅ ላይ አገራቸው የት መሆኑ እንደሚለያይ - ያን ያህልም ደሞ አማልክታቸውና አመለካከታቸው ይለያያሉ። አምላክ የሌለው ማህበረሰብ ግን እስከ ዛሬ ተገኝቶ አያውቅም።

አይነቱ ይለያይ እንጂ ሁሏም ማህበረሰብ የራሷ የሆነ አምላክ አላት። አንዳንዶቹማ ብዙ አማልክት ናቸው ያሏቸው ሀብታሞች ናቸው።

አቤት የአማልክቱ ቤቶች! ሰው ከሁሉም ትልቅና ውብ አድርጎ የሚሰራው የአምልኮ ቤቱን ነው። የህንድ ቤተ መቅደሶች ከነአስገራሚ ሀውልቶቻቸው በጥንት ግብፅ የካርናክ ቤተ መቅደስ፣ በአህጉረ እስላም መስጊዶች፣ በአህጉረ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያኖች።

እንግዲህ የሰው ዘር ሲባል የራሱ የሆነ ቋንቋ አለው። እንደዚሁም የራሱ የሆነ ሀይማኖት አለው። ሁሉም በየፊናው ቋንቋ ማለት የኛ ነው ይላል። ሁሉም በየቤተ አምልኮው የኛ ሀይማኖት ነው ትክክለኛው ሌላው ሁሉ መደናበርና ገደል መግባት ነው ይላል። ስለዚህ ለራሳችን ካላደላን በስተቀር የሁላችንም ድል ይሁን፣ ጉድ ይሁን፣ ሊታይ የሚችለው ከሞትን በኋላ ነው። ያኔ ወይ ሞተን እንቀራታለን፣ ወይ ሀይማኖት በየቋንቋው እንደሚለው ከሞት እንነሳለን፤ ወይም ነብሳችን እንደ ወፍ ወደ ላይ ቤት ትበራለች። ወይ እኛ እንደምንለው የኛ ሀይማኖት ብቻ ልክ ይሆንና እኛ ብቻ ነን እዚያ የምንደርሰው፤ ወይ ደሞ ቋንቋው የኛ ብቻ እንዳልሆነ ሁሉ ሀይማኖትም የኛ ብቻ አይሆንም፤ ትክክለኛው ሁሉም ልክ ይሆንና ሁላችንም ላይ ቤት እንደርሳለን።

እስቲ እናያለን ወይም አናይም።

ለማንኛውም ዛሬ እየኖርን ነው ፀሀፊም አንባቢም፤ የሰው ዘር በመሆናችን እኮ የሰው ዘር ማለት ምንድነው? ..... የሚለውን ጥያቄ እያሳደድን ነው፡፡ አንገብጋቢ ጥያቄ ይሉታል አንዳንድ ሰዎች፡፡

ሴሎች በሚሊዮናት እየተወለዱም የሴቱና የወንዱ ቁጥር እኩል ነው እድሜያቸው ሲደርስ ወንዱና ሴቷ ይጋባሉ ይወልዳሉ፡፡ ይህ ቤተሰብ ይባላል የኔ ቤተሰብ ከሌላው ሁሉ ይበልጥብኛል፡፡ የቤተሰብ ስብስብ መንደር ይባላል የኔ መንደር ከሌላው ሁሉ ጎሳዎች ይበልጥብኛል፡፡ የጎሳዎች ስብስብ ነገድ ይባላል ያኔ ነገድ ከሌሎች ሁሉ ነገዶች ይበልጥብኛል፡፡ የነገዶች ስብስብ አገር ይባላል የኔ አገር ከሌሎች አገሮች ሁሉ ይበልጥብኛል፡፡ ይህ አስተሳሰብ ወይም ሳይኮሎጂ ባማርኛ “ከራስ በላይ ነፋስ” ይባላል፡፡

በሌላ አባባል ሲበዛ የሰው ልጅ ወገናዊ ነው፡፡ የኔ ወገን ልክ፤ የሌላው ወገን ኤክስ! የኔ ወገን ይለምልም! ሌላው ወገን ይዘቅዘቅ!

እንግዲህ የኔ ወገን ሊሰፋም ሊጠብም ይችላል፡፡ ይህን የሚወስነው ያለሁበት ማህበረሰብ ፖለቲካዊና ባህላዊ የእድገት ደረጃው ይሆናል፡፡ ገና በጦርና በፍላፃ እያደነ ጫካ ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብ አባል ከሆንኩ የኔ ወገን ጎሳዬ ነው፡፡ ጎረቤቶቻችን ጎሳዎች ሁሉም ጠላቶቻችን ናቸው፡፡ የአደን ቦታም ይሁን፣ የግጦሽ ስፍራም ይሁን፣ ስለሚሻሙን በኛና በነሱ መሀል እርቅ የለም፡፡ ጎሳ ለጎሳ መዘራረፍ መገዳደል ነው፡፡

የራሴን ጎሳ አባላት እወዳለሁ፣ አከብራለሁ፣ እጠብቃለሁ፡፡ የሌላዎችን ጎሳዎች አባላት ከሆነ ግን እገድላቸዋለሁ፡፡ ጠላትን የገደለ ወንድ በጎሳው ፊት ልዩ ክብር ይኖረዋል፣ ሚስቱም እንደዚሁ፡፡ እና መግደልህ ብምን ይታወቃል? አሜሪካን ቀዮቹ ህንዶች ዘንድ ከሆነ የገደልከውን ጠላት የራስ ቅሉን በጥንቃቄ ትገፍና ቆዳና ፀጉሩን ይዘህ ወዳገርህ! አማዞን ወንዝ አካባቢ የሚኖሩት ጎሳዎች መካከልስ? የገደልከውን ጠላት አንገቱን ቆርጠህ ራሱን ይዘህ አገርህ ትገባና በልዩ ልዩ እፅዋት ሀይል(?) ታሳንሰዋለህ፡፡ እያነሰ ይሄድና ሲጨረማመት ቡጢ ሲያክል በቃ ጎጆህ ውስጥ ታንጠለጥለዋለህ፡፡ በነገራችን ላይ አንተ ቤት ስንት

አንጠለጠልክ? ሶስት ብቻ? ቀረብ ስንል በኛ አገር ጎሳዎች ዘንድ ደሞ የገደልከውን ጠላት ትሰልበውና ሰለባህን ይዘህ ወዳገርህ ሳይገድሉ መስለብም ይቻላል መሰለኝ።

እንግዲህ በጥቅሉ ብንናገር የኛን ጎሳ አባል የገደለ ወይ ይገደላል አልያም የደም ካሳ ይከፍላል። የሌላ ጎሳ አባል የገደለ ይከበራል። በሌላ አባል የኛ ጎሳ አባል ሰው ነው፣ የሌላ ጎሳ ግን ሰው አይደለም። ሌላ አጠቃላይ ነገር ብንናገር የወገንየው ስፋት ይለያያል እንጂ ነገድ አገር እያለ ያድጋል እንጂ የማይለወጠው ዘላቂው ስሜት ግን እንዲህ ይላል። ለኛ ወገን ወተትና ማር ሌላው ወገን አይኑን ላፈር! ይኸው ስሜት ከአገር በሰፋ ወገናዊነትም ሲሰራ ታይቷል።

ባለም አቀፍ ደረጃ ካፒታሊዝምና ሶሻሊዝም በተፋጠጡበት በቅርብ ባከተመው በቀዝቃዛው ጦርነት ላይ ታይቷል።

የሰው ልጅ ሲባል ወገኔ ነው። መላዋ ምድር አገሬ ናት የሚሉም አሉ። እነሱ ብፁአን ናቸው። እዚያ ለመድረስ ነው የሩቅ ተስፋው።

ነሀሴ 15 ቀን 1986

# ትዝታ

አንዳንድ ጊዜ ሰላም ሲሰማኝና ዘና ስል ወደ ትውስታዎቼና ትዝታዎቼ አገር እገባለሁ፣ እጎበኛቸዋለሁ። በአርእስት ተከፋፍለው ወይ በስርአት ተሰልፈው አላገኛቸውም፤ ተዘበራርቀው እየተንሳፈፉም የሚኖሩ ይመስሉኛል። የዛሬዎቹን ላስጎብኛችሁ። ሌላ ቀን ቢሆን ሌላዎች ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ለማንበብ እንዲያመች በተራ ቁጥር እናስቀምጣቸው።

<u>አንድ፡-</u>

ባስታወስኩት ቁጥር እንደ አዲስ የሚያስገርመኝ ነገር የአብርሀምና የይስሀቅ የመስእዋት ጉዳይ አንዱ ነው። እግዚአብሄር አንድ ልጅህን አረድና መስዋእት አቅርብልኝ ሲለው አብርሀም እሺ ብሎ ሊሰዋው ይዞት መሄዱ በጣም ያስደንቀኛል። በዚያም ላይ ማመኑ ያስቸግረኛል። እውነተኛ ታሪክ መሆኑን እያወኩም ማመኑ ያስቸግረኛል። ወጣት ሆኜም ማመኑ ያስቸግረኝ ነበር። አባት ከሆንኩ በኋላም ደሞ የባሰ ያስቸግረኛል። ዳሩ እኔ ማን ነኝና የአብርሀም ነገር ሊገባኝ ይችላል? መገረሜ ግን አይቀርም።

<u>ሁለት፡-</u>

ታሪክ ውስጥ ወረራዎችና ጦርነቶች በሽበሽ ናቸው። የሞንጎል ወረራዎች ግን አንድ ልዩ ምልክት ነበራቸው። ከሁሉ ዝነኞቹ

የጀንጂስካን እና የልጁ፣ ልጅ የቲሙርሌንክ (ወይም ተመርሌን) ወረራዎች ናቸው፡፡ አንድ ከተማ ሲማርኩ ኗሪዎችን በሙሉ አንገታቸውን ይቆርጡና ጭንቅላቶቹን በመከመር አንድ ፒራሚድ ይሰሩ ነበር፡፡ የነዚህ የሁለት ጦረኞች ፒራሚዶች ከሁሉም በላይ ትልቅ ነበሩ፣ ከሩቅ አገር ሆነው ይታያሉ፡፡ ያ ጋራ ምንድን ነው? ሲባል ‹‹የጀንጂስካን ፒራሚድ ነው›› ይባል ነበር፡፡

በአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተካሄዱ እነዚህ የሞንጎል ወረራዎች የጦርነት ታሪክ ውስጥ እንደሪኮርድ፣ ወይም ክብረወሰን ነገር ይዘዋል (ከፒራሚዶቹ ውጪ ማለቴ ነው) ይኸውም በሰላሳ አመት ውስጥ እስያንና አውሮፓን አጥለቀለቁ፡፡ ከወረራዎቹ ውጪ ግን ሌላ ታሪክ የሰሩ አይመስሉም፡፡

<u>ሶስት፡-</u>

የሀዋሪያው ጴጥሮስ ነገርም ሳስበው ግርም ይለኛል፡፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ‹‹እናንተስ ማን ነኝ ትላላችሁ?›› ብሎ ሲጠይቃቸው ጴጥሮስ ነው ‹‹አንተ የእግዚአብሄር ልጅ ነህ›› ብሎ የመለሰለት፡፡

ኢየሱስን ይሁዳ ስሞ ሲሸጠውና ሮማውያን ወታደሮች ሊይዙት ሲሉ ጴጥሮስ ነበር ሰይፉን የመዘዘውና የአንዱን ወታደር ጆሮውን የቆረጠለት፡፡ (ደግነቱ ኢየሱስ መልሶ ቀጠለለት እንጂ)

እንዲህ የተናገረውና ያደረገው ጴጥሮስ ታድያ እንዲያው መቶ በመቶ ይለወጥና ኢየሱስን ከተያዘ በኋላ ‹‹የሱ ተከታይ አይደለህም ወይ?›› ብለው ሲጠይቁት ‹‹እኔ ይህን የምትሉትን ሰውዬ አላውቀውም›› ብሎ ካዳ፡፡ ያውም ሶስት ጊዜ፡፡

ይኸው ጴጥሮስ ራሱ ደሞ ሮማ ከተማ ውስጥ ወንጌል ሲሰብክ አመት ካሳለፈ እና ብዙ ክርስቲያን ካፈራ በኋላ ተይዞ ሊሰቅሉት ሲሉ እንደ መፍራትና እንደ መለማመጥ ፈንታ ‹‹እንደ ጌታዬ አትስቀሉኝ፣ ቁልቁል ስቀሉኝ›› ብሎ ለምኖ ቁልቁል ተሰቀለ፡፡

<u>አራት፡-</u>

በእንግሊዝኛ ኢንሴክት ይባላሉ፡፡ እነዝምብ፣ እነ ቢራቢሮ፣ እነ ተርብና የመሳሰሉት፡፡ ከነዚህ አንዱዋ ተርብ መሳይ መርዘኛ ነገር ናት፡፡ አዳኝ ናት፡፡ ልዩ አይነት እንቁላሎቿን የምትጥልበት ጊዜ ሲደርስ ነው አደን የምትወጣው፡፡ ጉድጓድ ውስጥ የምትኖር ሸረሪት አለች፡፡ ያቺ ኢንሴክት ጉድጓዱ ውስጥ ትገባለች፡፡ ከሸረሪቷ ጋር የሞት የሽረት ግጥሚያ ይደረጋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ኢንሴክቷ ናት አሸናፊ፡፡ በመርዟ ስትወጋት ሸረሪቷ ጨርሳ ሽባ ትሆናለች፡፡ አትሞትም ሽባ እንደሆነች ኢንሴክቷ እሷ ላይ እንቁላሎቿን ጥላ ትሄዳለች፡፡ ጊዜያቸውን ጠብቀው እንቁላሎቹ ሲፈለፈሉ ሸረሪቷን ሽባይቱን እየበሉ ያድጋሉ፡፡ ስላልሞተች ስጋው ሳይበሰብስ ቆይቶላቸዋል፡፡ ከእነሱም ሴቶቹ አድገው ጊዜው ሲደርስ አደን ይወጣሉ፡፡ ልክ እንደእናታቸው እንግዲህ እናታቸውንም አይተዋት አያውቁም፡፡ ሽባዋ ሸረሪት ላይ ጥላቸው እንደሄደች ነው፡፡ እሷም እናቷን አይታ አታውቅም፡፡

እንዴት፣ እንዴት አርጎ ይፈጥረዋል እናንተ!? እውነትም አያልቅበትም አበው እንዳሉት፡፡

<u>አምስት፡-</u>

እቺ ደግሞ ከመግረምም አልፋ ደስ ትለኛለች፡፡ እጅግ በጣም በሚበርደውና በክረምቱ በረዶ በሚለብሰው በሰሜን ካናዳ አንድ ሳይንቲስት ይህን አስተዋለ፣ መዘገበ፡፡

አንዲት ከእንጨት የተሰራች አነስተኛ ቤት አለች፡፡ ኦና ነች፡፡ አንድ ተኩላ ክፉኛ ቆስሎ ኖሮ እየተጎተተ መጣና እዛች ባዶ ቤት ውስጥ ገባ፡፡ አንድ ጤነኛ ተኩላም አብሮት መጣና እዚያ ትቶት ሄደ፡፡

ሳይንቲስቱ በድብቅ ይመለከታል፡፡ በነጋታው ያ ጤነኛ ተኩላ በአፉ ትልቅ ስጋ ይዞ መጣና ወደ እንጨት ቤቷ ገባ፡፡ ጥቂት ቆይቶ ሄደ፡፡ በነጋታውም ሌላ ትልቅ ስጋ ባፉ አንጠልጥሎ መጣና ወደ ውስጥ ገባ፡፡ በነጋታውም እንደዚሁ ሲል፣ ሲል በርካታ ቀናት ካለፉ በኋላ

እንደተለመደው ጤነኛው ተኩላ ስጋ ባፉ አንጠልጥሎ መጣና ወደ ውስጥ ገባ። ጥቂት ጊዜ አለፈ። ከዚያ ሁለቱም ተኩላዎች ወጡና ሄዱ። ማስታመም ይሏችኋል እንዲህ ነው። እንዲያው ለመሆኑ ጓደኛው ይሆን? ወይስ ወንድሙ ይሆን? ወይስ ሁለቱም ይሆን?

ስድስት፡-

ባስታወስኳት ወይ በሰማኋት ቁጥር የምትገርመኝ የአማርኛ ተረት አለች። «የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ» ትላለች። እኮ ጦጣዋ የለመደችውስ ምንድነው? የሸመጠጠችውስ ምንድነው? አታውቀውም እሷ። ምክንያቱም እሷ የተረቱ መጨረሻ ናት እንጂ ከዚያ እሷ ከምትጨርሰው ታሪክ ጋር ተጠፋፍታለች። ላሟን እንዳጣች ጅራት መስላ ትታየኛለች። እና ታሳዝነኛለች። ምስኪን እኔም ምናልባት ባገናኛቸው ደስ ይላት ይሆናል ብዬ ብጠያይቅ ባጠያይቅ - እንዲያው ምንም አሮጊቶቹም፣ ሽማግሌዎቹም አያውቁም። እኔ የምፈራላት ቀስ፣ በቀስ «የለመደች ጦጣ» ብቻ ሆና እንዳትቀር ነው። ወይም «ሁል ጊዜ ሽምጠጣ» ብቻ ሆና እንዳትቀር ያስፈራታል። እዝጌር ይጠብቃት እንጂ እሷማ ምን ሀይል አላት? እንዴ መጥፋት ጀምራለች ለራሷ። ምስኪን!

ሰባት፡-

ለአደጋ ስለመጋለጥ። በዚህ ስራ ክፍፍል በነገሰበት ዘመን በስራህ ጠባይ የተነሳ ለአደጋ ትጋለጣለህ። ያ አደጋ ሊደርስብህም፣ ላይደርስብ ህም ይችላል። ግን ለአደጋው ትጋለጣለህ። ለምሳሌ ከጠመንጃ ዘመን በፊት የኖረ አዳኝ! በአውሬ ጥፍር የመቁሰል ወይም እስከነጭራሹ በአውሬ ጥርስ የመበላት አደጋ ሊደርስበት ይችል ነበር። እንክት እንጂ!

ለምሳሌ ያቺ የፈረደባት ሸርሙጣ በአብዛኛው ከፍቅርም ከትዳርም የተገለለችው እና እንደመደሰቻ እቃ የተቆጠረችው ከንቱ የሆነችው ቅጣቱ አነሳትና ለአባላዘሩ በሽታዎች ትጋለጣለች። በስራዋ ጠባይ የተነሳ። ሌባስ? እሱም በስራው ፀባይ የተነሳ አሩን እስኪበላ የመደብደብ አደጋ ሊደርስበት ይችላል። በኋላ ታዲያ ሰክረን ተጣልተን ነው ይልሀል። ‹አሄሄ! ስንተዋወቅ እንተናነቅ ነው› ወዳጄ።

(እቺም ሌላ ራሷን የቻለች ላሟን እንዳጣች ጭራ መስላ ልትታይ የምትችል ተረት ናት፡፡ ዋናው ታሪክ ጠፍቶ ቀርቷል፡፡ አልጠፋም የምትሉ ካላችሁ ጣፉልን፡፡ እባካችሁ ጦጣዋስ የምትሸመጥጠው ምንድነው? እየተዋወቅንስ የማንተናነቀው እንዴት ነው?)

ሳይካትሪስት እነሆ!

ቀኑን ሙሉ አእምሮአቸው ከታወከ ሰዎች ጋር ሲነጋገር ይውልና በትርፍ ሰአቱም ቢሆን ስለ አእምሮ መታወክ ሲያስብ ሲያሰላስል፣ ሲያወጣ ሲያወርድ ይቀጥልና ቀስ በቀስ ይሁን ወይስ በድንገት እሱም ራሱ ያብዳል፡፡ ባገሩ ጨርቅ መጣል ፋሽን ከሆነ ጨርቁን ይጥላል፡፡ ሳይካትሪስቱ ሁሉ ያብዳል ሳይሆን በስራው ፀባይ የተነሳ ለእብደት ይጋለጣል፡፡ አደገኛ ነው ይሄ ያለንበት አለም፡፡

ቢሮክራት እነሆ!

በሌላው ሰአት ጤነኛ ሰው እየሆኑ በስራ ሰአት ግን ሚጢጢ ቄሳር የመሆን አደጋ ይጠብቃቸዋል አቶ ቢሮክራት፡፡ ሰው አክባሪ ጦም ጧሚ ቤተስኪያን ሳሚ ናቸው'ኮ፡፡ አቤት ትህትና! ሰው ቀና ብለው አያዩም'ኮ፡፡ ይሄ የሚባልላቸው ሰውዬ ቢሮ ሲገቡ መለስተኛ ባለስልጣን ፊርማ ፈራሚ ይሆናሉ፤ ከዚያ በዚያች በቢሮ ይነግሱባታል፡፡ ወንበሯ ዙፋናቸው ትሆናለች፡፡ ባለጉዳይን መገላመጥ ነው፣ ስነ ስርአት ማስተማር ነው፣ ማመላለስ ነው፣ ማጉላላት ነው፣ ኮሚቴ መሰብሰብ ነው፣ ጉዳዮችን ያለምክንያት ማጓተት ነው፡፡ እግዜሩ ካልጠበቀው ቢሮክራቱ ሚጢጢ ቄሳር የመሆን አደጋ ይጠብቀዋል፡፡ አደገኛ አለም ነው ይህ ያለንበት፡፡ እሱው ይጠብቀን እንጂ፡፡ አሜን፡፡

**ነሀሴ 8 ቀን 1986**

# ትእዛዝ

ሙሴ ከማንም አንድ ግለሰብ የጠለቀ ለሰው ልጆች የሰጠው ስጦታ በሳምንት አንድ ቀን የማረፍ በረከተ ፀጋ ነው። ሙሴ ትእዛዙን ቢያውጅም ደሞ ፈጣሪ ስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፏል። ቀኑንም ቀድሶታልና እረፍ ቀኒቱንም ባርካት ቀድሳት አለ።

ትእዛዝ ይቀጥላል እንዲህ ሲል። አንተም ብቻ አይደለህም በሰባተኛው ቀን የምታርፍ። አሽከርህም፣ ባርያህም፣ አህያህም እንጂ። ሁሉም በሳምንት አንድ ቀን እረፍት ገንዘቡ ነው፣ አለ ሙሴ። እፎይ! ይኸውና እስከዛሬ ድረስ ቢያንስ የይሁዳው፣ የክርስቲያኑና የእስላሙ አለም ከነሚሊዮናት ህዝቦቹ እንደታዘዙት ይገኛሉ። የሙሴ እግዚአብሄር ይመስገን! የሙሴ የእረፍታችን ስም ይባረክ!

አሁን ከቆጠርኩላችሁ የሶስት ሀይማኖቶች ተከታዮች አልፎ በሳምንት አንድ ቀን እረፍትን መላው አለም እየታዘዘው ይገኛል። ማን እንደሙሴ እደግመዋለሁ፤ ማን እንደ ሙሴ! ይኸውላችሁ እኔ በተፈጥሮዬ የጠዋት እንቅልፍ እወዳለሁ ዝናብ ጭቃ ፀሀይ ውስጥ ብሰራ ደሞ ለኔ ኩነኔ ነው። ገበሬው ያመረተውን እየበላሁ ነው ለዚያውም። እንግዲህ እነ ገበሬዎች ጊዜውን ጠብቆ ተለወጠም እነ ፋብሪካ ሰራተኞች፤ እነዚህ ሰዎች በሳምንት አንድ ቀን ያርፋሉ ብሎ አዘዘ።

ትእዛዙ ከዕንፍ እስከ አፅናፍ በአለም ላይ የተዘረጋ ህግ ሆነ።

እኮ የማን ትእዛዝ እንዲህ ተዘርግቷል። ከፀሀይቱ የብርሀን ትእዛዝ በስተቀር? እንደው እኔስ ይህን ሙሴ ምናባቱ ላርገው ይሆን?

ሀውልቱን እንዳልቀርፅ! እሱ ራሱ አትቅረፅ ብሏል። እንዳልስለው ምስል አትስራ ብሏል።

ሙሴ አባ ሰንበት! እንደው ምን ላድርገው ይሆን ይህን ሰውዬ?

ልፋትና ላብ ድካም የበዛባቸው የመላው አለም ሰዎችና እንስሳት ቤዛ እና ጠበቃ! እኮ ማን እንደ ሙሴ? አልደግመውም። እሰልሰዋለሁ (ን'ጂ) ሙሴ ከተነሳ ዘንዳ ሀይማኖትን ወዲያ ትተን ሰውየውን እንደ አለማዊ አስተዳዳሪ ብናየው እሱ የኖረው ከሶስት ሺህ አመት በፊት ቢሆንም ከዘመን ዘመን እድገት አሳይቷል ቢባልም የዘመናችን የሶስተኛው አለም ከንቲባዎችና ጭፍራዎቻቸው ግን ሙሴ አደረሰበት የእድገት ደረጃ ገና የደረሱ አይመስልም። ለምሳሌ ሙሴ እንዲህ ይላል (በቀጥታ እንዳልጠቅስ ለጊዜው መፅሀፍ ቅዱስ አጣሁ ይቅርታ!) ‹‹ጉድጓድ ብትቆፍርና ሳትደፍነው ቀርተህ የጎረቤትህ በሬ ከጉድጓድህ ገብቶ ቢሰበር በሬውን ትከፍላለህ›› ሙሴ ለበሬው ያሰበለትን ዋጋ የሰጠውን ያህል ከንቲባዎቻችን የሶስተኛው አለማችን ለስካራሞቻቸውና ለአይነ ስውሮቻቸው እስኪያስቡ ድረስ ምዕአት ይቀድማቸዋል።

ሙሴ ቢሮክራሲውንም እንደዚያ ቀድሞ እስከንድቶት እናገኘዋለን። ምን ይላል ሙሴ? ለሰራተኛው የላቡን ዋጋ ወዲያውኑ ክፈለው እንጂ አታመላልሰው። በዚች በውድ አዲሳባችን እንኳ ንፁህ ክፍያውን ለመቀበል ስንት ሰው ምን ያህል እንደተጉላላ የቢሮክራሲ አምላክ ይቁጠራት መጉላላቱ ይቀጥላል! ወደ ፊት!

ሙሴን ካነሳን ዘንድ አብርሀም ወደዘራውና ሙሴ ራሱ ኮትኩቶ ወዳሳደገው ወደ እስራኤል አንዴ ብቅ እንበል። ኢየሱስ በሚያስተምርበት ጊዜ የሙሴን ህግጋት የሚያስጠብቁትና የሚያስፈፅሙት ካህናት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ይባሉ ነበር። ፀሀፍት የሚባሉም ነበሩበት።

እነዚህ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እንጀራቸው ጭምር ስለሆነ የሙሴን ህግጋት መንፈሱን ችላ ብለው ቃሉ ላይ ከመጠን በላይ ያተኩሩ ነበር። ከኢየሱስም ጋር ግጭታቸው ከዚህ የተነሳ ነበር። በአራቱ ወንጌሎች ከተመዘገቡት አያሌ ግጭቶች ሁለቱን እነሆ፡-

የማቲዎስ ወንጌል ምእራፍ አስራ ሁለት እንዲህ ይጀምራል፡- ‹‹በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በእርሻ መካከል አለፈ። ደቀ መዛሙርቱም ተራቡና እሸት ይቀጥፉም ይበሉ ጀመር። ፈሪሳውያንም አይተው፣ እነሆ ደቀመዛሙርትህ በሰንበት ቀን ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ አሉት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው ‹‹ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩት በተራቡ ጊዜ እርሱ ያደረገውን ወደ እግዚአብሄር ቤት እንዳገባ ካህናትም ብቻ እንጂ እርሱ፤ እና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሊበሉት ያልተፈቀደውን የመስዋእቱን ህብስት እንደበላ አላነበባችሁምን? ነገር ግን እላችኋለሁ ከመቅደስ የሚበልጥ ከዚህ አለ። ምህረትህን እወዳለሁ መስዋእትንም አይደለም የሰው ልጅ ምን እንደሆነ ብታውቁስ ሀጢአት የሌለባቸውን ባልኮነናችሁም ነበር። የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።

የሉቃስ ወንጌል ምእራፍ አስራ ሶስት ቁጥር አስር፤ ‹‹በሰንበትም በአንድ ምኩራብ ያስተምር ነበር። እነሆ ከአስራ ስምንት አመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች። እርሷም ጎባጣ ነበረች ቀንታምልትቆም ከቶ አልተቻላትም። ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና ‹‹አንቺ ሴት ከድካምሽ ተፈተሻል›› አላት እጁንም ጫነባት። ያን ጊዜ ቀጥ አለች። እግዚአብሄርንም አመሰገነች። የምኩራብ አለቃ ግን ኢየሱስ በሰንበት ስለፈወሰ ተቆጥቶ መለሰና ህዝቡን፡- ሊሰራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ። እንግዲህ በእነርሱ መጥታችሁ ትፈወሱ እንጂ በሰንበት አይደለም አለ። ጌታም መልሶ፡- ‹‹እናንት ግብዞች ከእናንተ እያንዳንዱ በሰንበት በሬውን፣ ወይም አህያውን ከግርግም ፈትቶ ውሀ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን? ይህችም የአብርሀም ልጅ ሆናከአስራ ስምንት አመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባትም›› አለው። ይህንም ሲናገር ሳለ የተቃወሙት ሁሉ አፈሩ።

እኮ ማን እንደ ሙሴ? ብዬ ዘርየውን የምድሪቱን ሰዎች ባስስ አጣሁ

እምላክነቱን ሸፍኖብኝ ሰውየውን ኢየሱስን እንደኛ የሚርበውንና የሚጠማውን፣ የሚደክመውን ርቦት በለስ ዛፍ ላይ ፍሬ ሊፈልግ ቢታጣ ጊዜ ማን እንደ ሙሴ? ብዬ የነበረውን መልሱ እምላክነቱን ወዲያ ትተን ሰውየውን ብቻ ብንወስድ ኢየሱስ እና ሙሴ እኩያ ለኩያ፡፡ እና ያኛው ሙሴ የጀመረውን ይህኛው ኢየሱስ ሲቀጥል፡፡

ያኛው ሙሴ ህግ ኖሮባት በማያውቅ አለም ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ ህግ ጀመረ ተከለ - ኮተኮተ አፀደቀ፡፡

ይኸኛው ኢየሱስ ሲመጣ ጊዜ ሙሴ የተከለው ወጣት ተወዛዋዥ ዛፍ አሁን ደርቋል፡፡ ተዉት የሙሴን ህግ በፈሪሳውያን በሰዱቃውያን እና በፀሀፍት የደረቀውን የፍቅር ለይቅርታ ቦታ የማይሰጠውን፡፡

አሁን የሙሴን ቃል ፊደል ለእነፈሪሳውያን እንተውላቸውና መንፈሱን እንደ እሳት አንስተን እኛ እየተቃጠልን እንኑረውና እናስተምረው አለ እኔ ልብ ውስጥ ያለው ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን ሰውዬው፡፡

**ነሀሴ 22 ቀን 1986**

# ያእቆብና ኤሳው

ባለፈው ስለሙሴና ስለ ሳራ እንዲሁም ስለሰባተኛው ቀን አለም አቀፍ እረፍት አወራን። ይህ እንግዲህ አብዛኛውን የሰው ልጅ ይመለከታል። በሰባተኛው ቀን የምታርፈው'ኮ ስድስቱን ቀን ጉልበትህን ስታሰራት ስለሰነበትክ ነው።

አሉ ታዲያ ጥቂቶች ከዚህ ህግ ውጭ የሚኖሩ። ጥቂቶች ሆነውም ለሰው ልጅ ግን በዝተውበታል። ወምበዴዎች ይባላሉ። በነሱ እምነት እነሱ ልዩ ፍጡር ናቸው። እኛ ላባችንን አንጠፍጥፈን የምናመጣውን እነሱ ሰርቀውንም ይሁን ነጥቀውን ሊወስዱት መብታቸው ነው። ከሰው በላይ ናቸው። በነሱ ቤት እኛ አህዮች ብንሆን እነሱ ጅቦች ናቸው። በልዩ፣ ልዩ መንገድ ይበሉናል። ኧረ እነሱ ከመብላት አይመለሱም! እርስ በርስ እንደተበላሉ ነው። ይህም ለኛ አንድ የቁጭት መፅናኛ ይሆናል።

የውምብድና ነብሷ ያው አንድ አይነት ሆኖ መልካቸው ግን ይለያያሉ፤ እንደ ታሪክ ወይም እንደ ተረት ስናያቸው ደሞ ወግ ወጉን ያጫውቱናል። ኪስ አውላቂ፣ ቤት ሰርሳሪ፣ ማጅራት መቺ ‹‹ይቅርታ አድርግልኝ ወንድም እንጀራ ሆኖብኝ ነው›› ሳይልህ ይቀራል። ከወደቅክበት የሚወስደውን ለመውሰድ ኪሶችህን እየፈታተሸ! ምንም ሳያገኝ ጊዜ ታድያ የወደቀ ሰውነትህን በንጼታዊ ግልፍታዊ እግሩ አንድ እርግጫ እያቀመሰ ‹‹ባይ ችስታ! ሀበሻ ባይ! ባይ! ያለው መሳይ እንትፍ!››

ይልብህና የሌቦች ጠባቂውን ሀይል እየተማፀነ ‹‹አቦ በሚቀጥለው ቅናኝና ካሰኘ። ሰባት ጧፌን ይገፄ ጠዋት እደጅህ ከተፍ ባልል ምናለ በለኝ›› ብሎ (ውስጥ ውስጡን እየፀለየ) ወይም እየተደራደረ ተመልሶ ጨለማ ውስጥ ይደበቅና ይጠብቃል። ችስታ ወይም መለስተኛ የመሰሉትን ያሳልፍና ወፍራም ኪስ ያለው የሚመስል ሰው ተፍ ተፍ እያለ ወደ ጉዳዩ እየሄደ ያለ ሲመስለው

ሰአሊለነ ቅድስት! ሌላውንስ አንናገረውም ወደ ውምብድና ዝርዝራችን እንመለሳለን። ቁጭ በሉ ነጋዴ፣ ቁጩ ይባል ነበር ደሞ ፎርጅድ

ፎርጅድ (Forgery) ከሚለው እንግሊዝኛ የተወሰደ የውሸት ሰነዶችን እውነት አስመስሎ የመስራት ጥበብ ነው። ‹‹ያ ለሚስትህ ገዝተህ የወሰድክላት ገረወይና ሙሉ ቅቤ ባይገርምህ ከስሩ አብዛኛው ሙዝ ኖሯል። ፎርጅድ ነው!›› በወረቀት ባይሆንም ማር አብዛኛው ሰም ሆኖ ያገኙት ብዙ ናቸው። ቁጥራቸውን እስታትስቲክስ መስሪያ ቤት እንዴት ሊያውቀው ይችላል? ደሞስ ቁጥራቸው ታወቀስ አልታወቀስ ልዩነት ያመጣል ወይ? ፎርጅድ የሚያወሩት እውነት ከሆነ አንዳንድ ብልጥ ለማኝ ጤነኛ እግሩን ቁስል መሳይ አስደንጋጭ ቀለም ይቀባና ይህንን ቁስሉን ለፀሀይና ለሰው አይን እያሳየ ይለምናል ስለ ሙሉ አካል! ፎርጅድ

ውምብድና'ኮ የራሷ የሆነ እጅግ የበዛ የስራ ክፍፍል አላት። የኛን የስድስት ቀን ሀቀኛ የስራ ክፍፍል ሳያክል ብዛቱ።

ውዲ አለን የሚባል ለሆሊውድ አስቂኝ ፊልሞችን በመስራት እጅግ የተሞገሰ አጠር ያለ ባለ መነፅር ሰውዬ። የኒውዮርክ ልጅ ነው ውዲ። አንድ ከሰአት አንድ መንገድ ማእዘን ላይ ህንፃውን ተደግፎ ጥቁር መነፅሩን አድርጎ ሳንቲም መቀበያ ኩባያውን በእጁ ይዞ የቆመውን አይነ ስውር የኒውዮርክ ለማኝ በእጁ አንድ ዶላር እያስጨበጠው፣

‹‹እንዴ ለመሆኑ ትላንትና በዚሁ ሰአት እዚሁ ቆመህ ሳለ አንድ ዶላር አልሰጠሁህም?›› ይለዋል።

‹‹አይ!›› ይለዋል አይነ ስውሩ ለማኝ ‹‹ለጎደኛዬ መሆን አለበት የሰጠሽው››

‹‹ላንተ አይደለም?››

‹‹እኔማ ትላንት በዚህ ሰአት ሲኒማ እያየሁ ነበር፡፡›› ፎርፎድ

እንደልማዳችን ከመፅሀፍ ቅዱስም ቅንጭብ አርገን እናጫውታችሁ (አይ እኛ! ደሞ ከመቼው እኛ ሆንን?)

ፎርፎድ፡- የያእቆብና የኤሳው ታሪክ ምናልባት የመጀመርያው ፎርፎድ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምስኪን ኤሳው፡፡ ሲወለድም እንደ ከብት ወይም እንደ አውሬ ፀጉር ለብሶ ተወለደ፡፡ ከያእቆብ ጋር መንታ ሲሆኑ ቀድሞ የተወለደው ግን ኤሳው ነው፡፡ የበኩር ልጅ ነበር ማለት ነው፡፡

ታሪኩ እንግዲህ ብልጡ ወምበዴ ያእቆብ ከገራገር ታላቅ ወንድሙ ከኤሳው በኩርነቱን እንዴት እንደወሰደበት ነው፡፡

ክፍል አንድ፡- አንድ ቀን ኤሳው በጣም ደክሞትና እጅግ በጣም ርቦት ከአደን ሲመለስ ያእቆብ ምን የመሰለች በቅመም ያበደች የምስር ወጥ ሰርቶ ያጋጥመዋል ‹‹እስቲ አብላኝ ርቦኛል›› ሲለው፣

‹‹በኩርነትህን በዚች ምስር ወጥ ሽጥልኝ›› ይለዋል

‹‹በቃ ሽጬልሀለሁ በራብ ከሞትኩ በኋላ በኩርነት ምን ያረግልኛል?›› ይልና ምሳውን ጥስቅ አርጎ ይበላል ኤሳው

ክፍል ሁለት፡- አባታቸው ይስሀቅ አርጅቶ ታወረ፡፡ አንድ ቀን ታመመና እየባሰበት ሄደ፡፡ ከዛሬ ነገ ሊሞት ሆነ፡፡ እናታቸው ርብቃ ታናሽየውን ያእቆብን እጅግ አብልጣ ትወደው ስለነበር ለብቻው ‹‹ግባና ለአባትህ እኔ ኤሳው ነኝ በረከትህን ስጠኝ በለው በኤሳው ድምፅ አስመስለህ›› ትለዋለች

‹‹አይሆንም ያውቅብኛል›› ሲላት ቆዳ እንደ መጫኛ አይነት በቀጫጭኑ ቆርጣ የያእቆብን እጆች (እና ደረት) ጥፍር አርጋ ጠመጠመችባቸው፡፡

‹‹ሂድ አይዞህ የኔ ገድ ይቀናሀል›› ብላው (ትንሽ ጆርባውን ገፋ ሳያደርጉት ይቀራሉ እኝህ ወይዘሮ ርብቃ?)

ያእቆብ ገባና አባቱን ‹‹ልጅህ ኤሳው ነኝ እንድትባርከኝ መጣሁ›› አለው አይኑ ስውሩ ይስሀቅ አልመስልህ አለውና ጠጋ በል ብሎ እጁን ዳሰሰው። ያው ፀጉራሙ ኤሳው ነው። ወይዘሮ ርብቃ ፎርጅድ እንዳደረጉት። ይስሀቅም ይህን ፎርጅድ ኤሳውን ባረከው። እሱ ከአባቱ ከአብርሀም የተቀበለውን በረከት ለዚህ ለልጁ አወረሰው። አበው ሴት መላ ታውቃለች ያሉት እንደነ ወይዘሮ ርብቃ ያሉትን ሴቶች እያሰቡ ሳይሆን አይቀርም።

እውነተኛ ኤሳው መጥቶ ‹‹አባቱን ልጅህ ኤሳው ነኝ ባርከኝ›› ቢለው

‹‹ምነው አሁን ባርኬህ?›› ይለዋል። ኤሳው በኩርነቱን በዚህ አኳኋን ተነጠቀ።

አባታቸው ይስሀቅ ወደ አባቶቹ አምላክ በተጠራ ጊዜ ያእቆብ ለአጎቱ ለላባ እረኝነት አደረ። ላባ ሁለት ሴት ልጆች ነበሩት ያእቆብ ታናሽቱን ራሄልን ወደዳት። ለአባቷ ዳርልኝ ሲል ለመነው። የነሱ ስርአት ይህን ይፈቅዳል። ላባም ‹‹ከፈለካት ሰባት አመት በነፃ አገልግለኝና ከዚያ ውሰዳት›› ይለዋል። ያእቆብም እሽ ይላል። ያ ሰባት አመት ሲሞላ ድል ያለ ሰርግ ተደገሰ ባህሉ በሚያዘው መሰረት ሙሽራ ማታ ሊሰናበት ሲል ሙሽሪት ተሸፋፍና ነው የምትሰጠው እስከ ነገ ጠዋት አያያትም።

ያእቆብም ሙሽሪትን አቅፎ አድሮ ጠዋት ቢያያት ራሄል አይደለችም። ሊያ ናት ይህ የእቶ ላባ ፎርጅድ ይባላል። ያእቆብ ሄደ ‹‹ምነው እንዲህ ጉድ ሰራኸኝ?›› ቢለው ላባ ‹‹ታላቅ ቁጭ ብላ እያለች ታናሽ አትዳርም ደምቡ አይፈቅድም›› አለው።

‹‹እኔ ታዲያ ራሄልን ላገባ ነው የተዋዋልኩት እንጂ ሊያን ነው እንዴ?››

‹‹እንግዲህ ሊያን አግብተሀል አገር እያየ፣ ራሄልን ከፈለግህ ሌላ ሰባት አመት ያለ ደሞዝ በነፃ አገልግለኝ››

‹‹እሺ›› አለ ያእቆብ። ፍቅር ነዋ! ሰባት አመት ምንድናት ራሄልን ያገኘ እንጂ! አይ የነሱ የሁለቱ ፍቅር!

ለማንኛውም ያእቆብ ኤሳውን ምን እንዳረገው ስናስብ ከላባ ቤት የእጁን አገኛት እንላለን። በል ተገዛ አስራ አራት አመት ሙሉ ወምበዴን፣ ወምበዴ ሲወነብደው!

ይሄኔ'ኮ ያእቆብና ኤሳው ሰማይ ቤት አልፎ አልፎ መገናኘታቸው አይቀርም። አንዳንድ በአል ቀን ሁሉም አብርሀም ቤት ይውላሉ እንበል። አንድ ቀን ታድያ ‹‹ወንድም ኤሳው ሆይ›› ይለዋል ያእቆብ ‹‹ያንተን በኩርነት ወስጀብህ ገነት ገባኊት ለልጆቼ ሲኦል ሆነች። እያቸው። እኔ በሰረቅኩ እነሱ ሲሰቃዩ። በግብፅ መራራውን የባርነት ፅዋ እስኪያንገሸግሻቸው ጠጡ። ከግብፅ ወጥተው አርባ አመት ሙሉ በምድረ በዳ ተንከራተቱ።

‹‹የወረሷትን አገር ጥቂት መቶ አመታት ብቻ እንደኖሩባት የሮማ ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ከወረረ በኋላ ልጆቹን በምድሪቱ ገፅ ላይ በታተናቸው ለብዙ አመታት በየአገሩ ተበታትነው በስደት ኖረው እየተጠሉ፣ እየተወገሩ፣ እየተቃጠሉ፣ አሁን በቅርቡ ሂትለር የሚባል ሰይጣን ፈጃቸው፣ አሰቃያቸው ፍዳቸውን አሳያቸው። አሁን የኔ ልጆች የሚደርስባቸው ጥቃትና ጥፋት ተቆጥሮ ያልቃል?

‹‹ወንድሜ ኤሳው ያንተ ልጆች ግን ምን አለባቸው? እሰው አይን አይገቡ። ታሪክም አላወሳቸው፤ ምክንያቱም በሰላምና በደስታ የሚኖሩ ህዝቦች ታሪክ የላቸውም››

ነሀሴ 29 ቀን 1986

# እግረ መንገድ ፪

# ውምብድና

## ውምብድና በየብስ

ኤልየት ኔል እና "የማይነኩት" የተባለው ምርጥ ፀረ ወንጀል ቡድን ሺካጎ ላይ ከመሰማራታቸው አያሌ አመታት አስቀድሞ በኒዮርክ ከተማ የአሜሪካን ርእሰ ጋንግስተሮች ስብሰባ ተደርጎ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የኒዮርክ ወንጀለኞች ርእሰ ሊቃነ ጳጳስ የነበረው ኤድ ኑሮው በስውር ከመሆኑ የተነሳ ሁለተኛ ስሙ እንኳ በውል አይታወቅም ነበር፡፡ ማለትም የእለሁ አለሁ ባዩ አልካፖን ተቃራኒ ነበር የሱ ባህሪይ፡፡

እዚህ ላይ የምናስታውሰው አለ፡፡ ከጥንት አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ወንጀለኛና ህግ አስከባሪ ሁል ጊዜ እንደተሽቀዳደሙ ነው፡፡ አንዴ ወንጀለኛ ይቀድማል ያመልጣል፤ አንዴ ህግ አስከባሪ ይቀድምና ይያዛል፡፡ ይህ መሰረታዊ እውነታ ሲዘረዘር በመፅሀፍ፣ በሲኒማ፣ በቴሌቪዥን፣ በቪዲዮ የምናገኛቸውን የወንጀል ምርመራ (የዲቴክቲቭ) እና የስለላ ስራዎችን ባህርይ ይገልፅልናል፡፡

እንግዲህ በአሜሪካ ከተሞች አንድ ወጣት ጋንግስተር በሰፈሩ ሲነሳ ሌሎች መሰሎቹ በየበኩላቸው ተነስተዋል፡፡ እነሱን አንድ በአንድ ካስገበረ ወይም ካስወጣ ካጠፋ በኋላ ሰፈሩን ይጠቀልላል፡፡ በሚቀጥለው ደረጃ መሰሎቹ በየበኩላቸው ሰፈራቸውን የጠቀለሉ አሉ፡፡ እነሱን ደሞ መሻሻልንና እድገትን እያሳየ በመጣው የወንጀል ጥበብና የመሳሪያና

የሰው ሀይል ጉልበቱ አንድ በአንድ ያስገብራቸዋል፡፡ ወይም ያጠፋቸውና ሲያበቃ ከተማውን ይጠቀልላል፡፡ የዚህን እለታዊ የሞት ሽረት ትግል ውስብስብነቱን ለጋንግስተሮቹና ለፈጣሪያቸው ትተን ለታሪካችን ስንል እጅግ ˈሲበዛ አቃልለነዋል፡፡

አሁንም በሚቀጥለው ደረጃ የአሜሪካን ጋንግስተሮች ደምብ የአንዱ ከተማ ንጉስ ከሌሎቹ ከተሞች ንጉሶች ጋር መፋጠጥ ነበር፡፡ ሳይቀድመኝ ልቅደመው ነበር የኒዮርኩ ኤድ ብቅ እስካለ ድረስ፡፡ ኤድ የሺካጎን (አልካፖንን) የዲትሮይትን፣ የኒው ኦርሊንስን እና የሌሎችን ታላላቅ ከተሞች የወንጀል ንጉሶች ስብሰባ ጠራ፡፡ እንዴት ሊያሳምናቸውና እንዴት እሺ ሊያሰኛቸው እንደቻለ አይታወቅም፡፡ እራሱን የቻለ የዲፕሎማሲ የማግባባት ተአምር ነበር፡፡ ኤድን እራሱን እሺ ይመኑት፡፡ የአሜሪካ ጋንግስተሮች እርስ በርሳቸው ሊተማመኑ እንዴት ቻሉ? ብዙዎች "አሄሄ! አሁን እውነት እገሌን አምኜ ኒዮርክ ድረስ ልሄድ? ወይ ስሄድ ወይ ስመለስ ቢያስደፋኝስ" ሳይሉ አይቀሩም በጥቅም የሚጋጩ ብዙ ናቸውና፡፡ እዚያ ላይ ነው ኤድ ተአምር የሰራው፡፡ ሰበሰባቸው፡፡

ኤድ ሁለተኛ ተአምር ሰራ፡፡ እነዚህን ምን ጊዜም ለመፋጀት ዝግጁ የነበሩትን የአሜሪካ ርእሰ ጋንግስተሮች ከስምምነት አደረሳቸው፡፡ ያስማማቸው ዋና ሀሳብ በአጭሩ እንዲህ የሚል ነበር፡፡ ‹‹አሁን እኛ የት ደርሰናል? እያንዳንዳችን አንዳንድ ከተማ ጠቅልለናል፡፡ ይበቃናል፡፡ ቀጥሎ ያለው እርስ በርሳችን መፋጠጥ፣ ሰፈርን ለመጠቅለል የምንሰራበት ታክቲክ ነበር፡፡ አሁን ግን አድገናል፡፡ እሱ ታክቲክ አይሰራም፡፡ እንበል ለምሳሌ አንተ የዲትሮይቱ ገዥ የኒው ኦርሊንስን እንዴት ትቆጣጠራለህ? የገደልከውን ሰውዬ ተክቶ ሌላ ጋንግስተር ይነሳል፡፡ ጠላት ለወጥክ እንጂ አላጠፋህም፡፡ አሁን የደረስንበት ደረጃ የመተባበርና የመከባበር መሆን አለበት፡፡ አንተ የኒው ኦርሊንስ ምን ጎደለህና ዲትሮይትን ትመኛለህ? ለዚያውም የማይቻል ነገር ነው፡፡ የኛ መጋጨት ለኤፍ ቢ አይ (ሀገር አቀፍ የወንጀል ተቆጣጣሪ ድርጅት) ያጋልጠናል እንጂ ለእኛ አይጠቅመንም፡፡ ይልቅ እንዴት ነው መተባበር የምንችለው? ምነው እነሱ ይተባበራሉ፣ ከነሱ እቺን እንኳን መማር ያቅተናል?...››

የወንጀል አለም ውስጥ አጀንዳዎች ቃለ ጉባኤዎች ቤተ መዛግብት ዝባዝንኪ የለምና ነው እንጂ...

በየአመቱ ኒዮርክ ውስጥ በኤድ ሰብሳቢነት የርእሰ ጋንግስተሮች ስብሰባ ይካሄዳል። ካስፈለገም ኤድ ልዩ ስብሰባ ይጠራል። የነኤልየት ኔስ የሺካጎ ምንጠራ ወደ አልካፓን ራሱ እየቀረበ ሲሄድ ጊዜ ኤድ ልዩ ስብሰባ ጠራ። አጀንዳው የሺካጎን ነገር እንዴት እናድርግ? ከሰፊ ውይይት በኋላ ሳይሆን አይቀርም እንዲህ የሚል ሀሳብና ውሳኔ ላይ ተደረሰ።

እነ ኤልየት ኔስ የሺካጎን ጋንግስተሮች በመልቀማቸው ሬዲዮ ጋዜጣው አጨብጭቧል፤ ህዝቡም ተደስቷል። ግን እስካሁን የያዙት ቀበሮዎቹን ተኩላዎቹንና ጅቦቹን ነው። አንበሳውን ሳይዙት እንዴት ይመለሳሉ? ተመለሱ ቢባሉም አይመለሱም። ስለዚህ...

እንፍቀድላቸውና አልካፓንንም ይያዙት። አንበሳው ተያዘ ብለው ሬዲዮ ጋዜጦች ይፎክራሉ ይሸልላሉ ግዳይ ይጥላሉ። የአሜሪካ ህዝብ ቁጣውን ይረሳና ወደየስራው። አልካፓን ለጥቂት ወራት "በእስር ይማቅቃል" (እዚህ ላይ ጉባኤው ሳይስቅ አይቀርም። ምክንያቱም በአልካፓን ኪስ መሆናቸው የታወቀ ነውና)

የአልካፓን ነገር በሌሎች አዳዲስ አከራካሪ ምክንያቶች ምክንያት መረሳት ሲጀምር የእስር ቤቱ ሹም እረፍት ላይ ሳለ ወይም ታሞ ተኝቶ ሳለ ትእዛዝ እናስተላልፍና እስር ቤቱን ሰብረው ያስወጡታል። ከዚያ ከሺካጎ ሌላ እፈለገበት ከተማ ይኖራል።

ጊዜው ሲደርስ በጉባኤው ውሳኔ መሰረት አልካፓን ተያዘና ታሰረ። አልካፓን እስር ቤቱ ውስጥ እየተዝናና የአሜሪካና የአለም ጋዜጦች ከእንትና ስንት ፎቶ ግራፍ ጋር ስንትና ስንት የእውነትም የውሸትም ታሪኮች ስላሉ እንደባፉ አየ። እንዲያው የሚወዳት ዝናው ቀጠሮዋን ጠብቃ በአለም አይን ወለል ብላ ታየችው። ይበቃዋል። ከእንግዲህ ጊዜውን ጠብቆ ከእስር ቤት ማምለጥ ነው።

አልካፖን ጊዜውን ቢጠብቅ ከእስር የሚፈታበትን ቀን ቢጠብቅ ያ ቀን አልመጣም አለ። ምነው? ቢባል ኒዮርክ የተሰበሰበው የጋንግስተሮች ጉባኤ እንዲህ ሲል በመወሰኑ።

‹‹እኛ እንደየአቅማችን የያዝነውን ይዘናል። ልታይ ልታይ ማለት፣ በከተማ መንገዶች ላይ መታኮስ፣ ከእንግዲህ ለኛ አይበጀንም። ለኛ የሚበጀን ድምፃችንን አጥፍተን የፖሊስና የእስር ቤት ሹማምንትን በተቻለ መጠን እየገዛን ወይ እያስፈራራን የተለመደ ስራችንን መቀጠል። አልካፖን እንደሆነ አያስችለውም። ወራት ሳያልፍ እንደገና መታኮስ መጀመሩ አይቀርም። ስለዚህ ይቅርበት።››

‹‹ይቅርበት። አርፎ እስራቱን ይጠጣ።››

በጋንግስተሮች አለም ውስጥ ማንም ለማንም አይታመንም። አልካፖን ከዛሬ ነገ ያስፈቱኛል ሲል ሲጓጓ ይሁን ወይስ በጋንግስተሮቹ የተሰራው ጉድ ገብቶት ተስፋ ከቆረጠ በኋላ ይሁን አይታወቅም፣ በእስራት እንዳለ ሞተ።

አይደለም! የሚል አጋጥመውናል። አልካፖን ከእስር ቤት አምልጦ ወደ ጣሊያን አገር ወደ ትውልድ መንደሩ ተመልሶ ሲኖር፣ የመንደሩ ብቸኛዋ ምግብና መጠጥ ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ቀይ ወይን ጠጅ እየጠጣ እያለ፣ ድንገት ከተፍ አሉ። ሶስት ፊታቸውን በሴት ስስ ካልሲ አፍነው የደፈጠጡ ታጣቂዎች።

“አልካፖን! ይኸውልህ ሰላምታ ከሌግስ ዳይመንድ!” ብለው በጥይት በሳሱትና በመኪናቸው ገብተው አመለጡ።

እንግዲህ ስለ አልካፖን ብዙ ልብ ወለዶች ተፅፈዋል። ልቦለዶቹን መነሻ አድርገው ብዙ ፊልሞች ተሰርተዋል። ከነዚህ አንዱን ያየ አሁን ከላይ የተፃፈውን አሟሟቱን አምኗል። ዳሩ ምን ይሆናል አልካፖን ወላጆቹ ኢጣሊያውያን አሜሪካውያን ይሁኑ እንጂ እሱ ግን የተወለደውም ያደገውም እዚያው ሺካጎ ውስጥ ነበር።

መስከረም 8 ቀን 1987

# ውምብድና በባህር

እንደ ልማዳችን እግረ መንገዳችንን ስንደናበር ሳይሆን አይቀርም ውምብድና አለም ውስጥ የገባነው። ይሁን ከገባንባት አልቀረ እንቀጥልባት።

ህይወት የጀመረችው በባህር ውስጥ ነው ይላሉ። ከዚያም ፈጣሪዋን እምና በድፍረት ወጣችና ምድርን አዳረሰች፤ እንዲሁም አየርን በክንፏ ቀዘፈችው። ከዚያም ወደ ባህር ተመለሰች። እንበል፣ በምሰሶዎች ላይ የተሰቀለ ሰፋፊ አራት ማእዘን ሸራ ጨርቅን ንፋሱ እፍ እያለ ተንሳፋፊ መርከቦችን ወደፈለጉበት በሚያደርሳቸው ዘመን። መርከቢቱ ውድ ሸቀጣ ሸቀጥ ተጭና ባህር ጤፍ ብላ ወደምትሄድበት እየተንሳፈፈች ሳለ እና ከሌላ መርከብ ጋር እየተላለፈች እያለ፤ ያችኛይቱ መርከብ ፎርጅ የነበረውን የአገር ምልክት ባንዲራዋን ትሰቅላለች። ጥቁሩ ባንዲራ መሀል ላይ በነጭ የተሳለ አፅም፤ የራስ ቅል። አቤት ያይኖቹ ቀዳዳ! የጥርሶቹ መግጠጥ ከራስ ቅሉ ስር ሁለት አፅም ቅልጥም በመስቀልኛ ተጋድሞ። አፅም የሞት ምልክት። እንግዲህ እግዜር ያሳያችሁ፤ እቺ የኛ መርከብ የንግድ ናት። ያቺ ወምበዴዋ መርከብ ግን የጦር ናት። ፓይሬት መርከብ (Pirate ship) ትባላለች አላልኳችሁም? ይኸው መድፍን ተኮሰችና! የኛ መርከብ ወዲያውኑ እጅዋን ሰጠች። ያችኛዋ ተጠጋችን። ባለ ትጥቅ ወምበዴዎቿ መርከቢቱ ወለሎች ላይ በተተከሉ አምዶች ላይ በታሰረ ገመድ እየተንጠላጠሉ እየተወዛወዙ ሀረግና ዝንጀሮ ይመስል ወደኛ መርከብ ተዛወሩ። አንድ አይና ባለ አንድ ጆሮ ባለ አንድ እግር ባለ አንድ እጅ ባለ ግንባሩ ላይ ጠባሳ፤ እና ሌሎችም አካላቸው ያልጎደለ ፓይሬቶች ወረሯት መርከባችንን። ምነው አካለ ጎደሎ መብዛቱ? ሁሏም መርከብ አይደለችማ እንደኛ መርከብ ባንድ አፍታ የምትሸነፍ። እሉ አልሞት ባይ ተጋዳዮች። እነሱ ውጊያ ላይ ነው ይኸ ሁሉ አካል የጎደለው። ፓይሬቶች ማን ነህ እያሉን በነገርናቸው ስማችንና ባዩት ልብሳችን ተመርተው እንዲሁም የገንዘብ ቦርሳችንን ፈትሸው ሀብታሞቹን ወደ መርከባቸው አዛወሯቸው። ጊዜው ሲያመች እነዚህን እስረኞች ዘመድ ወዳጆቻቸው በርከት ያለ ወርቅ ከፍለው ያስፈቷቸዋል - ራንሰም (Ransom) ይባላል።

ይህን ራንሰም የሚከፍልለት አያገኝም ብለው የገመቱትን ድሀ ብጤ ሰው ግን (ማለትም መርከቧ ላይ የነበረው አብዛኛውን) መዝናኛ፣ መጫወቻ ያረጉታል። ደም የጠማቸው ፓይረቶች አንዳንዶቹን ልክ እንደ ደረሱ ይሰይፏቸዋል። አንዳንዶቹን ሰይፍ ወደ አንገታቸው አካባቢ ሸጥ-ሸጥ ያረጉባቸዋል በማስፈራራት። የተስፈራራችው ደካማ ስጋ ሽንቷን ትለቃለች። ሌላም ባትጨምር ነው። ፓይረቶቹ ሳቅ! ለሳምንታትና ለወራት ያንኑ ባህር የሚመስል ሰማይ እያዩ እዚያው ሰማይ የሚመስል ባህር ላይ እየተንሳፈፉ ማሳለፍ እጅግ በጣም ሲበዛ ይሰለቻል፣ ነብስንና ህሊናን ያደነዝዛል። ስለዚህ አሁን እኛንና መርከባችንን ያንን የመሰልቸት ጭጋጋቸውን ማራገፊያ ያደርጉናል።

አብዛኛዎቹ የኛ መርከብ አባላት እንግዲህ ሳንቃውን መራመድ ሊኖርባቸው ነው። ይሄ ምን ማለት ነው? ከመርከቧ ጎን ወደ ባህሩ በረዥሙ የተዘረጋ፣ እና በዚህኛው በኩል ከመርከቧ አካል ጋር በፅኑ የተቸነከረ (ሳንቃ) ጣውላ አለ። አንድ ሰው ከመርከቧ ተነስቶ እስከ ሳንቃው ጫፍ ድረስ መራመድ ይችላል። የመርከባችን ተሳፋሪዎችና መርከበኞቿም የፓይረቶቹ ሳቅ ጭብጨባ ፉጨት እየተከተላቸው አንድ በአንድ በሳንቃው ላይ ሊራመዱ ነው ወደ ባህሩ እስኪወድቁ ድረስ። ለፓይረቶቹ ጨዋታ ነው እንግዲህ። የትኛው ሰው ሳንቃው ጫፍ ድረስ ይራመዳል? የቀሩትስ ከመነሻው እስከ የት ይራመዳሉ? እያሉ በመወያየትና በምወራረድ ጭምር መደሰት ነው። ሳንቃውን ተራምደህም አጋምሰህም ይሁን ጨርሰህ ጫፉ ደረስክ ያው ማለቂያህ ወደ ባህሩ መውደቅ ነው። የከፈተውን የአሳ ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም። በዚያን ዘመን እንግዲህ "በፓይረት እጅ አትጣለኝ!" ብለው የሚፀልዩ ብዙ ናቸው።

እንዲያ ብላችሁ ግን ፓይረት ሁሉ እንደነዚህ ያለ ሰው መሆኑን የረሳ የሰይጣን ቁራጭ አልነበረም ማለታችን አይደለም። ነበሩላችሁ፣ ድንቅና ልዩ የሆኑ ፓይረቶች። ከነዚህም ለኔ ዋነኛውና ቀንደኛው ድንቀኛው ፍራንሲስ ድሬይክ የሚባለው እንግሊዛዊ ነው።

እንደ ፍራንሲስ ድሬይክ የተዋጣለት ፓይረት ኖሮ ያውቅ ይሆን? በቅርቡ ሶቭየት ህብረትና አሜሪካን በቀዝቃዛው ጦርነት ሲፋጠጡ ትዝ ይበላችሁ:: ያ ጊዜ ደሞ አዲሱ አለም የተባለውን ደቡብና ሰሜን አሜሪካን እስፓኝ እና እንግሊዝ እየተሻሙት እየተቀራመቱት ነው:: በአህጉሮቹም ላይ በውቅያኖሶቹም ላይ እየተፋጠጡና ሲሆንላቸውም እየተጎሻሸሙ ናቸው::

ፍራንሲስ ድሬይክ በአንዲት መርከብ ተነስቶ ብዙ አመትም ሳይለፋ ባለሶስት መርከብ ፓይረት ሆነ:: እንግዲህ ሶስት የጦር መርከብ የሚያፈጥባት የንግድ መርከብ ምን ምርጫ ይኖራታል? መገበር ብቻ:: እነ ድሬይክ ግን "ሳንቃውን መራመድ" እና የመሳሰለውን ኢሰብአዊ ጨዋታ አይወዱም:: አላማ ያላቸው እንግሊዞች ናቸው:: ምርኮኛይቱ መርከብ ላይ ይወጡና ያላትን ወርቅና ውድ ሸቀጣ ሸቀጥ ወደ ራሳቸው መርከቦች ካዛወሩ በኋላ ለመርከበኞቹና ለተሳፋሪዎቹ በቂ ውሀና ምግብ ትተውላቸው ሲያበቁ ይሰናበቷቸዋል:: "ደህና ግቡ፤ ፍራንሲስ ድሬይክ ነው የዘረፈን በሉ" ይሏቸዋል::

የእስፓኝን መርከቦች ብቻ ነዋ ፍራንሲስ ድሬይክ የሚዘርፈው:: የእንግሊዝ መርከብማ እንዴት ይዘረፋል? ይልቅ እነ ድሬይክ የእንግሊዛ ባንዲራቸውን እያውለበለቡ ይጠጉዋትና ሰላምታም ዜናም ይለዋወጣሉ:: ምናልባትም በማእበል ወይም በሌላ ምክንያት ውሀና ስንቅ ጎድሎባት ከሆነ እነ ድሬይክ የጎደለውን ያሟሉላታል:: ፓይረት አደጋ ያደርስባታል ብለው ከገመቱም ሶስቱ መርከቦቻቸው ኮንቮይ ሆነው ይሸኙዋታል:: ፍራንሲስ ድሬይክ ስሙ ገነነ:: የስፓኝ ንጉስ በአምባሳደሩ በኩል ለንግስት ኤልሳቤጥ ቀዳማዊት ቅሬታውን ገልፆ ሲያበቃ ‹‹ፍራንሲስ ድሬይክ ከእንግዲህ ጥፋት ቢያደርስብን ከእንግሊዝ መንግስት እንደተሰነዘረብን ጥቃት ልንቆጥረው እንገደዳለን›› አለ::

ንግስቲቱም በዲፕሎማቲክ ቋንቋ አስተባበሉ:: ‹‹ፍራንሲስ ድሬይክ ተራ የባህር ወምበዴ ፓይረት ነው'ንጂ ከመንግስታችንም ይሁን ከግላችን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም›› አሉ::

ፍራንሲስ ድሬይክ ወደ ቤተመንግስት ተጠራ፡፡ “በእስፓኝ መርከቦች ላይ ያደረስከውን ብዙ ጥፋት ሰምተን ደስ ብሎናል›› አሉት ንግስቲቱ፡፡ ‹‹ኢንግላንድም ውስጡን እጅግ ትኮራብሀለች፡፡ በያዝከው ቀጥልበት፡፡ ግን አውቀህ ግባበት፡፡ ምናልባት እስፓኞች ቢይዙህ ኢንግላንድ እንደምታፍርብህ ወምበዴ እንጂ እንደምትኮራብህ ጀግና አድርጋ አትመለከትህም፡፡ ዲፕሎማሲ ነዋ!” አይ እንግሊዝ!

ፍራንሲስ ድሬይክ እጅ ነስቶ ወጣ፡፡ ጥቂት ጊዜ ያልፋል ለዝግጅት፡፡ ከዚያ የፍራንሲስ ድሬይክ ሶስት የፓይሬት መርከቦች ሹልክ እና ሰተት ብለው ገቡና የስፓኝ ዋነኛ ወደብ ላይ ያልታሰበ አደጋ ጣሉ፡፡ መርከቦችን አቃጠሉ፤ መርከበኞችንም ገዳደሉና ሲያበቁ፤ ማንም ምንም ሳያረጋቸው ወደመጡበት ባህር ተመልሰው ጠፉ፡፡

የስፓኝ ንጉስ ጨሱ፤ ተናደዱ፤ የእንግሊዝን ደሴት ለመውረር ከዚያ ቀደም ተሰርተው የማያውቁ ማንም የዘመኑ መርከብ ሊመልሳቸው የማይችል ልዩ ትላልቅ የጦር መርከቦች በብዛት እንዲገነቡ አዘዙ፡፡ ፍራንሲስ ድሬይክ ወደ ቤተመንግስት ተጠራ፡፡ የኤልሳቤጥ ፈገግታ ምን ይመስል ይሆን? “ምን ማድረግህ ነው ግን?” ሲሉ ጠየቁት ንግስቲቱ

“የስፓኝን ንጉስ ጊማቸውን በእሳት ጨረፍ አረኩላቸው፤ ንግስት ሆይ” አለ፣ የንግስቲቱ ታማኝ አገልጋይ ፓይረት፡፡ ንግስት ኤልሳቤጥም ያበጠው ይፈንዳ አሉና ለወምበዴው ድሬይክ ትልቅ ማእረግ ሰጡት፡፡ ሰር ፍራንሲስ ድሬይክ ተባለ፡፡ ለኢንግላንድ ትልቅ ውለታ የዋሉ ጥቂቶች ናቸው ‹‹ሰር›› የሚለው ማእረግ የሚሰጣቸው፡፡ ንግስቲቱ ሰር ፍራንሲስን የእንግሊዝ የጦር መርከቦች አዛዥ አድርገው ሾሙት፡፡ አይ እንግሊዝ!

እስፓኝ አርማዳ የተባለውን በምንም ሀይል የማይበገር የባህር ሀይል እንግሊዝ ላይ አዘመተች፡፡ እንግሊዝን ለአንዴና ለመጨረሻ ለመጨፍለቅ፡፡

“የስፓኝ አርማዳ መርከቦች ወደ ኢንግላንድ እየተጠጉ ነው!” የሚል መረጃ ሲመጣ ሰር ፍራንሲስ ድሬይክ ካንድ ጓደኛው ጋር ቴኒስ

እየተጫወተ ነበር፡፡ ጓደኛው ራኬቱን ጥሎ ወደ ጦር መርከቡ ሊሮጥ ሲል ታድያ፣ ሰር ፍራንሲስ ድሬይክ “ቆይ እንጂ ጨዋታችንን እንጨርስ!” አለው

ጨዋታውን ጨረሱና ሰር ፍራንሲስ ድሬይክ ከዚያ ሄዶ የስፓኝን አርማዳ ድባቅ መታው፡፡

ታሪኩ እንዲህ ቢያልቅ ይጥም ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ግን አርማዳን ድባቅ የመታት ንፋስና ባህር ተጋግዘው ማእበል አስነስተው ነው፡፡ የሰማይ ስባሪ ወይም የገደል ቅራፊ የሚያካክሉት የስፓኝ መርከቦች ትልቅነታቸው በዛባቸውና እንደ ልብ መንቀሳቀስ ተሳናቸው፡፡ ሚጢጢዎቹ የእንግሊዝ መርከቦች ግን እንደፈቀዳቸው እየተሽለኮለኩ ጉድ ሰሩዋቸው፡፡ ማእበሉ ራሱም በርካታ የስፓኝ መርከቦችን አሰመጠ፡፡

ከዚያ በኋላ እንግሊዝ ይበልጥ እየጎለበተች ስፓኝ ግን እየተዳከመች ሄደች፡፡ ወይ ሰር ፍራንሲስ ድሬይክ ውምብድና በባህር አትልም?

መስከረም 16 ቀን 1987

## ውምብድና በአየር

አለ ደሞ ውምብድና በአየር፡፡ ወምበዴዋ ኤሮፕላን ነጋዴዋን ኤሮፕላን በአየር ላይ ተጠግታ የምትማርካት ሳይሆን ጤነኛ ተሳፋሪ መስሎ ይገባና (ፎርጅ!) ኤሮፕላንዋ በረራዋን ከጀመረች በኋላ ሽጉጥ ፓይለቱ ላይ እያነጣጠረ፣ “ይህ ጠለፋ ነው አቅጣጫህን ለውጥ” ብሎ ወደመረጠው ከተማ ኤሮፕላን ማረፊያ ይበራሉ፡፡ እዚያ የወምበዴ ቡድኑ ከመንግስት ጋር ይሁን ከባለፀጋ ጋር ይደራደራል፡፡ “ተሳፋሪዎቹ እንዳይገደሉ ከተፈለገ...” ይልና እንዲደረግለት የሚፈልገውን ይናገራል፡፡

ከእለታት አንድ ቀን፣ ጓድ ብሬዥኔቭ የሶቭየት ህብረት ፕሬዝዳንት በነበሩበት ወቅት አንዲት ኤሮፕላን ከጆርጂያ ዋና ከተማ ቲቢሊስ ተነስታ ወደ ሞስኮ በረራ ጀመረች፡፡ እንግዲህ የጆርጂያ ሰዎች ከሌሎች የሶቭየት

ህብረት ዜጎች የተለዩ ናቸው፡፡ እንደ ፈረንሳይ ወይም እንደ ጣሊያን ላቲን ሰዎች ናቸው፡፡ ሳቅ ጨዋታ፣ ሙዚቃ ዳንስ ይወዳሉ ያዘወትራሉ፡፡ ወይን ጠጅ ያመርታሉ፡፡ የነሱ አገር ሙቀት በሚሆንበት ወራት ሞስኮ ክረምቱ ነጭ በነጭ አልብሷት በብርድ ትንቀጠቀጣለች፡፡ በዚያን ወራት በሞስኮ አበባ በጣም ይወደዳል፡፡ የጆርጂያ ሰዎች ደሞ በብዛት አበባ ይወስዳሉ ወደ ሞስኮ፡፡

አንድ ሁለት ሶስት ሆነው ከአበባው ጋር አንድ ሁለት ሶስት ሳጥን ሙሉ የወይን ጠጅ ጠርሙሶች ይዘው ይሄዱና አበባቸውን ሸጠው ሆቴላቸውን ተከራይተው ሲያበቁ ከዚያ መብላት መጠጣት መደሰት ነው፡፡ የልባቸውን ካደረሱ በኋላ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ፡፡

በዚሁ ወራት ነበር ያቺ የቅድሟ ኤሮፕላናችን ከቲቢሊስ የተነሳችው፡፡ ጥቂት እንደበረረች ከተሳፋሪዎቹ አንዱ እንዳይታወቅ ፊቱን ሸፋፍኖ ተነሳና ፓይለቱ ላይ ሽጉጡን አነጣጠረ፡፡

"ወደ ፓሪስ አዙር!" ሲል አዘዘ ጠላፊው፡፡ ፓይለት ትእዛዙን ፈፀመና በሬዲዮ ለሞስኮ ኤሮፕላን ማረፍያ ተጠልፈው ወደ ፓሪስ እየሄዱ መሆናቸውን ተናገረ፡፡ "በቃ እጅ እጅ አለን የናንተ ኮሚኒዝም፡፡ ወደ ነፃነት አገር መሄዳችን ነው›› ሲል አበሰረ ጠላፊው፡፡

በዚህን ጊዜ ሌላ ተሳፋሪ ብድግ አለ፡፡ በእጁ ቦምብ ይዟል፡፡ "ሽጉጥህን ጣል! አለዚያ ይህን ቦምብ አፈነዳዋለሁ፡፡"

ጠላፊው ሽጉጡን ጣለ

ባለ ቦምቡ ሰውዬ፤ "ጓድ ፓይለት ወደ ሞስኮ አዙር!" ሲል አዘዘ፡፡

ፓይለቱ ወደ ሞስኮ እያዞረ የቦምቡን ድራማ ለአየር ጣቢያው በሬዲዮ አስተላለፈ፡፡ ድንቅ ተባለ፤ ጋዜጠኛ በብዛት ተጠራ፤ የሞስኮ አየር ጣቢያ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ ካሜራዎች ተጣበበች፡፡ አድሀሪያን ጠላፊዎች አብዮታችንን ለማጉደፍ ቢፍጨረጨሩም አብዮታዊያን ጓዶች በወኔ ያከሸፏቸዋል፡፡

ድምፅ ማጉያው "የትቢሊስ በረራ አሁን አረፈ" ሲል ምድረ ጋዜጠኛ ወዘተ መቁነጥነጥ ባሰበት። ተሳፋሪዎቹ መጡ። የካሜራው ብልጭ ድርግም አይጣል ነው።

በመጨረሻም ጠላፊው በደህንነቶች ተይዞ ሲወሰድ ባለቦምቡን አብዮታዊ ጀግና ጋዜጠኞች፤ "ጓድ እንዲህ ህይወትህን ለአደጋ አጋልጠህ ኤሮፕላኗን ወደ ሞስኮ የመለስካት ለምንድ ነው?" ሲሉ ጠየቁት።

"አስቡት እንጂ ጓዶች" ሲል መለሰ፤ "በዚህ ሻንጣዬ የሞላሁት አንድ ሺ ዕንፈዳ ፓሪስ ብወስደው ምን ዋጋ ያወጣልኛል?››

ወይ የጆርጂያ ሰዎች ውምብድና በአየር አትልም?

## ውምብድና በየአይነቱ

አንዳንዴ እነዚህ ቀን የጎደለባቸው ሴቶች ትልቅ "ሆቴል" ውስጥ ይቀጠራሉ። ሙዚቃም መጠጥም ያለበት። የሴት ገላ ያማረው ወንድ የሚመጣበት። እዚሁ ሲሰሩ ውለው ያመሹና ሂሳብ ለእሜቴ የሆቴሉ ባለቤት ያስረክባሉ። በውሉ መሰረት ገላቸውን ለማንም ቀፋፊ ድብርታም ሳይቀር አከራይተው ያጠራቀሙትን ገንዘብ ወይ ሩቡን ወይ አንድ አምስተኛውን ይዘው ወደ መኝታ ይሄዳሉ። የገቢው ሶስት አራተኛ አምስተኛ የቤቱ ነው።

ጎረምሳው ባለ ሰባት ሴትም ሆቴለኛዋ ባለ ሀምሳ በየበኩላቸው ከገቢያቸው የተወሰነ ዶላር "ለበላይ አካል" በየሳምንቱ ያስረክባሉ። ምክንያቱም አንዲት ትልቅ ከተማ፤ ሩብዋም ይሁን ግማሽዋ ወይ ሙሉዋ ከሽርሙጥና የሚገኝ ገቢን በሚመለከት ከአንድ ጋንግስተር ስልጣን ስር ናት። ቁማርን በተመለከተ ሌላ ጋንግስተር ስር ናት። የጥበቃ ገንዘብ ደግሞ የሌላ። ጋንግስተር ለመባል ቢያንስ ብዙ ሀብት እና በቁጥርም በትጥቅም የተጠናከረ የግድያ ጓድ ሊኖር ያሻል። ጋንግስተሮቹ "ከመፋጀት መቀራመት" የሚል እምነት አላቸው። አማርኛ ባያውቁም እንደ ጋንግስተሮቹ ገዳይ ለመቀለብ አቅም የሌለው ግን አንድ ሰው

ለማስገደል የፈለገ አንድ ግለሰብ ለሚቹ ኮንትራት ይገዛለታል። እንበል አባትህ የናጠጡ ሀብታም ናቸው። ታዲያ ምን ዋጋ አለው? አልሞት ብለው ችክ አሉ ሽማግሌው። በየት በኩል እንውረስ? ልዩ አይነት ወንጀለኞች አሉልህ። ስራቸው አንተ ገንዘብህን ከፍለህቸው ያመለከትካቸውን ሰው መግደል ነው።

ለሽማግሌው ኮንትራት ልትገዛላቸው ድርድር ትጀምራላችሁ

"ለንዲህ አይነት ከባድ ስራ…"

‹‹ምን ከባድ ነው? ለራሱ ሊሞት አንድ ሀሙስ የቀረው ሽማግሌ!››

"እንግዲያው ኮንትራቱንም ለራስህ ሸጠው ሽማግሌውንም እራስህ ከንብላቸው"

"እንደሱ ማለቴ ሳይሆን… ስንት ልክፈል?"

"ደምቡ እንኳ ሀምሳ ሺ ነበር"

"ለዚች ለቀላል ስራ?"

"እኛ እቺን ቀላል ስራ ሰርተንልህ የሚሊዮን ብር ጌታ ልናረግህ ነው። አንተስ ውለታችንን እንዴት ትመልሳለህ? አሁን በቅድሚያ የሚከፈል ሀምሳ ሺ። ህጋዊ ወራሽ ከሆንክ ልክ በሳምንቱ ደግሞ ተጨማሪ መቶ ሺ።"

እሺ ከማለት ሌላ ምርጫ አይኖርህም። ወኔው የለህም'ንጂ አንተ'ኮ ለውርስ ብለህ አባትህን ስታስገድል ንፁህ የጋንግስተር ስራ ነበር የሰራ'ኸው። ደግነቱ አንተ ከዚያ አታልፍም። ሚሊዮንህን ወርስህ እንደፍጥርጥርህ ደስታህን እየገዛህ ሌላ ነብስ ሳታጠፋ ትኖራለህ።

"ምን ዋጋ አለው? ሽማግሌው በህልሜ እየመጣ አላስተኛ አለኝ። እንቅልፍን ያህል ነገር ሲነሳኝ ከአቅሙ።"

የዚያን ሰው በደል ብናይለት ተገቢ ነው። እኛህ አባትየው በፊት አላወርስ ብለው መቶ ሀምሳ ሺህ አስከሰሩት። አሁን ደሞ እየመጡ

እንቅልፉን ይነሱታል? አላበዙትም፡፡ የሱን ጉዳት ግን ያወቀለት የለም፡፡ ሰው ያወቀላቸው የሽማግሌውን መሞት፡፡ አሁን በዚያ እድሜያቸው ሞት ምንድን ነው? እረፍት ነው፡፡ በሱ እድሜ እንቅልፍን ያህል ነገር መከልከል ግን------- ብቻ በመጨረሻ የሚያፋርዳቸው ያፋርዳቸዋል፡፡

ሌላ ርእስ፡፡ እርስዎ እጅግ የተከበሩ በከተማው አሉ ከሚባሉት ከጥቂቶቹ የሚቆጠሩ ነዎት፡፡ ከሚሊዮናት አልፎ በቢሊዮናት ንግድ የሚንቀሳቀስ ኩባንያ የቦርድ ሊቀመንበር ነዎት፡፡

ታዲያ ምን ይሆናል፣ አንዳንድ ጎደሎ ቀን ያጋጥማል፡፡ ያቺ ከብዙ ወራት አንስቶ አይንዎን የምትፈታተን የልጅዎ ጓደኛ ዛሬ ልጅዎትም ያለችበት ፓርቲ አምሽታችሁ ያቺ ያበጠች ኮረዳ እንዴት አርጋ እንዳጭበረበረች እንጃ ማንም ሳይነቃባችሁ እሷ መኝታ ቤት ወሰደችዎ፡፡ ወጣት ስጋዋ በሳል ስጋዎትን ለኮሰው፡፡ ሲጠጡት ያመሹት ውስኪ ደሞ ምላስዎትን ፈታው፡፡ ብዙ ነገር ቀባጠሩላት፡፡

ከጥቂት ቀን በኋላ የኮረዳዋ ወንድም ነኝ የሚል ጎረምሳ ቀጠሮ ተቀብሎ ቢሮዎ ይገባል፡፡

"ምን ልርዳህ ወዳጄ?" ይሉታል፤

"ማንም ሌላ ሰው ሊሰማ እንደማይችል እርግጠኛ ነዎት?------ እሺ እንግዲያው" ይልና ከያዘው ሳምሶናይት ቴፕ ሪኮርደር ያወጣል፡፡ ይሰሙት ዘንድ ያጫውትሎታል፡፡ ያቺ ያበጠች ኮረዳ ለካ ስጋዎን ስትለኩስ የሚቀርፀውን ቴፕ ደሞ ተጭናዋለች፡፡ የሚተነፍሱት ትንፋሽና የሚናገሩት ብልግና ከርስዎ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ቴፑ ብዙም ሳይጫወት በእጅዎ አጥፋው ይሉታል፡፡ መሀረብ አውጥተው የእፍረት ላብ ከግንባርዎ እየጠረጉ፡፡

"ከዚህ ሌላ አራት ግልባጭ አለን በልዩ ልዩ ቦታ የደበቅናቸው፡፡ እህቴ ገና አስራ ስምንት አመት ስላልሞላት፤ ህጉ የሚያየው ህፃን ልጅ አባለጉ ብሎ ነው፡፡ ደሞስ እህቴ ምን መጣባት በለጋ እድሜዋ እንዲህ የሚሰሯት በሀብትዎት ተመክተው፡፡ እህቴ ግን እድሜ ለወንድሟ ሙሉ

ካሳ ታገኛለች። አስር ሺ በሳምንት ለሁልጊዜ። ለርስዎ ትንሽ ገንዘብ ናት። የመከፈል ብልሀት ደግሞ አይጠፋም።››

እሺ ከማለት ሌላ ምርጫ አይኖሮትም። ሲሰናበትዎት በማስጠንቀቂያ ነው "እኔ ወይ እህቴ ወይ ለየብቻ ወይ በአንድነት አንዳች አደጋ ቢደርስብን፣ ወዲያውኑ አንዱ ክር ለእንትን ጋዜጣ አንዱ ክር ወደ ፖሊስ ወንጀለኛ መምሪያ ክፍል ይደርሳል።"

እርስዎ ገቢ ከተደረጉ ዘንዳ እህት ተብዬዋ ሌላ የርስዎን ቢጤ ለማደን ጥፍሯንና ከንፈርዋን እየተቀባች ነው። ቅባት ሽቶም ተደርድሯል፤ እድሜ ለእርስዎ! ይህ አይነት ወንጀል (blackmail) ይባላል። "ጉድ ጉልጎላ"። ከሁለት አመት በኋላ ልጅቱ የሚገባት ክፍያ ከሀምሳ ሺ ወደ ሰማንያ ሺ ከፍ ይላል። እርስዎ እሺ ከማለት ሌላ ምርጫ አይኖርዎትም።

**መስከረም 22 ቀን 1987**

# ታክሲና ወያላ

ባሁኑ ጊዜ አዲሳባ ውስጥ በታክሲ መሄድ እንዴት ነው? እሺ በታክሲ መወሰድ እንበለው፣ ወሳጂው ማን እንደሆነ አይታወቀም። ታክሲ ቢሉዋችሁ ደሞ እነዚህን ድሮ እንደልብ የምንዘዋወርባቸውን አራት ተሳፋሪ ብቻ ይዘው ውር ውር ይሉ የነበሩትን ፊያቶች አይደለም። እነሱ በአሁኑ ጊዜ የተሳፋሪ ምልክት ስናሳያቸው እያዩን ባዷቸውን እየተሽከረመሙብን ያልፉናል። ከሀብታም ጋር ቀጠሮ ቢኖራቸው ይሆን? ትልልቅ ሆቴል አጠገብ ደሞ ተኮልኩለው ይታያሉ።

ታክሲ ስንላችሁ "ውይይት" የተባሉትን ወያላ የማስጮህ ክብርና ማእረግ የታደሉትን ማለታችን ነው። ታክሲ ከሩቅና በስም አንድ ቢሆንም ገብተው ሲሳፈሩት ግን ሶስት አካል ያለው መንኮራኮር መሆኑ ግልፅ ነው። እነዚህም ሶስት አካላት - አንድ መኪናው በፋብሪካ ተሰርቶ የመጣው፣ ሁለት ሾፌሩ መኪናውን የሚነዳው፣ እና ሶስት ወያላው ገንዘቡን የሚቀበለው ናቸው።

ታክሲ በስጋ እሳቦት ጠለቅ ተብሎ ሲመረመር ከነዚህ ከሶስት አካላቱ የበዛ ሆኖ ይገኛል። ከፋይ ተሳፋሪዎችንም ይጨምራል። ያለ ከፋይ ተሳፋሪዎች ታክሲ አይኖርም መኪና እንጂ።

በእድሜ በጣም የማይራራቁ፣ እርስበርስ ተስማምተው የሚሰሩ ሾፌርና ወያላ አዛውንት ልንላቸው የምንችል ሰውዬ፣

"ሰራተኞቹ በተስማሙ ባለቤትየው ምን ተጎዳ?"

"አይ መማር! ይሄ ነው መማር የምትሉት! ሁለቱ ከተስማሙ ሊበሉት አይደል? እንዴት ነው 'ሚበሉት ልንገርህ? ለምሳ ሁለት ክትፎ፤ ለእራት ሌላ ክትፎ አንድ አትልልኝም? ማታ መኪናዋንና ሂሳቡን አስረክበው ሲሄዱ ደሞ አምስት አምስት ድራፍት። በየቀኑ አስበውና በአመት ስንት ይመጣል? አያሳብድም? ጨርቅ አያስጥልም?"

"የማንን?"

"የባለቤትየውን ነዋ! ዋ ያልደረሰበት!" ይላሉ እራሳቸውን እየነቀነቁ። እነዚህ ውስጥ የራሳችን ሀበሽነት ብቅ ይልና ሰውየውን ምልክት አድርጎ "ይሄ ሁሉ እንግዲህ የዛሬውን አያርገውና በጊዜያችን ቀጥረን የምናሰራ ባለ ታክሲ ነበርን ለማለት ይሆን?" ይልና ተመልሶ ይደበቃል። እኛ እን ጠይቃለን፣ "ባለቤትየው የሚሻለው ሾፌርና ወያላው ባይስማሙ ነው?"

"ነው'ንጂ። አሁንም አይንና አፈር ይሁኑ! እሳትና ጭድ ያርጋቸው አንድዬ!"

"ያኔ ለባለቤቱ ጥቅሙ የት ላይ ነው?"

"አይበሉትማ! ካልተስማሙ እንዴት አርገው ይሮሉታል?"

ሾፌርና ወያላ ሳይስማሙ ሲቀሩ ወይም እሳትና ጭድ ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ለተሳፋሪው ይደብራል። መኪናው ሚኒባስ ሲሆን ሾፌሩ "አዋቂ ነኝ ስልጡን ነኝ፤ ወያላዬ ግን ደደብ ፋራ ነው" የሚለውን ባዶ ጉራ በተግባር ለማሳየት የፈለገ ይመስል፤ ዝም ብሎ መኪናውን እንደመንዳት ወደ ኋላ እየዞረ ወያላውን ይነዘንዘዋል እንደ ክፉ ባል "ጨኽ'ንጂ! እየው አንተ ስትኀተት ያ ጥይቱ ወያላ ቀለባቸው። በቃ ዝጋው! እንሂድ። እኔ ካልነገርኩህ አንተ ምንም አስበህ መስራት አትችልም ማለት ነው?"

የወያላው አባት አያርገንና፣ እሺ እኮ አሁን ገና የሚማርበት የሚጫወትበት እድሜ ነበር እንጂ ለማማ ሳንቲም ብሎ ከዚህ ከምላሳም መርዘኛ ሰውዬ ጋር የሚጠመድበት ጊዜ አልነበረም።

በተገላቢጦሹ ወያላው አዛዥ፣ ሾፌር ታዛዥ ሆነው ያጋጥሙናል። በአንድ ወቅት ከፒያሳ ተክለሀይማኖት፣ አብነት ጦር ሀይሎች፣ ቀጠና ሁለት፣ ያሳፈረኝ የውይይት ወያላ ገና ቅድም ያወረደኝ ያሀል ወለል ብሎ ይታየኛል። ቀላ ቀጠን ያለ የአስራ አራት አመት ወጣት ነው። በረባሶ ጫማ አድርጓል።

"አሁን ምናለ ቀስ ቢሉ?" ነጂውን እየጮኸባቸው የኋላ በሩን ዘጋና ከተሳፋሪዎቹ ተቀላቀለ። እራሱን በቁጭት እየነቀነቀ ግን ደሞ ፈገግታው ፊቱ ላይ እየታየ።

"አላሰራ አሉን'ኮ እኚህ ሽማግሌ" አለና ወደ ሾፌሩ በኩል እየተናገረ። "ሰው ሁሉ ሞልቶ ይነሳል፣ እኛ ይኸው ገና ሶስት ሰው ቀርቶናል። እና አንድ ጋቢና አራት ሰው። መንዳት ነው ብቻ። እሳቸው ተሳፋሪ ገባ አልገባም መንዳት!" አለና ተነስቶ በሩን ከፍቶ ይጣራ ጀመር።

"ጦር ሀይሎች" አለና በሩን ደጋግሞ በጥፊ መታው። ቆም ብሎ የነበረው መኪናችን ፍጥነት መጨመር ጀመረ።

ወያላው ሮጦ ይደርስብንና እየገባ "ኧረ እባኮትን አቁሙ!" ብሎ ጮኸ። አቆሙ። ወጣና ወደፊት ወደሳቸው እየሄደ ወደኋላ አሳያቸው። ተናገራቸው። ተመልሶ መጣ ገባና በሩን ዘጋ። አቀርቅሮ ቆየ። አሁንም ቀና ሲል ከንዴቱ ጋር ፈገግ አለ ራሱን እየነቀነቀ።

"አሁን ሄድኩና፣ እዩዋቸው እነዚያ እኔ ይዣቸው የነበረ ሁለት ተሳፋሪዎች። አሁን እርሶ አልቆምልህ ስላሉኝ እዚያኛው ታክሲ ውስጥ እየገቡ ነው - እዩዋቸው" አላቸው።

"እና ምናሉህ?" ይሉታል አንዲት ሴት ወይዘሮ

"ይግቡ አሉኛ! እሳቸው ምንም አልመሰላቸው። ጠጉሬን አስቆሙት!"

"በኋላ ሂሳቡን ስታስረክብ ባለቤትየው ስራህን በትጋት አልሰራህም ብሎ ይቆጣሀል 'ንዴ?"

"ኧረ'ሱስ ምንም አይሉኝ ማለቱ ራሳቸው ናቸው ባለቤቱ"

"እንግዲያው አንተ ምን አስጨነቀህ?"

"ምነው አያስጨንቀኝ? ስራ የሰጡኝ ዘመዶ አይደሉም? ምንስ የስጋ ዘመድ ባንሆን"

ብድግ አለና በሩን ከፍቶ ወደ ውጪ መጮህ ጀመረ "ጦር ሀይሎች፣ ቀጠና ሁለት፣ ሞቢል፣ ቶታል!"

አንድ ሌላ ወያላ ደሞ በሌላ ጊዜ ያጋጠመኝ እሱ እራሱ መቶ በመቶ ተረስቶኛል። የማስታውሰው ግን የጩኸት መልእክቱን ነው ለተፈላጊ ተሳፋሪዎች። ለዚያውም መኪናው ሞልቶ (ከአምባሳደር ፒያሳ) ጋቢና ብቻ ነው ባዶ። እና ወያላ "ፒያሳ በጋቢና! አያምልጣችሁ!›› ፒያሳ በጋቢና ባይባልም ታክሲው ይሞላ ነበር። እና ምን ይጠበስ በጋቢና መጠበሻ?!

በውይይት ሲጓዙ አብዛኛውን ጊዜ ከማያውቁት ሰው ፊት ለፊት ቁጭ ብሎ መተያየት አይቀርም። ታዲያ አንዳንድ ሰው ያጋጥማል ወንድም ይሁን ሴት ቢያዩ ቢያዩ ያ ሰው ሰው አይመስልም (ድንግጥ! ውስጡን) መኪና አስቁሞ ሲገባ ከተቀመጠ በኋላም ሳንቲሙን ሲከፍል አይተናል። ሆኖም ግን ስናየው ሰው አይደለም። የውሸት ሰው ነው። ለምን የውሸት ሰው ይሆናል? ደሞስ ማን ምንን ሊዋሸበት ነው የውሸት ሰው የላከብን?

"ሰባተኛ፣ አማኑኤል!" ሲል ይጮሀል ወያላችን በሩን ከፍቶ ዘሎ እየወረደ። ተሳፋሪ ብዙ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ልዩ የሆነ ሰው ያጋጥማል። አንዱ ልዩ ይሆንና ግን የሚሰለች ሰው ነው። የሚኒባስ ጋቢና ተቀምጦ ስለ ሞተርና ኤሌክትሪክ ወይም ዘይት በረዥሙ በድግግሞሽ በጣም በሚጮህ ድምፅ ያወራል። ከተሳፈረባት እስከወረደባት ደቂቃ ቴስቲኒ፣ ጎሚኒ፣ ማኞኒ፣ ኩሽኔታ እና አንድ አራት ሌሎች የጋራዥ ቃላት አወቅኩ ብሎ ጆሮአችንን ያደነዝዘዋል። ሲወርድልን ሰው ይተነፍሳል ይዝናናል፣ እፎይ!

አንዱ ግን ልዩ ይሆንና አይሰለችም። አንድ ቀጫጫ ባለመነፅር ጎረምሳ ገና ከመግባቱ "ስለተባበሩት መንግስታትና ስላልተባበሩት

መንግስታት አስር ጊዜ ተደናብረው አንድ ጊዜ ቢዋጣላቸው ነው ያውም በስለት፡፡ ያልተባበሩት መንግስታት ግን ምን አለባቸው? አልተባበሩ አልተደነባበሩ ነፃ ናቸው፡፡ ይህን በሚመለከት አንዲት ጥቅስ ነበረችኝ ጠፋችኝ፡፡ ትጥፋ በቃ፡፡ ሌላ ልጥቀስላችሁ፡፡

"እጠቅስሽ አልጥቀስሽ ማን ቆጦ ጠየቀኝ
ውሀ እንደቁም ነገር ስጠጣው ያነቀኝ"

ጥልቅ ቅኔ የተናገረ ይመስል ዘወር ዘወር ብሎ እያየን "ጥቅስን የመሰለ ነገር የለም" አለ፡፡ አሁን ለምሳሌ "የእስክንድር እናት ታጠቂ በገመድ፣ የቄሳርም እናት ታጠቂ በገመድ፣ የአኒባል እናት ታጠቂ በገመድ፣ የናፖሊዮን እናት ታጠቂ በገመድ፣ የእሮሜልም እናት ታጠቂ በገመድ፣ ከእንግዲህ ልጆችሽ አይበሉም እንቁላል"

ታክሲው ጉዞውን ይቀጥላል፡፡

አዲሳባ መንገዶች ላይ በወያላዊ ታክሲ መዘዋወር ስንቀጥል እንዴት ነው? "ካሳንቺስ የሞላ ካሳንቺስ የሞላ ያዝላቸው! (በሩን በጥፊ ይጠልዘዋል) ይኸው ግቡ ፋዘር! ካሳንቺስ የሞላ!"

እንገባለሁ፣ ታዲያ ባዶ ናት ታክሲዋ፡፡ ነጂዋ ሳይቀር ሞተሩን አጥፍቶ ሄዷል፡፡ መኪናዋ በጥፊ የተመታችለትና "ያዝላቸው!" የተባለው ለካ ያ መኪናዋ ውስጥ የሌለው ሾፌር ሰምቶ የመኪናውን ፍሬን እንዲይዝ እና እኔ እንድሳፈር ኖሯል፡፡

ሀበሻ አገር መሆኔን ባላስታውስ ኖሮ ወያላው ጨርቅ የማያስጥል እብደት አድሮበታል ብዬ እገምት ነበር፡፡ "ሳይሆን" አልኩት ለራሴ፤ "አገረ እብደት ሌላ፤ አገረ ሀበሻ ሌላ፡፡ ምንም ያህል ቢመሳሰሉ"

"ድንቄም ሞላች!" እያሉ ገቡ አንድ የጉልት ሸክም በነጠላ የያዙ ሴትዮ "ጢም ብሎ የሞላ ውስጥ ነው'ንዴ የጨመርከኝ እንተዬ? በየት ልተንፍስ?"

"አሁን ይሞላል እሜትዬ ምን አለ በሉኝ፡፡ ዳይ ያዝላቸው!" አለና አሁንም መኪናይቱን አንድ የከበሮ ጥፊ አጠዛት፡፡ "ካሳንቺስ የሞላ!"

ሰባት ስምንት ተሳፋሪ ከገባ በኋላ መኪናይቱ ሾፌሩን ወክላ የከበሮ ጥፊ ሲያርፍባት ጊዜ፤

"አቦ ጆሮ ያማል በሀይል አትምታት!" አለው አንዱ ተሳፋሪ በነጭናጫ ድምፅ።

"አይዞት አሁን ይሞላል" አለና ጥፊውን ደገማት በሙሉ ጉልበቱ። "ምን'ዚህ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ከበሮ አይመታም?" ብሎ ዝም። በሚጭን ወያላና በተሳፋሪ መሀል ያለው መደማመጥ ይህን ይመስላል።

"ካሳንቺስ የሞላ" ገና አሁን እውነት ሆነች። ሾፌሩ የለም'ንጂ! ቀየን ደቂቃዎች አለፉ። "ምን አይነት ብልግና ነው ባካችሁ እንውጣና ሹፌር ፍለጋ እንሂድ! እንዲያው'ኮ ሀበሻ ሀበሻን ሲንቀው!" ሲባባሉ ተሳፋሪዎቹ ወያላ አፍሮ ውጪ ቆሟል። ሾፌሩ ሲመጣ በንዴት "አስር ደቂቃ ታስጠብቀናለህ!" አለው።

ለአንዷ ስልክ ደውሎ ይሁን ጫማውን አስጠርጎ ይሁን ወይስ እግሮቹን አፍታቶ ይሁን. . . ወንድም ሾፌር ገባ። ይቅርታም አልጠየቀ፤ አስራ ሁለት ሰው ማስጠበቁን ልብ ያለው አይመስልም። ገቢናው ተዘጋ። መኪናውን አስነሳና "ተንቀሳቀሰ"። ተሳፋሪዎቹ ለሾፌሩ ምንም የተናገሩት ቅሬታ የለም። ወላ ትንፍሽ! ባለጌው ሾፌር ከነትእቢቱ ገቢናው ውስጥ ተዘግቶ ጉዞዋችንን...

ከጀመርን በኋላ፤ አንድ አንገታቸው ክራቫት የለመደ የሚመስሉ አዛውንት ጀመሩ። በባህላችን መሰረት በወያላው በኩል አርገው ለሾፌሩ የማይደርሰውን መልእክት ሲልኩ፤ እና እሱን ያልተናገሩ መስለው ለተቀሩት ተሳፋሪዎች ሲናገሩ፦

"ሰውን እንደዚህ ማስጠበቅ ነውር ነው። ከፍለን ነዋ የምንሄደው። አውቶብስ እስኪመጣ መጠበቅ ሰልችቶን የእጥፍ እጥፍ ከፍለን እዚህ እንገባለን፤ ለካ ሾፌር መጠበቅ የሚሉት ግብር አለብን! ፍትህና ዳኝነት የማይገባው ህዝብ!"

"ሰውኮ ቀጠሮ ይኖርበታል" (ሰአታቸውን መልከት አደረጉ። በልማድ እንጂ ዛሬ አላሰሯትም። ኪሳቸውን ፈተሽ ፈተሽ አደረጉ። እዚያም

የለችም። ኖራም አታውቅም ይሄኔ።) "ሰው ወይ እንዳቅሚቲ የአየር ባየር ጉዳይ ቀጠሮ ይኖረዋል። በሾፌር ጥበቃ እክል የተነሳ ቢዝነሱ ያመልጣል። ሰው የሽምግልና ቀጠሮም ሊኖርበት ይችላል።"

"ወይ ቤቱ ሲደርስ የሚውጠው ኪኒን ለራሱ ግማሽ ሰአት አልፎበታል ይሆናል" ይላል አንዱ ወጣት። ያሁኑ ወጣትም አሽሙር ይናገራል? ደግነቱ አዛውንቱ አልሰሙትም። እሳቸው አሁን መናገር እንጂ መስማት አይችሉም።

"አሁን የደጃች ዱባለና የባለቤታቸው ያርባጦም ቋንጣ ቀጠሮ እንዴት ነበር አገር ያበጣበጠው?" ይላሉ ተረት ይሁን ታሪክ ይሁን የራሳቸው ፈጠራ ይሁን የማያስታውቅ ነገር ከጥንታዊ ሀሳባቸው እየፈላለጉ።

ማን ይስማቸው ማን አይስማቸው አይታወቅም። ታክሲዋ ካሳንቺስ የሞላ እንደሆነ ትቀጥላለች።

*   *   *

"ፓስተር - ማላላለም - ኡንጌት!" ሲል ይጮህል በሆነች ድምፅ። እቺን ያህል እንኳን ለመጮህ የጉሮሮው ጅማቶች ተግተርትረዋል፤ እንዲሁም የግምባሩ ደም ስሮች።

እኔና አንድ ሰውየ ተከታትለን ገብተን ቁጭ አልን። ሊሞላ ትንሽ ቀርቶታል። ሁለት ሌሎች ሰዎች ተነስተው ሹልክ ብለው ወጡና ምን ነካቸው ብለን ስናያቸው ፈጥነው በህዝቡ መሀል ጠፉ። አንዲት ወፈር ያለች ቀይ ሴትዮ አስቤዛ የሞላ ዘምቢል እግሯ አጠገብ ያስቀመጠች፤ ተመቻችታ ተቀምጣ በሳቅ ትፍለቀለቃለች። ሁኔታዋ የሚገባ ስለሆነ ስሜቴን ለፈገግታ እያመቻቸሁ አየሁዋት።

"ገና ሌሎች ይወጣሉ!" አለችንና ሳቋን ቀጠለች። የሚጢጢው ወያላ ጥሪ የማይታለፍ ኖሮ ምንም ያህል ሳንቆይ ሶስት ጎረምሶች ጓደኛሞች እየተሳሳቁ ገቡ። ሴትዮዋ እንዳለችውም ሁለት ሌሎች ሰዎች ደሞ ተሽቀዳድመው ወጡና እንደቅድሞቹ ጠፉ።

"ይኸውሎታ!" አለችና ሳቋ ባሰባት እኔም ተጋባብኝ፡፡

"እኔ የሞላ ታክሲ ውስጥ ስገባ አንቺ ብቻ ነበርሽ ተሳፋሪ?" አልኳትና፡፡

"አይገርሞትም!" አለችኝ ሁለታችንም በረዥም ሳቅን፡፡

"አራት ግን አልበዛም?" አልኳት

"እኛ ሰው አይደለንም፤ አይገባንም ማለት ነው!" አለችና በሳቅ ፈረሰች፡፡ አቤት የሳቅነው ሳቅ!

መኪናው ሞላ፤ ወያላው ገባ፤ በሩ ተዘጋ፤ ተነሳን፡፡ ሚጢጢ ወያላ ሂሳብ ከአንድ ሰው ተቀብሎ ወደ ሌላ ዘወር ቢል ገና ጉርምስናቸውን ያልጨረሱ አዛውንት ናቸው፡፡

"ትማራለህ?" አሉት፡፡ እግዜር ያሳያችሁ፡፡

"አይ!" አላቸው ባጭሩ

"ተማር'ንጂ እንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም"

"እንግዲህ ስራ ላይ እያዩት እንዴት አርጎ ይማራል?" አለ አንዱ ጎረምሳ

"የማታ ትምህርት አለ እኮ" አሉ አዛውንቱ፤ የጎረምሳውን ብሽቀት ሳያስተውሉ፤ መለገስ ያለባቸውን ከንቱ ባዶ ምክር እየቀጠሉ፡፡

‹‹አሁን ይህ አንድ ፍሬ ልጅ ቀን ሲሰራ ውሎ ማታ ሊማር ይችላል?››

‹‹ያሬድ ማህሌታይን አታይም?"

"ያሬድ ማህሌታይ ወያላ ነበር ማለት ነው?" አላቸው፡፡ ሳይወዱ ዝም አሉ፡፡ ሆ! አዛውንቶቹ እነሱና ደሞ ጉርምስናቸውን ያልጨረሱ አዛውንት ይበቅሉ ጀመር?

* * *

አራት ኪሎ ቆመናል። ልጅነቱን ገና ያልጨረሰው ወያላ "ፒያሳ! ጊዮርጊስ! አውቶቡስ ተራ!" እያለ ይጮሀል። ቻው ተባባልንና ተሳፈርኩ። ፒያሳ ስደርስ ወደ ጊዮርጊስ አቅጣጫ አቆመና በሩን ከፈተልኝ ወያላ።

"ምነው ፒያሳ ጊዮርጊስ ብለ'ኸኝ?"

"እሱ እምቢ አለ ፋዘር!" አለኝ ሾፌሩን እያመለከተ። በእፍረት። ወያላው ከእንዲህ አይነት ሸፍጠኛ ሰው ጋር ሳይወድ መሸፈጡ ያሳፈረው መሰለኝና ነገሩ አሳዝኖኝ ልወርድ ስል አንዱ ቆጣ ያለ ሰውዬ በምልክት አትውረድ አለኝ። ቁጭ አልኩ።

"ውረዱ እንጂ ፒያሳ ወራጆች" አለ ሾፌር መስታወት ሽርተት አድርጎ።

"ጊዮርጊስ ነን" አለ ቁጡው ሰውዬ።

"ቀጥታ አውቶቡስ ተራ ነው 'ምንሄደው"

"ጊዮርጊስ አድርሰ'ኸን ነው 'ምትሄደው እንዲያ ብለህ ነው ያሳፈርከን"

"እኔ?"

"ወያላህ። ያው ናችሁ ለኛ"

"አንተ ልጅ ጊዮርጊስ እንዳታሳፍርብኝ ስልህ?"

"ውሸታም! ፒያሳ - ጊዮርጊስ - አውቶቡስ ተራ እያለ ሲጮህ በተከፈተው መስኮትህ ትሰማ ነበር። ይልቅ አሁን ወደ ጊዮርጊስ! እኮ ፈጠን!"

"ቀስ ብዬ!" እያለ መስኮቷ አፍራ ተንሸራተተችና ተዘጋች።

ጊዮርጊስ ስንወርድ ፈረሰኛውን ተሳለምነው።

መስከረም 29/ ጥቅምት 6 ቀን 1987

# ሞትና ህይወት

እንግዲህ በግራ ጎንህ ተነስተህ ሊሆን ይችላል፤ ብቻ ባዲሳባ መንገዶች ስትዘዋወር፤ እግረመንገድህን ሬሳ ያጋጥምሀል።

ድንግጥ! ካልዋሹ በስተቀር ሰው ድንገት ሬሳ ሲያይ መደንገጡ ይቀራል? ትቆምና እጅ ነስተህ እያሳለፍከው፤ ውስጥህ ያለው አላርፍ ባይ ከንቱ ክሮችን ይፈትላል፦ "አሁን እስኪ ማንነቱን ለማላውቀው ሬሳ እጅ መንሳት። አያውቅ እሱ እንደሆነ። ግድ የለው!"

"ሟችን መሰለህ የምንቀብረው?" ይላሉ እመት መሰለች፤ በድሮ ትውስታ ሲናገሩ "የሟችን ቤተዘመድ ነው'ንጂ። ሟችማ ምን አለበት? አንዴ ተሰናብቷል። የቀብርና የለቅሶ ጣጣ የቋሚ ነው"

ሌላ የሀሳብ ወይም የትዝታ ክር ትፈትላለህ፤ ፊታይዋን እንጃ'ንጂ "ከንጉስ ከሙሽራ ከሬሳ ማንኛው ነው ትልቅ?" ይላሉ መምሬ በለጠ፤ አቶ ዳምጠው ላይ እያፈጠጡ

"በላ ንጉስ ነዋ ከነሰራዊቱ" ይላሉ አቶ ዳምጠው አቦ ሰጡኝ ይቀናኝ ይሆናል ብለው።

"ተሳሳትኩ" ይላሉ መምሬ በለጠ፤ ድምፃቸው ውስጥ ምራቅ ከላይ ታች እየተነሰነሰ (በተጨባጭ ጭራ እንዳይገዙ በዛሬ ዋጋ ጭራዋ ከፈረስዋ እኩል ሆናለች። ይህን ጉቶ መሳይ ጥጃ ጭራ እንዳይዙ ደግሞ

ኤድያልኝ!) "ልንገርህ አድምጠኝ አገሩ የሰው አገር ከሆነ ንጉሱ ከነሰራዊቱና ሙሽራው ከነአጀቡ መንገድ ላይ ቢገናኙ ንጉስ ቆሞ ሙሽራን ያሳልፋል፡፡ ሙሽራ በሰርጉ ቀን ንጉስ ነውና፡፡ ንጉስ ከነሰራዊቱ ሬሳ ከነቀባሪዎቹ መንገድ ላይ ቢገናኙ ንጉስ ቆሞ ሬሳን እጅ ነስቶ ያሳልፈዋል፡፡ ሙሽራና ሬሳ ቢገናኙም ሙሽራ እጅ ነስቶ ያሳልፈዋል፡፡ እጅ ያስነሳል ሬሳ፡፡ ያንተ ሬሳ ሳይቀር እጅ ያስነሳል ታያለህ ምናለ በለኝ!"

"እንግዲህ እኔን ለቀቅ! ያለኔ የሚያሸንፉት የላቸውም እንዴ ሆ!" ብርሌ ብድግ!

"የኔታ" ይላል ፀደቀ የብርሌውን አንገት እየጨበጠ እና ላለመሳቅ እየተጠነቀቀ "እንግዲህ መንገድ ላይ የሙሽራ ሬሳና የንጉስ ሬሳ ቢገናኙ ማን ማንን ሊያሳልፍ ነው?"

"ሁለቱም አንተን ያሳልፉሀል፣ ፀደቀ ሆይ፣ አንተ የሬሳ ሬሳ ነህና፡፡ ለዚህም ነው የፀደከው፡፡" እድሜ ለፀደቀ፣ ሳቅ ይጀምራል፣ ንትርኩ ያበቃል፡፡

* * *

ሞት ያስፈራል፡፡ የማይፈሩት ካሉም ያከብሩታል፡፡ በየበከላቸው ግን ችላ የማይሉት ከባድ ነገር መሆኑን ገልፀዋል ወይም ሊሸሽጉት ሞክረዋል፡፡ አንዱ ዘዴ በቃላት ስልጣን የሞትን መልክ መቀየር ነው፡፡ ለምን እንደሚቀየር ቀያሪዎቹ ያውቁ ይሆናል፡፡ ውስጥ ግን ፍርሀት ሳይኖርበት አይቀርም፤ ጥቂት ምሳሌዎች እነሆ፡-

- "ሞቱ" ከማለት "አቶ እገሌ አረፉ" እንላለን (ከሚሞቱ ቢያርፉ ይሻለናል፡፡)
- "ሞተ" ከማለት "እገሌ በጦር ሜዳ ተሰዋ" እንላለን፡፡
- "ተገደለ" ከማለት "አብዮታዊ እርምጃ ተወሰደበት" እንላለን፡፡
- "የመሰለህን እንደመሰለህ ግደል" ከማለት "ነፃ እርምጃ ውሰድ" እንላለን፡፡

- "ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ" ሲባል ምን ማለት ነው? ከዚህ ዓለም ላይ በእሳት ሰረገላ ወይም በራእይ ወይም በምትሀት ሳይሆን በሞት ነው የተለዩት ለማለት ነው? ባይገርማችሁ ደሞ እኚህ ሰው ራሳቸው ቀደም ሲል "ከእናታቸው ከወይዘሮ አገሊትና ከአባታቸው አቶ አገሌ ተወለዱ" ተብሏል። እንግዲህ ከናታቸውና ከአባታቸው ካልሆነ ካክስታቸውና ካጐታቸው ሊወለዱ ኖሯል? ወይስ ከትውልድ መንደራቸው ውጪ ተወልደው እንዳይሆን ያሳስብ ኖሯል? ወይስ እንዲያው ማንም ያላሰበበት የቃላት መንጠባጠብ ይሆን?
- ጥንትም ይሁን ዛሬ ቤተ-መቅደስ ውስጥ ለአማልክት እንስሳ አይታረድላቸውም "መስዋት ይቀርብላቸዋል"
- "እንዴት እኛ ካገር ተለይተን በፋሲካ ቀን ደም ሳናፈስ እንውላለን?" ብላ ባልዋን በግ ያስገዛችው ሴትዮ ጊዜው ሲደርስ ቢላውን እያቀበለችው፣ "እረደው" አትልም "ባርከው" ነው የምትለው። ባልየው "በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ብሎ ይባርከዋል፤ እጅ ቢላዋ ጉሮሮ ግን አይናገሩም እንጂ ነገሩ ሌላ ነው። ሆድን ያህል እዳ ይዘን ላለመብላት አንችልምና ነው'ንጂ አሁን በግ ሆነ ዶሮ የሚታረዱ ነገሮች ነበሩ? እንዲያው ሲያዩዋቸው ደስ የሚሉ እንደኛው መኖር የሚወዱ ፍጡራን!

ሚስቲቱ ዳቦውንም ቢሆን "ቁረሰው" አትለውም ባኋን "ባርከው" ነው የምትለው።

እህልም እንደ እንስሳ ነብስ አለው። ማሳ ሙሉ ስንዴ እሸት በነፋስ ሲጫወት ያየ ሰው እህል ነብስ እንዳለውና ደስታን እንደሚያውቅ ይመለከታል። የአደይ አበባ ሜዳስ?

*　　*　　*

ህይወትን የምንወዳትን ያህል ሞትን እንጠላዋለን እንፈራዋለን። ደሞስ ምነው አንፈራው? እንዲያውስ ሞትን ያልፈራን ሌላ እንፈራ ኖሯል? ሞኝ ነን እኛ?

የሰው ልጅ ሞትን ምን ያህል እንደሚፈራና እንደሚሸሽ እንደሚመክት ለመገንዘብ የሚከተሉትን አንድ በአንድ እናስብባቸው፡- ጠበል መድሀኒት አዋቂ ሀኪም መድሀኒት ቤት የመድሀኒት ቅመማ ፋብሪካዎች የህክምና ትምህርት ዩኒቨስርቲ የመቃብር ሀውልቶች ሀይማኖቶች ወዘተ...

"እንቅልፍና ሞት ወንድማማቾች ናቸው" ይልሀል የምትሰለች ባህላዊ ትላንትናዊ ድምፅ፡፡ "ሞት ነው ታናሽ" ለዚህ ነው ጨክኖ የሚወስደን፡፡ እንቅልፍ ግን ታላቅ ነው አይጨክንም፣ ወሰድ መለስ ያረገናል... ደግሞ እንቅልፍ ተኝተን እረፍትና ጠቅላላ መታደስ ከየት ይሆን የሚመጣልን? ወይ እንቅልፍን ያህል በረከት!

"ሞት ግን ምላጭ ነው" ልንገርህ በቃሉ አይፀናም፡፡ አንድ የጥንት ሰው ነበሩ ጤናም እድሜም እንጀራም አብዝቶ የሰጣቸው፡፡ ይሰጣል'ኮ በል ሲለው እንዲህ አይምሰልህ፡፡ እኚህ የጥንት ሰው ታዲያ ቅምያታችን ሊሆኑ ይችላሉ መቼስ - ሁለት ቀን በበቅሎ ተጉዘው ቀብረው ሲመለሱ ሞትን መንገድ ላይ አገኙት፡፡

"እንደው ስሞት አፈር ስሆንልህ፣ እንዲት ነገር ብቻ ልለምንህ" አሉት፡፡

"ይለምኑኝ" አላቸው

"መቼስ መምጣትህ አይቀርም፡፡ ግን እንደ ሌሎች ድንገት ሳይታሰብ አትድረስብኝ፡፡ አስቀድመህ አስጠንቅቀኝ"

"እሺ" አላቸውና ተለያዩ፡፡ አመታት አለፉ፣ ሰውየው እርጅና እየተጫጫናቸው ሲሄድ ለቀብር ሲሉ ከአንድ ቀን በላይ የበቅሎ ጉዞ መሄዱን ተዉት፡፡ አገር እንደሆነ ያውቃል አይቀየማቸው፡፡ ሌሎች አመታት ሲያልፉ በበቅሎ መጓዙን ትተው ወንዝ መሻገሩን ትተው ቅርብ ካሉ መንደሮች ሰው ሲሞት ብቻ በምርኩዝም በደጋፊም እየሄዱ ሲቀብሩ ኖሩ፡፡

አንድ ቀን እዚያው እመንደራቸው ሰው ሞቶ ቀብረው እንደተመለሱ እንደማመም አላቸውና አልጋቸው ላይ ተጋደሙ፡፡

ሞት መጣና ታዲያ "እንሂድ፣ ጊዜው ደረሰ" አላቸው

"ምነው ልመጣ ስል አስጠነቅቅሀለሁ ብለኸኝ?" አሉት፡፡

"ኧረ ደጋግሜ ነው ያስጠነቀቅኩዎት!"

"ምላጭ ውሸታም!"

"ያስተውሉ እንጅ" አላቸው "ጎደኛው አቶ ሞት፡፡" "የሞተ ቀብረው በተመለሱ ቁጥር መቃብሪቱ ወደዚህ እየቀረበች አልሄደችም ነበር? ይኸው ዛሬ እዚህ ደረሰች፡፡ እንሂድ (አለ ወያላ)" አለና በታክሲው ወሰዳቸው፡፡

* * *

እኛ የሰው ልጆች ሞትን መጥላትና መሸሸ ብቻ ሳይሆን፣ ሞትን እንክደዋለን ወይም ልንክደው እንሞክራለን፡፡

አብዛኛው ሀይማኖት ጭብጡ ሞት እንደ እንቅልፍ ጊዜያዊ ነው ጊዜው ቢረዝምም ይላል፡፡ ከእንቅልፍ እንደመንቃት ሁሉ፣ ከሞትም እንነሳለን ስለዚህ አይዞን! ይህ እናት ስትሞትብን ወይ ልጅ ሲሞትብን የሚሰማን የአንጀታችን መበጠስና ቆስሎ መቅረት በኋላ ከሙታን ስንነሳ እንደ ህልም ቀላል ነገር ሆኖ ይታየናል፡፡ አይዞን! ተነፋፍቆ! የሚቀር የለም ሮሚዮና ጁሊየትም ይገናኛሉ፡፡ ለዘለአለምም አይለያዩም፡፡

እንግዲህ ይህ እምነት ነው በየዘመኑ በየአገሩ በየቋንቋውና ባህሉ ቤተመቅደሶችን እንዲያ አንቀጥቅጦና ለብዙ ብዙ ትውልድ እንዲተላለፍ አጠንክሮ የሰራቸው፡፡ የአማልክቱ ቤቶች ናቸውና፡፡ አማልክቱ ሞትን የሚያሸንፉት ለሰው ልጅ ትንሳኤን የሚሰጡት! ከቶ ለአማልክቱ ምን ያደርግላቸዋል? ከዙርያው ሁሉ የላቀና የተዋበ ቤት ይሰራላቸዋል፣ መዝሙር ይዘመርላቸዋል፣ እጣን ይታጠንላቸዋል፣ መስዋት ይቀርብላቸዋል፣ በእሳት ይከበርላቸዋል፣ ፀሎት ይፀለይላቸዋል፡፡ መች

እነሳቸው? እነሰን እላሉ፡፡ ከዚህም ጋር ብዙ ሰዎች ከወለድንና ዘር ተክተን ካለፍን ያልሞትን ያህል ነው፤ ሞትን አሸነፍነው ማለት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ እንደምንም ብለህ ካለፍክ በኋላ ስምህን የሚያስጠራ መውለድ፡፡ እኔ እንኳ ባልኖር ስሜ ይኑር፡፡ ስሜ ስለሆነ እኔን የሆነ ያህል ነው፤ ብለው የሚያምኑ ይመስላል ሲያወሩ፡፡ እውነት ያምኑ ይሆን? ባያምኑማ ምን ያናግራቸዋል? ባላምንም እንኳን ያመንኩ ልምሰል ብለው ይሆን እንዴ ምናልባት ከዜሮ ሳይሻል አይቀርም በሚል? ከንቱ! የሀሳብ ክር መንተቱ፡፡

እዚህ ከንቱነት ውስጥ መፋታት ይኖራል፡፡ "እቺ ሚስትህ አልወልድ አለች፡፡ ግዴለህም መሀን ናት ፍታት" ወይም - "ልጃችንን አፋቱልን እንጂ፡፡ ይህን ሁሉ አመታት ልጅ ሳይወለድ፡፡ እኛ እንደሆነ በዘራችን መሀን የለብንም" ወይም - "ተወው ልጁ ባታገባ ይቆይልህ፡፡ እስከዚያው አንድ ወልደህ አምጣልኝ እኔ አሳድጋለሁ፡፡ ወላድ የሆነች ፀሀይ የመሰለች የጨዋ ልጅ አውቃለሁ፡፡"

ሞትን ለመካድ ሌላ መንገድ ተሞክሯል፡፡ መውለድ ሳይሆንላቸው ቀርቶ ወይም ችላ ብለውት በትውልድ ፋንታ ስማቸውን በታሪክ አስመዝግበው ለማለፍ የሚሹ አልታጡም፡፡ አንዳንዶቹ ሲቀበሩ እንዲህ ይባልላቸዋል፡፡ "እሳቸው ዛሬ አፈር ብናለብሳቸውም ቅሉ ስማቸው ከመቃብር በላይ ህያው ሆኖ ለዘለአለም ይኖራል፡፡"

መቃብራቸው እንግዲህ ከእብነ በረድ የተሰራ ሳይሆን አይቀርም የመላእክቱ ዝምተኛ ህውልት የሚያንገርብበበት፡፡ ከጎኑ ጥቅስ ይኖራል - "ታሪክ ያለው አይሞትም"

እንግዲህ ትልልቆቹ መቃብሮች ብዙ ናቸው፡፡ እነሱ የሚኗት ታሪክ ደሞ መኖርዋን እንጃ፡፡

ኗሪ ፍጡር ሁሉ አይነተኛ ተግባሩ ወደደም ጠላም ራስን ጠብቆ ማኖር እና ጊዜው ሳያመልጥ ወልዶ ማሳደግ ነው፡፡ እኛ የወላጆቻችን ምትክ እንደመሆናችን ልጆቻችን የኛ ምትክ ናቸው - ልጆቻቸው የነሱ ምትክ፡፡ በሌሎች ፍጡራንም እንደዚሁ እንስሳትም እፅዋትም፡፡

ይሄ እየተኩ ማለፍ፣ እየተኩ ማለፍያው ያንኑ ማመላለስ፣ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ የት እንደሚያደርስ ወይስ እንዴት እንደተነሳ የሚያውቅ የለም። እኔ አውቃለሁ የሚለውን ሰው ‹እንኳን ደስ አለህ› እንለዋለን።

እኛ ፍጡራን የምናውቀው ግን በራብ እየተነዳን እንደምንበላና በፍትወት እየተጠለፍን እንደምንወልድ ነው። አብዛኞቻችን ሲርበን ሳንበላ አንችልም፣ ወንድና ሴት ሆነን ስንፈ.ቃቀድ ደሞ ሳንተቃቀፍ አንችልም። ግዴታ ነው ያስገድዱናል ለየምክንያታቸው።

ደሞ በጥበባቸው ውስጥ ውስጡን ሲጠቀሙብን ላይ ላዩን ያስደስቱናል። ሽፈ.ጡን ስንል ለልፋ.ታችን ይከፍሉናል። ሲርበን መብላትም እጅጉን በጣሙን ይጣፍጠናል ስንፈ.ቃቀድ መተቃቀፍ እጅግ በጣም ሲበዛ እስኪያስፈነጥዝ ይጥመናል። ኧረ በዚች በህይወታችን እንዳለን የማያረካን ሌላ ነገር ሊኖር እንዴት ይችላል? ይችላል እንጂ፣ ለነሱ ምን ይሳናቸዋል? ቆይተን ስናየው ደሞ ለካ ከልጃችን ጋር መጫወትን የመሰለ ፀጋ የለም። ይህን ሁሉ የመብላትም የመተቃቀፍም ሲሳይ የሚሰጡን እንግዲህ እንድንኖርላቸውና እንድንወልድላቸው እንድናሳድግላቸው ነው። ያቺ ህይወት ራሷን እየተካች እንድታልፍላቸው። ግና ያ ዝንታለም ተመላላሽ ድግግሞሽ መተካካት ለነሱ ምን ያረግላቸው ይሆን? ደሞስ እነሱ ማናቸው? ወይም እሱ ምንድን ይሆን?

ይህ የህይወት ድግግሞሽ ምስጢሩ ሊገባን አልቻለም እንጂ፣ የራሳችን ኑሮ ግን እጅግ ሲበዛ ጥሞናል። እኛ ራሳችን አንድዬ ነን አንደጋገምም፣ አንዴ ብቻ ነው የምንኖረው። ስለዚህ እቺኑ ጣፋጭ ኑሮ ለማራዘም ከሞት መሸሽ ማምለጥ ነው ዋናው ስራችን። ማምለጥ እስኪያቅተን ድረስ ማምለጥ።

ህንድ ከኛ ከመራቁ ብዛት ተረቶቹን ከታሪኮቹ መለየት ያቅተናል። ዳሩ ታሪክንና ተረትን ምን ለየው? አንድ ጎልማሳ ህንድ አንድ እግሩ ቆስሎበት በምርኩዝ ሲሄድ አመታት አለፉ። አንድ ቀን ትልቅ በአል ሆነና አምላክየው እንደኛ ቁልቢ ገብርኤል ስእለት ሰሚ ምኞት ፈፃሚ

የሚሉት ኖሮ፣ ይሄ ጎልማሳ ወደዚያ አምላክ ቤተ መቅደስ አቀና። አንድ እግሩን እየጎተተ ሲሄድ ፈጣሪውን ያማርር ነበር። "በምሮጥበትና በምዘልበት እድሜዬ እንዲህ በቁስል ያሰርከኝ ምን አጥፍቼ ይሆን? ኧረ ተው ዛሬንኳ በቃህ በለኝ ኧረ ተው! ሳይጎድልህ ለምን ንፉግ ትሆናለህ?" እንደምንም ደረሰና ጥቂት ለማረፍ ቤተ መቅደስ ካብ ተደግፎ ተቀመጠ። ብዙም ሳይቆይ ከሩቅ አንዲት ሴትዮ ራሷ ላይ ቅርጫት ተሸክማ ትመጣለች። ቀረብ ስትል ከቅርጫቱ በላይ የአንድ ሰውዬ እራስ ይታያል። ስትደርስ ሴትዮዋ ቅርጫቱን ከራሷ አወረደችና ጎረምሳው አጠገብ አኖረችው።

እውስጡ እጅም እግርም የሌላቸው ሰውዬ ተቀምጠዋል። ከሰላምታው በኋላ ጎልማሳው አላስችል አለውና እንዲህ አላቸው "ይቅርታ ያድርጉልኝና፣ እኔ እኮ በዚህ በአንድ እግሬ ቁስል በጣም ሳማርር ነበር። እንደዚህ እንደርስዎ አይቀጡት ቅጣት ከመሸከም መሞት አይሻልም?"

"ተው'ንጂ ጎበዝ" አሉት አዛውንቱ ራሳቸውን እየነቀነቁ። "ምነው ሞትን ትጠራብኛለህ? እኔ ለራሴ መኖሩን በጣም ወድጄዋለሁ። ይቺን ውድ ሚስቴን ከማስቸገሬ በስተቀር ገና ለብዙ ብዙ አመታት መኖር ምኞቴ ነው። ለብዙ ረዥም አመታት!››

ህይወትንስ እየጣመችን ብንኖር ነበር። ዳሩ ምን ይሆናል፤ አሟልክቱ በሉ ሲላቸው ድግግሞሹን ይተዉትና ተገላቢጦሽ ይልኩብናል። ለምሳሌ እንደሚከተለው። አንዲት ሴትዮ ነበሩ ረዥም እድሜ ሰጣቸውና፤ ዘንግቶ ወይም አውቆ ሆን ብሎ ጤናም እንጀራም ይነፍጋቸዋል። የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም የእንጀራ ፍርፋሪ ይጥልላቸዋል በሰው እጅ። እሱማ እጁን አያነሳም። ሰዎች ናቸው እጆቹ። ያቺ እህል ጉሮሮ ትዘጋለች'ንጂ አታጠግብ። በዚያ ላይ የለከፋቸው በሽታ ስቃዮች ቁጥርም መጠንም የላቸው!

"አምላኬ፤ ኧረ እባክህን ግደለኝ! ኧረ በተሰቀለው ልጅህ ሞቱን ስጠኝ!" ይላሉ አይሰጥም እሱ ደሞ።

ውድ አንባቢ ሆይ ፀሀፊ በበኩሉ "ውድ አንባቢ ሆይ" ሲል፤ አንባቢ በበኩሉ ቢጠራጠርና ቢጠነቀቅ ሳይሻል አይቀርም ለክፋም ለማንኛውም።

ውድ አንባቢ ሆይ በኪዳነ ምህረት እለት ለመንገድ ዳር ለማኝ ከኪስህ አስር ሳንቲም መዝዘህ እንደምትሰጠው ሁሉ (አባ መስጠት ነህና) እኚህ አሮጊት ደሞ ሞታቸውን ሲለምኑ ሞት ከኪስህ መዘዝ አርገህ ልትሰጣቸው ብትችል ኖሮ ትሰጣቸዋለህ ወይስ አትሰጣቸውም? እኮ ለምን?

ክቡር አንባቢ ሆይ! ፀሀፊ "እኮ ለምን?" ብሎ ሲጠይቅ፤ አንባቢ እንደመስቀለኛ ጥያቄ ቆጥሮት ዝም ቢለው ሳይሻል አይቀርም ይሆናል እንላለን።

እኮ የምን ዝምታ ነው እሱ? እኛ ከፈለግን ዝምታንም እንደመልስ ልንቆጥረው እንችላለን። ለለማኝ አስር ሳንቲም ቢሰጡ፤ ሳንቲሟን ጋልበው በለማኝና በድህነት መሀል ጥልቅ አሉ መፅሀፉም "ምፅዋት ስጡ" ይላል። ለኚህ አሮጊት ግን ሞትን ቢሰጡ ሞትን ጋልበው በሰውና በፈጣሪው መሀከል ጥልቅ አሉ አአ! ሞኝ ካልሆኑ በፈጣሪ ጉዳይ ጥልቅ አይሉም።

ጥያቄውን ጠለቅ እናረገዋለን። ጠንቀቅ ኦንባቢ ሆይ። እኚህ ሞታቸውን የሚለምኑ ሴትዮ የማንም ስም የለሽ ተራ አሮጊት እንዳይመስሉህ። እንያ በልጅነትህ ብዙውን ደስታህን የሰጡህ ጎረቤታችሁ እማማ 'ማዋይሽ ናቸው'ኮ። ዳቦና ሻዩስ፤ እንጀራና ወጡስ፣ ቂጣውስ ቆሎውስ? ያን ሁሉ ሲሰጡ የነበሩ እማማ 'ማዋይሽ ናቸውኮ። አጥፍተህ እንኳን በተገረፍክ ቁጥር ዘለው ገብተው ተሟሙተው ነጥቀው ወስደውህ የሚያባብሉህ። "አሁንስ ምን አረጋለሁ፤ ለዚህ ልጅ ከረሜላ ልግዛለት እንጂ" ሲሉ ድምፃቸው ትዝ አይልህም ያውም እራስህን እያሻሹህ።

(አንባቢ እያመነታ ይሁን እየለገመ ዝም ይላል)

ማመንታትም እንደ መልስ ሊቆጠር ይችላል። በዚህ በኩል ለ'ማማ 'ማዋይሽ አዘንክላቸው በዚያ በኩል ፈጣሪውን ፈራ'ኸው ምክንያቱም

ሞቷን ስከለክላት አንተን ምን ጥልቅ አረገህ? ቢልህስ እያፌጠጠብህ? ፈጣሪው ሳያይና በኋላም ሳያውቅ ለማማ ማዋይሽ ሞታቸውን ጣል አርገህላቸው ማለፍ ቢቻል ኖሮ ግን!

ጥያቄውን አሁንም ጠለቅ እናደርገዋለን። ሴጣን ጆሮው ይደፈንና፤ እኚህ ሞታቸውን የሚለምኑት ሴትዮ የማንም አሮጊት ሳይሆኑ፤ እኚያ ወልደው በፍቅር ያሳደጉህ እናትህ እራሳቸው ቢሆኑስ?

በትክክል መልሰህል ድንቅ አንባቢ ሆይ። ፀሀፊ (ድንቅ አንባቢ ሆይ) ብሎ ካለ አንባቢ እጥፍ ድርብ ጥንቃቄ ሳያሻው አይቀርም። ለማንኛውም አንባቢ ምን አለ? "እናትማ እራሷ ፈጣሪ አይደለችም'ንዴ? በልጅነቴ ጠምቶኛል ውሀ ስጠኝ ስትለኝ ደስ እያለኝ ሮጥ ብዬ እንደማጠጣት ሁሉ፤ በአሁን ሰአት በቅቶኛል ሞትን ስጠኝ ካለች፤ እና ሞቷን ልሰጣት ከቻልኩ፤ ማመንታትም አይኖርም። እማዬ ስትልከኝ እንዴት አልላክም? እማዬ ነቻ! እንግዲያውስ እኔ እያለሁላት ሌላውን ምን ያስለምናታል?"

ያኛው ፈጣሪ ቢያየኝም ይቅር ይበለኝና

* * *

እንግዲህ ዘመናዊ ሀኪም አለ። ማዳንም መግደልም በእጁ ነው። ወሰን ቢቸግረውም እንኳን በሽተኛ ያመጡለታል። ገዳይ በሽታ ነው የያዘው። በሽታው ደሞ ሲያይል ሲከፋ ስለቆየ እንግዲህ ለበሽተኛው የቀረው እስኪሞት መሰቃየትና ሞቴን አቅርብልኝ እያለ መፀለይ ብቻ ነው። ሲሰቃይ ሰአታት ያልፉና ትንሽ ፋታ ሲያገኝም ያለፈውን ህመም በማስታወስ የሚመጣውን በመፍራት ፋታዋ ትባክንበታለች። በሽተኛው አሁኑኑ ቢሞት ደስታውን አይችለውም። "ዶክተርዬ እንደው ለነብስዎ ይሆኖታል፤ ከዚህ ስቃይ ገላግሉኝ። ማንም ሳያውቅ የምትገድል ኪኒና ወይ መርፌ አትኖሮትም? አፈር ስሆን!"

ዶክተር እሺ አይልም። በህይወትና በሞት መካከል በሚካሄደው የሁልጊዜ ጦርነት ውስጥ ሀኪሙ ራሱን የሚቆጥረው በህይወት ወገን

እንደተሰለፈ ተራ ወታደር አድርጎ ነው። ወታደሩ በተሰማራበት ቦታ ባለው ሀይል መዋጋት እንጂ፤ አሁን እናጥቃ አሁን እንሽሽ የሚለው ውሳኔ ውስጥ እሱ የለበትም። ስለዚህ ህይወትን በማራዘም ስቃይን ማራዘም ነው - ስቃይ ኖረም አልኖረም እሱን አይመለከተውም።

ሌሎች ሀኪሞች ጋር ጨርሻለሁ። አንተጋ የመጣሁት ሞትን እንድትሰጠኝ ነው። ያውም ባንዳፍታ ኡ! ስቃዬን ባወቅከው!

እንግዲህ ዶክተርየው ምን ይዋጠው? ወይም ከዚያ የባሰ ቢሆንስ ኖሮ? እሱ'ንደሆን አያልቅበት (በሽተኛው ኀደኛው ሳይሆን ወላጅ እናቱ ራሳቸው ቢሆኑስ? ዶክተሩን አያርገን ብለን እናልፋለን።)

ታዲያ'ኮ ህዝቦች ባስተሳሰብ በባህል ይለያያሉና ነው እንጂ፤ የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ብናስብባቸው ሌላ ነው።

ጥንት ሮማውያን ሀብታሞች በመሆናቸው ምክንያት ራሳቸውን መግደል ይፈልጋሉ እንበል። መብታቸው ነው። አንዳንዶቹማ የቅርብ ወላጆቻቸውን ለስንብት እራት ይጋብዙዋቸዋል። ተበልቶ ተጠጥቶ ሲያበቃ፤ በወላጆቻቸው ተከበው እየተጫወቱ የሞቀ ባኞ ውስጥ ይገቡና ሁለቱም እጃቸው ዘንድ ከመዳፋቸው አጠገብ ያሉትን የደም ስሮች በጩቤ ይበጥሳሉ። ባኞው ሙቅ መሆኑ ደሙ እንዳይረጋና እንደ ልብ ፈስሶ ሰላም ያለው ሞት እንዲሞቱ ነው። ወይን ጠጅ እየጠጡ፤ ወግ እያወጉ፤ ቀልድ እየቀለዱ፤ "እንግዲህ ደህና ሁኑ ወላጆቼ!" ብለው ተሰናብቶ መሞት

እንዲሁም በጥንታዊት ጃፓን አንድ ሰው በሆነ ምክንያት ራሱን መግደል ቢፈልግ፤ ወዳጆቹን ይጠሩና ከበውት ይቀመጣሉ። የሚያምነውን ኀደኛውን "እንዲሸኘው" ይመርጠዋል። ቀራጡ ሰው ተከቦ እንደቀራጡ ሰው እንደተቀመጠ፤ ሰይፉ ይመዘዝና በሁለት ቀራጥ የእጅ እንቅስቃሴዎች የገዛ ሆድ'ቃውን ይዘረግፋል

አጠገቡ የቆመው ታማኝ ጓደኛውም በሰይፍ አንገቱን ይቀላዋል፡፡ "ይሸኘዋል፡፡"

በበለፀጉት አገሮች በአሁኑ ሰአት ራስን ስለመግደል መብት እና ለመሞትም በታማኝ ወዳጅ ስለመታገዝ ወይም ስለመረዳት የምር ውይይቶች በብዛት እየተካሄዱ ነው፡፡

እንግዲህ የኛ ሰው "ሞቴን አሳምርልኝ" ሲል በጣም አሪፍ ፀሎት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ወይንስ ያጠራጥራል ውድ ክቡር ድንቅ አንባቢ ሆይ?

እንግዲህማ በነቢያቱ ሰቆቃዊ ድምፅ እንቀጥል እንጂ የቀረን እሱ ብቻ ስለሆነ፡፡ እነሆ በምድሪቱ ገፅ ላይ የሚመላለስ ሁሉ የሆዱ ተገዥ ሆኖ ተገኝቷልና፡፡ እነሆ፤ ሳር ምድር ላይ በቀለ፤ በግ እርቦኛል ብሎ ሳርን በላው በግ ሞት መሆኑ ለሳር ተመለከተ፡፡ እነሆ፤ ሰው ነብር ገደለ ገንዘብ ያገኝበታል ሽልምልም ቆዳውን ለመሸጥ ሲል ነበር የገደለው፡፡ ሰው ሞት መሆኑ ለነብር ታየ፡፡ እነሆ፤ ኧረ ለሌላው ፍጡር ሞት ያልሆነ ፍጡር ይፈልግ ተባለ፡፡ ሲፈልግ ሲፈልግ ሲፈልግ - ሳር ሆኖ ተገኘ እነሆ፡፡

ለአረንጓዴነትህ በገናዬን እቃኛለሁ፡፡ ወኢትበልእ አንተ መኑሂ፡፡ (አንተ ማንንም አትበላምና) አለ ይበልኡኮ ለከ (አንተን ይበሉሀል እንጂ) ወአንተ ኢትነቅንቅ (አንተ አትንቀሳቀስምና) ወኢትገብር ለሀጢአት (ሀጢአትንም አትሰራምና) ወአንጎድጎዶ ሞት ከመነጎድጓድ መወፅአ፡፡

አስጠሊታም ሞት እየተንጎራደደ እንዲህ አለ፤ "የሳርን ነገር እንኳን ግዶለም፤ ውስጡን የመሬቱን ማን አውቆት? እኔ ዋና አመጣጤ የሰው ልጅን ልሽልም በገዳይነቱ፤ የሳርን እምቢታ የሚክሰኝ እሱ በመሆኑ፡፡ እነሆ፡፡

"እንስሳት ሁሉ በታዘዙኝና ፈጥነው እርስ በርስ ቢገዳደሉም፤ ሆድ እስከገፋቸው ድረስ ብቻ ነውና፡፡ የሰው ልጅ ግን የኔ ምርጥ አገልጋይዋ!

ስንት አይነት አገዳደል ይችላል! እስቲ ጥቂቶቹን ላውሳቸው ልደስትባቸው! እነሆ፡፡

ሀ/ ዋነኛው ገዳይ ታማኝ የሞት አገልጋይ አዳኝ ነው፡፡ ይሄ ሲርበው ለመብላት የሚያድነው ሳይሆን ያኛው አዳኝ ለመግደል ሲል ብቻ ወጥቶ የሚያድነው፡፡ የማይበላቸውን ወፎች ለመፍጀት ታጥቆ የሚወጣው አዳኝ፡፡ ያ ምናልባት እርስ በርስ ሲገናኝ ‹‹ታዲያስ፣ አደን እንዴት ነው? ስንት ገደልክ?" የሚባባለው፡፡ እነሆ የኔ ሀቀኛ ባለሟል እሱ ነው፡፡

ለ/ አለ ሌላ አይነት አዳኝ፡፡ አደን ሲወጣ በንፁህ ልብ የተቻለውን ብዛት ያህል ገድሎ ለመመለስ ሳይሆን ገድሎ ቆዳውን ወይም ቀንዱን ወይ ላባውን ወይ ሌላውን በገበያ ሸጦ ገንዘብ ለማግኘት ታጥቆ የሚወጣ አዳኝ አለ፡፡ የዝሆን ጥርስ በገበያ ብዙ ዋጋ ስለሚያወጣ፣ የዝሆን አገሮች ዝሆን ማደንን በህግ ቢከለክሉም፣ ወንበዴው በድብቅ እየገደለ በስውር ወደ ገበያ መላኩ አልቀረም፡፡ እንዴትስ ይቀራል? አንዱ የኔ የሞት መገልገያ መሳሪያዬ ገንዘብ አይደለምን? የአውራሪስ ዝርያም ታድኖ ሊያልቅ ብዙም አልቀረውም ቀንዱ በጣም ብዙ ገንዘብ ያስገኛል፡፡ ኧረ ሰው በቃኘን አያውቅምና ነው'ንጂ እሱስ በአጭር ጊዜ ያከብራል፡፡ ዙሪያውን ከተገላመጡ በኋላ በሹክሹክታ የሚነገር ከነዚያ በርካታ የቅርብ ምስራቅ ባለፀጋዎች አንዳንዶቹ እርጅና መጥቶባቸው በሴት ልጅ ገላ መደሰቱ እያቃታቸው ሲሄዱ፣ የአውራሪስ ቀንድ ተፈጭቶ ዱቄቱ በፈሳሽ ብጤ ነገር ተበጥብጦ ከዋጡት ለጥቂት ሰአታት ያህል ተመልሰው በጉርምስና መንፈስና ገላ ሴቲቱን ያቅፏታል ይባላል፡፡ ማቀፍስ ቢሉ ማቀፍ ነው! የተሟጠጠለት ተስፋ የቀረጠ ማቀፍ ይልቅ ሂድና አንድ አምስት አውራሪስ ግደል፡፡

በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ሀብታም ሴቶች ባርኔጣ ማድረግ ያዘወትሩ ነበር፡፡ ባርኔጣው ላይ ተሰክቶ በጣም የሚያምርባቸው ደሞ የአንድ አይነት የሞቃት አገሮች ወፍ ላባ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የዚያች ወፍ ላባ ብዙ ዋጋ ያወጣ ነበር፡፡ ወፊቱን አድነው አድነው ከምድረ ገፅ አጠፏት. . . ወዘተ ይላል መፅሐፉ፡፡

መ/ ሌላው ገዳይ የሞት አገልጋይ ጦረኛ ነው፡፡ ለሰዎች ትልቁ የጦር ሜዳ ለኔ ለሞት ሰፊው የሲሳይ አውድማ፡፡ ውእቱ በለው! ያው ነው፡፡ በጦረኛይቱ ሮማ ዘመን በአንድ ወቅት እንዲህ ነበር፡፡ ጦር ሜዳ ላይ ከሰማኒያ ሺ በላይ ጠላት የፊጀ የሮማ ጄኔራል ከሮማ ከተማ ዋና መንገዶች አንዲቱ ላይ ታላቅ እብነበረድ ቅስት ይገነባለትና እሱና ድል አድራጊው ሰራዊት በሰልፍ በዚያ ቅስት ስር ያልፋሉ ምርኮዋቸውን ለተመልካች እያሳዩ፡፡ እንቁልልጭ! (ቅስቱ መታሰቢያ ፅሁፍ ላይ ያልተነገረ እነሆ እዚያ ጦር ሜዳ ላይ ስንት ሮማዊ እንደረገፈ፡፡)

ጄንጅስካን፣ ናፖሊዮን፣ ቴዎድሮስ፣ ሂትለር፣ ወዘተ! እውቅ የሞት ባለሙያዎች! ታማኝ መሳሪያዎች፡፡ የሂሮሺማ ናጋሳኪው ደምሳሽ ቴክኖሎጂው ጌታ ሀሪ ትሩማን ይምጣልኝ!

ሰ/ የሆነስ ሆነና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንም ያልተጠቀሱትንም የሞት ባለስልጣኖች የሚበልጣቸው የሚያስከነዳቸው ማነው? ሲዊ ፓስተር ነው፡፡ ምክንያቱም ከሁሉም በላይ ብዙ ለሆኑ ፍጡራን የመሞቻቸው የመጥፊያቸው ምክንያት ፓስተር ሆኖ ቀይቷል፡፡ በሺ በመቶ ሺ አይደለም የፓስተር አገዳደል በሚሊዮናት በቢሊዮናት ነው፡፡ ያ ሁሉ ጀርም ይመስክር፡፡

ከነዘር ማንዘሩ የጠፋው አቤት መብዛቱ!

በፓስተር መንገድ ሄዶ ፔንሲሊኒን ያገኘው አሌክሳንደር ፍሌሚኒግ አለ፡፡ ሰር አሌክሳንደር ሆይ በርሶ የተነሳ ስንቱ የጀርምና የባክቴሪያ ቫይረስ ዝርያ ጠፋ! አይ የርስዎና የፓስተር የተከታዮቻችሁ የህይወት ጠባቂነት! ድንቂም ህይወት ተጠበቀች! አንድ ሰው በዳነ ቁጥር ስንት ሚሊዮን ጀርም ስንት ቢሊዮን ቫይረስ ሞተ! የህይወት ሰራዊት ፊትአውራሪ ናቸው ቢባልላችሁ ለካ እናንተስ በስውር ሳይታወቃችሁ የሞት የጦር አዛዥ ኖራችኋል! እንግዲህ ምን እናርግላችሁ? እኛ ሰው አይደለን ለሰው እናደላለን የሰው ነብስና የጀርም ነብስ አይበላለጥም - በቁጥር ካልሆነ በስተቀር፡፡ ተባለ'ንዴ?! ጌታቸው አቶ ሞት እኮ እንዲህ

በሳቸው ቤት አዲስ ነገር ለኛ ለሰው ልጆች መንገራቸው ይሆናል። እንደ መርዶ አይነት። ይልቅ ለገዛ ራሳቸው መርዶ እንንገራቸው።

ከጌታ ኢየሱስ አምስት መቶ አመት ቀድሞ በህንድ አገር ጌታ ቡድሀ ተወልዶ ብርሀንን ከማምጣቱ በፊት ለአያሌ መቶ አመታት እየታመነ የነበረውና አሁንም የሚታመነው የሂንዱ ሀይማኖት እንዲህ ይላል።

ይቺን ኑሮ ስኖራት ቆይቻለሁ ንጉስ ሆኜም ይሁን ለማኝ ሆኜም ይሁን ትንሽ ሆኜም ይሁን ዝሆን ሆኜም ይሁን ምንም አይነት ፍጡር ሆኜ ይሁን ---- ስኖራት ቆይቼ ማብቃቷ ነው። ነብሴ ከዚያ ከስጋ ትወጣለች። ሞትኩ ይባላል ተኛሁ እንደሚባለው። ነብሲቱ ቆይታ ቆይታ እንደገና ትወለዳለች። ነብሲቱ ያው እሷ እንደሆነች፣ መወለዷ ላይ ግን ንጉስ፣ ለማኝ፣ ዝሆን ወይም ማንኛው ፍጡር ሆና ልትወለድ ትችላለች። ትኖር ትኖርና እንደ አወላለዱ እድሜዋ ሲደርስ መኖር ታበቃለች። ሞተች ይባላል። ቆይታ ቆይታ እንደገና ትወለዳለች። ይሄ እየተመላለሱ መወለድና የልዩ ልዩ ፍጡራንን ኑሮ መኖር ይቀጥላል ይቀጥላል ማለቂያ የለውም።

ነብሴ የሽማኔ መወርወሪያ ይመስል ስጋ ለብሶ በመኖርና ስጋ ሳትለብስ በመቆየት መካከል ትመላለሳለች፣ ትመላለሳለች። ማለቡ እስኪታክት ድረስ ትመላለሳለች እቺ ነብስ እዚች አለም ላይ።

አቤት! እንዲህ ሲታይማ ሞትን የመሰለ ምን ነገር አለ? ዳሩ ምን ያደርጋል? ሞት የለ መኖር ነው ያለው። ደጋግሞ፣ ደጋግሞ ደጋግሞ መኖር መጥኔ!

ጥቅሶች

1/ "ኑሮ ምን እንደሆነ ለማወቅ ያህል በቂ እድሜ የኖረ ሰው ምን ያህል ትልቅ የአዳም ውለታ እንዳለብን ያውቃል። አዳም ነው ለዝርያችን የመጀመሪያው በጎ አድራጊ - ሞትን ወደ አለም ያመጣልን››

ማርክ ትወይን፣

2/ ልደት ስናይ የምንደሰተው ቀብር ስናይ ግን የምናዝነው ለምንድ ነው? ልደቱም ሞቱም የራሳችን ባይሆን ነው"

ማርክ ትወይን፣

3/ "የመሞቻህ ምክንያት መታመምህ ሳይሆን መኖርህ ነው"

ሲኔስ፣

4/ "መኖርማ እንፈልጋለን፣ መኖር የምንቀጥለው ሞትን በመፍራት ሀይል ሆነ እንጂ››

ጆርጅ ኦርዌል፣

5/ "ሰው በዚች ምድር ላይ ዘለአለማዊ ለመሆን አንድ መንገድ ብቻ ነው ያለው፣ ይኸውም ሟች መሆኑን መርሳት"

ዝን ዝርድ፣

6/ "የማይታበል ሀቅ እነሆ ሌሎች ሰዎች ይሞታሉ እኔ ግን ሌላ አይደለሁም፣ ስለዚህ እኔ አልሞትም"

ብላዲሚር ናቦኮቭ፣

/7/ "እንብላ እንጠጣ፣ ነገ መሞታችን ነውና"

ትንቢተ ኢሳይያስ፣

8/ "ያንዲት ቅጠል መርገፍ ለኗሪ ሰው መልእክት ያለው ሹክሹክታ ነው"

የእንግሊዝኛ ምሳሌ፣

9/ "ኑ የተስፋ ቤት የተገነባው ባሸዋ ላይ ነውና ወይን ይዛችሁ ኑ የህይወት ጨርቅ እንደነብስ ስስ ናትና"

ሀፊዝ፣

10/ "ጥያቄው ይኸው ራስን መግደል ከጣጣው መውጪያ ነውን?"

ኤመርሰን፣

11/ "ከህይወታችን መፅሀፍ አንዲቷንም ገፅ ቀደን ማውጣት አንችልም መፅሀፉን ግን እሳት ውስጥ ልንወረውረው እንችላለን።"

ዝርዥ ሳን!

ጥቅምት 13፣ 20፣ 27 ቀን 1987

# ሆድ

ሰውየው ግምበኛ ናቸው። አሁንም በስድሳ አምስት አመታቸው ስራ ውለው ይገባሉ፣ ምስጋና ይድረሰው። ጧት ጧት ከዳዊታቸው አንዱን መዝሙር ሳያነቡ አይወጡም። ሌላ ነገር አያነቡም? ምን ያረግላቸዋል? አንብበው የት ለመድረስ? ከግምበኛነታቸው አያልፉም። እሳቸውም ማለፍ አይፈልጉም ኧረ! መልካም ነው ተመስገን እያሉ ከሰሩ! አንዳንድ እሁድም እንደዚህ ብርሌ ጨብጦ ከሰው ጋር መጫወት ያስችላል ተመስገን፣ ምስጋናህ አይጓደል! (አይናቸውን ወደ ላይ ወርወር ያደርጋሉ፣ ምስጋናይቱን ለመሸኘት)

ምን መሰሎት? እኔ አማኝ ክርስቲያን ነኝ። ይኸው! (ማተባቸውን ያሳያሉ) ሚስቴ ፃድቅ ናት ልሎት እችላለሁ። ይኸውሎት፣ የኔ አልጋ እዚህ የሷ አልጋ እዚያ ነው። ለኔ ብዬም አይደል። ለሷ ብዬ ነው። የፅድቅ መንገዷ ላይ እንቅፋት እንዳልሆንባት። ደሞስ ከእንግዲህ ምን ሊያረግልን? ወልደን ከብደናል፣ ምስጋና ይግባው። ከእንግዲህ ምን ይቀረዋል ሰው? አምላኩን እያመሰገነ ሞቴን አሳምርልኝ ነው እንጂ።

እኛ የሰው ልጆች በሀኪም ትእዛዝም ይሁን በሀይማኖት ትእዛዝም ይሁን በእድሜ ትእዛዝም ይሁን የተውነውን ብንተው፣ ትተን ትተን ብናበቃ፥ መብላት ግን አንተውም እስከ መጨረሻው። ሆድ ነዋ! እኔ በበኩሌ ሆድን አከብረዋለሁ። እታዘዘዋለሁ። ሰው ብላ ቢለኝና ይሉኝታ

ግን ቢከለክለኝ፣ ሆድ አምጣ ካለኝ ይሉኝታን እንደሌለች ያህል ነው የምቆጥራት። ደሞም የለችም። ሆድ ግን እስከ ሞት አብሮኝ ያለ ነው። እንዴ ጌታዬ፣ ፈጣሪኮ እንዴ ፈጥሮ ትቶናል! ሆድ ነው የሚያኖረን።

የሆድ ነገር አይገርሞትም! እኔ አንዳንዴ ግርም ይለኛል። እንዲያው ሲበዛ ይገርመኛል። ጥሬውንስ ብስሉንስ ቂጣውንስ እንጀራውንስ ሽሮውንስ ጎመኑንስ ስጋውንስ፣ ቅልጥሙንስ ዶሮውንስ እንቁላሉንስ፤ ኸረ ስጋ ወደ አጥንት ወደ አይን ወደ ፈገግታ ወደ ደምግባት ወደ ሁለመናችን ይለወጣል።

ይፍረዱኝ እንግዲህ ጌታዬ፣ የኔ ሆድ ከስንትና ስንት እህል ውሀ ይህን የኔን ሰውነት እንዲገነባ ነው። የበላሁትና የሆንኩት'ኮ በምንም አይመሳሰሉም። በሆድ ስልጣን ነው 'ንግዲህ ይህ የሚደረገው። ሆድን ቢያከብሩትና ቢወዱት ቢታዘዙት ሲያንሰው ነው። እኔ ሆዴን እታዘዘዋለሁ፣ እድሜ ለፈጣሪ። አልደብቆት። ፆም ቀን ቢሆንና ሆዴ ስጋ ቢያምረውና ኪሴ ገንዘብ ቢኖረው ሰተት ብዬ ሆቴል ገብቼ ከፍዬ በልቼ አምላኬን እያመሰገንኩ ወደ ስራዬ!

ግን በሰፈሬ ወይም የሚያውቁኝ ሰዎች በሚሄዱበት አላረገውም። ለምን አንዳንዶቹን ላስቀይም፣ አንዳንዶቹንስ ለምን የሀሜት ሀጢያት ውስጥ አስገባቸዋለሁ? ዘወር ማለት እያለ። እኔና ሆዴ ግን "አልሸሹም ዘወር አሉ" እንባባላለን ቀይ ወጣችንን ከነቅልጥሙ እያቀላጠፍን። እኔ ሆዴን ባጠገብኩ ሀጢአት ሰራሁ አልልም። ስንትና ስንት ሀጢአት እያለ ደሞ መብላትም ሀጢአት ሊሆን? መፆም ዕድቅ ይሁን ግን መብላት ሀጢአት መሆን አለበት?

የሆድ ነገር እህል ውሀን መጥራቱ አይቀርም። እኮ ምንድነው እሱ እህል ውሀ? እህል ውሀ ብዙ ጥልቀት ያለው ይመስላል። ለምሳሌ በምንም በምንም አብረው የማይሄዱ የማይመሳሰሉ ወንድና ሴት ተጋብተው ባልና ሚስት ሆነው ለአመታት ተቀራኝተው ሲኖሩ ይታያሉ።

"እነዚህ ሁለቱ እንዴት ሊጋቡ ቻሉ? እንዴትስ ይህን ሁሉ ጊዜ አብረው ሊኖሩ በቁ?" ይላል ሰው እየተገረመ።

"እህል ውሀቸው ባንድነት ታገዘላቸው ነው፡፡ እህል ውሀቸው ሲያልቅ ሁለቱም በየፊናቸው ይሄዳሉ፤ የእንጀራ ገመድ ወደሚጎትታቸው ይሰማራሉ"

አንድ ተጓዥ አንዱን ምድረበዳ አቋርጣለሁ ሲል ውሀ ጥም ቢገድለው፤ እና "ሰውየው ወደዚያ ምን አስኬደው?" ቢባል

"እህል ውሀው ነው" ሲባል ይሆን?

እህል ውሀ ብቻ አይደለም ሆድ ውስጥ የሚገኘው፡፡ ነገርም ይገኛል፡፡

"ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል" ይባላል! "ሆድ ባዶ ይጠላል!" ከዚህም ጋር "ሆድ ካገር ይሰፋል"

ከዚህ ጋር ‹‹የሰው ሆዱን፣ የወፍ ወንዱን የሚያውቅ የለም››

ከዚህ ጋር፤ "መብላቱ ይቅርብህና ልበስ፡፡ የለበስከውን እንጂ የበላኸውን የሚያይብህ የለም" ይሉኝታይቱ ናት ይህን የምትለው፡፡

አንዱ የጠራ ሀበሻ፤ የይሉኝታይቱ ታማኝ ልጅዋ፤ አንዱን ዝርክርክ ጓደኛውን መንገድ አገኘውና ከነዚያ ከፈረደባቸው ሰላምታዎች በኋላ እንዲህ ይለዋል፤

"ምነው አንተን ያህል ሰው ጨምዳዳ ኮት ለብሰህ ትወጣለህ? ለላውንደሪ አላጣህ፡፡ ሽቅርቅር ብለህ መታየት ነው'ንጂ፤ ጠላቶችህን ደስ እንዳይላቸው"

"ኧረ ጠላትም የለኝ ቢኖረኝ ወላጆቼ ናቸው"

"እነሱስ ቢሆኑ ለምን ደስ ይበላቸው?"

እቺ እንግዲህ ጥልቀት ያላት አባባል ናት ወይም ባዶ የቃላት ሽክርክሪት፡፡ ከዚህም ጋር "ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል፡፡" ደግሞ ስለሚያስታውስ ነው አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ግን "ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው" ሳሩን እንዳያጭደው በማሰብም አይደለም ገብቶናል፡፡ ምን ዋጋ አለው? "ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ" ይሉናል፡፡

"እህሀ! ስንቱን በሆዴ ይገፎ" ይላሉ። አሮጊቷ ለምሳ ያስገቡትን እህል ውሀ ማለታቸው አይደለም፤ የታወቀ ነው። "ተው ቻለው ሆዴ!" አለ ዘፋኙ። እሱም እህል ውሀውን ማለቱ አይደለም። ይህም ሁሉ እየሆነ፤ "ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል" ከዚህም ጋር፤ "ሆድና ቂጥ እንዳስለመዱት ነው" ሊሆንም ይችላል፤ ላይሆንም ይችላል። እንደባለገጠመኙ።

ከዚህም ሌላ አንድ የአረብኛ አባባል "ሆድ ሲሞላ ጭንቅላት ባዶ ይሆናል" ይላል። እዚህ ሆነው ሲያዩት ደግሞ "ሆድ በጎመን ቢደልሉት፤ ጉልበት ዳገት ላይ ይለግማል" ብለዋል አበው፤ የሆድንና የጉልበትን ምስጢራዊ ግንኙነት እያስተዋሉ ሳይሆን አይቀርም። እንዲሁም መደምደሚያ ይሆን ዘንድ "ለሆድ ቁርጠት ብላበት፣ ለራስ ምታት ጨህበት" ተብሎ ሊሆን ይችላል።

ይህን ሁሉ ስለሆድ ስናወራ ቆይተን፤ እንዴት ስለ መብላት አልተናገርንም? ሸለጅብስ? "አያ ጅቦ ሳታመህኝ ብላኝ" አለች። አሁን ክፋትዋ ንፋግነትዋ ነው እንጂ፤ ከበላት አልቀረ ቢያመሀኝና ደስ ቢለው ምን ችገራት ነበር? አሉላችሁ ደግሞ አንዳንድ ብልጦች አራዳዎች፤ "ሲበሉት ያሰቡትን አሞራ ስሙን ይሉታል ጅግራ" (ወይኔ ያሞራይቱ ልጅ! መበላት አነሰኝና ደግሞ ጅግራ ነው ብለው ያዋርዱኛል?" ብሎ በተቆጨ ነበር፤ ወኔ የለም እንጂ።) "ውሻ በበላበት ይጮሀል" የማይታበል ሀቅ ይሉሀል ይሀ ነው። በተለይ ውሻው ሰው ከሆነ! "ሲሸም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚለው ሳይንሳዊ እምነት በሶስተኛው አለም በሚያስደነግጥ ፍጥነት ጥልቀት እየተስፋፋ መሆኑን የታመኑ የወሬ ምንጮች ሳይናገሩት ቀርተዋል ጨዋ በመሆናቸው። ከዚህም ጋር "ተሹመው የተሻሩበትና ሸንኮራ የተበላበት ቦታ መቆየት አያስመኝም" ("ለኔ ነው የምትነግረኝ?" ይሉ ነበር ጓድ እንትና ቢኖሩ ስልጣናቸውን ይማረውና!) ይሄ እንዳይበቃን ደግሞ "አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ"

"እኮ ምን ሲደረግ አይጥ በበላ ዳዋ ይመታል? እኔ አባ እምቢ በል ክንዴን ሳልንተራስ?" ብሎ ትጥቅ የሚያነሳ የለም። ድሮ ቀረ!

ሆድና መብላትን ከጠራን፤ ራብና ጥጋብን ለይተን ስንጠራቸው አይሆንልንም ወይም አይዋጥልንም።

"ድሀ ጥጋብ አይችልም" አንዳንዱን ነው ታድያ። እንዲያውም በጣም ጥቂቱ ነው። አሁን ማ ይሙት ለድሀ ስንት ጥጋብ ሰጥተው አይተውት ነው ጥጋብ አይችልም የሚሉት? እንኳን ጥጋብ እራብ እንችላለን!

"ጓዶች፤ አበላል እንደ ደርግ አባል" ተብሎ ተተረተብን'ኮ በገዛ ዘመናችን።

"ሳንጃው ሰው በላ!" "ውሀ በላው" አበላላቸው ይለያያል። መበላት የማይቀርልህ ቢሆን ታዲያ የቱ ቢበላልህ ይሻልህ ነበር?

"ቁረስት ብላ!" አልኩት በሆዬ፤ አፌ ስራ ይዞ ስለነበር

"እንብላ!" ሲባልማ ደስ ይል ነበር ጋባዥ ፓስታ በሹካ እየጠቀለለ ባይሆን ኖሮ። እሱ እየበላ ሰዎች ሲገቡ "እንብላ እንዳልላቸው ያልቅብኛል" የሚል ሰው ቢኖር "ትጨርሱብኛላችሁ" አላለም በሆዳቸው "እኛ ጅብ ነን እንዴ የምንጨርስብህ?" እንዳይሉት በመጠንቀቅ። ያልተጠነቀቀ ቆሞ ወደቀ። እንደሚታረድ በሬ። በሬ ብንጠራ ገበሬ ከተፍ! ጥጋብ ብትሉ "ካልጠገቡ አይዘሉ፤ ካልዘለሉ አይወድቁ ካልወደቁ አይሰበሩ፤ ካልተሰበሩ አይጠገኑ፤ ካልተጠገኑ አይድኑ" ከሁሉ አስቀድሞ ግን "ከፍትፍቱ ፊቱ"

ህዳር 4 ቀን 1987

# የአበላል ስርአት

በዚህ አካሄዳችን ገና ከአገረ ሀበሻ አልወጣንም። መች እንደምንወጣም አናውቅም፣ ምናልባት መንገዱን ካለፍነው በኋላ ብናየው እንጂ እስካሁን እንዳየነው ግን መንገድ ያንዳንድ ታሪክ ሰሪዎች መንገድ ይመስል ጠመዝማዛ ነው። የራሱ ጉዳይ!

ሞት ህይወት ዘር ሆድ ስንል ሰንብተን፣ አሁን ደሞ በዚች የስነ ስርአት ምንጭና መፍሰሻ እንዲሁም መድረሻ በሆነችው በአገረ ሀበሻችን ውስጥ የመብላት ስነ ስርአት እንዴት ነው? በአንባቢ ዘንድ የተስተዋለ፣ የምንጠይቀውም እኛ የምንመልሰውም እኛ ለምን እንጠይቃለን? መልስ ለመፈለግ ለማግኘት ለመስጠት ያመቸን ዘንድ፣ ይልሀል መፅሀፉ።

ገበታ ክቡር ነው፣ እህል ንጉስ ነው፣ ተቀምጠን እያለ ማንም ሰው ቢመጣ በከበሬታ ተነስተን "ኖር!" ብለን እንቀበለዋለን። እህል እየበላን እያለ ግን ማንም ቢመጣ እንብላ እንለዋለን እንጂ አንነሳለትም። ንጉስ እንኳን ቢመጣ ከእህል ላይ አንነሳም። እህል ከንጉስም በላይ ንጉስ ነው። ስለዚህ ገበታ ላይ አንዘፍንም አንቀልድም። እህሉን በክብር እንበላዋለን አብዛኛውን ጊዜ በፀጥታ። ለምንስ እናወራለን? አፋችን ሁለት ስራ ለምን ይያዝ? ደሞ ወሬው የት እንዳይሄድ? በልተን ተመስገን ካልን በኋላ አናወራውም? ያውም ጠላታችን ፊት እያልን እግዜሩ ፈቃዱ ከሆነ።

ምጣዱ ክብ በመሆኑ ሳይሆን አልቀረም እንጀራው ክብ ነው በክብ መሶብም ተዘርግቷል እኛም ከበነዋል፡፡

እኛ አገር ስንበላ አብረን በህብረት ነው፡፡ የጉዞ ወይም የስራ ጠባይ ካላስገደደን በስተቀር አንድ ሰው ብቻውን አይበላም፡፡ ምነው ምን መጣበት? አውሬ ነው'ንዴ ብቻውን የሚበላው? ‹‹ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል›› ነው ከነተረቱ፡፡

አብሮ መብላት ቀላል ነገር አይደለም፡፡ እኔና እርስዎ አብረን በልተናል ማለት ልንተማመን እንችላለን ማለት ነው፡፡ አብሮ መብላት ያስተሳስራል፡፡ አብረን ስንበላ እንግዲህ እመሀላችን ቄስ ካለ ይባርከዋል ቄስ ከሌለም ዲያቆን አልያም በእድሜ የሚበልጠን ወንድ ይባርከዋል አልያም ወጣት ወንድ አልያም ህፃን ወንድ ይባርከዋል፡፡ እንዲያው ልዩ አጋጣሚ ሆኖ ማንም ወንድ ባይኖር በእድሜ የምትበልጣቸው ሴት ትባርከዋለች "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ!" ማንም ባረከው ማን፣ ዋናው ነገር በስሙ መባረኩ ነው፡፡

"አሜን" ካልን በኋላ የባረከው ሰው ከእንጀራው ይቆርስና አንዳንድ ጉርሻ የሚያህል ለያንዳንዳችን ያድለናል፡፡ እሷ እንጀራ ወጥ ሳይነካት አስቀድመን የምንበላት ናት፡፡ ለምን? አይባልም፡፡ ደምብ ነው በቃ፡፡

ከዚያ ወጡ ይወጠወጥና መብላት እንጀምራለን፡፡

"ከፊትህ ብላ!" ይህ ከስነ ምግብ አስርቱ ቃላት አንዱ ነው፡፡

እኛ አገር በህፃንነታችን ነው ከፊታችን እንድንበላ የሚያስተምሩን፡፡ እረስተን ከሰው ፊት ልንቆርስ ስንል፣ እጃችንን በቀስታ መታ ያረጉንና "ከፊትህ ብላ!" ይሉናል፡፡ አንድ ቀን ታዲያ አሳድሩኝ ያለ እንግዳ ከቤተሰብ ጋር እራት ይበላል፡፡ ያራት አመት ልጅም አለች፣ እንግዳ በሀሳብ ተውጦ ይሁን ውቃቢው ገፋፍቶት ይሁን እንጃ፣ እጁን ወደ ልጅቱ ፊት ሰደድ ሲያደርግ እጁን በጣቶቿ ጧ! አደረገችና "ከፊትህ ብላ!" አለችው፡፡ "አፍሬ ቅል አከልኩ" አሉ እማሆይ፣ "ምን ቅል ብቻ? ጥፍሬን አልኩኝ'ጂ" ይቀጥላል፡፡

ሌላ የስነ ምግብ ትእዛዝ በቀኝ እጅህ የምትጠቀልለው ጉርሻ በመጠንም በፍጥነትም ከሌሎች አብረውህ ከሚበሉት እንዳይበልጥ።

እንዴ! አለዚያ ድርሻቸውን ትበላባቸዋለህ፣ ምናልባት'ኮ የቀረበው እህል ለቀረቡት ሰዎች ላይበቃ ይችላል። እንዴ! እህል አቅራቢ የሀብታም ሚስት ባትሆንስ? አብዛኛው ሰው ደሞ ሀብታም አይደለም። የሚበቃ እህል ቢኖረው ነው። ከዚያ በተስፋ ደመናውን አምኖ ማረስና መዝራት አለበት። ወይ ዝናብ ያንሳል ወይ ይበዛል ወይ በልክ ይወርዳል። ከተምችም ከአንበጣም ከወታደርም የጠበቀን እንደሆነ በቸርነቱ፤ ደሞ ለአንድ አመት ስንቅ የሚበቃ እህል ይኖረናል። ስለዚህ የእህል ጥያቄ "እንገብጋቢ" ከሚባሉት ጥያቄዎች ዋነኛው ነው። አበላል ያስተዛዝባል።

አሁን ይሄ የነአያ እገሌ ወንድም ሰው ነው? ጅብ እንኳ እንደዚያ አይበላም። አንዱን የጠገበ ጠብደል እንጀራ በሶስት ጉርሻ ይጨርሰዋል። ማን አብሮት ይበላል? ማንም። ለትዳር እድሜ ሲደርስ ታዲያ ይሄ መጥፎ አበላሉ ሚስት አሳጣው። እንዲያው ቆሞ ሊቀር ሆነ። ማን አባት ልጁን ለጅብ ይድራል? በራብ ልትሞትበት?

"ተው ይሄ አጎራረስ አይበጅም!" ብለው ቢመክሩት ቢገርፉት ሊድን አልቻለም። ጅል'ኮ ምክርም ዱላም አይመልሰውም።

ደግነቱ ሳይደግስ አይጣላም አንድ ብልህ አጎት ሰጥቶታል። እንደ ምንም ፈላልገው ከሩቅ አገር ሚስት አገኙለት። የሰርጉ እለት አጎት ከአጃቢዎች አንዱ ሆነው ሄዱ። ሴት ቤት ሊደርሱ ሲሉ አጎት ሙሽራን እንዲህ ብለው መከሩት

"ሙሽራ ማለት የአንድ ቀን ንጉስ ነው። የሁሉ አይን ያርፍበታል። ስለዚህ አሁን ገብተን ምግብ ሲቀርብልን በትንሹ እየቀረስክ ብላ። የዛሬን ብቻ! አደራህን!" እሺ ብሎአቸው ገቡ። ምግብ ቀረበ።

ሙሽራ ሆይ ታድያ የመጀመሪያውን ጉርሻ ይጠቀልልና አንድ ስምንት መሶብ ያህል ርቀው ወደተቀመጡት አጎቱ እያሳየ "ጋሼዬ እቺን እቺን ታክል ነው 'ምጎርሰው?" ይላቸዋል ጮክ ብሎ። አሁን እንዲህ ይባላል?

እነት ታዲያ ፈገግ እያሉ ራሳቸውን ይነቀንቁና እንዲህ ይሉታል "አይ አንተ! በሰርግህ ቀን እንኳን ቀልድ አትተውም?"

እንዲህ በያይነቱ ይፈጥራል። ከሙሽርየው ጅልነት ያነትየው ብልህነት።

ይህ ከእጦት ምንም ያህል ሳይርቁ መኖር ስለ መብላት ብዙ እንድናስብ ያደርገናል። ስለዚህ ጉዳይም አሪፍ የሆኑ እንደ እንቁ የሚያማምሩ ምሳሌዎችን አስፈጥሮናል። ጥቂቶቹን እነሆ -

1. እንዳዩ መብላት ሆድ ያሰፋል (ደሞ ሆድን ባታሰፋው ይሻላል በምን ትሞላዋለህ?)
2. እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው (በይሉኝታ አገር በዚህ ባለንበት ሰውን መጥመድ ይሉሀል እንዲህ አርጎ)
3. እንጀራ የለም እንጂ በወተት አምገህ ትበላ ነበር (ይሄኔ እኮ ወተቱም የለም)
4. እንጀራን ምን ይጨርሰዋል መጉረስ (ማንንም ጠይቅ)
5. እኛ በአገራችን ዳቦ ፍሪዳችን (አትለኝም! ይላል ተረበኛው)
6. አሞሌ ሲወፍር እወንዝ አውርዳችሁ እጠቡኝ ይላል (አይ አሞሌ በልቶ በልቶ ወፍሮ'ኮ ነው)
7. የሰማዩን ያህል እንጀራ ይስጥህ ቢለው የኮከቡን ያህል በላተኛ አክልበት አለ (እውነቱን! ሆኖም ግን አሜን ቢል አይሻልም ነበር?)
8. ሆዳም ቢሸከም የበላ ይመስለዋል
9. የማይበላ የለም፤ የማይጠግብ ባሰ
10. ሆዴ በጆርባ ቢሆን ገፍቶ ገደል በጣለኝ
11. እንኳን ያበሉኝ ገርፈው ሰደዱኝ (የእድል ጉዳይ ሆኖ ነው እንጂ አሁን ለሱ የሚሆን እህል አጥተው ነው?)
12. የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ
13. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ (እኮ ለምን?)
14. ኩራት እራት ነው (ይሄ እንግዲህ በይሉኝታ አገር ነው እንጂ)

15. እባብ አፈር ያልቅብኛል ብሎ በስስት ይኖራል (የማያልቅ የለምና ይልህ ነበር እባብ ቢሰማ)
16. ና ብላ ሳይሉት ከወጡ አውጡልኝ (በወተት እያማገ አይበላም!)
17. የሆድ ምቀኛ አፍ ነው (በይሉኝታ አገር)
18. የሚጣፍጥ ምግብ ምንድን ነው ቢሉት ሲርብ የበሉት
19. አህያ ተማምሎ ጅብን አወረደ (ስለ መብላት ስናወራ መበላላትም አለ ለካ)

ወደ መሶባችን እንመለስና፣ በልቶ የጠገበ በአፉ ወይም በሆዱ ("ተመስገን!" ይልና መብላት ያበቃል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን እኛ ሳንጠግብ ያልቃል፡፡ "ተመስገን!" ብለን ብዙ ውሀ እንጠጣለን፡፡ "የሚያጠግበው እህል ነው፤ መጥገቡን የሚለካው ግን ውሀ ነው፡፡" ኧረ ጠላስ ቢሆን? እንዲያውስ ጠጅስ ቢሆን? መች እንቻላለን? ይብላኝ ለምድሪቱ ችላ ለምትሸከመው መጥኔ ለአፈሩ፣ አብልቶ ለሚበላን!

አብሮ መብላት መጎራረስን ያመጣል፡፡ ማን ለማን ያጎርሳል? መልሱ ሰፋ ያለ ጥናትና ምርምር ይጠይቃል እስከዚያው ግን "ጉርሻና ፍቅር ሲያስጨንቅ ነው!" ለምን ግን? ጉርሻውስ ለምን ያስጨንቅ? ፍቅሩስ ለምን ያስጨንቅ? (ይሄ ከይሉኝታ አገር ምስጢሮች አንዱ ነው፡፡ ግን የሚያውቁ አይጠፉም ይኸኔ፡፡)

መብላት ካነሳን ዘንዳ ስለ መፆምም በዘረዘርነ፡፡ አብሮ መብላትን ካወሳን ዘንዳ ስለመቀላወጥ አንዳንድ ሳይንሳዊ ሀቅን በሰነዘርነ፡፡ ምን ያረጋል? የትስ ያደርሳል? እንዲያው ለጊዜው ብቻ በዚች ምሳሌ እንደመድማለን "ቀላዋጭ ወጥ ያውቃል"

ደሞ ወጥ በመስራቱ እንዳይመስላችሁ፡፡ ኧረ እሱ እቴ!

ህዳር 11፣ 18 ቀን 1987

# ውርስ

‹‹የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል›› ብለዋል አበው፡፡ እነሱ እንደዚያካሉ ዘንድ እኛ ስለውርስ ልንፅፍ ነው ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ውርስ አይነት አይነት አለው፡፡ በዘር የሚወርስ አለ፡፡ ቅላቴን ከአባቴ ውፍረቴን ከእናቴ ወርሼ ነው እንላለን፡፡

ይሄ አውራሾቹም ሆነ ወራሾቹ ሳናውቅ የሚወረስ ነው፡፡ ከቁጥጥራችን ውጪ አባቴ ቁመት ለኔ ከልክሎ ለታናሽ ወንድሜ ሰጠው ብለን አናስብም፡፡ ንብረትና ቅርስም ከወላጆቻችን እንወርሳለን፡፡ ይሄ አውቀውና ወደው የሚያወርሱን ነው፡፡ ደጃች እገሌ ትርፍ ቤታቸውን ተወረሱ እንላለን፡፡ በግዳቸው፡፡ ይሄ የጠሉት ይወርሳል አይነት ነው የተናቀ ያስረግዛል አይነቱም ሊሆን ይችላል፡፡

በነጃንሆይ ዘመንና ከዚያም በፊት አንዳንድ ሰዎች እንዴት እንዳበዱ ስንጠይቅ ‹‹ስራይ ነው›› ወይም ‹‹መድሀኒት አቅምሰዋቸው? እህታቸው ወይም ወንድማቸው ኧረ የበስመአብ ያለህ ምነው? እርስት እንዳይካፈሉዋቸው፡፡ አንዳንዴ ርስት መጥፎ ነው ሰይጣን ይጠራል፣ ወንድምና እህት ያጋድላል፡፡

ይሄ እንግዲህ በተራ ሰው ደረጃ ነው፡፡ በንጉስ ደረጃ ደግሞ አንዳንዴ ወንድማማች ለአልጋ ለዙፋን ለዘውድ ይጋደላሉ፡፡ እርስ በርስ መጋደላቸው አልበቃ፣ አገር ያጋድላሉ፡፡ አንዱ ድል አድርጎ እስኪነግስ

ብዙ ደም ይፈስሳል፡፡ ትልቅ ችግር በታሪካችን ውስጥ ይህን ችግር ለማስወገድ የተወሰደ እርምጃ ነበር፡፡

አቶ ይልማ ደሬሳ በ፲፱፻፷፱ ኢ.ም ባሳተሙት፤ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ዘመን›› በተባለው መፅሀፍ በገፅ ፲፰-፺፮ እንዲህ ይላል

*በዚህ ዘመን አምባ ግሼ በደብረ ዳሞ ፈንታ ከአልጋ ወራሽ በቀረ ነጋሴዎች ሁሉ የሚጋዙበት አምባ ነበር፡፡ ይህ የነጋሴዎች የግዞት አምባ የሚያስደንቅ ድርጅት በመሆኑና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ልዩ አይነት ነገር ስለነበር የዚህን ዘመን ታሪክ ከመቀጠል አስቀድመን የግዞት አምባን ታሪክ ማተት ባጭሩ አስፈላጊ ነው፡፡*

*የመጀመሪያው የግዞት አምባ ደብረ ዳሞ ነበር፡፡ ነጋሴዎችን ወደ አምባ ማጋዝ የጀመረችው ንግስት ሳባ ነች ሲሉ የፃፉ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው ታሪክ ይህን ዘዴ ለአብርሀና አፅብሀ ይሰጣቸዋል፡፡ በአፈ ታሪክ ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣልን መልአክ ለንጉስ አብርሀ በራእይ ታይቶ ከአልጋ ወራሹ በቀር ሌሎቹን ወንድ ልጆቹን ሁሉ ወደ አምባ ካላጋዛቸው በአገሪቱ ውስጥ ታላቅ ችግር እንደሚነሳና ሌሎች የንጉስ ልጆች ሸፍተው አገሩን እንደሚከፋፈሉትና በንጉስም ላይ አደጋ የሚያመጡ መሆናቸውን ገለፀለት ይባላል፡፡ አፄ አብርሀ በዚህ ራእይ ደንግጦና ተራራውም የሚገኝበትን አገር ለማወቅ ግራ ገብቶት እንደቆየ መልአኩ ደግሞ በራእይ ታይቶት ለዚህ ስራ የሚውል ተራራ በአገሪቱ ውስጥ እንደሚያስፈልግ ተራራውም የሜዳ ፍየሎች በላዩ ላይ እየተራመዱ ወደ ገደል የሚወድቁ መስለው የሚታዩበት አምባ መሆኑን ገለፀለት ይባላል፡፡ በመልአኩ ጥቆማ ተመርቶ ንጉሱ ደብረ ዳሞን መረጠ፡፡*

*የሆነው ሆኖ ከ፰ኛው መቶ ከአፄ አብርሀ ዘመነ መንግስት አንስቶ እስከ ፱፻፹ ኢ.ም ዮዲት የተባለች የፈላሻ ንግስት የጋፋት ወገኖችን ሰራዊት ይዛ የአክሱምን መንግስት አጥፍታ በደብረ ዳሞ ላይ የተጋዙትን የነጋሲ ወገኖች ሁሉ እስከፈጀቻቸው ድረስ ይህ አምባ የነጋሲዎች ማጋዣ ቦታ ሆኖ ቆየ፡፡ ከዮዲት ፍጅት በኋላ ግን የዛጉኤ ነጋሴ ወገኖች*

*በዚህ ዘዴ አልቀጠሉም፡፡ ከ ፲፱ ዘመን በሚበልጥ በዛጉዬ ነገስታት ዘመነ መንግስት ጊዜ ዘዴው ተረስቶ ከቆየ በኋላ አፄ ይኩኖ አምላክ እንደገና የማጋገሪ አምባ ዘዴ ሲጀምር በደብረ ዳሞ ፈንታ አምባ ግሼ ለዚህ ጉዳይ እንደተመረጠ በታሪክ ተነግሯል፡፡ አምባው የተመረጠው ዮዲት ደብረ ዳሞ ላይ ያደረገችው ፍጅት መታሰቢያ ለቤተ መንግስቱ ስለተረሳ ይመስላል፡፡ ቀጥለን እንደምንገልፀው ሁሉ*

*‹‹የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል›› እንደሚባለው ሁሉ በአምባ ግሼ ላይ የተጋዙትም የነጋሲዎች ድል ከ፲፱ አመት በፊት ደብረዳሞ ላይ ከነበሩት ልዩ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ግራኝም ተራውን በዚህ አምባ ላይ የተገኙትን ነጋሴዎች ከፈጀ በኋላ ልማዱ እንደገና ተረስቶ ቆይቶ በ፩ሺ፭፻፴፪ ዓ.ም አፄ ፋሲለደስ እንደገና አድሰውት በበጌምድር የሚገኘውን አምባ ወህኒ የተባለውን የነጋሴዎች ማጋገሪ አደረጉ፡፡ ይህም አምባ እስከ አፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ድረስ ለዚህ ዘዴ ሲያስፈልግ ቆየ፡፡ ይህን የአምባ ወህኒን ንግሳዊ እስር ቤትነት ባነበብኩት ጊዜ በጣም ገረመኝ፡፡ ድንቅ ተረት የሰማሁ ያህል ነበር፡፡ በአፈታሪክ እንደሰማሁት ከሆነ ጦር ሜዳ ውጊያው መሀል ንጉሱ ከተገደለ ወይም ከተማረከ ሰራዊቱ ወዲያው ይበተናል ‹‹አውራውን እንደ አጣ ንብ›› ይባል፡፡ ስለዚህ የጠላት ዋና አላማ ንጉሱን መጣል ይሆናል፡፡ ስለዚህ …*

… ስለዚህ አንዱ ጠቢብ ሊቀመኳስ በሀሳቡ እየጋለበ መጣለት … እኮ ማነ ነው? ሊቀመኳስ … ሊቀመኳስ ለማ ሌላው ንጉስ ነው፡፡ እንዴት ቢባል በውጊያ ሰአት ከመኳንንቱ አንዱ ልክ እንደ ንጉስ ይለብስና የንጉሱን በሚመስል ፈረስ ይቀመጣል፡፡ የኛም ወታደር ሆነ የጠላት፣ እውነተኛው ንጉስ የቱ ነው ሊቀመኳሱ የቱ ነው ለይተው አያውቁም፡፡ ስለዚህ ንጉሱም ቢወድቅ ወይም ሊቀመኳሱም ቢወድቅ ውጊያው ይቀጥላል፡፡ ማለት ንጉሱ ቢወድቅ እንኳ ሰራዊታችን ድል ሊያደርግ ይችላል፡፡ እድሜ ለሊቀመኳስ! (እንግዲህ መተማ ውጊያ ላይ አፄ ዮሀንስ ሊቀመኳስ አልነበራቸውም ማለት ነው? ሊቀመኳስን ያህል ብልሀት ለሳቸው እንደ ፍርሀት ሆኖ ታያቸው ይሆን?)

ይህ የሊቀመኳስ ነገር ታሪካዊ ልቦለድ ለሚፅፍ ደራሲ ብዙ ስሜት ሳይሰጥ አይቀርም፡፡ ትረካው ውስጥ ልብ ለማንጠልጠል ሊያመች ይችላል፡፡ እንዲሁም ለኮመዲ ወይም አስቂኝ ትረካ፡፡ በነገራችን ላይ የአፄ ቴዎድሮስ ሊቀመኳስ ቤል የተባለው የስኮትላንድ ተወላጅ ነበር ማለት ፈረንጅ፡፡ ለዚህ ነው አንተ ያልኩት፡፡ ፈረንጅና መልአክ እሳቸው አይባሉም - እሱ ወይም እሷ ነው፡፡

በነገራችን ላይ የጥንት ንጉሱም እሳቸው አይባልም፡፡ እሱ ነው፡፡ ምክንያቱ አይታወቅም ለምን አስፈለገው ምን ሊያደርግለት? ቤት አይሰራበት፤ ክትፎ አይበላበት፡፡

ሌላው በታሪካችን ውስጥ ያስገረመኝ የአፄ በካፋ ብልሀት ነው፡፡ በጥበብ ለአት የመጣለት ነው ያስታውቃል፡፡

ንጉስ ከህዝቡ ጋር ግል በግል አይገናኝም፡፡ ስለዚህ ህዝቡ በአስተዳደሩ የተከፋ ወይም የተደሰተ ለመሆኑ ንጉስ በቀጥታ ሊያውቅ አይችልም፡፡ ባለሟሎቹ በሚነግሩት መስራት ግድ ይሆንበታል፡፡ ባለሟሎቹ ደግሞ ሹመታቸውን ለመንከባከብና ለማሳደግ ሲሉ ሊዋሹት ይችላሉ፡፡

... ስለዚህ በካፋ ይህን ችግር እንዴት እንደፈታው በሚቀጥለው እንቀጥላለን፡፡ ይሄ የአንባቢን ልብ አንጠልጥሎ መተው ይባላል፡፡ ልብ ሲንጠለጠል ግን እንዴት ይሆን? እንደ ቋንጣ እንደ ጉትቻ እንደ ጭራ? ወይስ እንዴት?

**ህዳር 25 ቀን 1987**

# የአዬ ባካፋ ብልሀት

በልጅነቱ የበካፋ አስተማሪ ዝነኛውን ቅኔ የምንለውን የቃላት ጥበብ የፈጠረው ተዋነይ የተባለው ሊቅ ነበር ይባላል፡፡

ከእለታት አንድ ቀን፤ በዚያን ዘመን ልማድ ተዋነይና ተማሪው አጠገብ ላጠገብ ሆነው ወገባቸውን ሲሞክሩ ወይም ሲፀዳዱ ባዲሳባኛ ቋንቋ!

‹‹ምናለ በለኝ አንድ ቀን ትነግሳለህ፣ ልኡል ሆይ›› አለው መምህሩ በካፋም ታላላቅ ወንድሞች ነበሩትና የመንገስ እድሉ እጅግ የመነመነ መሆኑ በማወቅ ‹‹አይመስለኝም›› ሲል መለሰ፡፡

‹‹እሺ ተወው ጊዜ ያሳየን የለ? ይልቅ ምስራቹን አስቀድሜ ስለነገርኩህ ስትነግስ ምን ትሸልመኛለህ?››

‹‹የፈለከውን››

አመታት አለፉ እግዚአብሄርም በረቂቅ ጥበቡ በካፋን አነገሰው፡፡ ተዋነይም የቀድሞ ተማሪውን የአሁን አዜውን እንኳን ደስ አለህ ይለው ዘንድ ወደ ግቢ ሄደ፡፡ ዘበኞች ግን ተራ ቃላት ጠምጣሚ ደብተራ መስሏቸው መግባት ከለከሉት፡፡

ተዋነይ አሰብ አደረገና ሲያበቃ ትንሽ ብራና ላይ ቅኔ ፅፎ ለንጉሱ ይሰጡለት ዘንድ በትህትና ጠየቀ፡፡ ወሰዱለት፡፡ ሲነበብ እንዲህ ይላል፣

‹‹አትርሳን በካፋ ዘተዋነይን ክልኤገ ከመአለሁ ለአብርሀም አንተወብ እሲቱ እነ›› (ይቅርታ፤ ግእዙን በትክክል አልያዝኩትም) በቃል በቃል ሲተረጎም እንዲህ ነው አሉ፡፡

ሰሙ - "አትርሳ በካፋ የተጫወትነው ሁለታችን

አንተ የአብርሀም አባት ስለመሆንህ፤ እና ሚስቱም እኔ

ወርቁ - "'አትርሳ በካፋ ተዋነይ ነኝ

አንተ ተራ (የአብርሀም አባት ስሙ ታራ ይባላል) እኔ ሳራ (የአብርሀም ሚስት ስሟ ሳራ ነው) የተጫወትነውን

በካፋም እሱና መምህሩ እዳሪ ሲወጡ ወይም ሲፀዳዱ የተባባሉትን አስታውስ፡፡ ተዋነይን እንዲያስገቡት አዘዘ፡፡ በገባው ቃል መሰረትም መምህሩ የፈለገውን ሸለመው፡፡ እንግዲህ ተዋነይ ምንስ ፈለገ? ምንስ ተሸለመ? የነገረኝ ሰው የለም፡፡ የደብር አለቃ አድርጎ ሾመው ይሆን? ወይስ ምን? ገና መልስ ያልተገኘለት ጥያቄ፡፡

አፄ በካፋ ስለ አገዛዙ ህዝቡ ደስ ይበለው ወይስ ደንታ አይኑረው ማወቅ ይፈልግ ነበር፡፡ ጠቢቡ የሰሎሞን የልጅ ..ልጅልጅ.. ልጅ.. ልጅ፤ ‹‹የህዝቡን የልብ ትርታ›› በቀጥታ ይለካ ዘንድ ወደደ፡፡ ስለዚህም የተራ ሰው ልብስ ለብሶ ለብቻው ከቤተመንግስቱ ይወጣና ወደ ልዩ ልዩ ስፍራዎች እየሄደ ከህዝቡ እየተቀላቀለ ስሜታቸውን ይሰልል ነበር፡፡

አሁንም ከእለታት አንድ ቀን በካፋ እንደተራ ዜጋ ሆኖ ብቻውን አንድ ወንዝ ሲሻገር አንድ ሰውዬ ልብስ ሲያጥብ አገኘ፡፡ ከሰላምታ በኋላ በካፋ ‹‹መንገድ አድክሞኛልና እባክዎን ነጠላዬን አብረው ይጠቡልኝ›› አለው፡፡

‹‹እሺ ምን ገዶኝ? ያምጡ›› አለው፡፡ (የድሮ ሀበሻ ሰው አክባሪ እንግዳ ተቀባይ ነዋ!) እያጠበለት እያለ የሰውየውን ስምና መንደሩን የት እንደሆነ በካፋ ካወቀ በኋላ በጨዋታ ጨዋታ

‹‹በካፋ ጥሩ ንጉስ ነው ወይስ መጥፎ?›› ሲል ጠየቀ

‹‹አፄ ባካፋ በጣም ጥሩ ንጉስ ናቸው። ሺ አመት ይንገሱ››

‹‹ይገርምዎታል። እኔ ግን የሰማሁት በጣም የተለየ ነው››

‹‹የጠላት ወሬ ሰምተው ይሆናል››

‹‹ምን የጠላት ወሬ? ኧረ እሱ ከነገሰ ወዲህ ፍትህ ጠፋ፤ የግፍ አገዛዝ ሰፈነ ሲባል ነው 'ምሰማው።››

‹‹ሰውየው! ወሬ ለውጥ ወይ ዝም በል››

‹‹ግፍ እየተሰራ እንዴት ዝም እላለሁ?››

‹‹ግፍ ይሉሀል የደግ ንጉስ ስም ማጥፋት ነው›› ይልና ሰውየው ብድግ ብሎ በካፋን በጥፊና በቡጢ በእርግጫ ካገላበጠው በኋላ ነጠላውን ሳይሰጥ ያባርረዋል።

ከጥቂት ቀን በኋላ የንጉስ ወታደሮች መጡና ያንን ሰውዬ ወደ ቤተመንግስት ወሰዱት።

እና ዙፋን ላይ ማን ተቀምጦ ያያል፤ ወንዙ ጋ የደበደበው ባለጌ ስም አጥፊ! አቤት የደነገጠው መደንገጥ! ካሁን ካሁን አንገቴ ተቆረጠ ሲል በካፋ ፈገግ አለና፣

‹‹ንጉሱን የሚወድ ዜጋ ንጉሱን ቢያገለግል ተገቢ ነው›› አለው። እና ዋና አማካሪው አደረገው ይባላል።

እንደገናም ከእለታት አንድ ቀን በካፋ እንደልማዱ ተራ ሰው መስሎ ሲንዝ በድንገት ታመመና መሬት ላይ ተጋደመ። አንድ ርህሩህ ሰውዬ በዚያ ሲያልፍ አገኘውና ወደ ቤቱ ወስዶ መደብ ላይ አስተኛው። በካፋ በፅና ታመመ። ሰውየው እጅግ የተዋበች ልጅ ነበረችው። እሷም በሽተኛውን በብዙ እንክብካቤና ፍቅር አስታመመችው። እሱም ከሷ ፍቅር ያዘው። ደምብ ነዋ!

መቸም እግዚአብሄር ደግ ነው። በሽተኛው ድኖ ተነሳ ያስታመሙትን ቤተሰብ ከልብ አመስግኗቸው ሄደ።

አሁንም ከጥቂት ቀን በኋላ የንጉስ ወታደሮች መጡና ደጉን ሰውዬና ውቢቷን ልጁን ንጉስ ጠርቷችሁዋል ብለው በክብር አጅበው ወደ ቤተመንግስት ወሰዱዋቸው።

እና ዙፋኑ ላይ ማን ተቀምጦ ያያሉ፤ ያ አስታምመው ያዳኑት ጎረምሳ! ወይ አዬ በካፋ! ንጉሱም ውቢቱን አገባት፣ ፍቅራቸውም ለመለመ ይባላል።

ሌላም ይባላል። ንግስት ሻህራዛድ ‹‹አንድ ሺ ከአንድ ሌሊት›› ውስጥ የምትተርካቸው የአለምን ምናብ ያስገረሙት ተረቶች ውስጥ እንደምናነበው ሀሩን አል-ራሺድ የተባለው ተወዳጁ የባግዳድ ንጉስ ልክ እንደ በካፋ ተራ አረብ እየመሰለ ‹‹የህዝቡን የልብ ትርታ›› ያዳምጥ ነበር። ይኸው እንግዲህ እግዜሩ ጥበቡን ቢሻው ለአይሁድ ንጉስ--- ግን ጥበብ ይስጠው አይስጠው ገና የታወቀ ነገር የለም። ሊሰጠውም ይችላል። ለእሱ ምን ይሳነዋል? ለእኛም የበካፋን ታሪክ በወፍራም ታሪካዊ ልቦለድ አሳምሮ ዕፎ ከሽኖ የሚያስነብበን ወጣት ደራሲ (ወይም ደራሲት) ይሰጠን ይሆናል። ካልሰጠንም .መቸስ ምን እናረጋለን? ተመስገን ብለን ዝም ነው እንጂ። እስከዚያው ግን እግዜሩ ለፈረንጅ ንጉስ ጥበብ እንዳልሰጠው የታወቀ ነው። ደሞ ፈረንጅስ ጥበብ መች ፈለገና? ምን ሊያደርግለት? ሳይንስና ቴክኖሎጂ እያለለት!?

እንግዲህ ከሳይንስ-ቴክኖሎጂ እና ከጥበብ የቱ ይበልጣል? መልስ የሌለው ጥያቄ።

ታህሳስ 2 ቀን 1987

# ተረትና ታሪክ

የሰው ልጅ ንቀት ያበዛል፡፡ አንዳንድ ንቀቶች በልጅነታችን ፈገግ ሲያስብሉን አንዳንድ ንቀቶች ደግሞ መሰረተ-ቢስ ከመሆናቸው የተነሳ የኛን ንቀት ይቀሰቅሱብናል፡፡ እነሱ ከሚንቁት አስር ጊዜ የባሰ እኛ እንንቃቸዋለን፡፡ ላይዋ ንቀት መስሎ ውስጧ ግን ፍርሀት የሆነች አስመሳይም አለች - ለምሳሌ ጎረቤታም ህዝቦች ወይም ነገዶች ሲናናቁ፡፡ ወይም ለምሳሌ ሁለት ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በርስ ሲናናቁ፡፡ የሚከተሉት ንቀቶች የትኛው አይነት እንደሆኑ ትገምቱ ዘንድ ተጋብዛችኋል፡፡ የሀሳብ ጨዋታ ከፈለጋችሁም አንደኛ ንቀት ሁለተኛ ንቀት እያላችሁ ቅደም ተከተል አውጡላቸው፡፡ እኔ የማስፍራቸው በነሲብ ወይም በአቦ ሰጡኝ ቅደም ተከተል ነው፡፡

## 1.

አበው ከፈለጉ በተረት ስለሚጀምሩ፣ እኛም በተረት እንጀምር፡፡ እቺን የፃፉት ሩማ የተባለው እጅግ የተወደደ የጥንት ፋርስ (የዛሬ ኢራን) ገጣሚ ባለቅኔ እና መንፈሳዊ መምህር ነው፡፡ ‹‹የሰዋሰው ሊቁ እና ጀልባ ቀዛፊው›› ትላለች ርእሷ፡፡

አንድ የታወቁ የሰዋሰው ሊቀ ሊቃውንት የሆኑ አዛውንት በጀልባ እየሄዱ እያለ የሚቀዝፈውን ሰውዬ ‹‹ሰዋሰው ታውቃለህ?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡

‹‹ኧረ ድሀ ነኝ አላውቅም፣ ጌታዬ›› ሲል መለሰ ሰውየው፣ ጀልባውን እየቀዘፈ።

‹‹እንግዲያው ወዳጄ ግማሽ እድሜህን የኖርከው በከንቱ ነው›› ብለው አንኳሰሱት። ‹‹አፍሬ ቅል አከልኩ›› አሉ እማሆይ፤ ‹‹ምን ቅል ብቻ? ጥፍሬ ውስጥ ገባሁ እንጂ!›› ቅልዋ ሳትሆን ጀልባዋ ወደ ባህሩ ርቃ ከገባች በኋላ ሀይለኛ አውሎ ንፋስ ተነስቶ ከባድ ማእበል ቀሰቀሰ። በዚህ ጊዜ ጀልባ ቀዛፊው የሰዋሰው ሊቁን አዛውንት እንዲህ ሲል ጠየቃቸው

‹‹ዋና ይችላሉ?››

‹‹ኧረ አልችልም›› ሲሉ መለሱ።

‹‹እንግዲያው ጌታዬ፣ አብዛኛው እድሜዎን የኖሩት በከንቱ ነው።›› የሰዋሰው ሊቁም አፍረው ሳይሆን ፈርተው ቅል አከሉ። (ቅል ስለሚንሳፈፍ!)

## 2.

ከተረት ወደ ታሪክ። አውሮፓውያን በዘመናቸው ‹‹አዲሱን አለም›› (ማለትም አሜሪካን፣ አውስትሪያ፣ ኒውዝላንድ፣) እስያን እና አፍሪካን ቅኝ አገሮች ያደርጉዋቸዋል በሚከተለው ቅኝት ወይም ቅደም ተከተል ወይም ልት።

ሀ/ መርከበኞች፡- ከነሱ በፊት የነበሩት መርከበኞች የሄዱበትን በካርታ (ማፕ) ማጥናት እና እድልና ነፋስን እየለመኑ እና በከዋክብት እየተመሩ በመሄድ እነዚህን አገሮች ያገኙዋቸዋል። ለምሳሌ ማጄላን የተባለው ፖርቹጋላዊ የመርከብ ካፒቴን አፍሪካን ዞሮ ወደ ህንድ አገር መንገድ ቀየሰ። ኢጣሊያናዊው ካፒቴን ኮሎምቦስ ወደ ህንድ አዲስ መንገድ የቀየሰ እየመሰለው አሜሪካን አገኘ።

ለ/ ተጓገኞች፡- እነዚያን አዲስ የተገኙትን አገሮች እየተዘዋወሩ ያጠኑዋቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ ስለላ እንደ ማለት ነው፡፡ እነሱ ግን (ብዙዎቹ) የሰው ልጅን የእውቀት አድማስ እያሰፉ መሄዳቸውን ነው የሚያዩት፡፡

መ/ ሚሲዮናውያን፡- ለነዚህ አገሮች ህዝቦች ወንጌል ሊሰብኩላቸው ይሄዳሉ፡፡ ቋንቋቸውን፣ ታሪካቸውን፣ ባህላቸውን ያጠናሉ፡፡ በሌላ መልኩ አሁንም ስለላ እየተካሄደ ነው፡፡ ተጓገኞቹ አገሩን እንደሰለሉ ሁሉ፣ ሚሲዮኖች ደሞ ህዝቡን ይሰልላሉ፡፡ እነሱ ግን (ብዙዎቹ) የነዚህን እህዛብ ነብሳት ከዘላለም ጥፋት ወደ ዘላለም ህይወት መምራታቸው ነው፡፡

ሰ/ የጦር ሰራዊት፡- ከነሙሉ ዘመናዊ ትጥቁ ይመጣና አገሮቹን ይወራቸዋል (እኔስ ምን አልኩ? የተጓገኞቹም የሚሲዮኖቹም ስራ ባንድ መልኩ ስለላ ነው ብያለሁ፡፡ ወይስ አላልኩም? ብያለሁ 'ንጂ ይኸው አሁንም ደገምኩት) ሆነም የሚሲዮናውያንም ነብስ የማዳን ሉሳቸው እየነዳቸው በፓስፊክ ውቅያኖስ ወደሚገኙ ወደ ሀዋዪ ደሴቶች ገሰገሱ፡፡ ሀዋዪ ገነት ሆና ተገኘች፡፡ መልከ መልካም የሆኑትና መዋኘት መደገስ እና ግብረ-ስጋ በጣም የሚወዱትና የሚያዘወትሩት፡፡ የሀዋዪ ሰዎች እንደሌላው ህዝብ አይለፉም፡፡ የምን በግንባርህ ወዝ መብላት ነው እሱ? ኮኮናት የሚባለው ረገኛቸም ዛፉቸው ወተትና ስጋ ያለው ፍሬውን አመቱን ሙሉ እንደልብ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ላይ አሳው በገፍ ይሰገራል፡፡ ረሀብ ወይም ችግር የሚባል ነገር በሀዋዪ አይታወቅም፡፡ ችግር ስለሌለ ወንጀልም የለም፡፡ ሌላ ቀርቶ ሴቶቹ ሲወልዱ ምጥ አያውቁም፤ ጊዜው ሲደርስ መውሰድ ብቻ ነው፡፡ ያለምጥ'ኮ ልጅሽን በጣር በህመም ትወልጃለሽ የተባለውን አልሰሙም'ንዴ?

ሆነም፤ ሚሲዮናውያኑም ለሀዋዪ ሰዎች መፅሀፍ ቅዱስን አስተማሩዋቸው፡፡ ሴቶቹም ሀጢያተኞች መሆናቸውንና በምጥ መውሰድ የተፈረደባቸውም መሆኑን አመኑ፡፡ ክርስቲያን ሆኑ፡፡

ከዚያም ወዲህ የሀዋዪ ሴቶች እንደሌላው አለም ክርስቲያን ሴቶች በምጥ በጣር መውለዱን ቻሉበት። እድሜና ዕድቅ ለሚሲዮናውያን ይድረሳቸውና፤ የሀዋዪ ሴቶች ልጅ ወግ ደረሳቸው። ምጥ።

ሚሲዮናውያን ምንጊዜም የእግዚአብሄር ወኪል ነን ባይ ናቸውና። እሱን ወክለው መጥተው የሀዋዪን ህዝብ ከገነት አባረሩት። (እነዚህ ሚሲዮናውያን ምን በደሉኝና ነው አሁን እንዲህ የወረድኩባቸው? እግዜር ይቅር ይበለኝ)

## 3.

ከታሪክ ወደ ቀልድ። አሁንም ንቀት። ንቀታዊ ቀልድ።

ሀ/ የዛሬ እንግሊዞች አብዛኛዎቹ ገላቸውን ይታጠባሉ። ከሁለት ወይም ከሶስት መቶ አመት በፊት ዴንማርክን ጎብኝቶ የተመለሰ እንግሊዛዊ ግን ስለ ዴንማርክ ሰዎች እንዲህ ሲል ፅፏል፤ ‹‹ሴታ ሴት ህዝቦች ናቸው፣ በየሳምንቱ ገላቸውን ይታጠባሉ።››

ለ/ አሁንም እንግሊዛዊ ንቀት። እቺኛዋን ስናነብ፤ በነሱ አቆጣጠር በሺ 86 ዊሊያም ዘ ኮንከረር የሚሉት ፈረንሳዊ እንግሊዝን እንደወረረ እያስታወስን። እና እስከ ዛሬም በእንግሊዝ ዙፋን ላይ የሚቀመጡት ነገስት የዚሁ የፈረንሳዊ ወራሪ ዘሮች መሆናቸውን አበክረን እያስታወስን። በጣም የምወዳት የእንግሊዝ ጉራ እቻት፣ ‹‹በጣም ያሳዝናል እኛ እንግሊዞች ከመበላሸታችን ከመበሳበሳችን የተነሳ ዛሬ አንድ እንግሊዝ ሊደበድብ የሚችለው ሶስት ፈረንሳዮችን ብቻ ሆኗል።›› አለቻ ቡፋ!

## 4.

ከተረት ወደ ምሳሌ

ሀ/ አህያ የለው በቅሎ ይንቃል።

ለ/ በቅሎ አባትህ ማነው? ቢሉት፤ ፈረስ አጎቴ ነው አለ። (አልዋሽም ደሞ)

መ/ ለስምዋ መጠሪያ አንድ ቁና ሰፋች

ረ/ አህያ ሰባ፤ ምን ረባ?

ሰ/ አይን ካላዩበት ግንባር ነው።

ሸ/ አጋዘን ሲጠግብ የነፍጠኛ ጎጆ ይታከካል።

ቀ/ እንዲህ ብታየኝ መስየህ ድህ ያማቶቼ ቤት ባለ ጉልላት።

በ/ የሙት ቀናተኛ ሚስቱን አደራ ይላል።

ተ/ የእውር ቀበጥ ከመሪው ጋር ይጣላል

ቸ/ ቀንዱ ሰማይ ጠቀስ፤ ጭራው ምድር አበስ

ነ/ ቁርበት ምን ያንቋቋሀል ቢሉት ‹‹ባያድለኝ ነው'ንጂ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ›› አለ

ኘ/ ዝምብ ቢሰባሰብ መግላሊት አይከፍትም

አ/ እንኳን ለገንፎ ለሙቅም አልደነግጥ።

ከ/ እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ . . .

## 5.

ከቀልድ ወደ ሀገር ወዳድነት - ፓትሪክ ሄነሪ የተባለ አሜሪካዊ እንዲህ አለ፤ ‹‹እኔ የማዝነው ለሀገሬ ልሞትላት የምችለው አንዴ በመሆኑ ነው።›› አላበዛውም?!

አንድ እለት የማሪያም ማህበር ተደግሶ አንድ አዛውንት ሳይታሰብ ያጫወቱን ታሪክ እነሆ! ድሮ ልጅ አበበ ይባሉ የነበሩት ነጋድራስ አበበ ወልዴ የልእልት ሻሸወርቅ ባል ነበሩ። አንድ ቀን ግብዣ ተጠርተው ሲበሉ ሲጠጡ ውለው ወደ ማታ ላይ ቤተስኪያን ተሳልመው ተመልሰው ወደ በቅሏቸው ሲያመሩ፤ አጃቢ አሽከሮቻቸውን ‹‹ማነው የበላው?›› ብለው ጠየቁዋቸው። አጃቢዎቹ ሳይበሉ ውለው ስለነበረ፤

አንዳቸው ‹‹እኔ እርቦኛል›› አለ።

ነጋድራስም ‹‹እንካ ቅመስ!›› አሉና በያዙት ከዘራ አፉን አበሉት። ሁላችንም ስቀን ካበቃንበኋላ ነበር አንዳችን ‹‹ምስኪን አሽከር!›› ያልነው። ሌሎች ደሞ ‹‹ጥጋብ ይሉሀል ይሄ ነው!›› አሉ። አጭር ዝምታ።

‹‹አገር ቤት የቅኔ ተማሪ ቤት የሆነውን አስታወሰኝ›› አለ አንዱ፤ ማታ ነው። የእራት ሰአት ደርሷል። አንዱ ተማሪ ጮክ ብሎ ‹‹የኔታ ትላንት እራት ያልበላ ማነው ብለዋል›› ሲል ‹‹እኔ ነኝ!›› አለ ተሜ እየተቻኮለ።

‹‹ዛሬም ድገም ተብለሀል!›› ተባለ። ኩምታ ይሉሀል ይሄ ነው። የኔታ ትላንት ማንን እንደቀጡ የረሱ ይመስላል። ቅጣቱ መደገም እንዳለ በት ግን ንዴታቸው ነግሯቸዋል። ‹‹ማን ነው ትላንት እራት ያልበላ?›› ሲባል ዝም ቢል ኖሮስ? እራቱን ይበላ ነበር? (መልስ የሌለው ጥያቄ)

ሌላ ተማሪ። ልመና ሲዞር አንድ ባለ ጉልላት የሀብታም ቤት በሩጋ አንዲት ደርባባ ሴትዮ ቆመዋል።

‹‹በእንተ ስሟ ለማርያም?›› ሲል አዜመ

‹‹ርቦሀል?›› አሉት

‹‹አዎን፤ እሜቴ››

‹‹በጣም ነው የራበህ?››

‹‹በጣም እመቤቴ››

‹‹እንዲያው ሙርሙር አድርጎ ነው የራበህ?››

‹‹አዎን እሜቴ!››

‹‹በል እለፍ እግዜር ይስጥህ››

ተሜስ እግዜር ይሰጠዋል፣ የታወቀ ነው፤ እመቤቱ ግን ምን መሆናቸው ነው? ምናልባት ስለ ርሀብ እየተመራመሩ ይሆን? ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርምና። እንደዚህ ተማሪ ርሀቡ ሲያንከራትተን ግን

ምናልባት ሰው በእንጀራ ብቻ ሊኖር ይችላል እንላለን፡፡ (ደሞ ወጡ ተረስቶ እንዳይመስለን፣ እንጠንቀቅ)፡፡

ጨዋታዎች እርስ በርስ እንደሚጠራሩ የታወቀ ነው፡፡ የሚከተሉት ሁለት ጨዋታዎች እየተሸቀዳደሙ ደርሰውናል፡፡ ሁለቱም ስለ አፄ ቴዎድሮስ ናቸው፡፡ የታወቁ ቢሆኑም ተጠርተዋልና ይስተናገዳሉ፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ቁምጥናን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ቆርጠው ተነሱ፡፡ ቆማጣውን እየሰበሰቡ በጎጆ እያጎሩ በእሳት ያጋዩት ጀመር፡፡ አንዱ ትጋት የሚያበዛ አሽከር ቆማጣዎቹን በጎጆ እንደሰበሰበ፤

‹‹ሞላ ወይ?›› አሉት፡፡

‹‹አንድ ይጎድላል ጃንሆይ›› አለና የጎደለውን አምጥቶ ሊሞላ ሲጣደፍ፤ ‹‹ብል አንተ ግባ›› አሉና አስገብተውት ጎጆው ተለኮሰ፡፡ ምን ነካቸው አፄ? አሽከርየው ይህን ሰው የማቃጠል ስራውን ከመጠን በላይ ሲደሰትበት የታያቸው መስሏቸው ይሆን?

የቋራው መይሳው ካሳ የአፄን ዘውድ ለመድፋት የመጨረሻውን ጦርነት ከራስ ውቤ ጋር ሊገጥሙ ሰራዊታቸው ወደ ሰሜን እየተጓዘ ሳለ፤ ‹‹አቤት›› ስትል ሙሾች አንዲት ሴትዮ፡፡

ያገር አውራ እንደዚህ ሲጠሩት መቆምና አቤቱታ መስማት ግዴታው ነውና መይሳው ካሳም፥ ‹‹አቅርቧት›› ብሎ አዘዘ፡፡ አይ ማዘዙን ሲያውቁበት፤ መይሳውና አንዳንድ ቆራጥ መሪዎች!

አንዲት ጭርጭስ ብለው ያረጁ አሮጊት ቀረቡ፡፡ ከተፈለፈሉ ጥቂት ቀን ብቻ ያለፋቸው ሰባት ጫጩቶች ይዘዋል፡፡ (በቅርጫት ይሁን ባገልግል ይሁን ወይስ በሰፌድ አፈ ታሪካችን ለይቶ አይናገርም፡፡) ከዚህም ጋር ጫጩቶቹ አምስትም ዘጠኝም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዲት ዶሮ ስንት ጫጩት ለማቀፍ ትችላለች? ብለን አስልተን በዚያ ስሌት መሰረት የጫጩቶቹን ቁጥር ለመወሰን እንችላለን፡፡ ቆራጥ ውሳኔ ቢሆን ይመረጣል፡፡ እንደሚከተለው፣ ‹‹ምን ተበደሉ እናቴ?›› ብሎ ጠየቃቸው መይሳው፡፡

‹‹ድሀ ባልቴት ነኝ፤ ጌታዬ። ያለ አንዲት ዶሮና እነዚህ ጫጩቶቿ ሌላ ምንም ንብረት የለኝም። እሷም በዛች ብሎ ያንተ ወታደር አርዶ በላብኝ። እነዚህን ጫጩቶች እንዴት ላሳድጋቸው?››

መይሳው ተቆጣ። አሮጊቷን እየገላመጣቸው ‹‹አንቺ ቆማጢት! የመይሳው ወታደር ዶሮሽን ቢበላ ላንቺ ክብር ነው'ንጂ አቤቱታ የሚያስኬድ ነው፤ ለምን በሬሽን አይበላም?›› አላቸውና ወደ ወታደሮቹ ዞሮ ፈገግ እያለ፤ ‹‹ለመሆኑ ጎበዝ፤ ማናችሁ ነው ዶሮዋን የበላ?››

‹‹እኔ ነኝ ጌታዬ!›› አለ አንዱ

መይሳው ፊት ላይ የነበረው ፈገግታ ጠፍቶ በቁጣ ተተካ። ‹‹ብል እንካ፤ እናትና ልጆችን ማለያየት አይሆንም›› አለና ጫጩቶቹን ለወታደሩ ሰጠው። ወታደሩ ግራ ገብቶት ዝም ሲል ጊዜ ‹‹ብል'ኮ! እነዚህን ጫጩቶች እያየሁ አሁኑኑ ብላቸው››

ወቴ ጫጩቶቹን ጥስቅ አርጎ በላቸው። ያውም ከነላባቸው ከነአጥንታቸው። ‹‹አበው ግን አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል›› የሚሉት እንደ ወቴ አይነቱን ሰው አይደለም መቸም። ንጉሶችም ካለፉ በኋላ እንደ ተረት ናቸውና በተረት ሂደት መሰረት መይሳው ካሳ ባልቴቲቱን ካሳቸው - በቅርቡ የወለደች ላም ከነሴት ጥጃዋ!

‹‹መይሳው ካሳ! ዘመድ ከዘመዱ አደባላቂ!›› የተባለውም ጫጩቶቹን ከናታቸው እንዲቀላቀሉ ያስቻለ ፍርዱን በመስጠቱ ነው ይባላል።

በመጨረሻም የራስ ውቤና የመይሳው ካሳ ሰራዊቶች ሩቅ ለሩቅ እየተያዩ እያለ፤ ቄሶች ታቦት ይዘው ለማስታረቅ እየሞከሩ ስለነበር፤ ራስ ውቤን ለምነው አሁን መለኛውን መይሳውን ሊለምኑት መጡ። ከነሱ ጋር አንድ ስሙን ያልያዝነው (እና ቆሻሻ በመሆኑ ልንይዘው የምንጠየፍ) ደጃች እንቶኔ የምንለው ከሀዲ የይሁዳ ታናሽ ወንድም መጣ። ራስ ውቤ የላኩትን መልክት ለመይሳው ካሳ ነገረ። ሲጨርስ እንዲህ አላቸው፣

‹‹ይህን ያህል ሺ ወታደር አለኝ። ውጊያው ሲጀምር ዞሬ ራስ ውቤን ልውጋልዎት። ስናሸንፍ ምን ይሸልሙኛል?››

በሽልማቱ ተስማሙ። ደጃች እንቶኔም «የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ» ከሚሉት፤ ቢሞቱም ቃላቸውን ከማያጥፉት ጀግኖች አንዱ ነበርና (ድንቄም!) እንዳለው ውጊያው ሲጀመር ዞሮ ራስ ውቤን ወጋቸው። ድል ሆኑ። ከጦርነቱ በኋላ መይሳው ካሳ በተዋዋለው መሰረት ሽልማቱን ለደጃች እንቶኔ ሸለመውና እንዲህ አለው፤ «ስላገለገልከኝ ይሄው ሽልማትህ ከእንግዲህ ለኔ አድረሀል»

«እሺን ጌታዬ»

«ጌታህን የምትክድ በመሆንህ ግን እኔንም ትከደኛለህ ብዬ ስለምጠረጥርህ ለረዥም አመታት መታሰር ሊኖርብህ ነው»

ኩምታ ይሉሀል ይሄ ነው! «ያልጠረጠረ ተመነጠረ» የሚባለው ከዚያን ወዲህ ቢሆን እንዴት አሪፍ ነበር! አይደለም እንዴ። እቺም እራሷን የቻለች ኩምታ ናት ምንም ሚጢጢ ኩምታ ብትሆንም። እዚህ ላይ አበው ምን ሊሉ ይችሉ ነበር? «ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ» ባይገርማችሁ፤ ሰዎችና ወሮች ጨዋታዎች ብቻ ሳይሆኑ ቃላትም ይጠራራሉ። የማያልቅባቸው አበው እዚህ ላይስ ምን ይሉ ነበር? «ከስቴ ቢያዩኝ ድማት ለመነኝ።»

**ጥር 21 / 28 ቀን 1987**

# ጋዜጠኝነት

ጋዜጣ፣ ጋዜጠኛ፣ ጋዜጠኝነት ወዘተ የተጧጧፈ የክርክርና የውይይት የወዘተ ርእስ ሆኗል። (ድሮ ቀረ ሳንሱርን መራገም፤ ሁሉን ጠራርጎ ለሚወስደው ጊዜ ለምንለው ምስጢር ምስጋና ይግባውና! ቢሮክራሲ ግን በምድረ ሀበሻ ጊዜ ባለፈው መጠን እየተስፋፋ እየጎለበተ እየጠለቀ እንደሚሄድ እሙን መሆኑን በአራት ግልባጭ የሚመለከታቸው ክፍሎች እናስታውቃለን። የባለስልጣን ፊርማና ማህተም። የምክትል ባለስልጣን አስተያየት። ፓራፍ ቀን ቁጥር፤ ዝንታለሙን!)

ለታሪክ ፀሀፍት በአክብሮት እጅ ነስተን እንጀምራለን። የጋዜጣ ባህላዊ ወላጆቿ ወይዘሮ ወሬአሩጥ እና አቶ ወሬ አመላላሽ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ በየትም ዘመን በማንኛውም ቋንቋ የገጠር ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ጋዜጠኞች በዚህ ቅር ሊሰኙ ከቻሉ፣ የጋዜጣ ታሪካዊ አባቷ ማን እንደሆነ ስነግራቸው ሊኮሩ ሊኩራሩ ሊንቀባረሩ ይችላሉ። ጀግናው ጁሊየስ ቄሳር በነሱ አቆጣጠር በሀምሳ አምስት አመተ አለም (ወይም ከክርስቶስ ልደት በፊት) ወደ ምክር ቤት (ሴኔት) እየገባ እያለ በጥቂቶች የሴኔት አባላት ነው በጩቤ የተገደለ። የወታደሮቹ ጓደኛና ጣኦት፤ የአገሩ ባለውለታና ታሪክን ከቀረፁዋት ጥቂት ሰዎች አንዱ።

ጁሊየስ ቄሳር ስልጣን የያዘው ለብዙ ትውልዶች በእርስ በርስ ጦርነቶች ስትታመስ የኖረችውን የሮማን አለም ባንድ ጠንካራ ክንድ

ስጥ-ለጥ ካደረጋት በኋላ ስለነበረና የቀድሞ ጠላቶቹን ከልቡ ይቅር ብሎ አገር ግምባታው ውስጥ ከወዳጆቹ እኩል እንዲሳተፉ ፈቅዶላቸውና አስችሏቸውም ስለነበር፣ ነገር ግን ጠላቶቹ እንደሱ ልበ ሰፊ ስላልነበሩ የሴኔት ምክር ቤትን ውይይቶችና ውሳኔዎች በውሸትና በአሉባልታ እያጣመሙ የሱን ስራ ማደናቀፍ ወይም የራሳቸውን ቆዳ ማዋደጃ አድርገዋቸው ስለነበረ እቺ አረፍተ ነገር ማቆሚያ አራት ነጥብ መድረስ ስላቃታት አስናብተናታል፡፡

ሆነም፣ ጁሊየስ ቄሳርም የምክር ቤቱ ውይይቶችና ውሳኔዎች በብዙ ግልባጭ እንዲባዙ አዘዘ፡፡ እስከ ዛሬ ተፅፈው ምክር ቤቱ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚቀመጡት ቃለ ጉባኤዎች ከዛሬ ጀምሮ በሮማ ከተማ ዋና ዋና አደባባዮች እንዲለጠፉና የፈለገ ሰው ሊያነባቸው ወይም ሊያስነብባቸው እንዲችል አስደረገ፡፡ ጋዜጣ የተወለደው ያን ጊዜ ነበር፡፡ ውሸትና አሉባልታን ለማጋለጥና እውነቷን ለመግለጥ፡፡

እንግዲህ የነ ወይዘሮ ወሬ-አሩጥ አይነት ጋዜጠኞችና ጋዜጦችም አሉ፡፡ የሴኔት ቃለ ጉባኤዎች አይነት ጋዜጣ ጋዜጠኛም አለ ጥቂት ይሁን እንጂ፡፡ የሁለቱ ቅልቅል የሆኑም አሉ፡፡ ማን ምን እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡

እየታተመ የሚነበበው አይነት ጋዜጣ የተጀመረውና በአብዛኛውም ያደገው እንግሊዝ አገር ነው፡፡ ከእንግሊዝ አሜሪካ ይቀበላል፡፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለሺዎች ይደርስ የነበረውን በሬዲዮ ለሚሊዮናት፡፡ እዚህ ላይ ቢቢሲ ይጠቀሳል፡፡ በመላው አለም ለአብዛኛው ተራ ሰው ቢቢሲ ተናግሮታል ማለት እውነት ሳይሆን አይቀርም ማለት ነው፡፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጭምር እድገታቸውን ሲቀጥሉ ቴሌቪዥን መጣ፡፡ ከሩቅ ስንጠረጥረው ቲቪ የሲኒማና የሬዲዮ ጠባይን ያጣመረ ይመስላል፡፡ እንግዳ ቤትህ ወይም መኝታ ቤትህ እየተዝናናህ ትቆይና፣ የዜና ሰአት ሲደርስ ቲቪ ስትከፍት የሩዋንዳ ይሁን የሞቃዲሾ ፍጅት ወይም የኖቤል ሽልማት ስነ ስርአት ወለል ብሎ ይታይሀል፡፡ ወይም የፓሪስ ልብስ ፋሽን ብርቅርቅ ትርኢት፡፡

የእናት ሆድ ዝንጉርጉር ብለዋል አበው፡፡ (አበውና ሼክስፒር ምን ያላሉት አለ) ወይዘሮ ጋዜጣም እንደዚሁ፡፡ ለጊዜው ጋዜጣ ሶስት መልክ አላት፡፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፤ አራተኛውና አምስተኛው እንትንኛው መልክ ይጨምሩላት ይሆናል - እድሜ ይስጠን እንጂ፡፡

(የወይዘሮ ጋዜጣ ልጆች ሁለት አይነት ቦታ ተሰማርተው እናሳያችሁ ትእግስታችሁን አውሱን "ወዳጆች ሮማውያን ያገር ልጆች ጆሮዎቻችሁን አውሱኝ" እንዳለ የሼክስፒር ማርክ አንቶኒ፤ የጁሊየስ ቄሳርን ሞት እንደሰማ ፈጥኖ መጥቶ ለህዝቡ ንግግር!)

<u>ቦታ አንድ - ድርጊት አንድ</u>፡፡ የመድረክ ቅብ፡፡ የስጋጃ ቤት የባህል አዳራሽ ሰአሊ መስፍን ሀብተማርያም ቢሰራልኝ፡፡ (የቡና ቤት ስእሎች የሚል አልወጣኝም) መስፍን ሆይ! የይሁዳን መንፈስ ቀባልኝ፡፡ የክህደት መንፈስ፡፡ የይሁዳን መንፈስ ለመላበስ እንችል ዘንድ ያ የምንክደው ሰው መሰቀል የለበትም፤ ግንኙነታቸው አንዱ ሲያምነው ሌላው ሲክደው መሆኑ በቂ ነው፡፡ ከባለ ስሙ ይሁዳ ስሙን የምናውሰው ይሁዳ ይብሳል በክህደቱ ምክንያት፡፡ ኢየሱስ እያወቀ ነው የተከዳው የተያዘው የተሰቀለው፡፡ ይሄ ታሪካችን ግን አምኖ በወደደ እና አፍቅሮ በተሸጠ ሰው ላይ የደረሰ ነው፡፡

እናዝናለን ይህ የእውነት ታሪክ በመሆኑ፡፡ ምነው የሲኒማ ወይም የሲድኒ ሽልደን መፅሀፍ በሆነ! ሰውየው እስካለፉት ጥቂት ወራት ድረስ የውዲቱ የንግስት ኤልሳቤጥ ዳግማዊት መንግስት ውስጥ የኤታማጆር ሹም ነበሩ፡፡ ማእረግና ስራቸውን በደንብ አልመዘገብኩትም፡፡ ሰውነታቸው በለጠብኝ ምስክርነታቸው እንግዲህ እሳቸው የደረሱበት ማእረግና ስልጣን ከደረስክ ወልደሀል አላረጀህም እንጂ አያት ሆነሀል፡፡ እንዲያም ሆኖ ወንድ ነህና ቀዝቀዝ ያለ እድሜ ውስጥ ስትኖር የሴት ትኩስ እድሜ ያጋጥምሀና ያምስሀል ይቆላሀል፡፡ እኚህ ጄኔራል ካንዲት ኮረዳ ጋር ፍትወታዊ ፍቅር ያዛቸው (ማለትም ለእድሜ እኩያ ሚስታቸው ፍቅር አክብሮት እንደተጠበቀ ሆኖ) ከዚህም ጋር የአባታቸውን እድሜ ወንዶች

የሚወዱ ሴቶች አሉ፤ ብዙ ባይሆኑም፡፡ እቺም እንደዚያ አይነት ነች ወይም ለጀነራሉ የሚያሳምን ቃልና ድርጊት አስመሰለች፡፡

"ጉልቻ እንኳን ይጋጫል" እንዲሉ አበውና ሼክስፒር በየቋንቋቸው እኻህ ቀዠቃዣ ጀኔራልና እቺ ትኩስ ኮረዳ አንድ ጎደሎ ነጃሳ ሸቃባ ቀን ተጣሉና ተኳረፉ፡፡

ሶስት ወር ሙሉ ተኳረፉ (አይ እቺ ሶስት ቁጥር ጉልቻዎቹ ጠርተዋት ሳይሆን ይቀራል?) በእኔ እድሜ ሆኜ ልመሰክርላቸውና የንግስቲቱ ጀኔራል በመሆናቸው ሶስት ወር ሙሉ ቻሉት እንጂ ተራ ወንድ ቢሆን ከሶስት ቀን በላይ አይችለውም ጤነኛ ወንድ ከሆነ፡፡

ምንስ ቢሆን እባክህ ልጃችንም ትሁን ወይ እናታችን ወይ እንደዚህ ሰአት ውሽማችን ሴት ልጅን ከሶስት ቀን በላይ እናኮርፋታለን? እንዴ! ለምን ዮዲት ጉዲት ራሷ አትሆንም? እኛ ወንድ አይደለንም እንዴ? ግና ምን ይሆናል? የኛ ወንድነት እንደ ክብሪት ቦግ ብሎ አንድዶ ነዶ ቶሎ የሚጠፋ ሲሆን፤ እንደ ጀኔራል ኤንድ ለማለትም እንቶኔ ወንድነት ግን እንደ ረመጥ አመድ እሳት ለብሶ አድፍጦ ቆይቶ ጊዜው ሲደርስ ወጥቶ የገዛ ራሱን ጭምር የሚፈጅ ነው፡፡

ሴትስ ከእንግሊዝ ጀኔራል በምን ሊተናነስ? እሷም መለያየቱን ሶስት ወር ቻለችው፡፡ በመጨረሻ ግና የሄዋን ልጅ ናትና ቀድማ ተሸነፈች፡፡

እቢሮዋቸው ስልክ ደወለች፡፡ የእንግሊዝ ጀኔራል ዲስፐሊን ድምፅ ሲሰማ ኡፍ እንደሚሉት አመድ ቦነነ ወጣ ወንዱ፡፡ ጀኔራልነቱን አሰናበተ፡፡

የድሮዋቸው ሰዋራ ምግብ ቤት ለእራት ተቃጠሩ፡፡ የለመዷት የጥግ ጠረጴዛቸው ተቀመጡ በደብዛዛው ብርሀን፡፡ እራት እየበሉ ያቺን ሁለቱም የሚወዷትን ወይን ጠጃቸውን ፉት እያሉ የሶስት ወር ናፍቆታቸውን ኩርፊያቸውን እልሀቸውን እና ለሁለት ሶስት ጠርሙስ ወይን ጠጃቸውን እድሜ ተጫወቱ፣ አቤት ተኳርፈው እንደዚህ ሶስት መቶ ሺህ አመት ቆይተው ሲታረቁ ሰአቱ ደስ ማለቱ! መቸ በስጋ እንደሚገናኙ ተቃጠሩ፡፡

ሲሸኟት የመኪናዋን በር ከፍተውት የደህና እደሪ ጉንጯን ስመዋት ተመስገን እያሉ፤ ምናልባትም ውስጡን በገዛ ሙያቸው ሲቀልዱ "ቅዱስ ጊዮርጊስ ለኢንግላንድ!" ብሎ ይሆናል በምናቡ። (ላጤ ምኒልክ ብቻም አይደለም ቅዱስ ጊዮርጊስ የሚዋጋው ለኢንግላንድም ለግሪክም ምናልባትም ለሌሎችም) ምናባችንን ቦግ አርገን ስንከተላቸው ጄኔራል ቤት ሲደርሱ ሚስታቸው ‹‹የተጋበዝክበት ችኮ እራት እንዴት ነበረ?›› ሲሏቸው ‹‹ችኮ ነበረ። ወይን ጠጁ ግን እንደ ካሰኝ ይቆጠራል።››

በነጋታው ያቺ ሁለቱ የተለያዩ እድሜዎች ፍቅረኞቻችን ያሳለፏት የእርቅ ምሽት ንግግራቸው ለካ በድብቅ ተዘጋጅቶ በቆየ ቴፕ ተቀርፆ ኖሮ ጉንጯን ስመው ሲሰናበቷትም በስውር ቪዲዮ እየተቀረፀ ኖሮ አይነቱ ታብሎይድ በሚባል የማማ ወሬአሩጥ መንፈስ የታተመው እለታዊ ጋዜጣ ስሙ ፀያፍ ይሁን አልያዝኩትም እንዳልኳችሁ በነጋታው ያቺ የጄኔራሉ ምሽት በመላው ለንደን ተነበበች። እኛም ዘንድ ደረሰች። ይሁዳይቱ ለአንድ ይሁን ለሁለት ሚሊዮን ነው ጄኔራሉን የሸጠችው። እሱም ወዲያውኑ የስንብት ደብዳቤውን ለመከላከያ ሚኒስትሩ ፃፈ።

<u>ቦታ ሁለት - ድርጊት ሁለት</u>። በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዘመን ማለቂያ ላይ የወይዘሮ ልጅ-ጋዜጣ ተራ የወሬ ተቀባይና አሰራጭ የሲኒማ ሪፖርተር ጋዜጣ መስሎ መጥቶ የወሎ ረሀብን (ተሳስተውም መስሏቸው እያወቁም ለግል ጥቅማቸው ለቡፋ ባዶ የአክብሮት ፊኛቸው ባለስልጣኖቹ ደብቀውት የነበረውን የወሎን ረሀብ) በእንግሊዛዊ ሽወዳ ዘዴ ለአለም ያሳወቀና ለረሀብተኞቹ እርዳታ ይመጣ ዘንድ በሩን በርግዶ የከፈተው ጆናታን ዲንቢልቢ ነው። የሌኒንን ወደ ቦሌ ተራማጅ ሀውልት የሚያክል እዚያው አፍሪካ አዳራሽ ፊት ለፊት እናቆመው ነበር። እና ሀቅ ሀውልት በመሆኑ ማንም አያፈርሰውም ነበር። (ምንም የጋዜጠኛ ሀቅ ቢሆን) አለቻ ትህትና ከአበው የወረስናት!

የካቲት 5 ቀን 1987

# ድሮ ቀረ?

እቺ የምትከተለው ሀሳብ በተለያዩ አገሮችና ዘመናት የተለያየ መልክ ለብሳ እናገኛታለን። እሷ ግን ያው እሷ ናት። መልኮችዋን ልዘርዝርላችሁ እናንተን ደሞ እቺው "እንትን" በሌሎች መልኮች አጋጥማችሁ ሊሆን ይችላል።

<u>መልክ አንድ</u>

ከቅርሳችን፡- ከአፈ ታሪክ የምንሰማው እውነት ከሆነ ሚካኤል ተንታ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን አሰርተው አንቆጥቁጠው ካስጨረሱት በኋላ እሳቸው ሳይቀሩ በተንታ ሚካኤል ውበት ተደነቁ። በእውነቱ እንደዚያ ያለ ቤተ ክርስቲያን ተሰርቶ አያውቅም ተባለ።

"ደግሞ ይህን የመሰለ ድንቅ ነገር አይደገምም" ሲሉ ያሰቡ ይመስላሉ ንጉስ ሚካኤል "ሊደገምም አይገባውም። እንዳይደጋገም ለማረጋገጥ የግንበኞቹን እጅ መቁረጥ" ብለው በግጥም ደመደሙ። በመደምደም አልተመለሱ፤ ቁራጥ ናቸውና የግንበኞቹን እጅ ወዲያው አስቆረጡ። አንድ አንድ እጅ ብቻ ይቆረጥ ወይስ ሁለቱን ለማረጋገጥ አልተቻለንም። አንድ እጅ እንደሚበቃ ተስፋ አለን ለማንኛውም። የሽልማት በተገላቢጦሽ ወይም ባጎረስኩ ተነከስኩ አይነት ነው።

## መልክ ሁለት

አለፍ ብለን ታሪክ ይሁን ተረት ገና ምንነቱ ያልተረጋገጠ ታሪክ ወይም ተረት፡፡ ጥንት በመካከለኛው ዘመን፤ አንድ የምስራቅ አገር ንጉስ ወይም ሱልጣን አንዱን ባለልዩ ተሰጥኦ አርኪቴክት "ገንዘብ መቆጠብ ሳታስብ ከሁሉ ይበልጥ ያማረ ቤተ መንግስት ስራልኝ እኔ የሚገባህን እሸልምሀለሁ" አለው፡፡

ህንፃው ተገንብቶ ሲያልቅ ማማሩ አይንን ማመን እስኪያስቸግር ድረስ ሆኖ ተገኘ፡፡

ያዩት ሰዎች እጅጉን እየተደነቁ እርስ በርሳቸው "አሁን እንደዚህ ተሰርቶ ያውቃል? ኧረ እንኳን ሊሰራ ሊገነባ ይቅርና ታስቦም ታቅዶም አያውቅም" ሲባባሉ ንጉስየው ሲሰሙ በልባቸው ውስጥ የቅናት መንፈስ ተለኩሶ ወይም በሆዳቸው ውስጥ ቅናቱ አብዮታዊ ፍንዳታን አደረገ ይሆን? ለማንኛውም ንጉሱ ካንገታቸው እያዘኑ ያንን ተአምራዊ አርኪቴክት በስጦታ በሽልማት በክፍያ በሹመት አስደሰቱት እያዘኑም እንዲህ አሉት "ለስራህ ይሄም ሲያንስህ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ውበት እዚች አስቀያሚ ምድር ላይ ዳግም ይታይ ዘንድ ሀጢአት ነውና እንደገና ሰርተኸው ሀጢአት ከምትገባ ወደ ዘላለም ጭለማ ከምትወርድ፤ እቺ ሀላፊ ከንቱ ምድራዊ ብርሀን ብትቀርብህ ይመረጣል፡፡ ግማሽ ለአንተ ግማሽ ለራሴ ብዬ ነው" አሉና አይኑን አጠፉት፡፡ ሁለቱንም ነው እንጂ አንዱ አይን ከተረፈማ ምኑን አይን ጠፋ?

እንዲህ አይነት ታሪኮች ከሰው ሰው በመቀባበል ብዛት ከዘመን ዘመን ጭምር እና ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ቀስ በቀስ ተረት ሆነው ይቀራሉ፡፡ በበኩሌ ከላይ የፃፍኩላችሁን ነው አስቀድሜ የሰማሁት፡፡ ተረት ሆና ደረሰችኝ፡፡ ከብዙ አመታት በኋላ አንዱ ታሪክ ያነበበ ሰው እንዲህ አለኝ፡፡ "ታሪኩ ጉደኛው ኢቫን የተባለው የሩሲያ ንጉስ ነገስት የሰራው ነው፡፡ ህንፃው ግን ቤተ መንግስት ሳይሆን የሩሲያውቹ እንቁላል ‹ቤተ ክርስቲያን› ነው፡፡"

እኔ ፎቶውን ሳይ የምኖት ሀሳቦች ይመላለሱብኛል። እነዚህ ቤተስኪያኖች እንዴት ነበሩ? ውስጣቸውስ ምን ይመስል ይሆን? እነዚያ በፎቶ ሲታይ ሸንኩርት የሚመስሉት ጉልላቶቻቸው ጉልላት አይደሉም እንጂ እውስጥ ሆነን ወደ ላይ ብናያቸው ምን ይመስሉ ይሆን? ክቦች? ግድግዳውስ ላይ ምን አይነት ስእሎች? እና የመሳሰሉት።

እንግዲህ ጉደኛው ኢቫን ከሲኦል ይሁን ከገነት አንድ ቀን አስፈቅዶ ያችን የፈጣሪዋን አይን ያስጠፋችውን ህንፃ ሲያይ በጉጉት ወደ አገሩ ቢመለስና ምድረ ሩሲያ የሽንኩርት ጉልላት ቤተመቅደስ እንደ እንጉዳይ እንደበቀለባት ቢያይ ምን ይመስለው ይሆን?

አቶ ኢቫን!! ሽንኩርት እንቁላል - ጉልላት ቤተ ክርስቲያንን የሚፈጥር አንድ ሰው ከተወለደ የተፈጠረውን እያየ ደግሞ ድጋሚ ሊሰራው የሚችል አስር ሰው እንደሚወለድ አያውቅም?! ለምን አስር ግን? ለምን አስራ ሶስት አይሆንም? ደግሞስ የትኛው የህዝብ ቆጠራና የአርክቴክት መረጣ ነው ይህንን ስታትስቲካዊ ቁጥር ያስገኘው? ወይስ የስታቲክሱን ስም ለማጉደፍ ነው? ማርክ ትወይን ምን አለ? "ውሸት አለ፤ የተረገመ ውሸት አለ፤ ስታትስቲክስም አለ"

ኢቫን (ዮሀንስ ማለት ነው) በ1533 ተወለደ። የሶስት አመት ህፃን እያለ ዙፋን ላይ የወጣ፤ ሀምሳ ሁለት አመት ሙሉ ንጉስ ነገስት ሆኖ፣ በሩሲያ ታሪክም ትልቅ ሚና ተጫውቶ አለፈ። ቅፅል ስሙ "ጉደኛው"። ደሞ የተሳሳተ ትርጉም ነው ይባላል። በሩስኪ "መርእድ" ወይም ‹‹ግርማ-ሞገሱ የሚያስደነግጥ›› ማለት ነው ይላል ኤንሳይክሎፒድያ ብሪታኒካ!

<u>መልክ ሶስት</u>

ከዚያም ርቀት፡- ዛሬ ሜክሲኮ በሰሜን አሜሪካ በስተደቡብ በሚገኘው አገር ውስጥ ሄርናንዶ ኮርቴዝና ወታደሮቹ በስፓኝ መርከብ አትላንቲክ ውቅያኖስን ሄደው የአዝቴክ ንጉስን ሞንቴዙማን በጦር ድል አደረጉት። ሞንቴዙማ ድል የሆነበት ምክንያት እነኮርቴዝ በስልት ወይም በጀብዱ በልጠው ሳይሆን...

ታዲያ በምንድነው?

"ይበልጥ ለመዝለል ወደኋላ ማፈግፈግ" ይላል ፈረንሳይ! እኛም አሁን ዊ.ዊ! እስራኤላውያን እኛ የያህዌ ህዝብ ነን እንደሚሉ ሁሉ የአዝቴክ ሰዎችም የፀሀይ ህዝብ ነን ይሉ ነበር፡፡ የዚህ የአዝቴክ ህዝብ ታሪካዊ እጣ ወይም ተልእኮ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ዘላቂ ጦርነት አወጆ፡፡ ከትውልድ እስከ ትውልድ እርቀ ሰላም የማያውቁ ውጊያዎችን ማካሄድ ነው፡፡ ለምን? ማለታችን አይቀርም፡፡ እነንድ እስታሊንና እነ ጓድ መንግስቱ እንኳን የወዝ አደሩ መደብ ድሉን እስኪቀዳጅ ወደፊት! አሉና በአድሀሪያን መቃብር ላይ አገር ለመገንባት ቆርጠው ተነሱ እንጂ እስከ መቼም ማለቂያ የሌለው የትጥቅ ትግል አላወጁም፡፡ ያውም ሁልጊዜ በድል ላይ ድል እያስመዘገቡ ስለሚራመዱ ባጭር ጊዜ ውስጥ አድሀሪያንና ተስፈንጣሪያን የሌሉበት የበለፀገ አለም ውስጥ እንደምንኖር ነው፡፡ ያን ጊዜ እንኳን ጦርነቶች መንግስታትም አይኖሩም፡፡ ያን ጊዜ "ከያንዳንዱ እንደችሎታው ለያንዳንዱ እንደፍላጎቱ" ነው፡፡

የነሞንቴዙማ አባቶች እምነታቸው ሌላ ነው፡፡

ዊ-ዊ! አሁንም ይበልጥ ለመዝለል ወደኋላ እናፈገፍጋለን፡፡ አለም ከዚህ በፊት አራት ጊዜ ተፈጥሮ አራት ጊዜ ጠፍቷል፡፡ ይሄ አሁን ያለንበት ለአምስተኛ ጊዜ በአዲስ የተፈጠረ ነው፡፡ አማልክቱ ተሰበሰቡና ፀሀይና ጨረቃን ለመፍጠር ተማክረው በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ትልቅ እሳት አነደዱ፡፡ ከአማልክቱ ሁለቱ ዘለሉና ነበልባል ውስጥ ተቃጠሉ፡፡ ትልቅየው አምላክ ፀሀይ ሆነ፤ አነስተኛው ደግሞ ጨረቃ ሆነ፡፡ በተለይ (ለወጣት ደራሲያን) እቺን እየገፍኩ እያለሁ፤ ሳልጠራው ከኔ ከውስጤ ፈልቆ ወጥቶ አንድ ባለ ክንፍ ሚጢጢ ነፍሳት መሰል ሀሳብ እንዲህ አለኝ፡፡ የአማልክቱም ነብስ ሁለቷም አረገች! ፀሀይን የሚጠጉ ግን የማይፈጁቸው ነፍሳትን ሆነ...

ጨረቃ መሀሪ ናትና፡፡ ፀሀይ ግን ለካስ የከፈልኳችሁን ክፈሉኝ የሚል ገበያተኛ አምላክ ኖሯል፡፡ እንዳያችሁት ታሪኮች ካልተገፉ በስተቀር

በአፍ ሲበተኑ አሁን እንደጨመርኩበት እየተጨመረባቸው እየተለወጡ የለየላቸው ተረቶች ይሆናሉ። ነብሳቸው ወይም ይዞታቸው ግን ያው ሆኖ ይዘልቃል።

ሆነም፤ ፀሀይም እዚያ ላይ ሆኖ እውነቱን ይሁን ውሸቱን የማያስታውቅ መልክት ላከ። በቅርቡ በሚገኘው በእሳት እራት ላከ፣ እንዲህ ሲል፤ እኔ ለናንተ ፀሀይ ለመሆን ስል በእሳት ተሰውቻለሁና ስሰዋ እሳቱ የወሰደብኝን ጉልበት የሚተካልኝ ትኩስ የጦረኛ ደም በመሆኑ ያውም በጦር ሜዳ ያመረተው የጦር መሳሪያ አቁስሎት የዳነ መሳሪያ ካልሆነ በስተቀር በእንቅፋት ወይ ሌላ ተራ ቁስል ድኖ ጠባሳ ያለበት ለፀሀይ መስዋት ይሆን ዘንድ ብቃት የለውም። ስለዚህ እናንተ ምርጥ ህዝቤ አዝቴክ ብቻ መስዋእቱን ታቀርቡልኛላችሁ። ይበልጥ ብዙ በተሰዋልኝ መጠን ይበልጥ ስለምጎለብት እወቅበታ አዝቴክ

በአለም ህዝቦች ላይ ጦርነትን ክፈቱ። እኔም በጦረኞች ላይ ድሉን እሰጣችኋለሁ እናንተም የምርኮኞቻችሁን ደም ትሰጡኛላችሁ እንዲህም ማን ችሎን?...

ድሮ ቀረ ተከታታይ አምድ እያስተካከሉ መቅረፅ፤ ድሮ ግን አምድ የሚሉት ነገር አልነበረም'ንጂ!!

አለም ለስድስተኛ ጊዜ ሳትፈጠር ትቀራለች? የምን ድሮ ቀረ ነው እሉ? ነገ ይመጣል'ንጂ!

**የካቲት 12 ቀን 1987**

# የፀሀይ ህዝብ

"የፀሀይ ህዝብ" የሆነው የአዝቴክ ህዝብ ለፀሀይ መስዋእት የሚቀርቡ ምርኮኞች ለማግኘት ሲል በሰው ልጆች ላይ የማያበቃ ዘላቂ ጦርነትን እንደከፈተ እናስታውሳለን፡፡ ቁጥሩ ሀሳባችንን ያጠራልን ዘንድ ለምሳሌ አንዱ ንጉስ ዘውድ ሲደፋ በንግስ በአሉ ቀን ሰማንያ ሺህ ምርኮኞች ለፀሀይ ተሰጥተዋል፡፡ የነሱ ደምና ልባቸው ነው ፀሀይን የሚያጎለብተው፡፡ ይሄ መስዋእት ቢቀርበት ፀሀይ እየደከመ ይሄድና ይጠፋል፡፡

ስለዚህ የአዝቴክ የተቀደሰ ተግባር በተገኘው ሌላ ህዝብ ላይ እየዘመቱ የነዚያን ወታደሮች እየማረኩ ለፀሀይ መሰዋት ነው፡፡ ይህንን አስተምረው ለማሳመንና ስራ ላይ ለማዋል የቻሉት ቄሶች ግን በችሎታቸው እጅጉን የሚደነቁ ናቸው፡፡ ወይስ ይሄ "የፀሀይ ህዝብ" ደደብ ነው ልበል? ወይስ ማንኛውም ህዝብ ቄሶች ፈጥረው የሚሰጡትን አማልክት አሜን ብሎ ያምን ያመልክ ይሆን? ለማንኛውም ይህን የአዝቴክ ሀይማኖት የፈጠረው ሰውዬ (ወይም ሴትዮ) በዚህ በወታደራዊ መስዋእት መልኩ ስናየው ግንባር ለግንባር ብናነፃፅራቸው የኢየሱስ ተቃራኒ ነው፡፡ ይሄኛው ለሰው ሲል ሞተ፤ ያኛው በሰው ላይ የማያበቃ ሞትን አወጀ፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን ሁለቱ የሚመሳሰሉበት አለ፡፡ ለኢየሱስ ሲሉ ብዙ ብዙ ሰማእታት ሆን ብለው ተሰውተዋል ያውም በደስታ፡፡

ለፀሀይ ሲሉም ብዙ ብዙ የአዝቴክ ወታደሮች ውድ ህይወታቸውን በየጦር ሜዳው መስዋእት ከፍለዋል በደስታ ሊሆን ይችላል ብዙዎቹ የወደቁት - ሁሉም ባይሆኑም፡፡

የአዝቴክ ህዝብ ደደብነት ግን እጅግ ሲበዛ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ የቤተ መንግስቶች የቤተ መቅደሶች የከተማዎች ስራዎቻቸው ከጥንት ግብፃውያን ስራዎች አይተናነሱም ይባላል፡፡ የአስትሮኖሚ ማለትም የፀሀይ ጨረቃ ክዋክብት እንቅስቃሴን የሚያጠና ሳይንስ፡፡ እውቀታቸውም እንደዚሁ አስደናቂ ነበር፡፡ ለምሳሌ ቤተመቅደሳቸው ውስጥ ምርኮኛው በጀርባው ተጋድሞ ታስሮ ልቡ በድንጋይ ቢላዋ ተወግቶ የሚገደልበት ቦታ ላይ ልክ በየአመቱ በዚያች ደቂቃ የፀሀይዋ ጨረር ጣራው ላይ ባለችው ጠባብ ቀዳዳ እንደ ዘንግ ተወርውራ የምታርፍበት ቦታ ልክ የመስዋእቱ ሰውዬ ልብ ላይ ነው የምታርፈው፡፡ በየአመቱ አንዲት ሚሊም ዝንፍ አትልም፡፡ ይህም የማቲማቲክስ (የሂሳብ ስሌት) እውቀታቸው የላቀ ነበር ማለት ነው፡፡ እንዲያውም በአሮጌው አለም ዜሮ የምንለው አሀዝ ህንዶች ፈጥረውት ግኝቱ ለሌሎች ህዝቦች እንደተዳረሰ ሁሉ፣ እነክርስቶፎል ኮሎምቦስ ባገኙት በአዲሱ አለም ውስጥም አዝቴኮች ዜሮን በገዛ ራሳቸው ፈጥረዋታል፡፡ ይሄውላችሁ እንግዲህ እኛ ሙሉዎቹ አንዴ ብቻ እንፈጠራለን ዜሮ ባዶዋ ግን ሁለቴ ተፈጠረች እዝጌሩ ሲያድላት፡፡ አደላላት አላልኩም እኔ አይወጣኝም፡፡ እሱ እንደማያዳላ የታወቀ ነው፡፡ እድል አደላት ነው ያልኩት፡፡ ላንዱ ቁምጥናን ላንዱ ብልፅግናን እንደሚያድል አይነት፡፡ ከዚያም ተነስተው አበው የአርባ ቀን እድልህ ነው ይላሉ፡፡

ሆነም ቀረ አዝቴኮች ከአለም ታላቅ ስልጣኔዎች አንዱን ፈጥረው አሳድገው ትተውልን አልፈዋል፡፡ ያውም እንዲያ እየተዋጉ ነዋ!

ወደ ጨዋታችን ስንመለስ ሄርናንዶ ኮርቴዝ በጦር ስልት ችሎታውና በወታደሮች ወኔ ብርታት ንጉስ ሞንቴዙማን ድል የነሳው መስሎታል እንጂ ጉዳዩስ ሌላ ነው፡፡ "ያ ሌላ ይህ ሌላ!" ያሉት አበው የኮርቴዝን ድል እያስላሰሉ ሊሆን ይችል ነበር፡፡ አይደለም እንጂ!

ካልሆነም ይተወው! የራሱ ጉዳይ! እሱ ቀረበት እንጂ አበው ምን እንዳይቀርባቸው? አይ አበው! አልተቻሉም! እነሱ ማን ሊችላቸው? ኮርቴዝ ራሱ ቢዘምትባቸው እንኳን አይችላቸውም ነበር፡፡ "ሂድ ወዲያ ሞንቴዙማህን ፈልግ!" ይሉት ነበር፡፡ ሄዶም ታላቁን የአዝቴክን ስልጣኔ ያወድመው ነበር፡፡ ታሪካዊ ተልእኮ ነውና!

አዝቴክ ሀይማኖት እንደሚያስተምረው ከዌትዛልኮትል የተባለው አምላካቸው ነው እርሻንም ስልጣኔንም ያስተማራቸው፡፡ አስተምሮ ሲያበቃ ባረካቸውና ተሰናብቷቸው በባህር ሄደ፡፡ ከዌትዛልኮትል ሲሄድ "እመለሳለሁ" ብሎ ነበር የሄደው፡፡ ጦርነቱ ሳያቋርጥ መስዋእቱ በሽበሽ እየሆነ ወደውም ሳይወዱም የተሰዉት ምስጋና ይድረሳቸውና ፀሀይም አንድ ቀን እንኳ ሳትደክም እንደ በረታች የብርሀንና የሙቀት ፀጋዋን እየለገሰችን ብዙ ዘመናትና ትውልዶች አለፉ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ልክ ከዌትዛልኮትል በሄደበት አቅጣጫ ኮርቴዝ እየተንሳፈፈ ከተፍ አለ፡፡

ከዌትዛልኮትል ቃሉን ጠብቆ ይኸው ተመለሰ ብለው አመኑ ብዙዎቹ የአዝቴክ ሰዎች፡፡ ምንም ንጉሱ ሞንቴዙማ ትእዛዝህን ቢሰጥህ በምን ወኔህ ከአምላክ ሰራዊት ጋር ትዋጋለህ? ብትዋጋስ መሸነፍህ ይቀራል? ሆነም ንጉስ ሞንቴዙማንም እነኮርቴዝ ማረኩት፤ ክርስቲያን ናቸውና ይህን ጣኦት አምላኪ የአህዛብ ንጉስ በአረመኔያዊ ጭካኔ አዋርደው አሰቃይተው ገደሉት፡፡ እሱስ ይሙት ብዙ ሰዎችን አስገድሏል፡፡ ታላቁ አዝቴክ ስልጣኔም አብሮት ሞተ እንጂ፡፡ ጌታው አቶ ጄኔራል ኮርቴዝ፤ ነፍስህን አይማረው!...

የቀበርከውን ወርቅና ሌላ ሌላም ከቡር ድንጋይ የት እንደሆነ ምራ ቢሉት ሞንቴዙማ አሻፈረኝ አለ፡፡ "እኔ የአዝቴክቱ ልጅ? ወይ ፍንክች! አንተ ስግብግብ ነጭ ጅብ! እኔ የቀይቱ ልጅ ነኝ የዜጋዎቼን ህይወት አጥፍቼ ሳበቃ የራሴን የማድነው? እንኳን ያንተ የሲ አይ ኤ ቶርች ይምጣ! ኧረ የኬጂቢ ቶርች ራሱ ይምጣ! እኔ ሞንቴዙማ!"

ንጉስ ሞንቴዙማ መሸነፉን ሲያውቅ ጥቂት ታማኝ አጃቢዎቹን በሳጥኖቹ ወርቅ ወርቁን አሸክሞ እሱና እነሱ ብቻ የሚያውቋት ስዋራ

ቦታ ወስዶ ጉርጓድ አስቆፍሮ አስቀበረው፡፡ ከዚያም ምስጢሩ ምስጢር ሆኖ መቅረት ስላለበት ሞንቴዙማ እነዚያን ታማኝ አጃቢዎቹን ወዲያው አስገደላቸው፡፡ ምስጢሩ አብሯቸው ተቀበረ፡፡ (ይኸውላችሁ እንግዲህ አጉል ምስጢረኛ መሆን ይህን ያመጣል “ያወቁ አለቁ” ይሉ ነበር አሁን አበው ቢኖሩ፡፡ እኔ ራሴ ብለውስ? እንደ እንቁላልየው ቀስ በቀስ አበው እየሆንኩ አይደለም እንዴ፤ ይቅር ይበለኝና?)

ሞንቴዙማ ሳይናገር ቀረ፤ ስግብግብ ሞንቴዙማ ኩም እንዳለ ቀረ፡፡ የታባቱንስና! በአይጥ መርዝ መግደል ነበር፡፡ እሱም ከአይጥ አይሻል ኧረ ይብሳል! ለራሱ ቅማላም የጠፍር አልጋ ቱጂን! ደሞ እርሱን ብሎ የመርከብ ካፒቴን! እሱን ብሎ የጦር አዛዥ! ኮሎምበስን የሆነ መሰለው'ንዴ? አቅሙን የማያውቅ ቶስቷሳ! ዲስክራሲያቶ!

አቤት! አበው ይህን የስድብ ናዳ ቢያነቡት እንዴት በገረማቸው! ሄርናንዶ ኮርቴዝም ይህን የስድብ ነጎድጓድ ቢሰማ አፍሮ ጭራውን ሸጉጦ ወደዚያ ወደመጣበት የሸይጣን አለም በተመለሰ፡፡

የታሪክ ማስታወሻ፣ የሞንቴዙማ ቋንቋ ዛሬ በሜክሲኮ አገር አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ አዝቴኮች ይናገሩታል፡፡ ስልጣኔው ሞተ'ንጂ ህዝቡ አልሞተም፡፡

በመካከለኛው ዘመን፤ ማለትም መድፍና ሌሎች ፈንጂዎች ከመፈጠራቸው በፊት፤ ወራሪ ጦር ለመከላከል ሲባል ከተማዎች በወፍራም ካብ ይከበቡ ነበር፡፡ (የኛን የሀረር ጀጎል ያስታውሷል) ከተማው ውስጥ ደግሞ ቤተ መንግስቱ በሌላ ወፍራም ካብ ይከበባል፡፡ እንደ ደሴት ይሆን ዘንድ ከካቡ ዙሪያ ደሞ የባህር ቀለበት ነበረበት፡፡ እንኳን የዚያን ዘመን የጦር ትጥቅ የደረተ ቁር የራስ ጥሩር? ጋሻ ጦር ሰይፍ! ይህን ሁሉ ብረት የታጠቀ (ወታደር ቀርቶ) ራቁቱን የሆነ ሰው እንኳን በቀላሉ የማይሻገረው የባህር ቀለበት ነው፡፡

እንዲያው ለምናልባቱ ንጉስየው ወይ አገረ ገዢው የተሸነፈ እንደሆነ እሱና ቤተሰቡ በስውር ሸሽተው ካገር የሚያመልጡበት የምድር ውስጥ

ለውስጥ መንገድ ተሰርቶለታል። ይህን መንገድ የሚያውቁት ንጉሱና ቤተሰቡ ብቻ ናቸው። ያውም ያልደረሱ ልጆቹ አያውቁትም። መቸስ የታወቀ ነው! ያቺ ክፉ ቀን ከመጣች ማምለጥ ይችሉ ዘንድ ያ ማምለጫው ሚስጢር ሆኖ መቆየት ይኖርበታል። ይኸውም ይሆን ዘንድ ይህን ስውር ማምለጫ የሰሩት ጥቂት ታማኝ ሰራተኞች መገደል ነበረባቸው። እሱን ከእንግዲህ እድሜ ለንጉስ ለታማኝ አገልግሎታችን ወደፊት ወፍራም እንጀራ እንበላለን ብለው ተማምነው እያሉ! ልክ ሰርተው እንደጨረሱ ተገደሉ። አዬ ንጉስ የእጅህን አይንሳህ!

ምን ይደረግ ትላላችሁ? ወድጄ አይደለም ያስገደልኳቸው። ምስጢሩ እንዳይባክን ብዬ ነው። (የሽልማት ተገላቢጦሽ ወይም ባጎረስኩ ተነከስኩ)።

የመጨረሻው ምስልዎችን በሲሲሊ ወይም በጥሊያንኛው በሲቺልያ ተወልዶ ያደገውና እንደነኮርቴዝ አትላንቲክ ውቅያኖስን ተሻግሮ በአሜሪካ የነገሰው ማፊያ የሚባለው ዝነኛ የወንጀል ድርጅት ደምብ ይሆናል። ትልቅና አደገኛ ጠላት ይነሳባቸዋል። እንበል የከተማው የፖሊስ ሹም እንግዛህ ቢሉት እምቢ እናስፈራራህ ቢሉት አሻፈረኝ ብሎ እያደነ ሊያጠፋቸው ተነስቷል። እምቢ ካልክስ እንግዲያው እነሆ በረከት! ይሉና በጥይት ያስገድሉታል። ማን እንደገደለው እንዳይደረስበት ያንን ታማኝ ገዳይ በሌላ ታማኝ ገዳይ ይገደላል። ይህም ተራውን በሌላ ታማኝ ገዳይ ይገደላል። ይሄኛው ደሞ ዋነኛው የድርጅቱ ባለቤትና ሹም በማይጮህ ጥይት ያዳፍንበታል። ምስጢሩ ተዳፍኖ ይቀራል።

ኤኮ! (ፊኒቶ)!

የካቲት 19 ቀን 1987

# ሰውና ውሻ

"ውሻ በበላበት ይጮሀል" ብለዋል አበው። ማን ላይ ይጮሀል? ዞር ዞር ብለን ብናይ አበው ላይ አልጮኸም። ማንም ላይ እገሌ ብሎ ስም ጠርቶ አልጮኸም "ጌታዬ ቤት አትድረሱ!" ብቻ ነው ያለው "ለማኝም ሆንክ ንጉስ በግም ሆንክ ጅብ ፈጥነህ ከዚህ ጥፋ! አለዚያ ሀኝ!"

በተለይ ወጣቶች ፀሀፊያን ሆይ! የሰው ልጅ ሲበዛ ራስ ወዳድና ጠባብ ትእቢተኛ ስለሆነ ነው'ንጂ! ዙኦሎጂስቶች (ማለትም እንስሳትን ሁሉ ሰውንም ጨምሮ እንደ አንድ ቤተሰብ እያዩ የሚያጠኑ የባዮሎጂ ምሁራን) ሲነግሩን ግን ጉዳዩ ሌላ ነው።

ሰውና ውሻ አብረው እየተባበሩ ሲኖሩ፣ ለካ ውሻ አይደለም አገልጋዩ ሰው ነው'ንጂ። እንዲህ ውሻ እንደ ሰው መናኛ ትእቢተኛ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ብሎ ያስብና ይናገርም ነበር። አንድ ስም የለሽ "ቡህ! ቡህ" የሚባል የውሽኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት እንግሊዝ አገር አለ። ሶስት ወር ውሽኛ ቋንቋ ያስተምሩና ሰርተፍኬት ይሰጣሉ። ያውም ማህተም ያለው። እዚያ ተምሮ የመጣ የማምነው ጓደኛዬ የነገረኝን ነው የማጫውታችሁ።

ብትፈልጉ እንግሊዝ አገር የፈረስ ቋንቋ እንዲሁም የተለያዩ እንስሳት ቋንቋ ትምህርት ቤቶች አሉ ብሎኛል። አምነዋለሁ ብያችኋለሁ። ምክንያቱም እንግሊዝ የሰው ልጆች ሁሉ (ወይም ብዙዎቹ) ወይ በዚህ ወይ በዚያ ገዝቷቸው ወይ አስገድዷቸው ወይ በዝብዟቸው

የሚያውቅ ነው። እንዲያ ካላረገ ደሞ ከዚያች ከሚጢጢ ደሴት ተነስቶ በሚነሳበትም ዘመን በግምት ስድስት ሚሊዮን ብቻ ሆኖ ተነስቶ ሲያበቃ የአባይን የኮንጎን ወይ የአማዞንን ወንዝ መነሻ ምንጭ ይመስል- - -

እቺን ፅሁፍ በምታነቡበት ሰአት የእንግሊዝኛ ተናጋሪ ሰው ብዛት የት ደርሷል? አንድ ቢሊዮን (ማለት አንድ ሺ ሚሊዮን) የአለም ህዝብ ስድስት ወይም ከእዚያ በላይ ቢሊዮን ነው በሚባልበት በአሁኑ ጊዜ (ስለ አቆጣጠሩ ብዙ ጥያቄዎች ቢኖሩንም ቅሉ) ከውጭ አለማት ከአንዱ አንድ አስተዋይ ፍጡር ወዲህ መጥቶ ቋንቋ መናገር ቢሞክር የመጀመሪያው ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል። ምክንያቱም በቁጥር አሳንሰን ብንናገር ከስድስቱ የሰው ልጆች አንዱ እንግሊዝኛ ያውቃል።

ከነዚህም ግማሹ ማለትም አምስት መቶ ሚሊዮን (ምንጩ ሲነሳ ስድስት ሚሊዮን ብቻ እንደነበረ እያስታወስ) ሲወለድ እናቱ በእንግሊዝኛ ነው የምታናግረው።

ግማሹ በመቶዎች የሚቆጠሩ የናት ቋንቋዎች እያሉት እንግሊዝኛ ሁለተኛ ቋንቋው ናት (ወይ ሶስተኛ ወይ አራተኛ ወይ አምስተኛ) እና ወደ እንግሊዝኛና ወደ እንስሳት ስንመጣ እንግሊዝ የሰው ልጆችን የተጠቀመባቸውን ያህል የእንስሳ ልጆችን ጠቅሟቸዋል። እንዴት? ቢባል ከብዙ መረጃዎች አንዷን እንጠቅሳለን እኔና እስክሪብቶዬ።

የለንደን ኗሪዎች በፈረስና በሰረገላ በሚመላለሱበት ዘመን - በግምት ከመቶ አመት በፊት - አንድ ረኸም ጠብዚራ ሰውዬ በኪራይ ሰረገላ ይሄዳል። ባለጋሪው ወይ ከሚስቱ ተጣልቶ ወይ ሆድ ቁርጠት ይዞት ወይ እንዲሁ ብሽቅ መናኛ ሰው ኖሮ ሰረገላውን የሚጎትተውን ምስኪን ፈረስ ባለ በሌለ ጉልበቱ ይገርፈዋል። አለንጋውን አዘነበበት ልበላችሁ?

ተሳፋሪው ተናደደ ተነሳ። ባለጋሪውን በእንግሊዝ ቦክስ አሩን አበላው እሰይ! ተሳፋሪው በዚህ አልተወሰነም The Society for the protection of Animals (ለእንስሳት ደህንነት ተሟጋች ማህበር) አቋቋመ። ዛሬ ይህ ማህበር በእንግሊዝኛ ተናጋሪ አገሮች በሙሉ ተስፋፍቶ ይገኛል።

እርግጠኛ አይደለሁም እንጂ ምናልባት በሌሎቹ በሰለጠኑት (ማለትም ሀብታም በሆኑት) አገሮችም ይህ ለእንስሳት መብት የቆመው ማህበር ሳይስፋፋ አይቀርም። በእንግሊዝ አገር ይህ ማህበር ምን ምን እንደሚሰራ፤

ማንም ሰው ውሻውን ወይም ድመቱን ወይ ሌላ እንስሳውን በቂ የማይመግበው ከሆነ ጎረቤቶቹ ወደዚህ ማህበር ስልክ ይደውሉና ይናገራሉ። ጠቆሙበት አትሉኝም! ማህበሩ ባለቤትየውን ይከሰዋል። ጎረቤቶቹን ያስመሰክርበታል። እንስሳው በህግ ይወሰድበታል። እንስሳ ለሚወዱና ለሚንከባከቡ ሰዎች ይሰጣል። ምናልባትም ማህበሩ ስራውን ለመስራት ገቢ ስለሚያስፈልገው እንስሳው በገንዘብ ይሸጣል። ምናልባቶች አበዛን እንጂ።

የባዮሎጂ የዙኦሎጂ፣ የህክምና የኬሚስትሪ ሊቃውንት እንስሳትን ለምርምር ሲባል ብዙ ያሰቃዩዋቸዋል። ለምሳሌ የብርድና የሙቀትን ምስጢር ማወቅ ስለተፈለገ ብርድ ወይም ሙቀት እስኪሞቱ ያበዙባቸዋል። በስንት ሴንቲግሬድ ብርድ ወይም ሙቀት ሞተ? ይመዘገባል። ለሳይንስ አንድ ጠቃሚ እውቀት እንደተጨመረ ይታወቃል። እንስሳው ምግብ ሳይበላ ምን ያህል ጊዜ ይሰነብታል? እስኪሞት ያስርቡትና ውጤቱን ይመዘግቡታል። መድሀኒቱ ሰው ላይ ከመሞከሩ በፊት እንስሳት ላይ ይሞከራል ወ.ዘ.ተ።

የዚህ የእንስሳት መብት ተከራካሪ ማህበር አክራሪ አባላት አንድ ላይ ይሆኑና ወደ የላቦራቶሪ (የምርምር ማካሄጃው ቤት) እየሄዱ በሩን ሰብረው እየገቡ እንስሳቱን አውጥተው ነፃ ይለቁዋቸዋል። አይ እንግሊዝ! እንግሊዝ ይምጣልኝ!

አሁን በምናብ ድንገት ዝላይ ከኦሪት ዘከልብ እንጠቅሳለን፡-

ሆነም፤ ፈጣሪም ሰማይና ምድርን ከነሁለመናቸው በስድስት ቀን ፈጥሮ ሲያበቃ በሰባተኛው ቀን አረፈ። በስምንተኛው ቀንም ስራውን ሊቀጥል ተነሳ።

በስድስቱ ቀን የፈጠራቸውን ሁሉ አየ። እነሆ ሁሉም የሱ ስራ ናቸውና

ሆኖም ግን፣ ግና ነገር ግን ከጣት እንኳ ጣት ይበልጣልና ፈጣሪም ማዳላት በሌለባቸው አይኖቹ ፍጡራንን ሁሉ አያቸው።

በፈጣሪም አይን ሞገስ ያገኘው ሰማይን እንደ ምጣድ በክንፎቹ ፀጥተኛ ማሰሻ የሚያስሰው ንስር አልነበረም።

ባንድ ሁለት ሶስት ግሳት ፍጥረትን የሚያንቀጠቅጣት አንበሳም አልነበረም። ምን ኦሪት ዘሌላውያን ይመስል ስሞችና ቁጥሮችን ማብዛት ነው እሱ? ፍርጥ አርገን እንናገረውም ያውም ከትህትና ጋር?

ውሻ ተመረጠ።

ሆነም፤ ፈጣሪም የውሻን ሀቀኝነትና ቆራጥነት ካደነቀ በኋላ እንዲህ ሲል አሰበ

ውሻ ከዘመዶቹ ከነተኩላ ከነእንትና ጋር ኩታ ገጠም ርስት ብሰጠው በዚህ በእርስ በርስ ተባሉ ሁኔታ ዘሩ ከጥቂት ትውልድ በኋላ ያልቃል። በሱ ውስጥ ያለች ትንፋሽም ትጠፋለች።

"ስለዚህ"

ፈጣሪም እንዲህ አለ "ከፈጠርኳቸው ፍጡራን ሁሉ ውሻን ሊጠብቀው የሚችል ከኔ ጉልበት ቀጥሎ ጉልበተኛ የሆነ እሱ ውሻን ይጠብቀው"

ሰውና ውሻም እስከ መጨረሻ ተጎዳኙ

የካቲት 26 ቀን 1987

# እንግሊዝና ጋንዲሂ

ውሻ በበላበት ይጮሀል። እሱማ የትም ይበላል፣ የትም ይጮሀል። ግና የት ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የውሻ ልጅ ተወድዶና ተከብሮ የበላው? በእንግሊዝ አገር። እንግሊዛዊው ውሻውን ገና በቡችላነቱ ቤት ውስጥ እንዳይሸና ያስተምረዋል። ስለዚህ እንግሊዝና ውሻውን ምንም የሚያጣላቸው ነገር አይኖርም። እንግሊዝ ካልታመመ በስተቀር ጧትና ማታ ውሻውን ለአንድ ሩብ ወይ ግማሽ ሰዓት ሽርሽር ይወስደዋል። በስጋም በመንፈስም ይዝናናል ውሸየው

ዙኦሎጂስቶች እንደሚነግሩን ውሻ የሚውልበትንና የሚያድርበትን አካባቢ እንደ ቤቱ እንደ ግል ንብረቱ ይቆጥረዋል። ይህን አካባቢ በሽንቱ ጠረን ያጥረዋል። ለዚህ ነው እየዞረ በየምናምኑ ስር ሽንቱን ረጨት እያደረገ የሚያልፈው። ሌሎች ውሾች ወይም አውሬዎች በዚያ ሲያልፉ ውሻውም ባይኖር ጠረኑ እንዲህ ይላቸዋል ‹‹ይህ አካባቢ ተይዟል ማለፍ እንጂ መቆም አይፈቀድም።›› ያልፋሉ እንጂ አይቆዩም።

እንግሊዞች በየጊዜው የውሻ ትርኢት ያሳያሉ። የውሻ አይነት ይሰባሰብና ሲታይ ይውላል። ከየዘሩ አይነት በመልክ በክብደት በድሜ ወዘተ መስፈርት ተለክቶ ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ይሸለማል።

እንግሊዞች በውርርድ ብዙ ሚሊዮን ፓውንድ የሚከስሩና የሚከብሩባቸው የውሻ እሽቅድድሞሽ ያካሂዳሉ። እንዲሁም የፈረስ።

የውሻ ምግብ አዘጋጅቶ አሽጎ መሸጥ በጣም ትልቅ ቢዝነስ ነው።

እንግሊዝ ሚጢጢ ደሴት ናት ታሪክ የኂሊት እየተመለከተ ሲነግረን ይሄ ህዝብ በስፋቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ግዛት ግዛቱ ያደረገ ስድስት ሚሊዮን ያህል ብቻ ነበር። በአሁን ሰዓት አንድ ቢሊዮን ወይም አንድ ሺ ሚሊዮን ህዝብ እንግሊዝኛ ይናገራል። ከዚህም ግማሹ የትውልድ ቋንቋው ሲሆን የቀረው ግማሽ ደግሞ እንግሊዝኛ ከናት ቋንቋው ሌላ ተጨማሪ ቋንቋው ነው። እንደ ህንድ እና ናይጄሪያ ያሉ ብዙ ቋንቋዎች የሚነገሩባቸው አገሮች እንግሊዝኛን እንደ ብሄራዊ መግባቢያ ቋንቋ አድርገው ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ በህንድ አገር ኡርዱኛ እና ታሚልኛ ተናጋሪዎች እርስ በርስ የሚግባቡት በእንግሊዝኛ ነው።

እንግሊዝ የማይበገር የባህር ሀይል ነበራት። እንግሊዞች እንደ ሁለተኛ ብሄራዊ መዝሙር የሚዘምሩት በዚያን ዘመን የተገጠመ እንዲህ ይላል

‹‹አዛዥ ብሪታንያ፣ ብሪታንያ ሞገዶቹን ግዥ እንግሊዞች ከቶ ባሪያ አይሆኑም---››

("Rule Britannia, Britannia rules the waves Englishman never shall be slaves!)

በዚህ በባህር ሀይል ጉልበት፣ በህዝቧ ብርቱነት እና በመሪዎቿ ብልህነት የአለም በሙሉ ስፋት አንድ አራተኛውን በቁጥጥርዋ ስር አደረገች። ስለዚህም ነው ‹‹በእንግሊዝ ግዛት ፀሀይዋ አትጠልቅም›› የተባለው። በኢንግላንድ ብትጠልቅ በአውስትራሊያ እያበራች ነው በህንድ ብትጠልቅ በካናዳ እያሞቀች ነው። ታዲያስ?

‹‹ለምን መሰለህ በእንግሊዝ ግዛት ፀሀይዋ የማትጠልቀው?›› ይላል ጠላት ‹‹እግዚአብሄር በጨለማ እንግሊዝን ስለማያምነው ነዋ!›› እንግሊዝ ጠላት ብቻ አይደለም ያለው አድናቂም አለው። እና አድናቂው ምን አለ?

‹‹እግዚአብሄር እንግሊዛዊ ነው››

ከእንግሊዝ ግዛቶች ሁሉ ሀብታምዋና ጠቃሚዋ ህንድ ነበረች፡፡ እንግሊዝ ህንድን አራት መቶ አመት ገዝታታለች፡፡ እንግሊዝን የዘመን የሳይንስና ቴክኖሎጂ አብዮት ለማካሄድ ካስቻሉዋት ዋነኛ መሰረቶች አንዱ በዘረፋም በንግድም ከህንድ ወስዳ ያከማቸችው መነሻ ካፒታል ነው፡፡ ኸረ ጋንዲሂ ባይወለድ ኖሮ ከዚያም ለረዘመ ዘመን ትገዛ ነበር፡፡ ምን ዋጋ አለው? ጋንዲሂ የተባለ አደገኛ ሰውየ ተወለደ በነጮቹ አቆጣጠር በ1889፡፡ የጋንዲሂ እና የእንግሊዝ ትግል የዳዊትና የጎልያድ አይነት ነበረ፡፡ ከዚህም ጋር ታሪኩ ልክ ታላቁ ሼክስፒር የፃፈው ይመስል ድራማ ይበዛበታል

ገቢር አንድ - ትእይንት አንድ - ሞሀንደን ሄዶ ኢነርቴምፕል በተባለው ውዝግብ የህግ ትምህርት ቤት ትምህርቱን አጠናቋል፡፡ እንግሊዝን ያህል ሀያል መንግስት ከህንድ ለማስወጣት የተጠቀመበት መሳሪያም ይኸው የእንግሊዝ ህግ ‹‹ከሀቀኛነት ከሰላማዊነት የሚመነጭ፡፡›› ማለትም ገቢር አንድ - ትእይንት ሁለት - ጋንዲሂ ለጥብቅና ስራ ወደ ደቡብ አፍሪካ ይላካል፡፡ አስቦት ሳይሆን ባጋጣሚ የነፃነት ትግሉን ይጀምራል፡፡ ከእንግሊዝ ህግ ሌላ መሳሪያው ‹‹ሰላማዊ እምቢታ›› (passive ressiistance ወይም Non - vilolence) ነበር፡፡ ይህ ሰላማዊ እምቢታው በደንብ እንዲገባን ስለ ህንድ ባህል አንድ ሁለት መረጃዎችን እንቀነጭባለን፡፡

የህንድ ህብረተሰብ ጋንድሂና አዲስ ዘመን መጥተው እስከለወጡት ቀን ድረስ ከጥንት ጀምሮ በአራት ዘላቂ መደቦች የተከፈለ ነበር፡፡ መደቦቹ ዘላቂ የሆኑበትም ምክንያት ማንም ሰው የገዛ መደቡን አባል ያገባል እንጂ ከሌላ መደብ አባላት ጋር እንኳን ሊጋባ የአንድ ጊዜ የስጋ ግንኙነት እንኳን አያደርግም

ኸረ በሀሳቡም አይመጣም፡፡ ማንም ሰው ቢሆን በአለባበሱም የየትኛው ዘላቂ መደብ አባል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ዘላቂ መደቦቹ በስራ ክፍፍልና እንደዚሁም በክብርና ማረግ ቅደም ተከተል እነሆ፦

<u>አንደኛ ብራሀሚን ዘላቂ መደብ</u>፦ የዚህ መደብ አባላት ቀሳውስትና ምሁራን ናቸው፡፡ ለአማልእክቱ መስዋእት የሚያቀርቡ እነሱ ናቸው፡፡ የሌሎች መደቦች አባላት መስዋእት ሊያቀርቡ ሲፈልጉ፤ መስዋእቱን ወደ ብርሀሚኖቹ ወስደው ይሰጣሉ፤ ብርሀሚኖቹ ለአማልእክቱ ያቀርቡታል፡፡ ሀይማኖትና እውቀት በነሱ እጅ ነው ማለት ነው፡፡

<u>ሁለተኛ ከሻትሪያ ዘላቂ መደብ</u>፦ አባላቱ ወታደር፤ የጦር መሪ፤ መኳንንት ነገስት ይሆናሉ፡፡ አለም የነሱ ናት፡፡

<u>ሶስተኛ ባይሺያ ዘላቂ መደብ</u>፦ የባለሙያዎች መደብ ነው፡፡ ነጋዴ፣ አናጢ፣ ሀውልት ቀራጭ፣ ጠበቃ፣ ሸማኔ ወዘተ፡፡ ጋንዲሂ - የዚህ መደብ አባል ነበር፡፡

<u>አራተኛ ሹድራ ዘላቂ መደብ</u>፦ የዚህን መደብ አባላት ሶስቱ የላይኛዎቹ መደቦች አባላት እንደ ቆሻሻ ስለሚቆጥሩዋቸውና ስለሚፀየፏዋቸው እነሱ በተቀመጡበት ቦታም አይቀመጡም በእጃቸው እንኳን አይነኩዋቸውም፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኛ አገር ሰዎችም ጣና አካባቢ የሚኖሩትን የወይጦ ነገድ ልክ እንደነዚህ ሹድራዎች ያረጉዋቸው ነበር፡፡ ሰው የትም ቢሄድ ሰው ነው፡፡ ጨቋኝም አለ ነፃ አውጪም አለ፡፡ ወደዛሬ ታሪካችን ስንመጣ ደግሞ ዲሞክራት ሳይሆን እብሪተኛ እንግሊዝም አለ፡፡

የእንግሊዝን ትእቢት እንደ ተነፋ ፊኛ የሚያስተነፍስ ሰው እንደ ጋንድሂ ያለ የበጎ ሀይላት ተዋጊ እሾህም አለ፡፡

ቅድመ ጋንድሂ ለዘመናት ሰፍኖ በኖረው የህንድ እምነት የሹድራ መደብ አባላት ከሰው በታች ናቸው፡፡ ሰው የሚፀየፈውን ስራ እየሰሩ ነው የሚኖሩት፡፡ ቆሻሻ መጥረግ ቆዳ መፋቅ .... ወዘተ፡፡

አለም ጋንዲሂን ሲያስታውስ የማይበገረውንና የማይደፈረውን ሀያሉን እንግሊዝ ‹‹እባክዎትን በሰላም አገሮት ይግቡ›› ብሎ እጅ ነስቶ በፈገግታ ያስወጣ (ሌላ ሰው አድርጎት ቢሆን ግን በካልቾ ቂጡን ለጋውና

ከመጣበት ከሚመጣ ደሴቱ አደረሰው እንላቸው የነበረ።) የጀግኖች ጀግና ነው። ከሱ በፊት የሱን ተመሳሳይና ምናልባትም የበለጠ ስራ የሰራ ማለትም ጉልበተኛውን አንበሳ በደካማው በግ ጉልበት፣ ተንኮለኛውን አባብ በእርግብ የዋህነት ድል ያደረገ ኢየሱስ ነው። በዚህኛው አለም ቡድሀም፣ ማህቪራም፣ ሌሎችም አሉ። ጋንድሂም ኢየሱስን በኋላ ተዋውቆት ይሆናል እንጂ እዚህ የምታገቡት ሀይል ግን የሩቅ ምንጩ ማህቪራ ነው እንጂ ኢየሱስ አይደለም። እንግሊዝ ግን አራት መቶ አመት ብቻ ነበር የቆየው ጋንድሂ መጥቶ ጥይት ሳይተኩስ ድንጋይ ሳይወረውር ጥፊ እንኳን ሳይሰነዝር በሰላማዊ እምቢታ ሀይል ብቻ እስኪያሰናብተው ድረስ። ይህን የጋንድሂ አንድ እጁ የውጭ ጉዳዩን የለወጠውን ያህል፣ በሌላ እጁ የህንድን የውስጥ ጉዳይንም ሊለውጠው ተነስቶ ነበር ምን ያህል እንደለወጠው እርግጠኛ ባልሆንም። ከእንግዲህ ግን ሙሉው ለውጥ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው። ይኸውም አራት መቶ አራት ሺህ ስር ሰዶ የቆየውን ባንዲት ህንድ ውስጥ አራት የተለያዩ ህንዶች የሚኖሩበት ስርአት ጋንድሂ እና ዘመን ተባብረው ለወጡት። ከጋንዲሂ ወዲህ መደብ ቢኖር እንጂ ቋሚ ዘላቂ መደብ የለም። በልባችን እንዳገሩ ደንብ ሁለት መዳፋችንን አሳስመን ወደ ግንባራችን አሳልመን፣ በመጠኑ ጎምበስ ብለን በሰላማዊ ድምፅ «ናማስቴ!» እንላቸዋለን እኩል አፀፋውን ይመልሱልናል።

«ናማስቴ!» የሚለው ውብ ሰላምታ «በእርስዎ ውስጥ ላለው አምላክ እሰግዳለሁ» ማለት ነው። አፀፋውን ሲመልስልን እኛ ውስጥ ላለው አምላክ እየሰገደ ነው። ከውስጣችን አምላክ ነን፣ ውጪውን ሶስት የማይቀያየጡ ዘሮች ብንሆንም። አራተኛውም ሹድራ መደብን በምድርነቱ ይፀየፉትና አይነኩትም እንጂ በሩቅ «ናማስቴ!» ሳይሉት ይቀራሉ?

ማህተመ ጋንዲሂን «ናማስቴ!» ካልናቸው በኋላ አንባቢያንንም «ናማስቴ!»

መጋቢት 10 ቀን 1987

# ባለስልጣን

አይ! አሁንስ በዛ። ስለ አገራችንና ስለታሪካችን ስለ ባህላችን ጥሩ ጥሩውን ብቻ ነው'ንዴ መናገር ያለብን? ይሄማ ጉራ ከመንፋት በምን ተለየ? ደካማ ጎናችንስ አይነገርም? የዚያን የድንቅ ባህላችንን አስቀያሚ መልኩንስ አናሳይም? ‹‹በሽታውን የደበቀ መድሀኒት አይገኝለትም።›› ስለዚህ መድሀኒት ይገኛል የሚል ተስፋችን እጅግ የመነመነ ቢሆንም ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም። የክርስቲያን ልጅም ተስፋ አይቆርጥም። ከበሽታዎቻችን አንዱን ባጭሩ እተነትናለሁ መተንተን በልሳን እንዲል መፅሀፍ፡ የበሽታችን ስሙ ስልጣን ይባላል።

ተስፋ አረጋለሁ እንደ ዶስቶቭስኪ የሰው ልጅን ነብስ በጥልቀት የሚያሳየን የራሳችን የልብ-ወለድ ደራሲ ሲመጣ አንዱ አጉልቶ የሚስለው ገፀ ባህሪ የመስሪያ ቤት ዘበኛ አንዱን አስከፊ ገፅታችንን ይወክላል። ዘበኛ ስራው የመስሪያ ቤቱን ንብረት መጠበቅ ስሙ ሲሆን ወርቁ ስልጣን ነው። የዘበኛ ስልጣን ማለማመጥ ወይም መከልከል ነው። አቤት የለም ማለት ሲወድ! አይ አይሆንም ማለት ሲቀናው! እሷ ብቻ ነች ስልጣኑ። ቢሆንም ስልጣን ናት እንደልቡ ይሰለጥንባታል ይፈነጭባታል ይቦርቅባታል በልቡ።

መታወቂያችንን አይቶ ፈትሾ ማስገባት። ይሄ ሂደትዋን ያራዝማታል። እንደኛ መታወቂያችንን ለረዥም ጊዜ ያነበዋል አገላብጦ

ይመረምረዋል፤ መርማሪ መኮንን ይመስል ማለትም ለረዥም ጊዜ ባለስልጣኑ ዙፋን ፊት ያቆመናል፡፡

ሁለተኛ ‹ወዴት ነው?› ይለናል በመርማሪ መኮንን ድምፅ፡፡ እንነግረዋለን፡፡ ‹ማን ጋ ነው?› ይለናል እንነግረዋለን

‹‹ለምን ጉዳይ?›› ሲል ያፋጥጠናል፡፡

እንነግረዋለን

ያስባል ያስባል ያስባል፡፡ እያሰበ ሳይሆን እያስጠበቀን ነው፡፡ እየሰለጠነብን ነው፡፡ በስልጣኑ እንዲለ ሰምና ወርቅ ነው የዘበኞችን ነገር፡፡ መግባት መብታችን መሆኑን ዘበኛው አያውቅም፡፡ እሱ የሚያውቀው እንዳንገባ የመከልከል ስልጣን እንዳለው ብቻ ነው፡፡ ድሮ የትምህርት ሚኒስቴር ዘበኛ አንዱን ባለጉዳይ እንዲህ ሲለው ሰማሁት ‹‹እንግዲያማ ዝም በል! ልገተር መስለህ እዚህ የቆምኩት ልከለክል ነው እንጂ፡፡››

‹‹ምን ጉዳይ?›› ብሎ ሲጠይቀን እንደ እርጎ ዝምብ በማያገባው ጉዳይ ጥልቅ ማለቱ አይታየኝም፡፡ እሱ ጉዳያችንን ካልተናገርን መግባት ሊከለክለን መቻሉን ነው የሚያውቀው፡፡

በመጨረሻም በቃልም ይሁን በእጅ እንቅስቃሴ ‹‹እሺ ግቢ/ቡ›› ሲለን ውለታ እንደዋለልን ይቆጠራል፡፡ ሊከለክለን ይችል ነበራ! በዚህ በበጎ ስራው ብርሀን የነበስ ጭጋግ እንደ መብራት ይላል፡፡ በትንሹ በጥንጥየው፡፡

ከእዮብ በተማርነው ትዕግስት ዘበኛውን አልፈን ስንገባ ቢሮክራቱን (የቢሮ ባለስልጣኑን) እናገኛለን፡፡ ከቢሮክራቱ ፊት ስንቆም (እሱ ቁጭ ብሏል ከጠረጴዛው ኋላ በተሽከርካሪ ወንበር) አሁንም ያው የዘበኛው ፊት እንደቆምን ያህል ነው፡፡

ቢሮክራት ስራው ወረቀታችንን አንብቦ ፈርሞበት ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ ነው፡፡ በቃ፡፡

አሄሄ! ምን ይበቃል? ቢሮክራት'ኮ ሰምና ወርቅ ነው፡፡ ሰሙ ወረቀቶቻችንን ፈርሞ ማስተላለፍ ሲሆን ወርቁ ስልጣን ነው፡፡ ስልጣን

ማለት ደሞ ባለጉዳዩን ማመላለስና ማለማመጥ ነው ደጅ ማስጠናት። ቢሮክራቱ ወረቀቶችን ወዲያውኑ ፈርሞ ካስተላለፈልንማ ስልጣኑ የት ላይ ነው? በምን ይታያል? እኛስ እሱ በስራ ብዛት የተወጠረ ባለስልጣን መሆኑን እንዴት እናውቃለን? እሱስ ስልጣን ያለው ባለስልጣን መሆኑን በምን ያረጋግጣል? (እዚህ ላይ ለጉቦ የሚያመላልሰውን ባለስልጣን ማለቴ አይደለም። የኛ ጉዳይ ጥያቄ ሊነሳ የማይችልበት ነው እንበል)

ባለስልጣን እኛን ለማገልገል ወረቀታችንን ለመፈረም በደሞዝ የተቀጠረ ሰራተኛ መሆኑን አይደለም የሚያውቀው። እሱ የሚያውቀው ፊርማውን እንዲፈርምልን ከፈለግን ደጅ መጥናት እጅ መንሳት ግንባር ማስመታት እንዳለብን ነው።

ባለስልጣን ባይፈርምልን ይመረጣል። መፈረም ካለበት ቀስ ብሎ ተንቀባሮ ሰነባብቶ ያን የሚጠማውን የኛን ልምምጥ ጠብታ በጠብታ ጠጥቶ መሆን አለበት። ‹‹ቀላል እንዳይመስላችሁ የሳቸውን ፊርማ ማግኘት›› ይባልለታል። የሳቸውን ፊርማ ከማግኘት የድሮ ሴት ወይዘሮን ማግኘት ይቀላል።

የስንቱን ሰው ጊዜ በከንቱ አጥፍቶ፣ ስንቱን ሰው በብስጭት አብግኖ ሲያበቃ ባለስልጣን ነኝ ይላል በልቡ።

ባለስልጣን ሆይ! በዘበኛ መልክህም ሆነ በቢሮክራት መልክ ዞሮ ዞሮ የእጅህን ይስጥህ! ይህን ከፃፍኩ በኋላ ‹‹ዘበኛም'ኮ ሰው ነው ቢሮክራትም ሰው ነው። እናት አባት ወንድም እህት ሚስት ልጆች ያሉት ነው ልክ እንደኛ›› የሚል ሀሳብ መጣብኝ። እሱን ተወው! እንዴት ሊሆን ይችላል? ምናልባት በልጅነቱ ሰው ነበረ በለኝ እንጂ ዛሬ ግን ባለስልጣን ነው እሱኑ ጠይቀው።

<u>ማስተካከያ</u>

ለዚች ማስተካከያ አስፋው ዳምጤን አመሰግነዋለሁ በአንባቢያን ስም። ቢሮክራሲ ወደዚህ አገር ሲመጣ በሽታ ሆነ እንጂ ጤነኛ ቢሮክራሲ'ኮ ብዙ ሰዎች ለሚሰሩበት መንግስታዊም ሆነ ግላዊ ድርጅት

እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲያውም ያለ ቢሮክራሲ መዋቅር እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩት ሰዎች ንግስት እንደሌላቸው የቀፎ ንቦች ይሆናሉ፡፡

ቢሮክራሲ ሁለት አስፈላጊ ጠባዮች አሉት የስራ ክፍፍል እና የስልጣን ተዋረድ፡፡ በነገራችን ላይ ትጉ የሆኑ እና ሰው የማያመላልሱ፥ የባለጉዳዩን ወረቀት ወዲያው አንብበው ወዲያው ፈርመው ወድያው የሚያሰናብቱ አንድ ቢሮክራት አጋጥመውኝ ያውቃሉ፡፡ ዘይገርም!

**የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ መስከረም 1985**

**ግንቦት 27 ቀን 1987**

# ጥንታውያን የጥበብ ሰዎችና ስራዎቻቸው

ወጣቶች አንባቢያንና ደራሲያን ባመለከቱኝ መንገድ እየሄድኩ ነው። ደጋግሞ የመጣ ጥያቄ ስለሆነ ለሚቀጥሉት አያሌ ሰንበቶች የኛን አለም ስለሚነኩ ታላላቅ ጥንታውያን ስነ ጥበባዊ መፅሀፍት ባጭር ባጭሩ እናሰፍራለን።

## ጊልጋሜሽ

...ዛሬ ኢራቅ በሚባለው ሁለት ወንዞች በሚፈሱበት አገር፣ ጥንት ሱመራዊያን ከሚባሉት የዚያን አካባቢ ስልጣኔን ከጀመሩት ነገስታት አንዱ በግምት በሶስት ሺህ አመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ይኖር ነበር።

ጊልጋሜሽ ከሰውና ከአምላክ የተወለደ ኡሩክ የምትባለውን ከተማና አካባቢዋን ገጠር የሚገዛ እጅግ መልከ ቀና ጎበዝ ንጉስ ነበረ። የኖረውም ከክርስቶስ ልደት በፊት ከሁለት ሺህ አምስት መቶ አመት ቀድሞ ነበረ።

ጊልጋሜሽ አደንን እንደ ነብሱ ይወድ ነበረ። ከእለታት አንድ ቀን እንደ ልማዱ አንበሳንና የመሳሰሉትን ሊያድን ሩቅ ጫካ ሄደ። እና ሲያደፍጥ አንድ አውሬም እንዳደፈጠበት መሆኑ ይታወቀዋል። አደገኛ ሰአት። ጊልጋሜሽ ግን ቢጠነቀቅ እንጂ አይፈራም። ሁለቱም እኩል እያደፈጡ ሁለቱም እኩል ዘለሉ። እንደቆሙ እንደተፋጠጡ ደርቀው ቀሩ።

አውሬው አውሬ ሳይሆን ሰው ነው፡፡ ሰውየው ግን ቆዳው እንደ አውሬ ወይ እንደ ዝንጀሮ ፀጉር ለብሷል፡፡ መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ የያእቆብ ወንድም ኤሳው እንደለበሰው አብሮት እንደተፈጠረ ፀጉር ማለት ነው፡፡ ወይም የዝቋላው አቡዬ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንደነበራቸው ፀጉር፡፡ እነዚህ ሁለት ጀግኖች እንደተፋጠጡ ቀስ ብለው ሁለቱም እኩል ጨቤ የጨበጠ እጃቸውን ዝቅ አደረጉ፡፡ አብረው ወደ ኡሩክ ከተማ ሄዱ፡፡ ሲበዛ የሚዋደዱና የሚግባቡ ጓደኛሞች ሆኑ፡፡ አብረው አደን መውጣት ትልቁ ደስታቸው ነው፡፡

እኛ ኮሌጅ ሆነን (እዚህ አራት ኪሎ) የጥንት ታሪክ አስተማሪያችን ሚስተር ሀሎዲሂን የተባሉ ሩሲያዊ ነበሩ፡፡ ወጣት ሆነው የገዥ መደብ ተወላጅ ስለነበሩ፤ የነቭላድሚር ኤሊች ሌኒን አብዮት ሲፈነዳ፤ ሸሽተው ወደ ጎረቤት አገር ወደ ቡልጋሪያ ሄዱ፡፡ ቆይቶ ቆይቶ ቡልጋሪያ አገርም አብዮት ፈነዳ፡፡ ወደዚህ ወደ አዲሳባ ሸሽተው መጡ፡፡ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ እያስተማሩ እያለ የነደርጉ አብዮት ቢፈነዳ ወደ አውስትራሊያ ሸሽተው ሄዱ፡፡ እኚህ የስደት ሰው እዚህ እኛን ስለጥንት ታሪክ ሲያስተምሩን አንዳንድ ነጥቦች ከራሳቸው ይጨምሩባቸዋል፡፡ ደስ እንዲለን፡፡ መጨመራቸው መሆኑን ሳይደብቁን፡፡ ስለነጊልጋሜሽ አደን እቺን የምትከተለውን ይጨምሩበታል፡፡

ጊልጋሜሽና ኤንኪዱ እንኳን አብረው ለየብቻቸውም ቢሆን ማንም አውሬ የማያመልጣቸው አዳኞች ናቸው፡፡ ስለዚህ አውሬ መግደል ወይም ማጥመድ ሲሰለቻቸው፤ "በቃ እኔና'ንተ ይዋጣልን" ይባባላሉ፡፡ ያኔ በቃ አንዱ ረዥሙን ምልምል ዛፍ ባንድ እጁ ይነቅልና ሌላው ላይ አነጣጥሮ ይወረውረዋል፡፡ ያኛው ወይ ዘወር ይልና ያመልጣል ወይም ዛፉን በሁለት እጁ ይቀልባትና መልሶ እዚያኛው ላይ ይወረውርበታል፡፡ እንዲህ ሲወዳደሩ ውለው አንድ ሁለት አውሬ ይዘው ወደ ከተማ ይመለሳሉ፡፡

ጊልጋሜሽ ማለት በሱመር ቋንቋ "አባት" "ጀግና" ወይም "ሽማግሌው" ማለት ነው፡፡ ውቢቱ አስታርቴ የተባለችው ሴት የፍቅር አምልክት ወርዳ ስታየው ከጀግናው ከጊልጋሜሽ ጋር ፍቅር ይይዛታል፡፡

ጊልጋሜሽ ግን በንቀት አይን ያያትና "ለሴት ፍቅር ጊዜ የለኝም፤ ይቅርታሽን። አደን መሄዴ ነው። በይ ቻው!" ብሎ ይለያትና "ኤንኪዱ!" ብሎ ይጣራል። "ና አደን እንሂድ!" ተያይዘው ሁምባባ የተባለ ሀይለኛ ጆግና ወደሚጠብቀው ጫካ ይሄዳሉ።

ሴት ልጅ አማልክት ሆና ይቅርና የሄዋን ልጅ ሆና እንኳ ቢሆን ፍቅርን ሲንቁባት አትወድም አደገኛ ናት። አስታርቴ ጌልጋሜሽን ትቀጣው ዘንድ ወደደች። ጌልጋሜሽን ወግቶ ይገድለው ዘንድ አንድ ኮርማ ፈጥና ላከች። ጊልጋሜሽና ኤንኪዱ ተጋግዘው ኮርማውን ገደሉት። አስታርቴ በንዴት በገነች። በኤንኪዱም ላይ የሚያማቅቅ፣ የሚያመነምን በሽታ ላከችበት። ጆግናው ኤንኪዱ ሲማቅቅ፣ ሲመነምን ሰንብቶ ‹‹እቤት ያን ሁምባባን እንዴት ተጫወትንበት! በል ጊልጋሜሽን፣ ወደዚያ ወደሚጠብቀኝ የትቢያ ቤት እየሄድኩ ነው›› አለና እንዳለውም ሄደ። በፈገግታ ሞተ።

ጊልጋሜሽ የጓደኛው ሞት መረረውና አዋቂዎችን ሁሉ ሰብስቦ ስለሞት መድሀኒት ጠየቃቸው። እንዲህም አሉት ‹‹ጥንት በባቢሎናዊው የጥፋት ውሀ ጊዜ ሰው ሁሉ ሲያልቅ ኡትናፒሽቲም ግን ሞትን አምልጦ በምእራብ በኩል ተጉዞ የፀሀይን መጥለቂያ አልፎ ሩቅ ሩቅ ዘልቆ ዛሬ እዚያ በሀይወት ይገኛል››

ጊልጋሜሽም መንግስቱን ትቶ፣ ውድ ከተማውን ኡሩክን ለቆ ኡትናፒሽቲምን ፍለጋ ብዙ አደጋዎችን አሸንፎ ተጓዘ።

በመጨረሻም አንድ ትንሽ ወንዝ ተሻግሮ ቅድመ አያቱ ኡትናፒሽቲም ጋር ተገናኘ። ጊልጋሜሽ ማን እንደሆነና ለምንስ እንዴትስ እንደመጣ ሲነግረው ኡትናፒሽቲም እጅጉን ተደሰተ። ‹‹ይሄ ነው የኛ ልጅ!›› ብሎ አቅፎ ሳመውና ለብዙ ቀን አስተናገደው። ከዚያም የሞት መድሀኒት የሆነችውን ቅጠል ሰጠውና አሰናበተው።

ጊልጋሜሽ አያሌ ሰአታት ከተጓዘ በኋላ ውሀ ጥም ያቃጥለው ገባ። አንድ ምንጭጋ ደረሰ። እየተጣደፈ ተንበረከከና ቅጠሊቱን አስቀምጦ

ውሀውን በሁለት መዳፉ እያፈሰ ጠጣው። አይ መጣፈጡ! ጊልጋሜሽ ፊቱና ራሱ ላይ ውሀውን ሲጨምረው አይ ደስ ማለቱ!

መቼም ደስታ እንዳያልቅ የለም! ጊልጋሜሽ ደስታውን ጨረሰና ተነሳ። ቅጠሊቱ ኧረ የኡትናፒሽቲም ያለህ! ቅጠሊቱ ካስቀመጣት ስፍራ የለችም! አይኑን ወርወር ሲያደርግ አየው እባቡን። የሞት መድሀኒት የሆነችውን ቅጠሊቱን ባፉ እንደያዘ እየተንፏቀቀ ዳዋ ውስጥ ገባና ጠፋ።

## ኢሊያድ

አሁን የማወራላችሁ ‹‹ኤሊያድ›› ስለተባለው ላለፉት ሶስት ሺ ሁለት መቶ አመታት ምእራቡን አለም ሲያስደስት ስለኖረው መፅሀፍ ነው። ከዚህ በፊት የሞት መድሀኒት ፍለጋ ስለተጓዘው ስለ ንጉስ ጊልጋሜሽ ያጫወትኳችሁ መፅሀፍ ‹‹ኢልያድ››ን በግምት በአንድ ትውልድ ቀድሞታል። በግሪክ አገር አንድ ሺ ሁለት መቶ አመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ አይነ ስውር አዝማሪና ተራኪ ነበር ሆሜር የሚሉት። እጅግ በተወደደ ስነግጥም ነበር ለአድማጮች ያንኑ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ የሰሙትን የፍቅርና የጦርነት ገድል የሚተርክላቸው። ------በኦሎምፒያ ተራራ ላይ አማልክቱ አምብሮዚያ የተባለውን ከማር ወለላ አስር እጅ ይበልጥ የሚጣፍጠውን መጠጣቸውን የሚጠጡበትና ስሙን ያልያዝኩት ተአምራዊ ምግባቸውን የሚበሉበት አዳራሽ ነበረ የአማልክቱ የበላይ የሆነው ኬዮስ (CHAOS) ግብር የሚያበላበት ነው።

ከእለታት አንድ ቀን እየተበላ እየተጠጣ እያለ የአዳራሹ በር ይከፈትና ከወርቅ የተሰራ ኳስ እየተንከባለለ ይገባል። ኬዮስ የተባለው ነው የወረወረው። ኬዮስ ያዘባርቃል ይበታትናል ያበላሻል ያጠፋል፣ ጦርነት ያመጣል አባ ዘባርቄ ልንለው እንችላለን።

አባ ዘባርቄ የወረወራትን የወርቅ ኳስ አንስተው ቢያዩዋት አጭር መልእክት ተፅፎባታል *‹‹ከሁሉ ውብ ለሆነችው የሚሰጥ››* ኳሱን ለሚገባት ሴት አምላክ ይሰጣት ዘንድ አምጥተው ለኬዮስ ስጡት። ተቸገረ፥ ከሁለት የተዋቡ ሶስት ናቸው። ኳሱን ለሄራ እንዳይሰጥ ለሚስቱ

አዳልቶ ነው እንዳይሉት ፈራ፡፡ የጥበብ አምላክ ለሆነችው ለአቴና እንዳይሰጥ ልጅ ናት ሙሉ የጦር ትጥቋን እንደታጠቀች ከጭንቅላቱ የወጣች፡፡ ከአብራኩ የወጡ ሌሎች ናቸው፡፡ የፍቅር አማልክት ለሆነችው ለአፍሮዳይት እንዳይሰጥ ሚስቱ ትጠላዋለች ምን ተሻለ? ‹‹ውሰዱና ለልኡል ፖሪስ ስጡት፡፡ እሱ ለመሰለችው ይሸልማት›› ብሎ ከጣጣው አመለጠ፡፡

ልኡል ፖሪስ ትሮይ ከተማ አጠገብ በጐች ሲያግድ ተገኘ፡፡ ሶስቱም ሴቶች አማልክት በየበኩላቸው እየመጡ ጉቦ ሊሰጡት ሞከሩ - የግሪኮችም የሮማውያንም የሌሎችም አህዛብም አማልክት በሰው አምሳል የተፈጠሩ ናቸውና፡፡ ሄራ መጣችና ኳሷን ለኔ ከሰጠኸኝ ሙሉ ደስታ ያለው ጋብቻ እሰጥሀለሁ አለችው፡፡ አቴና መጥታ ለኔ ከሰጠኸኝ ከጠቢባን ሁሉ የላቀ ጠቢብ አደርግሀለሁ አለችው፡፡ አፍሮዳይት መጣችና የሞቀ ፈገግታ እያከናነበችው ‹‹ለኔ ከሸለምከኝ ከሴቶች ሁሉ በላይ የተዋበችውን ሴት እሰጥሀለሁ›› አለችው፡፡ ምን ጊዜም ቢሆን ለጤነኛ ጎረምሳ ውብ ሴት ትበልጥበታለችና ፖሪስ የወርቅ ኳሱን ለአፍሮዳይት ሰጣት እሷም በቃሏ ፀናች፡፡

የትሮይ ልኡል ፖሪስ በግሪክ አገር ሲጓዝ ቢመሽበት ንጉስ ሜኒላውስ ግቢ ሄዶ አሳድሩኝ አለ፡፡ ንጉስ ሜኒላውስና ንግስት ሄለን ተቀብለው አስተናገዱት፡፡ ከሄለን ጋር ፍቅር ያዘው እሷም አፀፋውን መለሰችለት፡፡ ተያይዘው ጠፉና ወደ ውቢቱ ታላቂቱ ሀብታሚቱ ከተማ ወደ ትሮይ ሄዱ፡፡

ሜኒላውስ የግሪክን ነገስታትና የጦር መኳንንት ‹‹ሚስቴን ተነጥቄ ክብሬ ተዋርዷልና ወደ ትሮይ ዘምቼ ሚስቴን ላመጣ ስለሆነ እግዙኝ›› አላቸው፡፡ እንዘምታለን አሉ፡፡ ለሜኒላውስ ክብር ብለው ይመስላል እንጂ ነገሩ ግን ሌላ ነው፡፡ ትሮይን ወርረው ያን ሁሉ ሀብቷን ለመዝረፍ ሄለን የሚሏት ሰበብ ተገኘች፡፡ ውቢቷ ግን እውነትም አፍሮዳይት እንደተነበየችው ነው፡፡ እንደ ገፀ ባህሪ ሲያያት ለሌላው እንዲህ ይለዋል ‹‹እየው ያ ፊት ነው ሺ መርከብ ያስዘመተው፡፡››

ግሪኮቹ አስቀድመው ቢያውቁት ኖሮ ባልዘመቱ። ትሮይን ከበቡዋት እንጂ ሊያንበረክኳት ግን አልቻሉም። አስር አመት ሙሉ ተዋጋቻቸው። አቤት ውጊያዎች! አንዳንዶቹ አማልክት ሳይቀሩ በሰው ተመስለው ገብተው ተዋግተዋል። ከግሪኮች ጀግኖች አንዱ ደዮ ሚሜደስ አንድ ቀን ተነሳበትና ጋሻና ጦር ይዞ ገባ - አልቻለም! ለትሮይ አግዘው የሚዋጉት አማልክት እንኳ አልቻሉትም። እንዲያም ሆኖ ግን ትሮይ አልተሸነፈችም።

አዲስዮስ ጀግና ብቻ ሳይሆን ብልህ ጭምር ነው። የጥበብ አማልክት የሆነችው አቲና በጣም ትወደዋለች ትጠብቀዋለች። አዲስዮስ ብልሀት አሰበ--------

---የትሮይ ሰዎች አምላካቸውን በፈረስ መልክ ያመልኩታል። ግሪኮቹ ብዙ ትልልቅ ዛፍ ቆረጡና አነስተኛ ቤት የሚያክል የፈረስ ሀውልት ሰርተው ሲያበቁ ትሮይ ከተማ መግቢያ በር አጠገብ ትተውት ወደ መርከቦቻቸው ገብተው ወደ አገራቸው ሄዱ። የትሮይ ኗሪዎች በደስታ ፈነጩ! መብላት መጠጣት ሆነ በከተማይቱ ውስጥ። አንዳንዶቹም ያንን ግሪኮች ትተውት የሄዱትን የእንጨት ፈረስ ተጋግዘው እየጎተቱ አስገቡትና የከተማዋን በር ዘግተው ወደ መደሰት መደነሳቸው ተሰማሩ። አዳሜ በወይንና በፍቅር እየሰከረ ሄደ።

እዚያ ግሪኮቹ ትተውት የሄዱትና የትሮይ ኗሪዎች ጎትተው ያስገቡት የእንጨት ፈረስ ውስጥ ጥቂት ምርጥ የግሪክ ወታደሮች አድፍጠው ቆይተዋል። አሁን በፍጥነት ወጡና የከተማዋን በር ከፈቱ። እነ አዲስዮስም በመርከቦቻቸው ጥቂት ራቁ እንጂ በጭለማ ተገን ተመልሰው ወርደው ከተማይቱ በር አጠገብ አሰፍስፈው ይጠብቃሉ። በሩ ተከፈተ። ገቡ። ትሮይ አለቀላት። ከሞት የተረፉት የትሮይ ኗሪዎች ለባርነት ተሰጡ። ጥቂት ማምለጣቸው አይቀርም። ከነዚህም አንዱ ኤልያድ የተባለ የልኡል ፖሪስ ወንድም ሲሆን፣ እሱ ሄዶ ነው የሮማን ከተማ የቆረቆራት ይባላል። ኤልያድን በቅርቡ ለማንበብ ዕቅድ ያላቸው አንባቢያን የሚከተለውን ባያነቡ ይመረጣል። ከሌሎች አንባቢያን ጋር

ወደፊት! የትሮይ ጦርነት አስረኛ አመቱ ላይ ነው፡፡ ኤልያድ የሚደረድርልን ድርጊቶች በዚህ ወቅት በአርባ ቀናት ውስጥ ይፈፀማል።

በግሪኮች ካምፕ ወይም የጦር ሰፈር ያ ወደር የሌለው ጦረኛ አኪሌስ አኩርፎ ድንኳን ውስጥ ተኮፍሷል እሱ በምርኮ ያመጣትን ቆንጆ ሴት የግሪኮች ዋና የጦር አዛዥ የሆነው አጋሜምናን ስለወሰደበት ‹‹ከወሰድክብኝ እንግዲያው እኔ ደግሞ እምቢ አልዋጋልህም!›› ብሎ ነው፡፡

ግሪኮቹ አኪሌስ በሌለበት ሲዋጉ የትሮይ ጎበዞች በጀግናው ሄክተር እየተመሩ ሲያጭዷቸው ዋሉ፡፡ ከወደቁት መካከል አኪሌስ በሙሉ ልቡ የሚወደው ጓደኛው ፖትሮክሎስ ይገኝበታል፡፡ አኪሌስ ተናደደ በገነ - ከኩርፊያው ንዴቱ በለጠበት - በነጋታው ውድ ጓደኛውን ፖትሮክሎስን ለመበቀል ታጥቆ ወጣ፡፡

የትሮይ ተወዳጅ ጀግና ሄክተር ህፃን ልጁንና ውብ ሚስቱን ስሞ ተሰናብቶ ታጥቆ ይወጣል፡፡ ሄክተርና አኪሌስ ብቻ ለብቻ ይገጥማሉ፡፡ ከሁለት አንዳቸው ድንገት ወኔው ይከዳውና ወደ ኋሊት ዞሮ ይፈረጥጣል፡፡ ሌላኛው ሲያባርረው ያኛው ሲሸሽ ትሮይን የከበባትን ክብ ይዞሩታል፡፡ አቤት ያቺ ሽሽት ስታሳዝን!

በሚቀጥለው ውጊያ ላይ አኪሌስ የጦር ሰረገላው ላይ ቆሞ በፍጥነት ይጋልባል፡፡ እየጋለበ ካለፈ በኋላ ፖሪስ ሊወጋው ቀስቱን አነሳ ፍላፃውን አነጣጠረ---------

--------- አኪሌስ ሲወለድ በአንድ አምላክ ምክር እናቱ ወደ ለቴ (LETHE) ወንዝ ወሰደችውና ነከረችው - በሁለት እጆቿ ሁለት ተረከዙን ይዛ ቁልቁል ንክር አድርጋ አወጣችው፡፡ ውሀው ቆዳውን ምንም የጦር መሳሪያ እንዳይበሳው አድርጐታል---------

--------- ጦረኛው አኪሌስ እየጋለበ አለፈ፡፡ ፖሪስ ፍላፃውን አነጣጠረ፡፡ ለቀቀ፡፡ ፍላፃዋ ሽው ብላ በራ ተወርውራ የአኪሌስ ተረከዝ ውስጥ ተሰካች፡፡ ደም በደም! አይ የአኪሌስ እናት! የህፃኑን ተረከዞች

የያዙት እጆችሽ ናቸው ወንዙ ውስጥ የተነከሩት እንጂ ተረከዞቹንማ ውሀው አልነካቸውም ጦር ሊበሳቸው ይችላል፡፡

ጦረኛው አኪሌስ እንዲህ ሆኖ ሞተ፡፡ ከምድር በታች የሚገኘው ጋዲዝ (GADES) የተባለው የሙታን አገር ውስጥ ከውድ ጓደኛው ከፖትሮክሎስ ጋር እንደሚገናኙ ተስፋ እናደርጋለን ---------

--------- በቅርቡ ዘመናት የሚታመነው የትሮይ ጦርነት የእነ ሆመር ፈጠራ ነው እየተባለ ነበር፡፡ ማለትም ትሮይ የሚሏት የለችም፡፡ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ግን ሀይን ሪክ ሽሊማን የተባለ ወጣት ኤሊያድን አነበበና ከትሮይ ጋር ፍቅር ያዘው፡፡ ትሮይ የእውነት ጦርነት ያቃጠላት ከተማ ናት ብሎ አመነ፡፡ ቆፍሮ ሊያገኛት ቆረጠ፡፡ እንዲያ ለማድረግ ብዙ ወጪ ስለሚጠይቅ አስቀድሞ ሀብታም መሆን አስፈለገው፡፡ ሽሊማን በትጋት እየሰራ በቢዝነስ አለም የተዋጣለት ባለፀጋ ሆነ፡፡ ተነሳና ወደ ቱርክ ገሰገሰ፡፡ ከዚያ ተነስቶ በግምት እዚህ ናት የትሮይ ከተማ ብሎ ያመነበትን ቦታ አስቆፈረ፡፡ የትሮይ ከተማ ተገኘች፡፡

ስለ ግሪክ ምርቃት

## አዲስዮስ

ባለፈው ፅሁፍ ኤሊያድ ስለተባለው ሆሜር የደረሰው በውብ ግጥም ተፅፎ የሚገኘው ረዥም ልብወለድ አጫወትኳችሁ ግሪኮቹ ጦረኞች የትሮይን ከተማ ከበቧት እንጂ አስር አመት ሙሉ ገትራ ያዘቻቸው፡፡ በአስረኛው አመት በአዲስዮስ ብልሀት ትሮይ ድል ተመታች፡፡ ተቃጠለች፡፡ ግሪኮቹ የተገኘውን ሀብት ዘርፈው በህይወት የተረፉትን የትሮይ ኗሪዎች ለባርነት ለመሸጥ ተከፋፍለው ወደ አገራቸው ተመለሱ፡፡ ንጉስ አዲስዮስ ግን የባህሪ አምላክ ፖሳይደም (Poseidom) ጠምዶ ስለነበረ አገሩ ለመግባት ሌላ አስር አመት ፈጀበት፡፡ በወጣ በሃያ አመቱ የኢታካ መኳንንት ሙቷል ብለው ስላሙት ሚስቱን ፔኔሎፒን (Penelope) ለማግባትና ለመንገስ ሽሚያውን ተያያዙት፡፡ ልጁን ቴሌማኩስን ደጋግመው አድፍጠው ሊገድሉት ሞከሩ፣ ግን አባቱን

አዲስዮስን በጣም የምትወደው የጥበብ አምላክ የሆነችው አቴና (Athens) ሙከራቸውን መላልሳ አከሸፈችባቸው።

መኳንንቱ አዲስዮስ ግቢ እየዋሉ እያደሩ እየበሉ እየጠጡ ብዙውን ንብረቱን አባከኑበት። ንግስት ፔኔሎፒንም አንዳችንን ምረጪ ብለው አስጨነቋት። እሷም እንዲህ አለቻቸው ‹‹ለክረምቱ የሚሆን ሱፍ ልብስ እየሸመንኩ ነው። እሱን ሰርቼ እስክጨርስ ጊዜ ስጡኝ›› እሺ አሉዋት ስትሸምን ትውልና ስታበቃ ቀን የሰራችውን ማታ ልትተኛ ስትል ትፈታዋለች። የማያልቅ ስራ ሆነላት።

አዲስዮስና አብረውት የዘመቱት ጎበዛዝት መርከባቸውን ተሳፍረው ወደ አገራቸው ጉዞ እንደጀመሩ ከጥቂት ቀን በኋላ አጂጂያ የተባለ ደሴት ደረሱ። የደሴቱ ንግስት ካሊፐሶ (Calypso) ትባላለች። ስሟ ‹‹ደባቂ›› ወይም ‹‹ሸሻጊ›› ማለት ነው። ደሴቱ ውስጥ አሳማዎችም በጎችም ከብቶችም አሉ። ከነዚህም ብዙዎቹ ሰዎች ናቸው በማጂክ የእንስሳት መልክ አልብሳ ደብቃቸው ነው እንጂ። ያቺ ምትሀተኛ ሸሻጊ ሌሎች መርከበኞች ወደ አጂጂያ ሲመጡ ካሊፐሶ እነዚያን መልካቸው ወደ እንስሳነት የተለወጠውን የቀድሞ መርከበኞች እያሳረደች እያስጠበሰች እያስቀቀለች ታበላቸውና እነሱን ደግሞ ወደ እንስሳነት ትለውጣቸዋለች። ከአዲስዮስ ጋር ፍቅር ስለያዛት እሱ ይሄ አደጋ አይደርስበትም። እንዲያውም ካገባሽኝ ለዘለአለሙ እንዳትሞት አደርግሀለሁ ትለዋለች። ደግሞ ትችላለች። አዲስዮስ ግን ልቡ ወደ ሚስቱ ፔኔሎፒ እና ወደ አገሩ ወደ ኢታካ ነው። ከሰባት አመት የግዴታ መስተንግዶ በኋላ አዲስዮስ ተለቀቀ። የአማልእክት አለቃ ዚዮስ መልክተኛውን ተረከዙ ላይ መብረሪያ ክንፍ ያለውን ሄርሜስን ላከባት ‹‹አዲስዮስን ልቀቂው አገሩ ይግባ›› ይላታል። አገሩ ለመድረስ ግን ሌላ ሶስት አመት ይወስድበታል።

ልጁ ቴሌማኩስ አሁን የሀያ አመት ጎረምሳ ነው። ስለ አባቱ መኖር አለመኖር ለማጣራት ካገሩ ይወጣል። ሽማግሌና እጅግ አስተዋይና ተወዳጅ ወደ ሆነው ወደ ኔስተር (Nestor) አገር ይሄዳል። ኔስተርም ጀግኖቹ ከአስር አመት በፊት ከትሮይ ጦርነት ሲመለሱ ብዙዎቹ በልዩ

ልዩ አደጋ ምክንያት ሳገራቸው መሬት ሳይበቁ ቀርተዋል፡፡ አቤት በጉዞው ላይ ስንቱ ጀግና ረገፈ! ስለ አዲስዮስ ግን ምንም የታወቀ ነገር የለም፡፡

ቀጥሎ ቴሌማኩስ ወደ ንጉስ ማኔላውስ ሄዶ ጠየቀ፡፡ አዲስዮስ በህይወት እንዳለ ነግሮት በቅርቡ አገሩ ሳይገባ አይቀርም አለው፡፡

እንግዲህ አዲስዮስ አገሩ ለመግባት አስር አመት በባህር ሲንዝና አብረውት ለዘመቻ ወጥተው ከነበሩት ውድ ጎበዛዝት ጋር አንድ በአንድ ወይም እያሌ በእያሌ አስደንጋጭ ወይም አስጨናቂ ወይ አስደናቂ ሁኔታዎች አጋጥመውታል፡፡ ከነዚህም ለናሙና እና ለቅምሻ ያህል ሁለቱን እነሆ፣

አሁዱ ይላችኋል የሊቲን ወንዝ ያህል በጠራ በተጣራ ግሪክኛ፤ አዲስዮስ በአቲና እርዳታ እና በራሱ ጉልበት ብልሀትም ጎበዝነትም የአስር አመቱን አደጋ የበዛበት ጉዞ ፈፅሞ አገሩ ገብቶ ከዚያም መልኩን በተቻለ መጠን ለውጦ (ሀያ አመትም ለውጦት መጥቶ) ምናልባት ምሳ ፍለጋ የመጣ ተራ ድሀ ሽማግሌ መስሎ ወደ ልዩ ቤተ መንግስቱ ገባ፡፡

አብዛኛውን በአይኑ ብርሀን እየተመራ የሚኖረው የሰው ልጅ ከሀያ አመት መለያየት በኋላ አዲስዮስን እንኳን ሊያውቀው ሊጠረጥረውም አልቻለም፡፡ ውሻ ግን! ውሻማ በጠረንህ ነው የሚያውቅህ፡፡ አዲስዮስ በቡችላ እድሜ ትቶት የሄደው ውሻ አሁን አርጅቷል፤ እድሜው ወደ ማለቂያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ጠረንን ለይታ የምታውቀው አፍንጫው ግን አዲስዮስን ባንድ አፍታ አወቀች፡፡

ውሻው በደስታ እየጮኸ እየሮጠ መጥቶ ያ እራት ሊቀላውጥ የመጣውን ሽማግሌ በውሻ አስተቃቀፍ ዘልሎ አቀፈው፡፡ አዲስዮስን የፈነቀለውን ደስታ ለአብዛኛው አንባቢ መንገር አያሻውም፡፡ ሽማግሌው ውሻ ሽማግሌ ጌታውን ከሃያ አመት ናፍቆት በኋላ ሳያስብ ሲያገኘው ጊዜ ልቡ በደስታ ፈነዳች፡፡ ሽማግሌዎቹ እንደተገናኙና ናፍቆታቸው ወደ ደስታ እንደተለወጠች ውሻው ነብሱ አለፈች፡፡ እቺ የስነ ፅሁፍና ተባብሮም የጓደኝነት ታሪክ (ያውም እውሩ ሆሜር የሚዘፍናት) ከኤልያድ

ከአዲስዮስም ውብ አካሎች ከቁንጮዎቹ አንዷ ነች፡፡ ለአዲስዮስ ከታደሉ በጣም ጥቂት ደስታዎች አንዷ ናት፡፡

ንጉስ አዲስዮስ ሞቷል ብለው ንግስት ፔኔሎፒንና የኢታካን መንግስት ለመውረስ አሰፍስፈው ይሻሙ ይወዳደሩ የነበሩት መኳንንት ዛሬም ለእራት ተሰብስበዋል፡፡ ሽማግሌው ድሀ እራት ተሰጥቶት እየበላ ያስተውላል ያዳምጣል፡፡ ንግስቲቱን እንግዲህ አንዳችንን ይምረጡ ይሏታል፡፡ እሷም ‹‹ያውና የአዲስዮስ ቀስት›› ትላቸዋለች ‹‹ፍላፃ መስፈንጠሪያው ሲባጎ ባንዱ ጫፍ ታስሯል ከሌላው ጫፍ ግን ወልቋል፡፡ ከመሀላችሁ በእጆቹ ብርታት የአዲስዮስን ቀስት ስቦ አቀራርቦ ሲባጎውን ለውጊያ ዝግጁ የሚያደርገው አለ? እችላለሁ የሚል ይሞክር››

ሁሉም አንድ በአንድ ሞከሩ - አልቻሉም፡፡ ድሀው ሽማግሌ ተነሳ፤ ቀስቱን ተቀበለ፤ የሲባጎውን ቀለበት እጅግም ሳይጨነቅ ከቀስቱ ሌላኛው ጫፍ ከተገቢው ስፍራ አጠለቀው፡፡ ፍላፃ አነሳ፤ በቀስቱ አነጣጠረ - ፍላፃዋ ተስፈነጠረች - ሽው ብላ ተወርውራ አንዱን መኳንንት ፈነገለችው፡፡ እራቱን እየበላ ሁኔታዎችን እያጠና ፈጣን የትግል እቅድ ሲያወጣ የቆየው አዲስዮስ በታወቀው ጉልበቱና ብልሀቱ እነዚያን መኳንንት ዋጋቸውን ሰጣቸው፣ ሁሉንም ረፈረፋቸው በነቴሌማኩስ እርዳታ፡፡ ፔኔሉፒ ይህን ጊዜ ሽማግሌ መሳዩ ሰውዬ ጀግናዋ አዲስዮስ ራሱ መሆኑ ገባት፡፡

ፍቅረኛሞች ሆነው ከሀያ አመት መለያየት በኋላ ተቃቅፈው ሲያድሩ እንዴት ይመስል ይሆን? ሌላ ገነት የለም እዚች ምድር ላይ፡፡

**ሀምሌ 2 / 30 ቀን 1987**

# ቻይና

ከአለም ታላላቅ ጥንታውያን ስልጣኔዎች አንዷ የሆነችው ቻይና በ1982 (በፈረንጅ አቆጣጠር ነው የምንቀጥለው) አንድ ሺ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን) ህዝብ ነበራት፡፡ (ማለትም ከአለም ህዝቦች ከስድስቱ አንዱ ቻይናዊ ነው፡፡) የቻይና ህዝብ ዘጠና አራት ከመቶው ሀን የተባለ ዘር ሲሆን፣ የተረፈው ስድስት ከመቶ በስድሳ የተለያዩ አናሳ ዘሮች ይከፈላል፡፡ በሶስተኛው ምእተ አመት ከክርስቶስ በፊት የተገነባው ታላቁ የቻይና ካብ በጥንት ዘመን ከሰባቱ የአለም አስደናቂ ስራዎች አንዱ ተብሎ ይታወቅ ነበር፡፡ ካቡ የተገነባው ከሰሜን እየጋለቡ አገሪቱን በመውረር እና በመዝረፍ ያስቸግሩ የነበሩትን ጎሳዎች እንዳይገቡ ለመከልከል ነበር፡፡ አጥር ነበር፡፡

በዚህ ትላንት ባለፈው አስራ ዘጠነኛው ምእት ግን እንግሊዝና ፈረንሳይ የተባሉት ምእራባውያን በባህር መጡ በደቡብ፡፡ ለቻይና ውርደትን እፍረትን ሊያከናንቡዋት መጡ፡፡ ይህን የምንልበት ምክንያት እስከዚያ ቀውጢ ጊዜ ድረስ ቻይና በቻይናውያን አይን የአለም እምብርት ወይም መሀል ነበረችና ነው፡፡ ንጉሰ ነገስቷም ማእረጋቸው "የሰማያት ልጅ" ነበረ፡፡ የውጭ ሰው በሰላም ቻይናን ሊጎበኛት ከመጣ ከዚህ ታላቅ ስልጣኔ ትምህርት ወይም ጥበብ ለመቅሰም ፈልጎ ነው ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ በጣም የጎላው ምሳሌ የጃፓናውያን የጥንት ጉብኝት ነው፡፡

በመቶዎች እየመጡ ቻይና ውስጥ አያሌ አመታት ሲማሩ አሳልፈው ወደ ጃፓን ይመለሳሉ። በዚህ መንገድ ነበር የዜን ቡድሂዝም ሀይማኖት ከቻይና ወደ ጃፓን የተወሰደው። ቻይናዊ ወይ ጃፓናዊ አጋጥሞኝ አልጠየቅኩም እንጂ ምእራባዊያን ፅፈውት እንዳነበብነው ከሆነ ቻይንኛና ጃፓንኛን ሲናገሩ በጣም የተራራቁ ቋንቋዎች ናቸው። ሲፃፉ ግን ሁለቱም በስእላዊ ስልት ነው። ስለዚህ በጃፓንኛ የተፃፈውን ቻይናዊው በቻይንኛ ሊያነበው ይችላል። እንደዚሁም በቻይንኛ የተፃፈውን ጃፓናዊው በጃፓንኛ ሊያነበው ይችላል። እኔ በበኩሌ ይሄ ነገር በጣም እያስገረመኝ ነው ለማመንም እያስቸገረኝ ነው። ግን ደሞ እውነት ባይሆን ሰው ለምን ብሎ ፈጥሮ ያወራው ነበር? ምን ጥቅም ሊያገኝበት? አስቸጋሪ ጥያቄ!

የዜን ቡድሂዝምን መንፈስ ለቅምሻ ያህል እነሆ፣ የዜን ቡድሂዝም መስራች ከሆኑት ታላላቅ ቻይናውያን አንደኛው ጁዋን ዙ (Juang Tzu) የሚባለው ፈላስፋ ነበር። በጣም ዝነኛ መምህር በሆነበት ጊዜ አንድ ቀን እሱ አሳ ለማስገር ወንዝ ዳር ቁጭ ብሎ ማታለያውን ትል አሳ እስኪው ጠው ይጠብቃል። ከዚያ ገመዱን ስቦ አሳውን ለማውጣት። በትእግስት አሳውን እየጠበቀ እያለ ደቀ መዛሙርት መርተዋቸው በጣም ሀይለኛ ከሆነ ጎረቤት አገር ሁለት መልእክተኞች መጥተው ከኋላው ቆመዋል። ወደነሱ ሳይገላመጥ (አሳ እያጠመደ ነዋ!) "ጉዳያችሁን ንገሩኝ" አላቸው።

"በጥበብዎ ስለታመነበት የኛ አገር ጠቅላይ ሚኒስቴር እንዲሆኑ ተጋብዘዋል" አሉት።

ጁዋንግ ዙ አሁንም ሳይገላመጥ "አሳ እያጠመድኩ ነው፣ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ግን ለኔ አይሆነኝም ይቅርታ" ብሎ አሰናበታቸው። እንግዲያውማ? የሀያል አገር አምባሳደሮች የሆኑ እንደሆነ ታድያ ለነሱ ክብር ሲባል አሳ ማጥመዱን ሊያቋርጥ? በዚያች ደቂቃ እኮ ዋናው ጉዳይ አሳ ማጥመዱ ነው እንጂ ሰላምታ መለዋወጡ አይደለም።

ቻይና የውጭ ንግድ የምንፈቅደው በካንቶን ወደብ ከተማ ብቻ ነው አለች። የእንግሊዝ ነጋዴዎች ግን የኦፒየም ንግዱን በኮንትሮባንድ

አጧጧፉት። ኦፒየም እጅግ አደገኛ አደንዛዥ እፅ በመሆኑ የቻይና መንግስት በካንቶን ተከማችቶ የተገኘውን ኦፒየም በሙሉ ወሰደና ደፋው ተበላሸ። እንግሊዝ ሰበብ አገኘች። ጦርነት ከፈተች። የኦፒየም ጦርነት የተባለው ከ1839 እስከ 1842 ተካሄደ ቻይና ተሸነፈች።

ተሸናፊ ከፋይ ነውና ቻይና ሆንግ ኮንግን ለእንግሊዝ ለቀቀች። ለዘጠና ዘጠኝ አመት ነዋ ያውም! ወደቦችንም እንዳለ ለውጭ ንግድ ክፍት እንዲሆኑ ፈቀደች። የውጭ ዜጋዎችም ህግ ቢጥሱ በቻይና ህጋዊ ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በገዛ ቆንስላቸው ወይም ኤምባሲያቸው በቻይና ህግ ሳይሆን በየአገራቸው ህግ እንዲፈረድባቸው ፈቀደች።

ከ1856 እስከ 1880 ደግሞ በቻይና ምድር እንግሊዞችና ፈረንሳዮች የጋለ ጦርነት ተዋጉ የቻይና ዋና ከተማ ፔኪንግ ተወረረችና ተዘረፈች። ጦርነቱ ሲያበቃ መላዋ ቻይና ለውጭ ንግድ ክፍት እንድትሆን ተገደደች። መች ይኸ ብቻ? የባሰ መጣ'ንጂ።

በባህልና ስነ ጥበብ የቻይና ውድ ልጅዋ ናት ትባል የነበረችው ጃፓን "ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" የሚባለውን አማርኛ ያወቀች ይመስል ተራዋን በቻይና ላይ ጦርነት ከፈተች። (ለመሆኑ ጦርነት የሚከፈትና የሚዘጋ ነው እንዴ?) ከ1894 እስከ 1895 በተካሄደው የቻይናና የጃፓን ጦርነት ቻይና ባንድ አመት ተሸነፈች። እንደ ትልቅ ውርደት ተቆጠረ። ገና የባሰ ሊመጣ ነው ከጃፓን።

በ1932 የቻይና የሰሜን ጎረቤት እና የረዥም ዘመን ቅኝ ግዛት የነበረችው ማንቹሪያ በጃፓን ግፊትና እርዳታ ከቻይና ነፃ ወጣች። ጃፓን ማንቹሪያን የስንቅና የዝግጅት መሳሪያ አደረገችና ሁሉ ነገር ሲጠናቀቅላት በ1937 ቻይናን ወረረች፣ ድል አደረገች። እና?

እና ጃፓን የቻይናን ዋና ዋና ከተማዎች በጉልበት ወሰደችና በሻንግሀይ የቻይና አሻንጉሊት መንግስት አቋቋመች። አሻንጉሊት መንግስት ማለት አገሩን የሚገዙት ያገሩ ሰዎች ሆነው ስራቸውን የሚሰሩት ግን በጉልበቱ ስልጣን ካስጨበጣቸው የውጭ መንግስት

ትእዛዝ እየተቀበሉ ነው እንጂ ለህዝባችን ይሄ ይበጃል ብለው በእምነታቸው እየተመሩ አይደለም።

ስልጣን ለመጨበጥ አገራቸውን ስጡ የሚባሉ ናቸው። ይኸ ውርደት ግን የቻይና ውድ ልጆች እነ ማኦ ዜዱንግ ሲመጡ ወዲያ በጣጥሰው የሚጥሉት ይሆናል።

በ1941 የጃፓን ትላልቅ የጦር መርከቦች የጦር አውሮፕላኖች ተጭነው በድብቅ አትላንቲክ ውቅያኖስን ተሻግረው ፐርል ሀርበር (pearl Harber) የተባለችውን የአሜሪካ ወደብ የቦምብ መአት አወረዱባት። ብዙ መርከቦችም ተቃጠሉ። ይሄኔ ቻይና በአክሲስ (axis) ሀይሎች ላይ ጦርነት አወጀች። አክሲስ ማለት በሁለተኛው የአለም ጦርነት ላይ አንድ ወገን የነበሩት የሂትለር-ጀርመን የሞሶሎኒ-ኢጣሊያ እና የንጉስ ሂሮሂቶ-ጃፓን ናቸው።

ቻይና ብዙ አስገራሚ ሰዎች በቅለውባታል። ከነዚህም አንዱ የህዝቡ ነፃ አውጪ የሆነው ማኦ ዜዱንግ ነው። ማኦ በኖቬምበር 19 ቀን 1893 ተወለደ። በ1918 በፔኪንግ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መፅሀፍ ውስጥ አነስተኛ ስራ ያዘ። እዚያም የዩኒቨርስቲው መምህራን ከሆኑ ሁለት ፕሮፌሰሮች ጋር ይተዋወቃል። በ1921 ሶስቱ የቻይናን ኮሙኒስቶች ፓርቲ ይመሰርታሉ።

በ1923 በሁናን ክፍለ ሀገር ያሳየው የአመራር ችሎታ የፓርቲው ብሄራዊ አመራር አባል ሆኖ እንዲመረጥ አብቅቶታል።

በ1925 ወደ ሁናን ተመለሰ። እዚያም አርሶ አደሩ ምን አይነት ሀይል ሊሆን እንደሚችል አስተዋለና እነዚህን አርሶ አደሮች ለመራራው ትግል አደራጃቸው። በተጨማሪ አብዮታዊ መፅሄቶች ለህትመት ያዘጋጅ ነበር።

በ1931 ማኦ ዜዱንግ የቻይና ሶቭየት ሪፐብሊክ ሊቀመንበር ሆኖ ተመረጠ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ሳለ የቻይና መንግስት ግን ቻንግ ካይቼክ የሚመራው ኮሚታንግ የተባለው ፖለቲካዊ ድርጅት ነው። ቻንግ ካይቼክ

የነማኦን ሰራዊት ለመደምሰስ ያለ የሌለውን ሀይል አዘመተባቸው፣ ኮሚኒስቱ ሰራዊት ማኦ ዜዱንግ እና ጆዴህ እየመሩት በኋላ ዝነኛና አስደናቂ የሆነውን ሩቅ የእግር ጉዞ ተያያዘው። እነዚህ ጀግኖች አስር ሺ ኪሎ ሜትር በእግር ተጓዙ። ርቀቱ የአዲስ አበባን አስመራን ርቀት ዘጠኝ ጊዜ ይረዝመዋል።

በዚህ ጉዞ ላይ ሳሉ ከአደጋ ሰወር ያለ ስፍራ ለጥቂት ቀን እያረፉ እያለ የጠላት አውሮፕላን መጣችና ብዙ ወረቀት በትና ሄደች። ባንዱ ገፅ ነው የተፃፈበት በጀርባው ባዶ ነው። ማኦ ዜዱንግ፣ ጆዴህ፣ ጁኤን ላይ እና ሌሎች የአመራር አባላት የሚገኙበትን ያሳየ የጠቆመ ወይም የመራ ለእያንዳንዳቸው አያሌ መቶ ሺ ዶላር እንደሚከፍል ያበስራል። እነማኦ በሰራዊታቸው አባላት ሙሉ በሙሉ ስለሚተማመኑ ወረቀቶችን ሰብስበው እንደማቃጠል አንድ በአንድ ደብተር እንዲያክሉ አድርገው እንዲጠርዙዋቸውና ትምህርት ሲሰጥ እንዲፅፉባቸው አዘዙ። እንደዚህ በእጅ አዙር ቻንግ ካይቼክ እነማኦን አገዛቸው።

ጥቂት ቃላት ስለ ጆዴህ። ከሩቅ አገር የደረሰን አፌ ታሪክ። ከ1916 እስከ 1928 አስራ ሁለት አመት የጦር ጌታ የሚባሉ አያሌ የጦር አበጋዞች በየፊናቸው ተነስተው በቻይና ህዝብ ላይ ብዙ ጉዳት አደረሱ። እያንዳንዳቸው በግል የሚያዝዙት የራሳቸው የሆነ የታጠቀ ሰራዊት አላቸው። እነዚህ የጦር አበጋዞች የሚኖሩትና ሰራዊታቸውን የሚያኖሩት በህግ ሳይሆን በጉልበት ግብር እየሰበሰቡ አልገብርም ያለውን ደሞ በጦር ወርረው እየዘረፉ ነበር። በዚህ አስከፊ ዘመን በቻይና ውስጥ በየአመቱ ቁጥሩ ከስድስት እስከ ስምንት ሚሊዮን የሚደርስ ሰው በረሀብ ያልቅ ነበር። ከነዚህ አፄ በጉልበቱ ከሆኑ የጦር አበጋዞች አንደኛውና ዝነኛው ጆዴህ ይባል ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ማኦ ዜዱንግ በዚህ በኩል፣ ሌሎች ተፃራሪ ሀይላት በዚያ በኩል ተሰልፈው ውጊያ ሊጀምር ሆነ። ከጠላት ሀይላት አንዱ የጆዴህ ሰራዊት ነው። እዚህ ላይ ግን ጆዴህ በገዛ ህሊናው ተቀስቅሶ ለሰራዊቱ ንግግር አደረገ። ለምሳሌ ምናልባት የንግግሩ ጭብጥ

እንደሚከተለው ሳይሆን አይቀርም "ወታደር! እስከ ዛሬ ግሩም ተዋግተናል ግን እስከ ዛሬ የምንዋጋው ለራሳችን ጥቅም ብቻ ነበር። ከዛሬ ጀምሮ ግን ሚናችንን ለውጠናል። ከእንግዲህ የምንዋጋው ለህዝባችን ደህንነትና ጥቅም ይሆናል። እኛም ከህዝባችን አብራክ የወጣን ነንና ህዝባችንን ስንጠቅም እራሳችንን እንጠቅማለን። ከእንግዲህ የነ ማኦ ዜዱንግ ወገን ነን››

እነማኦን ሊዋጋ ተሰልፎ የነበረው የጆዴህ አደገኛ ጦር ቀኝ ኋላ ዞሮ ጠላቶቻቸው ላይ ተኩስ ከፈተ። እነማኦ ዜዱንግ ከእንግዲህ በድል ላይ ድል የሚባል ሂደት ሲለምድባቸው ሆነ።

**ነሀሴ 21 ቀን 1987**

# አዳኝ እና ታዳኝ

ሊቃውንት ተፈጥሮን ሲያጤኑ ብዙ የሚያስደንቅ ነገር ይገጥማቸዋል። ጥቂቱን እንንገራችሁ። በነፍሳት እንጀምር። ነፍሳት ስንል ቢራቢሮ ፌንጣ ጉንዳን ንብ የመሳሰሉትን በእንግሊዝኛ ‹ኢንሴክት› የሚባሉትን ነው።

የአንድ ነፍሳት ዋና እለታዊ ተግባር የወፍ ወይም የሌላ ፍጡር ምሳ ከመሆን ማምለጥና ለራሱ ግን ምሳ ማግኘት ነው። ለዚህም አይነተኛው ብልሀት አካባቢውን መምሰል ነው ከሩቅ አይን ላለመሳብ።

በለንደን ከተማ የሚኖር አንድ አይነት ቢራቢሮ አለ። ከሁለት መቶና ከመቶ ሀምሳ አመታት በፊት የዚህ ቢራቢሮ ዘር አባላት አብዛኛዎቹ ነጭ ነበሩ። ከአስር አንድ ጥቁር ቢገኝባቸው ነው። ያን ጊዜ ግን ለንደን በፋብሪካ ጭስ እየጠቆረች ሄደች። ስለዚህ ነጫጮቹን ቢራቢሮዎች ወፎች በቀላሉ ያዩዋቸው ጀመር። ዋጥ ስልቅጥ። ጥቋቁሮቹ ግን አካባቢውን በመምሰላቸው በቀላሉ ስለማይታዩ ያመልጣሉ። ይዋለዳሉ ይባዛሉ። አሁን የዚያ ቢራቢሮ አይነቶች አብዛኛዎቹ ጥቋቁር ናቸው። ከአስር አንድ ነጭ ቢገኝባቸው ነው።

ነፍሳት ከመበላት የሚያመልጡበት ሌላው ዘዴ (ወይስ እድል እንበለው?) ያለመጣፈጥ ነው። አንድ ቀን የቀመሳቸው ወፍ ሁለተኛ ዞር ብሎ አያያቸውም ወይ መራራ ናቸው ወይ ቃናቸው አንድ በጣም

የሚያስጠላ ነገር አለው፡፡ እነዚህ እንግዲህ መደበቅ የለባቸውም፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ በብሩህ ቀለማት ያሸበረቁ ናቸው፡፡

አሉ ታዲያ ሌሎች ነፍሳት ልክ የነዚህን ቀለማት ለብሰው ‹‹የሚንጎራደዱ›› ስጋቸው ግን ይጣፍጣል፤ ብቻ ወፍ አያውቅም እንጂ (ሌባ ሆኖ የፖሊስ መለዮ ለብሶ እንደማምለጥ አይመስልም?)

ግን መቼም ኑሮ ነውና ታዳኙ ብቻ አይደለም ብልሀተኛ አዳኙም እንጂ፡፡ በራሪ ነፍሳት ከአበባ ወደ አበባ እየነጠሩ ጣፋጭ ምግብ ይቀስማሉ፡፡ እና አንድ አይነት አበባ አለ ቀለማቱም ከሩቅ የሚጠራ መአዛውም ከሩቅ የሚያስጎመጅ፡፡ ነፍሳቱ ጣፋጩን ለመሳብ ወይም ለመቅሰም ወደ አበባው ውስጥ ይገባል፡፡ አበባው በድንገት ዝግት ይላል፡፡ ለካ የጭራቅ አፍ ኖሯል! ‹‹ወይኔ የነፍሲቷ ልጅ! እበላ ብዬ ተበላሁ!›› ይል ይሆን በመጨረሻ ሀሳቡ?

የአንድ ነፍሳት ሌላው ዋና ተግባር መውለዱ ነው - ዘር ትቶ ለማለፍ ለመውለድ ወንዱ ሴቷን ማግኘት ይኖርበታል፡፡ እዚህ ላይ አንዳንዶቹ ወንድ ነፍሳት ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ ሴቲቱ በስሪያ ጊዜ ዮር ብላ የመብላት ጠባይ አለባት፡፡ ክፉ ጠባይ! አቤት ስንቱ ጀግና ነው ዘር ለመተው ሲል ተበልቶ የቀረ!

በአንዳንዱ የነፍሳት ዘር ወንዱ የሴቷ ምሳ ከመሆን የሚያመልጥበትን ብልሀት አግኝቷል፡፡ ይሄድና በድር ወይም በሀር መሳይ ነገር የተጠቀለለ የሌላ አይነት ነፍሳት እንቁላል ዘርፎ ወይም ሰርቆ ያመጣል አምጥቶ ለሴቲቱ ይሰጣል፡፡ እሷ መጠቅለያውን እስክትፈታና ውስጡ ያለውን እስክትበላ እሱ ይወጣባትና ዘሩን ዘርቶ ሲያበቃ ፈትለክ! ‹‹ተመስገን አምላኬ! ሌላ ቀንም እንዲሁ ጠብቀኝ!››

አሉ ታዲያ ‹‹ማጅራት መቺዎች!›› አንዱ በስንትና ስንት ፍለጋ አግኝቶ የተጠቀለለውን እንቁላል ለሴቲቱ ሊሰጥ ሲሄድ ሌላው በድንገት ይደርስና ይነጥቀዋል፡፡ ነጥቆ ወስዶ ለራሱ ሴት ገፀ-በረከት ይሰጣታል፡፡ የተነጠቀው እንግዲህ እንደገና ፍለጋ ይገባል፡፡ ያለ ገፀ-በረከት አይሆንማ!

‹‹ሆ! ትብላኝ?›› ሲል ይሰማችኋል በሀሳቡ? (የአዲስ አበባ ዘፋኝ አንጀቴን በላችው እያለ ሲዘፍን የነሱን ጣጣ መናገሩ አይመስልም?)

ሌላ አይነት ወንድ ነፍሳት አለ። እሱ የተጠቀለለ እንቁላል ፍለጋ አይሄድም። ምን አለፋው? አድፍጦም ከሌላው ለመንጠቅ አይሞክርም። አልነጠቅም ብሎ ቢፋለመውስ? ቀላሉ ብልሀት እያለ! እንቁላሎቹ ተፈልፍለው ድሮ ጥለውት የሄዱት ባዶ መጠቅለያ ያገኛል። በቀላሉ ያንን ባዶ መጠቅለያ ወስዶ ለሴቲቱ ገፀ-በረከት ይሰጣታል። እሷ ባዶውን መጠቅለያ ስትፈታታና የሚበላ ምናምን ስትፈላልግ እሱ ስራውን ሰርቶ ፈትለክ ነዋ! (የልጆችህን እናት እንደዚህ ማታለል አይገባም አሉኝ ጌታዬ? ወይ ጉድ! ያልተያዘ ግልግል ያውቃል። አይ! ኧረ ተሳሳቱ አላልኩም። እውነትምን ነው። ዝም ብዬ መበላት ነበረብኝ።)

በፍጡራን መካከል መበላላት አለ። መረዳዳትም አለ። መበላላቱን በጥቂቱ እንይ።

<u>ንብ አበባና ሌሎች</u>

ነፍሳትና አበባዎች እየተረዳዱ ይኖራሉ። አበባዎቹ ለነፍሳቱ ምግብ ይሰሩላቸዋል። ነፍሳቱ ደግሞ ከአንዱ አበባ ወደ ሌላው ሲበሩ የአበባውን ዘር ከወንዶው አበባ አንስተው ወደ ሴቱዋ አበባ ያደርሱታል። ‹‹አንስተው›› አልን እንጂ የአበባው ዘር ተጣብቆባቸው ነው።

ይህ በአበባዎችና በነፍሳት መካከል የሚደረገው መረዳዳት ‹‹ጥቀመኝ ልጥቀምህ›› ሲሆን ሳለ፤ አንዲት ልዩ ተንኮለኛ አበባ አለች። መመሪያዋ ‹‹ጥቀመኝ የጠቀምኩህ አይምሰልህ›› ነው። ለነፍሳቱ ምግብ አታዘጋጅም። ውሸት ነው የምታዘጋጅላቸው። በቅርፅም በቀለምም ልክ የወንዱን ነፍሳት እንስት ትመስላለች። ልክ ቁርጥ! ስለዚህ የዚህ ነፍሳት ተባእት አበባዋን ይሰራታል። በእሱ ቤት እንግዲህ ሴት አግኝቶ ዘሩን መዝራቱ ነው። ከዚቺኛው አበባ ተነስቶ ሲሄድ (እሷስ ተባእት አበባ ናት) የአበባው ዘር ይጣበቅባታል። ቀጥሎ የሚያገኛትን እንስት ነፍሳት የመሰለች አበባ (ሴት አበባ ናት) ዘሩን ይዘራባታል። ይመስለዋል። እንደ እውነቱ ግን

የራሱን ዘር አባክኖ የ‹‹ወንድ›› አበባውን ዘር ተጣብቆበት የነበረውን አቀብሏት በረራውን ይቀጥላል፡፡ እንግዲህ ጉድ መስራቱን ለዚህ ወንድ ነፍሳት ብንነግረው ምን ይለን ነበር? ኧረ 'ባክዎን? እኛ የአበባዎችንና የሴቶቻችንን ልዩነት አናውቅማ? እናንተ ናችኋ የምታውቁልን! በሉ ልንገርዎት፤ ብዙ ልጆች ወልጃለሁ፡፡ ከአበባ ነው የወለድኳቸው? ወይ ጉድ! ‹‹ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው አሉ?›› ብሎን ሲሄድ፤ አበባይቱ ደግሞ ‹‹እፍር! ይሄ ነው የሰባቂ ዋጋው! የምን ማቃጠር ነው እሱ?!›› ብላ ትወርድብን ነበር፡፡ ነፍሳቱ ላያምነን አበባይቱም ልትቀየመን ሆነ፡፡ ስለዚህ እንተወው፡፡ እንዲያውም ነፍሳቱንም አበባዎቹንም እንተዋቸው፡፡

አበባዎችና ንቦች ይተጋገዛሉ እንጂ መተጋገዛቸውን አያውቁም፡፡ ጉማሬና ወፊቱ ግን ሳያውቁ አይቀሩም፡፡ የነሱ ግንኙነት እንደ ሽርክና ሊቆጠር ይችላል፡፡ ጉማሬው አፍ ውስጥ (ትናጋው፤ ጉሮሮው ዘንድ) አልቅትና የመሳሰሉት ደም መጣጮች ይጣበቁበታል፡፡

‹‹እኛም አውቀናል! ጉድጓድ ምሰናል›› እያለ በልቡ፤ ከውሀው ወጣ ብሎ እጭቃው ላይ ይመቻቻል፡፡ ያቺ ሽርካው ወፍ ከአጠገቡ አትጠፋም፡፡ በሱ ጀርባና በዛፎቹ መካከል እየተመላለሰች ነው 'ምትውለው፡፡ ጉማሬው አፉን ይከፍታል፡፡ አቤት አፍ! ወፊቱ ትገባለች አፉ ውስጥ፡፡ አልቅቱንም ሌላውንም ግጥም አድርጋ ትበላለች፡፡ ስትጨርስ ትወጣለች፡፡ ጉማሬ አፉን ይዘጋል፡፡ ጉማሬውም ወፊቱን መገባት፤ ወፊቱም ጉማሬውን አከመችው፡፡ ጉማሬው አደጋ ሲመጣበትም ታስጠነቅቀዋለች ይላሉ ይህ ግን የተረጋገጠ አይደለም፡፡

የወፊቱና የጉማሬው ሽርክና አይነት በባህር ውስጥም ይገኛል፡፡ አንዳንድ አይነት ትላልቅ አሳዎች አፋቸው ውስጥ የሚጣበቁባቸው ጥቃቅን ፍጡራንን ለማስወጣት ትናንሽ አሳዎች ዘንድ ይሄዳሉ፡፡ ያው እንደ ጉማሬው አፋቸውን ይከፍታሉ፡፡ ትናንሾቹ አሳዎች ገብተው ምሳቸውን በልተው ይወጣሉ፡፡ ትንሹ አሳ ‹‹ጉማሬውን አሳ›› ፍለጋ ሲሄድ ብዙ አደጋ ሊገጥመው ስለሚችል ብዙውን ጊዜ እሱ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ይገኛል ወይም በቋሚነት ይኖራል፡፡ አፋቸውን ለመጥረግ

የሚሹ «ጉማሬ አሳዎች» ይህ «ወፍ አሳ» የሚገኝበትን ስፍራ ስለሚያውቁ ወደሱ ይመጣሉ። አንዳንዴ ሶስት አራት አምስት «የጉማሬ አሳዎች» ወረፋ የሚጠብቁበት ጊዜ አለ። የፀጉር አስተካካይ ቤት ወይም የውበት ሳሎን ውስጥ እኛ ወረፋ የምንጠብቀው አይነት።

‹ጉማሬ አሳዎች› ‹ወፍ አሳዎችን› ለይተው የሚያውቋቸው ሰዎች ሲያዩዋቸው ነው። የአካላታቸው እንቅስቃሴ ያስታውቃል። በዚያ አወኛኘት ጠጋ ሲሏቸው «ጉማሬ አሳዎች» መዝናናትና አፋቸውን መክፈት ነው። ግን እሉ ሌሎች «ብልጦች» የአካላቸውም መጠን ‹ወፍ አሳውን› ያክላል። የዋና ስልታቸውን ልክ እንደእነሱ አድርገው ጠጋ ማለት ነው። ጉማሬ አሳዎቹ መዝናናት። ተዝናንተው ሳለ ታዲያ ‹ወፍ አሳው› (ለካ አስመሳይ ኖሮ) ቦጨቅ ያደርጋቸውና አንድ ጉርሻ ሙሉ ስጋቸውን ሞጭልፎ እብስ!

ለዚህ ነው በየቦታው አፋቸውን ከመክፈት «ደንበኞቻቸው» ዘንድ ሄደው ወረፋም ቢኖር ተራቸውን የሚጠብቁት።

ሳይንቲስቶች ተፈጥሮን ሲመረምሩ ብዙ አስደናቂ ነገር ያጋጥማቸዋል። ለአሁኑ ይሄ ይበቃል።

**መጋቢት 17 ቀን 1987**

# ቢሮክራሲ!

‹‹ግልፅ ደብዳቤ›› ብለው በጋዜጣ ሲፅፉ ለብቻዬ በትንሹ እስቅባቸው ነበር። ለካ የኔ ሳቅ ‹‹ያልተነካ ግልግል ያውቃል›› አይነት ነበረች። ይኸዋ እኔው ራሴ ቀኑን ጠብቆ ደርሶብኝ ስጥፋት ግልፅ ደብዳቤዋን።

ግልፅ ደብዳቤ ከግንቦት ሃያ 1983 በኋላ ከቀናትም ካመታትም በኋላ - ቢሮክራሲ ውስጥ ለተሰማራችሁ አማርኛ ይሁን ትግርኛ ኦሮምኛ ወይ ሌላ ቋንቋ ለምትናገሩ እንደምን አላችሁ? አሁን ከሰላምታ ቀጥዬ ወደ ጉዳዩ እመለሳለሁ።

ስለቢሮክራሲ ውስብስብነት ከምር ልታስቡበትና ‹‹አብዮታዊ እርምጃ ልትወስዱበት›› ይገባል በጥናት ላይ የተመሰረተ ነው ደሞ። ይኸው አንድ ቀን ከለውጥ በፊት ብላታ ደሬሳ አመንቴ አራት ኪሎ ያለውን የንግድ ባንክ እያመለከቱኝ ‹‹ይኸ የተሰራበት መሬቱ የኔ ነበር፤ በልጅ ኢያሱ ጊዜ ነበር የገዛሁት። በሶስት ቀን ከአራት ባለስልጣናት ፊርማ በኋላ መሬቱ የኔ ሆነ። አሁን ይህን መሬቴን ለንግድ ባንክ እንድሸጠው ዋጋ ተስማማን። የስድስት ወር መመላለስና የሀምሳ አራት ባለስልጣን ፊርማ አስፈለገ። ያውም ብዙዎች ባለስልጣኖች ስለሚያውቁኝ በጣም እያፈጠኑልኝ ነው።››

የገዛ መሬታቸውን ባንክን ከሚያህል፤ ለህዝቡ አገልግሎት ለሚሰጥ መስሪያ ቤት ለመሸጥ ምን ይሆን ይህ የሚያስገርም የቢሮክራሲ

መራዘምና መንዛዛት ብዛት? በልጅ ኢያሱ ዘመን ባለስልጣናቱ ግፋ ቢል እስከ ስድስተኛ ክፍል ቢማሩ ነው። የዛሬ ባለስልጣናት ግን ባለድግሪ ናቸው። ስለዚህ ብዙ ስለተማሩ ብዙ ሰነድ መፈረም አለባቸው? ወይስ ብዙ ሰው ደሞዝ ማግኘት ስላለበት ሶስት ሰው (ቢበዛ ሰባት ሰው) ፈርሞበት ሽያጩ ሊፈፀም ሲችል ሀምሳ አራት ባለ ስልጣናት እንዲፈርሙበት ያስፈልጋል? ስራ ለመፍታት? ለባለስልጣናት ደሞዝ ማግኘት ሲባል ባለጉዳይ ዜጎች እጅ በመንሳት በመጉላላት መማረር አለባቸው? እኔ በበኩሌ መንግስት መስሪያ ቤት ጉዳይ ካለብኝ እዚያ ብቅ ባልኩ ቁጥር ሀበሻነቴን እንቀዋለሁ። እንደዚያ የምወደውን ሀበሻነቴን... አይ ቢሮክራሲ! የእውር እብድ ያረገህ!

እንዲያም ስንል ጤነኛውን ቢሮክራሲ መኮነናችን አይደለም። እሱማ አድልዎ እንዳይኖር፣ ሰው ሁሉ አገልግሎት የሚያገኘው እኩል እንዲሆን እና እንደዚሁም ቤተመዛግብት በመስሪያ ቤቱ የተከናወነውን ጉዳይ ሁሉ እንደ ታሪክ በመዝገብ እንዲያኖረው ያስችላል። በአንፃሩ ግን ያዲስ አበባ ቢሮክራሲ ክፋት ስለሚበዛበትና ባለስልጣኖች ሰውን እንደሰው ስለማያዩት፤ መመሪያው ‹‹እኛ የምናውቀው ሰው ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ባለጉዳይ ዜጋ በተቻለ መጠን ጉዳዩ እኩል እንዲጓተትበትና እኩል እንዲመላለስ እኩል እንዲጉላላ ‹እሺ ነገን› ታጥቀን እንታገላለን!›› ይመስላል። ከኮሚቴው በስተጀርባ ተሸሽገን።

ባዲስ አበባ ካንሰር መሰል ቢሮክራሲ አመለካከት ‹የሰው ልጅ ሲባል ቀጣፊ ውሸታም፤ አጭበርባሪ ነው ስለዚህ ሁሉም ነገር ደጋግሞ በተደጋጋሚ ባለስልጣናት መመርመርና መጣራት መረጋገጥ አለበት።› ጊዜ ይወስዳል? ይወስዳል! እኛ ሀበሻ ነን። ጊዜን ከቁብ አንቆጥረውም። ዘላለምን ያህል ነገር ወደፊት ተዘርግቶ እየጠበቀን ለጊዜ እንጨነቅለታለን? በጭራሽ!

ድሮ ሲነግሩን የእንግሊዝ ዳኛ መመሪያ እንዲህ ይላል ‹‹አንድ ንፁህ ሰው ባልሰራው ወንጀል ከሚቀጣ ዘጠኝ ወንጀለኞች ከቅጣት ቢያመልጡ ይመረጣል›› በአንፃሩ ያዲስ አበባ ቢሮክራሲ ውስጣዊ መመሪያ እንዲህ

የሚል ይመስላል፡፡ ‹‹አንድ ሰው ከሚገባው የበለጠ ወይም የፈጠነ አገልግሎት ከሚያገኝ ዘጠና ዘጠኝ ሰው ያለአስፈላጊ ቢመላለስና ቢጉላላ ቢንገላታ ይመረጣል›› ወይም ወደ አዲሳባዊ መፈክር ብንለዋውጥላቸው ‹‹አንዱ ከሚመርቀን ዘጠና ዘጠኙ ይርገመን!››...

እኔን እንደገጠመኝ ከሆነ ያዲስአባ ቢሮክራሲ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት አሰልቺ ነበር ጎታታነቱ፡፡ በደርጉ ዘመነ መንግስት ቢሮክራሲው በሂደት ለውጥ ሳይንሳዊ ሀቅን በመፈክር እያሳየ እድገቶችንና እመርታዎችን በስኬታማነት ሁኔታ አስመስክሮ በጎታታ አህያ ፍጥነት ሲጓዝ ቆይቶ የአይነት ለውጥ በኤሊ ፍጥነት መጋለብን አመጣ፡፡ ይህ የካንሰር ሂደት እየባሰበት ነው፡፡ ቢሮክራሲያችን ወያኔ ሳይል ታጋይ ሳይል፤ እየባሰበት ይሄድና በሽግግር መንግስታችን ዘመን ከኤሊ ቀስታነት ወደ ቀንድ አውጣ ወይም ወደ ቅንቡርስ ቀስ-ቀስታነት ተሸጋግሮ ይገኛል፡፡ ሂደቱን የሚቆርጥለት መቀሳዊ እርምጃ ካልተወሰደበት በስተቀር በሚቀጥሉት አምስት አመታት ጉዳይ አስገድዶት ወደ መንግስት መስሪያ ቤት የሚመጣ ዜጋ ሲኦል ደርሶ የሚመለስ እየመሰለው ይሄዳል፡፡ ባለጉዳዮች ኮሪደር ተገናኝተው የሚለዋወጡት ሰላምታ ይህን ይመስላል ‹‹ታዲያስ ሲኦል እንዴት ነው?›› ይለዋል አንዱ ‹‹ምንም አይል ለገሀነም አሪፍ ልምምድ ነው›› የባሰ አታምጣ!

‹‹የባሰ አታምጣ!››...

በጃንሆይ ዘመን ለመንግስት መስሪያ ቤት አንድ ስራ ሰርቼ ካስረከብኩ በኋላ ክፍያዬን ለማግኘት አንድ ቀን ካልቀናኝም ሁለት ቀን ይወስድብኝ ነበር፡፡ ቢሮክራሲው የአዲሳባ ባይሆን ኖሮ ግን አንድም ሰአት ባልፈጀ፡፡ በደርጉ ዘመን ከሁለት እስከ አምስት ቀን ይወስድብኝ ነበር፡፡

በሽግግሩ መንግስት ዘመን ያጋጠመኝን ልንገራችሁ፡፡ ዳሩ በአስተዳደሩ ብቃት ከንግድ ባንክና ከአየር መንገድ ጋር ይጠቀስ ከነበረው አንድ መስሪያ ቤት የህዝብ ግንኙነት ክፍል ስልክ ተደወለልኝና ለአመታዊ መፅሄታችን አንድ መጣጥፍ ፃፍልን እንከፍልሀለን ተባልኩ፡፡ የክፍያውን ልክ የሚወስነው ኮሚቴ ሰብሳቢ ወደ ውጭ አገር ስለሄዱ፤

እስኪመለሱ መጠበቅ ሊያስፈልግ ነው። መች ይመጣሉ? ከአንድ ሀያ ቀን በኋላ። ሰብሳቢ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ተተኪ ሰብሳቢ የለም እንዴ? እሱማ እኔ ራሴ ነበርኩ። እንግዲያው እሳቸው በሌሉበት ስንሰበሰብ ስልጣናቸውን የምሻማቸው እየመሰላቸው ጥምድ አርገው ይይዙኛል አይ የኛ ባለስልጣናት ምን ለማለት እችላለሁ? ምንም። በልቤ ብቻ ለከርሞም ፃፍልኝ እንዲሉኝ ተመኘሁ እምቢ እንድላቸውና ደስ እንዲለኝ። ታዲያ ክፍያው ጥሩ ነበር። ግን የዚህ መስሪያ ቤት ክፍያ በአፍንጫዬ ይውጣ! ይኸውላችሁ ያዲሳባ ቢሮክራሲ እንዴት እንደሚያስመርር።

ሌላ ጊዜ ደሞ ለአንድ መስሪያ ቤት የትርጉም ስራ ሰራሁ፤ ስራውን ያሰሩኝም ክፍያውን በደብዳቤ የሚያዙልኝም ይከፈለው ብለው የሚፈርሙልኝም ገንዘቡን ቆጥረው የሚከፍሉኝም በሙሉ የኢህአዴግ አባላት ወጣቶች ናቸው።

ስራውን ያስረከብኩት ሹም ይከፈለው የምትል ሶስት አራት መስመር ለመፃፍ አምስት ቀን አመላለሰኝ ያውም በስድስተኛው ቀን መንገድ ሲያገኝኝ «ይሄውልህ እኔ ያንተ ወንድም!» በሚል ድምፅና በትልቅ ፈገግታ «ደብዳቤውን ከፃፍኩልህ ተከታተለው» አለኝ ትልቅ ውለታ እንደዋለልኝ ቆጠረው መሰለኝ ከሁኔታው። ከገዛ ኪሱ አውጥቶ የሰጠኝ ያህል ነበር።

ተከታተለው እንዳለኝ ስከታተለው አንድ ሶስት አራት ቀን ተመላለስኩ። በመጨረሻም ትግስቴ አለቀና ለወጣቱ ባለስልጣን እንዲህ አልኩት። «ስማኝ ከሶስት ሺ አመት በፊት ሙሴ እንዲህ ሲል አወጀ ‹ሰራተኛውንም የልፋቱን ዋጋ ወዲያውኑ ክፈለው እንጂ አታመላልሰው።› ኢህአዴግ ግን አሁን እንደምናየው ሶስት ሺ አመት ወደኋላ ቀርቷል። የልፋቴን ዋጋ ከልክላችሁኝ ይኸው ስመላለስ ሰነበትኩ እንዲህ አርጎም የለ ተራማጅ ሀይል! አቤት ስንቱን ጓደኞቻችሁን ሰውታችሁ ስትመጡ ግን እንዴት ነበር ደስ የምትሉን! እንዴት ነበር የኮራንባችሁ!»

ወዲያው አፋጠነልኝና ተከፈለኝ። ግን እኔ ትግስቴ ያለቀበት ሽማግሌ መሆኔ ያስከፈለኝ እንጂ ወጣት ብሆን ኖሮ ይኸኔ ሌላ አስር ቀን

ይፈጅብኝ ነበር፡፡ ስጦታም አይደለም ብድርም አይደለም የሰራሁበትን ክፍያ ለማግኘት ያውም በሀያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ! ያውም በኢትዮጵያ በቅድስት አገር! አጀብ! አጃኢብ!... ‹‹በሽታውን የደበቀ መድሀኒት አይገኝለትም፡፡››

የአዲስ አበባ ቢሮክራሲ ጤነኛ ነው የሚል ሰው ካለ ቢሮክራሲ ባለስልጣን መሆን አለበት - ያውም እንጃ፡፡ በመጀመሪያ በሽተኛው ህመሙ ያመዋል፡፡ የሚታመመው የሚሰቃየው በሽተኛ እኛ ህዝቡ ነን፡፡ የሚያመን የሚያሰቃየን፡፡

በሽታ ቢሮክራሲ ነው፡፡ እኛ ብሶታችንን ተናግረናል ይኸውና (አሁን እኛ የምንለው ብዙ ብዙ ሰዎችን የምወክል መሆኔ ነው) ቀጥሎ እንግዲህ ሀኪሙ በሽታውን ያጠናዋል፡፡

ምርመራ በጥናቱ መሰረት መድሀኒቱን ያዝዛል፡፡

የኛ ቢሮክራሲ በሽታ ከመነሻዎቹ አንዱ ባህላችን የመሀይም ህዝብ ባህል መሆኑ ነው፡፡ በባህላችን ህዝቡ አያነብም አይፅፍም፡፡ ደብተራ ነው የሚያነበው የሚፅፈው፡፡ የሚፃፈው ደሞ ድግምት ክታብ ነው! ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ኧረ በጣም ከባድ ነገር ነው! ቅን ልብ ያለው ደብተራ የእግዚአብሄርን ቃል ይፅፋል ለነብሳችን የዘላለም ህይወት የሚሰጥ፡፡ እኩይ የሆነ ደብተራ የሰይጣን ቃል ይፅፋል ነብሳችንን ለገሀነም እሳት የሚዳርግ፡፡ ስለዚህ የተፃፈው ነገር በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ የእሳት ያህል አደገኛ ነው፡፡

ይህ መሀይም ህዝብ አዲሳባ ገብቶ ምሁራን ቢሮክራሲ ባለስልጣናት ዘንድ ሲደርስ ምን ይሆናል የተፃፈ ቃላትን እንደ ድግምት አክብሮ ማየት ያመጣል፡፡ ከባለጉዳይ ሰው ደብዳቤውን ያበልጣል፡፡ ከቢሮው ወጣ ካልን ከመስሪያ ቤቱ መግቢያ በር ቆም ብለን ብንመለከት ደሞ ከሰውየው መታወቂያው ይበልጣል፡፡ ሴትዮዋ ሊገቡ ሲሉ ‹‹መታወቂያ›› ይላቸዋል ዘበኛው

ቦርሳቸውን ከፍተው ካዩ በኋላ ‹‹እዬ አላመጣሁትም፡፡ ጓደኛዬ እዚህ ነው 'ምትሰራው አንዴ ገብቼ አይቻት ልምጣ፡፡››

‹‹ያለመታወቂያ አይቻልም››

አሁን ሴትዮዋ መታወቂያ ይያዙስ አይያዙስ ምናለበት ገብተው ቢጠይቁ አደጋ እንዳይጥሉ ተፈርቶ ይሆን?

ጉዳዩ ሌላ ነው ልጄ ደርሰንበታል! ጥናቱ አማርኛው የሚፃፍባቸው ፊደላት የግእዙ ፊደላት መሆናቸው ነው፡፡ ያ ድግምትስ ክታብስ የሚፃፍበት ፊደላት እኮ ነው፡፡ የደብተራው ፊደላት የምሁሩን ነብሱ ወይም አእምሮውን ወይም ሳይኮሎጂውን የደብተራው ያረገዋል፡፡ ዋ! እንዲህ ከሆነማ ምነው አማርኛይቱ ከእንግሊዘኛ ፊደላት በተፃፈች! ቢሮክራሲ ባለስልጣኖቻችን እንደ እንግሊዝ ቢሮክራሲ ቅን አገልግሎት ይሰጡን ነበር፡፡

**ግንቦት 20 ቀን 1987**

# ስብሀት ገብረእግዚአብሄር

የእውቀት ባህር ውስጥ ገብቶ መዋኘቱን በሩቁ የሚሉና የሚያፍሩትና የሚፈሩት አሉ፤ ሰምጠው የሚቀሩ እየመሰላቸው። እንዲህ የሚያስቡ ምንኛ ተሳስተዋል። ስብሀት ተቀድቶ የማያልቅ የዕውቀት ባህር ነው። እውቀትን እንደልባቸው ጠጥተው ለመርካት ዘለው የሚገቡበት ደፋሮች ሳይሆኑ ብዑካን ናቸው። "እግረ መንገድ" ረጅም ርቀት ልታጓጉዘን ደርሳለችና እንጓዝ!

<<እግረ መንገድ>> ውስጥ ያልዳሰሰው ምን ነገር አለ? ታሪኩ፣ ተረቱ፣ ፍልስፍናው፣ ስነልቦናው፣ ኪነጥበቡ ወዘተ ሁሉም ተገብኝተዋል። ይሄ ሀቅ አለተሰንበት አዲስ ዘመንን ያነበቡ ሁሉ የሚያውቁት ነው።

በዚህ አምድ ላይ ሳይቋረጡ በተከታታይ ለአምስት አመታት የወጡት መጣጥፎች ደራሲው ስብሀት ገብረእግዚአብሄር በንባብ፣ በልምድና በማያሰልስ ጥረቱ ያካበታቸው የእውቀት ዘርፎች ምን ያህል ስፋት እና ጥልቀት እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው።

በዚህ ቅፅ የቀረቡላችሁ መጣ ጥፎች ከትምህርትና ከንባብ የተቀሰሙ እውቀቶች ብቻ አይደሉም። ስብሀት በህይወቱ ያጋጠሙትን ነገሮች በራሱ አይን እያየ እናንተም እንድታዩዋቸው ማድረጉ መጣጥፎቹ አብነት ሊሆኑ ይችላሉ።

ደምሴ ፅጌ

*

ልጅ ሆኜ ነብሴን እጅግ ደስ የሚላት ጢቢ፣ ጢቢ ስጫወት ነበር። ጎረምሳ ሆኜ ነብሴን እጅግ ደስ የሚላት ሴት ልጅን ሳቅፍ ነበር። ዛሬ አርጅቼ ነብሴን እጅግ ደስ የሚላት ልጄ ስትስቅ ሳይ ነው። አሁን እነዚህን ሶስት እኔዎች ሳስተያያቸው አንድ ሰው ናቸው? - - - - - እኔ ሽማግሌውስ አንድም፣ አራትም ብሆን ይኸው እዚህ አለሁ። ያ እኔ የምለው ልጅና ያ እኔ የምለው ጎረምሳ ግን የት ሄዱ? የኔ ትውስታ ውስጥ ከልጅየውም ከጎረምሳውም ከብዙ በጥቂቱ እንደ ፊልም ተቀርፆ ይገኛል እንጂ እነሱ ግን የሉም።

*

ምጣዱ ክብ በመሆኑ ሳይሆን አልቀረም እንጀራው ክብ ነው በክብ መሶብም ተዘርግቷል እኛም ከበነዋል። - - - - - በልቶ የጠገበ በአፉ ወይም በሆዱ "ተመስገን!" ይልና መብላት ያበቃል። ብዙ ጊዜ ግን እኛ ሳንጠግብ ያልቃል። "ተመስገን!" ብለን ብዙ ውሀ እንጠጣለን። "የሚያጠግበው እህል ነው፤ መጥገቡን የሚለካው ግን ውሀ ነው።" ኧረ ጠላስ ቢሆን? እንዲያውስ ጠጅስ ቢሆን? መች እንቻላለን? ይብላኝ ለምድረቱ ችላ ለምትሽከመው መጦኔ ለአፈሩ፣ አብልቶ ለሚበላን!

**ዋጋ 200 ብር**
**ሁለት መቶ ብር ብቻ**

አሳብ አሳታሚ
Assab Publishers
+251-936 959 644 / +251-978 106 538

የሽፋን ገጽ ስዕልና ዲዛይን 0913450005